# አሪት ዘፍጥረት

## መግቢያ

### አሰያየሙ

በዕብራይስጡ መጽሐፍ ም 1፥1 ላይ ያለው የመጀመሪያው ሐርግ፣ "በረሺት" የሚል ሲሆን ትርጕሙም "በመጀመሪያ" ማለት ነው:: የዕብራይስጡ መጽሐፍ ስም ይኸው ቃል ነው::: (ጥንታውያን ጽሑፎች ስያሜያቸውን የሚያገኙት በጽሑፉ መጀመሪያ ላይ በሚገኙት ቃላት ነበር):: "ጀነሲስ" የሚለው የእንግሊዘኛ ስያሜ የተቀዳው የሰባ ሊቃናት የግሪክ ትርጕም በዘፍ 2፥4 እና 5፥1 ላይ 'ጄነሲ ዋስ' ካለው ቃል ነው:: "አሪት ዘፍጥረት" የሚለው፣ "የአማርኛ" ስም ከዕብራይስጡና ከግሪኩ ጋር ተመሳሳይ ትርጕም አለው:: "አሪት" ማለት ሕግ፣ ፍትህ፤ ትእዛዝ ማለት ሲሆን፣ "ፍጥረት" ማለት ደግሞ፤ እንደ አገባቡ መፍጠር፣ መፈጠር፣ አፈጣጠር፣ ፈጠራ፣ ፍጡርነት፣ ጥንት፣ ዘር፣ ሥር፣ ምንጭ፣ ልደት፤ ትውልድ ማለት ነው:: "ፍጥረት" ከሚለው ቃል ፊት የሚገኘው "ዘ" የግእዝ ዘርፍ አያያዥ መስተዋድድ ሲሆን የአማርኛ አቻው "የ" ነው:: ስለዚህ፣ "አሪት ዘፍጥረት" ማለት የፍጥረት ሕግ፣ የአፈጣጠር ደንብ፣ የፍጥረት ሥር፣ ምንጭ፣ ልደት፤ የፍጥረት ትውልድ ማለት ነው:: ቃሉ ከዐውደ ምንባቡ አኳያ የነገሮችን ሁሉ አጀማመር የሚተርክ መጽሐፍ መሆኑን ያመለክታል::

### ዳራው

ከሌሎች ምንጮች እንደምንረዳው ከም 1-38 ያለው ክፍል የጥንታዊቷን መስጴጦምያ ሕይወትና ባህል በእጅጉ የሚያንጸባርቅ ነው:: ፍጥረት፣ የትውልድ ሐረግ፣ የጥፋት ውሃ፣ የመልክዐ ምድር ትምህርትና የካርታ ሥራ፣ የሕንጻ ሙያ፣ የሕዝቦች ስደት፣ መሬትን መግዛትና መሸጥ፣ ባህላዊ ልማዶችና አካሄዶች፣ በግ ጥበቃና እንስሳትን ማርባት ወዘተ. ለጥንት መስጴጦምያ ነዋሪዎች ዋና ጕዳዮች ነበሩ:: ጸሓፊው የሰዎች የመጀመሪያ መኖሪያ የሆነችው ዔድን ገነት እንደ ሆነችና የምትገኘውም በመስጴጦምያ ወይም በአካባቢዋ እንደ ሆነ አሳይቶአል:: የባቤል ግንብ የታነጸው በዚህ ስፍራ ነው፤ አብርሃም የተወለደው በዚሁ ስፍራ ነው፤ ይስሐቅ ሚስቱን ያገኘው ከዚሁ ስፍራ ነው፤ ያዕቆብ ለሃያ ዓመት የኖረው በዚሁ ስፍራ ነው:: ምንም እንኳ ቀደምት አበው በፍልስጥኤም ምድር ይኑሩ እንጂ የበቀሉባት እናት ምድር መስጴጦምያ ነበረች:: ከዘፍ 1-38 ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ጥንታውያን መዛግብት ከመስጴጦምያ የተገኙ ናቸው:: ከእነዚህም አንዳንዶቹ ስለ ፍጥረተ ዓለም አጀማመር (ዘፍ 1)፣ ስለ ዘር ሐረግ (ዘፍ 5)፣ በዘፍ 6-8 ስለተተረከው የጥፋት ውሃ፣ ከም 1-8 ላይ ስለተጻፉት ዋና ዋና ክሥተቶች በተመሳሳይ የጊዜ ቅደም ተከተል ሲተርኩ ይገኛሉ:: እንዲሁም ቀደምት አበው (አብርሃም፣ ያዕቆብና ኢዮብን ጨምሮ) ስማቸው በእነዚህ መዛግብት ተጠቅሶ ይገኛል:: በተጨማሪም የአባቱን ርስት የሚወርስ ልጅ ከሌለ የማደጎ ልጅ ንብረቱን መውረስ እንደሚችል (15፥1-4)፣ በአሞራውያን አገር ከቦታ ቦታ እንደ ልብ መዘዋወር እንደሚቻል፣ መካን ሴት ልጅ ለማግኘት ስትል አገልጋይዋን ለባሏ እንደምትሰጥ (16፥2-4 ይመ)፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ አገልጋዪቱን ከነልጇ ከቤት ማባረር እንደሚቻል (21፥10-11)፣ እንደ ሙት ኑዛዜ ያሉ በቃል ብቻ የተካሄዱ ስምምነቶች በቅርብ ምሥራቅ አገሮች ከፍተኛ ስፍራ እንዲሁም ከበሬታ እንደነበራቸው እነዚሁ ጽሑፎች በስፋት ያትታሉ::

ከም 39-50 ያለው ታሪክ ደግሞ በቀጥታ ባይሆንም፣ የግብፅን ፍልስፍና የሚያንጸባርቅ ነው:: ለምሳሌ የግብፃውያን የወይን ተክል (40፥9-11)፣ በወንዝ ዳርቻ ስላለው ገጽታ (ም 41)፣ ግብፅ ለከነዓን የዳቦ ቅርጫት መሆኗ (ም 42)፣ ብዙ ልዩ ልዩ ምርቶች ከከነዓን ወደ ግብፅ እንደ ገቡ (ም 43)፣ የግብፃውያን አምልኮና ባሕል (43፥46)፣ የግብፃውያን አስተዳደር (ም 47)፣ ሥርዐተ ቀብራቸው (ም 50) እንዲሁም አያሌ የግብፃውያን ቃላትና ስሞች በምዕራፎቹ ውስጥ ተጠቅሰው ይገኛሉ::

### ጸሓፊውና የተጻፈበት ጊዜ

አይሁድና ክርስቲያኖች የመጀመሪያዎቹን የብሉይ ኪዳን አምስት መጻሕፍት የጻፈውና ያሰባሰበው ሙሴ ነው የሚል እምነት እንዳላቸው ከታሪክ እንግራለን:: እነዚህ መጻሕፍት፣ "ፔንታቱክ" ("ባለ አምስት ቅጽ መጽሐፍ" ማለት ነው) ተብለው ይጠራሉ:: በአይሁዳውያን ዘንድ ደግሞ፣ አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ይባላሉ:: በሐሥ 15፥1 የግዝረት ሥርዐት በሙሴ የተሰጠ ትምህርት እንደ ሆነ ይገልጻል፤ ይህም ከዘፍ 17 ጋር ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ስለሚገናኝ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ሙሴ የአሪት ዘፍጥረት ጸሓፊ እንደ ሆነ ይጠቁማል:: ቢሆንም በተለይ የጊዜ ገለጻን አስመልክቶ አንዳንድ የማስተካከያ ሥራዎች እንደ ተደረጉ ይገመታል (የ14፥14፤ 36፥31፤ 47፥11 ማብ ይመ):: ሙሴ የኖረበት ትክክለኛ ዘመን ብዙ በማያሻማ ርግጠኛነት በ1ኛ ነገሥት ውስጥ ተገልጾአል፤ የሰሎሞን ንግሥና አራተኛ ዓመት እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡበት 480ኛ ዓመት መሆኑ ተጠቅሶአል (1ነገ 6፥1):: ይህም ከ1446 እስከ 966 ዓ.ቅ.ክ መሆኑ ነው (የመጽሐፈ መሳፍንት መግቢያ ይመ) ከ1446 እስከ 1406 ዓ.ቅ.ክ. ድረስ እስ ራኤል በምድረ በዳ ባሳለፉት ዓመታት ሙሴ "ፔንታቱክ" ተብለው የሚታወቁትን አምስቱን የአሪት መጻሕፍት እንደ ጻፈ ይገመታል::

### ዐላማውና መልእክቱ

ኦሪት ዘፍጥረት ስለ ጅማሬዎች ይናገራል፤ የሰማያትንና የምድርን፣ የብርሃንንና የጨለማን፣ የውሃ አካላትንና የጠፈርን፣ የምድርንና የዕፀዋትን የፀሓይን የጨረቃንና የከዋክብትን፣ በባሕር በአየርና በምድር የሚንቀሳቀሱ እንስሳትን፣ እንዲሁም የፍጥረት ሁሉ ቍንጮ የሆነውን በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን የሰውን፣ የኀጢአትን የኀጢአት ስርየትን፣ የበረከትና የመርገምን፣ የማኅበረ ሰብና የሥልጣኔን፣ የጋብቻንና የቤተ ሰብን ወዘተርፈ ጅማሬ የሚናገር መጽሐፍ ነው::

ለዘፍጥረት መጽሐፍ ቍልፍ የሆነው፣ "ቴሌደት" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን፣ በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ትውልድ፣ ታሪክ፣ ክንውን፣ የትውልድ ሐረግ ወዘተ. እየተባለ ተተርጒሞአል፤ ይህ ቃል መጽሐፉን በዐሥር ዋና ዋና ክፍሎች ያካፍላል::

የዘፍጥረት መጽሐፍ ለተቀሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መሠረት ጣይ ነው:: መልእክቱም ሰፊና ጥልቅ ሲሆን፣ ዋና ዋና ጒዳዮቹን በዝርዝር ማቅረቡ አጠቃላዩን የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲታይ አድርጎታል:: ይህ መጽሐፍ የግንኙነት መጽሐፍ ነው፤ በእግዚአብሔርና በተፈጥሮ፣ በእግዚአብሔርና በሰው እንዲሁም በሰዎች መካከል ያለውን ዝምድና አጒልቶ ያሳያል:: መጽሐፉ አንድ አምላክ ብቻ እንዳለ በማስረገጥ አንዳምላካዊነትን እያጸና፣ ኢአማኒነትንና ሁሉአምላክነትን አጥብቆ ይቃወማል:: በተጨማሪም እውነተኛ የሆነው አንድ አምላክ በፍጥረቱ ላይ ልዑል እንደ ሆነ፣ በመለኮታዊ ምርጫውም ወሰን የሌለውን ነጻነቱን በመጠቀም የሰዎችን ባሕል፣ ሥርዐትና ዕቅድ እንደ ወደደው ብቻ እንደሚመራ ግልጽ በሆነ መንገድ ያስተምራል:: እግዚአብሔር ከመረጠው ከሕዝቡ ጋር በራሱ አነሣሽነት ቃል ኪዳን እንደሚገባ፣ ፍቅሩንና ታማኝነቱን እንደሚገልጽላቸው፣ እነርሱም ከእርሱ ጋር ቃል እንዲገቡ የሚያደርግበትን መንገድ ያሳያል:: መሥዋዕት ለሕይወት በተለዋጭነት የሚቀርብበትን ሥርዐት ይገነባል (ም 22):: ከክፉ ኀይላት የሚታደገውን የእግዚአብሔርን ችሮታ፣ የመጀመሪያውን ፍንጭ በጥቂቱ ያሳያል (3፥15፤ ከሮሜ 16፥17-20 ጋር ያነጻጽሩ):: እንዲሁም ለእምነት ጥንታዊና እጅግ ጥልቅ የሆነ ፍቺ ይሰጣል (15፥6):: በዕብ 11 ላይ ከተዘረዘሩት የእምነት አባቶች መካከል ከግማሽ በላይ የሆኑት በዘፍጥረት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ (የተጠቀሱ) ናቸው::

### ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርይው

የአንድ መጽሐፍ መልእክት በሥነ ጽሑፋዊ ውቅሩና መልኩቹ ይወሰናል:: ኦሪት ዘፍጥረት በዐሥር ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን፣ የእያንዳንዱ ክፍል መግቢያ፣ "ቴሌዶት" (ትውልድ) በሚለው ቃል ይጀምራል ይህ ቃል በአማርኛው፣ የዘር ሐረግ፤ ትውልድ፤ ታሪክ ወዘተርፈ እየተባለ ተተርጒሞአል (2፥4፤ 5፥1፤ 6፥9፤ 10፥1፤ 11፥27፤ 25፥12፤ 25፥19፤3 6፥1 እንዲሁም 36፥9 እና 37፥2 ይመ):: የመጽሐፉን መግቢያ ጨምሮ (1፥1-2፥3)፣ የመጀመሪያዎቹ አምስት ክፍሎች በአንድ ላይ የሚመደቡ ሲሆን፣ ከአዳም እስከ አብርሃም ያለውንም ዘመን የሚዘግቡ በመሆናቸው፣ "ጥንታዊ ታሪክ" ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ (1፥1-11፥26):: የመጨረሻዎቹ አምስት ክፍሎች ረጅሙን (ሆኖም አንድ ወጥ የሆነ) የትውልድ ዘገባ የያዙ ናቸው:: እነርሱም እግዚአብሔር ከአብርሃም፣ ከይስሐቅ፣ ከያዕቆብና ከዮሴፍ እንዲሁም ከየቤተ ሰቦቻቸው ጋር ከነበረው ግንኙነት ጋር ተያይዘዋል:: ስለዚህ ነው አብዛኛውን ጊዜ ይህ ክፍል፣ "የአበው ታሪክ" ተብሎ የሚጠራው (11፥27-50፥26):: ክፍሉ ራሱ እንደ ገና በሦስት የትረካ ዑደቶች ሊከፈል ይችላል፤ አብርሃም-ይስሐቅ (11፥27-25፥11)፣ ይስሐቅ-ያዕቆብ (25፥19-35፥29፤ 37፥1)፣ ያዕቆብ-ዮሴፍ (37፥2-50፥26):: እነዚህ ትራኪዎች በየመካከሉ የእስማኤልን (25፥12-18) እና የዔሳውን (ም 36) የትውልድ ሐረጎች ጣልቃ በማስገባት የተዋቀሩ ናቸው::

ትረካው በተደጋጋሚ ከበኩር ልጅ ይልቅ በሁለተኛ ልጅ ላይ ያተኩረ ነው:: ለምሳሌ:- በቃየን ፋንታ ሴት፣ በያፌት ፈንታ ሴም (የ10፥21 ማብ ይመ)፣ በእስማኤል ፈንታ ይስሐቅ፣ በዔሳው ፈንታ ያዕቆብ፣ ይሁዳና ዮሴፍ በሌሎቹ ወንድሞቻቸው ይልቅ እንዲሁም በምናሴ ፈንታ ኤፍሬም ትኵረት ተሰጥቶአቸዋል:: የዘፍጥረት መጽሐፍ በተመረጡት ሰዎችና ቤተ ሰቦቻቸው ላይ ትኵረት ማድረጉ፣ ምናልባት፣ መለኮታዊ ምርጫ የሚለው ርእስ ጒዳይ፣ በዘፍጥረት መጽሐፍ ለሚታየው ሥነ ጽሑፋዊና ነገረ መለኮታዊ ቅርጽ መሠረት እንደ ሆነ ሳይጠቁም አይቀርም:: ይህም የእግዚአብሔር ሰዎች የሰብአውያን እድገት ሂደት ያስገኛቸው ሳይሆኑ፣ ልዑል እግዚአብሔር በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ በጸጋ አሠራሩና በሉዓላዊነቱ የመግባቱ ውጤት እንደ ሆኑ ፍንትው አድርጎ ያሳያል:: ከወደቀው የሰው ዘር መካከል ለራሱ የሚሆን አዲስ ሕዝብ ለመንግሥትነት ቀድሶ አውጥቶ፣ ምድርን ሁሉ የሚባርክበት መሣሪያ አድርጎታል::

በዘፍጥረት መጽሐፍ ቍጥሮች የተለየ ትርጒም አላቸው:: ዐሥር ቍጥር መጽሐፉ የተከፋፈለበትን ክፍሎች ጨምሮ በም 5 እና 11 ላይ የተዘረዘሩትን የትውልድ ሐረግ ስሞች ያመለክታል (የ5፥5 ማብ ይመ):: ሰባት ቍጥርም ተደጋግሞ ተጠቅሶአል:: በዕብራይስጡ መጽሐፍ 1፥1 ላይ የሚገኙት ሰባት ቃላት ናቸው፤ 1፥2 ላይ ደግሞ የሚገኙት ሁለት ጊዜ ሰባት ቃላት ናቸው:: ፍጥረት በሰባት ቀናት ውስጥ ተጠናቀቀ፤ በም 4 በተጠቀሰው የትውልድ ሐረግ ሰባት ስሞች አሉ (የ4፥17-18 ማብ፤ 4፥15:24፤ 5፥31 ይመ)፤ በጥፋት ውሃ የተለያዩ ሰባት ክሥተቶች አሉ፤ የኖኅ የልጅ ልጆች 70 ነበሩ (ም 10)፤ ለአብራም የተገባለት ቃል ኪዳን ባለ ሰባት ነጥብ ነበር (12፥2-3):: በግብፅ የነበረው ሰባት የጥጋብና ሰባት የራብ ዓመታት (ም 11) ነበር:: የያዕቆብ ቤተ ሰብ አባላት 70 ነበሩ (ም 46):: ሌሎች በተደጋጋሚ የተጠቀሱ

ቍጥሮች 12 እና 40 ናቸው::

የዘፍጥረት መጽሐፍ በመሠረቱ በስድ ንባብ የተጻፈ ትረካ ሲሆን፣ የመጽሐፉ መጨረሻ ግን የተጻፈው በግጥም ነው (በ49፥2-27 ላይ የተጻፈው የያዕቆብ ባርኮት):: የንባቡ አብዛኛው ክፍል ቅኔያዊ ይዘት ሲኖረው ዘይቤያዊ አነጋገርና ሌሎች መንገዶችን (ስልቶችን) ይጠቀማል:: የአተራረክ ዘይቤው ከጥንታውያን ጽሑፎች መካከል እጅግ ተደናቂነት እንዲያገኝ አድርጎታል:: በፍጥረት ታሪክ በሁለት ጥንድ በቀረቡት የሦስት ቀናት ትረካ ውስጥ የሚታየው የቀጥታና የአግድሞሽ ትይዩነት (የ1፥11 ማብ ይመ)፣ በም 3 የቀረበው የኀጢአት ድርድርና፣ ቅደም ተከተሉን ገልብጦ የቀረበው የእግዚአብሔር ጥያቄና ተመልሶ የፊተኛውን ቅደም ተከተል የጠበቀው ፍርድ፣ በም 5 በየአንቀጹ መጨረሻ ላይ፣ "ከኖረ በኋላ ሞተ" የሚለው ቃል መደጋገሙ፣ በጥፋት ውሃ መካከል 'እግዚአብሔር ግን ኖኅን አሰበ' የሚለው ወሳኝ ሐረግ (8፥1)፣ በ11፥1-9 ላይ የተዘገበው የባቤል ግንብ ሁኔታ፣ በ40፥19 ስለ ግለሰቦች የወደፊት ዕድል በምሳሌ የተገለጠው፣ ስለ በኵር ልጆች ያለው አጭር ዘገባና ስለ ታናሽ ልጅ ያለው ረጅም ትረካ፣ እነዚህንና ሌሎችም የአጻጻፍ ስልቶች ለትረካው ጣዕም እንዲሁም አቀራረቡን ለማስዋብና የአንባቢያንን ልብ ለማንጠልጠል ዐይነተኛ ምክንያቶች ሆነዋል:: የአራት ዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች ርእሰ ጕዳዮችና ፍሬ ሐሳቦች፣ በራእይ መጽሐፍ የመጨረሻዎቹ ሦስት ምዕራፎች ውስጥ መንጸባረቃቸው የአጋጣሚ ጕዳይ አይደለም:: እንዲያውም፣ "ቅዱሳት መጻሕፍት በእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ተጻፉ" የሚያረጋግጥና የጻፉአቸውም ሰዎች፣ "በመንፈስ ቅድስ ተነድተው እንደ ጻፉ" የሚያረጋግጥ ሆኖ እናገኘዋለን (2ጢሞ 3፥16፤ 2ጴጥ 1፥21)::

**አስተዋፅኦ**

***ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጹን የተከተለ አስተዋፅኦ***

1. *መግቢያ* (1፥1-2፥3)
2. *ሐተታ* (2፥4-50፥26)
   - ሀ. የሰማያትና የምድር አፈጣጠር (2፥4-4፥26)
   - ለ. የአዳም ልጆች የትውልድ ሐረግ (5፥1-6፥8)
   - ሐ. የኖኅ ትውልድ (6፥9-9፥29)
   - መ. የሴም፣ የካምና የያፌት ትውልድ (10፥1-11፥9)
   - ሠ. የሴም ትውልድ (11፥10-26)
   - ረ. የታራ ትውልድ (11፥27-25፥11)
   - ሰ. የአብርሃም ልጅ የእስማኤል ትውልድ (25፥12-18)
   - ሸ. የአብርሃም ልጅ የይስሐቅ ትውልድ (25፥19-35፥29)
   - ቀ. የዔሳው ትውልድ (36፥1-37፥1)
   - በ. የያዕቆብ ትውልድ (37፥2-50፥26)

**ርእሰ ጕዳዩን የተከተለ አስተዋፅኦ**

1. *ጥንታዊ ታሪክ* (1፥1-11፥26)
   - ሀ. ፍጥረት (1፥1-2፥3)
     1. *መግቢያ* (1፥1-2)
     2. *ሐተታ* (1፥3-31)
     3. *ማጠቃለያ* (2፥1-3)
   - ለ. አዳምና ሔዋን በዔድን ገነት (2፥4-25)
   - ሐ. በኀጢአት መውደቅና ውጤቱ (ም 3)
   - መ. የኀጢአት መስፋፋት (4፥1-16)
   - ሠ. ሁለት ትውልዶች (4፥17-5፥32)
     1. የትዕቢት ትውልድ (4፥17-24)
     2. የሞት ትውልድ (4፥25-5፥32)
   - ረ. ከጥፋት ውሃ በፊት የኀጢአት መብዛት (6፥1-8)
   - ሰ. ታላቁ የውሃ ጥፋት (6፥9-9፥29)
     1. ከውሃ ጥፋት ለመዳን ዝግጅት (6፥9-7፥10)
     2. ፍርድና ትድግና (7፥11-8፥19)
        - ሀ. የውሃው ከፍ ማለት (7፥11-24)
        - ለ. የውሃው ሙላት መጕደል (8፥1-19)
     3. ድኅረ ጥፋት ውሃ (8፥20-9፥29)
        - ሀ. አዲስ ተስፋ (8፥20-22)
        - ለ. አዲስ ቃል ኪዳን (9፥1-7)
        - ሐ. አዲስ ኅብረት (9፥8-17)

መ. አዲስ ፈተና (9፥18-23)
ሠ. የኖኅ የመጨረሻ ቃል (9፥24-29)
ረ. የሕዝቦች መስፋፋት (10፥1-11፥26)
1. የሕዝብ መበታተን (ም 10)
2. የቋንቋ መደበላለቅ (11፥1-9)
3. የሴም የመጀመሪያ የትውልድ ሐረግ (11፥10-26)
2. ርእሳን አበው (11፥27-50፥26)
ሀ. የአብርሃም ሕይወት (11፥27-25፥11)
1. የአብርሃም ታሪካዊ ዳራ (11፥27-32)
2. የአብርሃም አገር (ም 12-14)
3. የአብርሃም ወገኖች (ም 15-24)
4. የአብርሃም መጨረሻዎቹ ቀናት (25፥1-11)
ለ. የእስማኤል ልጆች (25፥12-18)
ሐ. የያዕቆብ ሕይወት (25፥19-35፥29)
1. ያዕቆብ በአባቱ ቤት (25፥19-27፥46)
2. ያዕቆብ በባዕድ ምድር (ም 28-30)
3. ያዕቆብ ዳግም ከቤተ ሰቡ ጋር (ም 31-35)
መ. የዔሳው ልጆች (36፥1-37፥1)
ሠ. የዮሴፍ ሕይወት (37፥2-50፥26)
1. የዮሴፍ ተግባር (37፥2-41፥57)
2. የያዕቆብ ወደ ግብፅ መሰደድ (ም 42-47)
3. የያዕቆብ የመጨረሻ ዘመን (48፥1-50፥14)
4. የዮሴፍ የመጨረሻዎቹ ቀናት (50፥15-26)

## የፍጥረት አጀማመር

1 በመጀመሪያ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰማያት
ንና ምድርን ፈጠረ። 2ምድርም ቅርጽ የለ
ሽና ባዶ ነበረች።[ሀ] የምድርን ጥልቅ ስፍራ
ሁሉ ጨለማ ውጦት ነበር። የእግዚአብሔርም
(ኤሎሂም) መንፈስ በውሆች ላይ ይረብብ ነበር።
3ከዚያም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) “ብርሃን ይሁን” አለ፤
ብርሃንም ሆነ። 4እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ብር
ሃኑ መልካም እንደ ሆነ አየ፤ ብርሃኑን
ከጨለማ ለየ። 5እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ብርሃ
ኑን “ቀን”፣ ጨለማውን “ሌሊት” ብሎ ጠራው።
መሸ፤ ነጋም፤ የመጀመሪያ ቀን።
6እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ “ውሃን ከውሃ የሚለይ
ጠፈር በውሆች መካከል ይሁን” አለ።
7ስለዚህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ጠፈርን አድ
ርጎ ከጠፈሩ በላይና ከጠፈሩ በታች ያለ
ውን ውሃ ለየ፤ እንዳለውም ሆነ። 8እግዚአብ
ሔር (ኤሎሂም) ጠፈርን፣ “ሰማይ” ብሎ ጠራው።
መሸ፤ ነጋም፤ ሁለተኛ ቀን።
9ከዚያም እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ “ከሰማይ
በታች ያለው ውሃ በአንድ ስፍራ ይከ
ማች፤ ደረቅ ምድር ይገለጥ” አለ፤ እንዳ
ለውም ሆነ። 10እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ደረቁን
ምድር፣ “የብስ”፣ ብአንድነት የተሰበሰበ
ውን ውሃ፣ “ባሕር” ብሎ ጠራው። እግዚአ
ብሔር (ኤሎሂም) ይህ መልካም እንደ ሆነ አየ።
11እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ “ምድር ዕፀዋትንም፣
እንደየወገናቸው ዘር የሚሰጡ ተክሎች
ንና በምድር ላይ ዘር ያዘሉ ፍሬ የሚያ
ፈሩ ዛፎችን እንደየወገናቸው ታብቅል”
አለ፤ እንዳለውም ሆነ። 12ምድር ዕፀዋትን፣
እንደየወገናቸው ዘር የሚሰጡ ተክሎችንና
በውስጣቸው ዘር ያለባቸው ፍሬ የሚያ
ፈሩትን ዛፎች በየወገኑ አበቀለች። እግዚ
አብሔርም (ኤሎሂም) ይህ መልካም እንደ ሆነ አየ።

1፥1 ቍ6:21:27፤ ዘፍ2፥3፤14፥19፤2ነገ 19፥15፤ነህ9፥6፤ኢዮ 9፥8፤37፥16:18፤ 38፥4፤መዝ90፥2፤ 96፥5፤102፥25፤ 104፥2:5፤115፥15፤ 121፥2፤136፥5:6፤ 146፥6፤ ምሳ8፥23፤ ኢሳ37፥16፤40፥21: 22:28፤41፥4:26፤ 42፥5፤44፥24፤45፥12: 18፤51፥13:15፤ኤር 10፥12፤27፥5፤32፥17፤ ዮሐ1፥1-2፤ሐሥ14፥15፤ 17፥24፤ኤፌ3፥9፤ቈላ 1፥16፤ዕብ3፥4፤11፥3፤ ራእ4፥11፤10፥6 1፥2 ዘፍ2፥7፤8፥2፤ ዘዳ32፥11፤ኢዮ7፥12፤ 26፥8፤33፥4፤38፥9፤ መዝ36፥6፤42፥7፤ 104፥6:30፤107፥24፤ ምሳ30፥4፤ኢሳ23፥1፤ 24፥10፤27፥10፤31፥5፤ 32፥14:15፤34፥11፤ 45፥18፤ኤር4፥23፤ 1፥3 ቍ6፤መዝ 33፥6:9፤148፥5፤ 2ቆሮ4፥6፤ዕብ11፥3፤ 1ዮሐ1፥5-7 1፥4 ቍ10:12:14: 18:21:25:31፤ ዘፀ10፥21-23፤ኢዮ6፥10፤38፥19፤መዝ18፥28፤104፥20:31፤105፥28፤ 119፥68፤ኢሳ42፥16፤45፥7፤ኤር31፥35 1፥5 ቍ8:10:13:19:23: 31፤ዘፍ2፥19:23፤መዝ74፥16 1፥6 ቍ1:3:9፤መዝ24፥2፤136፥6፤ ኢሳ44፥24፤2ጴጥ3፥5 1፥7 ቍ9:11:15:24፤ዘፍ7፥11፤ኢዮ26፥10፤ 38፥8-11:16፤መዝ68፥33፤148፥4፤ምሳ8፥28፤ 1፥8 ቍ5፤ኢዮ9፥8፤ 37፥18፤መዝ19፥1፤104፥2፤ኢሳ40፥22፤44፥24፤45፥12፤ኤር10፥12፤ ዘካ12፥1 1፥9 ቍ7፤ኢዮ38፥8-11፤መዝ33፥7፤95፥5፤104፥6-9፤ምሳ 8፥29፤ኤር5፥22፤ዮና1፥9፤ሐጌ2፥6፤2ጴጥ3፥5 1፥10 ቍ4:5፤ኢዮ 38፥8፤95፥5፤መዝ33፥7፤90፥2፤95፥4 1፥11 ቍ7:12:21:24:25፤ ዘፍ2፥5፤6፥20፤7፥14፤ዘሌ11፥14:19:22፤ዘዳ14፥13:18፤መዝ65፥9- 13፤104፥14፤1ቆሮ15፥38 1፥12 ቍ4:11

[ሀ]2 ወይም ሆነች

1፥1 በስድስት ቀን ስለተከናወነው የመፍጠር ተግባር መቅድም ሆኖ የሚያገለግል መግለጫ ነው። የዚህ ቍጥር ክቡር እውነት በታላቅ ደስታ በባለቅኔው (መዝ 103፥25) እና በነቢዩ (ኢሳ 40፥21) ተረጋግጦአል። *በመጀመሪያ እግዚአብሔር፤* መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ሕላዌ ተቀብሎ ገለጻውን ይቀጥላል እንጂ ስለ እግዚአብሔር መኖር ክርክር አያቀርብም። ማንኛውም ነገር መጀመሪያ ያለው ሲሆን እግዚአብሔር ግን ዘላለማዊ ነው (መዝ 90፥2)። *በመጀመሪያ፤* በመፍጠር ተግባር ላይ የክርስቶስን ሥራ በአጽንዖት የሚናገረው ዮሐንስ (1፥1-10) ምዕራፉን የሚጀምረው በዚሁ ቃል ነው። *እግዚአብሔር... ፈጠረ፤* ኤሎሂም የሚለው የዕብራይስጥ ስም ብዙ ቍጥር ሲሆን ግሡ ግን ነጠላ ነው። ይህም እውነተኛውንና ብቸኛውን አምላክ የሚያመለክት የተለመደ አገላለጽ ነው። *ሰማያትንና ምድርን፤* “ሁሉንም ነገር” (ኢሳ 44፥24) ማለት ነው። እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪና መገኛ እንደ ሆነ በብዙ ሥፍራ ተጠቅሶአል (ኤር 10፥16፤ ዮሐ 1፥3፤ ቈላ 1፥16፤ ዕብ 1፥2)። በዚህ ክፍል ስለ ሥነ ፍጥረት የተሰጠው ትምህርት እጅግ ውብ በሆነ መንገድ በኢሳ 45፥18 ላይ ባጭሩ ቀርቦአል።

1፥2 *ምድር፤* ትረካው ያነጣጠረው ምድር ላይ ነው። *ቅርጽ የለሽና ባዶ፤* ይህ ሐረግ በሌላ ስፍራ በኤር 4፥23 ላይ ብቻ የሚገኝ ሲሆን፣ ለምዕራፉ ቀሪ ክፍል ቅርጽ የሚሰጥ ነው (የቍ 11 ማብ ይመ)። እግዚአብሔር በመጀሪያዎቹ ሦስት ቀናት ባደረገው፣ “የመለየትና”፣ “የማከማቸት” ሥራው፣ ለምድር ቅርጽን የሰጣት ሲሆን በተቀሩት ሦስት ቀናት የፈጸመው፣ “የመፍጠርና”፣ “የመሙላት” ሥራው ደግሞ ባዶነቷን አስወግዶአል። *ጨለማ... በውሆች፤* የብርሃን ምንጭ፣ የሥርዐት መሠረትና የሕይወት ፈጣሪ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በመጠባበቅ ላይ ያለችውን ዓለም የሚገልጽ ነው። *የእግዚአብሔርም፤* “እግዚአብሔር” በሚለው ቃል ላይ የወደቀችው አያያዥ ፊደል “ም”፣ “ነገር ግን” ተብላ ልትተረጐም ትችላለች። የመጀመሪያው የገሃዷዊው ፍጥረት አስፈሪ ገጽታ፣ ኀያሉ የእግዚአብሔር መንፈስ በክብርና በሞገስ በላዩ በረበበ ጊዜ ተወገደ። ይህም ተከትሎ የመጣውን የእግዚአብሔርን የመፍጠር ልዩ ችሎታ ወይም ኀይል የሚያመለክት ነበር። *የእግዚአብሔርም መንፈስ፤* በፍጥረት ተግባር ላይ ተሳትፎ የነበረው ሲሆን፣ ይህም ሥራው ዛሬም እንደ ቀጠለ ነው (ኢዮ 33፥4፤ መዝ 104፥30 ይመ)። *ይረብብ፤* ጫጩቶቿን ለመመገብና ከአደጋ ለመከላከል እንደምታንዣብብ ወፍ ማለት ነው (ዘዳ 32፥11፤ ኢሳ 31፥5 ይመ)።

1፥3 *እግዚአብሔር ... አለ፤* እግዚአብሔር በቃሉ ብቻ ሁሉን ነገር ካለመኖር ወደ መኖር አመጣ (መዝ 33፥6:9፤ 148፥5፤ ዕብ 11፥3 ይመ)። *ብርሃን ይሁን፤* አንድን ነገር ካለመኖር ወደ መኖር ወይም ካለመታወቅ ወደ መታወቅ ማምጣት የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል፣ ጨለማ ውስጥ ብርሃን እንዲሆን አደረገ። የእግዚአብሔር የፈጣሪነት ኀይሉ እንዲታይና የፍጡራንም ሕልውና እንዲጸና ብርሃን አስፈላጊ ነው። በብሉይ ኪዳን፣ ብርሃን የሕይወትና የበረከት ምሳሌ ነው (2ሳሙ 22፥29፤ ኢዮ 3፥20፤ 30፥26፤ 33፥30፤ 58፥8:10፤ 59፥9፤ 60፥1:3 ይመ)። እግዚአብሔር፣ ኀጢአት ባጨለመው ልብ ውስጥ አዲስ ፍጥረት መፍጠሩን ለማስረዳት ጳውሎስ ይህን ቃል ተጠቅሞአል (2ቆሮ 4፥6)።

*1፥4፤* እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር ሁሉ መልካም ነው (ቍ 10:12:18:21:25 ይመ)፤ የምዕራፉም የመዝጊያ ቃል የሚያመለክተው ሁሉም ነገር መልካም እንደ ሆነ ነው (ቍ 31)። በእግዚአብሔር መልክ እንዲሁም ሥርዐት በተፈጠረው ፍጥረት ውስጥ አንድም ሥርዐት አልባ ፍጡር ወይም በእግዚአብሔርና በሰው ላይ የተነሣ ኀይል የለም። ሌላው ቀርቶ ጨለማውና ጥልቁ እንኳ ሕይወትን ለመባረክና ለመጠበቅ በተፈጠረው ዓለም ውስጥ የተከበረ ተግባር ተሰጥቶአቸዋል (መዝ 104፥19-26፤ 127፥2 ይመ)።

1፥5 *ጠራው፤* ቍ 8-10 ይመ። በጥንት ጊዜ ለአንድ ነገር ወይም ለአንድ ሰው ስም ማውጣት፣ በዚያ ነገር ወይም ሰው ላይ የበላይ ወይም ባለቤት መሆንን ያመለክታል (17፥5:15፤ 2ነገ 23፥34፤ 24፥17፤ ዳን 1፥7 ይመ)። ቀኑም ሌሊቱም የጌታ ነው (መዝ 74፥16)። *የመጀመሪያ ቀን፤* አንዳንዶች የፍጥረት ቀኖች ባለ ሃያ አራት ሰዓት ቀኖች ናቸው ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ ቀኖቹ መለኪያቸው ምን እንደሆነ በውል አይታወቅም ይላሉ።

1፥6 *ጠፈር፤* ከምድር በላይ ያለ ከባቢ አየር ወይም፣ “ሰማይ” (ቍ 8) ማለት ነው። ይህንንም ለመግለጽ ከገቡት ስዕላዊ ገላጻዎች መካከል፣ “ከቀለጠ ናስ... እንደ ተሠራ መስተዋት” (ኢዮ 37፥18) እና “እንደ ድባብ” (ኢሳ 40፥22) የሚሉ ይገኙበታል።

1፥7 *እንዳለውም ሆነ፤* እግዚአብሔር “ይሁን” ብሎ ከተናገረ፣ እንዳለው ይሆናል (ቍ 9:11:15:24)

1፥9 *በአንድ ስፍራ፤* በሁሉም አቅጣጫ ደረቁን ምድር የከበበውን፣ የሐይቆችና የወንዞች ውሃ የሚፈሱበትን፣ “ባሕርን” ሥዕላዊ በሆነ መልክ (ቍ 10) የሚገልጽ ነው። “መሬትም ውሃ መካከልና በውሃም እንደ ተሠራች” (2ጴጥ 3፥5) “በባሕሮች ላይ መሥርቶአታል” (መዝ 24፥2) ውሆቹም ደግሞ ከተሰጣቸው ድንበር እንዲያልፉ አልተፈቀደላቸውም (መዝ 104፥7-9፤ ኤር 5፥22)።

1፥11 *እግዚአብሔር... አለ፤* ይህ ሐረግ በሦስተኛው ቀን ሁለት ጊዜ (ቍ 9:11)፣ በስድስተኛው ቀን ደግሞ ሦስት ጊዜ (ቍ 24፥26:29) ተጠቅሶአል። እንደ ምዕራፍ አንድ አወቃቀር፣ እነዚህ ሁለቱ ቀናት የሥራውን ሂደት ቍንጮዎች የሚያሳዩ ቀናት ናቸው። (“ቅርጽ የለሽና ባዶ” የሚለውን በተመለከተ የቍ 2 ማብ ይመ)።

13 መሸ፤ ነጋም፤ ሦስተኛ ቀን።
14 ከዚያም እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ "ቀኑን ከሌሊት
እንዲለዩ፣ የዓመት ወቅቶች፣ ቀናትና ዓመ
ታት የሚጀምሩበትንም እንዲያመለክቱ፣
15 ለምድር ብርሃን የሚሰጡ ልዩ ልዩ
ብርሃናት በሰማይ ይሁኑ" አለ፤ እንዳለውም
ሆነ። 16 እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ ለምድር ብርሃን
ይሰጡ ዘንድ ሁለት ታላላቅ ብርሃናት
አደረገ፤ ታላቁ ብርሃን በቀን እንዲሠለ
ጥን፣ ታናሹ ብርሃን በሌሊት እንዲሠለ
ጥን አደረገ። እንዲሁም ከዋክብትን
አደረገ። 17 ለምድር ብርሃን እንዲሰጡ
እነዚህን በሰማይ ጠፈር አኖራቸው።
18 ይኸውም በቀንና በሌሊት እንዲሠለ
ጥኑ፣ ብርሃንን ከጨለማ እንዲለዩ ነው።
እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ይህ መልካም እንደ
ሆነ አየ። 19 መሸ፤ ነጋም፣ አራተኛ ቀን።
20 እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ "ውሆች ሕይወት ባላ
ቸው በሕያዋን ፍጡራን ይሞሉ፤ ወፎች
ከምድር በላይ በሰማይ ጠፈር ይብረሩ"
አለ። 21 በዚህ መሠረት፣ እግዚአብሔር (ኤሎ
ሂም) በባሕር ውስጥ የሚኖሩ ታላላቅ ፍጡ
ራንን፣ በውሃ ውስጥ የሚርመሰመሱ ሕይ
ወት ያላቸውን ነገሮች ሁሉ እንደየወገናቸው
እንዲሁም ክንፍ ያላቸውን ወፎች ሁሉ እንደ

1፥13 ቊ5
1፥14 ቊ4፤ዘፍ 8፥22፤መዝ74፥16፤ 104፥19፤136፥7፤ኤር 10፥2፤31፥35-36፤ 33፥20:25
1፥15 ቊ7
1፥16 ዘዳ4፥19፤ 17፥3፤ኢዮ9፥9፤31፥ 26፤38፥7:31-33፤መዝ 8፥3፤36፥6፤74፥16፤ 104፥19፤136፥8:9፤ መክ12፥2፤ኢሳ40፥ 26፤ኤር8፥2፤31፥35፤ 43፥13፤ሕዝ8፥16፤ አሞ5፥8፤ያዕ1፥17
1፥18 ቊ4፤ኤር 33፥20:25
1፥19 ቊ5
1፥20 ዘፍ2፥19፤ መዝ146፥6
1፥21 ቊ1:4:11፤ ዘፍ8፥17፤9፥1:7:19፤ ዘሌ26፥9፤ኢዮ3፥8፤ 7፥12፤መዝ74፥13፤ 104፥25-26፤148፥7፤ ኢሳ27፥1፤ሕዝ32፥2፤ 36፥11፤47፥27
1፥22 ቊ28፤ዘፍ8፥ 17፤9፥17:19፤47፥27፤ ዘሌ26፥9፤ሕዝ36፥11
1፥23 ቊ5
1፥24 ቊ7:11፤ዘፍ 2፥19

የወገናቸው ፈጠረ፤ እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ይህ
መልካም እንደ ሆነ አየ። 22 እግዚአብሔርም
(ኤሎሂም)፣ "ብዙ ተባዙ፤ የባሕርንም ውሃ
ሙሏት፤ ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ" ብሎ
ባረካቸው። 23 መሸ፤ ነጋም፤ አምስተኛ ቀን።
24 እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ "ምድር ሕያዋን ፍጡራንን
እንደየወገናቸው፣ ከብቶችን፣ በምድር ላይ
የሚሳቡ ፍጡራንንና የዱር እንስሳትን
እያንዳንዱን እንደ ወገኑ ታስገኝ" አለ፤
እንዳለውም ሆነ። 25 እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
የዱር እንስሳትን እንደየወገናቸው፣ ከብ
ቶችን እንደየወገናቸው፣ እንዲሁም በም
ድር ላይ የሚሳቡ ፍጡራንን እንደየወገ
ናቸው አደረገ። እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ይህ
መልካም እንደ ሆነ አየ።
26 እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ "ሰውን በመልካ
ችን፣ በአምሳላችን እንሥራ፤ በባሕር ዓሦች፣
በሰማይ ወፎች፣ በከብቶች፣ በምድር[a] ሁሉ
ላይ፣ እንዲሁም በምድር በሚሳቡ ፍጡራን
ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራቸው" አለ።

1፥25 ቊ4:11፤ዘፍ7፥21-22፤ኤር27፥5 1፥26 ቊ27፤ዘፍ3፥5:22 ፤5፥3፤9፥2-6፤11፥7፤መዝ8፥5-8፤82፥6፤89፥6፤100፥3፤ኢሳ6፥8፤45፥ 18፤ሐሥ17፥28-29፤1ቆሮ11፥7፤2ቆሮ4፥4፤ቈላ1፥15፤3፥10፤ያዕ3፥9

[a]26 ዕብራይስጡም እንደዚሁ ሲሆን ሱርስቱ ግን *የዱር እንስሳት ሁሉ* ይለዋል።

የተፈጠሩበት ቀናት
1."ብርሃን" (ቊ 3)
2."ከጠፈሩ በላይና ከጠፈሩ በታች ያለውን ውሃ" (ቊ 7)
3. ሀ. "ደረቁ ምድር" (ቊ 9)
ለ. "ዕፀዋትን" (ቊ 11)

የተሞሉበት ቀን
4. "ብርሃን" (ቊ 15)
5. "በባሕር ውስጥ የሚኖሩ ታላላቅ ፍጡራንን... እንዲሁም ክንፍ ያላቸውን ወፎች ሁሉ" (ቊ 21)
6. ሀ1. "ምድር ሕያዋን ፍጡራንን እንደየወገናቸው ከብቶችን፣ በምድር ላይ የሚሳቡ፣ ፍጡራንንና የዱር እንስሳትን" (ቊ 24)
ሀ2. "ሰውን" (ቊ 26)
ለ. "ማንኛውም ለምለም ተክል ምግብ እንዲሆናቸው" (ቊ 30)

በቀኖቹ መካከል ያለው አግድማዊና ዐምዳዊ ግንኙነት፣ የምዕራፉን ሥነ-ጽሑፋዊ ውበት እና የእግዚአብሔርን ሥርዐት ያለው የመፍጠር ተግባር ያመለክታል። *እንደየወገናቸው፤* ቊ 12:21:24-25 ይመ። መፈጠርም ሆነ መራባቱ (መዋለድ) ሥርዐት ያላቸው ነገሮች ናቸው።

1፥14 *እንዲያመለክቱ፤* በዚህ ቦታ በገባው መሠረት እንጂ፣ በኮከብ ቈጠራ ወይም በሌላ በማንኛውም ዐይነት አገባብ አይደለም።

1፥16 *ሁለት ታላላቅ ብርሃናት፤* "ፀሐይ" እና "ጨረቃ" የሚሉት ቃላት ሆን ተብሎ የተወገዱ ይመስላል፤ ምክንያቱም ሁለቱም ቃላት በዚያን ወቅት ለነበሩት ሕዝቦች የአማልክቶቻቸው መጠሪያ ስሞች ነበሩ። ብርሃን የሚሰጡ አካላት በመሆናቸው ልናደንቃቸው እንጂ ልንፈራቸው የሚገቡ ኀይላት አይደሉም፤ እነዚህንም የፈጠረው፣ እውነተኛ አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ነውና (ኢሳ 40፥26)። ምናልባት በታላቁ ብርሃንና በታናሹ ብርሃን ላይ አጽንዖት በመደረጉ፣ ከዋክብት በመጨረሻ የተፈጠሩ ወይም ሁሉ ነገር ካለቀ በኋላ የታሰቡ ይመስላል። ነገር ግን ጨረቃ፣ "በሌሊት እንዲሰለጥን" በከዋክብት እንደምትታገዝ በመዝ 136፥9 ላይ ተጽፎአል። *እንዲሠለጥን፤* ታላቁ ፈጣሪ ንጉሥ እግዚአብሔር፣ ለአንዳንድ ፍጥረቱ የማስተዳደርን ሥልጣን ሰጥቶአል (ቊ 26:28 ይመ)።

1፥17-18 የሰማይ አካላት ያላቸውን ሦስት ዋና ዋና ተግባራት የሚገልጽ ነው።

1፥21 *በባሕር ውስጥ የሚኖሩ ... ፍጡራን፤* ይህን ሐረግ የሚገልጸው የዕብራይስጡ ቃል፣ በከነዓናውያን ሥነ-ተረት ውስጥ በጣም አስፈሪ ለሆነ አንድ የባሕር ውስጥ እንስሳ የተሰጠ ስያሜ ነው። ይህ አስፈሪ የባሕር ውስጥ እንስሳ፣ በብሉይ ኪዳን የቅኔ መጻሕፍት ውስጥ ምሳሌያዊ በሆነ አነጋገር እጅግ ኀያላን ከሆኑት የእግዚአብሔር ጠላቶች መካከል እንደ አንዱ ተጠቅሶአል፤ በአገር ተመስሎም ቀርቦአል (ባቢሎን ኤር 51፥34፤ ግብፅ ኢሳ 51፥9፤ ሕዝ 29፥3፤ 32፥2) ወይም በሰማይ አካል ተመስሎአል (ኢዮ 7፥12፤ መዝ 74፥13፤ ኢሳ 27፥1)፤ አንዳንዶች ግን ሁለተኛውን አማራጭ የሚያያይዙት ከግብፅ ጋር ነው። በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት የባሕር ፍጡራን ግን እንደ ጠላት የሚፈሩ ሳይሆኑ፣ የእግዚአብሔር መልካም ሥራዎች በመሆናቸው አድናቆት የሚገባቸው ናቸው። *ክንፍ ያላቸውን ወፎች፤* ቃሉ የሚበሩትን እንስሳት ሁሉ ያጠቃልላል (ዘዳ 14፥19-20)።

1፥22 *ብዙ ተባዙ፤* በውሃ ውስጥ ለሚኖሩና በአየር ላይ ለሚበሩ ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ የተሰጠ የእግዚአብሔር ቡራኬ ነው። እነዚህ እንስሳት አካባቢያቸውን በሕይወት ሊሞሉና ሊለመልሙ የሚችሉት ከእግዚአብሔር ባርኮት የተነሣ ነው (የቊ 28 ማብ ይመ)። እግዚአብሔር የፍጥረቱ ጌታ በመሆኑ ሕይወት ሁሉ ይለመልማል የተባረከም ይሆናል።

1፥26 *በመልካችን፣ በአምሳላችን እንሥራ፤* እግዚአብሔር ፈጣሪና ንጉሥ (ፈጣሪ-ንጉሥ) በመሆኑ ታላቅና ክቡር ሥራውን ያስተዋውቃል (3፥22፤ 11፥7፤ ኢሳ 6፥8፤ እንዲሁም 1ነገ 22፥19-23፤ ኢዮ 15፥8፤ ኤር 23፥18 ይመ)። *በመልካችን፣ በአምሳላችን፤* እነዚህ ሁለት ቃላት፣ በብሉይ ኪዳንም ሆነ (5፥1፤9፥6) በአዲስ ኪዳን ውስጥ (1ቆሮ 11፥7፤ ቈላ 3፥10፤ ያዕ 3፥9) ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸው በመሆኑ፣ በመካከላቸው ምንም ዐይነት ልዩነት መደረግ የለበትም። ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር መልክ በመሆኑ ክብርና አክብሮት ሊሰጠው ይገባል፤ መገደል (9፥6) ወይም መረገም (ያዕ 3፥9) የለበትም። "መልክ" የሚለው ቃል ጽድቅንና ቅድስናን (ኤፌ 4፥24) እንዲሁም ዕውቀትንና (ቈላ 3፥10) የመሳሰሉትን ባሕርያት አካቶ ይይዛል። አማኞች የክርስቶስን መልክ እንዲመስሉ ተወስኖአል (ሮሜ 8፥29)፤ አንድ ቀንም እርሱን እንደሚመስሉ ተነግሮአል (1ዮሐ 3፥2)። *ሥልጣን ይኑራቸው፤* ሰው እግዚአብሔር ከፈጠረው ፍጥረት ሁሉ የመጨረሻው ሲሆን፣ እግዚአብሔርም "የክብርና የሞገስን ዘውድ አቀዳጀኸው"፤ "ሁሉንም... አስገዛህለት" (መዝ 8፥5-8)። ሰው በመለኮታዊው ንጉሥ መልክ የተፈጠረ በመሆኑ፣ የሉዓላዊነት (የንጉሥነት/የገዥነት) የውክልና ገዥነት/መሪነት ተሰጥቶታል (የተዋጀው ሰው የሚቀበለውን የገዥነት ሥልጣን ከዕብ 2፥5-9 ላይ ይመ)።

27ስለዚህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰውን በራሱ መልክ
ፈጠረው፤
በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) መልክ ፈጠረው፤
ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።

28እግዚአብሔርም (ኤሎሂም)፣ "ብዙ ተባዙ፤ ምድ
ርን ሙሏት፤ ግዟትም፤ የባሕርን ዓሦች፣
የሰማይን ወፎች፣ እንዲሁም በምድር ላይ
የሚንቀሳቀሱትን ሕያዋን ፍጡራንን ሁሉ
ግዟቸው" ብሎ ባረካቸው።
29እግዚአብሔርም (ኤሎሂም)፣ እንዲህ አለ፤ "በም
ድር ላይ ያሉትን ዘር የሚሰጡ ተክሎ
ችን ሁሉ፣ በፍሬያቸው ውስጥ ዘር ያለባ
ቸውን ዛፎች ሁሉ ምግብ ይሆኑላችሁ
ዘንድ ሰጥቻችኋለሁ። 30እንዲሁም ለምድር
አራዊት ሁሉ፣ ለሰማይ ወፎች ሁሉ፣ በም
ድር ላይ ለሚንቀሳቀሱ ሕያዋን ፍጡራን
ሁሉ ማንኛውም ለምለም ተክል ምግብ
እንዲሆናቸው ሰጥቻለሁ" እንዳለውም ሆነ።
31እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ያደረገውን ሁሉ አየ፤
እነሆም፣ እጅግ መልካም ነበረ። መሸ፤ ነጋም፤
ስድስተኛ ቀን።

2 ሰማያትና ምድር፣ በውስጣቸውም ያሉት
ሁሉ አፈጣጠር በዚህ ሁኔታ ተከናወነ።
2እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ይሠራ የነበረውን ሥራ
በሰባተኛው ቀን ላይ ፈጽሞ ነበር፤ ስለዚህ
ከሠራው ሥራ ሁሉ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ።[ሖ]
3እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰባተኛውን ቀን ባረከው፤
ቀደሰውም፤ ከፍጥረት ሥራው
ሁሉ ያረፈው በሰባተኛው ቀን ነውና።

## አዳምና ሔዋን

4እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ሰማያትንና
ምድርን በፈጠረ ጊዜ የተከናወኑት እንደዚህ
ነበረ፤
እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ሰማያት
ንና ምድርን ሲፈጥር 5የሜዳ ቡቃያ ገና
በምድር[ሙ] ላይ አልታየም፤ የሜዳ ተክልም
ገና አልበቀለም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር
አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) በመሬት ላይ ገና ዝናብ
አላዘነበም ነበር፤ ምድርንም የሚያለማ ሰው
አልነበረም። 6ነገር ግን ውሃ[ሚ] ከመሬት
እየመነጨ የምድርን ገጽ ያረሰርስ ነበር።
7እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ከምድር ዐፈር
ወስዶ ሰውን[ሩ] አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕ
ይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው
ነፍስ ሆነ።

1፥27 ቆላ1:26፤ዘፍ 2፥7፤5፥1:2፤ዘዳ4፥32፤መዝ103፥14፤119፥7 3፤ማቴ19፥4፤ማር 10፥6፤ገላ3፥28
1፥28 ቆላ22:26፤ ዘፍ6፥1፤17፥6፤33፥5፤ ኢሱ24፥3፤መዝ8፥6-8፤113፥9፤115፥16፤ 127፥3:5፤ሐሥ17፥26
1፥29ዘፍ9፥3፤ዘዳ12፥15፤መዝ104፥14፤ 1ጢሞ4፥3
1፥30 ዘፍ2፥7፤7፥22 ፤ኢዮ38፥41፤መዝ78፥25፤104፥14:27፤ 111፥5፤136፥25፤ 145፥15፤147፥9
1፥31 ቆላ4:5፤መዝ 104፥24፤136፥5፤ምሳ 3፥19፤ኤር10፥12፤ 1ጢሞ 4፥4
2፥1 ዘዳ4፥19፤17፥3 ፤2ነገ17፥16፤21፥3፤ መዝ104፥2፤ኢሳ44፥24፤45፥12፤48፥13፤ 51፥13
2፥2 ቆላ2-3፤ዘፀ20፥11፤31፥17፤34፥21፤ ዘዳ5፥14፤ዮሐ5፥17፤ ዕብ4፥4
2፥3 ዘፍ1፥1፤ዘፀ16፥23፤20፥10፤23፥12፤ 31፥15፤35፥2፤ዘሌ23፥3፤ነህ9፥14፤መዝ95፥11፤ኢሳ58፥13፤ኤር 17፥22፤ዕብ4፥1-11
2፥4 ዘፍ1፥1፤5፥1፤ 6፥9፤10፥1፤ 11፥10:27፤25፥12:19፤36፥1:9፤37፥2፤ኢዮ38፥8-11 2፥5 ዘፍ1፥11 ፤ኢዮ38፥28፤መዝ65፥9-10፤ኤር10፥13 2፥7 ዘፍ1፥2:27:30፤3፥19: 3፤4፥2፤18፥27፤ኢዮ4፥19፤10፥9፤12፥10፤17፥16፤27፥3፤32፥8፤33፥4፤ 34፥14:15፤መዝ90፥3፤103፥14፤104፥29፤መክ3፥20፤12፥7፤ኢሳ2፥22 ፤29፥16፤42፥5፤43፥1:21፤44፥2፤57፥16፤ኤር18፥6፤ሕዝ37፥5፤ሐሥ 17፥25፤1ቆሮ15፥45:47

[ሖ]2 ወይም *ለቀመ*፤ በቍ 3 ላይም እንዲሁ
[ሙ]5 ወይም *መሬት*፤ በቍ 6 ላይም እንዲሁ
[ሚ]6 ወይም *ጭጋግ*
[ሩ]7 በዕብራይስጥ ሰው (አዳም) የሚለው ቃል፣ መሬት (አዳማኽ) ከሚለው ቃል ጋር በድምፅ ይመሳሰላል፤ በፍቺም ሳይዛመድ አይቀርም፤ አዳም የመጀመሪያው ሰው ስምም ነው (ዘፍ 2፥20 ይመ)

*1፥27፤* ይህ እጅግ ወሳኝ ቍጥር በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የመጀመሪያው ግጥም ነው (ወደ አርባ ከመቶ የሚጠጉት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት በግጥም ነው)። *ፈጠረው፤* ይህ ቃል በዚህ ሥፍራ ሦስት ጊዜ የተደገመው በስድስተኛው ቀን የተከናወነውን ታላቁን የእግዚአብሔርን ሥራ ለመግለጽ ነው (የቍ 1 ማብ ይመ)። *ወንድና ሴት፤* ሁለቱም በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥረዋል፤ ሁለቱም በአንድነት የመለኮትን በረከት ተካፋዮች ናቸው።

1፥28 *እግዚአብሔርም... ሙሏት፤ ግዟትም፤... ግዟቸው ብሎ ባረካቸው ፤* የሰው ልጅ በሌሎች የምድር ፍጥረታት ላይ ሥልጣኑን እየተለማመደ፣ ምድርን እየሞላና እየተንከባከበ በዚህ መለኮታዊ በረከት ሥር ይኖራል (ቍ 26፤2፥15፤ መዝ 8፥6-8 ይመ)። ሰው በኀጢአት ከወደቀ በኋላ በትዕቢት ተነሣሥቶ በእግዚአብሔር ላይ ቢያምጽም፣ በመሠረቱ የሰው ባህል ከእግዚአብሔር ጋር የሚጻረር አይደለም። ባህል፣ ሰው በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩን፣ እንዲሁም ሰው የእግዚአብሔር አገልጋይ ከመሆኑ የተነሣ በእግዚአብሔር መለኮታዊ አስተዳደር ውስጥ ተሳትፎ እንዳለው የሚገልጽ ነው። በፍጥረተ ዓለም የእግዚአብሔር ወኪል እንደመሆኑም፣ የእግዚአብሔር ፍጥረት አዛዥና መጋቢ ነው። ስለዚህ ሊጠነቀቅላቸው፣ ለእግዚአብሔርና ለሰውም አገልግሎት ሊጠቀምባቸው እንጂ ሊበዘብዛቸው፣ ሊያበላሻቸው ወይም ሊዘርፋቸው አይገባውም።

*1፥29-30፤* ሰዎችና እንስሳት፣ ከመጀመሪያው አትክልት ተመጋቢ እንደ ነበሩ የሚያመለክት ይመስላል (9፥3 ይመ)።

1፥31*እጅግ መልካም፤* የቍ 4 ማብ ይመ። *ስድስተኛ ቀን፤* የቀኑን የሥራ መደምደሚያነትና አስፈላጊነት ለማጉላት የተጠቀሰ ሊሆን ይችላል።

2፥2 *ፈጽሞ ... ዐረፈ፤* እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ያረፈው ደክሞት ሳይሆን፣ ባዶና ቅርጽ የለሽ ሆኖ የቀረ ምንም ነገር ስላልነበረ ነው አማራጭ ትርጕሙን ይመ። የፍጥረት ሥራውም ተጠናቀቀ፤ ሁሉም መልካም፣ ፍጹምና እጅግ ደስ የሚያሰኝ ሆነ (1፥31)። መድገም፣ መጠገን ወይም መከለስ አላስፈለገም፤ ፈጣሪም የሠራውን ሁሉ መለስ ብሎ ያይ ዘንድ ዐረፈ።

2፥3 *እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን ባረከው፤ ቀደሰውም፤ ... ያረፈውም፤* "ሰንበት" የሚለው ቃል በዚህ ሥፍራ ባይጠቀስም፣ "ያረፈው" ተብሎ በዚህ ቦታ የገባው የዕብራይስጡ ግስ (ቍ 2) ሰንበት ለሚለው ቃል መሠረቱ ነው። ዘፀ 20፥11 የቍ 3ን የመጀመሪያ ክፍል ይጠቅሳል፤ ሆኖም "ሰባተኛ" በሚለው ፈንታ "ሰንበት" የሚለውን ቃል በመተካቱ ሁለቱን ቃላት በእኩል ደረጃ አስቀምጦአቸዋል። የእስራኤል ሕዝብ ሰንበትን የመጠበቅ ግዴታ እንዳለበት ለመጀመሪያ ጊዜ የተነገረው ከግብፅ ወጥቶ ወደ ሲና በመጓዝ ላይ ሳለ ሲሆን (ዘፀ 16)፣ እንደ ነህ 9፥13-14 አባባል ደግሞ በሲና ተራራ ላይ ሕግ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ ሰንበትን የመጠበቅ ግዴታ አልነበረም።

2፥4 *የተከናወኑት፤* ይህ ቃል (ዕብራይስጡ) በዘፍጥረት መጽሐፍ በእያንዳንዱ ዋና ክፍል መግቢያ ላይ ዐሥር ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል (በመጽሐፉ መግቢያ ላይ "ሥነ ጽሑፋዊ ገጽታው" የሚለውን ይመ)። *ሰማያትንና ምድርን፤* የ1፥1 ማብ ይመ። "ሰማያትንና ምድርን በፈጠር ጊዜ የተከናወኑት" የሚለው ሐረግ፣ እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት የገጠመውን ነገር የሚናገር ነው። ኀጢአትና ዐመፅ፣ እግዚአብሔር በሠራው/ ባዘጋጀው በመልካም የአትክልት ሥፍራ የሚኖሩትን የአዳምንና የሔዋንን ታሪክ ያጨለመውን ሦስት እጥፍ መርገም አስከተለ፤ ይኸውም (1) በሰይጣን ላይ (3፥14)፤ (2) በሰው ምክንያት በምድር ላይ (3፥17) እና (3) በቃየን ላይ (4፥11)። 1፥1-2፥3 የፍጥረትን አጠቃላይ ታሪክ የያዘ ሲሆን፣ 2፥4-4፥26 ደግሞ በሰው ልጆች ታሪክ አጀማመር ላይ ያተኵራል። *እግዚአብሔር አምላክ፤* እግዚአብሔር (በዕብራይስጥ "ያህዌ") የግልና የቃል ኪዳን ስሙ ነው (የዘፀ 3፥15 ማብ ይመ)፤ ይህም እስራኤልን የሚቤዥና ለእሥራኤል የቃል ኪዳን አምላክ መሆኑን ይገልጻል (የዘፀ 6፥6 ማብ ይመ)። አምላክ (በዕብራይስጥ ኤሎሂም) የሚለው አጠቃላይ ስሙ ነው። ሁለቱም ስሞች በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ በብዙ ሺህ ጊዜ የተጠቀሱ ሲሆን፣ ልክ በዚህ ቦታ ተጠቅሶ እንደምናገኘው አብዛኛውን ጊዜ በአንድነት በመሆን "ብቻውን አምላክ የሆነውን" እግዚአብሔርን ያመለክታሉ።

2፥7 *አበጀው፤* የሸክላ ሠሪን ተግባር የሚያመለክት ቃል ነው (ኢሳ 45፥9፤ ኤር 18፥6)፤ የሸክላ ሥራ ባለ ሙያ የተለያዩ ዕቃዎችን በተለያዩ ቅርጾች ያዘጋጃል (ኢዮ 33፥6)። "እንሥራ"(1፥26)፣ "አበጀ" (2፥7) የሚሉት ቃላት እግዚአብሔር ሰውንና እንስሳትን እንደ ፈጠረ ለመግለጽ የገቡ ናቸው (ቍ 19፥1፡ 21:25)። *የሕይወት እስትንፋስ፤* ሰዎችና እንስሳት በውስጣቸው የሕይወት እስ

8*እግዚአብሔር* ኤሎሂም (ያህዌ ኤሎሂም) በምሥራቅ፣
በዔድን የአትክልት ስፍራ አዘጋጀ፤ ያበጀ
ውንም ሰው በዚያ አኖረው። 9*እግዚአብሔር*
ኤሎሂም (ያህዌ ኤሎሂም) ለዐይን የሚያስደስት ለመ
ብልም መልካም የሆነውን ዛፍ ሁሉ ከምድር
አበቀለ፤ በአትክልቱ ቦታ መካከልም የሕይ
ወት ዛፍ ነበረ፤ እንዲሁም መልካምና ክፉን
መለየት የሚያስችለው የዕውቀት ዛፍ ነበረ።
10የአትክልት ስፍራውን የሚያጠጣ ወንዝ
ከዔድን ይፈስ ነበር፤ ከዚያም በአራት ተከ
ፍሎ ይወጣ ነበር። 11የመጀመሪያው፣ ወርቅ
በሚገኝበት በሐዊላ ምድር ዙሪያ ሁሉ የሚ
ፈሰው የፊሶን ወንዝ ነው። 12ኤውላጥ ምርጥ
የሆነ ወርቅ፣ መልካም መዐዛ^ ያለው ክር
ቤና የከበረ ድንጋይ የሚገኝበት ምድር ነው።
13ሁለተኛው፣ በኢትዮጵያ# ምድር ዙሪያ ሁሉ
የሚፈሰው የግዮን ወንዝ ነው። 14ሦስተኛው፣
ከአሦር በስተ ምሥራቅ የሚፈሰው የጤግ
ሮስ ወንዝ ሲሆን፣ አራተኛው የኤፍራጥስ
ወንዝ ነው።
15*እግዚአብሔር* ኤሎሂም (ያህዌ ኤሎሂም) ሰውን
ወስዶ እንዲያለማትና እየተንከባከበ እንዲጠ
ብቃት በዔድን የአትክልት ስፍራ አስቀ
መጠው። 16*እግዚአብሔር* ኤሎሂም (ያህዌ ኤሎሂም)
ሰውን እንዲህ በማለት አዘዘው፤ "በአትክ
ልት ስፍራው ውስጥ ከሚገኝ ከማንኛውም
ዛፍ ፍሬ ትበላለህ፤ 17ነገር ግን መልካምና
ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ አትብላ፤ ምክን
ያቱም ከእርሱ በበላህ ቀን በእርግጥ ትሞታ
ለህ።"

18ከዚህ በኋላ *እግዚአብሔር* ኤሎሂም (ያህዌ ኤሎ
ሂም)፣ "ሰው ብቻውን መሆኑ መልካም አይ
ደለምና የሚስማማውን ረዳት አበጅለታ
ለሁ" አለ።
19*እግዚአብሔር* ኤሎሂም (ያህዌ ኤሎሂም) የዱር
አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ከምድር ሠርቶ
ነበር፤ ለእያንዳንዳቸውም ምን ስም እንደሚ
ያወጣላቸው ለማየት ወደ አዳም አመጣቸው።
አዳም ሕይወት ላላቸው ፍጡራን ሁሉ ያወ
ጣላቸው ስም መጠሪያቸው ሆነ። 20ስለዚህ
አዳም+ ለከብቶች፣ ለሰማይ ወፎች፣ ለዱር
አራዊት ሁሉ ስም አወጣላቸው።
ይሁን እንጂ ለአዳም ተስማሚ ረዳት አል
ተገኘለትም ነበር። 21*እግዚአብሔር* ኤሎሂም
(ያህዌ ኤሎሂም) በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍ ጣለ
በት፤ አንቀላፍቶም ሳለ ከጎድኑ አንዲት ዐጥ
ንት^ ወስዶ፣ ስፍራውን በሥጋ ሞላው። 22*እግ
ዚአብሔር* ኤሎሂም (ያህዌ ኤሎሂም) ከአዳም የወሰዳ
ትን ዐጥንት+ ሴት አድርጎ ሠራት፤ ወደ
አዳምም አመጣት።

23አዳምም እንዲህ አለ፤

"እነሆ፤ ይህች ዐጥንት ከዐጥንቴ፣
ሥጋም ከሥጋዬ ናት።
ከወንድ ተገኝታለችና ሴት* ትባል።"

2፥8 ቍ10:15፤ዘፍ 3፥23:24፤4፥16፤13፥10፤ኢሳ51፥3፤ሕዝ 28፥13፤31፥9:16፤36፥35፤ኢል2፥3
2፥9 ዘፍ3፥22:24፤ ሕዝ31፥8፤47፥12፤ ምሳ3፥18፤11፥30፤ራእ 2፥7፤
2፥10 ቍ8፤ዘኍ24፥6፤መዝ46፥4፤ሕዝ47፥5
2፥11 ዘፍ10፥7፤ 25፥18
2፥12 ዘኍ11፥7
2፥17 ዘፍ15፥18፤ 31፥21፤41፥1፤ዘፀ 23፥31፤ዘኍ22፥5፤ ዘዳ1፥7፤11፥24፤ኢሱ 1፥4፤2ሳሙ8፥3፤1ነገ 4፥21፤2ነገ23፥29፤24፥7፤1ዜና5፥9፤18፥3፤ 2ዜና35፥20፤ኤር13፥4፤46፥2፤51፥63፤ዳን 10፥4፤ራእ9፥14
2፥15 ቍ8
2፥16 ዘፍ3፥1-2
2፥17ዘፍ3፥1:3:11:7፤5፥5፤9፥29፤ዘዳ30፥15:19፤ኤር42፥16፤ ሕዝ3፥18፤ሮሜ5፥12፤6፥23
2፥18 ምሳ31፥11፤ 1ቆሮ11፥9፤1ጢሞ 2፥13
2፥19ዘፍ1፥5:20: 24፤መዝ8፥7
2፥20 ዘፍ3፥20፤4፥1
2፥21 ዘፍ15፥12፤ 1ሳሙ26፥12፤ኢዮ 33፥15
2፥22 1ቆሮ11፥8:9፤12፤1ጢሞ2፥13 2፥23 ዘፍ1፥5፤29፥14፤1ቆሮ11፥8፤ኤፌ5፥28-30

^12 ወይም *መልካም ዕንቁ*
#13 ደቡብ ምሥራቅ መስጴጦምያ ሊሆን ይችላል
+20 ወይም *ሰው* ^21 ወይም *ከሰው የጐን ክፍል ወሰደ*
+22 ወይም *ክፍል*
*23 *ሰው የሚል ትርጉም ያለው የዕብራይስጥ ቃል ሴት የሚል ትርጉም ካለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው*

ትንፋስ አላቸው (1፥30፤ ኢዮ 33፥4 ይመ)። *ሰውም ሕያው ነፍስ ሆነ፤* ለዚህ ዐረፍተ ነገር የገባው የዕብራይስጥ ሐረግ፣ "ሕያዋን ፍጡራን" ተብሎ በ1፥20 እና 24 ላይ ተተርጕሞአል። ስለዚህ የ2፥7 ቃላት፣ ሰውና እንስሳት ቢያንስ አካላዊ ተመሳሳይነት እን ዳላቸው ያሳያሉ። ይሁን እንጂ ሰው፣ "በራሱ መልክ" መፈጠሩ (1፥27) ከእግዚአብሔርም ከሌሎች ፍጡራንም ጋር ልዩ ግንኙነት እንዳለው ያስረዳል፤ ለእግዚአብሔር እንደ አገልጋይ፣ ለሌላው ፍጥረት ደግሞ እንደ ገዥና እንደ መጋቢ በመሆኑ፣ በሰውና በእንስሳት መካከል ከፍተኛ ልዩነት መኖሩን ያመለክታል (መዝ 8፥5-8)።

2፥8 *በምሥራቅ፤* የዘፍጥረትን መጽሐፍ የጻፈው ሰው ከቆመበት ሥፍራ አንሥቶ ማለት ነው። የአትክልቱ ሥፍራ ምናልባት የኤፍራጥስና የጤግሮስ ወንዞች በሚገናኙበት አቅራቢያ ሊሆን ይችላል (ቍ 14)፤ ይህም በአሁኑ ጊዜ በደቡባዊ ኢራቅ የሚገኝ ቦታ ነው። *በዔድን፤* "ገነት" ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፣ (1) በዕብራይስጥ "ታላቅ ደስታ" ወይም (2) በመስጴጦምያ ቋንቋ "ሜዳ" ከሚሉ ቃላት ጋር ይያያዛል፤ ጸሓፊው ምናልባት ሁለቱንም ፍችዎች እንዲፈነጥቅ ፈልጐ ይሆናል።

2፥9 *የሕይወት ዛፍ፤* የሕይወት ምሳሌ ነው፤ ፍሬው ለሚበሉት ሕይወትን ይሰጣል (3፥22፤ ራእ 2፥7፤ 22፥2:14 ይመ)። *መልካምና ክፉን መለየት የሚያስችለው የዕውቀት ዛፍ፤* የመልካምና የክፉ ምሳሌ ሲሆን፣ መልካሙንና ክፉውንም ያሳውቃል፤ ፍሬውን የሚበሉትንም ወደ ሞት ይወስዳቸዋል (ቍ 17፤ 3፥3) "መልካምና ክፉን መለየት የሚያስችለው" የሚለው የሥነ-ምግባር ዕውቀትን ያመለክታል (ዘዳ 1፥39፤ ኢሳ 7፥15-16 ይመ)። አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር የተፈጠሩ በመሆናቸው ሕይወት አላቸው፤ በጎን ነገር ከክፉ የመለየት ችሎታም አላቸው። የጥንት ጣዖት አምላኪዎች፣ "የአማልክት ምኞት ሰው ሁልጊዜ ሟች እንዲሆን ነው" ይላሉ። በዘፍጥረት እንደምናየው ግን፣ ሰው ወደ ሕይወት ዛፍ ደርሶ ከፍሬው መብላቱ፣ እግዚአብሔር ለእርሱ ያለው ፈቃድ ወይም ሐሳብ ሕይወት መሆኑን ያመለክታል። አዳምና ሔዋን መልካምንና ክፉን ከምታሳውቀው ዛፍ በመብላታቸው፣ በራሳቸው መንገድና አስተሳሰብ መልካምንና ክፉን ለመለየት እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጥገኝነት ተላቀው በራሳቸው ችሎታ ለመኖር መወሰናቸውን ያሳያል።

2፥11 *ፊሶን፤* ቦታው የት እንደ ሆነ በትክክል አይታወቅም። የዕብራይስጡ ትርጉም በተፈጥሮ ዘይት የተሞላ ጕድጓድ የሚል ነው።

2፥12 *ኤውላጥ፤* ምናልባት በ10፥29 ላይ በድጋሚ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ቦታው የት እንደ ሆነ ግን በትክክል አይታወቅም። ይህም በ10፥7 ላይ ከተጠቀሰው በግብፅ ከሚገኘው ኤውላጥ የተለየ ሳይሆን አይቀርም።

2፥13 *ግዮን፤* ቦታው የት እንደ ሆነ በትክክል አይታወቅም። በዕብራይስጥ በኀይል የሚወርድ ወንዝ ማለት ነው። ፊሶንና ግዮን በመስጴጦምያ ዝቅተኛ አካባቢ፣ በፋርስ ባሕረ-ሰላጤ አቅራቢያ የነበሩ ጅረቶች ሳይሆኑ አይቀሩም። ሙሴ መጽሐፉን በጻፈበት ወቅት እነዚህ ስሞች የተለመዱ ነበሩ።

2፥14 *አሦር፤* በጥንት ዘመን የሶርያ ዋና ከተማ ነበረች ("ሶርያ" እና "አሦር" ተዛማጅ ቃላት ናቸው) *ኤፍራጥስ፤* ከትልቅነቱና ከጠቀሜታው የተነሣ አብዛኛውን ጊዜ "ወንዙ" በመባል (1ነገ 4፥21:24) ይታወቃል።

2፥15 *እንዲያለማትና እየተንከባከበ እንዲጠብቃት፤* የ1፥28 ማብ ይመ። ሰው፣ ሁሉን ከሚችለው አምላክ በታች በመሆን ምድርን በኀላፊነት እንዲያስተዳድር ሥልጣን ተሰጠው።

2፥16 *ከማንኛውም ዛፍ፤* የሕይወትንም ዛፍ ጨምሮ ማለት ነው (ቍ 9)።

2፥17 *በእርግጥ ትሞታለህ፤* እባቡ "መሞት እንኳ አትሞቱም" ብሎ ቢክድም (3፥4)፣ ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ሞትን ያስከትላል።

2፥18-25 በጥንቱ የቅርብ ምሥራቅ ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ ትክክለኛውን የሴቶች አፈጣጠር በተሟላ ሁኔታ የሚያቀርብ ብቸኛ ጽሑፍ ነው።

2፥18 *ብቻውን መሆኑ መልካም አይደለም፤* ወንድ፣ ያለ ሴት ባልንጀራነትና የመዋለድ ተባባሪነት፣ ሙሉ ሰብዓዊነቱ ሊታወቅ አይችልም።

2፥19 *ስም እንዲያወጣላቸው፤* በዙሪያው ባለው ፍጥረት ሁሉ ላይ የበላይነቱን ያሳየበት የመጀመሪያ ተግባር ነው።

*2፥23 ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል* ዕብራይስጡ ወንዱን 'ኢሽ' ሲል፣ ሴቷን 'ኢሻ' ይላል፤ ድምፃቸው ይመሳሰላል።

[24]ስለዚህ ሰው ከአባቱና ከእናቱ ተለይቶ
ከሚስቱ ጋር ይጣመራል፤ ሁለቱም አንድ
ሥጋ ይሆናሉ።
[25]አዳምና ሚስቱ፣ ሁለቱም ዕራቍታቸውን
ነበሩ፤ ይሁን እንጂ አይተፋፈሩም ነበር።

## የሰው ውድቀት

3 እባብ *እግዚአብሔር* ስምባክ (ያህዌ ኤሎሂም) ከፈ
ጠራቸው የዱር አራዊት ሁሉ ተንኰለኛ
ነበረ፤ ሴቲቱንም፣ "በእርግጥ እግዚአብሔር (ኤሎ
ሂም)፣ 'በአትክልቱ ስፍራ ካሉ ዛፎች ከማናቸ
ውም እንዳትበሉ' ብሎአልን?" አላት።
[2]ሴቲቱም እባቡን እንዲህ አለችው፤ "በአ
ትክልቱ ስፍራ ካሉት ዛፎች ፍሬ መብላት
እንችላለን፤ [3]ነገር ግን እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
'በአትክልቱ ስፍራ መካከል ከሚገኘው ዛፍ
ፍሬ እንዳትበሉ፤ እንዳትነኩትም፤ አለበለዚያ
ትሞታላችሁ' ብሎአል።"
[4]እባቡም ሴቲቱን እንዲህ አላት፤ "መሞት
እንኳ አትሞቱም፤ [5]ከፍሬው በበላችሁ ጊዜ ዐይ
ናችሁ እንደሚከፈትና መልካምና ክፉን በማ
ወቅ፣ እንደ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) እንደምትሆኑ
እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ስለሚያውቅ ነው።"
[6]ሴቲቱ የዛፉ ፍሬ ለመብል መልካም፣
ለዐይን የሚያስደስትና ጥበብንም ለማግኘት
የሚያጓጓ እንደ ሆነ ባየች ጊዜ፣ ከፍሬው
ወስዳ በላች፤ ከእርሷም ጋር ለነበረው ለባሏ
ሰጠችው፤ እርሱም በላ። [7]የሁለቱም ዐይኖች
ተከፈቱ፤ ዕራቍታቸውን መሆናቸውንም ተገ
ነዘቡ። ስለዚህ የበለስ ቅጠል ሰፍተው አገ
ለደሙ።

2፥24 ሚል2፥15፤ማቴ19፥5፤ማር10፥7-8፤1ቆሮ6፥16፤ኤፌ5፥31
2፥25 ዘፍ3፥7:10-11፤ኢሳ47፥3፤ሰቆ1፥8
3፥1 ዘፍ2፥17፤ኢዮ1፥7፤2፥2፤2ቆሮ11፥3፤ራእ12፥9፤20፥2
3፥2 ዘፍ2፥16
3፥3 ዘፍ2፥17
3፥4 ዮሐ8፥44፤2ቆሮ11፥3
3፥5 ዘፍ1፥26፤14፥18:19፤መዝ7፥8፤ኢሳ14፥14፤ሕዝ28፥2
3፥6 ዘኍ30፥7-8፤ኤር44፥15:19:24፤2ቆሮ11፥3፤1ጢሞ2፥14፤1ዮሐ2፥16፤ያዕ1፥14-15
3፥7 ቍ21፤ዘፍ 2፥25
3፥8 ዘሌ26፥12፤ዘዳ23፥14፤ኢዮ13፥16፤23፥7፤31፥33፤34፥22:23፤መዝ5፥5፤139፥7-12፤ኢሳ29፥15፤ኤር16፥17፤23፥24፤49፥10፤ራእ6፥15-16፤ዘፀ19፥16፤20፥18፤ዘዳ5፥5፤1ሳሙ12፥18
3፥9 ዘፍ4፥9፤16፥8፤18፥9፤1ነገ19፥9:13
3፥10 ዘፍ2፥25፤ሚክ7፥17
3፥11 ዘፍ2፥17:25
3፥12 ዘፍ2፥22
3፥13 ሮሜ7፥11፤2ቆሮ11፥3፤1ጢሞ2፥14
3፥14 ዘዳ28፥15-20፤መዝ72፥9፤ኢሳ49፥23፤65፥25

[8]ቀኑ መሸትሸት ሲል፣ *እግዚአብሔር* ስም
ባክ (ያህዌ ኤሎሂም) በአትክልቱ ስፍራ ሲመላለስ
አዳምና ሔዋን ድምፁን ሰምተው *ከእግዚአ
ብሔር* ስምባክ (ያህዌ ኤሎሂም) ፊት በዛፎቹ መካ
ከል ተሸሸጉ። [9]*እግዚአብሔር* ስምባክ (ያህዌ ኤሎሂም)
ግን አዳምን ተጣርቶ፣ "የት ነህ?" አለው።
[10]አዳምም፣ "ድምፅህን በአትክልቱ ስፍራ
ሰማሁ፤ ዕራቍቴን ስለ ሆንሁ ፈራሁ፤ ተሸሸ
ግሁም" ብሎ መለሰ።
[11]*እግዚአብሔርም* (ያህዌ)፣ "ዕራቍትህን መሆ
ንህን ማን ነገረህ? 'ከእርሱ እንዳትበላ' ብዬ
ካዘዝሁህ ዛፍ በላህን?" አለው።
[12]አዳምም፣ "ይህች ከእኔ ጋር እንድት
ኖር የሰጠኸኝ ሴት፣ እርሷ ከዛፉ ፍሬ ሰጠ
ችኝና በላሁ" አለ።
[13]*እግዚአብሔር* ስምባክ (ያህዌ ኤሎሂም) ሴቲቱን፣
"ይህ ያደረግሽው ምንድን ነው?" አላት።
እርሷም፣ "እባብ አሳሳተኝና በላሁ" አለች።
[14]*እግዚአብሔር* ስምባክ (ያህዌ ኤሎሂም) እባብን
እንዲህ አለው፤ "ይህን ስለ ሠራህ፣

"ከከብቶችና ከዱር እንስሳት ሁሉ
ተለይተህ የተረገምህ ሁን፤
በሕይወትህ ዘመን ሁሉ፣ በደረትህ
እየተሳብህ ትሄዳለህ፤
ዐፈርም ትበላለህ።

[15]በአንተና በሴቲቱ፣
በዘርህና በዘሯ መካከል፣
ጠላትነትን አደርጋለሁ፤

3፥15 ዘፍ16፥11፤መሳ13፥5፤ኢሳ7፥14፤8፥3፤9፥6፤ማቴ1፥23፤ሉቃ1፥31፤ዮሐ8፥44፤ሐሥ13፥10፤ሮሜ16፥20፤ገላ4፥4፤ዕብ2፥14፤1ዮሐ3፥8፤ራእ12፥17

---

2፥24 *ከአባቱና ከእናቱ ተለይቶ፤* ወንድ፣ ከወላጆቹ ጥገኝነት በመላቀቅ ከሚስቱ ጋር ሆኖ አንድ አዲስ ቤተ ሰብ ይመሠርታል። *ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፤* አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ፣ አንድ ወንድም ለአንዲት ሴት እንዲሆን ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ብቻ እንዲመሠረት አምላካዊ ዕቅድ ነው። እነርሱም በአንድነት ሆነው የማይለያይ ኅብረት ይመሠርታሉ፤ "አንድ ሥጋ" የሚለውም ለዚህ ኅብረት ምልክትም መግለጫም ነው።

2፥25 *ዕራቍታቸውን... አይተፋፈሩም፤* ከመተፋፈር ነጻ መሆን የንጹሕነት ምልክት ነው፤ ሆኖም ይህ ነጻነት በኀጢአት ምክንያት ተወሰደባቸው (3፥7 ይመ)።

3፥1 *እባብ፤ ታላቁ አታላይ (ዋሾ)፣* እግዚአብሔር ከፈጠራቸው መልካም ፍጡራን መካከል አንዱ በሆነው በእባብ ራሱን መስሎ አቀረበ። እርሱም ሐሰትን እውነት አስመስሎ ክፉ ሥራን እንደ በጎ ሥራ ለማቅረብ ሞከረ፤ ይህ ሁሉ ፋሜ የራሱን ሐሳብ ለማሳካት ነበር። ስለዚህም "ዲያብሎስ" ወይም "ሰይጣን" በስተ ኋላ ላይ፣ "የጥንቱ እባብ" የሚል ስም ተሰጥቶት እናገኘዋለን (ራእ 12፥9፤ 20፥2)። *ተንኰለኛ፤* "ተንኰለኛ" እና "ዕራቍታቸውን" ለሚሉት ቃላት የገቡት የዕብራይስጥ ቃላት ተመሳሳይ ናቸው። አዳምና ሔዋን ዕራቁታቸውን ሆነው አይተፋፈሩም ነበር (2፥25)፤ በእባብ ተንኰል ተመርተው ኀጢአት ከሠሩ በኋላ ግን በዕራቁትነታቸው ማፈር ጀመሩ (ቍ 7)። *በእርግጥ እግዚአብሔር... ብሎአልን?* የሰው ልጅ ታሪክ የተለወጠው በዚህ ጥያቄና ለጥያቄው በተሰጠው መልስ ነው። ሴቲቱ የእግዚአብሔርን ቃል እንድትጠራጠር በማድረግ፣ ሰይጣን ክፋትን ወደ ዓለም አመጣ። እዚህ ላይ አሳቹ፣ ሰው ከእግዚአብሔር እንዲለይ አደረገ። በኢዮ 1-2 ላይ እንደተመለከተው ደግሞ ከሳሽ ሆኖ በመቅረብ እግዚአብሔርን ከሰው ለመለያየት ጕድጓድ ሲምስ ይታያል (እንዲሁም ዘካ 3፥1 ይመ)።

3፥3 *እንዳትነኩትም፤* ሴቲቱ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ጨመረች፤ መመሪያውንም አጣመመች። በዚህም፣ እባቡ ተንኰል የተሞላበትን መርዝ እንዲረጭ መንገድ ከፈተችለት።

3፥4 *መሞት እንኳ አትሞቱም፤* እግዚአብሔር በግልጽ የተናገረውን ትእዛዝ/ ቃል ፊት ለፊት የሚቃረንና ድፍረት የተሞላበት አነጋገር ነው (2፥17)።

*3፥5 ዐይናችሁ እንደሚከፈትና... እንደ እግዚአብሔር፤* ይህ አባባል በከፊል እውነትነት አለው፤ በእርግጥ ዐይናቸው ተከፍቶ አል (ቍ 7 ይመ)፤ ነገር ግን ውጤቱ እባቡ ካለው ጋር ፈጽሞ አይገናኝም። *መልካምና ክፉን በማወቅ፤* የ2፥9 ማብ ይመ። *እግዚአብሔር... ስለሚያውቅ፤* እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው ልብ ወይም ሐሳብ በጎ እንዳልሆነ አድርጎ በማቅረብ ሰይጣን እግዚአብሔርን ይከሳል። እንደዚሁም በኢዮ 1፥9-11፤ 2፥4-5 ላይ ጻድቁን ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ከሶታል።

3፥6 *ለመብል መልካም፣ ለዐይን የሚያስደስትና ጥበብንም ለማግኘት የሚያጓጓ፤* ሦስት የፈተና ሁኔታዎችን ያመለክታሉ (ከ1ዮሐ 2፥16፤ ሉቃ 4፥3:5:9 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥7 *ዕራቁታቸውን መሆናቸውንም ተገነዘቡ፤* እንደ ሕጻናት ንጹሐን መሆናቸው ከቀረ በኋላ፣ ስለ ራሳቸውና ስለ እርስ በእርሳቸው፣ አዲስ "ዕውቀትና ማስተዋል" አገኙ። *አገለደሙ፤* አዳምና ሔዋን፣ ኀፍረተ ሥጋቸውን ለመሸፈን ያደረጉት ጥረት ደካማና የማይረባ ነበር፤ ምክንያቱም የሰውን አሳፋሪ ነገር የሚሸፍን እግዚአብሔር ብቻ ነው (የቍ 21 ማብ ይመ)።

3፥8 *በአትክልቱ ስፍራ፤* በአንድ ወቅት ይህ ስፍራ የደስታና ከእግዚአብሔርም ጋር ኅብረት የማድረጊያ ስፍራ ነበር፤ በኋላ ግን የፍርሃትና ከእግዚአብሔር የመደበቂያ ስፍራ ሆነ።

3፥9 *የት ነህ?* መልስ አዘል ጥያቄ ነው (4፥9)።

3፥12 *ከእኔ ጋር እንድትኖር የሰጠኸኝ ሴት... ሰጠችኝ፤* አዳም ራሱን ነጻ በማድረግ እግዚአብሔርንና ሔዋንን ወነጀለ።

3፥13 *እባብ አሳሳተኝ፤* ሔዋን ራሷን ከመወንጀል ይልቅ እባብን ወነጀለች።

3፥14 *የተረገምህ* እባብ፣ አዳምና ሔዋን በፈጸሙት በደል ሁሉም ተፈረደባቸው፤ ነገር ግን ርግማኑ ለእባብና ለምድር ብቻ ነው። ምድር የተረገመችው በአዳም ምክንያት ነው (ቍ 17)። *ዐፈር፤* የሞት ምሳሌና (ቍ 17) የእባብ ምግብ ነው።

እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣[ኀ]
አንተም ተረከዙን ትቀጠቅጣለህ።”
16ሴቲቱንም እንዲህ አላት፤
“በምጥ ጊዜ ጭንቅሽን አበዛለሁ፤
በሥቃይም ትወልጃለሽ፤
ፍላጐትሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፤
እርሱም የበላይሽ ይሆናል።
17አዳምንም እንዲህ አለው፤ “የሚስትህን
ቃል ሰምተህ፣ ‘ከእርሱ አትብላ’ ብዬ ያዘ
ዝሁህን ዛፍ በልተሃልና፣
“ከአንተ የተነሣ ምድር የተረገመች ትሁን፤
በሕይወትህ ዘመን ሁሉ
ምግብህን ጥረህ ግረህ ከእርሷ ታገኛለህ።
18ምድርም እሾኽና አሜከላ
ታበቅልብሃለች፤
ከቡቃያዋም ትበላለህ።
19ከምድር ስለ ተገኘህ፣
ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ
ድረስ
እንጀራህን በፊትህ ላብ ትበላለህ፤
ዐፈር ነህና
ወደ ዐፈር ትመለሳለህ።”
20አዳምም[ነ] የሕያዋን ሁሉ እናት ናትና
ሚስቱን ሔዋን[ኘ] ብሎ ጠራት። 21እግዚአብ
ሔር ስምባክ (ያህዌ ኤሎሂም) ከቍዳ ልብስ አዘጋ
ጅቶ አዳምንና ሚስቱን አለበሳቸው። 22ከዚ
ያም እግዚአብሔር ስምባክ (ያህዌ ኤሎሂም)፣ “ሰው
መልካምንና ክፉውን ለይቶ በማወቅ ረገድ
አሁን ከእኛ እንደ አንዱ ሆኗል፤ አሁን
ደግሞ እጁን ዘርግቶ ከሕይወት ዛፍ ቀጥፎ
እንዳይበላ፣ ለዘላለምም እንዳይኖር ይከልከል”
አለ። 23ስለዚህ የተገኘበትን ምድር እንዲያ
ርስ፣ እግዚአብሔር ስምባክ (ያህዌ ኤሎሂም) ሰውን
ከዔድን የአትክልት ስፍራ አስወጣው፤ 24ሰው
ንም ካስወጣው በኋላ፣ ወደ ሕይወት ዛፍ
የሚወስደውን መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤል
ንና በየአቅጣጫው የምትገለባበጥ ነበልባላዊ
ሠይፍ ከዔድን በስተ ምሥራቅ አኖረ።[አ]

## ቃየንና አቤል

4 አዳም ሚስቱን ሔዋንን ተገናኛት፤ እር
ሷም ፀንሳ ቃየንን[ከ] ወለደች፤ “በእግዚአ
ብሔር (ያህዌ) ርዳታ ወንድ ልጅ አገኘሁ” አለች።
2ደግሞም ወንድሙን አቤልን ወለደች።
አቤል የበግ እረኛ፣ ቃየንም ዐራሽ ነበር።
3በአንድ ወቅት፣ ቃየን ከምድር ፍሬ ለእግ
ዚአብሔር (ያህዌ) መሥዋዕት አቀረበ። 4አቤ
ልም መጀመሪያ ከተወለዱት በጎች መካከል
ስባቸውን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። እግዚ
አብሔር (ያህዌ) ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ

3፥16 መዝ48፥5-6፤ ኢሳ13፥8፤21፥3፤26፥17፤ኤር4፥31፤6፥24፤ሚክ4፥9፤1ቆሮ11፥3፤ኤፌ5፥22፤1ጢሞ 2፥15
3፥17 ዘፍ2፥17፤5፥29፤6፥13፤8፥21፤29፥32፤31፥42፤47፥9፤ዘፀ3፥7፤ዘኍ35፥33፤ኢዮ5፥7፤7፥1፤14፥1፤መዝ66፥11፤106፥39፤127፥2፤መክ1፥13፤2፥23፤ኢሳ24፥5፤54፥9፤ኤር3፥1፤20፥18፤ሮሜ 8፥20-22
3፥18 ኢዮ31፥40፤መዝ104፥14፤ኢሳ5፥6፤ዕብ 6፥8
3፥19 ዘፍ2፥7፤14፥18፤ዘዳ8፥3፡9፤23፥4፤ሩት1፥6፤2፥14፤ኢዮ 7፥21፤መዝ104፥23፤146፥4፤1ቆሮ15፥47፤2ተሰ3፥10፤ዕብ9፥27
3፥20 ዘፍ2፥20፤2ቆሮ11፥3፤1ጢሞ 2፥13
3፥21 ቍ7
3፥22 ዘፍ1፥26፤2፥9፤ራእ2፥7
3፥23 ዘፍ2፥7፡8
3፥24 ዘፍ2፥8፡9፤ዘፀ25፥18-22፤1ሳሙ 4፥4፤2ሳሙ6፥2፤22፥11፤1ነገ6፥27፤8፥6፤2ነገ19፥15፤2ዜና5፥8፤ኢዮ40፥19፤መዝ18፥10፤80፥1፤99፥1፤104፥4፤ኢሳ27፥1፤37፥16፤ሕዝ10፥1፤28፥16

4፥1 ቍ17፡25፤ዘፍ2፥20፤ዕብ11፥4፤1ዮሐ3፥12፤ይሁ1፥11 4፥2 ዘፍ2፥7፤ማቴ23፥35፤ሉቃ11፥51፤ዕብ11፥4፤12፥24 4፥3 ዘኍ18፥12፤ዘሌ2፥1-2፤ኢሳ43፥23፤ኤር41፥5 4፥4 ዘፀ13፥2፡12፤ዘዳ15፥19፤ዘሌ3፥16፤2ዜና29፥35፤ዕብ11፥4

[ኀ]15 ወይም *ይመታል*
[ነ]20 ወይም *ሰውየው*፤ በ4፥1ም እንዲሁ
[ኘ]20 *ሔዋን* ማለት *ሕያው* ማለት ሳይሆን አይቀርም
[አ]24 ወይም *ፊት ለፊት አስቀመጠ*
[ከ]1 *ቃየን* የሚለው ስም *ማምጣት* ወይም *ማግኘት* የሚል ትር ጕም ካላቸው የዕብራይስጥ ቃላት ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው

3፥15 *እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ተረከዙን ትቀጠቅጣለህ*፤ በሰውና በእባብ መካከል ያለው ጠላትነት፣ በእግ ዚአብሔርና በሰይጣን መካከል ያለውን ታላቅ ፍልሚያ የሚመስል ነው፤ ይህም ፍልሚያ በሰው ልብና በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በተግባር እየታየ ያለ ነው። “የሴቲቱ ዘር የእባቡን ራስ ይቀጠቅ ጣል” የሚለው ቃል፣ በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ ሰይጣንን ድል በነሣ ጊዜ የተፈጸመ ነው፤ ይህም አማኞች ሁሉ የሚሳተፉበት ድል ነው (ሮሜ 16፥20)።

3፥16 *በምጥ ጊዜ ጭንቅሽ*፤ ፍርዱ ያረፈው የእርሷ ልዩ ባሕርይ በሆነው ማንነቷ ማለትም በሴትነቷና፣ በተስማሚ ረዳት ነቷ (2፥20) ላይ ነው። እንደዚሁም አዳም ምድር በቂ ምግብ እን ድትሰጠው “ጥሮ ግሮ” (ቍ 17) እንዲበላ ተፈረደበት። “ሕመም”፣ “ሥቃይ” እና “ጥረህ ግረህ” ለሚሉት ቃላት የገቡት የዕብራይ ስጥ ቃላት ተግቶ ከመሥራትና በሥራም ብዛት ከመድከም ጋር የተዛመደ ፍቺ እንዳላቸው የሚናገሩ ሰዎች አሉ (ምሳ 5፥10 ላይ “ልፋትህን”፣ 14፥23 ላይ ደግሞ “ለፍተው የሠሩት” የሚለውን ይመ)። *ትወልጃለሽ*፤ በፍርድ መካከል የተሰጠው ይህ ጸጋ፣ የሰው ዘር ቀጣይነት እንዳለው የሚያመለክት ነው። *ፍላጎትሽም... የበ ላይሽ*፤ ለባሏ ያላት ወሲባዊ ፍላጎትና ባሏም የእርሷ የበላይ (ራስ) መሆኑ፣ ያልተበረዘ ደስታንና በረከትን የምታገኝበት ሳይሆን፣ የምትቸገርበትና የምትጨነቅበት ነው።

3፥17-19 *ጥረህ ግረህ ከእርሷ ታገኛለህ*፤ ምንም እንኳን ጥሮ ግሮ እንዲበላ ቢደረግም (የፍርድ ምልክት ነው)፣ ሕይወቱን ለማኖር የሚያስችለውን ምግብ ሠርቶ ሊያገኝ ይችላል (የጸጋ ምሳሌ ነው)።

3፥19 *ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ... ዐፈር ነህና ወደ ዐፈር ትመለሳለህ*፤ ሰው በጥረቱ ሞትን ሊያስቀር አይችልም፤ የአካሉ አፈጣጠር (2፥7) እና የምግቡ ምንጭ (ቍ 17) አንድ ቀን ሟች መሆኑን የሚያመለክት ተምሳሌት ነው።

3፥21 *አለበሳቸው*፤ እግዚአብሔር ከጸጋው የተነሣ ለአዳ ምና ለሔዋን የተሻለ ልብስ ያማልበስ ኀፍረታቸውን እንዲሸፍኑ አደረገ (ከቍ 7 እና 10 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥22 *መልካምንና ክፉውን... በማወቅ*፤ የሰይጣን ትንቢት (ቍ 5) እጅግ በተጣመመ መንገድ እውን ሆነ። *ከእኛ*፤ የ1፥26 ማብ ይመ። *ለዘላለም እንዳይኖር*፤ ኀጢአት ምን ጊዜም ሞትን ያስከትላል (ሮሜ 6፥23፤ ያዕ 1፥14-15)፤ ኃጥእንንም የእግዚ አብሔር ስጦታ ከሆነው ከዘላለማዊ ሕይወት ያግደዋል።

3፥23 *እንዲያርስ... ከዔደን የአትክልት ስፍራ አስወጣው*፤ ሰው በኀጢአት ከመውደቁ በፊት ደስ በምታሰኝና ውብ በሆነች የአትክልት ስፍራ ውስጥ ይሠራ ነበር (2፥15)፤ አሁን ደግሞ እሾ ኽና አሜከላ እንድታበቅል በተረገመች፣ ለሥራም ምቹ ባልሆነች መሬት ላይ መሥራት ግድ ሆነበት (ቍ 18)።

3፥24 *ለመጠበቅ*፤ የእግዚአብሔር የፍርድ ሰይፍ በኀጢአት በወደቀው ሰውና በእግዚአብሔር ገነት መካከል ቆመ፤ ምክንያቱ በቍጥር 22 ላይ ተገልጾአል። ሰው ተመልሶ ወደ ሕይወት ዛፍ መድረስ የሚችለው፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ባዘጋጀው ቤዛነት ብቻ ነው (ራእ 2፥7፤ 22፥2፡14፡19 ይመ)። *ኪሩቤል*፤ በጥንት መስጴጦምያ በቤተ መንግሥትና በቤተ መቅ ደስ መግቢያ በር ላይ ዘብ (ለጥበቃ) ከሚቆሙ ክንፍና የሰው ራስ ካላቸው የበሬና የአንበሳ ሐውልቶች ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው (የዘፀ 25፥18 ማብ ይመ)።

4፥1 *በእግዚአብሔር ርዳታ*፤ የሕይወት ሁሉ ምንጭ እግዚ አብሔር መሆኑን ሔዋን መስከረች (ሐሥ 17፥25 ይመ)።

4፥2 *አቤል*፤ የስሙ ትርጕም፣ “እስትንፋስ” ወይም፣ “ጊዜ ያዊ” ወይም፣ “ከንቱ” ማለት ሲሆን (በመክ 1፥2፤ 12፥8 ላይ ያሉት የዕብራይስጥ ቃላት የተተረጐሙት ከዚህ ቃል ነው)፣ ይህም የአቤል ሕይወት በአጭር መቀጨቱን የሚያመለክት ነው።

4፥3-4 *ቃየን ከምድር ፍሬ... አቀረበ፤ አቤልም መጀመ ሪያ ከተወለዱት በጎች መካከል... አቀረበ*፤ ንጽጽሩ ባለማስተዋ ልና በግድ የለሽነት በቀረበው መሥዋዕትና በፍላጎትና በለጋስነት በቀረበው መሥዋዕት መካከል የተደረገ እንጂ፣ በዕፀዋት መሥ ዋዕትና በእንስሳት መሥዋዕት መካከል የተደረገ ንጽጽር አይደ ለም (ከዘሌ 3፥16 ጋር ያነጻጽሩ)። የመንፈስ መነሣሣትና የልብ ዝንባሌ ወሳኝነት አለው፤ እግዚአብሔር አቤልንና መሥዋዕቱን እንዲወድና እንዲመለከተው ያደረገው አቤል ያሳየው እምነት ነው (ዕብ 11፥4)። *መጀመሪያ ከተወለዱት*፤ የበግም ሆነ የፍየል መንጋ፣ እርባታውና ውጤቱ ከእግዚአብሔርና የእግዚአብሔር መሆኑን የሚያመለክት ነው።

ተመለከተ፤ 5በቃየንና በመሥዋዕቱ ግን አል
ተደሰተም፤ ስለዚህ ቃየን ክፉኛ ተናደደ፤ ፊቱም
ጠቈረ።
6*እግዚአብሔር* ስምዓከም (ያህዌ ኤሎሂም) ቃየንን
እንዲህ አለው፤ "ለምን ተናደድህ? ለምንስ
ፊትህ ጠቈረ? 7መልካም ብታደርግ ተቀባይ
ነትን አታገኝምን? መልካም ባታደርግ ግን፣
ኀጢአት በደጅህ እያደባች ናት፤ ልታሸን
ፍህ ትፈልጋለች፤ አንተ ግን ተቈጣጠራት።"
8ቃየንም ወንድሙን አቤልን፣ "እስቲ ና፤
ወደ መስኩ እንውጣ"[ሸ] አለው፤ በመስኩም
ሳሉ፣ ቃየን ወንድሙን አቤልን አጠቃው፤
ገደለውም።
9ከዚያም፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ቃየንን፣
"ወንድምህ አቤል የት ነው?" አለው።
ቃየንም፣ "አላውቅም፤ እኔ የወንድሜ ጠባቂ
ነኝን?" ሲል መለሰ።
10*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) እንዲህ አለ፤ "ምን
ድነው ያደረግኸው? ስማ! የወንድምህ ደም
ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል። 11እንግዲህ
የተረገምህ ነህ፤ የወንድምህን ደም ከእጅህ
ለመቀበል አፏን ከከፈተችው መሬት ትስ
ደዳለህ። 12ብታርሳትም ፍሬዋን አትለግስህም፤
በምድር ላይ ኰብላይና ተንከራታች ትሆና
ለህ።"
13ቃየንም *እግዚአብሔርን* (ያህዌ) እንዲህ
አለው፤ "ቅጣቴ ልሸከመው ከምችለው በላይ
ነው። 14እነሆ፤ ዛሬ ከምድሪቱ አባረርኸኝ፤
ከፊትህም እሸሸጋለሁ፤ በምድር ላይ ኰብላ
ይና ተንከራታች እሆናለሁ፤ የሚያገኘኝም
ሁሉ ይገድለኛል።"
15*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ግን፣ "የለም! እንደ
ርሱ አይሆንም፤[ፀ] ማንም ቃየንን ቢገድል፣
ሰባት ዕጥፍ የበቀል ቅጣት ይቀበላል" አለው፤
ስለዚህ፣ ያገኘው ሁሉ እንዳይገድለው *እግዚ
አብሔር* (ያህዌ) በቃየን ላይ ምልክት አደረ
ገለት። 16ቃየንም *ከእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
ወጥቶ ሄደ፣ ከዔድን በስተ ምሥራቅ በም
ትገኝ ኖድ[ዐ] በተባለች ምድር ተቀመጠ።
17ቃየን ሚስቱን ተገናኛት፤ እርሷም ፀንሳ
ሄኖክን ወለደች። ቃየን የቈረቈረውን ከተማ
በልጁ ስም ሄኖክ ብሎ ጠራው። 18ሄኖክ ኢራ
ድን ወለደ፤ ኢራድም መሑያኤልን፣ መሑ
ያኤልም ማቱሣኤልን፣ ማቱሣኤልም ላሜሕን
ወለደ።
19ላሜሕ ሁለት ሚስቶች አገባ፤ የአንደ
ኛዋ ስም ዓዳ፣ የሁለተኛዋም ጺላ ነበር።

4፥6 የና4፥4
4፥7 ዘፍ44፥16፤ዘኁ32፥23፤ኢሳ59፥12፤ኢዮ11፥15፤22፥27፤መዝ27፥3፤46፥21 ሮሜ6፥16
4፥8 ማቴ23፥35፤ሉቃ11፥51፤1ዮሐ3፥12፤ይሁ1፥11
4፥9 ዘፍ3፥9፤ዮሐ8፥44
4፥10 ዘፍ9፥5፤37፥20:26፤ዘፀ21፥12፤ዘኁ35፥33፤ዘዳ21፥7:9፤2ሳሙ4፥11፤ኢዮ16፥18፤24፥2፤31፥38፤መዝ9፥12፤106፥38፤ዕብ12፥24፤ራእ6፥9-10
4፥11 ዘዳ11፥28፤2ነገ2፥24
4፥12 ቍ14፤ዘዳ28፥15-24፤መዝ37፥25፤59፥15፤ 109፥10
4፥14ቍ12፤ዘፍ9፥6፤ዘፀ21፥12:14፤ዘሌ24፥17፤ዘኍ35፥19:21:27:33፤ዘዳ28፥64-67፤ዘዳ28፥64-7፤1ነገ2፥32፤2ነገ11፥16፤17፥18፤መዝ51፥11፤139፥7-12፤ኤር7፥15፤52፥3
4፥15 ቍ24፤ዘፀ21፥20፤ዘሌ26፥21መዝ79፥12፤ሕዝ9፥4:6፤
4፥16 ዘፍ2፥8፤ይሁ1፥11
4፥17 ቍ1፤መዝ55፥9፤49፥11 4፥19 ዘፍ6፥2፤29፥28፤ዘዳ21፥15፤ሩት4፥11፤1ሳሙ1፥2

ሸ8 *እስቲ ና፣ ወደ መስኩ እንውጣ* የሚለው ሐረግ በአራት ሳምራውያን፣ በሰብዓ ሊቃናት፣ በቩልጌትና፣ በሱርስት የሚገኝ ሲሆን በማሶሬቲክ ጽሑፍ ውስጥ ግን የለም
ፀ15 ዕብራይስጡ ከሰብዓ ሊቃናት፣ ከቩልጌትና ከሱርስቱ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *መልካም!* ይለዋል
ዐ16 ኖድ ማለት መቅበዝበዝ ማለት ነው (ቍ12 እና 14 ይመ)

4፥5 *ተናደደ፤* እግዚአብሔር በቃየንና በመሥዋዕቱ አልተደሰተም፤ ቃየን ለዚህ የሰጠው ምላሽ የሚጠበቅ ነበር፤ ምክንያቱም ገና ከመጀመሪያው አስተሳሰቡ የተበላሸ ነበረ።

4፥7 *ኀጢአት... እያደባች ናት፤* "እያደባች" ተብሎ የተተረጐመው የዕብራይስጥ ቃል፣ በጥንት ጊዜ የነበሩ ባቢሎናውያን በቤት ውስጥ ያሉ ሰዎችን ለማስጨነቅ ከቤት ውጭ የሚያደቡ ርኩሳን መናፍስትን ለመግለጽ ከሚጠቀሙበት ቃል ጋር የሚመሳሰል ነው። ይህ ኀጢአትም በቃየን ላይ ሊሰለጥን ፈልጐ፣ እንደዚያ ርኩስ መንፈስ የሚያደባበት መሆኑን የሚገልጽ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። ቃየን ወንድሙን ለመግደል ቀደም ብሎ ሳያስብበት አልቀረም። *ልታሸንፍህ ትፈልጋለች፤* ይህ ሐረግ በዕብራይስጡ "ፍላጐትሽም ወደ ባልሽ ይሆናል" (3፥16) ለሚለው ሐረግ ከገባው ጋር ተመሳሳይነት አለው (ማሕ 7፥10 ይመ)።

4፥8 *ወንድሙን አቤልን አጠቃው፤ ገደለውም፤* ይህ የመጀመሪያው የነፍስ ግድያ፣ "እስቲ ና፤ ወደ መስኩ እንውጣ" በማለት ዐይን ባወጣ ማታለል፣ በወንድም ላይና (ቍ 9-11፤ 1ዮሐ 3፥12 ይመ) በጻድቅ ሰው ላይ (ማቴ 23፥35፤ ዕብ 11፥4) የተፈጸመ አረመኔያዊ ድርጊት ነው። ይህም በኀጢአት መውደቅ ያስከተለውን አስፈሪ ገጽታ የሚገልጽ ነው።

4፥9 *የት ነው?፤* መልስ አዘል ጥያቄ ነው (3፥9 ይመ)። *አላውቅም፤* ዐይን ያወጣ ውሸት ነው። *እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን?* ከጭካኔ የመነጨ የግድየለሽነት አባባል ነው። ይህም በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ሁሉ የሚታይ ነው።

4፥10 *የወንድምህ ደም... ወደ እኔ ይጮኻል፤* በአንድ በኩል አቤል ነቢይ ነው (ሉቃ 11፥50-51)፤ "ቢሞትም እንኳ እስከ አሁን በእምነቱ ይናገራል" (ዕብ 11፥4)፤ ምክንያቱም የፈሰሰው ደሙ፣ በወንድሞቻቸው ላይ ክፉን በሚያደርጉ ሰዎች ምክንያት ወደ እግዚአብሔር ከመጮኽ አላቋረጠም። የክርስቶስ ደም ግን የተሻለውን ቃል ይናገራል (ዕብ 12፥24)።

4፥11 *የተረገምህ፤* ከሰው ኀጢአት የተነሣ ምድር ተረገመች (3፥17)፤ አሁን ደግሞ ቃየን ራሱ ተረገመ። እርሱም ቀደም ሲል ምድርን ያርስ ነበረ፤ ምድርም ፍሬ ትሰጠው ነበር (ቍ 2-3)። የወንድሙ የአቤል ደም የፈሰሰባት ምድር ከእንግዲህ ምንም ፍሬ አትሰጠውም (ቍ 12)፤ ይህም የሞት ተምሳሌት ነው።

4፥12 *ኰብላይ፤* ከወገኖቹ ተለይቶ ማረፊያ ቦታ በማጣት በምድር ላይ ተቅበዝባዥ ሆኖ እንደ ቀረ የሚያመለክት ነው።

4፥13 *ቅጣቴ ልሸከመው ከምችለው በላይ ነው፤* ከፈጸመው በደል የተነሣ በደረሰበት ርግማን ቃየን ለራሱ አዘነ እንጂ አልተጸጸተም። እንዲያውም በኀጢአት ላይ ኀጢአትን ይፈጽም ጀመር፤ እግዚአብሔርን ናቀ (ቍ 3)፤ ተበሳጨ (ቍ 5)፤ ቀናተኛ፣ አታላይና፣ ነፍስ ገዳይ ሆነ (ቍ 8)፤ ዋሾና (ቍ 9) ራስ ወዳድም ሆነ (ቍ 13)። የዚህ ሁሉ ውጤት ከእግዚአብሔር እንዲለይ አደረገው (ቍ 14:16)

4፥14-15 *የሚያገኘኝም ሁሉ... ማንም... ያገኘው ሁሉ፤* እነዚህ ቃላት ከቃየን ቤተ ሰብ በተጨማሪ ሌሎች በርካታ ሰዎች በምድር መኖራቸውን የሚያመለክቱ ይመስላል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ምናልባት ወደ ፊት በፍጥነት ሊያድግ የሚችለውን የሰው ዘር ሳያሳይ አይቀርም።

4፥15 *ምልክት፤* እርሱን ለመበቀል ከሚሹ ሰዎች ለመታደግ የተቀመጠ የማስጠንቀቂያ ምልክት ነው። ለጊዜውም ቢሆን የነፍስ ገዳዩ ሕይወት ከሞት እንዲተርፍ ተደርጓል (6፥7፤ 9፥6 ይመ፤ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነውን ሕዝ 9፥4 ይመ)።

4፥16 *ኖድ፤* የት እንደሆነ በትክክል አይታወቅም።

4፥17-18 *ቃየን... ሄኖክ፣ ኢራድ... መሑያኤል... ማቱሳኤል... ላሜሕ፤* አዳምን ጨምሮ እነዚህ ስሞች ሰባት ናቸው፤ ሰባት ቍጥር ደግሞ በአብዛኛው ሙሉነትን ወይም ፍጹምነትን ይወክላል (ቍ 15 ይመ)። በዚህ ቦታ የተዘረዘሩት ስድስቱ ስሞች እያንዳንዳቸው ከታች በም 5 ከተመለከተው የሴት የዘር ሐረግ ጋር ተጓዳኝነትና ተመሳሳይነት አላቸው። እነዚህም፦ ቃይናን (5፥12)፣ ሄኖክ (5፥21)፣ ያሬድ (5፥18)፣ መላልኤል (5፥15)፣ ማቱሳላ (5፥25)፣ ላሜሕ (5፥28) ናቸው። በእነዚህ የስም ስብስቦች መካከል ያለው ተመሳሳይነት አስደናቂ ከመሆኑም በላይ፣ ምርጥ የዘር ሐረግ መሆናቸውን ሳያመለክት አይቀርም (የ5፥5 ማብ ይመ)፤ እንዲሁም በ1ኛ ዜና መግቢያ ላይ "የዘር ሐረግ" የሚለውን ይመ)።

4፥17 *ከተማ፤* ቃሉ በዕብራይስጥ በቋሚ መኖሪያነት የሚያገለግለውን ማንኛውንም አነስተኛ ሰፈር ሊያመለክት ይችላል፤ ቃየን በገዛ እጁ ሠርቶ በመብላት ከተቅበዝባዥ ኑሮው ራሱን ለመታደግ ቻለ፤ ተንከራታች ሆኖ በሚኖርበትም ምድር ከተማን መሠረተ።

4፥19 *ሁለት ሚስቶች አገባ፤* በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ብዙ ሚስቶችን ማግባት በዚህ ጊዜ ተጀመረ። ሌሎችን መናቅ የሚወደው ላሜሕ፤ በቃየን የትውልድ ሐረግ ከአዳም ጀምሮ ሲቈጠር ሰባተኛ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ቀደም ሲል የሰጠውን በረከት (1፥28 እና ማብ ይመ) ብዙ ሚስቶችን በማግባት በራሱ መንገድ

20ዓዳ ያባልን ወለደች፤ እርሱም በድንኳን
ለሚኖሩ ከብት አርቢዎች አባት ነበረ።
21ወንድሙም ዩባል ይባላል፤ እርሱም በገናና
ደርዳሪዎችና የዋሽንት ነፊዎች አባት ነበረ።
22ሴላም ደግሞ ቱባልቃይን የተባለ ወንድ
ልጅ ወለደች፤ እርሱም ከብረትና ከናስ ልዩ
ልዩ መሣሪያዎችን እየቀረጸ የሚሠራ[ሀ] ነበር።
የቱባልቃይን እኅት ናዕማ ትባል ነበር።
23ላሜሕ ሚስቶቹን እንዲህ አላቸው፤

"ዓዳና ጺላ ሆይ ስሙኝ፤
የላሜሕ ሚስቶች ሆይ አድምጡኝ፤
አንድ ሰው ቢያቈስለኝ፣
ጕልማሳው ቢጐዳኝ፣ ገደልሁት፤[ለ]
24ቃየንን የሚገድል ሰባት ጊዜ ቅጣት ካገኘው፣
የላሜሕ ገዳይማ ሰባ ሰባት ጊዜ ቅጣት
ያገኘዋል።"

25አዳም እንደ ገና ሚስቱን ተገናኛት፤
እርሷም ወንድ ልጅ ወለደች። "ቃየን በገደ
ለው በአቤል ፈንታ እግዚአብሔር (ያህዌ) ምትክ
ሰጠኝ" ስትል ስሙን ሴት[ሐ] ብላ ጠራችው።
26ለሴትም ደግሞ ወንድ ልጅ ተወለደለት፤
ስሙንም ሄኖስ አለው።
በዚያም ዘመን ሰዎች የእግዚአብሔርን
(ያህዌ) ስም መጥራት[መ] ጀመሩ።

## ከአዳም እስከ ኖኅ

5 የአዳም የትውልድ ሐረግ እንደሚከተ
ለው ነው፦
እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰውን ሲፈጥረው በራሱ
አምሳል አበጀው፤ 2ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠ
ራቸው፤ ባረካቸው፤ በተፈጠሩም ጊዜ "ሰው"[ሠ]
ብሎ ጠራቸው።
3አዳም፣ ዕድሜው 130 ዓመት በሆነ ጊዜ፣
እርሱን ራሱን የሚመስል ወንድ ልጅ ወለደ፤
ስሙንም ሴት ብሎ ጠራው። 4ሴት ሄኖ
ስን ከወለደ በኋላ አዳም 800 ዓመት ኖረ፤
ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችንም ወለደ፤
5አዳም በአጠቃላይ 930 ዓመት ከኖረ በኋላ
ሞተ።
6ሴት፣ ዕድሜው 105 ዓመት ሲሆን ሄኖ
ስን ወለደ፤ 7ሴት ሄኖስን ከወለደ በኋላ
807 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች
ልጆችንም ወለደ። 8ሴት በአጠቃላይ 912
ዓመት ከኖረ በኋላ ሞተ።
9ሄኖስ፣ ዕድሜው 90 ዓመት በሆነ ጊዜ
ቃይናንን ወለደ፤ 10ሄኖስ ቃይናንን ከወለደ
በኋላ 815 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና
ሴቶች ልጆችንም ወለደ። 11ሄኖስ በአጠቃ
ላይ 905 ዓመት ከኖረ በኋላ ሞተ።
12ቃይናን፣ ዕድሜው 70 ዓመት ሲሆን
መላልኤልን ወለደ፤ 13ቃይናን መላልኤልን
ከወለደ በኋላ 840 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወን
ዶችና ሴቶች ልጆችንም ወለደ። 14ቃይናን
በአጠቃላይ 910 ዓመት ከኖረ በኋላ ሞተ።
15መላልኤል፣ ዕድሜው 65 ዓመት በሆነ
ጊዜ ያሬድን ወለደ፤ 16መላልኤል ያሬድን
ከወለደ በኋላ 830 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወን
ዶችና ሴቶች ልጆችንም ወለደ። 17መላል
ኤል በአጠቃላይ 895 ዓመት ከኖረ በኋላ
ሞተ።
18ያሬድ፣ ዕድሜው 162 ዓመት ሲሆን
ሄኖክን ወለደ፤ 19ያሬድ ሄኖክን ከወለደ
በኋላ 800 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና
ሴቶች ልጆችንም ወለደ። 20ያሬድ በአጠቃ
ላይ 962 ዓመት ከኖረ በኋላ ሞተ።
21ሄኖክ፣ ዕድሜው 65 ዓመት በሆነ ጊዜ
ማቱሳላን ወለደ፤ 22ሄኖክ ማቱሳላን ከወለደ
በኋላ አካሄዱን ከእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ጋር በማድረግ
300 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች

[ሀ]22 ወይም ለሚሠሩት ሁሉ መመሪያ የሚሠጥ
[ለ]23 ወይም እገድላለሁ
[ሐ]25 ሴት ማለት ሰጠ ሳይሆን አይቀርም
[መ]26 ወይም ማወጅ
[ሠ]2 በዕብራይስጥ አዳም ማለት ነው

4፥21 ዘፍ[illegible]፥27፤ ዘፀ15፥20፤1ሳሙ16፥16፤1ዜና25፥3፤ኢዮ 21፥12፤30፥31፤መዝ 33፥2፤43፥4፤150፥4፤ ኢሳ16፥11፤ዳን3፥5፤
4፥22 ዘፀ35፥35፤ 1ሳሙ13፥19፤2ነገ 24፥14
4፥23 ዘፍ9፥5-6፤ዘፀ 20፥13፤21፥12፤23፥7 ፤ዘሌ19፥18፤24፥17፤ ዘዳ27፥24፤32፥35
4፥24 ቍ15፤ዘዳ32፥ 35፤2ነገ9፥7፤መዝ18፥ 47፤94፥1፤ኢሳ35፥4፤ ኤር51፥56፤ናሆ1፥2፤ ማቴ18፥22
4፥25 ቍ1፡8፤ዘፍ 5፥3፤1ዜና1፥1
4፥26 ዘፍ5፥6፤12፥ 8፤13፥4፤21፥33፤22፥ 9፤26፥25፤33፥20፤ 35፥1፤ዘፀ17፥15፤1ነገ 18፥24፤1ዜና1፥1፤ መዝ116፥17፤ኢዩ2፥ 32፤ሶፎ3፥9፤ሉቃ3፥ 38፤ሐሥ2፥21
5፥1 ዘፍ1፥27፤2፥4፤ 1ዜና1፥1፤ቆላ3፥10
5፥2 ዘፍ1፥27፡28፤ ማቴ19፥4፤ማር10፥6፤ ገላ3፥28፤
5፥3 ዘፍ1፥26፤4፥ 25፤ሉቃ3፥38፤1ቆሮ 15፥49
5፥5 ዘፍ2፥17፤ዕብ 9፥27
5፥6 ዘፍ4፥26፤ሉቃ 3፥38
5፥9 1ዜና1፥2፤ሉቃ 3፥37
5፥12 1ዜና1፥2፤ ሉቃ3፥37
5፥15 1ዜና1፥2፤ ሉቃ3፥37
5፥18 1ዜና1፥3፤ ሉቃ3፥37፤ይሁ1፥14
5፥21 1ዜና1፥3፤ ሉቃ3፥37

ለማግኘት መሞከሩ ይሆናል። ነገር ግን እግዚአብሔር ጋብቻን ሲመሠርት አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት አድርጎ ነው (2፥23-24 ይመ)።

4፥20-22 *ያባልን… ዩባል… ቱባልቃይን፤* ሦስት የላሜሕ ወንዶች ልጆች ተመሳሳይ ስም የነበራቸው ሲሆን፣ የእያንዳንዱም ስም፣ "አመጣ፣ ተሸከመ፣ መራ" የሚል ትርጕም ካለው የዕብራይስጥ ግስ የተወሰዱና በድርጊት ላይ የሚያተኩሩ ቃላት ናቸው። ለዚህም ቱባልቃይን የሚለው ስም ተስማሚ ነው፤ ምክንያቱም ቃየን ማለት "ወርቅ አንጥረኛ" ማለት ነውና።

4፥22 *መሣሪያዎችን፤* ለዕርሻና ለግንባታ ሥራ የሚያገለግሉ ቢሆንም፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለጦር መሣሪያነትም ያገለግሉ ነበር።

4፥23 *ቢያቈስለኝ… ገደልሁት፤* እግዚአብሔር ከቶ አያስፈልገኝም የሚል አንድ ሰው፣ በቂም በቀል ተነሣሥቶ በጭካኔ፣ ርኅራኄ በጐደለው ሁኔታ የሰውን ነፍስ ማጥፋቱን የሚያመለክት ነው (ዘዳ 32፥35)። ላሜሕ፣ እርሱና ልጆቹ በራሳቸው ጥረት በቃየን ዘር በኩል የመጣውን ርግማን ማስወገድና የዕድል ፈንታቸውም ወሳኞች እነርሱ እንደሆኑ አድርጐ በኵራት ተናገረ። ይህ ብርቱ ንግግር ቃየን በራስ ወዳድነቱና በትዕቢቱ የጀመረውን ኀጢአት በመጨመር ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዲደርስ አድርጐታል።

4፥24 *ሰባ ሰባት ጊዜ፤* ላሜሕ በግል ቂም በቀል የወሰደው ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ፣ ጴጥሮስ ስለ ይቅርታ ለጠየቀው ጥያቄ ኢየሱስ ከሰጠው መልስ ጋር የሚመሳሰል ነው (ማቴ 18፥21-22)።

4፥25 *እንደ ገና… ምትክ ሰጠኝ፤* አቤል ሞተ፤ ቃየን ደግሞ ከሰው ሁሉ ተለይቶ እንዲኰበልል ተደረገ። ስለዚህ የዘር ግንዱ እንዲቀጥል እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ሌላ ሦስተኛ ልጅ ሰጣቸው።

4፥26 *ሄኖስ፤* የዕብራይስጡ ትርጕም፣ "አዳም" ለተባለው ስም ከተሰጠው ትርጕም ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ይኸውም "ሰው" ማለት ነው። *የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ጀምሩ፤* የላሜሕ ትዕቢትና በራሱ መመካት የቃየን ዘር ልዩ ምልክት ሲሆን፣ ይህም የሴት ዘር በእግዚአብሔር ላይ ካለው እምነት ጋር የሚነጻጸር ነው።

5፥1 *የትውልድ ሐረግ፤* የ2፥4 ማብ ይመ። *አምሳል፤* የ1፥26 ማብ ይመ።

5፥2 *ወንድና ሴት፤* የ1፥27 ማብ ይመ። *ባረካቸው፤* 1፥28 እና ማብ ይመ። *ሰው፤* በመጀመሪያዎቹ የዘፍጥረት ምዕራፍ ውስጥ ይህ ቃል ሁለቱንም ጾታዎች (የሰውን ዘር በሙሉ) የሚያመለክት ነው (3፥22-24 ይመ)። *ጠራቸው፤* የ1፥5 ማብ ይመ።

5፥3 *እርሱን ራሱን የሚመስል፤* የ1፥26 ማብ ይመ። እግዚአብሔር ፍጹም በሆነው በራሱ መልክ ሰውን እንደፈጠረ ሁሉ፣ አዳምም በተበላሸው በራሱ መልክ ወንድ ልጅ ወለደ።

5፥5 *930 ዓመት፤* ማረጋገጫ ባይኖራቸውም፣ በዘፍጥረት የመጀመሪያ ምዕራፎች ውስጥ የተገለጹት ከፍተኛ የሰው ዕድሜ ቍጥሮች ምሳሌያዊ ሳይሆኑ አይቀሩም ብለው የሚያስቡ አንዳንድ ሰዎች አሉ። *በኋላ ሞተ፤* በምዕራፉ ውስጥ አሳዛኝ ሁኔታን ለመግለጽ ተደጋግሞ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ከዚህ ከፉ ገጠመኝ የተረፈው ሄኖክ ብቻ ነው (የቍ 24 ማብ ይመ)። ይህ ሐረግ በአዳም ውድቀት ሳቢያ እግዚአብሔር በኀጢአት ላይ ያሳየውን ጽኑ ፍርድ ያሳስባል።

5፥22 *አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረግ፤* በዚሁ

ልጆችንም ወለደ:: 23 ሄኖክ በአጠቃላይ 365
ዓመት ኖረ፤ 24 ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር
(ኤሎሂም) ጋር አደረገ፤ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ስለ
ወሰደውም አልተገኘም::
25 ማቱሳላ፣ ዕድሜው 187 ዓመት ሲሆን
ላሜሕን ወለደ፤ 26 ማቱሳላ ላሜሕን ከወለደ
በኋላ፣ 782 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና
ሴቶች ልጆችንም ወለደ፤ 27 ማቱሳላ በአጠ
ቃላይ 969 ዓመት ከኖረ በኋላ ሞተ::
28 ላሜሕ፣ ዕድሜው 182 ዓመት በሆነ
ጊዜ፣ ልጅ ወለደ:: 29 ስሙንም "እግዚአብሔር
(አዶናይ) በረገማት ምድር ከልፋታችንና ከጕ
ልበታችን ድካም ያሳርፈናል" ሲል ኖኅ[ነ] ብሎ
ጠራው:: 30 ላሜሕ ኖኅን ከወለደ በኋላ፣ 595
ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆ
ችንም ወለደ:: 31 ላሜሕ በአጠቃላይ 777 ዓመት
ከኖረ በኋላ ሞተ::
32 ኖኅ ዕድሜው 500 ዓመት ሲሆን ሴምን፣
ካምንና ያፌትን ወለደ::

## የጥፋት ውሃ

6 ሰዎች በምድር ላይ እየበዙ ሲሄዱ ሴቶች
ልጆች ተወለዱላቸው:: 2 የእግዚአብሔር (ኤሎ
ሂም) ወንዶች ልጆች የሰዎችን ሴቶች ልጆች
ውብ ሆነው አዩአቸው፤ ከመካከላቸውም የመ
ረጧቸውን አገቡ:: 3 *እግዚአብሔርም* (ያህዌ)፣
"ሰው ሟች[ጠ] ስለ ሆነ መንፈሴ እያዘነ[ጡ] ከእ
ርሱ ጋር ለዘላለም አይኖርም፤ ዕድሜው 120
ዓመት ይሆናል" አለ::
4 የእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ልጆች የሰዎችን ሴቶች
ልጆች ተገናኝተው ልጆች በወለዱ ጊዜም
ሆነ ከዚያም በኋላ ኔፊሊም የተባሉ ሰዎች
በምድር ላይ ነበሩ:: እነርሱም በጥንቱ ዘመን
በጀግንነታቸው ከፍ ያለ ዝና ያተረፉ ናቸው::
5 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) አምላክ የሰው ዐመፅ
በምድር ላይ የበዛና የልቡም ሐሳብ ዘወትር
ወደ ክፋት ብቻ ያዘነበለ መሆኑን ተመለ
ከተ:: 6 *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰውን በምድር
ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፤ ልቡም እጅግ አዘነ::
7 ስለዚህም *እግዚአብሔር* (ያህዌ)፣ "የፈጠርሁ
ትን የሰው ዘር ከምድረ ገጽ አጠፋለሁ፤
ከሰው እስከ እንስሳ በምድር ላይ ከሚሳቡ
ፍጡራን እስከ ሰማይ ወፎች አጠፋለሁ፤
ስለ ፈጠርኋቸው ተጸጽቻለሁና" አለ:: 8 ኖኅ
ግን *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ዘንድ ሞገስን አገኘ::

5፥22 ቍ 24፤ዘፍ 6፥9፤17፥1፤24፥40፤ 48፥15፤2ነገ20፥3፤ መዝ116፥9፤ሚክ6፥8፤ ሚል2፥6 5፥24 ቍ 22፤2ነገ2፥ 1:11፤መዝ49፥15፤ 73፥24፤89፥48፤ዕብ 11፥5 5፥25 1ዜና1፥3፤ ሉቃ3፥36 5፥29ዘፍ3፥17፤1ዜና 1፥3፤ሉቃ3፥36፤ሮሜ 8፥20 5፥32 ዘፍ6፥10፤7፥6 :11፤8፥13፤9፥18፤10፥ 1፤1ዜና1፥4፤ኢሳ 65፥ 20፤ሉቃ3፥36 6፥1 ዘፍ1፥28 6፥2 ቍ 4፤ዘፍ4፥19 ፤ዘዳ21፥11፤ኢዮ1፥6፤ 2፥1 6፥3 ኢዮ10፥9፤34፥ 14፤መዝ78፥39፤ 103፥14፤ኢሳ40፥6፤ 57፥16፤ገላ5፥16-17፤ 1ጴጥ3፥20 6፥4 ቍ 2፤ዘፍ11፥4 ፤ዘኍ13፥33 6፥5ዘፍ8፥21፤38፥7፤ ኢዮ34፥26፤መዝ14፥ 1-3፤ኤር1፥16፤44፥5 ፤ሕዝ3፥19 6፥6 ዘፀ32፥14፤ 1ሳሙ15፥11:35፤ 2ሳሙ24፥16፤1ዜና 21፥15፤ኢሳ63፥10፤ ኤር18፥7-10፤ኤፌ4፥30 6፥7 ቍ 17፤ዘፍ7፥4:21፤ዘዳ28፥63፤29፥20 ፤ሕዝ33፥28፤ሶፎ1፥2:18 6፥8 ዘፍ19፥19፤39፥4፤ዘፀ33፥12:13፡17፤ 34፥9፤ዘኍ11፥15፤ሩት2፥2፤ሕዝ14፥14፤ሐሥ7፥46፤ሉቃ1፥30

[ነ]29 ኖኅ የሚለው ስም መጽናናት የሚል ትርጕም ካለው የዕብራ ይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው
[ጠ]3 ወይም በሰባሽ
[ጡ]3 ወይም መንፈሴ አይኖርም

ምዕራፍ ውስጥ በሌሎች አንቀጾች ላይ የተጠቀሰውን፣ "ኖረ" የሚ ለውን ቃል የሚተካ ሲሆን አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግና እንዲያው መኖር እጅግ የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን ያሳስባል::

5፥24 *እግዚአብሔር ስለወሰደውም አልተገኘም*፤ በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ በሌሎች አንቀጾች ላይ የተጠቀሰውን "... በኋላ ሞተ" የሚለውን ሐረግ የሚተካ ነው:: ወደ ሰማይ እንደ ተወሰ ደው እንደ ኤልያስ (2ነገ 2፥10) ሄኖክም ሞትን ሳያይ (ዕብ 11፥5) ተወሰደ ማለት ነው (ከመዝ 49፥15፤73፥24 ጋር ያነጻጽሩ):: በቃየን የዘር ሐረግ ከአዳም ጀምሮ ሲቈጠር ሰባተኛ የሆነው ላሜሕ የክፉ ተምሳሌት ነበር:: በሴት የዘር ሐረግ ከአዳም ጀምሮ ሲቈጠር ሰባተኛ የሆነው ሄኖክ ግን (ይሁ 14) እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ (ዕብ 11፥5) ተመስክሮለታል::

5፥27 *969 ዓመት*፤ ከጥፋት ውሃ ያመለጡት ኖኅና ቤተ ሰቡ ብቻ ነበሩ:: ዕድሜን በሚያመለክቱ ቍጥሮች መሠረት፣ ማቱ ሳላ የሞተው የጥፋት ውሃ በመጣበት ዐመት ነበር (በቍ 25:28 እና 7፥6 ያሉትም የዕድሜ ቍጥሮች ሲደመሩ የማቱሳላን ዕድሜ ወደ 969 ከፍ ያደርጉታል)::

6፥1 *እየበዙ* የ1፥22 ማብ ይመ::

6፥2 *የእግዚአብሔርም ወንዶች ልጆች የሰዎችን ሴቶች ልጆች... አገቡ*፤ ቍ 4 ይመ፤ በዚህ ቦታ፣ "የእግዚአብሔር ልጆች" የሚለው ሐረግ መላእክትን ወይም ሰዎችን የሚያመለክት ነው የሚሉ አሉ:: ኢዮ 1፥6፤2፥1 እና ምናልባትም መዝ 29፥1 ("ኀያ ላን" ተብሎ የተተረጐመው) መላእክትን ያመለክታል፤ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ይሁ 6-7 ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሐሳብ እንዳለው ይናገራሉ:: ሌሎች ተርጓሚዎች እንደሚ ያስቡት ግን፣ ምንም እንኳን በመላእክትና በሰው ልጆች መካ ከል መጋባትና አብሮ የመኖር ልማድ እንዳለ በጥንት ሥነ ተረ ቶች ውስጥ የታወቀ ቢሆንም፣ የሥነ ፍጥረት ሥርዐት እንደሚ ያሳየው ከሆነ ግን እንዲህ የመሰለው ልማድና ድርጊት ፈጽሞ ቦታ የለውም:: (ም 1፤ ማር 12፥25):: በሌላ ቦታ፣ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከሚለው አገላለጽ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው አነጋገ ሮች የሚያመለክቱት የሰውን ልጆች ነው (ዘዳ 14፥1፤ 32፥5፤ መዝ 73፥15፤ ኢሳ 43፥6፤ ሆሴ 1፥10፤ 11፥1፤ ሉቃ 3፥38፤ 1ዮሐ 3፥1-2:10 ይመ) "የእግዚአብሔር ልጆች" (ቍ 2:4) የሚለው ሐረግ ምናልባት ጻድቃንን የሚያመለክት ሲሆን፣ "የሰዎች ሴቶች ልጆች" የሚለው ደግሞ ከክፋው የቃየን የዘር ሐረግ የተገኙትን ኀጢአተኞች ሴቶችን ያመለክታል ("የእግዚአብሔር ልጆች" ያል ተባሉትም ለዚሁ ሳይሆን አይቀርም):: እውነታው ይህ ከሆነ ዐውደ ንባቡ የሚያሳየን ከቍ 1-2 ላይ ያለው ሐሳብ በም 5 ላይ በሴት የዘር ሐረግ ("የእግዚአብሔር ልጆች") እና በም 4 ላይ በቃየን የዘር ሐረግ ("የሰዎች ሴቶች ልጆች") መካከል የተደረገውን ጋብቻ ነው::

በዚህ ጉዳይ ላይ የተሰጠው ሌላው አስተያየት እንደሚያ ትተው፣ "የእግዚአብሔር ልጆች" የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ነገሥታትን ነው (በጥንት ቅርብ ምሥራቃውያን ዘንድ ነገሥታ ትና አማልክት የቅርብ ዝምድና አላቸው ተብሎ ይታመናል):: እነዚህ ነገሥታት የቃየንን ልጅ የላሜሕን ክፉ ተግባር ለማስፋ ፋት ለራሳቸውም ቤተ መንግሥታዊ ቍባቶች ለማስቀመጥ ያሰቡ ሳይሆኑ አይቀርም::

6፥3 በዚህ ቍጥር ላይ ያሉት ሁለት ቍልፍ ሐረጎች "ሟች ስለሆነ" እና፣ "አይኖርም" የሚሉት ግልጽ አይደሉም:: አንዳንዶች፣ ይህ ጥቅስ በእግዚአብሔር የፍርድ ዐዋጅና ፍርዱ በሚፈጸምበት ጊዜ መካከል ያለው የጸጋ ዘመን 120 ዓመት መሆኑን ይናገራል ይላሉ (1ጴጥ 3፥20):: ጥቅሱ በቀጥታ ከተወ ሰደ ግን የሰው ዕድሜ ባጭር መገደቡን ያመለክታል::

6፥4 *ኔፊሊም*፤ ረጃጅሞችና ብርቱዎች የነበሩ ሰዎች ናቸው (ዘኍ 13፥31-33 ይመ):: የቃሉ ትርጕም በዕብራይስጥ፣ "የወደቁ" ማለት ነው:: እነርሱም በሰው አመለካከት፣ "በጀግንነታቸው ከፍ ያለ ዝና ያተረፉ" ሲሆኑ፣ በእግዚአብሔር ፊት ግን ኀጢአተ ኞችና ("የወደቁ") ለፍርድም የተዘጋጁ ናቸው::

6፥5 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰውን ፍጹም ውድቀት ከሚገልጹት መካከል አንዱና ዋነኛው ጥቅስ ነው:: የሰው ሁኔታ ምንም ለውጥ ባለማሳየቱ፣ ከጥፋት ውሃ በኋላም የተሻለ ነገር አልተገኘም (8፥21)::

6፥6 *እግዚአብሔር ... ተጸጸተ፤ ልቡም እጅግ አዘነ* የሰው ኀጢአት እግዚአብሔርን ያሳዝናል (ኤፌ 4፥30 ይመ)::

6፥7 *የሰው ዘር ከምድር ገጽ አጠፋለሁ*፤ የጸጋ ዘመን ወደ ማብቂያው አካባቢ ደርሶ ነበር (ቍ 3 እና ማብ ይመ):: *እንስሳ... ፍጡራን... ወፎች*፤ እንስሳት በተፈጥሮአቸው ንጹሐን ቢ ሆኑም፣ በሰው እኩይ አገዛዝ ሥር እስካሉ ድረስ ከሰው ጋር ይፈረድባቸዋል::

6፥8-9 *ሞገስን አገኘ... ጻድቅና ከበደል የራቀ... አካሄዱ ንም ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ* የ5፥22 ማብ ይመ:: የኖኅ

9የኖ[illegible] ታሪክ እንደሚከተለው ነው፤ ኖኅ
በዘመ[illegible] ከነበሩት ሰዎች ሁሉ ይልቅ ጻድቅና
ከ[illegible] የራቀ ሰው ነበር፤ አካሄዱንም ከእግ
[illegible]ብሔር (ኤሎሂም) ጋር አደረገ::
10ኖኅም ሴም፣ ካምና ያፌት የሚባሉ
ሦስት ወንዶች ልጆች ነበሩት::
11ምድር በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፊት በክፉ ሥራ
ረክሳ ችተ፤ በዐመፅም ተሞላች:: 12እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) ምድር ምን ያህል በክፉ ሥራ እንደ
ረከሰች አየ፤ እነሆ፤ ሰው ሁሉ አካሄዱን አበ
ላሽቶ ነበርና 13ስለዚህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ኖኅን እንዲህ አለው:- "ሰውን ሁሉ ላጠፋ
ነው፤ ምድር በሰው ዐመፅ ስለ ተሞላች በእ
ርግጥ ሰውንም ምድርንም አጠፋለሁ:: 14አንተ
ግን በጎፈር[a] ዕንጨት መርከብ ሥራ፤ ለመር
ከቧም ክፍሎች አብጅላት፤ ውስጧንና ውጭ
ዋን በቅጥራን ለብጠው:: 15እንዲህ አድርገህ
ሥራት:- ርዝመቷ 140 ሜትር፣ ወርዷ 23
ሜትር፣ ከፍታዋ 13.5 ሜትር ይሁን:: 16ለመ
ርከቧ ጣራ አብጅላት፣ ጣራና ግድግዳው በሚ
ጋጠምበት ቦታ ግማሽ ሜትር ክፍተት ተው፤[b]
ከጐኗ በር አውጣላት፤ ባለ ሦስት ፎቅ አድ
ርገህ ሥራት:: 17እኔም ከሰማይ በታች የሕ
ይወት እስትንፋስ ያለባቸውን ሕያዋን ፍጡ
ራን ሁሉ ለማጥፋት እነሆ በምድር ላይ የጥ
ፋት ውሃ አወርዳለሁ፤ በምድር ላይ ያለ ሁሉ
ይጠፋል:: 18ካንተ ጋር ግን ቃል ኪዳን እመ
ሠርታለሁ:: አንተና ወንዶች ልጆችህ፣ ሚስ
ትህና የልጆችህ ሚስቶች ከአንተ ጋር ወደ
መርከቧ ትገባላችሁ:: 19ከአንተ ጋር በሕይ
ወት እንዲቈዩ ከሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ተባዕ
ትና እንስት እያደረግህ ሁለት ሁለቱን ወደ
መርከቧ ታስገባለህ:: 20ከእያንዳንዱ የወፍ
ወገን፣ ከእያንዳንዱ የእንስሳ ወገን፣ በም
ድር ላይ ከሚሳቡ ፍጥረት ሁሉ በየወገናቸው
በሕይወት ይቈዩ ዘንድ ሁለት ሁለት እየሆኑ
ወደ አንተ ይመጣሉ:: 21ለአንተና ለእነርሱ
የሚያስፈልገውን ምግብ ሁሉ አከማች::"
22ኖኅም ሁሉን እግዚአብሔር (ኤሎሂም) እንዳዘ
ዘው አደረገ::

7 እግዚአብሔር (ያህዌ) ኖኅን እንዲህ አለው፤
"በዚህ ትውልድ መካከል አንተን ጻድቅ
ሆነህ አግኝቼሃለሁና ቤተ ሰብህን በሙሉ
ይዘህ ወደ መርከቧ ግባ:: 2ከንጹሕ እንስሳት
ሁሉ ሰባት ሰባት[c] ተባዕትና እንስት፣ 3ንጹህ
ካልሆኑት እንስሳት ደግሞ ሁለት ሁለት ተባ
ዕትና እንስት 3እንዲሁም ከወፎች ወገን
ሁሉ ሰባት ተባዕትና ሰባት እንስት፣ በምድር
ላይ ለዘር እንዲተርፉ ከአንተ ጋር ታስገባለህ::

6፥9 ዘፍ2፥4፤5፥22፤17፥1፤27፥1፤ዘዳ18፥13፤2ሳሙ22፥24፤ኢዮ1፥1፤4፥6፤9፥21፤12፥4፤31፥6፤መዝ15፥2፤18፥23፤19፥13፤37፥37:39፤ምሳ2፥7፤ኤር15፥1፤ሕዝ14፥14:20፤ዳን10፥11፤ሉቃ1፥6፤ዕብ11፥7፤2ጴጥ2፥5
6፥10 ዘፍ5፥32፤ሉቃ3፥36
6፥11 ዘዳ31፥29፤መሳ2፥19፤መዝ7፥9፤73፥6፤ዕዝ7፥23፤8፥17፤28፥16፤ሚል2፥16
6፥12 ዘዐ32፥7፤ዘዳ4፥16፤9፥12:24፤መዝ14፥1-3
6፥13 ቍ17፤ዘፍ7፥4:21-23፤ዘዳ28፥63፤ኢዮ34፥15፤2ነገ8፥19፤ዕዝ9፥14፤ኢሳ5፥6፤24፥1-3፤ኤር44፥11: 27፤ሕዝ7፥2-3
6፥14 ዘዐ2፥3፤ዕብ11፥7፤1ጴጥ3፥20
6፥17 ቍ7:13፤መዝ29፥10፤2ጴጥ2፥5
6፥18 ዘፍ7፥1:7:13፤9፥9-16፤17፥7፤19፥12፤ዘዐ6፥4፤34፥10:27፤ዘዳ29፥13:14-15፤መዝ25፥10፤74፥20፤106፥45፤ኢሳ55፥3፤ኤር32፥40፤ሕዝ16፥60፤ሐጌ2፥5፤1ጴጥ3፥20
6፥19 ዘፍ7፥15
6፥20 ዘፍ1፥11፤7፥3:15 6፥22 ዘፍ7፥5:9:16፤ዘዐ7፥6፤39፥43፤40፥16:19:21:23:25:27:29:32 7፥1 ዘፍ6፥9:18፤ሕዝ14፥14፤ማቴ24፥38፤ሉቃ17፥26-27፤ዕብ11፥7፤1ጴጥ3፥20፤2ጴጥ2፥5 7፥2 ቍ8፤ዘፍ8፥20፤ዘሌ10፥10፤11፥1-47፤ዘዳ14፥3-20፤ሕዝ44፥23፤ሐጌ2፥12፤ሐሥ10፥14-15 7፥3 ዘፍ6፥20

[a]14 በዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጕም አይታወቅም
[b]16 ወይም *ለብርሃን መግቢያ አድርገህ፣ ሥራ*
[c]2 ወይም *ሰባት ጥንድ፤* በቍ 3ም እንዲሁ

የተቀደሰ ሕይወት፣ በዘመኑ ከነበሩት ሰዎች ርኵሰት ፍጹም ተቃራኒ ነበር (ቍ 5 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም ቍ 12 ይመ):: ሆኖም ይህ የኖኅ ታሪክ ኀጢአት አልባ ፍጹምነትን አያመለክትም::

6፥9 *ታሪክ፤* የ2፥4 ማብ ይመ:: *ጻድቅ፤* የመዝ 1፥5 ማብ ይመ::

6፥14 *መርከብ፤* ይህን ቃል ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጥ ቃል በሌላ ቦታ ጥቅም ላይ የዋለው፣ ሕፃኑ ሙሴ የዳነበትን ቅር ጫት ለማመልከት ብቻ ነው (ዘፀ 2፥3-5):: *በቅጥራን ለብጠው፤* የሙሴ እናት ውሃ እንዳይገባበት በተመሳሳይ መንገድ ቅርጫቱን ለቅልቃዋለች (ዘፀ 2፥3)::

6፥16 *ጣራ፤* ዝናብ ወደ ውስጥ እንዳይገባ በአሞራ ክንፍ ዐይ ነት የተሠራ ሳይሆን አይቀርም:: *ግማሽ ሜትር ክፍተት፤* የኖኅ መርከብ ከላይ በኩል በጣራውና በግድግዳው መካከል ዙሪያውን ግማሽ ሜትር ክፍተት ያላቸው (8፥6 ይመ) የብርሃንና የአየር ማስገቢያ ትናንሽ መስኮቶች ሳይኖሩት አይቀርም::

6፥17 *ከሰማይ በታች የሕይወት እስትንፋስ ያላቸውን ሕያ ዋን ፍጡራን ሁሉ ለማጥፋት፤* አንዳንዶች፣ በዚህ ቦታና በሌሎች ቦታዎች ያሉትን የቃላት አጠቃቀሞች መሠረት በማ ድረግ የጥፋት ውሃው ያጥለቀለቀውና ያጠፋው ምድርን ሁሉ ነው ይላሉ (ቍ 7:12-13፤ 7፥4:19:21-23፤ 8፥21፤9፥11:15):: ሌሎች ደግሞ ከም 6-9 ባለው ትረካ ውስጥ የተገደለው የጥፋት ውሃ ያጥለቀ ለቀው የተወሰነን ክልል ብቻ ነው የሚል አመለካከት እንዳይኖ ረን የሚከለክል ምንም ፍንጭ የለም ይላሉ፤ ሆኖም ሙሴ በወ ቅቱ ከነበረው መልክዐ ምድራዊ ዕውቀት አንጻር ከታየ፣ ዓለም ዐቀፋዊ ሊያሰኝ ይችላል ይላሉ:: "ምድር" ጠበብ ባለ ትርጕሙ "መሬት" ማለት ነው (2፥5):: "ከሰማይ በታች የሕይወት እስት ንፋስ ያላቸውን ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ" የሚለው ሐረግ ኖኅ የሚ ያውቃቸውን ሕያዋን ፍጡራን ብቻ የሚያመለክት ሳይሆን አይቀ ርም (በዮሴፍ ዘመን የተከሰተውን ድርቅና ራብ ለመግለጽ የገ ባውን ዓለም ዐቀፋዊ ቋንቋ በ 41፥54:57 ላይ ይመ፤ እንዲሁም የ41፥57 ማብ ይመ):: የጥፋት ውሃ ዐላማ ኀጢአተኛውን ሰው ለማ ጥፋት መሆኑንና (ቍ 13) ጸሓፊውም በአእምሮው ይዞት የነበ ረው የጥንቱን የቅርብ ምሥራቅ ሕዝቦች ስለ ነበር የጥፋት ውሃው ዓለም ዐቀፋዊ ክሥተት ያለው ላይሆን ይችላል:: ያም ሆነ ይህ ሐዋ ርያው ጴጥሮስ የጥፋት ውሃው ያስከተለው ጥፋት ዓለም ዐቀፋዊ ገጽታ እንደነበረው የሚያምን ይመስላል (2ጴጥ 3፥6 እና ማብ ይመ)::

6፥18 *ቃል ኪዳን፤* የ9፥9 ማብ ይመ:: ኖኅ፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን ምንነት በትክክል የተረዳው የጥፋት ውሃው ከምድር ላይ ከደረቀ በኋላ ነው (9፥8-17 ይመ):: *ወደ መርከቧ ትገባላችሁ፤* የኖኅ ከጥፋት ውሃ መዳን እግዚአ ብሔር ልጆቹን ለመቤዠት ያደረገውን በጎ ተግባር ያሳያል (ዕብ 11፥7፤ 2ጴጥ 2፥5 ይመ) *አንተና ወንዶች ልጆችህ፣ ሚስትህና የልጆችህ ሚስቶች፤* እግዚአብሔር ከፍቅሩ የተነሣ የሚያደርገውን መልካም ነገር ለጻድቁ ኖኅ ቤተ ሰብ ሁሉ አሳየ፤ ይህም እግዚአ ብሔር በሕዝቡ ታሪክ ውስጥ ተሳትፎ ባደረገ ጊዜ ሁሉ የታየ እውነታ ነው፤ ወላጆች ለልጆቻቸው ሊያሳዩት የሚገባውን ከእነ ርሱም የሚጠበቀውን ኀላፊነት በግልጽ ይጠቍማል (17፥7-27፤ 18፥19፤ ዘዳ 30፥19፤ መዝ 78፥1-7፤ 102፥28፤ 103፥17-18፤ 112፥1-2፤ ሐሥ 2፥38-39፤ 16፥31፤ 1ቆሮ 7፥14 ይመ)::

6፥19 *በሕይወት እንዲቈዩ ከሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ተባ ትና እንስት፤* በርካታ እንስሳት በጥፋት ውሃ እንዲጠፉ ተደር ገዋል (የቍ 7 ማብ ይመ)፤ ይሁን እንጂ ውሃው በጐደለ ጊዜ ምድርን እንደ ገና እንዲሞሏት ከእያንዳንዱ ወገን አንድ አንድ ጥንድ እንስሳት በሕይወት እንዲቈዩ ተጠብቀዋል::

6፥20 *ወገን፤* የ1፥11 ማብ ይመ::

6፥22 *እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ፤* የኖኅን ታዛዥነት የሚገልጽ ነው (7፥5:9:16 ይመ)::

7፥1 *ጻድቅ፤* የ6፥8-9 ማብ ይመ:: ኖኅም እንደ ጽድቅ ሰባኪ (2ጴጥ 2፥5) ስለሚመጣው ፍርድ በዘመኑ ለነበሩት ሰዎች እያስጠነቀቀ፣ የራሱ እምነት ምን ያህል ጽኑ እንደ ሆነ ይመሰክር ነበር (ዕብ 11፥7 ይመ):: *ወደ መርከቧ ግባ፤* የጥፋት ውሃ ከመ ምጣቱ በፊት እግዚአብሔር ለኖኅ ከተናገራቸው ንግግሮች የመጀ መሪያው ነው:: ከጥፋት ውሃ በኋላም እግዚአብሔር ለኖኅ የተናገ ረው የመጀመሪያ ቃል ተመሳሳይ በሆነ መንገድ፣ "ከመርከቧ ውጡ" ብሎ ይጀምራል (8፥16)

7፥2-3 *ከንጹሕ እንስሳት ሁሉ ሰባት ሰባት ተባዕትና እን ስት፣ ንጹሕ ካልሆኑት እንስሳት ደግሞ ሁለት ሁለት ተባዕትና እንስት፤* ከጥፋት ውሃው ንጹሕ ያልሆኑት እንስሳት እንዲራቡ ሲደ ረግ፣ በሥርዐቱ ንጹሕ የሆኑት እንስሳት ግን ኖኅ ለሚያቀርበው መሥዋዕትና (8፥20 ይመ) ለምግብነት አስፈላጊ ነበሩ (9፥3 ይመ)::

[4]ከሰባት ቀን በኋላ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት
በምድር ላይ ዝናብ አዘንባለሁ፤ የፈጠርሁት
ንም ሕያው ፍጡር ሁሉ ከምድር ገጽ አጠ
ፋለሁ::"
[5]ኖኅም እግዚአብሔር (ያህዌ) ያዘዘውን ሁሉ
አደረገ::
[6]የጥፋት ውሃ በምድር ላይ በወረደ ጊዜ
ኖኅ የ600 ዓመት ሰው ነበር:: [7]ኖኅና ወን
ዶች ልጆቹ፣ ሚስቱና የልጆቹ ሚስቶች
ከጥፋት ውሃ ለመትረፍ ወደ መርከቧ ገቡ::
[8]ንጹሕ ከሆኑትና ንጹሕ ካልሆኑት እንስሳት፣
ከወፎችና በምድር ላይ ከሚሳቡ ፍጡራን ሁሉ
ጥንድ ጥንድ፣ [9]ተባዕትና እንስት ሆነው ወደ
ኖኅ መጡ፤ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ኖኅን ባዘዘውም
መሠረት ወደ መርከቧ ገቡ:: [10]ከሰባት ቀንም
በኋላ የጥፋት ውሃ በምድር ላይ መጣ::
[11]ኖኅ በተወለደ በ600ኛው ዓመት፣ በሁ
ለተኛው ወር፣ ከወሩም በዐሥራ ሰባተኛው
ቀን፣ በዚያ ቀን የታላቁ ጥልቅ ምንጮች
በሙሉ ተነደሉ፤ የሰማይ መስኮቶችም ተከ
ፈቱ፤ [12]አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በምድር
ላይ ዝናብ ዘነበ::
[13]በዚያኑ ዕለት ኖኅና ልጆቹ ሴም፣ ካምና
ያፌት፣ እንዲሁም ሚስቱና ሦስቱ የልጆቹ
ሚስቶች ወደ መርከቧ ገቡ:: [14]ከዱር እንስ
ሳት ከየወገኑ፣ ከቤት እንስሳት ከየወገኑ፣
በምድር ላይ ከሚሳቡ ፍጡራን ከየወገናቸው፣
ከወፎችም ከየወገናቸውና ክንፍ ያላቸው ሁሉ
አብረዋቸው ገቡ:: [15]የሕይወት እስትንፋስ
ያለባቸው ፍጡራን በሙሉ ጥንድ ጥንድ እየ
ሆኑ ወደ ኖኅ በመምጣት መርከቧ ውስጥ
ገቡ:: [16]ከሕያዋንም ፍጡራን ሁሉ እግዚአ
ብሔር (ኤሎሂም) ኖኅን ባዘዘው መሠረት ተባዕትና
እንስት እየሆኑ ገቡ፤ ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ)
ከውጭ ዘጋበት::

7፥4 ቍ12፡17፤ዘፍ
8፥2፡6፥7፡13፤ዘፀ24፥
18፡32፥1፤34፥28፤
ዘኍ13፥25፤ዘዳ9፥9፡
11፡18፡25፤10፥10፤
1ሳሙ17፥16፤1ነገ
13፥34፤19፥8፤ኢዮ
37፥6፡13፤ማቴ4፥2፤
ኤር28፥16፤
7፥5 ዘፍ6፥22
7፥6 ዘፍ5፥32
7፥7 ዘፍ6፥18
7፥8 ቍ2
7፥9 ዘፍ6፥22
7፥10 ቍ4
7፥11 ዘፍ1፥7፡5፥
32፤8፥2፡4፡14፤2ነገ7፥
2፤ኢዮ28፥11፤መዝ
36፥6፤42፥7፤78፥23፤
ምሳ8፥24፤ኢሳ51፥
10፡24፥18፤ሕዝ26፥
19፤ሚል3፥10
7፥12 ቍ4፤1ሳሙ
12፥17፤ኢዮ28፥26
7፥13 ዘፍ6፥18፤
8፥16፤1ጴጥ3፥20፤
2ጴጥ2፥5
7፥14 ዘፍ1፥11
7፥15 ቍ8-9፤ዘፍ
6፥19
7፥16 ዘፍ6፥22
7፥17 ቍ 4
7፥19 መዝ104፥6
7፥20 ዘፍ8፥4-5፤
2ጴጥ3፥6
7፥21 ዘፍ6፥7፡13፤
2ጴጥ3፥6
7፥22 ዘፍ1፥30
7፥23 ኢዮ14፥19፤
21፥18፤22፥11፡16፤
መዝ90፥5፤ኢሳ28፥2፤
ማቴ24፥39፤ሉቃ17፥
27፤ዕብ11፥7፤1ጴጥ
3፥20፤2ጴጥ2፥5፤
7፥24 ዘፍ8፥3፤
ኢዮ12፥15
8፥1 ዘፍ9፥15፤19፥
29፤21፥1፤30፥22፤

[17]የጥፋት ውሃም ለአርባ ቀናት ያለማቋ
ረጥ በምድር ላይ ዘነበ፤ ውሃው እየጨመረ
በሄደ መጠን መርከቧን ከምድር ወደ ላይ
አነሣት:: [18]ውሃው በምድር ላይ በጣም እየ
ጨመረና ከፍ እያለ ሲሄድ፣ መርከቧ በው
ሃው ላይ ተንሳፈፈች:: [19]ውሃው በጣም ከፍ
በማለቱ፣ ከሰማይ በታች ያሉትን ታላላቅ
ተራሮች ሁሉ ሸፈናቸው:: [20]ውሃው ከተራ
ሮቹ ጫፍ በላይ 7 ሜትር ያህል ከፍ አለ::
[21]በምድር ላይ የነበሩ ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ፦
ወፎች፣ የቤት እንስሳት፣ የዱር እንስሳት
በምድር የሚርመሰመሱ ፍጡራን፣ ሰዎችም
በሙሉ ጠፉ:: [22]በአፍንጫቸው የሕይወት
እስትንፋስ ያላቸው በየብስ የነበሩ ፍጡራን
ሁሉ ሞቱ:: [23]ሕይወት ያላቸው ፍጡራን
ሁሉ ከምድር ገጽ ጠፉ፤ ሰዎችና እንስሳት
በምድር ላይ የሚሳቡ ፍጡራንና የሰማይ
ወፎች ከምድር ላይ ጠፉ፤ ኖኅና ከእርሱ
ጋር በመርከቧ ውስጥ የነበሩት ብቻ ተረፉ::
[24]ውሃውም ምድርን ሸፍኖ መቶ አምሳ ቀን
ቆየ::

8 እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ኖኅንና በመርከቧ ውስጥ
ከእርሱ ጋር የነበሩትን የዱርና የቤት
እንስሳት ሁሉ አሰበ፤ በምድር ላይ ነፋስ
እንዲነፍስ አደረገ፤ ውሃውም ጐደለ:: [2]የጥ
ልቁ ምንጮችና የሰማይ ውሃ መስኮቶች
ተዘጉ፤ ዝናቡም መዝነቡን አቆመ:: [3]ውሃው
ከምድር ላይ ቀስ በቀስ እየቀነሰ መጣ፤
ከመቶ አምሳ ቀን በኋላም ጐደለ:: [4]በሰባተ
ኛው ወር፣ በዐሥራ ሰባተኛው ቀን መርከቧ
በአራራት ተራሮች ላይ ዐረፈች:: [5]ውሃው

ዘፀ2፥24፤14፥21፤ዘኍ10፥9፤ኢሱ2፥10፡3፥16፤ሩት4፥13፤1ሳሙ1፥11፡
19፤2ነገ20፥3፤1ዜና16፥15፤ነህ1፥8፡5፥19፤13፥14፡22፡31፤ኢዮ12፥15፤
14፥13፤መዝ66፥6፤105፥42፤106፥4፤ኢሳ11፥15፤44፥27፤ናሆ1፥4፤
ሉቃ1፥54፡72 8፥2 ዘፍ7፥4፡11 8፥3 ዘፍ7፥24 8፥4 ዘፍ7፥11፡
20፤2ነገ19፥37፤ኤር51፥27

7፥4 *አርባ ቀንና አርባ ሌሊት፡* በድነት (በእግዚአብሔር የማዳን) ታሪክ ውስጥ ወሳኝ የሆኑ ጊዜያትን የሚያመለክት ሐረግ ነው (ቍ 12፤ ዘዳ 9፥11፤ ማቴ 4፥1-11 ይመ)::

7፥7 *ከጥፋት ውሃ ለመትረፍ ወደ መርከቧ ገቡ፡* ኖኅና ቤተ ሰቡ ከጥፋት ውሃ ተረፉ፤ ለሌሎቹ ግን ከጥፋት ውሃ የሚተርፉበት ቀን እስኪያበቃ ድረስ ሕይወት ያው እንደቀድሞው ነበር (ማቴ 24፥37-39 ይመ)::

7፥13 *ኖኅና ልጆቹ... ሚስቱና ሦስቱ የልጆቹ ሚስቶች፡* ከጥፋት ውሃ የተረፉት፣ "ጥቂት ነበሩ፤ ይኸውም ስምንት ሰዎች ብቻ ናቸው" (1ጴጥ 3፥20፤ 2ጴጥ 2፥5 ይመ)::

7፥14 *ከዱር እንስሳት... ከቤት እንስሳት... በምድር ላይ ከሚሳቡ ፍጡራን:: ከወፎችም፡* በ1፥21-25 ላይ ከተጠቀሱት ከአምስቱ የእንስሳት ፍጡራን ዐይነት ውስጥ አራቱ በዚህ ቦታ ተጠቅሰዋል:: አምስተኛው ዐይነት እንስሳ ግን ከመርከብ ውጭ መኖር የሚችል የባሕር ውስጥ ፍጡር ነው::

7፥16 *እግዚአብሔር ኖኅን ባዘዘው መሠረት ... እግዚአብሔር ከውጭ ዘጋበት፡* ትእዛዙን የሰጠው እግዚአብሔር እንደ አዳኝ አምላክነቱ (የ2፥4፤ የዘፀ 6፥6 ማብ ይመ) ኖኅና ቤተ ሰቡ መርከቧ ውስጥ ከገቡ በኋላ ከበስተ ኋላ ዘጋባቸው:: አስፈሪው የጥፋት ውሃ ኀጢአተኛ በሆነው በሰው ልጅ ላይ በሚወርድበት ወቅት፣ ይህ መለኮታዊ ስም በቀረው የም 7 ክፍል ውስጥ አንድም ጊዜ አልተጠቀሰም::

7፥20 *ውሃው ከተራሮች ጫፍ በላይ 7 ሜትር ያህል ከፍ አለ፡* መርከቧ 13 ሜትር ያህል ከፍታ (6፥15) የነበራት ሲሆን፣ መሬት እንዳትነካም ውሃው በቂ ጥልቀት ነበረው::

7፥22 *የሕይወት እስትንፋስ፡* በፍጥረት ጊዜ ለሰዎች የተሰጠ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (1፥30፤ 2፥7 ይመ)፤ ሆኖም በኀጢአት ምክንያት ተወሰደ::

8፥1 እስካሁን ድረስ የጥፋት ውሃ ታሪክ የፍርድ ታሪክ ነበር፤ ከዚህ ጀምሮ ግን የድነት (መዳን) ታሪክ ሆኖ ይቀጥላል:: *እግዚአብሔር ኖኅን ... አሰበ፡* ከ7፥16 ወዲህ ስሙ ባይጠቀስም ወይም ለአንድ መቶ አምሳ ቀን ያህል ድምፁ ባይሰማም (7፥24 ይመ) እግዚአብሔር ኖኅንና ቤተ ሰቡን አልረሳም:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ "አሰበ" ማለት ያለፈውን በአእምሮ መልሶ አስታወሰ ማለት ብቻ አይደለም:: ነገር ግን ከፍቅር የተነሣ ለአንድ ሰው እንክብካቤ አደረገ ማለት ነው:: እግዚአብሔር ሕዝቡን ባሰበ ጊዜ ለሕዝቡ መልካም ነገር በማድረግ ፍቅሩን ይገልጻል (ነህ 5፥19፤ 13፥31):: *ነፋስ፤* በ1፥2 ላይ "መንፈስ" ተብሎ የተተረጐመው የዕብራይስጥ ቃል በዚህ ቦታ "ነፋስ" ተብሎአል፤ ይህም በም 1 እና ከ8-9 ባሉት ምዕራፎች መካከል ያሉ ድርጊቶች በሥነ ጽሑፋዊ ቅርጻቸው ተጓዳኝነት እንዳላቸው ያሳያል፤ ለዚህም 8፥2ን ከ1፥7 ጋር፤ 8፥5ን ከ1፥9 ጋር፤ 8፥7ን ከ1፥20 ጋር፤ 8፥17ን ከ1፥25 ጋር፤ 9፥1ን ከ1፥28 ጋር፤ 9፥2ን ከ1፥28 ጋር፤ 9፥3ን ከ1፥30 ጋር ያነጻጽሩ:: ም 1 የሥነ ፍጥረትን መጀመሪያ ሲያብራራ፣ ከ8-9 ያሉት ምዕራፎች ደግሞ ከጥፋት ውሃ በኋላ ያለውን አዲሱን ጅማሬ ይገልጻሉ::

8፥4 *አራራት፡* ይህ ስም ኡራርቱ ከምትባል የአሦር ግዛት ጋር የሚዛመድ ሲሆን፣ ግዛቲቱም ተራራማ የሆነች ናት፤ ኡራርቱ ሰሜኑን የመስጴጦምያ ግዛት (ኤር 51፥27 ይመ፤ እንዲሁም ኢሳ 37፥38 ይመ) እና የአሁኗን ቱርክ ምሥራቃዊ ክፍል የሚያጠቃልል ነው፤ የኖኅ መርከብ በደቡባዊ ኡራርቱ ላይ ሳታርፍ እንደማትቀር ይገመታል:: *ተራሮች፡* ቃሉ በብዙ ቍጥር የገባና የተራራ ሰንሰለትን የሚያመለክት ነው::

እስከ ዐሥረኛው ወር ድረስ እየቀነሰ መጣ፤
በዐሥረኛው ወር፣ በመጀመሪያው ቀን የተ
ራሮቹ ጫፎች ታዩ::
6ከአርባ ቀን በኋላ ኖኅ የሠራውን የመር
ከቧን መስኮት ከፍቶ፣ 7ቍራን ወደ ውጭ
ላከ፤ ቍራውም ውሃው ከምድር ላይ እስኪ
ደርቅ ድረስ ወዲያና ወዲህ ይበር ነበር::
8ከዚያም በኋላ፣ ኖኅ ውሃው ከምድር ገጽ
ጐድሎ እንደ ሆነ ለማወቅ ርግብን ላከ፤
9ነገር ግን ውሃው የምድርን ገጽ ገና እንደ
ሸፈነ ስለ ነበር፣ ተመልሳ ኖኅ ወዳለበት
መርከብ መጣች፤ እርሱም እጁን ዘርግቶ
ተቀበላት፤ ወደ መርከቢቱም አስገባት:: 10ሰባት
ቀን ከቈየ በኋላ ኖኅ ርግቧን እንደ ገና
ላካት:: 11እርሷም ወደ ማታ ተመለሰች፤
እነሆም የለመለመ የወይራ ቅጠል በአፏ ይዛ
ነበር፤ ያን ጊዜ ኖኅ ውሃው ከምድር ላይ
መጕደሉን ዐወቀ:: 12ሰባት ቀንም ቈይቶ
ርግቧን እንደ ገና ላካት፤ በዚህ ጊዜ ግን
ርግቧ ወደ እርሱ አልተመለሰችም::
13ኖኅ በተወለደ በ601ኛው ዓመት፣ በመ
ጀመሪያው ወር፣ ከወሩም በመጀመሪያው
ቀን ውሃው ከምድር ላይ ደረቀ:: 14ኖኅ
በመርከቡ ላይ ያለውን ክዳን አንሥቶ ተመ
ለከተ፤ የመሬቱም ገጽ እንደ ደረቀ አየ::
በሁለተኛው ወር፣ በሃያ ሰባተኛው ቀን ምድ
ሪቱ ሙሉ በሙሉ ደረቀች::
15ከዚያም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ኖኅን እንዲህ
አለው፤ 16“አንተና ሚስትህ፣ ልጆችህና የል
ጆችህ ሚስቶች ከመርከቧ ውጡ:: 17እንዲ
ዋለዱ፣ እንዲራቡና በምድር ላይ እንዲበዙ፣
ከአንተ ጋር ያሉትን እንስሳትና በምድር ላይ
የሚሳቡ ሕያዋን ፍጡራንን ሁሉ ይዘሃቸው
ውጣ::”
18ኖኅም ከልጆቹ፣ ከሚስቱና ከልጆቹ ሚስ
ቶች ጋር ወጣ:: 19እንስሳቱ ሁሉ፣ ወፎችም፣
በምድር የሚንቀሳቀሱ ሁሉ በየወገናቸው
ከመርከቧ ወጡ::
20ከዚያም ኖኅ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) መሠ
ዊያ ሠራ፤ መሠዊያው ላይ ንጹሕ ከሆኑት
እንስሳት ሁሉ፣ እንዲሁም ንጹሕ ከሆኑት
ወፎች የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ፤ 21“እግ
ዚአብሔርም (ያህዌ) ደስ የሚያሰኘውን መዐዛ
አሸተተ፤ በልቡም እንዲህ አለ፤ “ምንም
እንኳ ሰው ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ሐሳቡ ወደ
ክፋት ያዘነበለ ቢሆንም[ˊ] በእርሱ ምክንያት
ሁለተኛ ምድርን አልረግማትም፤ አሁን እን
ዳደረግሁት ሕያዋን ፍጡራንን ዳግመኛ
አላጠፋም::

22“ምድር እስካለች ድረስ፣
የዘር ወቅትና መከር፣
ሙቀትና ቅዝቃዜ
በጋና ክረምት፣
ቀንና ሌሊት፣
አይቋረጡም::”

## እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር የገባው ኪዳን

9 እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ኖኅንና ልጆቹን እን
ዲህ ሲል ባረካቸው፤ “ብዙ ተባዙ፤ ምድ
ርንም ሙሏት፤ 2አስፈሪነታችሁና አስደንጋ
ጭነታችሁ በዱር አራዊት፣ በሰማይ አዕ
ዋፍ፣ በደረት በሚሳቡ ተንቀሳቃሽ ፍጡሮ
ችና በባሕር ዓሦች ሁሉ ላይ ይሁን፤ በእ
ጃችሁ ተሰጥተዋል:: 3ሕያውና ተንቀሳቃሽ
ፍጡር ሁሉ ምግብ ይሁናችሁ፤ ለምለሙን

ˊ21 ወይም ስለሆነ

8፥6 ዘፍ7፥12
8፥7 ቍ11፤ዘሌ11፥15፤ዘዳ14፥14፤1ነገ17፥4፡6፤ኢዮ38፥41፤መዝ147፥9፤ምሳ30፥17፤ኢሳ34፥11፤ሉቃ12፥24
8፥8 ኢዮ30፥31፤መዝ55፥6፤74፥19፤መኃ2፥12፡14፤ኢሳ38፥14፤59፥11፤60፥8፤ኤር48፥28፤ሕዝ7፥16፤ሆሴ7፥11፤11፥11፤ናሆ2፥7፤ማቴ3፥16፤10፥16፤ዮሐ1፥32
8፥11 ቍ7
8፥13 ዘፍ5፥32
8፥14 ዘፍ7፥11
8፥16 ዘፍ7፥13
8፥17 ዘፍ1፥22
8፥18 1ጴጥ3፥20፤2ጴጥ2፥5
8፥20 ዘፍ7፥8፤12፥7-8፤13፥18፤22፥2፡9፤13፤26፥25፤33፥20፤35፥7፤ዘፀ10፥25፤17፥15፤20፥24፤24፥4፤40፥29፤ዘሌ1፥3፤4፥29፤6፥8-3፤ዘኍ6፥11፤መሳ6፥26፤11፥31፤ሳሙ20፥29፤ኢዮ1፥5፤42፥8
8፥21 ዘፍ3፥17፤6፥5፤9፥11፡15፤ዘፀ29፥18፡25፤ዘሌ1፥9፡13፤2፥9፤4፥31፤ዘኍ15፥3፡7፤መዝ51፥5፤ኢሳ54፥9፤ኤር17፥9፤44፥11፤ማቴ15፥19፤ሮሜ1፥21፤2ቆሮ2፥15
8፥22 ዘፍ1፥14፤ኢሉ3፥15፤መዝ67፥6፤74፥17፤ኤር5፥24፤ዘካ14፥8
9፥1 ዘፍ1፥22
9፥2 ዘፍ1፥26
9፥3 ዘፍ1፥29፤

8፥6 *መስኮት*፤ የ6፥16 ማብ ይመ::

8፥11 *እርሷም ወደ ማታ ተመለሰች፤ እነሆም የለመለመ የወይራ ቅጠል በአፏ ይዛ ነበር*፤ የወይራ ዛፍ በደጋ ወይም ከፍ ባለ ቦታ ስለሚበቅል ርግቢቱ ይዛ የተመለሰችው የለመለመ የወይራ ቅጠል፣ ውሃው መጕደሉን የሚያሳይ ምልክት ነበር:: በአሁኑ ጊዜ ሰላምን ለመግለጽ ሰዎች የሚጠቀሙበት ምልክት በአፏ የወይራ ቅጠል የያዘች ርግብ ሲሆን፣ ይህም ከዚህ ታሪክ ጋር የተገኘ ምሳሌያዊ ድርጊት ነው::

8፥13 *ኖኅ በተወለደ በ601ኛው ዓመት፣ በመጀመሪያው ወር፣ ከወሩም በመጀመሪያው ቀን*፤ ይህ የቀን አቈጣጠር ከጥፋት ውሃ በኋላ የሰውን ልጅ አዲስ ጅማሬ ያመለክታል::

8፥14 *በሁለተኛው ወር፣ በሃያ ሰባተኛው ቀን*፤ የጥፋት ውሃ ከአንድ ዓመት በላይ በምድር ላይ ቈይቶአል (7፥11 ይመ)::

8፥16 *ከመርከቧ ውጡ*፤ የ7፥1 ማብ ይመ::

8፥17 *እንዲዋለዱ፣ እንዲራቡና በምድር ላይ እንዲበዙ*፤ 1፥22 እና ማብ ይመ:: እንስሳትና አዕዋፍ እንደየወገናቸው እንደ ገና ተባዙ::

8፥20 *እግዚአብሔር*፤ አምልኮ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የግል ጕዳይ ስለ ሆነ፣ ኖኅ መሥዋዕቱን ያቀረበው ለእግዚአብሔር አምላክ ነው (የ2፥4 ማብ ይመ):: *የሚቃጠል መሥዋዕት*፤ ዘሌ 1፥4 ይመ::

8፥21 *እግዚአብሔርም ደስ የሚያሰኘውን መዐዛ አሸተተ*፤ እግዚአብሔር፣ ልጆቹ እርሱን ሲያመልኩ ምን ያህል ደስ እንደሚለው የሚያመለክት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው (ኤፌ 5፥2፤ ፊል 4፥18 ይመ)፣ *ምንም እንኳን ሰው ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ሐሳቡ ወደ ክፋት ያዘነበለ ቢሆንም*፤ ተመሳሳይ ለሆነ አገላለጽ 6፥5 ይመ:: የሰው ልጅ ክፋት እጅግ ብዙ ከመሆኑ የተነሣ እግዚአብሔር የጥፋት ውሃን በማምጣት (6፥17) የሰውን ዘር ከምድረ ገጽ አጠፋ (6፥7)፤ ጻድቁ ኖኅና ቤተ ሰቡ ከጥፋት ውሃ ቢተርፉም፣ የአዳም ዘር በመሆናቸው የውርስ ኀጢአት በልባቸው ይዘዋል:: እግዚአብሔር ከምሕረቱ የተነሣ በሰው ኀጢአት ምክንያት እንዲህ ዐይነቱን አስከፊ የጥፋት ውሃ ዳግመኛ እንደማያመጣ ቃል ገባ (9፥11፡15 ይመ):: የሰው ልጅ ታሪክ፣ እግዚአብሔር አዲስና ቤዛዊ በሆነ መንገድ ይሳተፍበት ዘንድ ክፍት ሆነ፤ ይህም አዲስና ቤዛዊ ተሳትፎ የባቢሎንን ግንብ በማፈራረስና (የ11፥6፡8 ማብ ይመ) አብርሃምን በመጥራት በተግባር ታየ (12፥1):: *ከልጅነቱ ጀምሮ*፤ ይህ ሐረግ በ6፥5 ላይ፣ “ዘወትር” የሚለውን ቃል የሚተካ ሲሆን፣ ኀጢአት ከጽንስ ጀምሮ የሰውን ልጅ ሕይወት የሚበክል መሆኑን ያመለክታል (መዝ 51፥5፤ 58፥3):: *ምድርን አልረግማትም*፤ ዕብራይስጡ በዚህ ስፍራ፣ “አልረግማትም” ለሚለው የተለየ ቃል ቢኖረውም፣ ቃሉ በ3፥17 የተጠቀሰውን ርግማን ያመለክታል:: እዚህ ላይ ምናልባት ቃየንም እንደ ተረገመ ሁሉ፣ (4፥12) በርግማን ላይ ርግማን ላለመጨመር እግዚአብሔር ቃል መግባቱን ያመለክታል::

8፥22 ጊዜና ወቅት በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ተፈጠሩ (1፥14)፤ *ታሪክ እስኪያበቃና እስኪፈጸም አያልፉም*::

9፥1-7 በዚህ አዲስ *መጀመሪያ*፣ እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ቡራኬና (1፥28) ለሰው ልጆችም ምግባቸውን ለመስጠት የገባውን ቃል አደሰ (ከቍ 3፤1፥29-30 ጋር ያነጻጽሩ):: ኀጢአት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ብጥብጥን ስላስከተለ እግዚአብሔር የሰው ልጆች ከሚበሉት ምግብ ውስጥ ሥጋ አንዱ እንዲሆን ስለ ወሰነ (ቍ 3)፣ ተጨማሪ መለኮታዊ ትእዛዝ መስጠት አስፈላጊ ሆነ (ቍ 4-6):: ይህም ሆኖ የእግዚአብሔር ቡራኬ በሁሉ ላይ ጐልቶ የሚታይና ሁሉን የሚያቅፍ ነው (ቍ 7 ይመ)::

9፥2 *በእጃችሁ ተሰጥተዋል*፤ የሰው ልጅ፣ የእንስሳትና የፍጥረት ሁሉ አዛዥ (ገዥ) መሆኑን እግዚአብሔር በድጋሚ አረጋገጠ (የ1፥26 ማብ ይመ)::

9፥3 *ሕያውና ተንቀሳቃሽ ፍጡር ሁሉ ምግብ ይሁናችሁ*፤ ሥጋም ለሰው ልጆች ተጨማሪ ምግብ እንዲሆን ተደረገ::

ዕፀዋት እንደ ሰጠኋችሁ፣ አሁን ደግሞ ሁሉን
ሰጠኋችሁ::
4“ነገር ግን ሕይወቱ፣ ማለት ደሙ ገና
በውስጡ ያለበትን ሥጋ አትብሉ:: 5ሰውን
የገደለ ሁሉ ስለሚቹ ደም ተጠያቂ ነው፤
የሚቹን ሰው ደም ከገዳዩ፣ ከእንስሳም ይሁን
ከሰው እሻለሁ::

6“የሰውን ደም የሚያፈስ ሁሉ፣
ደሙ በሰው እጅ ይፈሳል፤
በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) አምሳል፣
እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰውን
ሠርቶታልና::
7እናንተ ግን ብዙ ተባዙ፤ ዘራችሁ በም
ድር ላይ ይብዛ፤ ይንሠራፉ::”
8እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ኖኅንና አብረውት ያሉ
ትን ልጆቹን እንዲህ አላቸው፤ 9“እነሆ፤ ከእ
ናንተና ከእናንተ በኋላ ከሚመጣው ዘራችሁ
ጋር ኪዳኔን እመሠርታለሁ፤ 10እንዲሁም ከእ
ናንተ ጋር ከነበሩት ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ:-
ከወፎች፣ ከቤት እንስሳት፣ ከዱር እንስሳት፣
ከእናንተ ጋር ከመርከቧ ከወጡት በምድር ላይ
ካሉት ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ጋር ኪዳን እገባ
ለሁ:: 11ከእንግዲህ ሕይወት ያለው ፍጡር
ሁሉ በጥፋት ውሃ እንደማይጠፋ፣ ዳግመኛም
ምድርን የሚያጠፋ ውሃ ከቶ እንደማይመጣ
ከእናንተ ጋር ኪዳን እገባለሁ::”
12እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) እንዲህ አለ፤ በእ
ኔና በእናንተ መካከል፣ ከእናንተም ጋር
ካሉ ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ጋር ከሚመጣ
ውም ትውልድ ሁሉ ጋር፣ የማደርገው የኪ
ዳኑ ምልክት ይህ ነው፤ 13ቀስተ ደመናዬን

ሐሥ10፥15፤ቆላ2፥16
9፥4 ዘሌ3፥17፤7፥26፤17፥10-14፤19፥26፤ዘዳ12፥16:23-25፤15፥23፤1ሳሙ14፥33፤ሕዝ33፥25፤ሐሥ15፥20:29
9፥5 ዘፍ4፥10፤42፥22፤50፥15፤ዘፀ21፥28-32፤1ነገ2፥32፤2ዜና24፥22፤መዝ9፥12
9፥6 ዘፍ1፥26፤4፥14፤መሳ9፥24፤ማቴ26፥52
9፥7 ዘፍ1፥22
9፥9 ቍ11፤ዘፍ6፥18
9፥11 ቍ9:16፤ዘፍ8፥21፤ኢሳ24፥5፤33፥8፤ሆሴ6፥7
9፥12 ቍ17፤17፥11:12፤ዘፀ12፥14፤ዘሌ3፥17፤6፥18፤17፥7፤ዘኍ10፥8
9፥13 ቍ14፤ሕዝ1፥28፤ራእ4፥3፤10፥1
9፥14 ቍ13
9፥15 ዘፍ8፥1:21፤ዘፀ2፥24፤6፥5፤34፥10፤ዘሌ26፥42:45፤ዘዳ7፥9፤መዝ89፥34፤103፥18፤105፥8፤106፥45፤ሕዝ16፥60
9፥16 ቍ11:13፤ዘፍ17፥7:13:19፤2ሳሙ7፥13፤23፥5፤መዝ105፥9-10፤ኢሳ9፥7፤54፥10፤55፥3፤59፥21፤61፥8፤ኤር31፥31-34፤32፥40፤33፥21፤ሕዝ16፥60፤37፥26፤ዕብ13፥20
9፥17 ቍ12

በደመና ላይ አደርጋለሁ፤ ይህም በእኔና
በምድር መካከል ለገባሁት ኪዳን ምልክት
ይሆናል:: 14ደመናን በምድር ላይ በጋረድ
ሁና ቀስቴም በደመና ላይ በሚታይበት ጊዜ
ሁሉ፣ 15ከእናንተና ከሕያዋን ፍጡራን ሁሉ
ጋር የገባሁትን ኪዳን አስባለሁ፤ ሕይወት
ያለውንም ሁሉ ያጠፋ ዘንድ፣ ከእንግዲህ
የጥፋት ውሃ ከቶ አይመጣም:: 16ቀስቱ
በደመና ላይ ተገልጦ በማይበት ጊዜ ሁሉ፣
በእኔና በምድር ላይ ባሉ ሕያዋን ፍጡራን
መካከል ያለውን ዘላለማዊ ኪዳን አስባለሁ::”
17ስለዚህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ኖኅን፣ “ይህ
በእኔና በምድር ላይ በሚኖሩ ሕያዋን ሁሉ
መካከል የገባሁት ኪዳን ምልክት ነው” አለው::

## የኖኅ ልጆች

18ከመርከቧ የወጡትም የኖኅ ልጆች ሴም፣
ካምና ያፌት ነበሩ፤ ካም የከነዓን አባት
ነው:: 19ሦስቱ የኖኅ ልጆች እነዚህ ሲሆኑ፣
በምድር ላይ የሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ የተገ
ኙት ከእነዚሁ ነው::
20ኖኅ ገበሬ ነበረና ወይን ተከለ፤[T] 21ከወ
ይኑም ጠጅ ጠጥቶ ሰከረና በድንኳኑ ውስጥ
ዕርቃኑን ተኛ:: 22የከነዓን አባት፣ ካም የአባቱን
ዕርቃን ሥጋ አየ፤ ወደ ውጭም ወጥቶ ለሁ
ለቱ ወንድሞቹ ነገራቸው:: 23ሴምና ያፌት
ግን ልብስ ወስደው በጫንቃቸው ላይ አደ
ረጉና የአባታቸውን ዕርቃን ሥጋ እንዳያዩ
ፊታቸውን አዙረው የኋሊት በመሄድ የአባታ
ቸውን ዕርቃን ሥጋ ሸፈኑ::

9፥18 ቍ25-27፤ዘፍ5፥32፤10፥6:15፤ሉቃ3፥36 9፥19 ዘፍ1፥22፤5፥32፤10፥32፤11፥4:8:9 9፥21 ዘፍ19፥35 9፥22 ዕን2፥15
[T]20 ወይም *የመጀመሪያ ነበር*

9፥4 *ሕይወቱ፣ ማለት ደሙ ገና በውስጡ ያለበትን ሥጋ አትብሉ፤* ዘሌ 17፥14 ደግሞ፣ “የፍጡር ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና” በማለት በደምና በሕይወት መካከል ያለውን የጠበቀ ግን ኙነት በአጽንዖት ይገልጻል:: ሕይወት የእግዚአብሔር ውድና ምስጢራዊ ስጦታ ነች፤ የሰው ልጅ፣ “በደም ውስጥ” (ዘሌ 17፥11) የሚገኘውን “ሕይወት” በመብላት ሕይወቱን ለማቈየ ትም ሆነ ዕድሜውን ለማራዘም መሞከር የለበትም፤ አያሌ ጣዖት አምላኪ ሕዝቦች ደምን በመብላት ሕይወትን ማቈየትና ዕድሜን ማራዘም ይቻላል የሚል እምነት ነበራቸው::

9፥5 *ሰውን የገደለ... ተጠያቂ ነው፤ የሚቹን ሰው ደም ከገዳዩ ከእንስሳም ይሁን ከሰው እሻለሁ፤* የሰው ሕይወት ታላቁ ተሟጋች እግዚአብሔር ራሱ ነው (4፥9-12 ይመ)፤ ሰው በእግዚ አብሔር አምሳል (ቍ 6) የተፈጠረ በመሆኑ፣ በእግዚአብሔር ፊት ክቡር ነው፤ ደግሞም በምድር ላይ የእግዚአብሔር ተወካይና የእግዚአብሔርም መንግሥት ዋና ትኵረት ነው:: በሲና ተራራ ላይ በጸናው የእግዚአብሔር አገዛዝ መሠረት አንድ የቤት እንስሳ ሰው ከገደለ በድንጋይ ተወግሮ ይገደል ነበር (ዘፀ 21፥28-32)::

9፥6 *የሰውን ደም የሚያፈስስ ሁሉ፣ ደሙ በሰው እጅ ይፈሳል፤* እግዚአብሔር ራሱ ሕዝቡን በሚያስተዳድርበት በኋለ ኞቹ ዘመናት ሰውን ሆን ብለው የሚገድሉ ሰዎች በሞት እንዲ ቀጡ ይደረግ ነበር (ዘፀ 21፥12-14፤ ዘኍ 35፥16-35፤ እንዲሁም ሮሜ 13፥3-4፤ 1ጴጥ 2፥13-14 ይመ):: *በእግዚአብሔር አምሳል እግዚአብሔር ሰውን ሠርቶታልና፤* 1፥26 እና ማብ ይመ:: አንድ ነፍሰ ገዳይ ሰውን በመግደሉ፣ እግዚአብሔርን እንዲሁም ባልንጀ ራውን መናቁን ያሳያል::

9፥9 *ኪዳን እመሠርታለሁ፤* እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ያለው ዐላማ ሙሉ በሙሉ እውን እስኪሆን ድረስ (“ምድር እስካለች ድረስ” 8፥22) ሰውንና ምድርን ዳግመኛ ላያጠፋ ለኖኅ ዘሮችና ለሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ቃል ኪዳን እንደገባ የሚያሳይ ነው (ለሰው ዘር ሁሉ አዲስ አባት ለሆነው ለጻድቁ ኖኅ የተበረከተ ስጦታ ነው):: በተ መሳሳይ ሁኔታ እግዚአብሔር ከአብራም (15፥18-20)፣ ከፊንሐስ እና (ዘኍ 25፥10-13) ከዳዊት ጋር (2ሳሙ 7) የገባውን ቃል ኪዳን ይመ:: በገጽ 18 ላይ፣ “በብሉይ ኪዳን የተደረጉ/የተገቡ ዋና ዋና ኪዳኖች” የሚለውን ይመ::

9፥11 *ከእንግዲህ ሕይወት ያለው ፍጡር ሁሉ በጥፋት ውሃ እንደማይጠፋ፣* ይህ ሐረግ “ከእንግዲህ... ከቶ” (ቍ 11:15)፣ “ትውልድ ሁሉ ጋር የማደርገው” (ቍ 12) እና “ዘላለማዊ” (ቍ 16) በሚሉት ቃላትና ሐረጐች እንደ ተገለጸው፣ እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር ያደረገው ዘላለማዊ ኪዳን ማጠቃለያ ሐሳብን የያዘ ነው::

9፥12 *ምልክት፤* የቃል ኪዳን ምልክት የሚታይ ማኅተም ሲሆን፣ በኪዳኑ የተገባውን ውል የሚያስታውስ ነው:: ግዝረት ከአብርሃም ጋር ለተገባው ቃል ኪዳን (17፥11 ይመ)፣ ሰንበት ደግሞ ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር በሲና ለተገባው ቃል ኪዳን ምል ክት ነው (ዘፀ 31፥16-17 ይመ)::

9፥13 *ቀስተ ደመናዬን፤* ዝናብና ቀስተ ደመና በኖኅ ዘመን ከተከሠተው የጥፋት ውሃ በፊት እንደ ነበሩ ምንም አያጠራጥርም:: ነገር ግን ቀስተ ደመና ከጥፋት ውሃ በኋላ ለኖኅ ዘር የቃል ኪዳን ምልክት ሆኖአል::

9፥19 *የተገኙት፤* የሕዝቦችን በነገድ በነገድ መከፈል የሚ ያመለክት ነው (የ11፥8 ማብ ይመ)::

9፥20 *ገበሬ፤* ኖኅ እንደ አባቱ እንደ ላሜሕ ገበሬ ነበር (5፥29 ይመ)::

9፥21 *ከወይኑም ጠጅ ጠጥቶ ሰከረና፤* ለመጀመሪያ ጊዜ የወይን ጠጅ ከስካር ጋር ተያይዞ የቀረበው እዚህ ላይ ነው:: *በድ ንኳኑ ውስጥ ዕርቃኑን፤* ከመጠን ያለፈ የወይን ጠጅ መጠጣት ለከፋ ተግባር ያጋልጣል (19፥30-35 ይመ)::

9፥22 *የከነዓን አባት፤* ካም በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሰው የከነዓን (ማለትም የከነዓናውያን፤ የ15፥16 ማብ ይመ) እውነተኛ አባት በመሆን ነው:: *ለሁለቱ ወንድሞቹ ነገራቸው፤* የአባቱን ኀፍረት በመሸፈን ፈንታ ነውሩን በየቦታው አወራ::

9፥23 *እንዳያዩ ፊታቸውን አዙረው፤* በአባታቸው ላይ ሌላ አሳፋሪ ነገር እንዳይደርስ ፈለጉ::

## በብሉይ ኪዳን የተደረጉ/ የተገቡ ዋና ዋና ኪዳኖች

| ኪዳን | ጥቅስ | ዐይነት | አባላት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| ከኖኅ | ዘፍ 9፥8-17 | ንጉሣዊ ቸርነት | "ጻድቅ" ከሆነው ከኖኅ ጋር (6፥9) የተደረገ (ልጆቹ እንዲሁም በምድር ላይ ሕይወት ያለው ነገር ሁሉ) | ተመሳሳይ በሆነ የተፈጥሮ አደጋ በምድር ላይ ሕይወት ያለውን ነገር ላለማጥፋት በሁኔታዎች ላይ ያልተመሠረተ መለኮታዊ ተስፋ ሲሆን፣ የኪዳኑ "ምልክት" ደግሞ ቀስተ ደመና ነው |
| ከአብርሃም ሀ | ዘፍ15፥9-21 | ንጉሣዊ ቸርነት | እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ከተቈጠረለት ከአብርሃምና (ቍ 6) ከልጆቹ ጋር (ቍ 16) የተደረገ | በሁኔታዎች ላይ ያልተመሠረተ፣ ርስትን ለመስጠት የተሰጠ መለኮታዊ ተስፋ |
| ከአብርሃም ለ | ዘፍ 17 | ሱዜራዊ ገባርነት | እንደ ቅድመ አበውነቱና እንደ ቤተ ሰብ መሪነቱ ከአብርሃም ጋር የተደረገ | የአብርሃምና የልጅ ልጆቹ አምላክ ለመሆን በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ኪዳን ነው (ቍ 4 ከቍ 9 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ቅድመ ሁኔታው ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር መለየትን ለማሳየት መገረዝ ነበር:: |
| በሲና የተደረገ | ዘፀ 19-24 | ሱዜራዊ ገባር መንግሥት | የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ ልጆች ከሆኑትና እግዚአብሔር ከምድራዊ ኀይላት እጅ ዐርነት ካወጣው ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የተደረገ | እንደ ጠባቂዋና ወደ በረከት ርስቷ የሚያደርሳት የእስራኤል አምላክ ለመሆን በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ኪዳን፤ ቅድመ ሁኔታው እስራኤል በእግዚአብሔር ሕግ የምትኖርና ዐላማውን የምታገለግል ለእርሱም የተለየ ሕዝብ (የእርሱ መንግሥት) ሆና መገኘት ነው:: |
| ከፊንሐስ | ዘኍ25፥10-13 | ንጉሣዊ ቸርነት | ለእግዚአብሔር ከሚቀናው ከካህኑ፣ ፊንሐስ ጋር የተደረገ | የፊንሐስ ዘር የክህነት አገልግሎት ዘላቂነት እንደሚኖረው የተገባና በሁኔታዎች ላይ ያልተመሠረተ (በውስጡም እስራኤል ለዘላለም ታማኝ ካህን እንደሚኖራት የሚያሳይ) ኪዳን ነው |
| ከዳዊት | 2ሳሙ 7፥5-16 | ንጉሣዊ ቸርነት | የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን ዳዊት ከተመረጠ በኋላ ታማኝ ከመሆኑ የተነሣ የተደረገ | በእስራኤል ዙፋን ላይ የዳዊትን ሥርወ መንግሥት ለመመሥረትና ለማጽናት፤ ለእስራኤል እንደ ዳዊት ያለ እግዚአብሔርን የሚፈራ ንጉሥ ለመስጠትና በዚህ ሥርወ መንግሥትም በዳዊት ዘመን እግዚአብሔር ምድሪቱን እንዳሳረፈ አሁንም ለማሳረፍ በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ መለኮታዊ ኪዳን (1ነገ 4፥20-21፤ 5፥3-4) |
| አዲስ | ኤር 31፥31-34 | ንጉሣዊ ቸርነት | ዐመፀኛዋ እስራኤል በኪዳኑ መሠረት ከተስፋዪቱ ምድር ከመወገዷ በፊት የተገባላት ኪዳን | ታማኝ ያልሆነችው እስራኤል፣ ኀጢአቷን ይቅር እንደሚላትና በአዲስ መሠረት ከእርሷ ጋር ግንኙነት እንደሚጀምር ያስታወቀበትና የጸጋ ኪዳን የሆነውን ሕግ 'በልባቸው ላይ" እንደሚጽፍ የተነገረበት ነው |

## በጥንታዊው የቅርብ ምሥራቅ አካባቢ የነበሩ ዋና ዋና ንጉሣዊ የኪዳን/ስምምነት ዐይነቶች

**ንጉሣዊ ቸርነት (በሁኔታዎች ላይ ያልተመሠረተ)**

ታማኝ የሆነ አገልጋይ ስለታማኝነቱ ወይም ልዩ ስለ ሆነ አገልግሎቱ ከንጉሥ የሚደረግ የርስት ወይም የተለየ ስጦታ ነው:: ስጦታው በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ባይሆንም፣ የዚህ አገልጋይ ወራሾች እንደ እርሱ በታማኝነት እስከተገኙ ድረስ ብቻ የሚጠቀሙበት ነው (ከ1ሳሙ 8፥14፤ 22፥7፤ 27፥6፤ አስ 8፥1 ጋር ያነጻጽሩ)

**አቻ ወገኖች**

እኩል በሆኑ ወገኖች መካከል የሚደረግ፣ ተደጋጋፊ ለሆነ ወዳጅነት ወይም ለሁለቱም ወገን የጋራ ፍላጎት የሚበጅ ኪዳን ነው:: በዚህ ሁኔታ የተያያዙት "ወንድማማቾች" እንደ ሆኑ ተደርገው ይቈጠራሉ (ከዘፍ 21፥27፤ 26፥31፤31፥44-54፤ 1ነገ 5፥12፤ 15፥19፤ 20፥32-34፤ አሞ 1፥9 ጋር ያነጻጽሩ)

**ሱዜራዊ ገባርነት (በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ)**

በታላቅ ንጉሥና በገባሪ ነገሥታት መካከል ያለውን ግንኙነት የሚቈጣጠር ኪዳን ሲሆን፣ ታላቁ ንጉሥ ፍጹም ሉዓላዊ መብት እንዳለው ገባሪውም በፍጹም ታማኝነትና ታዛዥነት አገልግሎት የሚሰጥበት ነው:: ገባሪው በታማኝነት እስከ ቈየ ድረስ፣ ግዛቱና ንግሥናው በታላቁ ንጉሥ እንደሚጠበቅለት የተደረገበት ኪዳን ነው:: ኪዳን የተገባበት "ጌታ" እና "አገልጋይ/ባሪያ" ወይም "አባት" እና "ልጅ" ተብለው ይጠራሉ (ከኢሱ 9፥6፡8፤ ሕዝ 17፥13-18፤ ሆሴ 12፥1 ጋር ያነጻጽሩ)

በእነዚህ ኪዳኖች የሚደረጉ ግዴታዎች፣ በቃል ወይም በአምልኮ ሥርዐት ወይም በሁለቱም መንገዶች የሚደረጉ መሐላዎችን የያዙ ናቸው:: ኪዳን የሚገቡት አማልክቶቻቸውን ለምስክርነትና ኪዳኑን የሚያፈርስ ወገን ካለ የመሐላውን መርገም እንዲፈጽሙባቸው ይጠራሉ::

24ኖኅ ከወይን ጠጁ ስካር ሲነቃ፣ ታናሽ ልጁ ያደረገበትን ዐወቀ፤ 25እንዲህም አለ፤

"ከነዓን የተረገመ ይሁን፤
ለወንድሞቹም፣ የባሪያ ባሪያ ይሁን።"
26ደግሞም፤

"የሴም ስምባከ እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) ይባረክ፤
ከነዓንም የሴም[ሀ] ባሪያ ይሁን።"

27"እግዚአብሔር (ኤሎሂም) የያፌትን[ለ] ግዛት ያስፉ፤
ያፌት በሴም ድንኳኖች ይኑር፤
ከነዓንም የእርሱ[ሐ] ባሪያ ይሁን" አለ።
28ኖኅ ከጥፋት ውሃ በኋላ 350 ዓመት
ኖረ፤ 29ኖኅ በአጠቃላይ 950 ዓመት ኖሮ ሞተ።

## የኖኅ ልጆች ትውልድ

10 የኖኅ ልጆች የሴም፣ የካምና የያፌት ትውልድ ይህ ነው፤ እነርሱም ራሳቸው ከጥፋት ውሃ በኋላ ወንዶች ልጆችን ወለዱ።

### የያፌት ዝርያዎች

10፥2-5 ተጓ ምብ - 1ዜና 1፥5-7

2የያፌት ልጆች:-[መ]
ጋሜር፣ ማጎግ፣ ማዴ፣ ያዋን፣ ቶቤል፣
ሞሳሕ፣ ቴራስ ናቸው።
3የጋሜር ልጆች:-
አስከናዝ፣ ሪፋት፣ ቴርጋማ ናቸው።
4የያዋን ልጆች:-
ኤሊሳ፣ ተርሴስ፣ ኪቲም፣ ሮዳኢ[ሠ] ናቸው።
5ከእነዚህም በየነገዳቸው፣ በየጐሣቸውና በየ
ቋንቋቸው ተከፋፍለው በባሕር ዳርና በደሴ
ቶች፣ በየምድራቸው የሚኖሩ ሕዝቦች ወጡ።

### የካም ዝርያዎች

10፥6-20 ተጓ ምብ - 1ዜና 1፥8-16

6የካም ልጆች:-
ኩሽ፣ ምጽራይም፣ [ረ]ፉጥ፣ ከነዓን ናቸው።
7የኩሽ ልጆች:-
ሳባ፣ ኤውላጥ፣ ሰብታ፣ ራዕማ፣ ሰብቃታ ናቸው።

9፥25 ቍ18፤ዘፍ 25፥23፤27፥12:29: 37:40፤37፥10፤49፥8፤ ዘፀ20፥5፤ዘኍ24፥18፤ ኢሱ9፥23፤መዝ79፥8፤ ኢሳ14፥2፤ኤር31፥29፤32፥18
9፥26 ዘፍ14፥20፤ ዘፀ18፥10፤መዝ7፥17፤ 1ነገ9፥21
9፥27 ዘፍ10፥2-5፤ ኤፌ2፥13-14፤3፥6
9፥29 ዘፍ2፥17
10፥1 ቍ32፤ዘፍ 2፥4፤5፥32፤1ዜና1፥4
10፥2 ኢሳ66፥19፤ ሕዝ27፥13:19፤32፥26 ፤38፥2:6፤39፥1:6፤ ራእ20፥8
10፥3 ኤር51፥27፤ ሕዝ27፥14፤38፥6
10፥4 ዘኍ24፥24፤ መዝ48፥7፤72፥10፤ ኢሳ2፥16፤23፥1:6:10: 12:14፤60፥9፤66፥19፤ ኤር2፥10፤10፥9፤ሕዝ 27፥6:7:12:25፤38፥13 ፤ዳን11፥30፤ዮና1፥3
10፥5 ዘፍ9፥27
10፥6 ዘፍ9፥18፤2ነገ 19፥9፤2ዜና12፥3፤16፥8፤ኢሳ11፥11፤18፥1፤ 20፥3፤43፥3፤ኤር46፥9፤ ሕዝ27፥10፤30፥4:9፤38፥5፤ናሆ3፥9፤ሶፎ2፥12፤3፥10
10፥7 ዘፍ2፥11፤ 25፥3፤1ነገ10፥1፤1ዜና1፥32፤2ዜና9፥1፤ኢዮ1፥15፤6፥19፤16፥11፤መዝ 72፥10:15፤ኢሳ21፥13፤43፥3፤60፥6፤ኤር6፥20፤25፥23-24፤49፥8፤ 38፥13፤ሕዝ27፥15:20:22፤38፥13፤ኢል3፥8

[ሀ]26 ወይም የእርሱ ባሪያ ይሁን
[ለ]27 ያፌት የሚለው ቃል መዘርጋት የሚል ትርጉም ካለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው
[ሐ]27 ወይም የእነርሱ
[መ]2 ልጆች ማለት ዘር ትውልዶች ወይም ወራሾች ወይም ሕዝቦች ማለት ሊሆን ይችላል፤ በቍ 3:4:6:7:20-23: 29 እና 31 እንዲሁ
[ሠ]4 ጥቂት የማሶሬቲክ የጥንት ጽሑፎች፣ ከአሪተ ሳምራውያን፣ ሰብዐ ሊቃናትና አብዛኞቹ የማሶሬቲክ የጥናት ጽሑፎች የሚሉት ዶዳኒም ነው
[ረ]6 ቍ13ትንም ጨምሮ ግብፅን ያመለክታል

9፥25 *ከነዓን የተረገመ ይሁን፤* የካም ልጅ (ቍ 18:22 ይመ) የተቀጣው በአባቱ ኀጢአት እንደ ሆነ አንዳንዶች ይናገራሉ (ዘፀ 20፥5 ይመ)፤ ነገር ግን ዘፀ 20 እንደሚያሳየው እንዲህ ያለው ቅጣት የሚደርሰው "እግዚአብሔርን በሚጠሉ" ሰዎች ላይ ነው። ከነዓንና ዘሮቹ የተቀጡት ክፋታቸው ከካምም እንኳ የሚበልጥ ሆኖ ስለሚገኝ (ዘሌ 18፥2-3:6-30) ነው ብሉ መገመቱ የተሻለ ነው። *የባሪያ ባሪያ፤* ኢያሱ የገባዖንን ሰዎች ባሪያ ማድረጉ (ኢሱ 9፥27) የትንቢቱን ፍጻሜ ያመለክታል (ኢሱ 16፥10፤ መሳ 1፥28: 30:33:35፤ 1ነገ 9፥20-21 ይመ)። እዚህ ላይ የተረገሙት የቀውቃዛውያን (ካውኬዚያን) ዘሮች የሆኑት ከነዓናውያን በመሆናቸው፣ የኖኅ ትንቢት ጥቁሮችን ለመግዛትና ባሪያ ለማድረግ በሚያመች መልኩ ሊወሰድ አይችልም።

9፥26 *እግዚአብሔር ይባረክ፤* እግዚአብሔር ለሴም የበረከት ምንጭ በመሆኑ ከሴም ይልቅ የተባረከ ነው። እንደዚሁም እግዚአብሔር የሴምና የዘሮቹ (ማለትም እስራኤላውያንን የሚጨምረው የሴማውያን) አምላክ ነው።

9፥27 *በሴም ድንኳኖች ይኑር፤* ለሴም የፈሰሰውን በረከት ይካፈል ማለት ነው።

9፥29 *ሞተ፤* የ5፥5 ማብ ይመ። ኖኅ በሴም የትውልድ ሐረግ ውስጥ ዐሥረኛና የመጨረሻ እንደ መሆኑ (5:3-32)፣ መልካም ስም እንዳላቸው እንደ አባቶቹ ለእርሱም አሟሟቱን የሚገልጽ ታሪክ ተጻፈለት።

10፥1 *ትውልድ፤* የ2፥4 ማብ ይመ። በዚህ ቦታ የተጠቀሰው የትውልድ ዝምድና ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ የዘር ሐረግ ላይ የተመሠረተ ብቻ ሳይሆን መልክዐ ምድራዊ፣ ታሪካዊና የቋንቋ ሁኔታንም የሚያጠቃልል ነው (የቍ 5 ማብ ይመ፤ እንዲሁም የቍ 2:8፤ 11፥10 አማራጭ ትርጕም ይመ) እንዲሁም በ1ኛ ዜና መግቢያ ላይ "የዘር ሐረግ" የሚለውን ይመ።

10፥2 *ያፌት፤* በታሪክ ውስጥ ያለው ተሳትፎ ዝቅተኛ በመሆኑና ምናልባትም ይህ ክፍል ከቍ 21 ጋር ሲታይ ያፌት የኖኅ የመጀመሪያ ልጅ በመሆኑ ዘሮቹ በቅድሚያ ተጠቅሰዋል። የተመረጠው የሴም የዘር ሐረግ ግን ከምዕራፉ በስተ መጨረሻ ይገኛል (ቍ 21-31 ይመ እንዲሁም 11፥10-26 ይመ)። ከያፌት ዘር የተገኙት 14 ነገዶች፣ ከካም ዘር የተገኙት 30 ነገዶችና ከሴም ዘር የተገኙት 26 ነገዶች በአንድነት ሲደመሩ 70 ነገዶች ይሆናሉ (የ10 እና 7 ብዜት 70 ሲሆን፣ ሁለቱም ቍጥሮች ፍጹምነትን ወይም ሙሉነትን ያመለክታሉ፤ የ5፥5 ማብ ይመ)። ይህም በግብፅ የነበረውንና 70 ሰዎችን የያዘውን የያዕቆብን ቤተ ሰብ ሳያመለክት አይቀርም። ያፌታውያን ከፓሌስቲና በስተ ሰሜንና በስተ ምዕራብ በሚገኘው የአውሮፓና የእስያ ምድር ይኖሩ ነበር። *ጋሜር፤* የጋሜር ሕዝቦችና ነገዶች በጥቁር ባሕር አካባቢ ይኖሩ ነበር (በኋላ ሲሜራውያን ወይም ጋሜራውያን ተብለዋል ቍ 3 ይመ)። *ማጎግ፤* የሲቲያን ሕዝቦች አባት ሊሆን ይችላል፤ ይኖሩ የነበሩትም ከጥቁር ባሕር በስተ ደቡብ ምሥራቅ ነበር። *ማዴ፤* በኋላ ሜዶስ የተባሉት ናቸው። *ያዋን፤* ምናልባት በትንሿ እስያ በስተ ምዕራብ (ደቡባዊ ግሪክ) የሚኖሩ ናቸው። *ቶቤል፣ ሞሳሕ፤* በአሁኗ ሩሲያ ከሚገኙት ከቶቦልስካና ከሞስኮ ጋር ምንም ዝምድና የላቸውም። ቶቤልና ሞሳሕ እንዲሁም ማጎግ በጥንት የአሦራውያን መዝገብ ላይ ተጠቅሰዋል። በተጨማሪም ሕዝ 38፥2 ይመ። ምናልባት ቶቤል በፋንጡስ፣ ሞሳሕ ደግሞ በሞሺያን ተራሮች ላይ ሳይኖሩ አይቀሩም። የፈለሱትም ከትንሹ እስያ ደቡብ ምሥራቅ ተነሥተው ወደ ጥቁር ባሕር ነው። *ቴራስ፤* ከጊዜ በኋላ "ትራስ" ተብሉአል።

10፥3 *አስከናዝ፤* በኋላ ሲቲያውያን ተባሉ፤ በዚህ ቍጥር ላይ የተመለከቱት ሦስቱ ስሞች የኤፍራጥስን ወንዝ የላይኛውን ክልል ይዘው የሚኖሩ ሕዝቦች ናቸው።

10፥4 *ኤሊሳ፤* አሊሺያን (የቆጵሮስ የጥንት ስም) ወይም በደቡባዊ ኢጣሊያ አቅራቢያ የምትገኘውን ሲሲሊን የሚያሳይ ነው። *ተርሴስ፤* በስፔን ደቡባዊ ክፍል የሚገኝ ሳይሆን አይቀርም። *ኪቲም፤* በቆጵሮስ ደሴት ላይ የሚኖሩ ሕዝቦች ናቸው። *ሮዳኢ፤* ሮዶስ በተባለች የግሪክ ደሴት ላይ የሚኖሩትን ሕዝቦች የሚገልጽ ስም ሳይሆን አይቀርም።

*10፥5፤* ቍ 20:31 ይመ። *በየነገዳቸው፣ በየጐሣቸውና በየቋንቋቸው፤* መልክዐ ምድርን፣ ብሔርን፣ ፖለቲካንና ቋንቋን የሚገልጹ ስያሜዎች ናቸው። እነዚህ መመዘኛዎች የተለያዩ የሕዝብ ክፍሎችን ለማመልከት የሚያገለግሉ ናቸው።

10፥6 *ካም፤* ካማውያን በደቡብ ምዕራብ እስያና በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ ሰፍረው ይኖሩ ነበር። *ኩሽ፤* ከግብፅ በስተ ደቡብ በላይኛው ናይል በኩል የሚገኝ ክልል ነው። *ምጽራይም፤* የቃሉ ትርጕም "ሁለት ግብፆች" ማለት ነው፤ ይህም ላይኛውንና ታችኛውን ግብፅ ያመለክታል። *ፉጥ፤* ሊቢያን (የቍ 13 ማብ ይመ)፣ ወይም በጥንት ጊዜ ግብፆች "ፑንት" (የዛሬዋን ሶማልያ) ብለው የሚጠሩት አገር ነው። *ከነዓን፤* የስሙ ትርጕም "ሐምራዊ መሬት" ማለት ሲሆን (ይህ አካባቢ በግሪክ ፊንቄ ተብሉ ይታወቃል)፤ እንዲህም የተባለበት ምክንያት ከነዓን በነገሥታት ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነት የነበረውን ሐምራዊ መንከሪያ ቀለም አምርታ ወደ ውጭ በመላክ የታወቀች በመሆኗ ነው፤ ይህ ግዛት ከብዙ ጊዜ በኋላ፣ በተለይም ፍልስጥኤማውያን (ቍ 4 ይመ) ከመጡ ወዲህ መካከለኛው ምሥራቅ ተብሉአል።

10፥7 *የኩሽ ልጆች፤* በዚህ ሥፍራ የተጠቀሱት ሰባቱ የኩሽ ሕዝቦች በሙሉ በዐረብ ምድር ይኖሩ ነበር። ሺባና ድዳን ወይም ሞክሺዎቻቸው የአብርሃም የልጅ ልጆች ሆነው እንደ ገና

የራዕማ ልጆች፡-
ሳባ፣ ድዳን ናቸው።
8ኩሽ የናምሩድ አባት[ሀ] ነበረ፤ ናምሩድም
በምድር ላይ ኀያል ሰው እየሆነ ሄደ። 9በእ
ግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት ብርቱ አዳኝ ነበረ፤
ስለዚህም፣ "በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት እንደ
ናምሩድ ብርቱ አዳኝ" ይባል ነበር። 10የግዛ
ቱም የመጀመሪያ ከተሞች፡- ባቢሎን፣ ኦሬክ፣
አርካድና ካልኔ ናቸው፤ እነዚህ በ[ለ]ሰናዖር[+]
ምድር ነበሩ። 11ከዚያም ምድር ወደ አሦር
ወጥቶ ነነዌን፣ ረሆቦትን፣[ሐ] ካለህን 12እንዲ
ሁም በነነዌና በካለህ መካከል ሬሴን ቈረ
ቈረ፤ ታላቂንም ከተማ መሠረተ።
13ምጽራይም፡-
የሉዳማውያን፣ የዕናሚማውያን፣ ላህቢያውያን፣
የነፍታሌማውያን፣ 14የፈትሩሲማውያን፣ ፍልስ
ጥኤማውያን የተገኙባቸው የከስሉሂማውያን፣
የቀፍቶሪማውያን አባት ነበረ።
15ከነዓንም፡-
የበኵር ልጁ[+] የሲዶን፣ የኬጢያውያን፣
16የኢያቡሳውያን፣ የአሞራውያን፣ የጌርሳው
ያን አባት ነበረ፤ 17እንዲሁም የኤዊያውያን፣
የዐርኪዋናውያን፣ የሲኒያውያን፣ 18የአራዱ
ዋናውያን፣ የሰማሪናውያን፣ የአማቲያውያን
አባት ነበረ።

10፥8 ሚክ5፥6
10፥9 ዘፍ25፥27፤
27፥3፤2ዜና14፥9፤
16፥8፤ኢሳ18፥2
10፥10 ዘፍ11፥2:9፤
14፥1፤2ዜና36፥17፤
ዕዝ4፥9፤ኢሳ10፥9፤
13፥1፤ 47፥1፤ኤር
21፥2፤25፥12፤50፥11
አሞ6፥2፤ዘካ5፥11
10፥11 2ነገ19፥36፤
መዝ83፥8፤ኢሳ37፥37
፤ሚክ5፥6፤ዮና1፥2፤
3፥2:3፤4፥11፤ናሆ1፥1
፤ሶፎ2፥13
10፥14 ዘፍ21፥32
:34፤26፥1:8፤ዘዳ2፥23
፤1ዜና1፥12፤ኢሱ13፥
2፤መሳ3፥3፤ኢሳ14፥
31፤ኤር47፥1:4፤
አሞ9፥7
10፥15 ቍ19፤ዘፍ
9፥18፤15፥20፤23፥3:
20፤25፥10፤26፥34፤
27፥46፤49፥32፤ዘፀ4፥22፤ዘኍ1፥20፤3፥2፤13፥29፤18፥15፤26፥5፤33፥
4፤ኢሱ1፥4፤11፥8፤መሳ10፥6፤1ሳሙ26፥6፤ኢሳ23፥2:4፤ኤር25፥22፤
27፥3፤47፥4፤ሕዝ16፥3፤28፥21፤32፥30፤ኢል3፥4፤ዘካ9፥2 10፥16
ዘፍ15፥18-21፤ዘፀ3፥8፤ዘኍ13፥29፤21፥13፤32፥39፤ዘዳ1፥4፤7፥1፤ኢሱ
2፥10፤መሳ19፥10፤1ዜና11፥4፤2ዜና8፥7፤ዕዝ9፥1 10፥17 ዘፍ34፥2፤
36፥2፤ዘፀ3፥8፤ዘዳ7፥1፤መሳ3፥3 10፥18 ዘፍ12፥6፤13፥7፤50፥11
፤ሕዝ27፥8፤ዘፀ13፥11፤ዘኍ13፥29፤14፥25፤21፥3፤33፥40፤ዘዳ1፥7፤
መሳ1፥1፤1ዜና18፥3

[ሀ]8 ቍ13:15:24 እና 26ትን ጨምሮ *አባት ማለት ቅድመ አያት ወይም ተተኪ ወይም መሥራች* ማለት ሊሆን ይችላል።
[ለ]10 *ወይም ኦሬክና አርካድ፣ ሁሉም በ...*
[+]10 ባቢሎን ነው [ሐ]11 *ወይም ነነዌ ከነከተማዋ አደባባዮች*
[+]15 *ወይም ከሲዶናውያን የመጀመሪያው*

ተጠቅሰዋል (25፥3 ይመ)። በሕዝ 27፥20-22 ላይም ከራዕማ ጋር ተጠቅሰዋል።

10፥8 *ኩሽ፡* ምናልባት ቍ 6-7 ላይ ካለው ጋር አንድ ላይሆን ይችላል። መስጴጦምያ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ ግን፣ ከጊዜ በኋላ ከመጡት ካሳውያን ጋር ዝምድና ያለው ይመስላል። *ናምሩድ፡* የአርካድ የመጀመሪያ ገዥ (ቍ 10 ይመ) ሲሆን፣ የዕብራይጥ ስሙ ቀዳማዊ ሣርጎን ሳይሆን አይቀርም።

10፥10 *ኦሬክ፡* በጥንት መስጴጦምያ ከነበሩት ታላላቅ ከተሞች ውስጥ አንዱ ሲሆን፣ የዕብራይስጥ ስሙ ኡሩክ ነው (በአሁኑ ጊዜ ዋርካ ተብሎ የሚጠራ)።

10፥12 *ታላቂንም ከተማ፡* "ካላህ" ወይም "ሬሴን" የተባሉትን ከተሞች፣ በይበልጥም ነነዌን የሚያመለክት ነው (ዮና 1፥2፤ 3፥2፤ 4፥11 ይመ)፤ ይህም ነነዌን ብቻዋን ወይም በዙሪያዋ ያሉትን ከተሞች ጥምር ሊያመለክት ይችላል።


10፥13 *ሉዳማውያን፡* ምናልባት በትንሹ እስያ የሚገኙ ሊዲያውያን የተባሉ ጐሣዎች ሳይሆኑ አይቀርም (የቍ 22 ማብ ይመ)። *ዕናሚማውያን፡* በሰሜን አፍሪካ ከግብፅ በስተ ምዕራብ በቀሬና አጠገብ ይገኛል። *ላህቢያውያን፡* በሊቢያ ምድረ በዳ የሚኖሩ ጐሣዎች ሳይሆኑ አይቀሩም (የቍ 6 ማብ ይመ)። *ነፍታሌማውያን፡* በታችኛው ግብፅ የሚኖር ሕዝቦች ናቸው።

10፥14 *ፈትሩሲማውያን፡* የላይኛው ግብፅ ነዋሪዎች ናቸው (የቍ 6 ማብ ይመ) በጥንት ጊዜ ፈትሩሲማ በመባል የምትታወቀው ቀርጤስ ላጭር ጊዜ ለተለያዩ የፍልስጥኤም ብሔሮች መኖሪያ ነበረች (ኤር 47፥4፤ አሞ 9፥7 ይመ)። ፍልስጥኤማውያን ራሳቸው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ12 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ፣ ግብፅን የወረሩ የኢንዶ አውሮፓውያን ብርቱ መርከበኞች ነበሩ። ከግብፅ ከተባረሩ በኋላ ወደ ደቡብ ምዕራብ ከነዓን ፈለሱ፤ ከዚያም ቀስ በቀስ የምድሪቱን ሰፊ ክፍል ያዙ። በርሳን አበው ዘመን ጥቂት ቍጥር የነበራቸው ፍልስጥኤማውያን (21፥32:34፤ 26፥2:8:14-15 ይመ) በከነዓን ሰፍረው እንደ ነበር የሚካድ አይደለም።

10፥15 *ሲዶን፡* በከነዓን ሰሜን ምዕራብ ጠረፍ የምትገኝ ትልቅ የንግድ ከተማ ናት። *ኬጢያውያን፡* ከክርስቶስ በፊት በግምት ከ1800-1200 ድረስ በነበረው ዘመን ሰፊውን የከነዓን ክፍል ይዘው በትንሹ እስያ ይኖሩ የነበሩ ጠንካራ ሕዝቦች ናቸው።

10፥16 *ኢያቡሳውያን፡* የእስራኤል ሕዝብ ከነዓን ድል ባደረጉ ጊዜ በኢየሩሳሌም ሰፍረው የነበሩ ሕዝብ ናቸው። ኢየሩሳሌምም በታሪኳ ውስጥ ኢያቡስ ተብላ የምትታወቅበት ጊዜ ነበር (መሳ 19፥10-11፤ 1ዜና 11፥4 ይመ)። *አሞራውያን፡* ይህ ስም ከአካዳውያን ቋንቋ የተገኘ ሲሆን ትርጕሙም "ምዕራባዊ" ማለት ነው (ከባቢሎን አንጻር ሲታይ ምዕራብ)። እስራኤላውያን ወደ ከነዓን በገቡ ጊዜ፣ አሞራውያን በተራራማው የከነዓን አገር ይኖሩ ነበር።

10፥17-18 እነዚህ ወገኖች ከጌርሳውያን ጋር በመሆን (ቍ 16) በትናንሽ ከተሞች ይኖሩ ነበር።



የኖኅ ልጆች (ዘፍ 10)
ካም ሴም ያፌት

ከጊዜ በኋላ የከነዓን ጐሣዎች በየስፍራው
ተሠራጩ፤ 19የከነዓን ወሰን ከሲዶና አንሥቶ
በጌራራ በኩል እስከ ጋዛ ይደርሳል፤ ከዚያም
በሰዶም በኩል ገሞራን፣ አዳማንና ሰቦይን
ይዞ እስከ ላሣ ይዘልቃል።
20እነዚህም በየጐሣቸውና በየቋንቋቸው፣
በየምድራቸውና በየነገዳቸው ይኖሩ የነበሩ
የካም ዝርያዎች ናቸው።

## የሴም ዝርያዎች

10፥21-31 ተጓ ምብ - ዘፍ 11፥10-27፤ 1ዜና 1፥17-27

21ለያፌት ታላቅ ወንድም[ሀ] ለሴም ደግሞ
ወንዶች ልጆች ተወለዱለት፤ እርሱም የዔ
ቦር ልጆች ሁሉ ቅደመ አያት ነው።
22የሴም ልጆች:-
ኤላም፣ አሦር፣ አርፋክስድ፣ ሉድ፣ አራም
ናቸው።
23የአራም ልጆች:-
ዑፅ፣ ሁል፣ ጌቴር፣ ሞሶሕ[ለ] ናቸው።
24አርፋክስድ ሳላን ወለደ፤[ሐ]
ሳላም ዔቦርን ወለደ።
25ለዔቦርም ሁለት ወንዶች ልጆች ተወለ
ዱለት፤
አንደኛው ልጅ በዘመኑ ምድር ተከፍላ
ስለ ነበር ፍሌቅ[መ] ተባለ፤ ወንድሙም ዮቅጣን
ተባለ።
26ዮቅጣንም:- የኤልሞሳድ፣ የሣሌፍ፣ የሐ
ስረሞት፣ የያራሕ፣ 27የሀደራም፣ የአውዛል፣
የደቅላ አባት ነበረ፤ 28እንዲሁም የዖባል፣
የአቢማኤል፣ የሳባ፣ 29የኦፊር፣ የኤውላጥ፣
የዮባል አባት ነበረ፤ እነዚህ ሁሉ የዮቅጣን
ልጆች ናቸው።

30መኖሪያ ስፍራቸውም እስከ ሶፋር ድረስ
ይዘልቃል።
31እነዚህም በየጐሣቸውና በየቋንቋቸው፣
በየምድራቸውና በየነገዳቸው ይኖሩ የነበሩ
የሴም ዝርያዎች ናቸው።
32የኖኅ ወንዶች ልጆች ጐሣዎች እንደ
ትውልዳቸው በየነገዳቸው እነዚህ ነበሩ። ከጥ
ፋት ውሃ በኋላ ሕዝቦች በምድር ላይ የተ
ሠራጩት ከእነዚሁ ነው።

## የባቤል ግንብ

11 በዚያን ጊዜ ሰዎች ሁሉ የሚናገሩ
ትና የሚግባቡበት ቋንቋ አንድ ብቻ
ነበር። 2ሰዎቹም ምሥራቁን[ሠ] ይዘው ሲጓዙ፣
በሰናዖር[ረ] አንድ ሜዳ አግኝተው በዚያ ሰፈሩ።
3እነርሱም እርስ በርሳቸው፣ "ኑ፤ ጡብ እን
ሥራ፤ እስኪበቃውም በእሳት እንተኩሰው"
ተባባሉ። በድንጋይ ፈንታ ጡብ፣ ለማያያ
ዣም ቅጥራን ተጠቀሙ። 4ከዚያም "ለስማ
ችን መጠሪያ እንዲሆንና በምድር ላይ እን
ዳንበተን፣ ኑ፤ ከተማና ሰማይ የሚደርስ
ግንብ ለራሳችን እንሥራ" አሉ።
5*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ግን ሰዎቹ ይሠሩ የነ
በሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ።

10፥19 ቍ15፤ዘፍ 11፥31፤12፥1፤13፥12፤14፥2፤17፥8፤24፥3፤26፥34፤27፥46፤28፥1፡6፡8፤31፥18፤35፥6፤37፥1፤49፥13፤ዘሌ 25፥38፤ዘዳ2፥23፤29፥23፤ኢሱ10፥41፤11፥22፤15፥47፤19፥28፤መሳ1፥18፡31፤6፥4፤16፥1፡21፤18፥28፤1ሳሙ6፥17፤2ሳሙ 24፥6፤2ዜና14፥13፤ኤር25፥20፤47፥1፤አሞ1+6፤ሶፎ2፥4
10፥21 ቍ24፤ዘኍ24፥24
10፥22 ዘፍ14፥1፤ዘኍ24፥22፡24፤መሳ 3፥10፤1ነገ11፥25፤19፥15፤20፥34፤22፥31፤2ነገ5፥1፤8፥7፤ኢሳ 11፥11፤21፥2፤ኤር 25፥25፤49፥34፤ሕዝ 27፥23፤32፥24፤ዳን 8፥2፤ሉቃ3፥36
10፥23 ዘፍ22፥21፤ኢዮ1፥1፤ኤር25፥20፤ሰቆ4፥21
10፥24 ቍ21፤ሉቃ 3፥35
10፥27 ሕዝ27፥19
10፥28 1ነገ10፥1፤ኢዮ6፥19፤መዝ72፥10፡15፤ኢሳ60፥6፤ሕዝ 27፥22
10፥29 1ነገ9፥28፤10፥11፤1ዜና29፥4፤ኢዮ22፥24፤28፥16፤መዝ45፥9፤ኢሳ13፥12
10፥32 ቍ1፤ዘፍ9፥19
11፥1 ቍ6
11፥2 ዘፍ10፥10
11፥3 ዘፍ14፥10፤ዘፀ1፥14፤5፥7፤ኢሳ9፥10፤ኤር43፥9፤አሞ5፥11 11፥4 ዘፍ6፥4፤9፥19፤ዘዳ1፥28፤4፥27፤6፥10፤9፥1፤30፥3፤1ነገ22፥17፤አስ3፥8፤ኢዮ20፥6፤መዝ44፥11፤ኤር31፥10፤40፥15፤51፥53፤ሕዝ6፥8፤ኢል3፥2 11፥5 ቍ7፤ዘፍ18፥21፤ዘፀ3፥8፤19፥11፡18፡20፤መዝ18፥9፤144፥5

[ሀ]21 ወይም *ሴም፣ የ...ታላቅ ወንድም*
[ለ]23 ሰብዐ ሊቃናትንና 1ዜና 1፥17 ይመ፤ በዕብራይስጡ *ማሽ* ይለዋል።
[ሐ]24 ከዕብራይስጡ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ሰብዐ ሊቃናት ግን *የቃይናን አባት፣ ቃይናንም የ...አባት ነበረ* ይላል
[መ]25 ፍሌቅ ማለት ክፍፍል ማለት ነው
[ሠ]2 ወይም *ከምሥራቅ፣ በምሥራቅ*
[ረ]2 ባቢሎንን ያመለክታል

10፥19 *ሰዶም... ገሞራን፣ አዳማንና ሰቦይን፤* 14፥2:8 ይመ (እንዲሁም የ13፥10 ማብ ይመ)፤ ከሙት ባሕር በስተ ምሥራቅ ወይም በስተ ደቡብ ምሥራቅ የሚገኝ ሳይሆን አይቀርም።

10፥21 *ለሴም ደግሞ ወንዶች ልጆች ተወለዱለት፤* የሴም ዘሮች ሴማውያን ተብለው ይጠራሉ። ዔቦር፦ ምንም እንኳን የሴም የሩቅ ዘር ቢሆንም (ቍ 24-25፤ 11:14-17 ይመ)፣ ዔቦር የዕብራውያን አባት መሆኑ አስቀድሞ በዚህ ቦታ ተነግሮአል ("ዕብ ራውያን" የሚለው ቃል "ዔቦር" ከሚለው ቃል የመጣ ነው)። የኢብላ ጽላቶች (የመግቢያውን ዳራ ይመ) ኢብራዩም ተብሎ የሚጠራውን ንጉሥ 28 ዓመት ሙሉ ኢብላን መግዛቱንና ይናገ ራሉ። ኢብራዩምና ዔቦር ለአንድ ሰው የተሰጡ ስሞች ይመስ ላሉ።

10፥22 *ኤላም፤* ኤላማውያን ከመስጴጦምያ በስተ ምሥ ራቅ ይኖሩ ነበር። *አሦር፤* አሦራውያን ለሚለው ስም መሠረቱ ሲሆን (የ2፥14 ማብ ይመ)ከመስጴጦምያ በስተ ሰሜን የሚገኙ ሕዝ ቦች ናቸው። *አርፋክስድ፤* 11፥10-13 ይመ፤ ከለዳውያን ለሚለው ጥምር የዕብራይስጥ ቃል ሳይሆን አይቀርም፤ *ሉድ፤* በትንሿ እስያ የሚገኙ ሊዲያውያን ሳይሆኑ አይቀሩም (የቍ 13 ማብ ይመ)። *አራም፤* ከከነዓን በስተ ሰሜን ምሥራቅ የሚገኝ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ሶርያ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ነው።

10፥24 *ሳላ፤* 11፥12-15 ይመ።

10፥25 *ፍሌቅ፤* አግራጭ ትርጕሙን ይመ፤ 11፥16-19 ይመ። *ምድር ተከፋፍላ ስለ ነበር፤* በ11፥1-9 ላይ ከተመለከተው የሕዝብ መበተን የተነሣ ሳይሆን አይቀርም።

10፥26 *ዮቅጣን፤* በደቡብ ዐረቢያ የሚገኙ አያሌ መንግ ሥታት የተገኙበት ነው።

10፥28 *ሳባ፤* በደቡብ ምዕራብ ዐረቢያ የሚገኝ ሲሆን፣ አካ ባቢው በአሁኑ ጊዜ የመን ተብሎ ይጠራል። ብዙ ዘመን ቈይቶ የሳባ ንግሥት የተባለች ከክርስቶስ ልደት በፊት በ10ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ንጉሥ ሰሎሞንን ጐበኘች (1ነገ 10፥1-13 ይመ)።

10፥29 *ኦፊር፤* የንጉሥ ሰሎሞን የወርቅ ምንጭ ነበረ (1ነገ 9፥28፤10፥11 ይመ)። የሚገኘውም ከመካከለኛው ምሥራቅ በስተ ደቡብ ማለትም በአፍሪካ ውስጥ ወይም በዐረብ አገር በስተ ደቡብ በኩል ሳይሆን አይቀርም (ነገር ግን የ1ነገ 9፥28 ማብ ይመ)።

11፥1-9 በጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት ይህ ክፍል ከምዕ ራፍ ዐሥር በፊት ሊመጣ የሚገባው በመሆኑ፣ በምዕራፍ ዐሥር ላይ የተዘረዘሩት ሰዎች ለምን እንደ ተበተኑ በግልጽ ይናገራል።

11፥1 *ሰዎች ሁሉ፤* ከጥፋት ውሃ የተረፉትንና የእነርሱን ዘሮች ያመለክታል (ቍ 4:8-9 ይመ)።

11፥3 *በድንጋይ ፈንታ ጡብ፣ ለማያያዣም ቅጥራን ተጠ ቀሙ፤* በከነዓን፣ ድንጋይና ሲሚንቶ የቤትና የሕንጻ መሥሪያ በመሆን ያገለግላሉ። በቍፋሮ ከከርሰ ምድር የተገኙ ጥንታዊ ቅርሶች እንደሚያመለክቱት፣ በመስጴጦምያ የድንጋይ እጥረት ስለ ነበር ከጭቃ የተሠራ ጡብ ይጠቀሙ ነበር።

11፥4 *ለስማችን... እንሥራ፤* የሕዝቡ ዓላማ የራሳቸውን ስም ማስጠራትና ራሳቸውንም ከፍ ከፍ ማድረግ ነበር። *ለስማችን፤* በብሉይ ኪዳን፣ ስም መልካም ዝናንና ታዋቂነትን ያመለክታል (ኔፊሊም በ6፥4 ላይ የታወቁ ሰዎች ናቸው)። በባቢሎን (የቍ 9 ማብ ይመ) አንድ ዐመፀኛ ሰው የእግዚአብሔርን ፍጥረት በቍጥ ጥሩ ሥር ለማ ድረግና የራሱንም ስም ለማስጠራት አንድ ዐመፀኛ ቡድን አቋቁሞ ነበር ከ10፥8-12፤ 2ሳሙ 18፥18 ጋር ያነጻጽሩ)። *ሰማይ ጠቀስ፤* በ28፥12 ላይ የተጠቀሰው ይኸው ዚጉራት ሳይሆን አይቀርም። ሌሎች የመስጴጦምያ ዚጉራቶች ምድርን ከሰማይ የሚያገናኝ ደረጃ ያላቸው በመሆኑ፣ የተሰጣቸውም ስም ይህንኑ ሁኔታ የሚገልጽ ነው። ይኸውም፣ "ሰማይና ምድርን ለማያያዝ የተሠራ ቤት (በላርሳ)፣ የሰማይና የምድር ሰባቱ መመሪያ ቤት (በቦርሲ)፣ የሰማይና የምድር መሠረት ቤት (ባቢሎን)፣ የፍጥ ረተ ዓለም ተራራ ቤት (በአሦር) ናቸው"። *ግንብ፤* ዚጉራት በመ ባል የሚታወቀው የመስጴጦምያን ቤተ መቅደስ መሠረቱ አራት ማእዘን ቅርጽ ያለው ጐንና ጐኖቹ ሾጠጥ ብለው የሚወጡና ከላዩ በኩል የሚጋጠሙ ናቸው።

6እግ[illegible] እንዲህ አንደ አንድ ሕዝብ
[illegible] ቋንቋ በመናገር ይህን ማድረግ ከጀ
መሩ፣ ከእንግዲህ ያቀዱትን ሁሉ ማከናወን
አያዳግታቸውም:: 7ኑ እንውረድ፤ እርስ በር
ሳቸውም እንዳይግባቡ ቋንቋቸውን እንደበ
ላልቀው::”
8ስለዚህ እግዚአብሔር (ያህዌ) በምድር ሁሉ
ላይ በታተናቸው፤ ከተማዋንም መሥራት
አቆሙ:: 9እግዚአብሔር (ያህዌ) በዚያ የመላ
ውን ዓለም ቋንቋ ስለ ደበላለቀ የከተማዪቱ
ስም ባቤል[ሀ] ተባለ:: ከዚያም እግዚአብሔር
(ያህዌ) ሰዎቹን በምድር ሁሉ በተናቸው::

## ከሴም እስከ አብራም

11፥10-27 ተጓ ምብ - ዘፍ 10፥21-37፤ 1ዜና 1፥17-27

10የሴም ትውልድ ይህ ነው:-
ሁለት ዓመት ከጥፋት ውሃ በኋላ ሴም
በ100 ዓመቱ አርፋክስድን ወለደ:: 11ሴም፣
አርፋክስድን ከወለደ በኋላ 500 ዓመት ኖረ፤
ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ::
12አርፋክስድ በ35 ዓመቱ ሳላን ወለደ፤
13ሳላንን ከወለደ በኋላ አርፋክስድ 403 ዓመት
ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶችን ወለደ::[ለ]
14ሳላ በ30 ዓመቱ ዔቦርን ወለደ፤ 15ዔቦ
ርን ከወለደ በኋላ ሳላ 403 ዓመት ኖረ፤
ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ::
16ዔቦር በ34 ዓመቱ ፋሌቅን ወለደ፤ 17ፋሌ
ቅን ከወለደ በኋላ ዔቦር 430 ዓመት ኖረ፤
ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ::
18ፋሌቅ በ30 ዓመቱ ራግውን ወለደ፤
19ራግውንን ከወለደ በኋላ ፋሌቅ 209 ዓመት
ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ::
20ራግው በ32 ዓመቱ ሴሮሕን ወለደ፤
21ሴሮሕን ከወለደ በኋላ ራግው 207 ዓመት
ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ::
22ሴሮሕ በ30 ዓመቱ ናኮርን ወለደ፤
23ናኮርን ከወለደ በኋላ ሴሮሕ 200 ዓመት
ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ::
24ናኮር በ29 ዓመቱ ታራን ወለደ፤ 25ታራን
ከወለደ በኋላ ናኮር 119 ዓመት ኖረ፤
ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ::
26ታራ 70 ዓመት ከሆነው በኋላ አብራ
ምን፣ ናኮርንና ሐራንን ወለደ::
27የታራ ትውልድ ይህ ነው:-
ታራ፣ አብራምን ናኮርንና ሐራንን ወለደ፤
ሐራንም ሎጥን ወለደ:: 28ሐራን፣ አባቱ ታራ
ገና በሕይወት እንዳለ በከለዳውያን ምድር
በምትገኘው በተወለደባት ከተማ በዑር ሞተ::
29አብራምና ናኮር ሁለቱም ሚስት አገቡ፤
የአብራም ሚስት ሦራ ስትባል፣ የናኮር
ሚስት ደግሞ ሚልካ ትባል ነበር፤ ሚል
ካም የሐራን ልጅ ናት፤ ሐራንም የሚልካና
የዮስካ አባት ነበረ:: 30ሦራ መካን ነበረች፤
ልጅ አልነበራትም::
31ታራ ልጁን አብራምን፣ ሐራን የወለደ
ውን የልጅ ልጁን ሎጥን እንዲሁም የአብ
ራምን ሚስት ምራቱን ሦራን ይዞ ወደ
ከነዓን ለመሄድ በከለዳውያን ምድር ከምት
ገኘው ከዑር አብረው ወጡ፤ ነገር ግን ካራን
በደረሱ ጊዜ በዚያ ተቀመጡ::
32ታራ 205 ዓመት ኖሮ በካራን ሞተ::

11፥6 ቍ1
11፥7 ቍ5፤ዘፍ1፥26፤42፥23፤ዘጸ28፥49፤ኢሳ28፥11፤33፥19፤ኤር5፥15፤1ቆሮ14፥2:11
11፥8 ዘፍ9፥9፤ዘጸ32፥8፤ሉቃ1፥51
11፥9 ዘፍ10፥10፤መዝ 55፥9፤ኢሳ2፥10:21፤13፥14፤24፥1፤ሐሥ2፥5-11
11፥10 ዘፍ2፥4፤ሉቃ3፥36
11፥12 ሉቃ3፥35
11፥14 ሉቃ3፥35
11፥16 ሉቃ3፥35
11፥18 ሉቃ3፥35
11፥20 ሉቃ3፥35
11፥22 ሉቃ3፥34
11፥24 ሉቃ3፥34
11፥26 ኢሱ24፥2፤2ነገ19፥12፤ኢሳ37፥12፤ሕዝ27፥23፤ሉቃ3፥34
11፥27 ቍ29:31፤ዘፍ2፥4፤12፥4፤13፥1:5:8:12፤14፥12፤19፥1፤31፥53፤ሉቃ17፥28፤2ጴጥ2፥7
11፥28 ቍ31፤ዘፍ15፥7፤ነህ9፥7፤ኢዮ1፥17፤16፥11፤ሕዝ23፥23፤ሐሥ7፥4
11፥29 ቍ27:31፤ዘፍ12፥5:11፤16፥1፤17፥15፤22፥20:23፤24፥10:15:24፤29፥5፤
11፥30 ዘፍ16፥1፤18፥11፤25፥21፤29፥31፤30፥1:22፤መሳ13፥2፤1ሳሙ1፥5፤መዝ113፥9፤ሉቃ1፥7:36
11፥31 ቍ27:28:29፤ዘፍ10፥19፤12፥4፤38፥11፤27፥43፤28፥5:10፤29፥4፤ዘሌ18፥15፤20፥12፤ሩት1፥6:22፤2፥20፤4፥15፤1ሳሙ4፥19፤2ነገ19፥12፤1ዜና2፥4፤ሕዝ22፥11፤27፥23፤ሚክ7፥6፤ሐሥ7፥4
11፥32 ኢሱ24፥2

[ሀ]9 ባቢሉንን ያመለክታል:: *ባቤል* የሚለው ቃል ድንግርታ የሚል ትርጕም ካለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር አንድ ዐይነት ድምፅ አለው::

[ለ]12-13 ከዕብራይስጡ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ሰብዐ ሊቃናት ግን (በተጨማሪ ሉቃ3፥35-36 እና የዘፍ10-24 ማብ ይመ) እንዲሁ ይሉታል፤ 12 *በ35 ዓመት ቃይናንን ወለደ፤ 13 ቃይናንን ከወለደ በኋላ፣ አርፋክስድ 430 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ፤ ቃይናንም 130 ዓመት ከኖረ በኋላ ሳላን ወለደ፤ ሳላንን ከወለደ በኋላ፣ ቃይናን 330 ዓመት ኖረ፤ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ* ይላል::

11፥6 *ከጀመሩ፣ ከእንግዲህ፤* መላው የሰው ዘር በትዕቢት ተነሣሥቶ በራሱ ጥረት ዕድል ፈንታውን መወሰን ቢችልና ዓለማትን ቢቈጣጠር ኖሮ፣ በእግዚአብሔር ላይ እጅግ ክፉ ዐመፅ ያደርግ ነበር::

11፥7 *እንውረድ፤* የ1፥1:26 ማብ ይመ:: “ኑ፣ እንውረድ” የሚለው ከሰማይ የወጣው የእግዚአብሔር ቃል፣ “ኑ...እንሥራ” (ቍ 4) ለሚለው ከምድር ለወጣው የሰው ቃል አፀፋ ነው:: *እርስ በርሳቸውም እንዳይግባቡ፤* የጋራ ቋንቋ ከሌለ፣ በጋራ መሥራትና አብሮ መኖር አይቻልም (ቍ 8 ይመ)::

11፥8 *በታተናቸው፤* ቍ 4፤9፥19 ይመ:: ከትዕቢታቸውና ከዐመፀኝነታቸው የተነሣ እግዚአብሔር የምድርን ሕዝቦች በየአገሩ በታተናቸው:: የሰው ኀይል ተሰብስቦ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ማሰናከል አይችልም::

11፥9 *ባቤል፤* 10፥10 ይመ:: ቃሉ ከአካዳውያን ቋንቋ የተወሰደ ሲሆን ትርጕሙም፣ “ወደ አማልክት የሚያስገባ በር” ማለት ነው (በተመሳሳይ ሁኔታ ያዕቆብ በሕልሙ ያየው መሰላል “የሰማይ ደጅ” ተብሎአል 28፥17 ይመ):: *ስለ ደበላለቀ፤* በዚህ ቦታ የገባው “ባላል” የተሰኘው የዕብራይስጥ ቃል “ባቢሎን” ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው::

11፥10-26 እንደ ሴት በዐሥር የተመደበ የዘር ሐረግ ነው (5፥3-31 ይመ፤ እንዲሁም የ5፥5 ማብ ይመ):: የሴም የዘር ሐረግ እንደ ሴት የዘር ሐረግ በውስጡ የተዘረዘሩትን ሰዎች ዕድሜ አይገልጽም፤ እያንዳንዱንም አንቀጽ “በኋላ ሞተ” ብሎ አይዘጋም፤ ይህ ክፍል በሴምና በአብርሃም መካከል ያለውን ዘመን የሚሸፍን ነው::

11፥10 *ትውልድ፤* የ2፥4 ማብ ይመ::

11፥26 *ታራ... አብራምን፣ ናኮርንና ሐራንን ወለደ፤* የእነዚህ ስም ልክ እንደ ሴም፣ እንደ ካምና ያፌት ምናልባትም በዕድሜና በጊዜ ቅደም ተከተል የተቀመጠ ላይሆን ይችላል (9፥24፤ 10፥21 ይመ):: ሐራን የሞተው አባቱ በሕይወት እያለ ነበር (ቍ 28 ይመ)::

11፥27 *ትውልድ፤* የ2፥4 ማብ ይመ::

11፥28 *በከለዳውያን ምድር በምትገኘው...ከተማ በዑር፤* ዑር የምትገኘው ምናልባት በመስጴጦምያ በስተ ሰሜን፣ ወይም በኢራቅ በስተ ደቡብ በኤፍራጥስ ወንዝ ዳርቻ ላይ ሳይሆን አይቀርም፤ ሊዮናርድ ውሉ በተባለ የጥንት ታሪክ መርማሪ እ.አ.አ. ከ1922-1934 ዑር ተቈፍራ እንደ ተገኘች ይገመታል፤ ከአብራም ዘመን አስቀድሞ እንኳን ሥልጣኔና ባህል ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ እንደ ነበር ከዑር የተገኙ ፍርስራሾችና ቅርጻ ቅርጾች ያመለክታሉ፤ አብራም በነበረበት ዘመን የነበረው ንጉሥ ዑርናሙም መንግሥቱንና ሕዝቡን ለማስተዳደር ባወጣው ሕግ ታዋቂ ነው::

11፥30 *ሦራ መካን ነበረች፤* የአብራም ሚስት መካን በመሆኗ (15፥2-3፤ 17፥17 ይመ) የእግዚአብሔር ሕዝብ ከድኅረ ባቤል ሕዝቦች ትውልድ እንዳልሆኑ በአጽንዖት ያመለክታል:: አዳምና ኖኅ በኀጢአት ለወደቀው የሰው ዘር አባት እንደ ነበሩ ሁሉ፣ እግዚአብሔርም አብራም አባት የሆነለትን (17፥5) አዲስ የሰው ዘር ያዘጋጅ ነበር::

11፥31 *ካራን በደረሱ ጊዜ፤* በዑርና በካራን የጨረቃ አምላክ ይመለክ ነበር፤ የአብራም አባት ታራ ራሱ ጣዖት አምላኪ ስለነበር (ኢሱ 24፥2 ይመ)፤ ሁለቱንም ከተሞች ለመኖሪያነት ተጠቅሞባቸዋል:: በ19ኛው መቶ ዓ.ቅ.ክ. ላይ ካራን የታወቀች የንግድ ከተማ ነበረች፤ በ18ኛው መቶ ዓ.ቅ.ክ. ግን በአሞራውያን አገዛዝ ሥር ነበረች (የ10፥16 ማብ ይመ)::

## የአብራም መጠራት

12 እግዚአብሔር (ያህዌ) አብራምን እንዲህ
አለው፤ “አገርህን፣ ወገንህንና የአባ
ትህን ቤት ትተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር
ሂድ።

2“ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፤
ደግሞም እባርክሃለሁ፤
ስምህን ገናና አደርገዋለሁ፤
ለሌሎች በረከት ትሆናለህ።

3የሚባርኩህን እባርካለሁ፤
የሚረግሙህን እረግማለሁ፤
በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች፣
በአንተ አማካይነት ይባረካሉ።”

4ስለዚህ አብራም እግዚአብሔር (ያህዌ) እን
ዳዘዘው ወጣ፤ ሎጥም አብሮት ሄደ። አብራም
ከካራን ሲወጣ ዕድሜው 75 ዓመት ነበረ።
5አብራምም ሚስቱን ሦራንና የወንድሙን
ልጅ ሎጥን አስከትሎ በካራን ሳሉ ያፈሩትን
ሀብትና የነበራቸውን አገልጋዮች ይዘው በመ
ንዝ ከነዓን ምድር ገቡ።
6አብራም ትልቁ የሞሬ ዛፍ እስከሚገኝ
በት እስከ ሴኬም ድረስ በምድሪቱ ዘልቆ
ሄደ። በዚያን ጊዜ ከነዓናውያን በዚሁ ምድር
ይኖሩ ነበር። 7እግዚአብሔርም (ያህዌ) ለአብራም
ተገለጠ፣ “ይህችን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ”
አለው። እርሱም ለተገለጠለት አምላክ (ያህዌ)
በዚያ ስፍራ መሠዊያ ሠራ።
8ከዚያም ተነሥቶ ከቤቴል በስተ ምሥራቅ
ወዳሉት ተራሮች ሄደ፤ ቤቴልን በምዕራብ፣
ጋይን በምሥራቅ አድርጎ ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) መሠዊያ ሠራ፤ የእግዚአብሔርን (ያህዌ)
ስም ጠርቶ ጸለየ። 9አብራምም ከዚያ ተነ
ሥቶ ወደ ኔጌብ ሄደ።

### አብራም በግብፅ አገር

12፥10-20 ማመ - ዘፍ 20፥1-18፤ 26፥1-11

10በዚያም ምድር ጽኑ ራብ ገብቶ ነበር፤
ከዚህም የተነሣ አብራም ለጥቂት ጊዜ በዚያ
ለመኖር ወደ ግብፅ ወረደ። 11ግብፅ ለመግ
ባት ጥቂት ሲቀረው አብራም ሚስቱን ሦራን
እንዲህ አላት፤ “መቼም አንቺ ውብ ሴት
መሆንሽን ዐውቃለሁ፤ 12ግብፃውያን አንቺን
በሚያዩበት ጊዜ፣ ‘ይህች ሚስቱ ናት’ ብለው
እኔን ይገድላሉ፤ አንቺን ግን ይተዉሻል።
13ስለዚህ ለአንቺ ሲሉ እንዲንከባከቡኝ፣ ሕይ
ወቴም እንድትተርፍ፣ ‘እኅቱ ነኝ’ በዪ።”

12፥1 ዘፍ10፥19፤ 15፥7፤20፥13፤ 24፥4:23:40፤26፥2፤ ኢሱ24፥3፤ሐሥ7፥3፤ዕብ11፥8 12፥2 ዘፍ13፥16፤ 15፥5፤17፥2:4፤18፥18፤22፥17:18፤24፥1:35፤25፥11፤26፥3:4፤ 28፥3:4:14፤32፥12፤ 35፥11፤41፥49፤46፥3፤47፥27፤48፥4:16:19፤ዘፀ1፥7፤5፥5፤20፥24፤32፥13፤ዘኍ22፥12፤23፥8:20፤24፥9፤ ዘዳ1፥10፤10፥22፤13፥17፤26፥5፤ኢሱ11፥4፤ 24፥3፤2ሳሙ17፥11፤ 1ነገ3፥8፤4፥20፤1ዜና 27፥23፤2ዜና1፥9፤ነህ 9፥23፤መዝ67፥6፤ 107፥38፤115፥12፤ ኢሳ6፥13፤10፥22፤ 19፥24፤44፥3፤48፥19፤51፥2፤54፥3፤60፥22፤61፥9፤65፥23፤ ኤር4፥2፤33፥22፤ሚክ 4፥7፤ሐጌ2፥19፤ዘካ8፥13፤ሚል3፥12፤ 12፥3 ዘፍ15፥5፤18፥18፤22፥18፤26፥4፤ 27፥29፤28፥4:14፤ዘፀ 23፥22፤ዘኍ24፥9፤ዘዳ 9፥5፤30፥7፤መዝ72፥17፤ኢሳ19፥25፤ሐሥ 3፥25፤ገላ3፥8 12፥4 ዘፍ11፥27:31፤16፥3:16፤17፥1:17:24፤21፥5 12፥5 ቍ16፤ዘፍ 11፥29:31፤13፥2:6፤ 16፥3፤31፥18፤46፥6፤ 14፥14፤15፥3፤17፥23፤መክ2፥7፤ዕብ11፥8 12፥6 ዘፍ10፥18፤33፥18፤35፥4፤37፥12፤ዘዳ11፥30፤ኢሱ17፥7፤20፥7፤24፥1:26፤መሳ7፥1፤8፥31፤9፥6፤21፥19፤1ነገ12፥1፤መዝ60፥6፤108፥7፤ዕብ11፥9 12፥7 ዘፍ8፥20፤13፥4:15:17፤15፥18፤17፥8፤18፥1፤23፥18፤24፥7፤26፥2-4፤28፥13፤35፥1:12፤48፥4፤50፥24፤ዘፀ3፥8፤6፥3:4:8፤13፥5:11፤32፥13፤33፥1፤ ዘኍ10፥29፤11፥12፤ዘዳ1፥8፤2፥31፤9፥5፤11፥9፤30፥5፤34፥4፤2ነገ25፥21፤1ዜና16፥16፤2ዜና20፥7፤መዝ105፥9-11፤ኤር25፥5፤ሕዝ47፥14፤ ሐሥ7፥2:5፤ሮሜ4፥13፤ገላ3፥16፤ዕብ11፥8 12፥8 ዘፍ4፥26፤8፥20፤13፥3፤26፥25፤28፥11:19፤35፥1:8:15፤ኢሱ7፥2፤8፥9፤12፥9፤1ሳሙ7፥16፤1ነገ12፥29፤ዕዝ2፥28፤ነህ7፥32፤ኤር49፥3፤ሆሴ12፥4፤አሞ3፥14፤4፥4፤ዕብ11፥9 12፥9 ዘፍ13፥1:3፤20፥1፤24፥62፤ዘኍ13፥17፤33፥40፤ዘዳ34፥3፤ኢሱ10፥40 12፥10 ዘፍ41፥27:30:54:56:57፤42፥5፤43፥1፤47፥4:13:20፤ሩት1፥1፤2ሳሙ21፥1፤2ነገ8፥1፤መዝ105፥16:19 12፥11 ቍ14፤ዘፍ11፥29፤24፥16፤26፥7፤29፥17፤39፥6 12፥13 ዘፍ20፥2፤26፥7

12፥1 *አብራምን... አለው፤* “ወደ ካራን ከመምጣቱ በፊት፣ ገና በመስጴጦምያ ሳለ” (ሐሥ 7፥2) እግዚአብሔር ለአብራም ተናገረው። *ትተህ እኔ ወደማሳይህ፤* አብራም የተመቻቸ ኑሮ የሚኖርበትን የድኅረ-ባቤልን ዓለም ትቶ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀለት የተሻለ ዓለም መሄድ ነበረበት (24፥7 ይመ)።

12፥2-3 እግዚአብሔር ለአብራም የሰጠው ተስፋ ሰባት ዐበየት ተስፋዎችን ይዞአል፤ (1) *ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፤* (2) እባርክሃለሁ፤ (3) ስምህን ገናና አደርገዋለሁ (4) ለሌሎች በረከት ትሆናለህ፤ (5) የሚባርኩህን እባርካለሁ፤ (6) የሚረግሙህን እረግማለሁ፤ (7) በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች በአንተ አማካይነት ይባረካሉ። እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ለመባረክ ገና ከመጀመሪያው የነበረው ሐሳብ (2፥28) እንደ ገና በአብራምና በዘሮቹ ፍጻሜ እንደሚያገኝ ያመለክታል። እነዚህ የተስፋ ቃሎች በተለያየ መንገድና ደረጃ ለአብራም እንደ ገና (ቍ 7፤ 15፥5-21፤ 17፥4-8፤ 18፥18-19፤ 22፥17-18)፣ ለይስሐቅ (26፥2-4)፣ ለያዕቆብ (28፥13-15፤ 35፥11-12፤ 46፥3) እና ለሙሴ (ዘፀ 3፥6-8፤ 6፥2-8) ተነግረዋል። ሰባተኛው የተስፋ ቃል በሐሥ 3፥25 ላይ የጴጥሮስ አድማጮች ለነበሩትና በሥጋ የአብራም ዘሮች ለሆኑት አይሁዳውያን የተጠቀሰ ሲሆን፣ በገላ 3፥8 ላይ ደግሞ የጳውሎስ አድማጮች ለነበሩትና በመንፈስ የአብራም ዘሮች ለሆኑት አሕዛብ ተጠቅሶአል።

12፥4 *አብራም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ወጣ፤* ዕብ 11፥8 ይመ። ይህ የሕዝቦች አባት ከእምነቱ የተነሣ ለእግዚአብሔር ያሳየው ታዛዥነት በሕይወቱ ሁሉ የሚታይ ልዩ ባሕርይ ነው (17፥23፤ 21፥14፤ 22፥3 ይመ)። *ሎጥም አብሮት ሄደ፤* 13፥1:5 ይመ። በመጀመሪያ ሎጥ የወሰደው መሬት አብራም ከወሰደው የሚበልጥ ነበር። *ዕድሜው 75 ዓመት፤* አብራም በተጠራ ጊዜ ዕድሜው ትልቅ ቢሆንም፣ ከዚህ በኋላ ግን አንድ ሙሉ ምእተ ዓመት ኖሮአል (25፥7 ይመ፤ እንዲሁም የ5፥5 ማብ ይመ)።

12፥5 *ያፈሩትን... አገልጋዮች፤* በጥንት ጊዜ ሀብታሞች ከብቶቻቸውን የሚጠብቁላቸው አገልጋዮች ነበሯቸው (15፥3፤ 24፥2 ይመ)። በዚያን ዘመን አገልጋዮች ሁሉ ባሪያዎች አልነበሩም፤ በፈቃዳቸው ተቀጥረው የሚያገለግሉም ነበሩ።

12፥6 *ትልቁ የሞሬ ዛፍ እስከሚገኝበት፤* 35፥4፤ መሳ 9፥6:37 ይመ። የከነዓን ማእከል በሆነችው በሴኬም የታወቀ ቤተ መቅደስ ስለ ነበር፣ በእንዲህ ያሉ የአምልኮ ቦታዎች ትላልቅ ዛፎች ማየት የተለመደ ነው። አብራም ግን በዚያ ስፍራ ለጣዖት ሳይሆን ለእግዚአብሔር ይሰግድ ነበር።

12፥7 *እግዚአብሔርም... ተገለጠ፤* እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ለአብራምና ለሌሎች ሰዎች ራሱን ይገልጥ ነበር፤ እግዚአብሔር ራሱን ይገልጥ የነበረው ግን በሙሉ ክብሩ አልነበረም (ዘፀ 33፥18-20፤ ዮሐ 1፥18 ይመ)። *መሠዊያ፤* አብራም የማይረሱ መንፈሳዊ ገጠመኞችን በተለማመደባቸው ቦታዎች ሁሉ፣ ለእግዚአብሔር ከሠራቸው መሠዊያዎች መካከል የመጀመሪያው ይህ ነው (ቍ 8፤ 13፥18፤ 22፥9 ይመ)። የከነዓን ምድር በተለየ መንገድ የእግዚአብሔር መሆኑ ተገንዝቦአል (ዘፀ 20፥24፤ ኢሱ 22፥19 ይመ)።

12፥8 *ቤቴል፤* ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን የምትገኝ ስትሆን፣ በጥንቱ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሃይማኖታዊ ታሪክ ውስጥ የታወቀች ከተማ ነበረች (28፥10-22፤ 35፥1-8፤ 1ነገ 12፥26-29 ይመ)። በብሉይ ኪዳን ብዙ ጊዜ በመጠቀስ የምትበልጣት ኢየሩሳሌም ብቻ ናት።

12፥9 *ኔጌብ፤* ከቤርሳቤህ ጀምሮ ወደ ደቡብ ተንጣሎ የሚገኝ ደረቅና ጠፍ መሬት ነው። ይኸው የዕብራይስጥ ቃል በ13፥14 ላይ፣ “ደቡብ” ተብሎ ተተርጕሞአል።

12፥10 *ጽኑ ራብ ገብቶ ነበረ፤... ወደ ግብፅ ወረደ፤* ግብፅ ከናይል ወንዝ በምታገኘው ውሃ የተትረፈረፈ የምግብ አቅርቦት ሊኖራት ችሎአል።

12፥11 *ውብ፤* ቍ 14 ይመ። በዚያን ጊዜ የሦራ ዕድሜ 65 ዓመት ነበር (ቍ 4፤ 17፥17 ይመ)። “የዘፍጥረት አፖክሪፋ” (ከሙት ባሕር አካባቢ የተገኘው ጥቅልል መጽሐፍ) የሦራን ቍንጅና ያደንቃል። ይህ የአብራም የግብፅ ገጠመኝ፣ እስራኤል በግብፅ ምድር የሚገጥማትን ነገር አስቀድሞ እንደሚያመለክት የዘፍጥረት መጽሐፍ ጸሓፊ እስራኤላውያን ከግብፅ ምድር ከወጡ በኋላ መጽሐፉን በሚጽፍበት ወቅት አስተውሎታል። በእርግጥም አብራም የእስራኤል ሕዝብ “አባት” ነው።

12፥13 *‘እኅቱ ነኝ’ በዪ፤* ፈርዖን፣ ሦራ የአብራም ሚስት መሆኗን እያወቀ ለራሱ ሚስቱ ሊያደርጋት ቢፈልግ ኖሮ በመጀመሪያ አብራምን መግደል ይችል ነበር።

14አብራም በግብፅ አገር እንደ ደረሰ ግብ
ፃውያን፣ ሦራ እጅግ ውብ ሴት እንደ ሆነች
አዩ፤ 15የፈርዖንም ሹማምት ባዩአት ጊዜ፣
ለፈርዖን አድንቀው ነገሩት፤ ወደ ቤተ መንግ
ሥትም ወሰዷት። 16በእርሷም ምክንያት ፈርዖን
አብራምን አክብሮ አስተናገደው፤ በጎችና
ከብቶች፣ ተባዕትና እንስት አህዮች፣ ወንድና
ሴት አገልጋዮች እንዲሁም ግመሎችን ሰጠው።
17*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) በአብራም ሚስት
በሦራ ምክንያት ፈርዖንንና ቤተ ሰዎቹን በጽኑ
ደዌ መታቸው። 18ከዚያም ፈርዖን አብራ
ምን አስጠርቶ እንዲህ አለው፤ "ይህ ያደ
ረግህብኝ ነገር ምንድን ነው? 'ሚስትህ እንደ
ሆነች ለምን አልነገርኸኝም? 19ለምን 'እኅቴ
ናት' አልኸኝ? ሚስቴ ላደርጋት ነበር። በል
አሁንም ሚስትህ ይህችው፤ ይዘሃት ሂድ!"
20ከዚያም ፈርዖን ስለ አብራም ለባለሚሎቹ
ትእዛዝ ሰጠ፤ እነርሱም አብራምን ከሚስቱና
ከንብረቱ ሁሉ ጋር አሰናበቱት።

## የአብራምና የሎጥ መለያየት

13 አብራም ሚስቱንና ንብረቱን ሁሉ
ይዞ ከግብፅ ወደ ኔጌብ ሄደ፤ ሎጥም
አብሮት ነበረ። 2አብራም በከብት፣ በብርና
በወርቅ እጅግ በልጽጎ ነበር።
3አብራም ከኔጌብ ተነሥቶ እስከ ቤቴል
ተጓዘ፤ ቀድሞ በቤቴልና በጋይ መካከል ድን
ኳኑን ከተከለበት፣ 4ለመጀመሪያ ጊዜም መሠ
ዊያ ካቆመበት ስፍራ ደረሰ፤ በዚያም የእግ
*ዚአብሔርን* (ያህዌ) ስም ጠራ።
5ከአብራም ጋር አብሮት ይጓዝ የነበረው
ሎጥ በጎች፣ ከብቶችና ድንኳኖች ነበሩት።
6ሆኖም ሁለቱ አንድ ላይ ሲኖሩ ስፍራው
አልበቃቸውም፤ ንብረታቸው እጅግ ብዙ ስለ
ነበር፣ አብረው መኖር አልቻሉም። 7ይህም
በመሆኑ በአብራምና በሎጥ እረኞች መካከል
ጠብ ተፈጠረ። በዚያን ዘመን ከነዓናውያ
ንና ፌርዛውያን በዚያው አገር ይኖሩ ነበር።
8አብራምም ሎጥን እንዲህ አለው፤ "እኛ
ወንድማማቾች ነንና በአንተና በእኔ ወይም
በእረኞቻችን መካከል ጠብ ሊኖር አይገባም።
9ይኸው እንደምታየው አገሩ ሰፊ ነው፤ ብን
ለያይ ይሻላል። አንተ ግራውን ብትመርጥ፣
እኔ ወደ ቀኝ እሄዳለሁ፤ አንተ ቀኙን ብት
መርጥ፣ እኔ ወደ ግራ አመራለሁ።"
10ሎጥ ዐይኑን አቅንቶ ሲመለከት፣ የዮር
ዳኖስ ረባዳ ሜዳ እንደ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ገነት፣ በዞዓር አቅጣጫ እንዳለው እንደ
ግብፅ ምድር ውሃማ ቦታ ሆኖ አገኘው።
እንዲህም የነበረው *እግዚአብሔር* (ያህዌ) የሰ
ዶምንና የገሞራን ከተሞች ከማጥፋቱ በፊት
ነው። 11ሎጥ የዮርዳኖስን ረባዳ ሜዳ በሙሉ
መርጦ ወደ ምሥራቅ አመራ፤ ሁለቱ ሰዎች
በዚሁ ተለያዩ። 12አብራም መኖሪያውን በከ
ነዓን ምድር አደረገ፤ ሎጥ ግን በረባዳው ሜዳ
ውስጥ ባሉት ከተሞች መካከል በሰዶም አቅ
ራቢያ ድንኳኑን ተከለ። 13የሰዶም ሰዎች ግን
ክፉዎችና *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት እጅግ
ኃጥአን ነበሩ።
14ሎጥ ከተለየው በኋላ *እግዚአብሔር* (ያህዌ)
አብራምን እንዲህ አለው፤ ካለህበት ስፍራ
ቀና ብለህ ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ፣ ወደ
ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ተመልከት፤ 15ዐይ
ንህ የሚያየውን ምድር ሁሉ ለአንተና ለዘ
ርህ ለዘላለም እሰጣለሁ። 16ዘርህን እንደ ምድር

12፥14 ቍ11
12፥16 ቍ5፤ዘፍ 24፥35፤26፥14፤30፥43፤32፥5፤34፥23፤47፥17፤ኢዮ1፥3፤31፥25
12፥17 2ነገ15፥5፤1ዜና16፥21፤ኢዮ30፥11፤መዝ105፥14፤ኢሳ53፥4፡10
12፥18 ዘፍ20፥9፤26፥10፤29፥25፤31፥26፤44፥15፤ዕዝ16፥3፤ኢሳ43፥27፤51፥2
12፥19 ዘፍ20፥5፤26፥9
13፥1 ዘፍ11፥12፤12፥9፤45፥25
13፥2 ዘፍ12፥5፤26፥13፤32፥15፤ኢዮ1፥3፤ምሳ10፥22፤
13፥3 ዘፍ12፥8፡9፤ኢሱ7፥2
13፥4 ዘፍ4፥26፤12፥7
13፥5 ዘፍ11፥27
13፥6 ዘፍ12፥5፤33፥9፤36፥7
13፥7 ዘፍ10፥18፤12፥6፤15፥20፤26፥20፡21፤34፥30፤ዘፀ3፥8፤ዘኁ20፥3፤መሳ1፥4
13፥8 ዘፍ11፥27፤19፥9፤ዘፀ2፥14፤ዘኁ16፥13፤መዝ133፥1፤ምሳ15፥18፤20፥3
13፥9 ዘፍ20፥15፤34፥10፤47፥6፤ኤር40፥4
13፥10 ዘፍ2፥8-10፤4፥2፤14፥8፤19፥17-30፤46፥7፤ዘኁ13፥29፤33፥48፤ዘዳ29፥23፤34፥3፤1ነገ7፥46፤2ዜና4፥17፤ኢዮ39፥6፤መዝ107፥34፤ኢሳ15፥5፤51፥3፤ኤር4፥26፤48፥34፤ሕዝ31፥8-9

13፥12 ቍ10፤ዘፍ10፥19፤11፥27፤19፥17፡25፡29፤14፥12 13፥13 ዘፍ3፥9፤18፥20፤19፥4፡5፤20፥6፤39፥9፤ዘኁ32፥23፤1ሳሙ12፥23፤2ሳሙ12፥13፤መዝ51፥4፤ኢሳ1፥10፤3፥9፤ሕዝ16፥49-50፤2ጴጥ2፥8 13፥14 ዘፍ28፥14፤32፥12፤48፥16፤ዘዳ3፥27፤13፥17፤ኢሳ54፥3 13፥15 ዘፍ12፥7፤ገላ3፥16

12፥15 *ፈርዖን፤* የዘፀ 1፥11 ማብ ይመ።

*12፥16፤* በጥንት ዘመን የሀብት ብዛት ይለካ የነበረው በቀንድ ከብቶች ብዛት ነው (13፥2 ይመ)። *ወንድና ሴት አገልጋዮች፤* የቍ 5 ማብ ይመ። *ግመሎች፤* ምንም እንኳ ግመሎችን በስፋት መጠቀም የተጀመረው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቢሆንም (መሳ 6፥5 ይመ)፣ ከርእሳን አበው ዘመን ጀምሮ የቤት እንስሳት እንደ ነበሩ በቍፋሮ የተገኙ የታሪክ መዛግብት አረጋግጠዋል።

12፥19 *ለምን 'እኅቴ ናት' አልኸኝ?* የግብፃውያን የሥነ ምግባር ሕግ ፍጹም እውነተኛነትን (ሐቀኛነትን) የሚያጠብቅ በመሆኑ፣ የአብራምን ውሸታምነት አጋልጦአል።

12፥20 *ፈርዖን... ትእዛዝ ሰጠ፤* ዘፀ 12፥31-32 ይመ።

13፥2 *እጅግ በልጽጎ ነበር፤* አብራም ቀድሞ ከነበረው የበለጠ ብዙ ሀብት ይዞ ከግብፅ ተመለሰ፤ ከእርሱ በኋላም የእስራኤል ሕዝብ ከግብፃውያን የበዘበዙትን ብዙ ሀብት ይዘው ከግብፅ ወጡ (ዘፀ 3፥22፤ 12፥36)።

13፥4 *የእግዚአብሔርን ስም ጠራ፤* ቀደም ሲል በዚሁ ቦታ የእግዚአብሔርን ስም እንደ ጠራ ሁሉ አሁንም እንዲሁ አደረገ (12፥8 ይመ)።

13፥6 *ስፍራው አልበቃቸውም፤* ከሀብታቸው ውስጥ ብዙውን ስፍራ የሚይዘው የከብቶቻቸው ብዛት ነበር፤ በዚህ ምክንያት በቤቴልና በአይ አካባቢ የሚገኘው ቦታ ለከብቶቻቸው በቂ ውሃ ወይም የግጦሽ ቦታ ሊያስገኝላቸው አልቻለም (ቍ 10:26:17-22:32፤ 36፥7 ይመ)።

13፥7 *ፌርዛውያንም፤* ከከተማ ነዋሪዎች ይልቅ የገጠር ነዋሪዎችን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም።

13፥8 *ወንድማማቾች፤* ዘመዳሞች ማለት ነው (በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙውን ጊዜ የቅርብ ዝምድናን የሚያሳይ ነው)።

*13፥9* አብራም ዘወትር ቸር ስለ ነበር ደስ ያሰኘውን መሬት እንዲወስድ ምርጫውን ለሎጥ ሰጠ፤ ይህንንም ያደረገው እግዚአብሔር ካልባረከው በቀር ሀብትን ማግኘት እንደማይችል ስለ ተገነዘበ ነው (14፥22-24 ይመ)።

13፥10 *ረባዳ ሜዳ፤* በዚህ ክፍል የተጠቀሰው የዮርዳኖስ ሸለቆ እንደ ዕንቁላል ሞላላ መሆኑን ለዚህ ሐረግ የገባው የዕብራይስጥ ቃል ሥዕላዊ በሆነ መልክ ይገልጻል። *እንደ ግብፅ ምድር፤* ግብፅ የተትረፈረፈና አስተማማኝ የውሃ አቅርቦት ስለነበራት (የ12፥10 ማብ ይመ)፣ የኤደንን ልዩ ልምላሜ ለመግለጽ የሚያስችል ተቀራራቢነት ነበራት (2፥10 ይመ)። *እግዚአብሔር የሰዶምንና የገሞራን ከተሞች ከማጥፋቱ በፊት፤* በተለይም 18፥16-19፥29 ይመ። ሰዶምና ገሞራ የሰው ልጆችን ክፋትና የእግዚአብሔርን ፍርድ ለማስታወስ የሚያገለግሉ ምሳሌዎች ሆነዋል። በሥነ-ቅርስ እንደተረጋገጠው፣ ሰዶምና ገሞራ በእግዚአብሔር ፍርድ ከመጥፋታቸው በፊት፣ አሁን ከሙት ባሕር በስተ ምሥራቅና ደቡብ ምሥራቅ በኩል ያለው በረሐማ አካባቢ (የ10፥19 ማብ ይመ) በቂ የውሃ ክምችትና ብዙ ሕዝብ ይኖርበት ነበር።

13፥12 *ሎጥ... ድንኳኑን ተከለ፤* የሰዶም ሰዎች በክፉ ሥራቸው የታወቁ ስለ ነበሩ (ቍ 13 ይመ)፣ ሎጥ ከእነርሱ ተጉራብቶ ለመኖር የወሰደው እርምጃ ከፍተኛ ፈተና አስከተለበት፤ የሎጥን ውሳኔ ከአብራም ውሳኔ ጋር ያነጻጽሩ (ቍ 18)።

13፥14 *ቀና ብለህ... ተመልከት፤* ዘዳ 34፥1-4 ይመ። ሎጥና አብራም የተለያየ አመለካከት ያላቸው ሰዎች ናቸው፤ የመጀመሪያው ስስታምና የራሱን ፍላጐት ብቻ ለመሙላት የሚሯሯጥ (ቍ 10) ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት የሚመላለስና የተባረከም ሰው ነበር።

13፥16 *ምድር ትቢያ፤* ብዛታቸው ከቍጥር በላይ የሆነውን

ትቢያ አበዛዋለሁ፤ ማንም የምድርን ትቢያ
ሊቈጠር እንደማይችል ሁሉ የአንተም ዘር
የማይቈጠር ይሆናል። [17]እንግዲህ ምድሪቱን
ስለምሰጥህ ተነሥ፤ በርዝመቷም፣ በስፋቷም
ተመላለስባት።”
[18]አብራምም ድንኳኑን ነቀለ፤ ሄዶም ኬብ
ሮን በሚገኙት ትልልቅ የመምሬ ዛፎች
አጠገብ ተቀመጠ፤ በዚያም ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) መሠዊያ ሠራ።

## አብራም ሎጥን መታደጉ

14 አምራፌል የሰናዖር[o] ንጉሥ፣ አር
ዮክ የእላሳር ንጉሥ፣ ኮሎዶጎምር
የኤላም ንጉሥ፣ ቲድዓል የጎይም ንጉሥ
በነበሩበት ዘመን፣ [2]ከሰዶም ንጉሥ ከበላ፣
ከገሞራ ንጉሥ ከብርሳ፣ ከአዳማ ንጉሥ ከሰ
ነአብ፣ ከሰቦይ ንጉሥ ከሰሜበር፣ እንዲሁም
ዞዓር ከተባለች ከቤላ ንጉሥ ጋር ለመዋጋት
ወጡ። [3]እነዚህ የኋለኞቹ አምስቱ ነገሥታት
በሲዲም ሸለቆ፣ በጨው ባሕር[ʺ] ተሰበሰቡ።
[4]እነርሱም ዐሥራ ሁለት ዓመት ለኮሎዶጎ
ምር ከተገዙ በኋላ በዐሥራ ሦስተኛው ዓመት
ዐመፁ።
[5]በዐሥራ አራተኛው ዓመት ኮሎዶጎምርና
ከርሱ ጋር የተባበሩት ነገሥታት ወጡ፤ ራፋ
ይምን በአስጣሮት ቃርናይም፣ ዙዚምን በሃም፣
ኤሚምን በሴዊ ቂርያታይም፣ [6]የሖር ሰዎች
ንም በተራራማው አገር በሴይር በረሓማ
አጠገብ እስካለው እስከ ኤልፋራን ድረስ
ድል አደረጓቸው። [7]ከዚያም ተመልሰው ዓይን
ሚስፖጥ ወደ ተባለው ወደ ቃዴስ መጡ፤
የአማሌቃውያንና በሐሴስ ታማር ይኖሩ የነ
በሩትን የአሞራውያንን ግዛት በሙሉ ድል
አድርገው ያዙ።
[8]ከዚያም የሰዶም፣ የገሞራ፣ የአዳማ፣ የሰ
ቦይ እንዲሁም ዞዓር የተባለችው የቤላ ነገ
ሥታት በሲዲም ሸለቆ ሰራዊታቸውን አስተባ
በሩ፤ [9]እነዚህ አምስቱ፣ በኤላም ንጉሥ በኮ
ሎዶጎምር፣ በጎይም ንጉሥ በቲድዓል፣ በሰ
ናዖር ንጉሥ በአምራፌል፣ በእላሳር ንጉሥ
በአርዮክ፣ በእነዚህ በአራቱ ላይ ዘመቱባቸው።
[10]በሲዲም ሸለቆ ብዙ የቅጥራን ጕድጓዶች
ስለ ነበሩ የሰዶምና የገሞራ ነገሥታት ሲሸሹ
ከሰዎቻቸው አንዳንዶቹ በነዚህ ጕድጓዶች
ውስጥ ወደቁ፤ የቀሩትም ወደ ተራሮች ሸሹ።
[11]አራቱ ነገሥታትም በሰዶምና በገሞራ ያገ
ኙትን ሀብትና ምግብ ሁሉ ዘርፈው ሄዱ።
[12]የአብራም ወንድም ልጅ ሎጥ፣ ሰዶም ይኖር
ስለ ነበር እርሱንም ማርከው ንብረቱንም ዘር
ፈው ሄዱ።
[13]ከዚህም ያመለጠ አንድ ሰው መጥቶ
ለዕብራዊው ለአብራም ይህን ነገረ፤ አብራም
በዚያ ጊዜ ይኖር የነበረው በአሞራዊው
መምሬ ታላላቅ ዛፎች አጠገብ ነበር። መምሬ፣
ወንድሞቹ[ʺ] እስኮና አውናን የአብራም የኪ
ዳን አጋሮቹ ነበሩ። [14]አብራም የወንድሙን
ልጅ መማረክ እንደ ሰማ በቤቱ ተወልደው
አድገው የሠለጠኑ 318 ጦረኞች አሰልፎ እስከ ዳን

13፥16 ዘፍ12፥2፤ 16፥10፤17፥20፤21፥13፡18፤25፥16፤ዘኍ 23፥10
13፥17 ቍ15፤ዘኍ 13፥17-25፤ዘፍ12፥7፤15፥7
13፥18 ዘፍ8፥20፤ 14፥13፡24፤18፥1፤ 23፥2፡17፡19፤25፥9፤ 35፥27፤37፥14፤49፥30፤ 50፥13፤ዘኍ 13፥22፤ኢሱ10፥3፡36፤መሳ1፥10፤1ሳሙ 30፥31፤2ሳሙ2፥1፡3፡11፤1ዜና11፥1
14፥1 ቍ4፡9፡17፤ ዘፍ10፥10፡22
14፥2 ዘፍ10፥19፤ 13፥10
14፥3 ቍ8፡10፤ዘኍ 34፥3፡12፤ዘዳ3፥17፤ ኢሱ3፥16፤12፥3፤ 15፥2፡5፤18፥19
14፥4 ቍ1
14፥5 ቍ1፤ዘፍ15፥20፤ዘዳ2፥10፡11፡20፤ 3፥11፡13፤ኢሱ12፥4፤ 13፥12፤17፥15፤ 1ዜና20፥4
14፥6 ዘፍ21፥21፤ 32፥3፤33፥14፡16፤ 36፥8፡20፤ዘኍ10፥12፤12፥16፤13፥3፡26፤ዘዳ1፥2፤2፥1፡5፡12፡22፤ኢሱ11፥17፤ 24፥4፤1ዜና4፥42፤ኢሳ 34፥5፤ሕዝ25፥8፤35፥2፤አሞ1፥6፤ዕን3፥3
14፥7 ዘፍ16፥14፤ 20፥1፤ዘፀ17፥8፤ዘኍ 13፥26፡29፤14፥25፤ 20፥1፤24፥20፤25፥17፤32፥8፤ዘዳ1፥2፡4፤25፥17፤ኢሱ2፥10፤10፥41፤
13፥41መሳ3፥13፤6፥3፤10፥12፤11፥16፤12፥15፤1ሳሙ14፥48፤15፥2፤28፥18፤2ሳሙ1፥1፤1ዜና4፥43፤2ዜና20፥2፤መዝ29፥8፤83፥7፤ሕዝ 48፥28 14፥8 ቍ3፤ዘፍ13፥10፤ዘዳ29፥23፤ሆሴ11፥8 14፥9 ቍ1 ፤ዘፍ10፥22 14፥10 ቍ3፡17፡21፤ዘፍ11፥3፤19፥17፡30፤ኢሱ2፥16፤ መዝ11፥1 14፥11ቍ16፡21 14፥12 ዘፍ11፥27 14፥13 ዘፍ 13፥18፤37፥28፤39፥14፡17፤40፥15፤41፥12፤43፥32፤ዘፀ3፥18፤ዘኍ13፥23፤32፥9፤ዘዳ1፥24፤1ሳሙ4፥6፤14፥11 14፥14 ቍ12፤ዘፍ12፥5፤ ዘዳ4፥9፤34፥1፤መሳ18፥29፤1ነገ15፥20፤ምሳ22፥6

[o]1 በቍ 9 ላይ ያለውንም ጨምሮ ባቢሎንን ያመለክታል።
[ʺ]3 የሙት ባሕር ማለት ነው

የአብራም ልጆች ለማመልከት የገባና በቀድሞ ቅርብ ምሥራቅ ነዋሪዎች ዘንድ የታወቀ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው (28፥14፤ 2ዜና 1፥9፤ እንዲሁም ዘኍ 23፥10 ይመ)። “እንደ ሰማይ ከዋክብት” እና “እንደ ባሕር ዳር አሸዋ” የሚሉትም ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ናቸው (22፥17)።

13፥17 *በርዝመቷም፣ በስፋቷም ተመላለስባት፤* ለመቈጣጠር ወይም በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ለመግዛት ሊሆን ይችላል፤ ይህም ተስፋ የተገባላትን ርስት መውረሱን ያመለክታል።

13፥18 *ትልልቅ…ዛፎች፤* የ12፥6 ማብ ይመ። *መምሬ፤* ከአብራም አጋሮች በአንዱ ስም የተሰየመች ከተማ ነች (14፥13 ይመ)። *ኬብሮን፤* ቂርያት አርባቅ ናት (የ23፥2 ማብ ይመ)። *መሠዊያ፤* የ12፥7 ማብ ይመ።

*14፥1 አምራፌል፣ የሰናዖር ንጉሥ፤* ታላቁ የባቢሎን ንጉሥ ሐሙራቢን አይደለም። *ኤላም፤* የ10፥22 ማብ ይመ። *ጎይም፤* የዕብራይስጡ ቃል፣ “የአሕዛብ መንግሥታት” የሚል ትርጕም አለው (እንደ ኢሳ 9፥1 ሁሉ)፤ በዚህ ቦታ በስም ደረጃ ገብቶአል።

14፥3 *በጨው ባሕር፤* ሌላ ስሙ ሙት ባሕር ነው፤ ይህ ባሕር፣ ከመቶ ሃያ አምስት እጅ የሚሆን የክሎራይድና የብሮማይድ ጨው ይዘት ሲኖረው፣ ይህም ጨዋማ ይዘቱ በዓለም ላይ በውፍረቱና በብዛቱ ተወዳዳሪ የሌለው አድርጎታል።

14፥6 *የሖር ሰዎች፤* ቀደም ባለው ጊዜ የዋሻ ነዋሪዎች ተደርገው ይታዩ ነበር (በዕብራይስጥ ቋንቋ “ሖር” ማለት ዋሻ ማለት ነው)፤ ሖራውያን ተብለው የሚታወቁና በጥንት ቅርብ ምሥራቅ ተበታትነው ከሚኖሩ ከሴማውያን ወገን እንዳልሆኑ ተረጋግጦአል።

14፥7 *ዓይንሚስፖጥ፤* የቃዴስ ሌላ ስም ሲሆን፣ ትርጕሙም “የፍርድ ምንጭ” ማለት ነው። በዘዳ 32፥51 ላይ መሪባ ቃዴስ ወይም፣ “የቃዴሱ አምባጓሮ” ተብሎ ተጠርቶአል (ዘኍ 27፥14 ይመ)። *ቃዴስ፤* በደቡብ ምዕራብ ኔጌብ ይገኛል (የ12፥9 ማብ ይመ)፤ በኋላ ግን ቃዴስ በርኔ ተብሎአል። *አማሌቃውያን፤* በኔጌብና በሲና ልሳነ ምድር የሚኖሩ ሕዝብ ናቸው። *አሞራውያን፤* የ10፥16 ማብ ይመ።

14፥10 *የቅጥራን ጕድጓዶች፤* አብዛኛውን ጊዜ የአስፋልት ግግር እስከ ዛሬ ድረስ በሙት ባሕር በስተ ደቡብ ጠረፍ አካባቢ ተንጣሎ ይገኛል። *ተራሮች፤* በዓለም ላይ በረባዳነቱ የታወቀው ሙት ባሕር (ከባሕር ወለል በታች 1300 ጫማ) በተራሮች የተከበበ ነው።

14፥12 *ሎጥ፣ ሰዶም ይኖር ስለ ነበር፤* ክፉ በሆኑት የከተማዋ ነዋሪዎች መካከል ይኖር ነበር (2ጴጥ 2፥8 ይመ)። ሎጥ ምንም እንኳ፣ “ጻድቅ” ሰው ቢሆንም፣ አሁን ግን “የዐመፀኞችን በሴሰኛ ድርጊት” (2ጴጥ 2፥7) በሚኖርበት አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ገባ።

14፥13 *ዕብራዊ፤* የዕብራውያን አባት የሆነው አብራም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዕብራዊ በመባል የመጀመሪያው ሰው ነው (በ10፥21 ማብ ላይ የተጠቀሰውን “ዔቤር” ይመ)። ይህ ስያሜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የብሔር ስያሜ ሲሆን፣ አይሁዳዊ (እስራኤላዊ) ያልሆኑ ሕዝቦች እስራኤላውያንን ለማንኳሰስ ይጠቀሙበታል (39፥17 ይመ)። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ “ሐቢሩ” ወይም “ኢጲሩ” (ዕብራዊ ከሚለው ጋር ተዛማጅነት ሳይኖረው አይቀርም) በመባል የታወቁትን ድኻ፣ ጥገኛና ፈላሽ የሆኑትን ሰዎች ያመለክታል። ስለ እነሱ የተሰጠው ጸያፍ አገላለጽ ‘አማርና ደብዳቤዎች’ በተባሉት ጽሑፎች (በግብፅ የተገኘ የሸክላ ጽላት ነው) ውስጥ ይገኛል። *መምሬ፤* በአብርሃም አጋሮች ስም የተጠራች ከተማ ናት (13፥18 እና ማብ ይመ)።

14፥14 *በቤቱ ተወልደው አድገው የሠለጠኑ 318 ጦረኞች፤* አብራም ብዙ ሀብት እንደነበረው በግልፅ የሚያመለክት ነው። በዕብራይስጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ ላይ፣ “የሠለጠኑ ጦረኞች” የሚለው ሐረግ የሚገኘው በዚህ ቦታ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ፣ ከዚህ ሐረግ ጋር ተዛማጅነት ያለውና፣ “የታጠቁ አገልጋዮች” የሚል ትርጕም ያለው ሌላ ሐረግ በጥንት ጽሑፎች

ድረስ ገሠገሠ:: [15]አብራም ጠላቶቹን ለማጥ
ቃት አገልጋዮቹን ሌሊቱን በቡድን በቡድን ከፋ
ፍሎ ከደማስቆ በስተ ሰሜን እስከሚገኘው
እስከ ሖባ ድረስ አሳደዳቸው:: [16]አብራም ጠላት
የማረከውን በሙሉ አስጣለ፤ የወንድሙን ልጅ
ሎጥን፣ ንብረቱን እንዲሁም ሴቶቹንና ሌሎ
ቹን ምርኮኞች አስመለሰ::

[17]አብራም ኮሎዶጎምርንና አብረውት የተ
ሰለፉትን ነገሥታት ድል አድርጎ ሲመለስ፣
የሰዶም ንጉሥ፣ "የንጉሥ ሸለቆ" ተብሎ በሚጠ
ራው በሴዊ ሸለቆ ሊቀበለው ወጣ::

[18]የልዑል እግዚአብሔር (ኤል-ኤልዮን) ካህን የነ
በረው የሳሌም[ፀ] ንጉሥ መልከ ጼዴቅም እን
ጀራና የወይን ጠጅ ይዞ ወጣ፤ [19]አብራምንም
እንዲህ ሲል ባረከው፤

"ሰማይንና ምድርን የፈጠረ[ፈ] ልዑል
 እግዚአብሔር (ኤል-ኤልዮን) አብራምን ይባርክ፤
[20]ጠላቶችህን አሳልፎ በእጅህ የሰጠህ፣
 ልዑል እግዚአብሔር (ኤል-ኤልዮን)
 ይባረክ::"

አብራምም ካመጣው ሁሉ ዐሥራትን ሰጠው::
[21]የሰዶም ንጉሥም አብራምን፣ ሰዎቹን ለእኔ
ስጠኝ፤ ንብረቱን ግን ለራስህ አስቀር" አለው::
[22]አብራም ግን ለሶዶም ንጉሥ እንዲህ
አለው፤ "ሰማይንና ምድርን ወደ ፈጠረ ወደ
እግዚአብሔር (ያህዌ)፣ ወደ ልዑል አምላክ
(ኤል-ኤልዮን) እጆቼን እንሥቻለሁ፤ [23]'አብራምን
አበለጸግሁት' እንዳትል፣ ብጣሽ ክርም ሆነ
የጫማ ማሰሪያ እንኳ ከአንተ አንዳች አል
ፈልግም:: [24]ሰዎቹ ከበሉትና ከእኔ ጋር ከሄ
ዱት ሰዎች ድርሻ በስተቀር ለራሴ አንዳች
ነገር አልቀበልም፤ አውናን፣ ኤስኮልና መምሬ
ድርሻቸውን ይውሰዱ::"

## እግዚአብሔር ለአብራም የገባው ኪዳን

**15** ከዚህም በኋላ፣ የእግዚአብሔር (ያህዌ)
ቃል እንዲህ ሲል በራእይ ወደ አብ
ራም መጣ፤

"አብራም ሆይ፤ አትፍራ፤
 እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ፤[ፐ]
 ታላቅ ዋጋህም[ሀ] እኔው ነኝ::

[2]አብራምም፣ "እግዚአብሔር (ያህዌ) አምላክ ሆይ፤
ያለ ልጅ የቀረሁ ስለ ሆንሁ፣ የቤቴ ወራሽ[ለ]
የደማስቆ ሰው ኤሊዔዘር ነው፤ ታዲያ ምን
ትሰጠኛለህ?" [3]አንተ ልጆች ስላልሰጠኸኝ፣
ከቤቴ አገልጋይ አንዱ ወራሼ መሆኑ አይ
ቀርም" አለው::

[4]በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር (ያህዌ) ቃል እን
ዲህ ሲል መጣለት፤ "ይህ ሰው ወራሽህ
አይሆንም፤ ነገር ግን ከአብራክህ የሚከፈል

14፥15 ዘፍ15፥2፤ መሳ7፥16፤2ሳሙ8፥5፤1ነገ20፥34፤2ነገ16፥9፤ኢሳ7፥8፤8፥4፤10፥9፤17፥1፤ኤር49፥23:27፤ሕዝ27፥18፤አሞ1፥3-5
14፥16 ቍ11፤1ሳሙ30፥8:18
14፥17 ቍ1:10፤2ሳሙ18፥18
14፥18 ቍ22፤ዘፍ3፥19፤መሳ9፥13፤19፥19፤እስ1፥10፤መዝ7፥8:17፤76፥2፤104፥15፤110፥4፤ምሳ31፥6፤መክ10፥19፤መሓ1፥2፤ዳን7፥27፤ዕብ5፥6፤7፥2:17:21
14፥19 ቍ18:22፤ዘፍ1፥1፤24፥3፤ኢሱ2፥11፤መዝ148፥5፤ማቴ11፥25፤ዕብ7፥6
14፥20 ዘፍ9፥26፤24፥27፤28፥22፤ዘዳ14፥22፤26፥12፤ሉቃ18፥12፤ዕብ7፥4
14፥21 ቍ10:11
14፥22 ቍ10:18:19፤ዘፀ6፥8፤ዘኍ14፥30፤ዘዳ32፥40፤ነህ9፥15፤ሕዝ20፥5፤ዳን12፥7፤ራእ10፥5-6
14፥23 1ሳሙ15፥3:19፤2ነገ5፥16፤አስ8፥11፤9፥10:15
14፥24 ዘፍ13፥18
15፥1 ዘፍ21፥17፤26፥24፤46፥2:3፤ዘፀ14፥13፤20፥20፤ዘኍ12፥6፤24፥4፤ዘዳ33፥29፤ሩት1፥20፤1ሳሙ15፥10፤2ሳሙ7፥4፤22፥3:31፤1ነገ6፥11፤12፥22፤2ነገ6፥16፤2ዜና20፥15:17፤ኢዮ33፥15፤መዝ3፥3፤5፥12፤18፥2:20፤27፥1፤28፥7፤33፥20፤37፥25፤58፥11፤84፥11፤119፥114፤144፥2፤ምሳ2፥7፤30፥5፤ኢሳ3፥10፤7፥4፤41፥10:13-14፤43፥1:5፤ኤር1፥8:13፤ሕዝ3፥16፤ዳን10፥1፤ሐጌ2፥5 15፥2 ቍ8፤ዘፍ14፥15፤ኢሳ49፥22፤ኤር44፥26፤ሕዝ5፥11፤16፥48፤ሐሥ7፥5 15፥3 ዘፍ12፥5፤24፥2:34 15፥4 ገላ4፥28

[ጸ]13 ወይም ዘመድ፣ ወይም ጓድ
[ፀ]18 ኢየሩሳሌም ናት
[ፈ]19 ወይም በቍ 22 ላይ ያለውንም ጨምሮ ባለቤት ሊሆን ይችላል
[ፐ]1 ወይም ገዥ
[ሀ]1 ወይም ዋጋህም እጅግ ታላቅ ይሆናል
[ለ]2 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጕም አይታወቅም

ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል:: *ዳን፤* በሰሜን በኩል የነበረውና በጣም የታወቀው ይህ ከተማ እስከ መሳፍንት ዘመን ድረስ "ዳን" በሚል ስም አልተጠራም (መሳ 18፥19 ይመ):: ይህ ስም በዚህ ቦታ የገባው ከሙሴ ዘመን በኋላ በነብሩ አርታኢዎች ሳይሆን አይቀርም::

14፥17 *'የንጉሥ ሸለቆ'፤* በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ምናል ባትም በስተ ምሥራቅ በኩል የሚገኝ ሳይሆን አይቀርም (2ሳሙ 18፥18 ይመ)::

14፥18 *ካህን... የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም፤* ዕብ 7፥1 ይመ:: በጥንት ዘመን በተለይም እስራኤላውያን ባልሆኑ ሕዝቦች መካከል የክህነትና የንጉሥነት ተግባር የሚከናወነው በራሳቸው በካህናትና በነገሥታት ነበር:: "መልከ ጼዴቅ" ማለት "የእኔ ንጉሥ ጻድቅ ነው" ወይም "የጽድቅ ንጉሥ" ማለት ነው (ዕብ 7፥2 ይመ):: "ሳሌም" የሚለውም ቃል "ኢየሩሳሌም" ለሚለው ቃል የገባ ምኅጻረ ቃል ነው (መዝ 76፥2 ይመ)፤ "ሰላም" ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ተዛማጅነት አለው (ዕብ 7፥2 ይመ):: የኢየሩሳሌም ንጉሥ የነበረው የ"አዶኒጼዴቅ" ስም (ኢሱ 10፥1 ይመ) መልከ ጼዴቅ ከሚለው ስም ጋር በጣም ተመሳሳይ ሲሆን፣ ትርጕሙም "የእኔ ጌታ ጻድቅ ነው" ወይም "የጽድቅ ጌታ" ማለት ነው:: *እንጀራና የወይን ጠጅ፤* የዘወትር ምግብ በመሆኑ (መሳ 19፥19 ይመ) በአዲስ ኪዳን ካለው የጌታ እራት ሥርዐት ጋር ምንም ዝምድና የለውም:: መልከ ጼዴቅ ምግቡንና መጠጡን ያቀረበው ወዳጅነቱንና እንግዳ ተቀባይነቱን ለመግለጽ ነው::

14፥19 *ሰማይንና ምድርን የፈጠረ፣ ልዑል እግዚአብሔር፤* በጥንት ዘመን "ልዑል"፣ "የሰማይ ጌታ/አምላክ" እና "የምድር ፈጣሪ" የሚሉት የማዕረግ ስሞች ለከነዓናውያን አማልክት ውለው እናገኛለን:: ለአማልክቱ የተሰጠው ስያሜና አማልክቱ የሚገኙበት ቦታ (ኢየሩሳሌም በከነዓን እምብርት/መካከለኛ ክፍል ትገኛለች) እንደሚያመለክቱት፣ መልከ ጼዴቅ ምናልባት የከነዓናውያን ንጉሥና ካህን ሳይሆን አይቀርም:: አብራም ግን መልከ ጼዴቅን "ልዑል እግዚአብሔር"፣ "አምላክ" ብሎ በመጥራቱ (ቍ 22) መልከ ጼዴቅ ያውቀው/ያመልከው ስለነበረው እውነተኛውና ብቸኛው አምላክ ይመሰክራል::

14፥20 *አብራም ካመጣው ሁሉ ዐሥራትን ሰጠው፤* ምንም እንኳ መልከ ጼዴቅ ስለ እግዚአብሔር ያለው አመለካከት ጕድለት ያለበት ቢሆንም፣ አብራም ለመልከ ጼዴቅ ባርኮት የሰጠው ምላሽ እንደሚያመለክተው እርሱ የሚያገለግለውን አምላክ መልከ ጼዴቅም ያገለግለው እንደነበር አብራም ተረድቶአል (ቍ 18 ይመ):: ስለዚህ አብራም በምርኮ ካገኘው ሀብት ዐሥራት አውጥቶ ለልዑል እግዚአብሔር አቀረበ፤ ይህ አንድ ዐሥረኛ የንጉሥ ድርሻ ነው (1ሳሙ 8፥15:17 ይመ):: መልከ ጼዴቅ ሊመጣ ላለው "ታላቅ ሊቀ ካህን" (ዕብ 4፥14) ለኢየሱስ አምሳል እንደ ሆነና የሚመጣውም ሊቀ ካህናት፣ ክህነቱ እንደ አሮን የክህነት ሹመት ሳይሆን፣ እንደ መልከ ጼዴቅ የክህነት ሹመት መሆኑን የሚያመለክት ነው (ዕብ 7፥11፤ መዝ 110፥4 ይመ)::

14፥22 *እጆቼን እንሥቻለሁ፤* በጥንት ዘመን መሐላ ሲደረግ እጅን ማንሣት የተለመደ ወግ ነው (ዘዳ 32፥40፤ ራእ 10፥5-6 ይመ)::

14፥23 *ከአንተ አንዳች አልፈልግም፤* ከ2ነገ 5፥16 ጋር ያነጻጽሩ:: አብራም ከእግዚአብሔር በቀር የማንም ባለ ዕዳና ባሪያ እንዳይሆን ቍርጥ አቋም ወሰደ:: እንዲህ ባያደርግ ኖሮ ይህ የከነዓን ንጉሥ የአብራም ንጉሥ ነኝ ሊል ይችል ነበር::

15፥1 *እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ፤* በዚህ ቦታ "ጋሻህ" ወይም "ጌታህ" ማለት ነው አማርጭ ትርጕሙን ይመ፤ ይህም የአብራም ንጉሥ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ያሳያል:: በሌሎች ቦታዎች ላይ ንጉሥ በሚለው ምትክ "ጋሻ" የሚለው ቃል ገብቶ ይገኛል (ዘዳ 33፥29፤ 2ሳሙ 22:3 መዝ 7፥10፤ 84፥9):: *ታላቅ ዋጋህም እኔው ነኝ፤* አብራም ባለጸጋ ሰው ቢሆንም (13፥2)፣ የአብራም ትልቁ ሀብት እግዚአብሔር ብቻ ነው (ከዘዳ 10፥9 ጋር ያነጻጽሩ)::

15፥2 *የደማስቆ ሰው ኤሊዔዘር፤* አብራም ከካራን ተነሥቶ ወደ ደቡብ በሄደ ጊዜ ያገኘው አገልጋይ ሳይሆን አይቀርም (12፥5 ይመ):: ምናልባትም ስሙ ያልተጠቀሰ፣ "የንብረቱ ሁሉ ኀላፊ አገልጋይ" የተባለው (24፥2) ይኸው ሰው ሊሆን ይችላል::

*15፥3-4* በጤግሮስ ወንዝ ኪርኩክ አቅራቢያ ኑዚ ተብሎ በሚጠራውና በሌሎች ቦታዎች የተገኙ ጥንታዊ መዛግብት እንደሚያመላክቱት፣ ልጅ የሌለው አንድ ሰው ከወንድ ባሪያዎቹ መካከል አንዱን እንደ ልጁ ሊያሳድገውና ወራሹም ሊያደርገው ይችላል::

ልጅ ወራሽህ ይሆናል::" 5ወደ ውጪም አው
ጥቶ፣ "ቀና ብለህ ወደ ሰማይ ተመልከት፤
እስቲ መቍጠር ከቻልህ፣ ከዋክብቱን ቍጠ
ራቸው፤ ዘርህም እንዲሁ ይበዛል" አለው::
6አብራም እግዚአብሔርን (ያህዌ) አመነ፤ እር
ሱም ጽድቅ አድርጎ ቈጠረለት::
7ደግሞም እግዚአብሔር፣ "ይህችን ምድር
ላወርስህ፣ ከከለዳውያን ምድር፣ ከዑር ያወ
ጣሁህ እግዚአብሔር (ያህዌ) እኔ ነኝ" አለው::
8አብራምም፣ "እግዚአብሔር (ያህዌ) አምላክ
ሆይ፤ ይህችን ምድር እንደምወርሳት በምን
ዐውቃለሁ?" አለ::
9እግዚአብሔርም (ያህዌ) "እያንዳንዳቸው ሦስት
ዓመት የሆናቸው አንዲት ጊደር፣ አንድ
ፍየልና አንድ በግ፣ በተጨማሪም አንድ ዋኖ
ስና አንድ ርግብ አብረህ አቅርብልኝ" አለው::
10አብራምም እነዚህን ሁሉ አቀረበለት፤
ቈርጦም ሁለት ቦታ ከከፈላቸው በኋላ፣ እያ
ንዳንዱን ክፍል በሌላው ወገን ትይዩ አስቀ
መጠ፤ ዋኖሷንና ርግቧን ግን ለሁለት አል
ከፈላቸውም:: 11አሞሮችም ሥጋውን ለመ
ብላት ወረዱ፤ አብራም ግን አባረራቸው::
12ፀሓይ ልትገባ ስትል አብራም እንቅልፍ
ወሰደው፤ የሚያስፈራም ድቅድቅ ጨለማ
መጣበት:: 13እግዚአብሔርም (ያህዌ) እንዲህ
አለው፤ "ዘርህ በባዕድ አገር ስደተኛ እንደ
ሚሆን በእርግጥ ዕወቅ፤ አራት መቶ ዓመ
ትም በባርነት ተረግጦ ይገዛል:: 14ነገር ግን
በባርነት የሚገዛቸውን ሕዝብ እፈርድበታ
ለሁ፤ ከዚያም ብዙ ሀብት ይዘው ይወጣሉ::
15አንተ ግን ወደ አባቶችህ በሰላም ትሄዳ
ለህ፤ ዕድሜም ጠግበህ ወደ መቃብር ትወ
ርዳለህ፤ 16በአራተኛውም ትውልድ ዘርህ
ወደዚህ ምድር ይመለሳል፤ የአሞራውያን
ኀጢአት ገና ጽዋው አልሞላምና::"
17ፀሓይ ጠልቃ ከጨለመ በኋላ የምድጃ ጢስና
የሚንበለበል ፋና ታየ፤ በተከፈለውም ሥጋ
መካከል ዐለፈ:: 18በዚያ ዕለት እግዚአብሔር
(ያህዌ) ለአብራም እንዲህ ሲል ኪዳን ገባለት፤
"ከግብፅ ወንዝ[a] ጀምሮ እስከ ታላቁ የኤፍራ
ጥስ ወንዝ ድረስ ያለውን ምድር ለዘርህ
እሰጣለሁ፤ 19የምሰጣቸውም የቄናውያንን፣
የቄኔዛውያንን፣ የቃድሞናውያንን፣

15፥5 ዘፍ12፥2፤ኢዮ 11፥8፤35፥5፤መዝ8፥3፤ 147፥4፤ኤር 30፥19፤33፥22፤ሮሜ 4፥18፤ዕብ11፥12
15፥6 መዝ106፥31፤ ሮሜ4፥3:20-24፤ገላ 3፥6፤ያዕ2፥23
15፥7 ዘፍ11፥28፤ 12፥1፤13፥17፤17፥8፤ 28፥4፤35፥12፤48፥4፤ ዘፀ6፥8፤20፥2፤ዘዳ 9፥5፤ሐሥ7፥3:4፤ ዕብ11፥8
15፥8 ቍ2፤ዘዳ12፥ 20፤19፥8፤ሉቃ1፥18
15፥9 1ሳሙ1፥24፤ ዘሌ1፥14፤5፥7:11፤ 12፥8፤ዘኍ19፥2፤ዘዳ 21፥3፤ሆሴ4፥16፤ አሞ4፥1
15፥10 ቍ17፤ዘሌ 1፥17፤5፥8፤ኤር 34፥18
15፥11 ዘዳ28፥26፤ ኤር7፥33
15፥12 ዘፍ2፥21
15፥13 ቍ16፤ዘፀ1፥ 11፤3፥7፤5፥6:10-14: 18፤6፥5፤12፥40፤ዘኍ 20፥15፤ዘዳ5፥15፤12፥ 40፤ኢዮ3፥18፤ሐሥ7፥ 16:17፤ገላ3፥17
15፥14 ዘፍ50፥24፤ ዘፀ3፥8፤6፥6-8፤12፥ 25:32-8፤ዘኍ10፥29፤ ኢሱ1፥2፤ሐሥ7፥7
15፥15 ዘፍ25፥8፤35፥29፤47፥30፤49፥29፤ዘፀ23፥26፤ዘዳ31፥16፤ 34፥7፤ኢሱ14፥11፤መሳ8፥32፤2ሳሙ7፥12፤1ነገ1፥21፤1ዜና29፥28፤ ኢዮ5፥26፤21፥23፤42፥17፤መዝ49፥19፤91፥16፤ምሳ3፥16፤9፥11፤ኢሳ 65፥20 15፥16 ቍ13፤ዘፍ28፥15፤46፥4፤48፥21፤50፥24፤ዘፀ3፥8: 17፤12፥40፤ዘሌ18፥28፤ኢሱ13፥4፤መሳ10፥11፤1ነገ21፥26፤2ነገ16፥3፤ 21፥11፤ሕዝ16፥3 15፥17 ቍ10፤መሳ7፥16:20፤15፥4:5 15፥18 ዘፍ12፥7፤17፥2:4:7፤ዘፀ6፥4፤34፥10:27፤ዘኍ34፥5፤1ዜና16፥16ኢሱ 15፥4:47፤1ነገ8፥65፤2ነገ24፥7፤2ዜና7፥8፤መዝ105፥9፤ኢሳ27፥12፤ ኤር37፥5፤46፥2፤ሰቆ4፥17፤ሕዝ30፥22፤47፥19፤2፥14 15፥19 ዘኍ 24፥21፤መሳ1፥16፤4፥11:17፤5፥24፤1ሳሙ15፥6፤27፥10፤30፥29፤ 1ዜና2፥55

[a]18 *ወይም ደረቅ ወንዝ*

አብራም ኤሊዔዘርን እንደ ልጁ አድርጎ ለማሳደግ ቀደም ብሎ ሳያስብበት ወይም ልጁ ሳያደርገው አይቀርም::

15፥5 ***እስቲ መቍጠር ከቻልህ፣ ከዋክብቱን ቍጠራቸው፤*** 22፥17 ይመ:: በቅርብ ምሥራቅ አገሮች፣ በሌሊት ከ8000 ከዋክብት በላይ በግልጽ ይታያሉ:: ***ዘርህም እንዲሁ ይበዛል፤*** ይህ ቃል ኪዳን በመጀመሪያ የተፈጸመው በግብፅ ነበር (ዘፀ 1፤ ዘዳ 1፥10፤ ዕብ 11፥12 ይመ):: የክርስቶስ የሆኑት ሁሉ የአብራም ልጆች ናቸው (ገላ 3፥29 ይመ)::

*15፥6፤* አብራም "ለሚያምኑ... የሁሉ አባት" ነው (ሮሜ 4፥11)፤ ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ በእምነት መቀበልን አስመልክቶ የሚናገር የመጀመሪያ ጥቅስ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ፣ እግዚአብሔር ከቸርነቱ የተነሣ እርሱ የተናገረውን ቃል በእምነት ለሚቀበል ሁሉ እምነቱን ጽድቅ አድርጐ እንደሚቈጥርለት የሚያስተምር ጥቅስ ነው (ዕብ 11:7)::

15፥7 ***ከዑር ያወጣሁህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤*** የጥንት ንጉሣዊ ቃል ኪዳን አብዛኛውን ጊዜ የሚጀምረው፣ (1) ንጉሡ የራሱን ማንነት በማስታወቅና (2) በአጭር ታሪካዊ መግቢያ ነው፤ ይህም በዚሁ ክፍል ላይ ተመልክቶአል (ዘፀ 20፥2 ይመ)::

15፥8 ***በምን ዐውቃለሁ?፤*** ከሉቃ 1፥18 ጋር ያነጻጽሩ:: አብራም ወንድ ልጅ እንደሚወልድ የተገባለትን ተስፋ አምኖአል፤ ነገር ግን ምድሪቱን እንደሚወርስ ለተገባለት ተስፋ ማረጋገጫ ጠየቀ::

15፥9 ***ሦስት ዓመት የሆናቸው፤*** ለመሥዋዕት የሚቀርቡ እንስሳት ዕድሜያቸው ቢያንስ ሦስት ዓመት መሆን አለበት:: (1ሳሙ 1፥24 ይመ)::

15፥10 ***ዋኖሷንና ርግቧን ግን ለሁለት አልከፈላቸውም፤*** እጅግ ትንንሽ ከመሆናቸው የተነሣ ሊሆን ይችላል (ዘሌ 1፥17 ይመ)::

15፥13 ***በባዕድ አገር፤*** ግብፅ ናት (46፥3-4 ይመ):: ***አራት መቶ ዓመት፤*** ጥቅል ቍጥር ነው፤ በዘፀ 12፥40 ላይ እንደተገለጸው የእስራኤል ሕዝብ በግብፅ የቆየው ለ430 ዓመት ያህል ነበር::

*15፥15፤* በዚህ ክፍል ላይ የተሰጠው ተስፋ በ25፥8 ላይ እንደ ተፈጸመ ተጽፎአል::

15፥16 ***በአራተኛውም ትውልድ፤*** ከ400 ዓመት በኋላ ማለት ነው (ቍ 13 ይመ):: "አንድ ትውልድ" የሚባለው አንድ ሰው የመጀመሪያ ልጁን እስከሚወልድበት ጊዜ ድረስ ያለው ዘመን ነው፤ አብራምን በተመለከተ ግን አንድ ትውልድ 100 ዓመት ነው (21፥5 ይመ):: ***የአሞራውያን ኀጢአት ገና ጽዋው አልሞላምና፤*** የከነዓን ሃይማኖቶች የቱን ያህል በኀጢአት የተበከሉ እንደነበሩ በሰሜን ሶሪያ ጠረፍ፣ ራስ ሻምራ (በጥንት ኡጋሪት) በተባለው ቦታ ከ1929 ወዲህ በሥነ ቅርስ ጥናት የተገኙ ጥንታዊ መዛግብቶችና የራሳቸው የከነዓናውያን የታሪካዊ ሥነ ጽሑፎች አረጋግጠዋል:: እነዚህ ሕዝቦች ጣዖት አምላኪዎች ከመሆናቸውም በላይ ሕፃናትን መሠዋት፣ ጣዖትን ማምለክና መናፍስትን መጥራት በአምልኮ ሥርዐቶቻቸው ላይ የሚገኙ ልማዶች ናቸው (ከዘዳ 18፥9-12 ጋር ያነጻጽሩ):: እግዚአብሔር ግን እንዲህ የረከሱ ከነዓናውያንን እንኳ ይታገሣቸው ነበር::

15፥17 ***የምድጃ ጢስና የሚንበለበል ፋና ታየ፤*** የእግዚአብሔርን መገኘት የሚያስታውቅ ምልክት ነው (ዘፀ 3፥2፤ 14፥24፤ 19፥18፤ 1ነገ 18፥38፤ ሐሥ 2፥3-4 ይመ):: ***በተከፋፈለውም ሥጋ መካከል አለፈ፤*** በታረዱት እንስሳት ሥጋ መካከል ማለት ነው (ቍ 10):: በጥንት ዘመን፣ ቃል ኪዳን የተጋቡ ሁለት ወገኖች የተጋቡትን ቃል ኪዳን በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ የሚያከብሩ መሆናቸውን የሚያረጋግጡት አንድ እንስሳ ዐርደው፣ ሥጋውን ከቈራረጡ በኋላ የተቈራረጠውን ሥጋ በግራና በቀኝ አስቀምጠው በመካከሉ በማለፍ ነው (ኤር 34፥18-19 ይመ):: ይህ ጥንታዊ ልማድ የሚያመለክተው፣ "የገባሁትን ቃል ኪዳንና መሐላ ባልጠብቅ በእንስሳቱ ላይ የደረሰው በእኔም ላይ ይድረስ" በማለት በራስ ላይ መርገምንና መኰነንን መጥራት ነው:: እግዚአብሔር የአብራምን እምነት ጽድቅ አድርጐ ከቈጠረለት በኋላ፣ ከቸርነቱ የተነሣ አብራም ቃል ስለተገባለት ምድር ከእርሱ የሚፈልገውን ማረጋገጫ ሰጠው:: እግዚአብሔር ለኖኅ ተስፋን መሠረት ያደረገ ቃል ኪዳን እንደገባለት ሁሉ፣ ለአብራምም እንዲሁ አደረገ (9፥9 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም "በብሉይ ኪዳን የተደረጉ/የተገቡ ዋና ዋና ኪዳኖች" የሚለውን ሰንጠረዥ በገጽ 18 ላይ ይመ)::

15፥18 ***ኪዳን ገባለት፤*** ቃል በቃል ሲተረጐም "ቃል ኪዳን ከፈለለት/ቈጠረለት" ማለት ሲሆን፣ የሚያመለክተውም ሁለት ቃል ኪዳን ተጋቢዎች የሚያርዱትን እንስሳ ነው (ይኸው የዕብራይስጥ ግስ በኤር 34፥18 ላይ "የገቡትን" እና "ከፍለው" ተብሎ ተተርጕሞአል):: ***ከግብፅ ወንዝ፤*** ከሲና በስተ ሰሜን ምሥራቅ በኩል የሚገኘውና በአሁኑ ወቅት ዋዲ ኤል-አሪሽ ተብሎ የሚጠራው ሳይሆን አይቀርም:: ***ምድር... እሰጣለሁ፤*** እግዚአብሔር ይህን ኪዳን በኢያሱ በኩል ፈጽሞአል (ኢሱ 1፥2-9፤ 21፥43፤ እንዲሁም 1ነገ 4፥20-21 ይመ)::

*15፥19-21፤* ተመሳሳይ የዐሥር ሕዝቦች ዝርዝር በ10፥15-18

[20]የኬጢያውያንን፣ የፌርዛውያንን፣ የራፋይ
ምን፣ የአሞራውያንን፣ የከነዓናውያንን፣ የጌር
ጌሳውያንንና የኢያቡሳውያንን ምድር ነው።"

## አጋርና እስማኤል

16 የአብራም ሚስት ሦራ፣ ልጆች አል
ወለደችለትም ነበር፤ እርሷም አጋር
የምትባል ግብፃዊት አገልጋይ ነበረቻት።
[2]አብራምንም፣ "እግዚአብሔር (ያህዌ) ልጅ እን
ዳልወልድ አድርጎኛል። ምናልባት በእርሷ
በኩል ልጆች አገኝ እንደሆን ሂደህ ከአገ
ልጋዬ ጋር ተኛ" አለችው።
አብራምም ሦራ ባለችው ተስማማ። [3]አብ
ራም በከነዓን ምድር ዐሥር ዓመት ከኖረ
በኋላ ሚስቱ ሦራ ግብፃዊት አገልጋይዋን አጋ
ርን ሚስት እንድትሆነው ለባሏ ሰጠችው። [4]አብ
ራምም ከአጋር ጋር ተኛ፤ እርሷም ፀነሰች።
አጋርም ነፍሰ ጡር መሆኗን ባወቀች ጊዜ
እመቤቷን መናቅ ጀመረች። [5]ሦራም አብ
ራምን፣ "ለደረሰብኝ በደል ተጠያቂው አንተ
ነህ፤ አገልጋዬ ዕቅፍህ ውስጥ እንድትገባ
እኔው ሰጠሁህ፤ አሁን ግን ይኸው ማርገዟን
ስታውቅ ትንቀኝ ጀመር፤ እግዚአብሔር (ያህዌ)
በአንተና በእኔ መካከል ይፍረድ" አለችው።
[6]አብራምም፣ "አገልጋይሽ እንደሆነች በእ
ጅሽ ውስጥ ናት፤ የፈለግሽውን አድርጊባት"
አላት። ከዚያም ሦራ ስላሠቃየቻት አጋር
ጥላት ኰበለለች።
[7]*የእግዚአብሔር (ያህዌ) መልአክ* አጋርን በአ
ንድ የውሃ ምንጭ አጠገብ በምድረ በዳ
አገኛት፤ ምንጩም ወደ ሱር በሚወስደው
መንገድ ዳር ነበር። [8]*መልአኩም*፣ "የሦራ
አገልጋይ አጋር ሆይ፤ ከየት መጣሽ? ወዴ
ትስ ትሄጃለሽ?" አላት፤
እርሷም፣ "ከእመቤቴ ከሦራ ኰብልዬ መም
ጣቴ ነው" ብላ መለሰች።
[9]*የእግዚአብሔርም (ያህዌ)* መልአክ፣ "ወደ
እመቤትሽ ተመለሽ፤ ለእርሷም ተገዥላት"
አላት። [10]*ደግሞም* መልአኩ፣ "ዘርሽን እጅግ
አበዛለሁ፤ ከብዛቱም የተነሣ ሊቈጠር አይ
ችልም" አላት።
[11]*የእግዚአብሔርም (ያህዌ)* መልአክ በተጨማሪ
እንዲህ አላት፤

"እነሆ፤ ፀንሰሻል፤
ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ፤
*እግዚአብሔር (ያህዌ)* ችግርሽን ተመልክቶአል፤
ስሙን እስማኤል[a] ትዪዋለሽ።
[12]እርሱም እንደ ዱር አህያ ይሆናል፤
እጁንም ባገኘው ሰው ሁሉ ላይ ያነሣል፤
ያገኘውም ሁሉ እጁን ያነሣበታል፤
ከወንድሞቹ ሁሉ ጋር እንደ ተጣላ
ይኖራል።"[a]

[13]እርሷም ያናገራትን *እግዚአብሔርን (ያህዌ)*፣
ኤልሮኢ ብላ ጠራችው፤ ምክንያቱም "የሚ
ያየኝን አሁን አየሁት"[a] ብላ ነበርና። [14]ከዚህ
የተነሣ የዚያ ምንጭ ስም፣ "ብኤርለሃይሮኢ"[c]
ተብሎ ተጠራ፤ እስካሁንም በቃዴስና በባሬድ

15፥20 ዘፍ10፥15፤ 13፥7፤14፥5፤ዘዳ7፥1
15፥21 ዘፍ10፥16፤ ኢሱ3፥10፤24፥11፤ ነህ9፥8
16፥1 ቍ3-4:8:15፤ ዘፍ11፥29:30፤21፥14፤24፥61፤25፥12፤27-61፤29፥24:29፤31፥33፤46፥18፤ሉቃ1፥7:36፤ገላ4፥24-25
16፥2 ዘፍ19፥32፤ 29፥31፤30፥2-4:9-10
16፥3 ዘፍ12፥4:5
16፥4 ቍ1፤ዘፍ30፥1፤1ሳሙ1፥6
16፥5 ዘፍ31፥53፤ዘፀ5፥21፤መሳ11፥27፤ 1ሳሙ-24፥12:15፤ 26፥10:23፤መዝ50፥6፤75፥7
16፥6 ዘፍ31፥50፤ ኢሱ9፥25
16፥7 ቍ11:14፤ ዘፍ20፥1፤21፥17:19፤ 22፥11:15፤24፥7:40፤ 25፥18፤31፥11፤48፥16፤ዘፀ፥2፤14፥19፤15፥22፤23፥20:23፤32፥34፤33፥2፤ዘኍ22፥22፤ መሳ2፥1፤6፥11፤13፥3፤1ሳሙ15፥7፤27፥8፤ 2ሳሙ24፥16፤1ነገ19፥5፤2ነገ1፥3፤19፥35፤ መዝ34፥7፤ዘካ1፥11፤ ሐሥ5፥19
16፥8 ቍ1፤ዘፍ3፥9
16፥10 ዘፍ13፥16
16፥11 ቍ7፤ዘፍ3፥15፤12፥2-3፤17፥19፤18፥19፤21፥13፤29፥32፤31፥42፤37፥25: 28፤39፥1፤ዘፀ2፥24፤ 3፥7:9፤4፥31፤ዘኍ20፥16፤ዘዳ26፥7፤ነህ9፥7፤ ኢሱ44፥1፤መሳ8፥24፤1ሳሙ9፥16፤አሞ3፥2፤ማቴ1፥21፤ሉቃ1፥13:31፤ ሐሥ5፥19
16፥12 ዘፍ25፥18፤ኢዮ6፥5፤11፥12፤24፥5፤39፥5፤መዝ104፥11፤ኤር2፥24፤ሆሴ8፥9
16፥13 ዘፍ32፥30፤33፥10፤ዘፀ24፥10፤33፥20:23፤ዘኍ12፥8፤መሳ6፥22፤13፥22፤መዝ139፥1-12፤ኢሳ6፥5
16፥14 ቍ7፤ዘፍ14፥7፤24፥62፤25፥11

[a]11 *እስማኤል ማለት እግዚአብሔር ይሰማል ማለት ነው*
[a]12 *ወይም በስተ ምሥራቅ ይኖራል* [a]13 *ወይም በኋላዬ አየሁት*
[c]14 *ብኤርለሃይሮኢ ማለት የሚያየኝ 'የሕያዉ' ምንጭ ማለት ነው*

ላይ ይገኛል (ያንኑ ማብ ይመ)። ዐሥር ቍጥር ፍጹምነትን ያመለ ክታል።

16፥1 *ልጆች አልወለደችለትም፤* የ11፥30 ማብ ይመ። *ግብፃዊት፤* አጋር የተገኘችው አብራምና ሦራ በግብፅ በነበሩበት ወቅት ሳይሆን አይቀርም (12፥10-20 ይመ)።

16፥2 *እግዚአብሔር ልጅ እንዳልወልድ አድርጎኛል፤* እግ ዚአብሔር በ15፥4 ላይ ለአብራም ከተገለጠለት ወዲህ ጥቂት ጊዜ አልፎአል፤ ሦራም ትዕግሥት በማጣቷ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን እንዳጠፈ ያሰበች መሆኑን ትጠቍማለች። *ሂደህ ከአገል ጋዬ ጋር፤* ወራሽ ወንድ ልጆችን በዚህ ዐይነት መንገድ ማግኘት በጥንት ዘመን የነበረ ልማድ ሲሆን፣ ይህም ሐሙራቢ በቀረጸው በአሦራውያን የጋብቻ ውልና በኑዚ ጽላቶች ላይ በግልፅ ተጠቅሶ ይገኛል (የ15፥3-4 ማብ ይመ)። ሦራ የመካንነቷን ችግር በራሷ መንገድ ለመፍታት ሞከረች።

16፥3 *ዐሥር ዓመት፤* በዚህ ጊዜ የአብራም ዕድሜ ሰማንያ አምስት ዓመት ነበር (12፥4፤ 16፥16 ይመ)።

16፥4 *እመቤቷን መናቅ፤* ፍናናም እንደዚሁ ሐናን ንቃት ነበር (1ሳሙ 1፥6 ይመ)።

16፥5 *እግዚአብሔር በአንተና በእኔ መካከል ይፍረድ፤* የጥላቻ ወይም የጥርጥር አገላለጽ ነው (31፥53 ይመ፤ እንዲሁም 31፥49 ይመ)።

16፥7 *የእግዚአብሔር መልአክ፤* የእግዚአብሔር መልአክ፣ በእግዚአብሔር ሆኖ የተናገረው በአንደኛ መደብ ነጠላ ቍጥር (ቍ 10) በመሆኑና አጋርም፣ "ያናገራትን እግዚአብሔርን ኤል ሮኢ ብላ ጠራችው" (ቍ 13) ስለሚል፣ ይህ መልአክ ባንድ ወገን ከጌታ የሚለይ ቢሆንም (ምክንያቱም መልእክተኛ ተብሎ ተጠርቶአል፤ "መልአክ" ለሚለው የዕብራይስጡ ፍች፣ "መልእክ ተኛ" ማለት ነው) ከጌታ ጋር የሚመሳሰል ይመስላል። እንዲህ ያለውን ልዩነትና ተመሳሳይነት በ19፥1:21፤ 31፥11:13፤ ዘፀ 3፥2: 4፤ መሳ 2፥1-5፤ 6፥11-12:14፤ 13፥3:6:8-11:13:15-17:20-23፤ ዘካ 3፥1-6፤12፥8 ላይ ይመ። በክርስቲያኖች ትውፊታዊ አተረጓ ጐም መሠረት፣ ይህ "መልአክ" ሥጋ ከመሆኑ በፊት የእግዚአ ብሔር መልእክተኛና አገልጋይ ሆኖ የተገለጠው/የታየው ክርስቶስ ነው። ይሁን እንጂ መልአኩ የእግዚአብሔር ልዩ መልእክተኛ በመሆን እግዚአብሔርን ወክሎና የእርሱንም ሥልጣን ይዞ በላከው ስም (ይህ ከላከው ጋር ያመሳስለዋል) ተናግሮ ሊሆን ይችላል (በተለይ 19፥21 ይመ፤ ከ18፥2:22፤ 19፥2 ጋር ያነጻጽሩ)። እንግዲህ "ይህ መልአክ" የሥላሴ ሁለተኛው አካል ይሁን ወይም አይሁን እርግጠኛ መሆን አይቻልም። *ሱር፤* ከግብፅ በስተ ምሥራቅ ይገ ኛል (25፥18፤ 1ሳሙ 15፥7 ይመ)።

16፥8 *ከእመቤቴ... ኰብልዬ፤* አጋር ወዴት እንደምትሄድ በትክክል ካለማወቋ የተነሣ፣ መልአኩ ካቀረበላት ጥያቄዎች መካ ከል የመጀመሪያውን ብቻ መለሰችለት።

*16፥10፤* ይህ የተስፋ ቃል በ17፥20 ላይ እንደ ገና የተረጋ ገጠ ሲሆን፣ በ25፥13-16 ላይ ደግሞ ተፈጽሞአል።

16፥11 *እስማኤል፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ። ይህ አብ ራምና ሦራ በአጋር ላይ የፈጸሙትን ክፋት እግዚአብሔር አይቶ ምላሽ መስጠቱን የሚያመለክት ነው።

16፥12 *እንደ ዱር አህያ፤* እስማኤል እንደ ዱር አህያ ከሰው ተለይቶ በየምድረ በዳው ይቅበዘበዛል (ኢዮ 24፥5፤ ሆሴ 8፥9 ይመ)። *እንደ ተጣላ፤* በሦራና በአጋር መካከል (ቍ 4-6 ይመ) የነበረው ጠላትነት ወደ ዘሮቻቸው ተላለፈ (25፥18 ይመ)።

16፥13 *"የሚያየኝን አሁን አየሁት"፤* አማራጭ ትርጕ ሙን ይመ። ከዘፀ 33፥23 ጋር ያነጻጽሩ። በጥንት ዘመን እግዚ አብሔርን ማየት ሞትን ያመጣል ተብሎ ይታመን ነበር (32፥30፤ ዘፀ 33፥20 ይመ)።

16፥14 *"ብኤርለሃይሮኢ"፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ፤ ለዚህ ቃል አማራጭ ሊላው ትርጓሜ፣ "ሕያው የሆነውና የሚያ የኝ አምላኬ" የሚለው ነው። *በቃዴስ፤* የ14፥7 ማብ ይመ።

መካከል ይገኛል።
15አጋር ለአብራም ወንድ ልጅ ወለደች
ለት፤ አብራምም ስሙን እስማኤል ብሎ
ጠራው። 16አብራም፣ አጋር እስማኤልን በወ
ለደች ጊዜ ዕድሜው 86 ዓመት ነበር።

## የግዝረት ኪዳን

17 አብራም ዕድሜው 99 ዓመት በሆነ
ጊዜ፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ተገልጦ
ለት እንዲህ አለው፤ “እኔ ኤልሻዳይ”[ተ] ነኝ፤
በፊቴ ተመላለስ፤ ነቀፋም አይኑርብህ፤ 2በእ
ኔና በአንተ መካከል የተመሠረተውን ኪዳን
አጸናለሁ፤ ዘርህንም እጅግ አበዛለሁ።”
3አብራም በግንባሩ መሬት ላይ ተደፋ፤
እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) እንዲህ አለው፤ 4“እነሆ፤
የምገባልህ ኪዳን ይህ ነው፤ የብዙ ሕዝቦች
አባት ትሆናለህ። 5ከእንግዲህ ወዲያ ስምህ
አብራም[ሀ] መባሉ ቀርቶ አብርሃም ይሆናል፤
የብዙ ሕዝቦች አባት አድርጌሃለሁና። 6ዘር
ህን እጅግ አበዛለሁ፤ ብዙ ሕዝብም አደር
ግሃለሁ፤ ነገሥታትም ከአንተ ይወጣሉ። 7በእ
ኔና በአንተ፣ ከአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር
ከትውልድ እስከ ትውልድ የዘላለም ኪዳኔን
እመሠርታለሁ፤ በዚህም የአንተና ከአንተም

16፥15 ቍ1፤ዘፍ 17፥18፤21፥9፤25፥12፤28፥9፤ገላ4፥22
16፥16 ዘፍ12፥4
17፥1 ዘፍ5፥22፤12፥4፡7፤20፥5፤28፥3፤35፥11፤43፥14፤48፥3፤49፥25፤ዘፀ6፥3፤ዘዳ18፥13፤ሩት1፥20፤1ነገ3፥6፤9፥4፤ኢዮ1፥1፤5፥17፤6፥4፡14፤22፥21፤33፥16፡19፤መዝ15፥2፤18፥23፤78፥72፤101፥2፤ኢሳ13፥6፤ሚክ6፥9፤ኢል1፥15
17፥2 ዘፍ12፥2፤15፥8፤22፥16-18
17፥3 ቍ17፤ዘፍ18፥2፤19፥1፤33፥3፤ዘፀ18፥7፤ዘኍ14፥5፤ኢሱ5፥14፤7፥6፤መሳ13፥20፤ሕዝ1፥28፤3፥23
17፥4 ቍ16፤ዘፍ12፥2፤15፥18፤25፥23
17፥5 ቍ15፤ዘፍ32፥28፤35፥10፤37፥3፡13፤43፥6፤46፥2፤1ነገ18፥31፤2ነገ17፥34፤1ዜና1፥34፤ነህ9፥7፤ኢሳ48፥1፤ዮሐ1፥42፤ሮሜ4፥17
17፥6 ቍ16፡19፤

በኋላ የዘርህ አምላክ (ኤሎሂም) እሆናለሁ። 8ይህ
ችን አሁን በእንግድነት የምትኖርባትን የከ
ነዓንን ምድር በሙሉ ለአንተና ከአንተም
በኋላ ለዘርህ ለዘላለም ርስት አድርጌ እሰ
ጣለሁ፤ አምላካቸውም (ኤሎሂም) እሆናለሁ።”
9ከዚያም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) አብርሃምን እን
ዲህ አለው፤ “በአንተም በኩል፣ አንተና ከአ
ንተ በኋላ የሚመጣው ዘርህ ከትውልድ እስከ
ትውልድ ኪዳኔን ትጠብቃላችሁ። 10አንተና
ከአንተም በኋላ የሚመጣው ዘርህ የምትጠ
ብቁት ኪዳን ይህ ነው፤ በመካከላችሁ ያለ
ወንድ ሁሉ ይገረዝ። 11ስለዚህ ሁላችሁም ሸለ
ፈታችሁን ትገረዛላችሁ፤ ይህም በእኔና በእናንተ

ዘፍ1፥28፤18፥10፤21፥1፤22፥17፤26፥22፤28፥3፤35፥11፤36፥31፤41፥52፤47፥27፤48፥4፤49፥22፤ዘሌ26፥9፤ዘዳ7፥13፤ኢሳ51፥2፤ማቴ1፥6
17፥7 ዘፍ6፥18፤9፥16፤15፥18፤ዘፀ7፥20፥2፤29፥45፡46፤ዘሌ11፥44-45፤18፥2፤22፥33፤25፥38፤26፥9፡12፡15፡45፤ዘኍ15፥41፤ዘዳ4፥20፤7፥6፡21፤29፥13፤2ሳሙ7፥24፤ኤር14፥9፤ሮሜ9፥8፤ገላ3፥16፤ዕብ13፥20፤ራእ21፥7 17፥8 ቍ7፤ዘፍ10፥19፤12፥7፤15፥7፤23፥4፤28፥4፤35፥27፤37፥1፤ዘፀ6፥4፤1ዜና29፥15፤ኤር31፥1 17፥9 ዘፍ18፥19፤22፥18፤ዘፀ19፥5፤ዘዳ5፥2 17፥10 ቍ23፤ዘፍ21፥4፤ዘሌ12፥3፤ኢሱ5፥2፡5፡7፤ዮሐ7፥22፤ሐሥ7፥8፤ሮሜ4፥11 17፥11 ዘፍ9፥12፤ዘፀ2፥48፤ዘዳ10፥16፤ሮሜ4፥11

[ተ]1 *ሁሉን የሚገዛ ማለት ነው*
[ሀ]5 *አብራም ማለት የከበረ አባት ማለት ነው*

*17፥1 ዕድሜው 99 ዓመት በሆነ ጊዜ፤* በዚህ ወቅት እስማኤል ከተወለደ ዐሥራ ሦስት ዓመት ዐልፎት ነበር (16፥16፤ 17፥24-25 ይመ)። *ተገለጠለት፤* የ12፥7 ማብ ይመ። *እኔ... ነኝ፤* የ15፥7 ማብ ይመ። *ኤልሻዳይ፤* ቃሉ በዕብራይስጥ ሁሉን ቻይ አምላክ ማለት ነው፤ ምናልባት፣ “ተራራው አምላክ” የሚል ትርጒም ሳይኖረው (ይህም የማይታየውን የእግዚአብሔርን ኀይል ወይም ተራሮች የእግዚአብሔር መኖሪያ መሆናቸውን ምሳሌያዊ በሆነ መንገድ የሚገልጽ ሊሆን ይችላል) አይቀርም (መዝ 121፥1 ይመ)። ይህ ስም እግዚአብሔር ራሱን ለእስራኤል ርእሳን አበው የገለጠበት ልዩ ስም ነው (ዘፀ 6፥3 ይመ)። “ሻዳይ” የሚለው ቃል በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ ሠላሳ አንድ ጊዜ፣ በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ደግሞ ዐሥራ ሰባት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል። *በፊቴ ተመላለስ፤ ነቀፋም አይኑርብህ፤* “ከእኔ ጋር ነቀፋ የሌለበት ሰው ሆነህ ተራመድ” ማለት ይመስላል (የ5፥22፤ 6፥8-9 ማብ ይመ)። አብራምና ሦራ በራሳቸው መንገድ ባዘጋጁት ሴት አማካይነት፣ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል እውን ለማድረግ ሙከራ ካደረጉ በኋላ እግዚአብሔር ለአብራም ተገለጠለት። አብራም የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል መቀበል ከፈለገ፣ በእግዚአብሔር ፊት ታማኝና ታዛዥ አገልጋይ መሆን እንዳለበት እግዚአብሔር በግልጽ አስታውቈታል። እምነቱም፣ “በእምነት አማካይነት ወደሚገኘው መታዘዝ” የተገለጠ መሆን አለበት (ሮሜ 1፥5፤ ም 22 ይመ)።

17፥2 *ኪዳን፤* 12፥2-3፤ 13፥14-16፤ 15፥4-5 ይመ። ኪዳኑ የእግዚአብሔር ነው። ከቍ 2-21 ባለው ክፍል ላይ እግዚአብሔር ይህንን ኪዳን፣ “ኪዳኔ” በማለት ዘጠኝ ጊዜ ይጠራዋል፤ ይህን ኪዳን የመሠረተው (15፥18 ይመ)፣ ያጸናው (ቍ 2) እና ያቆመው (ቍ 7) እርሱ ነው። *ዘርህን፤* 13፥16 እና ማብ ይመ። ከዚህ በፊት እግዚአብሔር የተስፋዪቱን ምድር አስመልክቶ የገባውን ቃል ኪዳን እንዲጠብቅ ቃል ገብቶ ነበር (ም 15)፤ በዚህ ቦታ ደግሞ የገባውን ቃል ኪዳን በማስፋት፣ ኪዳኑ ዘሮቹን ሁሉ እንደሚያጠቃልል ተናገረ።

17፥5 *አብራም... አብርሃም፤* የመጀመሪያ ስሙ “የከበረ አባት” ማለት ሲሆን፣ ይህም እግዚአብሔርን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም (ማለትም “እግዚአብሔር የከበረ አባት ነው”)። *ስምህ... ይሆናል፤* እግዚአብሔር ለአብራም አዲስ ስም በመስጠት (ነህ 9፥7 ይመ) የእርሱ የራሱ አገልጋይ መሆኑን አረጋገጠ (የ1፥5፤ 2፥19 ማብ ይመ)።

17፥6 *ሕዝብም...ነገሥታትም፤* ይህ የተስፋ ቃል ለሦራም ተሰጥቶ ነበር (ቍ 16)፤ ለያዕቆብም ታድሶ ነበር (35፥11፤ 48 ይመ)። ቃሉ የአብርሃም ልጆች አንድ ቀን እንደ ኖኅ ልጆች (ም 10 ይመ) በዝተውና ብዙ ሕዝብ ሆነው በምድር እንደሚሠራጩ ያመለክታል፤ ይህ የተስፋ ቃል በመጨረሻ በሮሜ 4፥16-18፤ 15፥8-12፤ ገላ 3፥2፤ ራእ 7፥9፤ 21፥24 ላይ ተፈጽሞአል።

17፥7 *የዘላለም፤* ከእግዚአብሔር አንጻር ሲታይ የዘላለም ኪዳን ቢሆንም (ቍ 13፡19 ይመ)፣ ከሰው አንጻር ሲታይ ግን ሊጣስ የሚችል ኪዳን ነው (ቍ 14 ይመ፤ ከኢሳ 24፥5፤ ኤር 31፥32 ጋር ያነጻጽሩ)። *የአንተ... አምላክ እሆናለሁ፤* እግዚአብሔር ለገባው ኪዳን መሠረት ሲሆን፣ በብሉይ ኪዳን ተደጋግሞ የተነገረ ቃል ነው (ለምሳሌ ቍ 8፤ ኤር 24፥7፤ 31፥33፤ ሕዝ 34፥30-31፤ ሆሴ 2፥23፤ ዘካ 8፥8 ይመ)። ይህም እግዚአብሔር የሕዝቡ ጠባቂ፣ ለሕዝቡ የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያዘጋጅና ለሕዝቡም ታላቅ በረከትን አንድ ቀን እንደሚሰጥ የሚያረጋግጥ ዋስትና ነው (15፥1 ይመ)።

17፥8 *ምድር፤* 12፥7፤ 15፥18፤ ሐሥ 7፥5 ይመ። *ለዘላለም ርስት፤* የከነዓን ምድር ከእግዚአብሔር የተሰጠች የዘላለም ርስት ብትሆንም፣ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ካለመታዘዙ የተነሣ ምድሪቱ ለጊዜው ልትወሰድባቸው ችላለች (ዘዳ 28፥62-63፤ 30፥1-10 ይመ)።

17፥9 *በአንተም በኩል፤* እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለትን ኪዳን እንደ ገና ካስታወሰውና (15፥8-12 ይመ) ኪዳኑም ወደፊት ከእርሱ የሚገኙትን ዘሮቹን ሁሉ እንደሚመለከት ካስታወቀው በኋላ፣ “በፊቴ ተመላለስ፤ ነቀፋም አይኑርብህ” በማለት አብርሃምም በበኩሉ ለእግዚአብሔር ኪዳን እንዲገባ ጠየቀው። *ኪዳኔን ትጠብቃላችሁ፤* ለአብርሃም የተሰጠውን የተስፋ ቃል ለመካፈል ታዛዥ ሆኖ መገኘት ወሳኝ ነው (18፥19፤ 22፥18፤ 26፥4-5 ይመ)።

17፥10 *ይገረዝ፤* ግዝረት እግዚአብሔር ላቆመው “ኪዳን ምልክት” (ቍ 11) ሲሆን፣ አብርሃም ራሱን ለእግዚአብሔር ለመስጠት የገባው ኪዳን የሚታመንበትና የሚያገለግለው አምላክ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን የሚገልጽ ነው። ግዝረት ራስን በመሐላ ለእግዚአብሔር የመስጠት ምልክት ነው፤ (ይህም እግዚአብሔር ከማለው መሐላ ጋር ተመሳሳይ ነው የ15፥17 ማብ ይመ)። መሐላው እንዲህ የሚል ነው፦ “ለእግዚአብሔር ታማኝና ታዛዥ ሆኜ ካልተገኘሁ የሥጋ ሸለፈቴን እንደ ቈረጥሁ ሁሉ የጌታ ሰይፍ እኔንና ልጆቼን ይቍረጥ” (ቍ 14 ይመ)። በዚህ ዐይነት አብርሃም ራሱን በንጉሡ በእግዚአብሔር አገዛዝ ሥር በማድረግ ራሱን፣ ዘሮቹንና ሀብቱን ሁሉ ለጌታ አገልግሎት መለየት ነበረበት። ግዝረት ለጌታ መለየትን ወይም መቀደስን የሚያሳይ መሆኑን ለመገንዘብ ዘፀ 6፥12፤ ዘሌ 19፥23፤ 26፥41፤ ዘዳ 10፥16፤ 30፥6፤ ኤር 4፥4፤ 6፥10፤ 9፥25-26፤ ሕዝ 44፥7፡9 ይመ። ሌሎችም ሕዝቦች የግዝረት ልማድ ቢኖራቸውም (ኤር 9፥25-26፤ ሕዝ 32፥18-19 ይመ) ልማዱን የሚፈጽሙት እንደ እስራኤል የኪዳን ምልክት እንዲሆን በማሰብ አልነበረም።

መካከል ላለው ኪዳን ምልክት ይሆናል::
[12]የሚመጣውም ትውልድ ሁሉ፣ ማንኛውም
ወንድ ልጅ፣ ስምንት ቀን ሲሞላው ይገረዝ፤
እንደዚሁም በቤትህ የተወለደውና ከውጭ
በገንዘብ የተገዛ ባዕድ ሁሉ ይገረዝ:: [13]በቤ
ትህ የተወለደም ሆነ በገንዘብህ የተገዛ ሁሉ
መገረዝ አለበት፤ በሥጋችሁ የሚፈጸመው
ይህ ኪዳኔ የዘላለም ኪዳን ይሆናል:: [14]የሥጋ
ሸለፈቱን ያልተገረዘ ማንኛውም ወንድ ኪዳ
ኔን በማፍረሱ ከወገኖቹ ይወገድ::"
[15]እግዚአብሔር (ኤሎሂም) አብርሃምን እንዲህ
አለው፤ "ሦራን ከእንግዲህ ሦራ ብለህ አትጠራ
ትም፤ ስሟ ከዛሬ ጀምሮ ሣራ ይሁን:: [16]እኔ
እባርካታለሁ ከእርሷም ወንድ ልጅ እሰጥ
ሃለሁ፤ የብዙም ሕዝቦች እናት ትሆን ዘንድ
እባርካታለሁ፤ የሕዝቦችም ነገሥታት ከእርሷ
ይወጣሉ::"
[17]አብርሃምም በግንባሩ መሬት ላይ ተደፋ፤
ሣቀና በልቡ፣ "እንዲያው ምንስ ቢሆን
የመቶ ዓመት ሽማግሌ የልጅ አባት መሆን
ይችላልን? ሣራስ በዘጠና ዓመቷ ልጅ መው
ለድ ትችላለችን?" አለ:: [18]አብርሃም እግዚ
አብሔርን (ኤሎሂም)፣ "እስማኤልን ብቻ ባርከህ
ባኖርህልኝ" አለው::
[19]እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) እንዲህ አለ፤ "ይሁን
እሺ፤ ነገር ግን ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅ
ትወልድልሃለች፤ ስሙንም ይስሐቅ^ ብለህ
ትጠራዋለህ፤ እኔም ከእርሱ በኋላ ለዘሩ
ሁሉ የሚሆን የዘላለም ኪዳን ከእርሱ ጋር
እገባለሁ:: [20]ስለ እስማኤልም ቢሆን ልመ
ናህን ሰምቼሃለሁ፤ እርሱንም እባርከዋለሁ፤
ፍሬያማም አደርገዋለሁ፤ እጅግም አበዛዋ
ለሁ፤ የዐሥራ ሁለት አለቆች አባት ይሆ
ናል፤ ታላቅም ሕዝብ አደርገዋለሁ:: [21]ኪዳ
ኔን ግን የዛሬ ዓመት በዚሁ ጊዜ ሣራ ከም
ትወልድልህ ልጅ፣ ከይስሐቅ ጋር አደርጋ
ለሁ::" [22]እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከአብርሃም ጋር
መነጋገሩን ከፈጸመ በኋላ ወደ ላይ ወጣ::
[23]በዚያችም ዕለት አብርሃም እግዚአብሔር
(ያህዌ) ባዘዘው መሠረት ልጁን እስማኤልን፣
በቤቱ ውስጥ የተወለዱትንና ከውጭ በገን
ዘቡ የገዛቸውን ወንዶች በሙሉ ገረዛቸው::
[24]አብርሃም ሲገረዝ ዕድሜው 99 ዓመት
ነበር:: [25]ልጁም እስማኤል ሲገረዝ 13 ዓመቱ
ነበር:: [26]አብርሃምና ልጁ እስማኤል፣ ሁለ
ቱም በዚያኑ ቀን ተገረዙ:: [27]በአብርሃም ቤት
ያሉ ወንዶች ሁሉ፣ በቤቱ የተወለዱትም
ሆኑ ከውጭ በገንዘብ የተገዙ ከእርሱ ጋር
ተገረዙ::

## ሦስቱ እንግዶች

18 ቀትር ላይ አብርሃም በመምሬ ትል
ልቅ ዛፎች አቅራቢያ በምትገኘው
ድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር
(ያህዌ) ተገለጠለት፤ [2]ቀና ብሎም ሲመለከት፣
ሦስት ሰዎች ቆመው አየ፤ ወዲያውም ከድ
ንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ፣ ፈጥኖ ወደ ሰዎቹ
ሄደ፤ ወደ መሬት ዝቅ ብሎም እጅ ነሣ::

17፥12 ዘፍ9፥12፤ 21፥4፤ዘሌ12፥3፤ኢሱ 5፥2፤ሉቃ1፥59
17፥13 ዘፍ9፥16፤ ዘፀ12፥44:48
17፥14 ቍ23፤ዘፀ 24-26፤12፥15:19፤ 30፥33፤ዘሌ7፥20: 25፤17፥4፤18፥29፤ 19፥8፤20፥17፤ዘኍ 9፥13፤15፥30፤19፥ 13፤ዘዳ17፥12፤ኢሱ 5፥2-8፤ኢዮ38፥15፤ መዝ37፥28፤ሕዝ44፥7
17፥15 ቍ5፤ዘፍ 11፥29
17፥16 ቍ4:6፤ዘፍ 24፥60፤ኢሳ29፥22፤ ገላ4፥31
17፥17 ቍ3፤ዘፍ 12፥4፤18፥11:12: 13፤21፥6:7፤24፥ 1:36፤ኤር20፥15፤ ሉቃ1፥18፤ሮሜ4፥ 19፤ገላ4፥23፤ዕብ 11፥11
17፥18 ዘፍ16፥15፤ 21፥11
17፥19 ቍ6:21፤ ዘፍ9፥16፤16፥11፤ 18፥14፤21፥2፤26፥3፤ 50፥24፤ዘፀ13፥11፤ ዘዳ1፥8፤1ሳሙ1፥20፤ ማቴ1፥21፤ሉቃ1፥13: 31፤ገላ3፥16
17፥20 ዘፍ13፥16፤ 25፥12-16:18፤48፥19
17፥21 ቍ19፤ዘፍ 18፥10:14፤ዘፀ34፥10
17፥22 ዘፍ18፥33፤ 35፥13፤ዘኍ12፥9
17፥23 ቍ5:10: 14፤ዘፍ12፥5
17፥24ዘፍ12፥4፤ሮሜ4፥11 17፥25ዘፍ16፥16 17፥27ዘፍ14፥14
18፥1ዘፍ12፥7፤13፥18፤19፥1፤23፥10:18፤34፥20:24፤ሩት4፥1፤መዝ 69፥12፤ሐሥ7፥2፤ዕብ11፥9 18፥2ቍ16:22፤ዘፍ17፥3፤19፥1:10፤24፥63፤ 32፥24፤43፥28፤ኢሱ5፥13፤መሳ13፥6-11፤ሆሴ12፥3-4፤ዕብ13፥2

^19 *ይስሐቅ ማለት ይሥቃል ማለት ነው*

17፥11 ***ኪዳን ምልክት ይሆናል፤*** የ9፥12፤ የ15፥17 ማብ ይመ:: ግዝረት የኪዳን ምልክት ከመሆኑም ሌላ (የቍ 10 ማብ ይመ)፣ እግዚአብሔር የአብርሃምን እምነት ጽድቅ አድርጐ እንደቈጠረለት ያሳያል (15፥6):: ጳውሎስ ይህ ዐይነቱ የቃል ኪዳን ምልክት ምን እንደ ሆነ በሮሜ 4፥11 ላይ አብራርቶ ገልጿል::

17፥12 ***ስምንት ቀን ሲሞላው፤*** በ21፥4፤ ሐሥ 7፥8 (ይስሐቅን)፣ ሉቃ 1፥59 (መጥምቁ ዮሐንስን)፣ ሉቃ 2፥21 (ኢየሱስን)፣ ፊል 3፥5 (ጳውሎስን) ይመ:: አብርሃም፣ አዲሱ የግዝረት ሥርዐት በእርሱ ላይ በተፈጸመ ጊዜ ዕድሜው ዘጠና ዘጠኝ ዓመት ነበር (ቍ 24 ይመ):: ራሳቸውን የእስማኤል ዝርያ አድርገው የሚቈጥሩት ዐረቦችም ዕድሜአቸው ዐሥራ ሦስት ዓመት ሲሞላ ይገረዛሉ (ቍ 25 ይመ):: በእነርሱም ይሁን በሌሎች ሕዝቦች ዘንድ፣ ይህ ዕድሜ ከልጅነት ወደ ጐልማሳነት ከዚያም በኅብረተሰቡ ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ ወደሚያስችል ደረጃ ለመሸጋገር ያገለግላል::

17፥14 ***ከወገኖቹ ይወገድ፤*** በመለኮታዊ ፍርድ ከቃል ኪዳኑ ሕዝብ ተለይቶ እንዲወገድ ይደረጋል (የቍ 10 ማብ ይመ)::

17፥15 ***ሦራን... ሣራ፤*** የሁለቱም ስሞች ትርጒም፣ "ልዕልት" ማለት ነው:: እንደ ገና መሰየሟ፣ የሕዝቦችና የነገሥታት እናት (ቍ 16 ይመ) በመሆን የእግዚአብሔርን ዕቅድ የምታገለግል መሆኗን በአጽንዖት ለመግለጽ ነው (የቍ 5 ማብ ይመ)::

17፥16 ***ወንድ ልጅ፤*** በይስሐቅ መወለድ ተፈጽሞአል (21፥2-3 ይመ)::

17፥17 ***ሣቀ፤*** የሣቀው ካለማመኑ የተነሣ ነው (18፥12፤ ይመ፤ ከሮሜ 4፥19-21 ጋር ያነጻጽሩ):: ግሡ "ይስሐቅ" ከሚለው ስም ጋር ይመሳሰላል፤ "ሣቀ" ማለትም ነው (18፥12-15፤ 21፥6 ይመ)::

17፥20 ***አበዛዋለሁ፤*** የ13፥16 ማብ ይመ:: ***የዐሥራ ሁለት አለቆች አባት፤*** በ25፥16 ላይ ተፈጽሞአል::

*17፥21፤* ጳውሎስ የይስሐቅን መመረጥ (የእስማኤልን ሳይሆን)፣ እግዚአብሔር ሰዎችን በጸጋ ብቻ ለመምረጥም ሆነ ለማዳን ሉዓላዊ መብት እንዳለው እንደ አንድ ማስረጃ በመጥቀስ ያስረዳል (ሮሜ 9፥6-13 ይመ):: ***የዛሬ ዓመት በዚሁ ጊዜ፤*** 21፥2 ይመ::

17፥22 ***እግዚአብሔር... ወደ ላይ ወጣ፤*** የንግግራቸው ማጠቃለያና መዝጊያ ነው::

17፥23 ***በዚያችም ዕለት፤*** እግዚአብሔር የሚሰጠውን ትእዛዝ ተቀብሎ ወዲያውኑ መታዘዝ የአብርሃም ባሕርይ ነበር (የ12፥4 ማብ ይመ)::

18፥1 ***ተገለጠለት፤*** የ12፥7 ማብ ይመ:: ***ትልልቅ ዛፎች፤*** የ12፥6 ማብ ይመ:: ***መምሬ፤*** የ13፥18 ይመ:: ***ቀትር ላይ፤*** የቀኑ ፀሓይ በበረታ ጊዜ ማለት ነው::

18፥2 ***ሦስት ሰዎች፤*** ቢያንስ ከሦስቱ ሰዎች ሁለቱ መላእክት ናቸው (19፥1 ይመ፤ እንዲሁም የ16፥7 ማብ ይመ)፤ ምናልባት ራሱ እግዚአብሔር ሳይሆን አይቀርም (ቍ 1:13:17:20: 26:33 ይመ፤ በተለይም ቍ 22 ይመ):: ***ፈጥኖ፤*** ከቍ 2-8 ያለው ታሪክ በመካከለኛው ምሥራቅ ያለውን እንግዳ ተቀባይነት በብዙ መንገድ ያብራራል:: ይኸውም፣ (1) አብርሃም እንግዶቹ ለሚያስፈልጋቸው ነገር አፋጣኝ መልስ ሰጠ (ቍ 2:6-7)፤ (2) ግንባሩ መሬት እስኪነካ ዝቅ ብሎ ሰገደ (ቍ 2)፤ (3) ከእንግዶቹ አንዱን፣ "ጌታዬ ሆይ" በማለት ራሱን ደግሞ "አገልጋያችሁ" በማለት ጠራ፤ በዚያን ዘመን ለአንድ አለቃ የሚገባ አቀራረብ ነበር (ቍ 3:5)፤ ለአንድ ታላቅ ሰው የሚሰጥ የአክብሮት ቃል ነው (19፥2:18-19 ይመ)፤ (4) እንዲያገለግላቸው ቢፈቅዱለት እንደ ታላቅ ክብር ይቈጥረዋል (ቍ 3-5)፤ (5) እግራቸውን የሚታጠቡበት ውሃ እንዲቀርብላቸው ጠየቀ (ቍ 4)፤ ይህም በሙቀትና በዐቧራ የተጐዳን መንገደኛ ለማዝናናት የሚደረግ ነው (19፥2፤ 24፥32፤ 43፥24 ይመ)፤ (6) የተትረፈረፈ ማዕድ አዘጋጅቶ አቀረበ (ቍ 5-8)፤ እንዲህ ዐይነት ማዕድ በመሳ 6፥18-19፤ 13፥15-16 ላይ ለተጠቀሰው የእግዚአብሔር መልእክተኛም ተዘጋጅቶ ቀርቦአል:: ፈቃዳቸውን ለመፈጸም እንደ ተዘጋጀ አገልጋይ በአጠገባቸው ቆሞ አስተናገዳቸው (ቍ 8:22):: በዕብ 13፥2 ላይ ያለውን ሐሳብ ከቍ 2-8 እና ከ19፥1-3 ላይ የተጠቀሰ ሳይሆን አይቀርም::

3አብርሃምም እንዲህ አለ፤ “ጌታዬ፣[ሀ] በፊ
ትህ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ፣ ባሪያህን አል
ፈህ አትሂድ፤ 4ጥቂት ውሃ ይምጣላችሁና
እግራችሁን ታጠቡ፤ እዚህም ከዛፉ ሥር ዐረፍ
በሉ። 5ወደ እኔ ወደ አገልጋያችሁ ከመጣ
ችሁ፣ እህል ቀምሳችሁ ትበረቱ ዘንድ ምግብ
ላቅርብላችሁና ጕዞአችሁን ትቀጥላላችሁ።”
እነርሱም፣ “መልካም፤ እንዳልኸው አድ
ርግ” አሉት።
6አብርሃም በፍጥነት ሣራ ወዳለችበት
ወደ ድንኳኑ ገብቶ፣ “ቶሎ ብለሽ ሦስት
መስፈሪያ[ለ] ስልቅ ዱቄት አቡኪና ቂጣ ጋግሪ”
አላት።
7ከዚያም ወደ መንጋው በጥድፊያ ሄዶ፣
አንድ ፍርጥም ያለ ሥጋው ገር የሆነ ጥጃ
መርጦ ለአገልጋዩ ሰጠው፤ አገልጋዩም ጥጃ
ውን ዐርዶ አዘጋጀው። 8አብርሃምም እርጎ፣
ወተትና የተዘጋጀውን የጥጃ ሥጋ አቀረበ
ላቸው፤ ሲበሉም ዛፉ ሥር አጠገባቸው ቆሞ
ነበር።
9እነርሱም አብርሃምን፣ “ሚስትህ ሣራ የት
አለች?” ብለው ጠየቁት።
እርሱም፣ “ድንኳን ውስጥ ናት” አላቸው።
10እግዚአብሔርም (ያህዌ)፣[ሐ] “የዛሬ ዓመት
በዚሁ ጊዜ በእርግጥ ተመልሼ እመጣለሁ፤
ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅ ትወልዳለች” አለው።
ሣራም በዚህ ጊዜ ከበስተ ጀርባው ካለው
ከድንኳኑ ደጃፍ ሆና ትሰማ ነበር። 11በዚ
ያን ጊዜ አብርሃምና ሣራ አርጅተው፣ ዕድሜ
አቸው ገፍቶ ነበር፤ ሣራም ልጅ የመውለ
ጃዋ ዕድሜ ዐልፎ ነበር። 12ሣራ በልቧ፣
“ካረጀሁና ጌታዬም[መ] ከደከመ በኋላ በዚህ
ነገር መደሰት ይሆንልኛል?” ብላ ሣቀች።
13እግዚአብሔርም (ያህዌ) አብርሃምን እንዲህ
አለው፤ “ሣራ፣ ‘ካረጀሁ በኋላ ልጅ እንዴት
አድርጌ እወልዳለሁ’ ስትል ለምን ሣቀች?
14ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የሚሳነው ነገር አለን?
የዛሬ ዓመት በተባለው ጊዜ ተመልሼ እመ
ጣለሁ፤ ሣራም ልጅ ይኖራታል።”
15ሣራ ስለ ፈራች፣ “አረ አልሣቅሁም”
ብላ ዋሸች።
እርሱ ግን፣ “ሣቅሽ እንጂ” አላት።

## አብርሃም ስለ ሰዶም ማለደ

16ሰዎቹም ለመሄድ ሲነሡ፣ ቍልቍል
ወደ ሰዶም ተመለከቱ፤ አብርሃምም ሊሸኛ
ቸው አብሮአቸው ወጣ። 17እግዚአብሔርም
(ያህዌ) እንዲህ አለ፤ “እኔ የማደርገውን ነገር
ከአብርሃም እሰውራለሁን? 18አብርሃም በእ
ውነት ታላቅና ብርቱ ሕዝብ ይሆናል፤ የም
ድር ሕዝቦችም ሁሉ በእርሱ ይባረካሉ።
19ትክክለኛና ቀና የሆነውን በማድረግ የእግ
ዚአብሔርን (ያህዌ) መንገድ ይጠብቁ ዘንድ
ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤተ ሰቦቹን እን
ዲያዝ መርጬዋለሁ፤ ይኸውም እግዚአብሔር
(ያህዌ) ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ ሁሉ እንዲፈ
ጸም ነው።”
20ደግሞም እግዚአብሔር (ያህዌ) እንዲህ አለ፤
“በሰዶምና በገሞራ ላይ የሚሰማው ጩኸት
እጅግ በዝቶአል፤ ኀጢአታቸውም እጅግ ከፍ
ቶአል፤ 21አድራጎታቸው እኔ ዘንድ እንደ
ደረሰው ጩኸት መሆኑን ለማየት ወደዚ
ያው እወርዳለሁ፤ እንደዚያ ካልሆነም ዐው
ቃለሁ።”
22ሰዎቹም ፊታቸውን ወደ ሰዶም አቅን
ተው ሄዱ፤ አብርሃም ግን በእግዚአብሔር
(ያህዌ) ፊት እንደ ቆመ ነበር።[ሠ] 23አብርሃምም

18፥3 ዘፍ19፥19፤ 32፥4፡18፡20፤33፥5፤ 39፥4፤ሩት2፥2፡10፡ 13፤1ሳሙ1፥18፤ አስ2፥15
18፥4 ዘፍ19፥2፤ 24፥32፤43፥24፤መሳ 19፥21፤2ሳሙ11፥8፤ ሉቃ7፥44
18፥5 መሳ13፥15፤ 19፥5
18፥6 ዘፍ19፥3፤ 2ሳሙ13፥8
18፥7 1ሳሙ28፥ 24፤ሉቃ15፥23
18፥8 መሳ4፥19፤ 5፥25፤6፥19፤ኢሳ7፥ 15፡22
18፥9 ዘፍ3፥9፤ 24፥67፤ዕብ11፥9
18፥10 ዘፍ17፥6፡ 21፤21፥2፤2ነገ4፥16፤ ሮሜ 9፥9
18፥11 ዘፍ11፥30፤ 17፥17፤ሉቃ1፥18፤ ሮሜ4፥19፤ዕብ11፥ 11-12
18፥12 ዘፍ17፥17፤ 1ጴጥ3፥6
18፥13 ዘፍ17፥17
18፥14 ቍ10፤ዘፍ 17፥19፤ኢዮ42፥2፤ ኢሳ40፥29፤50፥2፤ 51፥9፤ኤር32፥17፡ 27፤ማቴ19፥26፤ ሮሜ4፥21፤9፥9፤ ገላ4፥23
18፥16 ቍ2
18፥17 ዘፍ19፥24፤ ኢዮ1፥ 16፤መዝ 107፥34፤አሞ3፥7
18፥18 ዘፍ12፥2፤ ገላ3፥8
18፥19 ዘፍ16፥11፤ 17፥9፤22፥12፡18፤26፥ 5፤ዘዳ4፥9-10፤6፥7፤ ኢሱ24፥15፤2ሳሙ 8፥15፤መዝ17፥2፤ 99፥4፤ኢሳ14፥1፤ኤር 23፥5፤ኤፌ6፥4
18፥20 ዘፍ19፥13፤13፥13፤ኢሳ1፥10፤ኤር23፥14፤ሕዝ16፥46
18፥21 ዘፍ11፥5 18፥22 ቍ2፤ዘፍ19፥1፡27

[ሀ]3 ወይም ጌታ ሆይ
[ለ]6 22 ሊትር ገደማ ይሆናል
[ሐ]10 ዕብራይስጡ ከዚያም እርሱ ይለዋል
[መ]12 ወይም ባሌ
[ሠ]22 ከማሶሬቲኩ ጽሑፍ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን የጥንት ዕብራውያን የጸፉት ትውፊት ግን እግዚአብሔር ግን በአብርሃም ፊት እንደ ቆመ ነበር ይላል

18፥6 *ቂጣ፤* ክብና ስስ ዳቦን የሚያመለክት የብዙ ቍጥር ቃል ነው።

*18፥10፤* 17፥21 ይመ። ጳውሎስ፣ ስለ ይስሐቅ መወለድ የተነገረውን የተስፋ ቃል (ቍ 14 ይመ) በሮሜ 9፥9 ላይ በመጥቀስ፣ ከአብርሃም መንፈሳዊ ልጆች ጋር አዛምዶታል (ሮሜ 9፥7-8 ይመ)።

18፥12 *ሣቀች፤* አብርሃም ካለማመን የተነሣ እንደ ሣቀ ሁሉ፣ እርሷም ሣቀች (የ17፥17 ማብ ይመ)።

18፥14 *ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?* ለሣራም ሆነ የእርሷ ዝርያዎች ለሆኑት ለማርያምና ለኤልሳቤጥ፣ መልሱ “ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና” (ሉቃ 1፥34-37 ይመ) የሚል ነው። መፍጠርም (ኤር 32፥17 ይመ) ቢሆን ማዳን (ማቴ 19፥25-26 ይመ) ለእግዚአብሔር ከቶ አይሳነውም።

18፥16 *ሰዶም፤* የ10፥19፤ 13፥10 ማብ ይመ።

*18፥17፤* አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ነበር (ቍ 19፤ 2ዜና 20፥7፤ ያዕ 2፥23፤ እንዲሁም ኢሳ 41፥8 እና ማብ ይመ)። አሁን አብርሃም የእግዚአብሔር የኪዳን ወዳጅ (ኢዮ 29፥4 ይመ) በመሆኑ፣ እግዚአብሔር ሰማያዊ ጉባኤውን በአብርሃም ድንኳን ውስጥ ሰበሰበ (የ1፥26 ማብ ይመ)። በዚያም ለአብርሃም ያለውን በጐ ዐላማና (ቍ 10) በክፉዎች ላይ የሚያመጣውን ፍርድ አስታወቀ (ቍ 20-21)። እንዲሁም አብርሃም በተሰበሰበው ጉባኤ መካከል እንዲናገርና በሰዶምና በገሞራ ለሚኖሩ ጻድቃን እንዲማልድ ዕድል ተሰጠው። በዚህም ምክንያት አብርሃም ነቢይ ተብሎ ተጠራ (20፥7)። በዚህ ቦታ እንደሚታየው፣ ለእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ የተሰጠው ልዩ መብት በአብርሃም ሕይወት ተመስሎ ተገልጦአል፤ ይኸውም እግዚአብሔር ሐሳቡን ለቃል ኪዳን ሕዝቡ ገልጦአል፤ ድምፃቸውም (ምልጃቸውም) በሰማያዊ ጉባኤ እንዲሰማ ፈቅዶአል።

18፥18 *ታላቅና ብርቱ ሕዝብ ይሆናል... በእርሱ ይባረካሉ፤* የ12፥2-3 ማብ ይመ።

18፥19 *መርጬዋለሁ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም፣ “ዐውቄዋለሁ” ማለት ነው (አሞ 3፥2)።

18፥20 *ገሞራ፤* የ10፥19፤13፥10 ማብ ይመ። *ጩኸት፤* ከደረሰባቸው ግፍ የተነሣ የተሰማ የጻድቃን ጩኸት/ሮሮ ሲሆን (በ4፥10 ላይ የተጠቀሰውን የአቤልን ደም ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ)፣ ለሰዶምና ለገሞራ ከተሞች መጥፋት ምክንያት ከሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ ይህ ጩኸት ነበር (19፥13 ይመ)። *ኀጢአታቸውም እጅግ ከፍቶአል፤* የሰዶምን (ምናልባትም የገሞራን) ኀጢአት እንደ ምሳሌ መጥቀስ ከተጀመረ ዘመናት አልፈዋል (13፥13፤ ሕዝ 6፥49-50 ይመ)።

18፥21 *ለማየት፤* የእግዚአብሔርን ሁሉን ዐዋቂነት የሚክድ አነጋገር ሳይሆን፣ እግዚአብሔር አንድን ነገር ከሥር ከመሠረቱ ላይ መረምር ሰዎች ወደ እርሱ ስለ ጮኹ ብቻ በስሜት ተነሣሥቶ እርምጃ እንደማይወስድ ለመግለጽ የገባ ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው። *እወርዳለሁ፤* እግዚአብሔር ለሰዎች እንደ ሥራቸው ለመስጠት እንደሚወርድ ሁሉ (በ11፥5-9 ላይ እንደተጠቀሰው)፣ ሰዎችንም ለማዳን ይወርዳል (በዘፀ 3፥8 ላይ እንደተጠቀሰው)።

18፥22 *አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት እንደ ቆመ ነበር፤* በእግዚአብሔርና በአገልጋዩ መካከል ያለውን አንድነትና ግንኙነት የሚገልጽ ነው።

ወደ እርሱ ቀረብ ብሎ እንዲህ አለ፤ “በእ
ርግጥ ጻድቁን ከኀጢአተኛው ጋር አብረህ
ታጠፋለህን? 24አምሳ ጻድቃን በከተማዪቱ
ቢገኙ፣ በውኑ ነዋሪዎቹን ሁሉ ታጠፋለህን?
በውስጧ ለሚገኙ አምሳ ጻድቃን ስትል
ከተማዪቱን አትምርምን?+ 25እንዲህስ አይ
ሁን፤ ጻድቁን ከኀጢአተኛው ጋር እንዴት
ትገድለዋለህ? ይህን የመሰለው አድራጎት
ከአንተ ይራቅ፤ የምድር ሁሉ ዳኛ° በቅን
አይፈርድምን?”

26እግዚአብሔርም (ያህዌ)፣ “በሰዶም ከተማ
አምሳ ጻድቃን ባገኝ ለእነርሱ ስል አገሪቱን
በሞላ እምራለሁ” አለ።

27ደግሞም አብርሃም እንዲህ አለ፤ “እኔ
ከንቱ፣ ትቢያና ዐመድ ሆኜ ሳለሁ ከጌታ
(አዶናይ) ጋር ለመናገር እንዴ ደፍሬአለሁ፤
28ለመሆኑ ከአምሳው ጻድቃን አምስት ቢጐ
ድሉ በአምስቱ ሰዎች ምክንያት መላ ከተማ
ዋን ታጠፋለህን?”

እርሱም፣ “አርባ አምስት ጻድቃን ባገኝ
አላጠፋትም” አለ።

29አብርሃምም እንደ ገና፣ “ምናልባት አርባ
ጻድቃን ቢገኙስ?” አለ

እርሱም፣ “ለአርባው ስል እምራታለሁ”
አለ።

30ደግሞም አብርሃም፣ “ጌታዬ (አዶናይ) አይ
ቈጣ፤ እባክህ ልናገር፤ ሠላሳ ጻድቃን ብቻ
ቢገኙስ?”

እርሱም፣ “ሠላሳ ባገኝ አላጠፋትም” ብሎ
መለሰ።

31አብርሃምም፣ “ከጌታ (አዶናይ) ጋር እናገር
ዘንድ መቼም እንዴ ደፍሬአለሁና ምና
ልባት ሃያ ብቻ ቢገኙስ?” አለ።

እርሱም፣ “ሃያ ቢገኙ፣ ለእነርሱ ስል
እምራታለሁ” አለ።

32አብርሃምም፣ “ጌታዬ (አዶናይ) አይቈጣ፤ አንድ
ጊዜ ብቻ ልናገር፤ ምናልባት ዐሥር ብቻ
ቢገኙስ?” አለ።

እርሱም “ስለ ዐሥሩ ስል አላጠፋትም”
ብሎ መለሰ።

33እግዚአብሔር (ያህዌ) ከአብርሃም ጋር ንግ
ግሩን ከጨረሰ በኋላ ሄደ፤ አብርሃምም ወደ
ቤቱ ተመለሰ።

## ሰዶምና ገሞራ ጠፉ

19 ሁለቱ መላእክት ምሽት ላይ ሰዶም
ደረሱ፤ ሎጥም በሰዶም ከተማ መግ
ቢያ በር ተቀምጦ ነበር፤ ሎጥም መላእክቱን
ሲያይ ሊቀበላቸው ብድግ አለ፤ በግምባሩም
ወደ ምድር ተደፍቶ እጅ ነሣቸው። 2እር
ሱም፣ “ጌቶቼ፤ እባካችሁ ወደ እኔ ወደ
ባሪያችሁ ቤት ጎራ በሉ፤ ከዚያም እግራች
ሁን ታጠቡ፤ አድራችሁም ጧት በማለዳ
ጕዞአችሁን ትቀጥላላችሁ” አላቸው።

እነርሱም፣ “አይሆንም፤ እዚሁ አደባባይ
ላይ እናድራለን” አሉት።

3ሎጥ ግን አጥብቆ ስለ ለመናቸው አብረ
ውት ወደ ቤቱ ገቡ፤ ከዚያም ቂጣ ጋግሮ
አቀረበላቸውና በሉ። 4ከመተኛታቸውም በፊት፣
የሰዶም ከተማ ነዋሪዎች የሆኑ ወንድ ወጣ
ቶችና ሽማግሌዎች ከያካባቢው መጥተው
ቤቱን ከበቡት። 5ሎጥንም ጠርተው፣ “በዚ
ህች ምሽት ወደ ቤትህ የገቡት ሰዎች የት
አሉ? ሩካቤ ሥጋ እንድንፈጽምባቸው ወደ
ውጭ አውጣልን” አሉት።

6ሎጥም ሊያነጋግራቸው ወደ ውጭ ወጣ፤
መዝጊያውን ከበስተ ኋላው ዘግቶ፣ 7እንዲህ
አለ፤ “ወዳጆቼ ሆይ፤ እባካችሁ እንዲህ ያለ
ውን ክፉ ነገር አታድርጉ። 8እነሆ፣ ወንድ የማ
ያውቁ ሁለት ሴቶች ልጆች አሉኝ። እነር
ሱን ላውጣላችሁና የፈለጋችሁትን አድርጉባ
ቸው። በእነዚህ ሰዎች ላይ ግን አንዳች ነገር

18፥23 ዘፀ23፥7፤ ዘሌ4፥3፡22፡27፤ዘኍ16፥22፤ዘዳ27፥25፤ 2ሳሙ24፥17፤መዝ11፥4-7፤94፥21፤ሕዝ18፥4፤2ጴጥ2፥9
18፥24 ቍ26፤ ኤር5፥1
18፥25 ዘፍ20፥4፤ 44፥7፡17፤ዘዳ1፥16-17፤32፥4፤መሳ11፥27፤2ዜና19፥7፤ዕዝ9፥15፤ነህ9፥33፤ኢዮ8፥3-7፡20፤9፥15፤34፥10፤36፥23፤መዝ7፥11፤58፥11፤75፥7፤94፥2፤119፥137፤ ኢሳ3፥10-11፤15፥20፤ሕዝ18፥25፤ዳን4፥37፤9፥14፤አሞ5፥15፤ሚል2፥17፤3፥18፤ሮሜ3፥6፤ዕብ12፥23
18፥26 ቍ24
18፥27 ዘፍ2፥7፤ ኢዮ2፥8
18፥30 ቍ32፤ ዘፍ44፥18፤ዘፀ32፥22
18፥32 ቍ30፤ መሳ6፥39፤ኤር5፥1
18፥33 ዘፍ17፥22፤ 31፥55፤ዘፀ31፥18
19፥1 ዘፍ11፥27፤ 17፥3፤18፥1፡2፡22፤ 48፥12፤ሩት2፥10፤ 1ሳሙ25፥23፤2ሳሙ14፥33፤2ነገ2፥15፤ ዕብ13፥2
19፥2 ዘፍ18፥4፤ ሉቃ7፥44፤መሳ19፥15፡20
19፥3 ዘፍ18፥6፤ 33፥11፤ዘፀ12፥39፤ ኢዮ31፥32
19፥4 ዘፍ13፥13
19፥5 ዘፍ13፥13፤ ዘሌ18፥22፤ዘዳ23፥18፤መሳ19፥22፤ ሮሜ1፥24-27
19፥6 መሳ19፥23
19፥8 መሳ19፥24፤ 2ጴጥ2፥7-8

+24 ወይም ይቅርታ ማድረግ ሊሆን ይችላል፤ ይህም በቍ26 ላይ ያለውንም ጨምሮ ነው።
°25 ወይም ገዥ

*18፥23፤* አብርሃም ለሁለተኛ ጊዜ ለዘመዶቹና ለሰዶም ሰዎች ማለደ (14፥14-16 ይመ)።

18፥24 *አምሳ ጻድቃን፤* ሎጥ አንዱ ነበር (2ጴጥ 2፥7 ይመ)። አብርሃም፣ ኀጢአተኞች እንዲጠፉ ከማይፈልገው (ከማይፈቅደው) ከእግዚአብሔር ጋር የተከራከረውም በከንቱ አልነበረም (ከሕዝ 33፥11 ጋር ያነጻጽሩ)።

18፥25 *የምድር ሁሉ ዳኛ፤* አብርሃም ለልመናው (ለምልጃው) መሠረት ያደረገው የእግዚአብሔርን ቅን ፈራጅነትና ሥልጣን ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ትክክለኛ የሆነውን ነገር እንደሚያደርግ እርግጠኛ ነበርና (ዘዳ 32፥4 ይመ)።

18፥27 *ትቢያና ዐመድ፤* አብርሃም እጅግ በከበረው በእግዚአብሔር ፊት ራሱን የሚያየው እንደ ዐመድና ትቢያ ነው (ኢዮ 30፥19፤ 42፥6 ይመ)። *ጌታ፤* አብርሃም በሚጸልይበት ጊዜ ሁሉ፣ “እግዚአብሔር” የሚለውን ስም ሳይሆን፣ “ጌታ” የሚለውን ይጠቀም ነበር፤ ደግሞም፣ “የምድር ሁሉ ዳኛ” በማለት አቤቱታውን ወደ እግዚአብሔር ያቀርብ ነበር።

18፥32 *አንድ ጊዜ ብቻ፤* አብርሃም በቍ 23-32 ላይ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች ያቀረበው ዋጋ ለሌለው ክርክር ሳይሆን፣ ለወገኖቹ ካለው ርኅራኄና ፍቅር፣ እንዲሁም የእግዚአብሔርን መንገድና አሠራር ለማወቅ ካለው ፍላጐት የተነሣ ነው። *ዐሥር፤* አብርሃም ዐሥር ላይ ደርሶ ያቆመበት ምክንያት፣ ምናልባትም በሚጸልይበት ጊዜ ሎጥንና ሚስቱን፣ ሁለት ወንዶች ልጆቹን (19፥12 ይመ)፣ ያገቡ ሁለት ሴቶች ልጆቹን ከነባሎቻቸው (19፥14 ይመ) እንዲሁም ሁለት ያላገቡ ሴቶች ልጆቹን ይቈጥር ስለ ነበረ ሳይሆን አይቀርም (19፥8 ይመ)።

18፥33 *ቤቱ፤* በመምሬ ወዳለው ማለት ነው (ቍ 1 ይመ)። በማግሥቱ አብርሃም እግዚአብሔር የሠራውን ለማየት ተመልሶ ሄደ (19፥27 ይመ)።

*19፥1-3፤* የ18፥2 ማብ ይመ።

19፥1 *ሁለቱ መላእክት፤* የ16፥7፤ 18፥2 ማብ ይመ። *ሎጥም በሰዶም ከተማ መግቢያ በር ተቀምጦ ነበር፤* በጥንት ዘመን የከተማ መግቢያ በሮች፣ የአስተዳደርና የፍትሕ ማእከል በመሆናቸው ሕግ ነክ ጕዳዮች የሚታዩትና የሚወሰኑት በእነዚህ ቦታዎች ነበር፤ ሎጥ የሰዶም ከተማ ገዥና ሽንጉ አባል ሳይሆን አይቀርም (ሩት 4፥1-12 ይመ)።

19፥2 *አደባባይ፤* በዋናው የከተማ መግቢያ በር አጠገብ የሚገኝና (2ዜና 32፥6 ይመ) ሕዝባዊ ስብሰባዎች የሚካሄዱበት አውላላ ሜዳ ነው። እንደ ኢየሩሳሌም ያሉ ታላላቅ ከተሞች ሁለት ወይም ከዚያ በላይ አደባባዮች ነበሯቸው (ነህ 8፥16 ይመ)።

19፥3 *ቂጣ፤* ቂጣው እርሾ የሌለው በመሆኑ ቶሎ እንዲበስል ያደርገዋል (18፥6፤ ዘፀ 12፥29 ይመ)።

*19፥4-9፤* መሳ 19፥22-25 ይመ።

19፥5 *ሩካቤ ሥጋ እንድንፈጽምባቸው፤* ወንዶች ከወንዶች ጋር የሚፈጽሙት የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት፣ በሰዶም ሰዎች የተጀመረ በመሆኑ (ይሁ 7 ይመ) እስከ ዛሬ ድረስ ግብረ ሰዶም ተብሎ ይጠራል።

አታድርጉባቸው፤ እኔን ብለው ወደ ቤቴ
ገብተዋልና::"
9እነርሱም፣ "ዞር በል! ይህ ሰው ራሱ ትና
ንት ተሰዶ የመጣ ነው፤ ዛሬ ደግሞ ዳኛ
ልሁን ይላል:: ዋ! በእነርሱ ካሰብነው የከፋ
እንዳናደርስብህ!" አሉት፤ ከዚያም ሎጥን
እየገፈታተሩ የበሩን መዝጊያ ለመስበር ተን
ደረደሩ::
10ከቤቱ ውስጥ የነበሩት እንግዶች ግን
እጃቸውን በመዘርጋት ስበው ወደ ውስጥ
አስገቡት፤ በሩንም ዘጉ:: 11ከዚያም በሩን እን
ዳያገኙት በቤቱ ደጃፍ ላይ የተሰበሰቡትን
ወጣቶችና ሽማግሌዎች ዐይን አሳወሩ::
12ሁለቱ ሰዎችም ሎጥን እንዲህ አሉት፤
"በከተማዋ ውስጥ የሚኖሩ የአንተ የሆኑ
ሰዎች አሉህ? ዐማቾች፣ ወንዶችና ሴቶች
ወይም ሌሎች ዘመዶች ካሉህ ቶሎ ብለህ
ከዚህ እንዲወጡ አድርግ፤ 13ይህን ስፍራ
ልናጠፋው ነው:: በሕዝቦቿ ላይ ወደ እግዚ
አብሔር (ያሕዌ) የቀረበው ጩኸት ታላቅ በመ
ሆኑ፣ እንድናጠፋት እግዚአብሔር ልኮናል::"
14ሎጥ ከቤቱ ወጥቶ የሴት ልጆቹ እጮ
ኞች[+] የሆኑትን ዐማቾቹን፣ "እግዚአብሔር
(ያሕዌ) ይህችን ከተማ ሊያጠፋት ነውና በፍ
ጥነት ከዚህ ስፍራ ውጡ" አላቸው፤ ዐማ
ቾቹ ግን የሚቀልድ መሰላቸው::
15ሲነጋጋም መላእክቱ ሎጥን፣ "ከከተማ
ዪቱ ጋር አብራችሁ እንዳትጠፉ፣ ሚስት
ህንና ሁለቱን ሴት ልጆችህን ይዘህ ከዚህ
ቦታ በፍጥነት ውጣ" ብለው አቻኰሉት::
16ሎጥ ሲያመነታም፣ እግዚአብሔር (ያሕዌ)
ስለ ራራላቸው ሰዎቹ የእርሱን፣ የሚስቱ
ንና የሁለት ሴቶች ልጆቹን እጅ ይዘው
ከከተማዪቱ በደኅና አወጧቸው:: 17እንዳ
ወጧቸውም፣ መልአኩ፣ "ሕይወታችሁን ለማ
ትረፍ ፈጥናችሁ ሽሹ፤ መለስ ብላችሁ ወደ
ኋላችሁ አትመልከቱ፤ ከረባዳው ስፍራ እንኳ
ቆም አትበሉ፤ ወደ ተራራው ሽሹ፤ አለበለ
ዚያ ትጠፋላችሁ" አላቸው::
18ሎጥም እንዲህ አላቸው፤ "ጌቶቼ ሆይ፤[*]
እባካችሁ እንደዚህስ አይሁን፤ 19እነሆ፤ እኔ
ባሪያህ አንዴ በፊትህ ሞገስ አግኝቻለሁ፤ ሕይ
ወቴን ለማዳን ታላቅ ርኅራኄ አድርገህል
ኛል፤ እኔ እንደሆንሁ ወደ ተራሮቹ ሸሽቼ
ማምለጥ ስለማልችል የሚወርደው መዓት
ደርሶ ያጠፋኛል:: 20እነሆ፤ ወደዚያ ሸሽቶ
ለማምለጥ ቅርብ የሆነች ትንሽ ከተማ አለች፤
ወደ እርሷ ልሽሽ፤ በጣም ትንሽ አይደለ
ችም እንዴ? ወደዚያ ብሸሽ እኮ ሕይወቴ
ትተርፋለች::"
21እርሱም እንዲህ አለው፤ "ይሁን እሺ፣
ልመናህን ተቀብያለሁ፤ ያልካትንም ከተማ
አላጠፋትም:: 22አንተ እዚያ እስክትደርስ
ድረስ አንዳች ማድረግ ስለማልችል ቶሎ
ብለህ ወደዚያ ሽሽ" ስለዚህም የዚያች ከተማ
ስም ዞዓር[ˀ] ተባለ::
23ሎጥ ዞዓር ሲደርስ ፀሐይ በምድሩ ላይ
ወጥታ ነበር:: 24ከዚያም እግዚአብሔር (ያሕዌ)
በሰዶምና በገሞራ ላይ ከሰማይ ከእግዚ
አብሔር (ያሕዌ) ዘንድ የሚያቃጥል ዲኑና
እሳት አዘነበባቸው:: 25እነዚያንም ከተሞችና
ረባዳውን ምድር በሙሉ፣ በከተሞቹም የሚ
ኖሩትን ሰዎች ሁሉ፣ የምድሩን ቡቃያ ሳይ
ቀር ገለባበጠው:: 26የሎጥ ሚስት ግን ወደ
ኋላዋ ስለ ተመለከተች የጨው ዐምድ ሆና
ቀረች::
27አብርሃም በማግስቱ፣ ማለዳ ተነሥቶ ከዚህ
ቀደም በእግዚአብሔር (ያሕዌ) ፊት ቆሞ ወደ
ነበረበት ቦታ ሄደ:: 28ሰዶምንና ገሞራን፣ እንዲ
ሁም በረባዳው ስፍራ የሚገኘውን ምድር ሁሉ
ቍልቍል ተመለከተ፤ ከእቶን የሚወጣ የመ
ሰለ ጥቅጥቅ ያለ ጢስ ከምድሪቱ ወደ ላይ
ሲትጐለጐል አየ::
29እንደዚህ አድርጐ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
በረባዳው ስፍራ የነበሩትን ከተሞች ሲያጠፋ
አብርሃምን አሰበው፤ ስለዚህም የሎጥ መኖ
ሪያ የነበሩትን ከተሞች ካጠፋው መዓት
ሎጥን አወጣው::

## ሎጥና ሴት ልጆቹ

30ሎጥ በዞዓር መኖርን ስለ ፈራ፣ ከዚያ
ተነሥቶ ከሁለቱ ሴት ልጆቹ ጋር በአቅራ
ቢያው ወደሚገኙት ተራሮች ሄደ፤ መኖሪያ
ውንም ከሁለት ሴት ልጆቹ ጋር በዋሻ ውስጥ

19፥9 ዘፍ13፥8፤ 23፥4፤ሐሥ7፥27
19፥10 ዘፍ18፥2
19፥11 ዘዳ28፥28-29፤2ነገ6፥18፤ሐሥ 13፥11
19፥12 ዘፍ6፥18
19፥13 ዘፍ18፥20፤ ዘፀ12፥29፤2ሳሙ24፥16፤2ነገ19፥35፤1ዜና 21፥12:15፤2ዜና32፥21፤መዝ78፥49፤ኤር 21፥12፤25፥18፤44፥22፤51፥45
19፥14 ዘኍ16፥21፤ ዘፀ9፥21፤1ነገ13፥18፤ ኤር5፥12፤43፥2፤ሉቃ 17፥28፤ራእ18፥4
19፥15 ዘኍ16፥26፤ ኢዮ21፥18፤መዝ58፥9፤73፥19፤90፥5፤ራእ 18፥4
19፥16 ዘፀ34፥6፤ መዝ33፥18-19፤ 2ጴጥ2፥7
19፥17 ቍ19:26፤ ዘፍ13፥12፤14፥10፤ 1ነገ19፥3፤ኤር48፥6፤ ማቴ24፥16
19፥19 ቍ17:30፤ ዘፍ6፥8፤18፥3፤24፥12፤39፥21፤40፥14፤47፥29፤ሩት1፥8፤ 2፥20፤3፥10
19፥21 1ሳሙ25፥35፤2ሳሙ14፥8፤ኢዮ 42፥9
19፥22 ዘፍ13፥10
19፥23 ዘፍ13፥10
19፥24 ዘፍ18፥17፤ ዘሌ10፥2፤ዘዳ29፥23፤ ኢዮ18፥15፤መዝ11፥6፤ኢሳ1፥9፤13፥19፤ 30፥33፤34፥9፤ኤር 49፥18፤50፥40፤አሞ 4፥11፤ማቴ10፥15፤ ሉቃ17፥29፤ሕዝ 38፥22
19፥25 ቍ24፤ዘፍ 13፥12፤መዝ107፥34፤ኢሳ1፥10፤ኤር 20፥16፤23፥14፤ሰቆ 4፥6፤ሕዝ16፥48፤26፥16፤ሶፎ3፥8፤ሐጌ2፥22
19፥26 ቍ17፤ ሉቃ17፥32
19፥27 ዘፍ18፥22
19፥28 ዘፍ15፥17፤ ዘፀ19፥18፤ራእ9፥2፤ 18፥9
19፥29 ዘፍ8፥1፤ 13፥12፤14፥12፤ሕዝ14፥16፤2ጴጥ2፥7 19፥30 ቍ19:22፤ዘፍ 13፥10፤14፥10

[+]14 *ወይም ሴት ልጆቹን ያገቡትን* [*]18 *ወይም እንደዚህስ አይሁን ጌታ፤ ወይም እንደዚህስ አይሁን ጌታዬ*
[ˀ]22 *ዞዓር ማለት ትንሽ ማለት ነው*

19፥8 *እኔን ብለው ወደ ቤቴ፤* በጥንት ዘመን አንድ ሰው እንግዶችን ተቀብሎ ሲያስተናግድ፣ እንግዶቹን ከማንኛውም ክፉ ነገር የመከላከል ግዴታ ነበረበት::

19፥9 *ይህ ሰው ራሱ ትናንት ተሰዶ የመጣ ነው፣ ዛሬ ደግሞ ዳኛ ልሁን ይላል፤* ከብዙ ምእተ ዓመታት በኋላ ሙሴም እንደ ባዕድ ሰው ራሱን ገዥና ዳኛ አድርጐ ለመሾም እንደ ተነሣሣ ሰው ተቈጥሮ ነበር (ዘፀ 2፥14፤ ሐሥ 7፥27 ይመ)::

19፥13 *ይህን ስፍራ ልናጠፋው ነው፤* የሰዶም ክፋት እያደገ ሄዶ ከተማዋን ለጥፋት ዳረጋት (ኢሳ 3፥9፤ ኤር 23፥14፤ ሰቆ 4፥6፤ ሶፎ 2፥8-9፤ 2ጴጥ 2፥6፤ ይሁ 7 ይመ)::

19፥14 *ዐማቾቹ ግን የሚቀልድ መሰላቸው፤* ሎጥ የራሱን ቤተ ሰብ እንኳ ለማሳመንና ከጥፋት ለማዳን አቅቶት ነበር::

19፥16 *ሲያመነታ፤* ምናልባት ያፈራውን ምድራዊ ሀብት ጥሎ ላለመሄድ ያሳየው ወላዋይነት ነው:: *እግዚአብሔር ስለራራላቸው፤* ድነት በእግዚአብሔር ምሕረት ብቻ የሚገኝ እንጂ፣ በሰው ጽድቅ የሚገኝ አይደለም (ከቲቶ 3፥5 ጋር ያነጻጽሩ):: *የእርሱን፣ የሚስቱንና የሁለት ሴቶች ልጆቹን እጅ፤* ሰዶምን ከጥፋት ያድናሉ ተብሎ ተስፋ የተጣለባቸው ዐሥር ጻድቃን ሰዎች ቢገኙ (18፥32 ይመ)፤ የተባለው አሁን ቍጥራቸው ወደ አራት ዝቅ አለ::

19፥24 *አዘነበባቸው፤* አስፋልት የሚተፋ ብርቱ የምድር መናወጥ ዛሬም በዚህ ስፍራ ይታያል::

19፥26 *የሎጥ ሚስት ግን ወደ ኋላዋ ስለ ተመለከተች የጨው ዐምድ ሆና ቀረች፤* ከማመንታቷ የተነሣ ያሳየችው አለ መታዘዝ (ቍ 17 ይመ)፣ ከእርሷ በኋላ ላለው ትውልድ ምሳሌ በመሆን ያገለግላል (ሉቃ 17፥32 ይመ):: በአሁኑ ጊዜ ከሙት ባሕር በስተ ደቡብ ጫፍ የሚገኘው የጨው ቍልል ባለማስተዋል ላደረገችው ነገር መታሰቢያ ነው::

19፥29 *እግዚአብሔር... አብርሃምን አሰበው፤* የ8፥1 ማብ ይመ:: *መዓት ሎጥን አወጣው፤* የአብርሃም ትልቅ ጸሎት (18፥23-32) ሎጥ ከመዓቱ እንዲድን ሲሆን፣ እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰምቶ መለሰለት::

አደረገ። 31አንድ ቀን ታላቂቱ ልጅ፣ ታናሺ
ቱን እንዲህ አለቻት፤ "አባታችን አርጅቶ
አል፤ በምድር ሁሉ እንደሚኖሩ ሰዎች መገ
አብሮን የሚተኛ ወንድ በአካባቢያችን የለም።
32ስለዚህ አባታችንን የወይን ጠጅ እናጠጣ
ውና ከእርሱ ጋር እንተኛ፤ የትውልድ ሐረ
ጋችን እንዳይቋረጥ ዘር ከአባታችን እናት
ርፍ።"

33በዚያችም ምሽት አባታቸውን የወይን ጠጅ
አጠጡት፤ ከዚያም ትልቋ ልጁ ሄዳ ከአባቷ
ጋር ተኛች፤ እርሱ ግን ስትተኛም ሆነ ስት
ነሣ አላወቀም ነበር።

34በማግስቱም ታላቂቱ ልጅ ታናሺቱን፣
"እኔ ትናንትና ማታ ከአባቴ ጋር ተኝቻለሁ፤
ዛሬም እንደ ገና የወይን ጠጅ እናጠጣው፤
አንቺም ደግሞ ከእርሱ ዘንድ ገብተሽ ተኚ፤
በዚህም የትውልድ ሐረጋችን እንዳይቋረጥ
ከአባታችን ዘር ማትረፍ እንችላለን" አለቻት።
35በዚያችም ምሽት ደግሞ አባታቸውን የወ
ይን ጠጅ አጠጡት፤ ትንሿ ልጁም ሄዳ
ከአባቷ ጋር ተኛች፤ እርሱ ግን ስትተኛም
ሆነ ስትነሣ አላወቀም ነበር።

36ስለዚህ ሁለቱም የሎጥ ሴት ልጆች ከአ
ባታቸው አረገዙ። 37ትልቋ ልጁ ወንድ
ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ሞዓብ ብላ ጠራ
ችው፤ እርሱም የዛሬዎቹ ሞዓባውያን' አባት
ነው። 38ትንሿ ልጁም እንደዚሁ ወንድ
ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ቤንአሚ† ብላ ጠራ
ችው፤ እርሱም የዛሬዎቹ አሞናውያን አባት
ነው።

## አብርሃምና አቤሜሌክ

20፥1-18 ተጓ ምብ - ዘፍ 12፥10-20፤ 26፥1-11

20 አብርሃም ከዚያ ተነሥቶ ወደ ኔጌብ
አካባቢ ሄዶ በቃዴስና በሱር መካ
ከል ሰፈረ፤ ለጥቂት ጊዜም በጌራራ ተቀ
መጠ። 2በዚያም አብርሃም ሚስቱን ሣራን፣
"እህቴ ናት" ይል ነበር። ስለዚህ የጌራራ
ንጉሥ አቢሜሌክ መልእክተኛ ልኮ ሣራን
ወሰዳት።

3እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) በአንድ ሌሊት በሕ
ልም ወደ አቢሜሌክ መጥቶ፣ "እነሆ፤ በወ
ሰድሃት ሴት ምክንያት ምውት ነህ፤ እርሷ
ባለ ባል ናት" አለው።

4አቢሜሌክም ገና አልደረሰባትም ነበርና
እንዲህ አለ፤ "ጌታ ሆይ፤ በደል ያልፈጸመ
ውን ሕዝብ ታጠፋለህን? 5'እኅቴ ናት'
ያለኝ ራሱ አይደለምን? ደግሞስ ራሷም
ብትሆን፣ 'ወንድሜ ነው' አላለችምን? እኔ
ይህን ያደረግሁት በቅን ልቦናና በንጹሕ
እጅ ነው።"

6እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) በሕልሙ እንዲህ አለው፤
"አንተ ይህን ያደረግኸው በቅን ልቦና መሆ
ኑን ዐውቄአለሁ፤ በእኔም ላይ ኀጢአት እን
ዳትሠራ የጠበቅሁህና እንዳትነካትም ያደረ
ግሁት ለዚሁ ነው። 7አሁንም ሚስቱን ለሰ
ውዬው መልስለት፤ ነቢይ ነውና ይጸልይል
ሃል፤ አንተም ትድናለህ፤ ባትመልስለት ግን
አንተም ሆንህ የአንተ የሆነ ሁሉ እንደም
ትሞቱ ዕወቅ።"

8በማግስቱም ማለዳ፣ አቢሜሌክ ሹማም
ንቱን ሁሉ ጠርቶ፣ የሆነውን ሁሉ ነገራቸው፤
እነርሱም ታላቅ ፍርሀት አደረባቸው። 9ከዚ
ያም አቢሜሌክ አብርሃምን አስጠርቶ እን
ዲህ አለው፤ "ይህ ያደረግህብን ነገር ምን
ድን ነው? ምን በደልሁህና ነው በእኔና በግ
ዛቴ ላይ እንዲህ ያለውን ታላቅ የጥፋት
መዘዝ ያመጣብህን? በእውነቱ መደረግ የማ
ይገባውን ነው ያደረግህብን።" 10ከዚያም
አቢሜሌክ፣ "ለመሆኑ ይህን ያደረግህበት
ምክንያት ምንድን ነው?" ሲል አብርሃምን
ጠየቀው።

11አብርሃምም አቢሜሌክን እንዲህ አለው፤
"እዚህ ቦታ ፈሪሀ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) አለ
መኖሩን ተገንዘብሁ፤ ሰዎቹም ለሚስቴ ሲሉ
ይገድሉኛል ብዬ ሠጋሁ፤ 12ደግሞም እኮ
በእርግጥ እኅቴ ናት፤ ከአንድ እናት ባንወ
ለድም በአባት አንድ ነን፤ ኋላም አገባኋት።
13እግዚአብሔር (ኤሎሂም) አዞኝ ከአባቴ ቤት ወጥቼ
በየአገሩ ስዞር፣ 'ለእኔ ያለሽን ፍቅር በዚህ
ግለጭልኝ፤ በየደረስንበት ስፍራ ሁሉ "እርሱ
ወንድሜ ነው" በዪ' ብያት ነበር።"

19፥32 ቍ34:36፤ ዘፍ16፥2፤38፥18
19፥33 ቍ35
19፥34 ቍ32
19፥35 ቍ33፤ዘፍ 9፥21
19፥36 ቍ32
19፥37 ዘፍ36፥35፤ ዘፀ15፥15፤ዘኍ22፥4፤ 24፥17፤25፥1፤ዘዳ 2፥9፤መሳ3፥28፤ሩት 1፥4:22፤1ሳሙ14፥ 47፤22፥3-4፤2ሳሙ 8፥2፤2ነገ1፥1፤3፥4፤ ዕዝ9፥1፤መዝ108፥9፤ ኢሳ15፥1፤25፥10፤ ኤር25፥21፤48፥1፤ ሕዝ25፥8፤ሶፎ2፥9
19፥38 ዘኍ21፥24፤ ዘዳ2፥19፤23፥3፤ኢያ 12፥2፤መሳ3፥13፤ 10፥6:7፤1ሳሙ11፥ 1-11፤14፥47፤1ዜና 19፥1፤2ዜና20፥23፤ 26፥8፤27፥5፤ነህ2፥ 19፤4፥3፤ኤር25፥21፤ 40፥14፤49፥1፤ሕዝ 21፥28፤25፥2፤አሞ 1፥13
20፥1 ዘፍ12፥9፤ 14፥7፤16፥7፤18፥1፤ 26፥1:3:6:17
20፥2 ቍ14፤ዘፍ 12፥13:15፤21፥22፤ 26፥1
20፥3 ቍ7፤ዘፍ 26፥11፤28፥12፤31፥ 10:24፤37፥5:9፤40፥5 ፤41፥1፤ዘፀ10፥7፤12፥ 33፤ዘኍ12፥6፤22፥9: 20፤ዘዳ13፥1፤1ዜና 16፥21፤ኢዮ33፥15፤ መዝ105፥14:38፤ ዳን2፥1፤4፥5
20፥4 ዘፍ18፥25
20፥5 ዘፍ12፥19፤ 17፥1፤መዝ7፥8፤25፥ 21፤26፥6፤41፥12
20፥6 ዘፍ13፥13፤ መዝ41፥4፤51፥4፤ 1ሳሙ25፥26:34
20፥7 ቍ3:17፤ዘፀ 8፥8፤ዘኍ11፥2፤12፥ 13፤ዘዳ18፥18፤34፥ 10፤1ሳሙ7፥5፤1ነገ 13፥6፤2ነገ3፥11፤ 5፥3፤1ዜና16፥22፤ ኢዮ42፥8፤መዝ9፥ 5፤105፥5፤ኤር18፥ 20፤37፥3፤42፥2
20፥9 ዘፍ12፥18፤ 34፥7 20፥11 ዘፍ12፥12፤31፥31፤42፥18፤ነህ5፥15፤ኢዮ31፥23፤ መዝ36፥1፤ምሳ16፥6፤ 20፥12 ዘፍ12፥13 20፥13 ዘፍ12፥1:13፤ ዘዳ26፥5፤1ዜና16፥20፤ኢሳ30፥28፤63፥17

'37 *ሞዓብ የሚለው ቃል ከአባት የሚል ትርጉም* ካለው የዕብ ራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው።
†38 *ቤንአሚ ማለት የሕዝቤ ልጅ ማለት ነው*

19፥33 *አባታቸውን የወይን ጠጅ አጠጡት፤ ከዚያም ትልቋ ልጁ ሄዳ ከአባቷ ጋር ተኛች፤* ሎጥ በድርጊቱ ውስጥ የተ ሳተፈው ያለ ፈቃዱ ቢሆንም፣ በጣም በመስከሩና በዚህም ምክን ያት ሁለቱ ሴቶች ልጆቹ ከእርሱ በማርገዛቸው ተጠያቂ ነው (ቍ 36 ይመ)።

*19፥36-38፤* ከሎጥ ሴት ልጆች የተወለዱት የሞዓባውያንና የአሞናውያን ቅድመ አያቶች ሲሆኑ (ዘዳ 2፥9:19 ይመ)፣ ሞዓባ ውያንና አሞናውያን ደግሞ የአብርሃም ዘር ጠላቶች ነበሩ (1ሳሙ 14፥47፤ 2ዜና 20፥1 ይመ)።

20፥1 *በቃዴስና በሱር መካከል፤* የ14፥7፤ 16፥7 ማብ ይመ። *ጌራራ፤* ይህ ቦታ የሚገኘው በፍልስጥኤም ምድር ጠርዝ ላይ ሲሆን፣ ይህም በጋዛና (በሜድትራኒያን ባሕር ጠረፍ) በቤር ሳቤህ (በኔጌብ በስተ ሰሜን) መካከል ላይ ነው።

20፥2 *አቢሜሌክ፤* ከጊዜ በኋላ ለነገሠውና በዚሁ ስም ለሚጠ ራው ንጉሥ አባት ወይም አያት ሳይሆን አይቀርም (26፥1 ይመ)።

20፥3 *ሕልም፤* እግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ የቃል ኪዳኑን ልጅ እናት ከጥፋት ለመታደግ ተገለጠ። በብሉይ ኪዳን እግዚአ ብሔር ራሱን ከገለጠባቸው መንገዶች አንዱ ሕልም ነው (28፥ 12፤ 31፥10-11፤ 37፥5-9፤ 40፥5፤ 41፥1፤ ዘኍ 12፥6፤ መሳ 7፥13፤ 1ነገ 3፥5፤ ዳን 2፥3፤ 4፥5፤ 7፥1 ይመ)።

20፥7 *ነቢይ፤* የ18፥17 ማብ ይመ። በዚህ ስም ከተጠሩት ሰዎች መካከል የመጀመሪያው ሰው አብርሃም ነው (መዝ 105፥ 15 ይመ)።

20፥11 *ፈሪሀ እግዚአብሔር፤* "እውነተኛ ሃይማኖት" ከሚለው ሐሳብ ጋር እኩልነት ያለውና ለዚህም መግለጫ የሚ ሰጥ ነው። "መፍራት" የሚለው ቃል በእግዚአብሔር መታመን ንና ለእርሱም ፈቃድ መታዘዝን ያጠቃልላል።

20፥12 *በእርግጥ እኅቴ ናት፤ ከአንድ እናት ባንወለድም በአባት አንድ ነን፤* አብርሃም በከፊል እውነትነት ያለው ነገር ቢና ገርም፣ መዋሸቱ ንግግሩን ተቀባይነት ያሳጣዋል።

14ከዚያም አቢሜሌክ፣ በጎችና የቀንድ ከብ
ቶች፣ ወንድና ሴት አገልጋዮችን ለአብር
ሃም ሰጠው፤ ሚስቱን ሣራንም መለሰለት።
15አቢሜሌክም አብርሃምን፣ "እነሆ፤ አገሬ
አገርህ ናት፤ በፈቀድህበት ስፍራ መኖር
ትችላለህ" አለው።

16ሣራንም፣ "እነሆ፤ ለወንድምሽ ለአብር
ሃም 1000 ጥሬ ብር[ሀ] እሰጠዋለሁ፤ ይህም
በአንቺ ላይ ለተፈጸመው በደል ካሣ እንዲ
ሆንና አብረውሽ ያሉ ሁሉ እንዲያውቁት
ነው፤ በዚህም ንጽሕናሽ ይረጋገጣል" አላት።

17ከዚያም አብርሃም ወደ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ጸለየ፤ እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) አቢሜሌክን፣
ሚስቱንና ሴት አገልጋዮቹን ፈወሳቸው፤
እንደ ገናም ልጅ ለመውለድ በቁ። 18እግዚ
አብሔር (ያህዌ) በአብርሃም ሚስት በሣራ ምክ
ንያት፣ በአቢሜሌክ ቤት የሚገኙትን ሴቶች
ማሕፀናቸውን ሁሉ ዘግቶ ነበርና።

## የይስሐቅ መወለድ

21 እግዚአብሔር (ያህዌ) በተናገረው መሠረት
ሣራን አሰባት፤ የገባውንም ተስፋ ፈጸ
መላት። 2ሣራ ፀነሰች፤ ልክ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ባለው ጊዜ ለአብርሃም ወንድ ልጅ ወለደ
ችለት። 3አብርሃም፣ ሣራ የወለደችለትን ልጅ
ስሙን ይስሐቅ[ለ] አለው። 4አብርሃም፣ እግዚአ
ብሔር (ኤሎሂም) ባዘዘው መሠረት ልጁን ይስሐቅን
በተወለደ በስምንተኛው ቀን ገረዘው። 5አብ
ርሃም፣ ልጁ ይስሐቅ ሲወለድለት፣ ዕድሜው
መቶ ዓመት ነበረ።

6ሣራም፣ "እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሣቅ አድ
ሎኛል፤ ስለዚህ፣ ይህን የሚሰማ ሁሉ ከእኔ
ጋር ይሥቃል" አለች። 7ደግሞም፣ "ለመ
ሆኑ፣ 'ሣራ ልጆች ታጠባለች' ብሎ ለአብ
ርሃም ማን ተናግሮት ያውቅ ነበር? ይኸው
በስተርጅናው ወንድ ልጅ ወለድሁለት"
አለች።

20፥14 ቍ2፤ዘፍ 12፥16
20፥15 ዘፍ13፥9፤ 45፥18
20፥17 ቍ7፤ኢዮ 42፥9
20፥18 ዘፍ12፥17
21፥1 ዘፍ8፥1፤17፥6፤21፤18፥14፤1ሳሙ 2፥21፤ገላ4፥23፤ዕብ 11፥11
21፥2 ዘፍ17፥19፤ 30፥6፤18፥10፤ገላ 4፥22፤ዕብ11፥11
21፥3 ዘፍ16፥11፤ 17፥19፤ኢሱ24፥3
21፥4 ዘፍ17፥10፡ 12፤ሐሥ7፥8
21፥5 ዘፍ12፥4፤ ዕብ6፥15
21፥6 ዘፍ17፥17፤ ኢዮ8፥21፤መዝ126፥ 2፤ኢሳ12፥6፤35፥2፤ 44፥23፤52፥9፤54፥1
21፥7 ዘፍ17፥17
21፥8 1ሳሙ1፥23
21፥9 ዘፍ16፥15፤ 39፥14፤ ገላ4፥29
21፥10 ዘፍ39፥ 17፤ 25፥6፤ገላ4፥30
21፥11 ዘፍ17፥18
21፥12 ማቴ1፥2፤ ሮሜ9፥7፤ዕብ11፥18
21፥13 ዘፍ13፥16
21፥14 ቍ31፡32፤ ዘፍ16፥1፤22፥19፤26፥ 33፤28፥10፤46፥1፡5፤ ኢሱ15፥28፤19፥2፤ መሳ20፥1፤1ሳሙ3፥ 20፤1ዜና4፥28፤ነህ 11፥27
21፥16 ኤር6፥26፤ አሞ8፥10፤ዘካ12፥10
21፥17 ዘፀ3፥7፤ 15፥1፤16፥7፤22፥ 11፡15፤ዘኍ20፥16፤ ዘዳ26፥7፤መዝ6፥8
21፥18 ዘፍ17፥20

## የአጋርና የእስማኤል መባረር

8ሕፃኑ አደገ፤ ጡት መጥባቱንም ተወ።
አብርሃምም ይስሐቅ ጡት በጣለባት ዕለት
ታላቅ ድግስ ደገሰ። 9በሌላ በኩል ደግሞ፣
ግብፃዊቷ አጋር ለአብርሃም የወለደችለት
እስማኤል፣ በይስሐቅ ሲያሾፍበት ሣራ አየች፤
10አብርሃምንም፣ "ይህችን ባሪያ ከነልጇ አባ
ርልኝ፤ ምንም ቢሆን የዚህች ባሪያ ልጅ፣ ከልጄ
ከይስሐቅ ጋር ውርስ አይካፈልም አለች።"

11እስማኤል ልጁ ስለ ሆነ ነገሩ አብርሃ
ምን እጅግ አስጨነቀው። 12እግዚአብሔርም
(ኤሎሂም) አብርሃምን እንዲህ አለው፤ "ስለ ልጁም
ሆነ ስለ አገልጋይህ አሳብ አይግባህ፤ ዘር
የሚጠራልህ በይስሐቅ በኩል ስለ ሆነ፣ ሣራ
የምትልህን ሁሉ ስማ። 13የአገልጋይህም
ልጅ የራስህ ልጅ ስለ ሆነ፣ እርሱንም
ታላቅ ሕዝብ አደርገዋለሁ።"

14በማግስቱ አብርሃም ማልዶ ተነሣ።
ጥቂት ምግብ ወስዶ፣ ውሃ በእርኮት አድ
ርጎ ለአጋር ሰጣት፤ በትከሻዋም አሸክሞአት
ከነልጇ አሰናበታት። እርሷም ሄደች፤ በቤ
ርሳቤህም ምድረ በዳ ትንከራተት ጀመር።

15በእርኮት የነበረው ውሃ ባለቀ ጊዜ፣ ልጁን
ከአንድ ቍጥቋጦ ሥር አስቀመጠችው።
16ከዚያም፣ "ልጁ ሲሞት ዐይኔ አያይም"
ብላ፣ የቀስት ውርወራ ያህል ርቃ ዐረፍ
አለች፤ እርሷም[ሐ] እየተንሰቀሰቀች ታለቅስ
ጀመር።

17እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) የልጁን ጩኸት ሰማ።
የእግዚአብሔር (ኤሎሂም) መልአክ ከሰማይ አጋ
ርን እንዲህ አላት፤ "አጋር ሆይ፤ ምን ሆነ
ሻል? ልጅሽ ከተኛበት ሲያለቅስ እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) ሰምቶታል፤ ስለዚህ አትፍሪ። 18ተነ
ሥተሽ ልጁን አንሺው፤ ያዢውም፤ ታላቅ
ሕዝብ አደርገዋለሁና።"

[ሀ]16 11.5 ኪ.ግ. ገደማ ይሆናል።
[ለ]3 ይስሐቅ ማለት ይሥቃል ማለት ነው
[ሐ]16 ዕብራይስጡና ሰብዐ ሊቃናት ልጁ ይላሉ።

*20፥14-16፤* የአቢሜሌክ ቸርነት ከአብርሃም ፈሪነትና ውሸ ታምነት ጋር የሚነጻጸር ነው።

*20፥16፤* በዕብራይስጡ ቅጅ ላይ ባይሆንም አንዳንድ ቅጆች፣ "ጥሬ ብር" በሚለው ምትክ፣ "ሰቅል" ይሉታል፤ በዚህ ቦታ ግን ቃሉ በትክክለኛው አገባብ ተጠቅሶአል። ሰቅል በጥንት ዘመን የታወቀ የክብደት መለኪያ ሲሆን ለመገበያያ ሳይሆን ለመለኪያነት ብቻ ያገለግል ነበር፤ ምክንያቱም ከክርስቶስ ልደት በፊት እስከ ዐሥራ ሰበተኛው ምእተ ዓመት ድረስ የገንዘብ ሳንቲም አልተሠራም ነበር።

21፥1 *በተናገረው መሠረት ሣራን አሰባት፤* 17፥16 ይመ። *የገባውንም ተስፋ ፈጸመላት፤* ገላ 4፥22-23፡28 ይመ።

21፥3 ይስሐቅ፤ የ17፥17 ማብ ይመ።

*21፥4፤* የ17፥10፡12 ማብ ይመ።

*21፥5፤* አብርሃም የተገባለት ተስፋ በመፈጸሙ (17፥16 ይመ) በ100 ዓመት ዕድሜው ታምራዊ በሆነ መንገድ የልጅ አባት ሆነ (17፥17 ይመ)።

21፥6 *ሣቅ ... ይሥቃል፤* የ17፥17 ማብ ይመ።

21፥8 *ጡት መጥባቱንም ተወ፤* በጥንቱ መካከለኛው ምሥ ራቅ አገሮች እንደተለመደው፣ ሕፃናት ጡት መጥባት የሚተ ውት በሁለት ወይም በሦስት ዓመት ዕድሜአቸው ነው።

21፥9 *ግብፃዊቷ አጋር ... የወለደችለት፤* በዚህ ጊዜ የእስ ማኤል ዕድሜ ወደ ሃያዎቹ ተጠግቶ ነበር (16፥15-16 ይመ)። *ሲያሾፍበት፤* "በጨዋታ ላይ" ሳሉ ማለት ነው። ያም ሆነ ይህ ይስሐቅ በተነገረለት የተስፋ ቃል መሠረት እንዳይወርስ እስማ ኤል እንቅፋት ሊሆንበት እንደሚችል ሣራ ተረድታለች (ቍ 10)።

21፥10 *ይህችን ባሪያ ከነልጇ አባርልኝ፤* ገላ 4፥21-31 ይመ። እነርሱን ወዲያ ማባረር፣ እስማኤል ከይስሐቅ ጋር እንዳ ይወርስ ያደርገዋል።

21፥11 *ነገሩ አብርሃምን... አስጨነቀው፤* አብርሃምን ያስጨነቀው ለልጁ ያለው ፍቅርና የሚኖርበት ማኅበረ ሰብ የሕግ ሥርዐት ነው። እርሱ በሚኖርበት ዘመን የአንዲትን አገልጋይ ልጅ ያለ ምንም ምክንያት ከቤት ማባረር ትክክል እንዳልሆነ ያውቃል፤ ይህም ሕግ ከጊዜ በኋላ በኑዚ ጽላት ላይ ተጽፎ ተገ ኝቶአል።

21፥12 *ሣራ የምትልህን ሁሉ ስማ፤* እግዚአብሔር የአብር ሃምን ሐሳብ ወደ ጐን በመተው፣ (ቀደም ሲል እንዳደረገው ሁሉ 15፥4 ይመ) ይስሐቅና እስማኤል የብዙ ሕዝቦች አባት እንደሚ ሆኑ ተስፋ ሰጠው። *ዘር የሚጠራልህ በይስሐቅ በኩል ስለ ሆነ፤* የዚህ ዐረፍተ ነገር የተራዘመ መንፈሳዊ ትርጉም በሮሜ 9፥6-8 እና በዕብ 11፥17-19 ላይ ይመ።

21፥14 *በማግስቱ ... ማልዶ፤* ምንም እንኳ አብርሃም አሁን ለመጀመሪያ ጊዜ ከእስማኤል ሊለይ ቢሆንም፣ እግዚአብ ሔር ለተናገረው/ላዘዘው ነገር ወዲያውኑ ታዘዘ (የ12፥4 ማብ ይመ)። *ቤርሳቤህ፤* የቍ 31 ማብ ይመ።

21፥15 *ከአንድ ቍጥቋጦ፤* የቍ 33 ማብ ይመ።

21፥17 *እግዚአብሔር... ሰማ... እግዚአብሔር ሰምቶታል፤* እስ ማኤል ለሚለው ስም የተሰጠና ሁለት ትርጉም ያለው ቃል ነው።

19እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ዐይኖቿን ከፈተላት፤
የውሃ ጕድጓድም አየች፤ ሄዳም በእርኮቱ
ውሃ ሞልታ ልጇን አጠጣች።
20እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከልጁ ጋር ነበር፤ ልጁም
እያደገ ሄደ፤ መኖሪያውንም በምድረ በዳ
ውስጥ አደረገ፤ ጐበዝ ቀስተኛም ሆነ። 21በፋ
ራን ምድረ በዳ ሳለም፣ እናቱ ከግብፅ አን
ዲት ሴት አምጥታ አጋባችው።

## በቤርሳቤህ የተደረገው ስምምነት

22በዚያን ጊዜ አቢሜሊክ ከሰራዊቱ አለቃ
ከፊኮል ጋር ሆኖ አብርሃምን እንዲህ አለው፤
"በምታደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ከአንተ ጋር ነው። 23እንግዲህ እኔንና ልጆ
ቼን፣ ዘሬንም በመሸንገል እንዳች ክፉ ነገር
እንዳታደርስብን በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፊት
ማልልኝ። እኔ ለአንተ ቸርነት እንዳደረግሁ፣
አንተም ለእኔና በእንግድነት ለተቀመጥህ
ባት ለዚች ምድር ቸርነት አድርግ።"
24አብርሃምም፣ "እሺ፤ እምላለሁ" አለ።
25ከዚያም አብርሃም፣ የአቢሜሌክ አገልጋ
ዮቹ ነጥቀው ስለያዙበት የውሃ ጕድጓድ
መከፋቱን ለአቢሜሌክ ገለጠለት። 26አቢሜ
ሌክም፣ "መቼም ይህን ድርጊት ማን እንደ
ፈጸመ በበኩሌ አላውቅም፤ አንተም አልነገ
ርኸኝም፤ ነገሩንም ገና አሁን መስማቴ ነው"
አለው።
27ስለዚህ አብርሃም፣ በጎችና ከብቶች አም
ጥቶ ለአቢሜሌክ ሰጠው፤ ሁለቱም በመካከ
ላቸው የስምምነት ውል አደረጉ። 28አብር
ሃም ከመንጋው ሰባት እንስት በጎች ለየ፤
29አቢሜሌክም፣ "እነዚህን ሰባት እንስት

21፥19 ዘፍ16፥7፤ ዘኍ22፥31
21፥20 ዘፍ26፥3፡ 24፤28፥15፤39፥2፡ 21፡23፤ሉቃ1፥66
21፥21 ዘፍ14፥6፤ 24፥4፡38፤28፥2፤ 34፥4፡8፤መሳ14፥2
21፥22 ቍ23፡32፤ ዘፍ20፥2፤26፥26፡28፤ 28፥15፤31፥3፡5፡42፤ 39፥2፡3፤1ሳሙ3፥19፤ 16፥18፤2ዜና1፥1፤ መዝ46፥7፤ኢሳ7፥14፤ 8፥8፡10፤41፥10፤ 43፥5
21፥23 ቍ22፡31፤ ዘፍ25፥33፤26፥31፤ 31፥53፤1ሳሙ24፥ 21፤ኢሱ2፥12፤1ነገ 2፥8፤
21፥25 ዘፍ26፥15፡ 18፡20-22
21፥27 ቍ31፡32፤ ዘፍ26፥28፡31፤31፥ 44፡53
21፥30 ቍ25፤ዘፍ 26፥25፡32፤31፥44፡47 ፡48፡50፡52፤ኢሱ22፥ 27፤24፥27፤28፥34፤ ኢሳ19፥20፤ሚል2፥14
21፥31 ቍ14፡23፡27
21፥32 ቍ14፡22፡ 27፤ዘፍ10፥14
21፥33 ዘፍ4፥26፤ ዘፀ15፥18፤ዘዳ32፥ 40፤33፥27፤1ሳሙ 22፥6፤31፥13፤ኢዮ 36፥26፤መዝ10፥16፤ 45፥6፤90፥2፤93፥2፤ 102፥24፤103፥19፤ 146፥10፤ኢሳ40፥28፤ ኤር10፥10፤ዕን1፥12፤ 3፥6፤ዕብ13፥8

በጎች ለይተህ ለብቻ ያቆምሃቸው ለምንድ
ነው?" ሲል አብርሃምን ጠየቀው።
30አብርሃምም፣ "ይህን የውሃ ጕድጓድ
የቈፈርሁ እኔ ለመሆኔ ምስክር እንዲሆን
እነዚህን ሰባት እንስት በጎች እንካ ተቀበ
ለኝ" አለው።
31ስለዚህ ቦታው፣ ሁለቱ ተማምለው የተ
ስማሙበት ስፍራ በመሆኑ ቤርሳቤህ* ተባለ።
32በቤርሳቤህ የስምምነት ውል ካደረጉ
በኋላ፣ አቢሜሌክና የሰራዊቱ አለቃ ፊኮል
ወደ ፍልስጥኤማውያን ምድር ተመለሱ።
33አብርሃምም በቤርሳቤህ የተምር ዛፍ ተከለ፤
በዚያም የዘላለም አምላክን (ኤል ኦላም) ስም
ጠራ። 34አብርሃምም በፍልስጥኤማውያን
ምድር ለረጅም ጊዜ በእንግድነት ኖረ።

## አብርሃም ተፈተነ

22 ከዚህ ሁሉ በኋላ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
አብርሃምን ፈተነው፤ "አብርሃም!"
አለው። እርሱም "አቤቱ! አለሁ" አለ።
2እግዚአብሔርም (ኤሎሂም)፣ "የምትወደውን አን
ዱን ልጅህን፣ ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያ
ምድር ሂድ፤ እኔ በማመለክትህ በአንዱ
ተራራ ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገህ
ሠዋው" አለው።
3በማግስቱ ጠዋት አብርሃም ማልዶ ተነሣ፤
አህያውን ጭኖ፣ ሁለት አገልጋዮቹንና ልጁን

21፥34 ዘፍ10፥14 22፥1 ቍ11፤ዘፍ31፥11፤46፥2፤ዘፀ15፥25፤ 16፥4፤20፥20፤ዘዳ8፥2፡16፤13፥3፤መሳ2፥22፤3፥1፤1ሳሙ3፥4፡6፡8፤ 2ዜና32፥31፤መዝ66፥10፤ኢሳ6፥8፤ዕብ11፥17፤ያዕ1፥12-13 22፥2 ቍ9፡12፡16፤ዘፍ8፥20፤2ዜና3፥1፤1ዮሐ3፥16፤ዕብ11፥17፤1ዮሐ4፥9

*31 *ቤርሳቤህ ማለት ሰባት የውሃ ጕድጓድ ወይም የመሐላ የውሃ ጕድጓድ ማለት ሊሆን ይችላል።*

21፥21 *በፋራን ምድረ በዳ፤* በሰሜን ማዕከላዊ ሲና የሚገኝ ቦታ ነው። *እናቱ ከግብፅ አንዲት ሴት አምጥታ አጋባችው፤* አብዛኛውን ጊዜ የልጆቻቸውን ጋብቻ የሚያመቻቹት ወላጆች ነበሩ (ም 24 ይመ)።

21፥22 *አቢሜሌክ፤* 20፥2 እና ማብ ይመ። *ፊኮል፤* ከ60 ዓመት በኋላ (25፥26) በተመሳሳይ ዑደት ውስጥ (26፥26) በድጋሚ ተጠቅሶ ስለሚገኝ የቤተ ሰብ ስም ወይም ሕጋዊ ማዕርግ ሳይሆን አይቀርም።

21፥23 *በእግዚአብሔር ፊት ማልልኝ... ለእኔ... ቸርነት አድርግ፤* ሰዎች ቃል ኪዳን ሲገቡ ወይም ውል ሲዋዋሉ የሚናገሩት የተለመደ አባባል ነው (ቍ 27፡32 ይመ)። በዚህ ቦታ፣ "ቸርነት" የሚለው ቃል በሁለት ወዳጆች መካከል ያለውን ቅርበት ያመለክታል (ከቍ 27፤ ከ20፥14 ጋር ያነጻጽሩ)። እንዲህ ዐይነቱ ቃል ኪዳን ደግሞ ምን ጊዜም መሐላን ይጠይቃል።

21፥27 *በጎችና ከብቶች፤* የውሉ ሥነ ሥርዐት በሚፈጸምበት ጊዜ የሚቀርብ ሳይሆን አይቀርም (15፥10 ይመ)።

21፥31 *ሁለቱ ተማምለው የተስማሙበት ስፍራ በመሆኑ ቤርሳቤህ፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ 26፥33 ይመ። ቤርሳቤህ በሰሜናዊ ኔጌብ የምትገኝ የታወቀች ከተማ ስትሆን፣ በኋለኞቹ ዘመናት ለደቡባዊው የእስራኤል መንግሥት ወሰን ነበረች (2ሳሙ 17፥11 ይመ)። በዚህ ስፍራ የሚገኘው የጥንት የውሃ ጕድጓድ፣ "የአብርሃም የውሃ ጕድጓድ" ይባላል (ቍ 25 ይመ)፤ ሆኖም ምን ያህል እውነት እንደ ሆነ አይታወቅም።

21፥32 *ፍልስጥኤማውያን፤* የ10፥14 ማብ ይመ።

21፥33 *ተምር፤* በበረሓ የሚበቅል ቍጥቋጦ ወይም አጭር ዛፍ ነው። ቅጠላማ ቅርንጫፎቹ ለጥላነት የሚያገለግሉ ሲሆን፣ አጋር ልጇን እስማኤልን ያሳረፈችበት ቍጥቋጦ ይሁን ወይም አይሁን በውል አይታወቅም (ቍ 15)። *የዘላለም አምላክ፤* በዕብራይስጥ ኤል ኦላም ማለት/ ሲሆን፣ በዚህ ስፍራ ብቻ የሚገኝ ስም ነው። ይህም "ኤል" የሚለውን ቃል ከሚያካትቱት የእግዚአብሔር ስሞች ውስጥ አንዱ ነው (14፥19 እና ማብ ይመ፤ 17፥1 እና ማብ ይመ፤ 33፥20፤ 35፥7 ይመ)።

22፥1 *ከዚህ ሁሉ በኋላ፤* በ21፥34 ላይ ("ለረጅም ጊዜ") እንደ ተመለከተው ይስሐቅ ጐረመሰ ወይም ሙሉ ሰው ሆነ። *ፈተነው፤* ተፈታተነው አይደለም፤ እግዚአብሔር ማንንም በክፉ አይፈትንም (ያዕ 1፥13)። ሰይጣን እንድንወድቅ ይፈትነናል (1ቆሮ 7፥5 ይመ)፤ እግዚአሔር የሚፈትነን ግን እምነታችን የጸና እንዲሆን (ዘፀ 20፥20) ወይም ለእርሱ የተሰጠ የማይናወጥ እምነት እንዳለን ለማረጋገጥ ነው (ዘዳ 8፥2)። የማቴ 4፥1 ማብ ይመ። *አቤቱ አለሁ፤* እግዚአብሔር ሙሴንና ሳሙኤልን በስማቸው በጠራ ጊዜ (ዘፀ 3፥4፤ 1ሳሙ 3፥4፡6፡8 ይመ) እንደ አንድ አገልጋይ መልስ እንደ ሰጡ ሁሉ፣ አብርሃምም ለእግዚአብሔር መልስ ሰጠ።

22፥2 *የምትወደውን አንዱን ልጅህን፣ ይስሐቅን፤* ይስሐቅ "አንዱን ልጅህን" የተባለለት ምክንያት የቃል ኪዳን ልጅ ስለሆነ ነው (21፥12)። *ሞሪያ ምድር፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ይህን ምድር ያያያዘው የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ከሚሠራበት ቦታ ጋር ነው (2ዜና 3፥1)። ሙስሊሞች በ691 ዓ.ም. ያነጹት ውብና ክብ ሕንጻ በአሁኑ ጊዜ በሞሪያ ተራራ ላይ ይገኛል። በሕንጻውም ውስጥ ያለው ትልቅ ድንጋይ ይስሐቅ ሊሠዋበት የነበረው ቦታ ነው ተብሎ የሚነገርለትን ስፍራ ያመለክታል። *መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው፤* አብርሃም እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ቃል ኪዳን ገባ፤ ልጁን ይስሐቅንም በመግረዝ ለእግዚአብሔር ሰጠ። እግዚአብሔርም የአገልጋዩን እምነትና ታማኝነት በእጅጉ ፈተነ፤ ከዚህ በኋላ በቃል ኪዳኑ መሠረት ራሳቸውን ቀድሰው ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ እግዚአብሔር አብርሃምን፣ ይስሐቅንና ዘራቸውን አዘዘ። ይህ ፈተና ሌላው የአብርሃም ዘርና በመንፈስ የእርሱ ልጆች የሆኑትን ሁሉ፣ ለእግዚአብሔር ለመለየትና የቃል ኪዳኑንም ግዴታዎች ለመፈጸም፣ ራሱን ባቀረበ ጊዜ የሚያልፍበት ፈተና መሆኑን (የቍ 16 ማብ ይመ) አስቀድሞ የሚያመለክት ነው።

22፥3 *በማግስቱ ጠዋት፤* አብርሃም እጅግ ከባድ በሆነ ፈተና ውስጥ ቢሆንም፣ እግዚአብሔርን መታዘዝ ግን የዘወትር ልምዱ ነው (የ12፥4 ማብ ይመ)።

ይስሐቅን ይዞ፣ ለመሥዋዕት የሚበቃውን ዕን
ጨት ከቈረጠ በኋላ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ወዳ
መለከተው ቦታ ለመሄድ ጕዞውን ጀመረ፤
4በሦስተኛው ቀን አብርሃም ቀና ብሎ ቦታ
ውን ከሩቅ ተመለከተ፤ 5አገልጋዮቹንም "እና
ንተ አህያውን ይዛችሁ እዚህ ቈዩን፤ እኔና
ልጄ ግን ወደዚያ ሄደን ለእግዚአብሔር
ሰግደን እንመለሳለን" አላቸው።
6አብርሃም ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆ
ነውን ዕንጨት ወስዶ፣ ልጁን ይስሐቅን አሸ
ከመው፤ እሳቱንና ቢላዋውንም ራሱ ያዘ።
ሁለቱም አብረው ሄዱ። 7ይስሐቅም አባቱን
አብርሃምን፣ "አባቴ ሆይ" አለው።
አብርሃምም፣ "እነሆኝ፤ አለሁ ልጄ" አለው።
ይስሐቅም፣ "እሳቱና ዕንጨቱ ይኸው፤
ነገር ግን የሚቃጠለው መሥዋዕት የት አለ?"
ብሎ ጠየቀ።
8አብርሃምም፣ "ልጄ ሆይ፤ ለሚቃጠለው
መሥዋዕት የሚሆነውን በግ እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) ራሱ ያዘጋጃል" አለው። ሁለቱም አብ
ረው ጕዞአቸውን ቀጠሉ።
9እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ወዳመለከተው ቦታ እንደ
ደረሱ፣ አብርሃም መሠዊያ ሠራ፤ በላዩም ላይ ዕን
ጨት ረበረበ፤ ልጁን ይስሐቅንም አስሮ በመ
ሠዊያው ዕንጨት ላይ አጋደመው። 10ከዚ
ያም ልጁን ለማረድ እጁን ዘርግቶ ቢላዋ
ውን አነሣ። 11የእግዚአብሔር (ያህዌ) መልአክ
ግን ከሰማይ፣ "አብርሃም፤ አብርሃም፤" ብሎ
ጠራው፤
አብርሃምም፣ "እነሆ፤ አለሁ" አለ።
12እርሱም፣ "እጅህን በብላቴናው ላይ አታ
ሳርፍ፤ ምንም ጕዳት አታድርስበት፤ እነሆ፤
እግዚአብሔርን (ኤሎሂም) እንደምትፈራ ተረድቻ
ለሁ፤ ልጅህን፣ ያውም አንዱን ልጅህን
ለእኔ ለመስጠት አልሳሳህምና።" አለው።
13አብርሃም ቀና ብሎ ሲመለከት በቍጥ
ቋጦ መካከል ቀንዶቹ የተጠላለፉ አንድ
አውራ በግ ከበስተ ኋላው አየ፤ ወደዚያው
ሄዶ በጉን አመጣና የሚቃጠል መሥዋዕት
አድርጎ ሠዋው። 14ከዚህም የተነሣ፣ አብ
ርሃም የዚያን ስፍራ ስም፣ "እግዚአብሔር
(ያህዌ) ያዘጋጃል" (ያህዌ ይርኤ) ብሎ ጠራው። እስከ
ዛሬም ድረስ፣ "በእግዚአብሔር (ያህዌ) ተራራ
ላይ ይሰጣል" ተብሎ ይነገራል።
15የእግዚአብሔርም (ያህዌ) መልአክ አብር
ሃምን ከሰማይ ዳግመኛ ጠራው፤ 16እንዲህም
አለው፤ "እግዚአብሔርም (ያህዌ) በራሴ ማልሁ
አለ፤ አንዱን ልጅህን ለእኔ ለመስጠት አል
ሳሳህምና፣ 17በእርግጥ እባርክሃለሁ፤ ዘርህን
እንደ ሰማይ ከዋክብት፣ እንደ ባሕር ዳር
አሸዋም አበዛዋለሁ። ዘሮችህም የጠላቶቻቸ
ውን ደጆች ይወርሳሉ፤ 18ቃሌን ስለ ሰማህ
የምድር ሕዝቦች ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ።"
19ከዚያም አብርሃም ወደ አገልጋዮቹ ተመ
ለሰ፤ ተያይዘውም ወደ ቤርሳቤህ ሄዱ፤ አብ
ርሃምም በቤርሳቤህ ኖረ።

## የናኮር ልጆች

20ከዚህ በኋላ እንዲህ ተብሎ ለአብርሃም
ተነገረው፤ "ሚልካም ደግሞ የልጆች እናት
ሆናለች፤ ለወንድምህም ለናኮር ወንዶች ልጆ
ችን ወልዳለች። 21እነርሱም የበኵር ልጁ ዑፅና
ወንድሙ ቡዝ፣ የአራም አባት ቀሙኤል፣
22ኮዛት፣ ሐዞ፣ ፊልዳሥ፣ የድላፍና ባቱኤል
ናቸው።" 23ባቱኤልም ርብቃን ወለደ። ሚልካ
ለአብርሃም ወንድም ለናኮር የወለደችለት
እነዚህ ስምንት ወንዶች ልጆች ናቸው። 24ከእ
ነዚህም ሌላ የናኮር ቁባት ሬናሕ ደግሞ
ጥባሕ፣ ገሐም፣ ተሐሽና ሞክሳ የተባሉ ወን
ዶች ልጆች ወለደችለት።

22፥3 ኢሱ8፥10
22፥5 ዘፀ24፥14
22፥6 ቍ10፤መሳ19፥29፤ዮሐ19፥17
22፥7 ዘፀ29፥38-42፤ዘሌ1፥10፤ራእ13፥8
22፥8 ቍ13፡14፤ዮሐ1፥29
22፥9 ቍ2፤ዘፍ4፥26፤8፥20፤ዘሌ1፥7፤1ነገ18፥33፤ዕብ11፥17-19፤ያዕ2፥21
22፥10 ቍ3፡6፤ዘፍ18፥9
22፥11 ቍ1፤ዘፍ16፥7፡21፥17፤46፥2
22፥12 ቍ2፤ዘፍ18፥19፤42፥18፤ዘፀ18፥21፤1ሳሙ15፥22፤ኢዮ1፥1፤37፥24፤ምሳ8፥13፤ያዕ2፥21-22፤ዮሐ3፥16፤1ዮሐ4፥9
22፥13 ቍ8፤ዘፍ8፥20፤ሮሜ8፥32
22፥14 ቍ8፤ዘፀ17፥15፤መሳ6፥24፤ኢሳ30፥29
22፥15 ዘፍ16፥7፤21፥17
22፥16 ቍ2፤ዘፀ13፥11፤32፥13፤33፥1፤ኢሳ45፥23፤62፥8፤ኤር22፥3፤44፥26፤49፥13፤51፥14፤አሞ6፥8፤ሉቃ1፥73፤ዕብ6፥13
22፥17 ዘፍ12፥2፤15፥5፤24፥60፤26፥24፤ዘፀ32፥13፤ዘዳ7፥7፤28፥62፤ኢሳ9፥2፤ሆሴ1፥10፤ሮሜ9፥27፤ዕብ6፥14፤11፥12
22፥18 ቍ10፤ዘፍ12፥2፡3፤17፥2፡9፤መዝ105፥9፤ሐሥ3፥25፤ገላ3፥8
22፥19 ዘፍ21፥14፤26፥23፤28፥10
22፥20 ዘፍ11፥29
22፥21 ዘፍ10፥23፤ኢዮ32፥2፤ኤር25፥23 22፥22 ዘፍ24፥15፡47፤25፥20 22፥23 ዘፍ11፥29፤24፥15 22፥24 ዘፍ25፥6፤35፥22፤36፥12፤መሳ8፥31፤2ሳሙ3፥7፤1ነገ2፥22፤11፥3፤1ዜና1፥32፤ማሕ6፥8

22፥4 *በሦስተኛው ቀን፤* ከቤርሳቤህ (ቍ19 ይመ) ተነሥቶ ኢየሩሳሌም ለመድረስ ሦስት ቀን ይፈጃል።

22፥5 *ልጄ* ቍ 12 ይመ። የዕብራይስጡ ቃል ሰፊ ትርጕም ያለው ሲሆን፣ ከሕፃንነት ዕድሜ አንሥቶ (ዘፀ 2፥6 ይመ) ውትድርና እስከሚገባበት የወጣትነት ዕድሜ ክልል ውስጥ ያለውን ሁሉ ያጠቃልላል (1ዜና 12፥28 ይመ) *እንመለሳለን፤* የእምነት ሰውና፣ "ለሚያምኑ ሁሉ አባት" (ሮሜ 4፥1) የሆነው አብርሃም፣ "እግዚአብሔር ከሙታን እንኳ ሊያነሣው" ይችላል እስከሚለው ድረስ ለመሄድ አላመነታም (ዕብ 11፥19)።

22፥8 *በግ እግዚአብሔር ራሱ ያዘጋጃል፤* አብርሃም እግዚአብሔርን እስከዚህ ድረስ በመታመኑ በቍ 13 ላይ ፈጣን መልስ ያገኘ ሲሆን፣ ለዚህ እምነቱ የመጨረሻው ትልቁ መልስ ግን የእግዚአሔር በግ ነው (ዮሐ 1፥29፡36)።

22፥9 *ልጁን ይስሐቅንም አስሮ በመሠዊያው ዕንጨት ላይ፤* እዚህ ላይ ይስሐቅ የክርስቶስ አምሳል ነው (የቍ 16 ማብ ይመ)።

22፥11 *የእግዚአብሔር መልአክ፤* የ16፥7 ማብ ይመ። *አብርሃም፤ አብርሃም፤* የስሙ መደጋገም የነገሩን አጣዳፊነት የሚያመለክት ነው (46፥2፤ ዘፀ 3፥4፤ 1ሳሙ 3፥10፤ ሐሥ 9፥4 ይመ)። *እነሆ፤ አለሁ፤* የቍ 1 ማብ ይመ።

22፥12 *እግዚአብሔርን እንደምትፈራ፤* የ20፥11 ማብ ይመ። *ልጅህን፣ ያውም አንዱን ልጅህን ለእኔ ለመስጠት አልሳሳህምና፤* ቍ 16 ይመ። የአብርሃም "እምነት በሥራ ፍጹም ሆነ" (ያዕ 2፥21-22)።

*22፥13፤* ራስን ለሌላው ምትክ አድርጎ መሠዋት ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው በዚህ ስፍራ ነው። በይስሐቅ ምትክ በጉ እንደ ሞተ ሁሉ፣ ኢየሱስ የራሱን ሕይወት ስለ ብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሰጥቶአል (ማር 10፥45)።

22፥14 *በእግዚአብሔር ተራራ፤* እስራኤል በንጉሣዊ አገዛዝ ሥር ትተዳደር በነበረበት ወቅት ቤተ መቅደሱ የነበረበትን ተራራ የሚያመለክት ነው (መዝ 24፥3፤ ኢሳ 2፥3፤ 30፥29፤ ዘካ 8፥3 ይመ)።

22፥16 *በራሴ ማልሁ፤* እግዚአብሔር፣ ስሙን ጠርቶ ሊምልበት የሚችል ከራሱ የበለጠ ሌላ ስም የለም (ዕብ 6፥13 ይመ)። *ልጅህን፣ ለእኔ ለመስጠት አልሳሳህምና፤* የአብርሃም ፍቅር፣ በዮሐ 3፥16 ላይ ከተመለከተውና በሮሜ 8፥32 ላይ ከተጠቀሰው የእግዚአብሔር ፍቅር ጋር ተጓዳኝ ነው።

22፥17 *ዘርህን እንደ ሰማይ ከዋክብት ... አበዛዋለሁ፤* 13፥16፤ 15፥5 እና ማብ ይመ። *እንደ ባሕር ዳር አሸዋ፤* በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት በከፊል ተፈጽሞአል (1ነገ 4፥20 ይመ)። *ደጆች፤* የአንድን ከተማ ደጅ መውረስ ከተማውን በሙሉ እንደ መውረስ ይቈጠር ነበር (24፥60 ይመ)።

22፥18 *ቃሌን ስለ ሰማህ፤* የ17፥9 ማብ ይመ። *የምድር ሕዝቦች ሁሉ... ይባረካሉ፤* የ12፥2-3 ማብ ይመ።

*22፥23-24፤* የአብርሃም ወንድም ናኮር (11፥26 ይመ) ከሚስቱ ስምንት ወንዶች ልጆች፣ ከቁባቱ ደግሞ አራት ወንዶች ልጆች ወለደ። እነርሱም በኋላ ላይ የዐሥራ ሁለቱ የአራም ነገዶች (ቍ 21 ይመ) ቅድመ አያቶች ነበሩ። የአብርሃም የልጅ ልጅ የነበረው ያዕቆብም የዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ቅድመ አያት ነበር (49፥28 ይመ)።

## የሣራ ሞት

23 ሣራ አንድ መቶ ሃያ ሰባት ዓመት
ኖረች፤ [2]በከነዓን ምድር፣ በቂርያት
አርባቅ ማለትም በኬብሮን ከተማ ሞተች፤
አብርሃምም ለሣራ ሊያለቅስና ሊያዝን መጣ።
[3]ከዚያም አብርሃም ከተቀመጠበት ከሚ
ስቱ ሬሳ አጠገብ ተነሣ፤ ኬጢያውያንንም[o]
እንዲህ አላቸው፤ [4]“እኔ ለአገሩ እንግዳ፣
ለሰዉ ባዳ ሆኜ በመካከላችሁ የምኖር ነኝና
ለመቃብር የምትሆን ቦታ ሽጡልኝ፤ የሚስ
ቴንም ሬሳ ልቅበርበት።”
[5]ኬጢያውያንም ለአብርሃም እንዲህ ሲሉ
መለሱለት፤ [6]“ስማን ጌታዬ፤ አንተ እኮ በእኛ
ዘንድ እንደ ኀያል መስፍን ነህ፤ ከመቃብር
ቦታችን በመረጥኸው ስፍራ ሬሳህን መቅ
በር ትችላለህ፤ ማናችንም ብንሆን የሞተ
ብህን ሰው እንዳትቀብርበት የመቃብር
ቦታችንን አንከለክልህም።”
[7]ከዚያም አብርሃም ተነሥቶ የአገሬውን
ሕዝብ፣ ኬጢያውያንን እጅ ነሣ፤ [8]እንዲ
ህም አላቸው፤ እንድቀብር ከፈቀዳችሁልኝ፣
አንዴ ስሙኝና የሰዓርን ልጅ ኤፍሮንን ስለ
እኔ ሆናችሁ ለምኑልኝ። [9]ይኸውም በዕር
ሻው ድንበር ላይ ያለችውን መክፈላ የተባ
ለችውን ዋሻውን እንዲሸጥልኝ ነው፤ በመካ
ከላችሁም የመቃብር ቦታ እንድትሆነኝ
በሙሉ ዋጋ እንዲሸጥልኝ ለምኑልኝ።
[10]ኬጢያዊው ኤፍሮንም እዚያው መካከ
ላቸው ተቀምጦ ስለ ነበር፣ ወደ ከተማው
በር መግቢያ መጥተው የተሰበሰቡት ኬጢያ
ውያን በሙሉ እየሰሙ ለአብርሃም እንዲህ
ሲል መለሰለት፤ [11]“እንዲህ አይደለም ጌታዬ፤
አድምጠኝ፤ ዕርሻውን በውስጡ ካለው ዋሻ
ጋር ውሰደው፤ እነሆ፤ በወገኖቼ ኬጢያው
ያን ፊት ሰጥቼሃለሁ፤[n] ሬሳህን ቅበርበት።”
[12]አብርሃም እንደ ገና የአገሬውን ሕዝብ
እጅ ነሣና [13]ሁሉም እየሰሙት፣ የዕርሻውን
ቦታ ዋጋ ልክፈል፤ እባክህን ተቀበለኝና ሬሳ
ዬን ልቅበርበት” አለው።
[14]ኤፍሮንም ለአብርሃም እንዲህ ሲል መለሰ
ለት፤ [15]“የመሬቱ ዋጋማ አራት መቶ ጥሬ
ብር[v] ነው፤ ታዲያ ይህ በእኔና በአንተ መካ
ከል ምን ቁም ነገር አለው? ይልቅስ ሬሳ
ህን ቅበርበት” አለው።
[16]አብርሃምም፣ ኤፍሮን በኬጢያውያን ፊት
በተናገረው ዋጋ ተስማማ፤ በወቅቱም የን
ግድ መለኪያ መሠረት አራት መቶ ጥሬ
ብር መዘነለት።
[17]በዚህ ሁኔታ፣ በመምሬ አጠገብ በመክ
ፈላ ያለው የኤፍሮን ዕርሻ ቦታ ከነዋሻው
በክልሉ ካሉት ዛፎች ሁሉ ጭምር ለአብር
ሃም በርስትነት ተላለፈ፤ [18]ወደ ከተማው
በር በመጡት ኬጢያውያንም ሁሉ ፊት
የአብርሃም ንብረት መሆኑም ተረጋገጠለት።
[19]ከዚህም በኋላ አብርሃም በከነዓን ምድር፣
በመምሬ አጠገብ፣ መክፈላ በተባለች ዕርሻ ውስጥ
ባለችው ዋሻ የሚስቱን የሣራን ሬሳ ቀበረ፤
ይህችም ኬብሮን ናት። [20]ስለዚህ ዕርሻውና

[o]3 ወይም *የኬጢ ልጆች*፤ ቍ 5:7:10:16:18 እና 20 እንዲሁ
[n]11 ወይም *ሸጬልሃለሁ*
[v]15 4.5 ኪ.ግ. ገደማ ይሆናል

23፥2 ዘፍ13፥18፤ 24፥67፤ኢሱ14፥15፤1 5፥13፤20፥7፤21፥11
23፥3 ዘፍ10፥15
23፥4 ዘፍ17፥8፤19፥9፤49፥30፤ዘፀ፥22፤ዘሌ 25፥23፤መዝ39፥12፤105፥12፤119፥19፤ዕብ 11፥9:13፤ሐሥ7፥16
23፥6 ዘፍ14፥14-16፤24፥35
23፥8 ዘፍ25፥9
23፥9 ቍ 17:19፤ ዘፍ25፥9፤47፥30፤49፥30፤50፥13
23፥10 ቍ 18፤ዘፍ 18፥1፤ዘዳ22፥15፤25፥7፤ኢሱ20፥4፤ሩት4፥11፤2ሳሙ15፥2፤2ነገ 15፥35፤መዝ127፥5፤ ምሳ31፥23፤ኤር26፥10፤36፥10
23፥11 2ሳሙ24፥23
23፥15 ሕዝ45፥12
23፥16 2ሳሙ14፥26፤24፥24፤ኤር32፥9፤ዘካ11፥12
23፥17 ቍ 9፤ ዘፍ 13፥18
23፥18 ቍ 10፤ዘፍ 12፥7፤18፥1
23፥19 ቍ 9፤ ዘፍ 13፥18፤49፥31፤ኢሱ 14፥13፤1ዜና29፥27

23፥2 *ቂርያትአርባቅ*፤ “የአርባቅ ከተማ” ማለት ነው። (አርባቅ በኬብሮን አካባቢ ይኖር የነበረ የታወቀ የአንድ ጐሣ አባል ነበር፤ ኢያ 14፥15 ይመ)። አናቅ (ኢያ 15፥13-14፤ 21፥11 ይመ) እና ሦስቱ ልጆቹ ይኖሩበት የነበረውን ቦታ ለማመልከት (መሳ 1፥10:20 ይመ) የገባ ስለ ሆነ፣ “የአራት ከተማ” ተብሎ ሊተ ረጐም ይችላል። *መጣ፤* ከቤርሳቤህ ተነሥቶ ወደ ኬብሮን መሄዱን ወይም የሣራ አስከሬን ወዳለበት ቦታ መምጣቱን የሚ ያመለክት ነው።

23፥3 *ኬጢያውያን፤* የ10፥15 ማብ ይመ። በዚያን ወቅት የኬብሮንን ግዛት ይቈጣጠሩ ነበር።

23፥4 *ለአገሩ እንግዳ፣ ለሰዉ ባዳ፤* የእስራኤል አባቶችና ዘሮቻቸው ያሉበትን ሁኔታ ለማመልከት ይህን ሐረግ ብዙ ጊዜ ይጠቀሙበት ነበር (1ዜና 29፥15፤ መዝ 39፥12 ይመ፤ እንዲ ሁም ዕብ 11፥13 ይመ)። አብርሃም በዚች ምድር ይኖር የነበ ረው በምድር ላይ በጣም ጊዜያዊ በሆነ መኖሪያ ይኸውም፣ “በድንኳን” ነበር (ዕብ 11፥9)፤ ይሁን እንጂ የዕብራውያን መልእ ክት ጸሓፊ፣ “መሠረት ያላትን፣ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራ ትን ከተማ” በማለት የሚጠራትን ዘላለማዊ መኖሪያ እግዚአብሔር በገባለት ቃል መሠረት ይጠባበቅ ነበር (ዕብ 11፥10)።

23፥6 *ኀያል መስፍን ነህ፤* ምናልባት ለማቈላመጥ የገባ አነጋገር ሳይሆን አይቀርም።

23፥9 *በዕርሻው ድንበር ላይ፤* አብርሃም ዕርሻውን በሙሉ ቢገዛ ተጨማሪ የገንዘብ ወጪና የማኅበራዊ ጕዳዮች ግዴታ ስለሚያስከትልበት የዕርሻውን ጥቂት ክፍል ብቻ ለመግዛት ዐሰበ። የኬጢያውያን ሕግ አንድ የመሬት ባለቤት ከመሬቱ ጥቂቱን ክፍል ብቻ ለሌላ ሰው ከሸጠ፣ ሻጩ የመሬቱን ማንኛውንም ዕዳ የመ ክፈል ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል። ነገር ግን የመሬቱ ባለቤት መሬቱን በሙሉ ከሸጠ፣ ገዥው የመሬቱን ማንኛውም ዕዳ በሙሉ መክፈል አለበት። *መክፈላ የተባለችውን ዋሻውን፤* በአ ሁኑ ጊዜ ወደ ዋሻው ውስጥ ዘልቆ መግባት ባይቻልም፣ የአ ብርሃምና የሣራ፣ የይስሐቅና የርብቃ፣ የያዕቆብና የሊያ መቃብ ሮች እዚያ ይገኛል (ቍ 19 ይመ እንዲሁም 25፥8-10፤ 49፥30-31፤ 50፥12-13 ይመ)። የሙስሊሞች ቅዱስ ቦታ በሆነው በኬብ ሮን፣ የአብርሃም መስጊድ ተብሎ ከሚጠራው ቦታ ከበስተ ታቹ ባለው አንድ ትልቅ ዋሻ ውስጥ እንደሚገኙ በትውፊት ይነገራል።

23፥10 *ወደ ከተማው በር መግቢያ መጥተው የተሰበሰ ቡት ኬጢያውያን በሙሉ እየሰሙ፤* በጥንት ዘመን ወደ ከተማ የሚያስገቡ ዋና ዋና በሮች፣ ፍርድና ዳኝነት የሚሰጥባቸው ስፍራ ዎች ነበሩ (ቍ 18 ይመ፤ እንዲሁም የ19፥1 ማብ ይመ)።

23፥11 *ጌታዬ፤* ምናልባት አብርሃምን ለማቈላመጥ ፈልጐ ሊሆን ይችላል።

23፥15 *አራት መቶ ጥሬ ብር ነው፤ ታዲያ ይህ በእኔና በአንተ መካከል ምን ቁም ነገር አለው?* የ20፥16 ማብ ይመ። ኤፍሮን ለአብርሃም ቸርነት ያደረገ መስሎ ቢታይም፣ በዚያን ዘመን ግን አንድ የዕርሻ ቦታ በምንም ዐይነት አራት መቶ ጥሬ ብር (ሰቅል) ሊያወጣ አይችልም (ኤር 32፥9 ይመ)። ኤፍሮን በአብ ርሃም ሐዘን ገብቶ የራሱን ጥቅም ለማስጠበቅ ብዙ ሞከረ። ይህን ያደረገው አብርሃም ሣራን ለመቅበር ቦታ ስለሚያስፈል ገው፣ የቦታ ግዥውን ጕዳይ በፍጥነት መጨረስ እንዳለበት ያውቅ ስለ ነበር ነው፤ ስለዚህም አብርሃም መሬቱን እንዲገዛውና የዕዳውንም ኀላፊነት እንዲወስድለት ወተወተው።

23፥16 *በወቅቱም የንግድ መለኪያ መሠረት፤* በየጊዜው የሚለዋወጥ ሚዛን ሲሆን፣ ትክክለኛነቱ አስተማማኝ በነበረውና ነገሥታት ከሚጠቀሙበት ሚዛን የበለጠ ለማጭበርበር የሚያ መች ነበር (2ሳሙ 14፥26 ይመ)።

23፥17 *ዕርሻ ቦታ ከነዋሻው በክልሉ ካሉት ዛፎች ጭምር፤* ኤፍሮን የመክፈላ ዋሻ የሚገኝበት የዕርሻ ቦታና ከቦታውም ጋር ከሚገናኝ ማናቸውም ግዴታ ነጻ ለመሆን ሲል፣ ዕርሻውንና በዕ ርሻው ቦታ ላይ የሚገኘውን ማንኛውም ነገር ሁሉ የሚሸጥበትን ቀን ሆን ብሎ ያራዝም ነበር (የቍ 9 ማብ ይመ)።

23፥19 *በከነዓን ምድር ... የሚስቱን ... ሬሳ ቀበረ፤* በዚ ያን ዘመን የነበሩ ሰዎች በተወለዱበት ምድር፣ “ከአባቶቻቸው ጋር” (የ25፥8 ማብ ይመ) ለመቀበር ከፍተኛ ፍላጐት ነበራቸው። አብርሃም፣ በከነዓን ምድር የመቃብር ቦታ በመግዛቱ፣ እግዚአ ብሔር ለሰጠው ተስፋ ያለውን ታማኝነት አረጋገጠ። ከነዓን የአ ብርሃም አዲስ መኖሪያ ናትና።

በውስጡ የሚገኘው ዋሻ የመቃብር ቦታ እን
ዲሆን፣ ከኬጢያውያን ለአብርሃም በርስት
ነት ተላለፈለት።

## የይስሐቅና የርብቃ ጋብቻ

24 በዚህ ጊዜ አብርሃም ሸመገለ፤ ዕድሜ
ውም ገፋ፤ እግዚአብሔርም (ያህዌ)
አብርሃምን በሁሉ ነገር ባረከው። 2አብርሃም
የንብረቱ ሁሉ ኀላፊ፣ የቤቱ ሁሉ አዛዥ[r]
የሆነውን አረጋዊ አገልጋዩን እንዲህ አለው፤
"እጅህን ከጭኔ በታች አድርግ፤ 3ልጄን፣
በመካከላቸው ከምኖር ከከነዓናውያን ሴቶች
ልጆች ጋር እንዳታጋባው በሰማይና በምድር
አምላክ በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ማልልኝ። 4ነገር
ግን ወደ አገሬ፣ ወደ ገዛ ዘመዶቼ ሄደህ
ለልጄ ለይስሐቅ ሚስት ትፈልግለታለህ።"
5አገልጋዩም፣ "ሴቲቱ ከእኔ ጋር ወደዚህ
ምድር ለመምጣት ፈቃደኛ ባትሆን ምን
አደርጋለሁ? ልጅህን አንተ ወደ መጣህበት
አገር ልውሰደውን?" ሲል ጠየቀው።
6አብርሃምም እንዲህ አለው፤ "ምንም ቢሆን
ልጄን ወደዚያ እንዳትመልሰው ተጠንቀቅ፤
7ከአባቴ ቤት፣ ከትውልድ አገሬ ያወጣኝና፣
'ለዘርህ ይህችን ምድር እሰጣለሁ' ብሎ በመ
ሐላ ተስፋ የገባልኝ የሰማይ አምላክ እግዚ
አብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) መልአኩን ከፊትህ ይል
ካል፤ ለልጄም ሚስት ከዚያ ታመጣለታለህ።
8ሴቲቱ አብራህ ወደዚህ ለመምጣት ፈቃ
ደኛ ካልሆነች ግን ካስማልሁህ መሐላ ነጻ
ትሆናለህ፤ ነገር ግን ወደዚያ አትውሰደው"
አለው። 9ስለዚህም አገልጋዩ እጁን ከጌታው
ከአብርሃም ጭን በታች አድርጐ ስለዚህ
ጒዳይ ማለለት።
10አገልጋዩም ከጌታው ግመሎች መካ
ከል ዐሥሩን ወሰደ፤ ምርጥ ምርጡንም ዕቃ
ሁሉ ጭኖ፣ የናኮር ከተማ ወደምትገኝበት
ወደ ሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ ተጓዘ።
11እዚያም እንደ ደረሰ፣ ግመሎቹን ከከተ
ማው ውጭ የውሃ ጒድጓድ አጠገብ እን
በረከከ፤ ጊዜውም ጥላ የበረደበት፣ ሴቶች
ውሃ ለመቅዳት የሚወጡበት ነበር።

23፥20 ዘፍ10፥15፤ 35፥29፤47፥30፤49፥30፤50፥5፡13፤ኤር 32፥10
24፥1 ቍ35፤ዘፍ 12፥2፤17፥17፤ኢሱ 23፥1፤ገላ3፥9
24፥2 ቍ9፤ዘፍ15፥3፤39፥4-6፤47፥29
24፥3 ቍ7፡37፤ዘፍ 10፥15-19፤14፥19፤47፥31፤50፥25፤ዘኍ 20፥14፤ዘዳ7፥3፤ 2ቆሮ 6፥14፡17
24፥4 ቍ29፤ዘፍ 12፥1፤21፥2፤መሳ 14፥3
24፥5 ቍ39፤ዕብ 11፥15
24፥6 ቍ8
24፥7 ቍ3፤ዘፍ12፥1፡7፤16፥7፤ሮሜ4፥13፤ገላ3፥16
24፥8 ቍ6፡41፤ኢሱ 2፥12፡17፡20፤9፥20
24፥9 ቍ2፤ዘፍ 32፥4፤33፥8
24፥10 ቍ19፡22፡30፡47፡53፤ዘፍ11፥29፤43፥11፤45፥23፤ዘኍ 23፥7፤ዘዳ23፥4፤መሳ 3፥8፤1ነገ10፥2፤1ዜና 12፥40፤ኢሳ30፥6
24፥11 ቍ13፤ዘፍ 29፥2፡9-10፤ዘፀ2፥15፡16፤1ሳሙ9፥11፤ዮሐ4፥7
24፥12 ቍ21፡27፡40፡42፡48፡51፡56፤ዘፍ 19፥19፤26፥24፤27፥20፤28፥13፤31፥42፡53፤32፥9፤43፥23፤46፥3፤ዘፀ3፥6፡15፡16፤4፥5፤ኢሱ2፥12፤ነህ1፥11፤1ነገ18፥36፤ኢዮ 10፥12፤መዝ75፥9፤94፥7
24፥13 ቍ11፡43፤ዘፍ29፥8
24፥14 ቍ18፡19፡44፡46፤ኢሱ2፥12፤መሳ6፡17፡37፤1ሳሙ 14፥10፤1ነገ13፥3፤መዝ86፥17፤ኢሳ 38፥7፤ኤር44፥29
24፥15 ቍ45፤ዘፍ 11፥29፤22፥22፡23

12ከዚያም እንዲህ ሲል ጸለየ፣ "የጌታዬ
የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ)
ሆይ፤ በዛሬው ቀን ጒዳዬን አሳካልኝ፤ ለጌ
ታዬ ለአብርሃም ቸርነትህን አሳየው፤ 13እነሆ፤
እኔ በዚህ ምንጭ አጠገብ ቆሜአለሁ፤ የከ
ተማዪቱ ሴቶች ልጆች ውሃ ለመቅዳት ወደ
ዚህ ይመጣሉ። 14እንግዲህ፣ 'እንስራሽን አው
ርጂና ውሃ አጠጪኝ' ስላት፣ 'እንካ ጠጣ፤
ግመሎችህንም ላጠጣልህ' የምትለኝ ቈንጆ
እርሷ ለባሪያህ ለይስሐቅ የመረጥካት ትሁን፤
በዚህም ለጌታዬ ቸርነትህን እንዳሳየኸው ዐው
ቃለሁ።"
15እርሱም ገና ጸሎቱን ሳይጨርስ፣ እነሆ፤
ርብቃ እንስራዋን በትከሻዋ ላይ አድርጋ
ብቅ አለች። እርሷም ከአብርሃም ወንድም
ከናኮርና ከሚስቱ ከሚልካ የተወለደው የባቱ
ኤል ልጅ ነበረች። 16ልጃገረዲቱ እጅግ
ውብና ወንድ ያልደረሰባት ድንግል ነበረች።
ወደ ምንጩም ወርዳ ውሃ በእንስራዋ ሞልታ
ተመለሰች።
17አገልጋዩም ወደ እርሷ ፈጥኖ ቀረበና፣
"እባክሽ ከእንስራሽ ጥቂት ውሃ አጠጪኝ"
አላት።
18እርሷም፣ "ጌታዬ፤ ጠጣ" አለችው፤ ፈጥ
ናም እንስራዋን ወደ እጇ አውርዳ አጠጣ
ችው።
19እርሱን ካጠጣችው በኋላ፣ "ግመሎችህም
ጠጥተው እስኪጠግቡ ድረስ ውሃ እቀዳላ
ቸዋለሁ" አለች። 20ፈጥናም በእንስራው ውስጥ
የነበረውን ውሃ በገንዳ ውስጥ ገለበጠች፤
እየሮጠች ከጒድጓዱ ውሃ እያመላለሰች
ግመሎቹ እስኪበቃቸው ድረስ አጠጣቻቸው።
21አገልጋዩም አንዲት ቃል ሳይናገራት፣ እግ
ዚአብሔር (ያህዌ) መንገዱን አሳክቶለት እንደ
ሆነ ወይም እንዳልሆነ ለማወቅ ልጂቱን
በአንክሮ ይከታተል ነበር።
22ግመሎቹ ጠጥተው ካበቁ በኋላ ሰውዬው

24፥16 ዘፍ12፥11፤ዘዳ22፥15-21 24፥17 ቍ45፤1ነገ17፥10፤ዮሐ4፥7 24፥18 ቍ14 24፥19 ቍ10፡14 24፥20 ቍ46
24፥21 ቍ12

[r]2 ወይም ታላቅ

24፥2 *የቤቱ ሁሉ አዛዥ የሆነውን አረጋዊ አገልጋዩን፤* ምናልባት የደማስቆው ኤሊኤዘር ሳይሆን አይቀርም (የ15፥2 ማብ ይመ)። *እጅህን ከጭኔ በታች አድርግ፤* በዘር አካል አቅራቢያ ማለት ነው፤ ምክንያቱም ይህ መሐላ የአብርሃም ዘር በይስሐቅ በኩል (47፥29 ይመ) ይቀጥላል ከሚለው ጋር ዝምድና ሳይኖረው አይቀርም።

24፥3 *በሰማይና በምድር አምላክ በእግዚአብሔር፤* ቍ 7 ይመ። አብርሃም በእግዚአብሔር ስም በማለ ጊዜ እንዲህ ያለውን ገርማ ሞገሳዊ ማዕርግ መጠቀሙን በ14፥22 ላይ ይመ።

24፥4 *አገሬ፤* መስጴጦምያ (የቍ 10 ማብ ይመ) ነው። *ሚስት ትፈልግለታለህ፤* የ21፥21 ማብ ይመ።

24፥7 *ለዘርህ ይህችን ምድር እሰጣለሁ፤* በ12፥7 ላይ የተጠቀሰው ተስፋ እዚህ ላይ ተደግሞአል። *መልአኩን፤* የ16፥7 ማብ ይመ።

24፥10 *ግመሎች፤* የ12፥16 ማብ ይመ። *የናኮር ከተማ፤* በአብርሃም ወንድም ስም የተጠራ ሳይሆን አይቀ ርም (ቍ 15፤ 11፥26 ይመ)። ናኮር የሚለው ስም ፈረንሳዮች በ1933 መጀ መሪያዎቹ ላይ በኤፍራጥስ ወንዝ አቅራቢያ በምትገኘው በጥ ንት ሜሪ ከተማ ከከርሰ ምድር ቈፍረው ባወጡት የሸክላ ጽላቶች ላይ ተጠቅሶአል። ናኮር በካራን አውራጃ የምትገኝ ስትሆን፣ (የ11፥31 ማብ ይመ)፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ18ኛው ምእተ ዓመት ላይ አንድ የአሞራውያን ልዑል ይገዛት ነበር። *መስ ጴጦምያ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "በወንዞች መካከል" ማለት ነው። ከዚህ በፊት ይህ ቦታ፣ "አራም ናሃራይም" ተብሎ የሚ ታወቅ ሲሆን፣ ከጊዜ በኋላ ግሪኮች "መስጴጦምያ" የሚለውን ስም አወጡለት።

24፥11 *ጊዜውም... ሴቶች ውሃ ለመቅዳት የሚወጡበት ነበር፤* የቀኑ ቀዝቃዛ ክፍል ነው።

24፥14 *በዚህም... ዐውቃለሁ፤* እንደ ጌታው እንደ አብር ሃም ሁሉ፣ አገልጋዩ ለጒዞው ማረጋገጫ የሚሆነውን ነገር ከእግ ዚአብሔር ጠየቀ (የ15፥8 ማብ ይመ)። *ቸርነትህን፤* ቍ 27 ይመ። በይስሐቅ በኩል ለብዙ ትውልድ ተስፋ የሆነውን፣ ይኸ ውም እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባውን ቃል ኪዳን የሚያ መለክት ሳይሆን አይቀርም (17፥19፤ 21፥12 ይመ)።

24፥15 *ጸሎቱን ሳይጨርስ፤* እግዚአብሔር ገና ድሮ ጸሎ ቱን መመለስ ጀምሮአል። *ርብቃ... ከአብርሃም ወንድም... የባቱኤል ልጅ፤* በዚህ ዐይነት፣ ይስሐቅ የአጎቱን የልጅ ልጅ አግብቶአል ማለት ነው (ቍ 48 ይመ)።

ስድስት ግራም የሚጠጋ የወርቅ አምባሮች
አውጥቶ፣ 23“ለመሆኑ አንቺ የማን ልጅ
ነሽ? በአባትሽ ቤት የምናድርበት ስፍራ ይገኝ
እንደ ሆነ፣ እባክሽ ንገሪኝ” ብሎ ጠየቃት::
24እርሷም፣ “እኔ፣ ሚልካ ለናኮር የወለደ
ችለት፣ የባቱኤል ልጅ ነኝ” አለችው፤ 25ደግ
ሞም፣ “በቤታችን በቂ ገለባና ድርቆሽ እን
ዲሁም ለእናንተ የሚሆን ማደሪያ አለን”
አለችው::
26ሰውየውም ተደፍቶ ለእግዚአብሔር (ያህዌ)
ሰገደ፤ 27እንዲህም አለ፤ “ቸርነቱንና ታማኝ
ነቱን ከጌታዬ ያላጓደለ፣ እኔንም ወደ
ጌታዬ ዘመዶች ቤት የመራኝ፣ የጌታዬ
የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር (ያህዌ) የተ
መሰገነ ይሁን::”
28ልጅቷ ሮጣ ሄዳ፣ የሆነውን ሁሉ ለእ
ናቷ ቤተ ሰቦች ነገረች:: 29ርብቃም ላባ
የተባለ ወንድም ነበራት፤ እርሱም ሰውየው
ወዳለበት የውሃ ጕድጓድ ፈጥኖ ሄደ::
30እኅቱ ያደረገችውን የወርቅ ቀለበትና
አምባሮች እንዳየ፣ እንዲሁም ርብቃ ሰው
የው ያላትን ስትናገር እንደ ሰማ፣ ወዲያ
ውኑ ወደ ሰውየው ሄደ፤ በምንጩም ዳር
ከግመሎቹ አጠገብ ቆሞ አገኘው፤ 31እር
ሱንም “አንተ የእግዚአብሔር (ያህዌ) ቡሩክ
ሆይ፤ ና፤ እዚህ ውጭ የቆምኸው ለምንድን
ነው? እነሆ፤ ለአንተ ማረፊያ ለግመሎ
ችህም ማደሪያ አዘጋጅቻለሁ” አለው::
32ሰውየው ከላባ ጋር ወደ ቤት ሄደ፤ የግ
መሎቹ ጭነት ተራግፎ ገለባና ድርቆሽ
ተሰጣቸው፤ ለእርሱና አብረውት ለነበሩት
ሰዎች የእግር ውሃ ቀረበላቸው:: 33ለሰውየ
ውም ማዕድ ቀረበለት፤ እርሱ ግን፣ “የመ
ጣሁበትን ጕዳይ ሳልናገር እህል አልቀም
ስም” አለ::
ላባም፣ “እሺ፤ ተናገር” አለው::
34እርሱም እንዲህ አለ፤ “እኔ የአብርሃም
አገልጋይ ነኝ፤ 35እግዚአብሔር (ያህዌ) ጌታ
ዬን እጅግ ባርኮታል፤ እርሱም በልጽጓል፤
በጎችና ከብቶች፣ ብርና ወርቅ፣ ወንድና
ሴት አገልጋዮች፣ ግመሎችና አህዮች ሰጥ
ቶታል:: 36የጌታዬ ሚስት ሣራ በስተርጅ
ናዋ[x] ወንድ ልጅ ወልዳለታለች፤ ጌታዬም
ያለውን ሀብት ሁሉ ለልጁ ሰጥቶታል::
37ጌታዬ እንዲህ ሲል አማለኝ፤ ‘ከዚህ ከም
ኖርበት አገር፣ ከከነዓናውያን ሴቶች ልጆች
ጋር ልጄን አታጋባው፤ 38ነገር ግን ወደ አባቴ
ቤት፣ ወደ ገዛ ወገኖቼ ሄደህ ለልጄ ሚስት
አምጣለት’::
39“እኔም ጌታዬን፣ ‘ሴቲቱ ከእኔ ጋር ወደ
ዚህ ለመምጣት ባትፈቅድስ?’ ብዬ ጠየቅ
ሁት::
40“እርሱም እንዲህ አለኝ፤ ‘አካሄዴን በፊቱ
ያደረግሁ እግዚአብሔር (ያህዌ) መልአኩን ከአ
ንተ ጋር ይልካል፤ ከገዛ ወገኖቼና ከአባቴ
ቤት፣ ለልጄ ሚስት እንድታመጣለት መን
ገድህን ያቃናል:: 41ወደ ወገኖቼ ከሄድህ፣
ከመሐላው የተፈታህ ትሆናለህ፤ እነርሱ
እንኳ ልጂቱን አንሰጥም ቢሉህ፣ ከመሐላው
ንጹሕ ትሆናለህ’ አለኝ::
42“እኔም ዛሬ ወደ ውሃው ጕድጓድ ስደ
ርስ እንዲህ ብዬ ጸለይሁ፤ ‘የጌታዬ የአብር
ሃም አምላክ እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) ሆይ፤
ፈቃድህ ቢሆን የመጣሁበትን ጕዳይ አቃ
ናልኝ፤ 43እነሆ፤ በምንጩ አጠገብ ቆሜአ
ለሁ፤ ውሃ ልትቀዳ የምትመጣውን ኮረዳ፣
“ከእንስራሽ ውሃ አጠጪኝ” ስላት፣ 44እሺ
ጠጣ፤ ለግመሎችህም እቀዳላቸዋለሁ” የም
ትለኝ እርሷ እግዚአብሔር (ያህዌ) ለጌታዬ
ልጅ የመረጣት ትሁን::’
45በልቤ የምጸልየውን ጸሎት ገና ሳልጨ
ርስ፣ ርብቃ እንስራዋን በትከሻዋ ላይ አድ
ርጋ ብቅ አለች፤ ወደ ምንጩም ወርዳ
ውሃ ቀዳች:: እኔም፣ ‘እባክሽ፤ ውሃ አጠ
ጪኝ’ አልኋት::
46“እርሷም ፈጥና እንስራዋን ከትከሻዋ
አውርዳ፣ ‘ጠጣ፤ ግመሎችህንም አጠጣለሁ’
አለች:: እኔም ጠጣሁ፤ ግመሎቼንም አጠጣች::
47“ለመሆኑ የማን ልጅ ነሽ” ብዬ ጠየቅ
ኋት::
“እርሷም፣ ‘ሚልካ ለናኮር የወለደችለት፣
የባቱኤል ልጅ ነኝ’ አለችኝ::
“ከዚያም ቀለበቱን አደረግሁላት፤ አም
ባሩንም በእጇ አስገባሁላት:: 48ተደፍቼም
ለእግዚአብሔር (ያህዌ) ሰገድሁ፤ ለጌታዬ ወን
ድም የልጅ ልጅ የሆነችውን ቈንጆ፣ ለጌ
ታዬ ልጅ እንዳገኝለት በቀና መንገድ የመ
ራኝ የጌታዬ የአብርሃምን አምላክ እግዚአ
ብሔርን (ኤሎሂም ያህዌ) አመሰገንሁ:: 49እንግ
ዲህ አሁን ለጌታዬ በጎነትና ታማኝነት
የምታሳዩ ከሆነ ሐሳባችሁን አስታውቁኝ፤
ካልሆነ ግን ቍርጡን ንገሩኝና የምሄድበትን
ልወስን::”
50ላባና ባቱኤል እንዲህ ሲሉ መለሱ፤
“ነገሩ ከእግዚአብሔር (ያህዌ) ስለሆነ በዚህም
ሆነ በዚያ ምንም ማለት አንችልም:: 51ርብቃ
ይቻትልህ፤ ይዘሃት ሂድ፤ እግዚአብሔር (ያህዌ)
እንደተናገረው ለጌታህ ልጅ ሚስት ትሁነው::”
52የአብርሃም አገልጋይ ያሉትን በሰማ
ጊዜ በምድር ላይ ተደፍቶ ለእግዚአብሔር
(ያህዌ) ሰገደ:: 53ከዚያም የወርቅና የብር ጌጣ

24፥22 ቍ10:47፤ ዘፍ41፥42፤ ኢሳ3፥21፤ ሕዝ16፥11-12
24፥23 ቍ47፤ መሳ19፥15፤ 20፥4
24፥24 ቍ29:47፤ ዘፍ11፥29
24፥25 ቍ32፤ መሳ19፥19
24፥26 ቍ48:52፤ ዘፀ4፥31፤ 12፥27፤ 1ዜና29፥20፤ 2ዜና20፥18
24፥27 ቍ12:48:49፤ ዘፍ12፥1፤ 14፥20፤ 32፥10፤ 47፥29፤ ዘፀ18፥10፤ ኢሱ2፥14፤ ሩት4፥14፤ 1ሳሙ25፥32፤ 2ሳሙ18፥28፤ 1ነገ1፥48፤ 8፥56፤ መዝ28፥6፤ 41፥13፤ 68፥19፤ 98፥3፤ 106፥48፤ ሉቃ1፥68
24፥28 ዘፍ29፥12
24፥29 ቍ4፤ ዘፍ25፥20፤ 27፥43፤ 28፥2:5፤ 29፥5:12:13
24፥30 ቍ10፤ ሕዝ23፥42
24፥31 ዘፍ26፥29፤ መዝ115፥15
24፥32 ቍ25፤ ዘፍ18፥4
24፥34 ዘፍ15፥3
24፥35 ቍ1፤ ዘፍ12፥2:16፤ 23፥6
24፥36 ዘፍ17፥17፤ 25፥5፤ 26፥14
24፥37 ቍ3፤ ዘፍ50፥5:25
24፥38 ዘፍ21፥21
24፥39 ቍ5
24፥40 ቍ12፤ ዘፍ5፥22፤ 12፥1፤ 16፥7
24፥41 ቍ8
24፥42 ቍ12
24፥43 ቍ13:14፤ ዮሐ30፥19፤ ኢሳ7፥14
24፥44 ቍ14
24፥45 ቍ15:17፤ 1ሳሙ1፥13፤ ዮሐ4፥7
24፥46 ቍ18-20
24፥47 ቍ10:22:23:24፤ ዘፍ22፥22፤ ኢሳ3፥19፤ ሕዝ16፥11-12
24፥48 ቍ12:26:27
24፥49 ቍ27
24፥50 ዘፍ22፥22፤ 31፥7:24:29:42፤ 48፥16፤ መዝ118፥23
24፥51 ቍ12
24፥52 ቍ26

[x]36 ወይም በስተርጅናው

24፥22 ስድስት ግራም፤ ግማሽ ሰቅል ነው (ዘፀ 38፥26 ይመ)፤ የ20፥16 ማብ ይመ::
24፥32-33፤ የ18፥2 ማብ ይመ::
24፥34-49፤ አገልጋዩ የመጣበትን ጕዳይ ለርብቃ ቤተ ሰብ አስረዳ:: የአገልጋዩ ንግግር የምዕራፉን የመጀመሪያ ክፍል በአጭሩ የሚተርክ ሲሆን፣ በጥንት ዘመን ታሪክ እንዴት ይተረክ እንደ ነበር በግሩም ሁኔታ የሚገልጽና የአንድን ታሪክ ዝርዝር ሐሳብ በሰሚዎች ኅሊና ውስጥ በማይረሳ መልኩ ለማስቀመጥ የሚያገለግል ነበር::
24፥40 አካሄዴን በፊቱ ያደረግሁ፤ የ5፥22፤ 6፥8-9፤ 17፥1 ማብ ይመ::

ጌጥ፣ እንዲሁም ልብሶች አውጥቶ ለርብቃ
ሰጣት፤ ደግሞም ለወንድሟና ለእናቷ ከፍ
ያለ ዋጋ ያላቸው ስጦታዎች ሰጣቸው።
54 እርሱና አብረውት የነበሩ ሰዎችም በል
ተው፣ ጠጥተው እዚያው ዐደሩ፤
በማግስቱ ጠዋት ሲነሡ፣ የአብርሃም አገ
ልጋይ፣ "እንግዲህ ወደ ጌታዬ እንድመለስ
አሰናብቱኝ" አለ።
55 ወንድሟና እናቷም፣ "ልጂቷ ከእኛ ጋር
ቢያንስ ዐሥር ቀን ያህል ትቈይና ከዚያ
በኋላ ልትሄድ[ፀ] ትችላለች።" ብለው መለሱ።
56 እርሱ ግን፣ "እግዚአብሔር (ያህዌ) መን
ገዴን አቅንቶልኛልና አታዘግዩኝ፤ ወደ
ጌታዬ እንድመለስ አሰናብቱኝ" አላቸው።
57 እነርሱም፣ "ለማናቸውም ልጂቱን እንጥ
ራትና ትጠየቅ" አሉ። 58 ስለዚህ ርብቃን
ጠርተው፣ "ከዚህ ሰው ጋር መሄድ ትፈቅ
ጃለሽ?" ሲሉ ጠየቋት።
እርሷም፣ "አዎን፤ እሄዳለሁ" አለች።
59 ከዚያም እኅታቸውን ርብቃን ከሞግ
ዚቷ ጋር፣ እንዲሁም የአብርሃምን አገልጋ
ይና አብረውት የነበሩትን ሰዎች አሰናበቷ
ቸው። 60 ርብቃንም እንዲህ ብለው መረቋት፤

"እኅታችን ሆይ፤ እልፍ አእላፋት ሁኚ፤
ዘርሽ የጠላቶቹን ደጆች ይውረስ"።

61 ከዚያም ርብቃና አገልጋዮቿ ተዘጋጁ፤
ግመሎቻቸውም ላይ ወጥተው ሰውየውን
ተከተሉት፤ በዚህ ሁኔታ አገልጋዩ ርብቃን
ይዟት ሄደ።
62 በዚህን ጊዜ፣ ይስሐቅ በኔጌብ ይኖር ስለ
ነበር፣ ከብኤርላሃይሮኢ መጥቶ ነበር። 63 እር
ሱም አንድ ምሽት ላይ በጥሞና[ገ] ለመ
ቈየት ወደ መስክ ወጣ አለ፤ ቀና ብሎ ሲመ
ለከትም፣ ግመሎች ከሩቅ ሲመጡ አየ።
64 ርብቃም እንደዚሁ አሻግራ ስትመለከት፣
ይስሐቅን አየች፤ ከግመልም ወረደች፤ 65 አገ
ልጋዩንም፣ "ይህ ሊገናኘን በመስኩ ውስጥ
ወደዚህ የሚመጣው ሰው ማን ነው?" ስትል
ጠየቀችው።

24፥53 ቍ10፤ዘፍ 45፥22፤ዘፀ3፥22፤ 12፥35፤2ነገ5፥5
24፥54 ቍ56:59፤ ዘፍ30፥25
24፥55 መሳ19፥4
24፥56 ቍ12:54
24፥57 መሳ19፥3
24፥58 ሩት1፥16
24፥59 ቍ54፤ዘፍ 35፥8
24፥60 ዘፍ17፥16፤ 22፥17፤27፥4:19፤28፥ 1፤31፥55፤48፥9:15: 20፤ኢሱ22፥6፤መዝ 127፥5፤ምሳ27፥11
24፥61 ዘፍ16፥11 30፥3፤46፥25
24፥62 ዘፍ12፥9፤ 16፥14
24፥63 ኢሱ1፥8፤ መዝ1፥2፤18፥2፤ 77፥12፤119፥15: 27:48:97:148፤ 143፥5፤145፥5
24፥64 ዘፍ31፥17: 34፤1ሳሙ30፥17
24፥65 ዘፍ38፥14፤ ማሕ1፥7፤4፥1:3፤ 6፥7፤ኢሳ47፥2
24፥67 ዘፍ18፥9፤ 23፥1-2፤31፥33፤25፥ 20፤29፥18:20፤34፥3፤ 49፥31፤መሳ16፥4
25፥2 ዘፍ36፥35፤ 37፥28:36፤ዘፀ2፥15፤ ዘኍ22፥4፤25፥6: 18፤31፥2፤ኢሱ13፥ 21፤መሳ6፥1:3፤7፥1፤ 8፥1:22:24፤9፥17፤ 1ነገ11፥18፤ኢዮ2፥11 18፥1፤መዝ83፥9፤ኢሳ 9፥4፤10፥26፤60፥6፤ ኤር25፥25፤ዕን3፥7
25፥3 ዘፍ10፥7
25፥4 ኢሳ60፥6
25፥5 ዘፍ24፥36
25፥6 ዘፍ21፥10፤ 22፥24፤29፥1፤መሳ 6፥3:33፤1ነገ4፥30፤ ኢዮ1፥3፤ሕዝ25፥4
25፥7 ቍ26፤ዘፍ 12፥4፤35፥28፤47፥9: 28፤50፥22:26፤ኢዮ 42፥16
25፥8 ቍ17፤

አገልጋዩም፣ "ጌታዬ ነው" ብሎ መለሰ
ላት፤ እርሷም መሸፈኛዋን ተከናነበች።
66 አገልጋዩም ያደረገውን ሁሉ ለይስሐቅ
ነገረው። 67 ይስሐቅም ርብቃን ወደ እናቱ
ወደ ሣራ ድንኳን ይዟት ገባ፤ አገባትም፤
ሚስት ሆነችው፤ እርሱም ወደዳት። ይስሐቅም
ከእናቱ ሞት ተጽናና።

## የአብርሃም መሞት

25፥1-4 ተጓ ምብ - 1ዜና 1፥32-33

25 አብርሃም ኬጡራ የተባለች ሌላ ሚስት
አገባ።[ጠ] 2 እርሷም፦ ዘምራንን፣ ዮቅሳ
ንን፣ ሜዳንን፣ ምድያምን፣ የስቦቅንና ስዌሕን
ወለደችለት። 3 ዮቅሳንም ሳባንና ድዳንን
ወለደ፤ የድዳንም ልጆች፦ አሦራውያን፣ ለጡ
ሳውያንና ለኡማውያን ናቸው። 4 የምድያም
ልጆች፦ ጌፌር፣ ዔፌር፣ ሄኖኅ፣ አቢዳዕና ኤል
ዳድ ናቸው። እነዚህ ሁሉ የኬጡራ ልጆች
ናቸው።
5 አብርሃም ያለውን ሀብት ሁሉ ለይስሐቅ
አወረሰው፤ 6 ለቁባቶቹ ልጆች ግን በሕይ
ወት እያለ ስጦታ አደረገላቸው፤ ከልጁ ከይ
ስሐቅም ርቀው እንዲኖሩ ወደ ምሥራቅ
ምድር ሰደዳቸው።
7 አብርሃም በጠቅላላው መቶ ሰባ አምስት
ዓመት ኖረ። 8 ከዚያም ዐረፈ፤ ዕድሜ ጠግቦ
በመልካም ሽምግልና ሞተ፤ ወደ ወገኖቹም
ተሰበሰበ። 9 ልጆቹ ይስሐቅና እስማኤል በመ
ምሬ አጠገብ በምትገኝ በኬጢያዊው በሰዓር
ልጅ በኤፍሮን ዕርሻ በመክፈላ ዋሻ ቀበሩት፤
10 ይህም የዕርሻ ቦታ አብርሃም ከኬጢያው
ያን[ጨ] የገዛው ነበር፤ ከሚስቱ ከሣራ አጠገብ
በዚያ ተቀበረ። 11 አብርሃም ከሞተ በኋላ
እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ይስሐቅን ባረከው፤ በዚህ
ጊዜ ይስሐቅ በብኤርላሃይሮኢ አቅራቢያ ይኖር
ነበር።

ዘፍ15፥15፤35፥29፤49፥29:33፤ዘኍ20፥24፤31፥2፤ዘዳ31፥14፤32፥50፤ 34፥5 25፥9 ዘፍ13፥18፤23፥8:9፤35፥29፤47፥30፤49፥31፤50፥13፤ 25፥10 ዘፍ10፥15 25፥11 ዘፍ12፥2፤16፥14

[ፀ]55 ወይም *ልትሄጂ*
[ገ]63 በዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጒም አይታወቅም
[ጠ]1 ወይም *አግብቶ ነበር*
[ጨ]10 ወይም *የኬጢ ልጆች*

*24፥53፤* ለርብቃና ለቤተ ሰቧ የተሰጠው ውድ ስጦታ፣ ከምትወዳቸውና ከትውልድ አገሯ ርቃ እንድትሄድ ለጋብቻ የጠየቃት ቤተ ሰብ ምን ያህል ሀብታም እንደሆነ ያመለክታል።

*24፥60፤* 22፥17 እና ማብ ይመ።

24፥62 *ብኤርለሃይሮኢ፤* የ16፥14 ማብ ይመ።

24፥65 *መሸፈኛዋን ተከናነበች፤* ያላገባች መሆኗን የሚያሳይ ምልክት ሳይሆን አይቀርም (ከ38፥14:19 ጋር ያነጻጽሩ)።

24፥67 *ድንኳን፤* እንደ ሙሽራ ቤት አድርገው ይጠቀሙበት ነበር (መዝ 19፥4-5 ይመ)።

25፥1 *ሌላ ሚስት አገባ፤* ሌላ ሴት የሚለው፣ "ቁባቱን" እንዳገባ ያመለክታል (1ዜና 1፥32)። *አገባ፤* በዚህ ጊዜ የአብርሃም ዕድሜ 140 ዓመት ነበር።

*25፥2-4፤* በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ስሞች በአብዛኛው የዐረብ ስሞች ናቸው። ይህም እግዚአብሔር፣ "የብዙ ሕዝቦች አባት ትሆናለህ" ብሎ ለአብርሃም የገባው ኪዳን መፈጸሙን ያመለክታል (17፥4 ይመ)።

25፥5 *ያለውን ሀብት ሁሉ ለይስሐቅ አወረሰው፤* በዚያን ዘመን በነበረው ሥርዐት መሠረት፣ አባት ሲሞት የመጀመሪያ ልጁ የሀብቱን ሁለት ዕጥፍ የመውረስ መብት ነበረው (ዘዳ 21፡15-17)። በኑዚ፣ በለርሳ (ባቢሎን) እና በአሦር የነበረው ሥርዐት ከዚህ ጋር ይመሳሰላል። በሕጉ መሠረት ይስሐቅ የአብ ርሃም የበኵር ልጅ ነበር።

25፥6 *ስጦታ፤* ለሌሎች የአብርሃም ልጆች ተርፎ የነበረውን ውርስ ያመለክታል። *ቁባቶቹ፤* ምንም እንኳ ብዙ ሚስቶችን ማግባት የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ፈቃድ ባይሆንም (የ4፥19 ማብ ይመ)፣ በጥንት ዘመን የእግዚአብሔር ሰዎች የሚባሉት እንኳ ብዙ ሚስቶች የማግባት ልምድ ነበራቸው።

25፥7 *መቶ ሰባ አምስት ዓመት፤* አብርሃም ከካራን ከወጣ በኋላ አንድ ድፍን ምእተ ዓመት ኖረ (12፥4)።

25፥8 *ዕድሜ ጠግቦ፤* ለኢዮብም እንዲህ ተብሎ ተነግሮለታል (ኢዮ 42፥17 ይመ)። *በመልካም ሽምግልና ሞተ፤* በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል መሠረት፣ (15፥15 ይመ)። *ወደ ወገኖቹም ተሰበሰበ፤* በሞት ተለይተውት የነበሩትን ቅድመ አያቶቹን ወይም ዘመዶቹን ተቀላቀላቸው ማለት ነው (2ነገ 22፥20፤ 2ዜና 34፥28 ይመ)።

25፥9 *ይስሐቅና እስማኤል፤* ይስሐቅ ሕጋዊ የበኵር ልጅ በመሆኑ (የቍ 5 ማብ ይመ) ስሙ በመጀመሪያ ተጠቅሶአል።

25፥11 *በብኤርለሃይሮኢ፤* የ16፥14 ማብ ይመ።

## የእስማኤል ልጆች

25፥12-16 ተጓ ምብ - 1ዜና 1፥29-31

12ግብፃዊቷ የሣራ አገልጋይ አጋር፣ ለአ
ብርሃም የወለደችለት የእስማኤል ትውልድ
ይህ ነው::
13የእስማኤል ልጆች ስም እንደ ዕድሜያ
ቸው ቅደም ተከተል እንዲህ ነው:- የእስማ
ኤል የበኵር ልጅ ነብዳኤል፣ መብሳም፣
14 ነባዮት፣ ቄዳር፣ ማስማዕ፣ ዱማ፣ ማሣ፣
15ኩዳን ቴማን፣ ኢጡር፣ ናፌስና ቄድማ::
16እነዚህ የእስማኤል ልጆች ነበሩ፤ እነርሱም
በኖሩባቸውና በሰፈሩባቸው ቦታዎች የዐሥራ
ሁለት ነገድ አለቆች ስሞች ናቸው:: 17እስ
ማኤል በጠቅላላው መቶ ሠላሳ ሰባት ዓመት
ኖረ፤ ከዚያም ሞተ፤ ወደ ወገኖቹም ተሰበሰበ::
18ዘሮቹም መኖሪያቸውን ከግብፅ ድንበር አጠ
ገብ፣ ወደ አሦር በሚወስደው መንገድ፣
በኤውላጥና በሱር መካከል አደረጉ፤ ከወን
ድሞቻቸውም ሁሉ ጋር በጠላትነት ኖሩ::[ሀ]

## ያዕቆብና ዔሳው

19የአብርሃም ልጅ የይስሐቅ ትውልድ ይህ
ነው፤
አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤ 20ይስሐቅ ርብ
ቃን ሲያገባ ዕድሜው አርባ ዓመት ነበር፤
ርብቃ በሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ የሚ
ኖረው የሶርያዊው የባቱኤል ልጅ፣ የሶር
ያዊውም የላባ እኅት ነበረች::
21ይስሐቅ፣ ርብቃ መካን ስለ ነበረች ስለ
እርሷ ወደ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ጸለየ፤ *እግዚ
አብሔርም* (ያህዌ) ጸሎቱን ሰማ፤ ርብቃም ፀነ
ሰች:: 22ልጆቹም በማሕፀኗ ውስጥ እርስ
በርሳቸው ይጋፉ ጀመር፤ እርሷም "ለምን
እንዲህ ይሆንብኛል?" ብላ *እግዚአብሔርን* (ያህዌ)
ለመጠየቅ ሄደች::
23*እግዚአብሔርም* (ያህዌ) እንዲህ አላት፤
"ወገኖች በማሕፀንሽ አሉ፤
ሁለትም ሕዝቦች ከውስጥሽ ተለያይተው
ይወጣሉ፤
አንደኛው ከሌላው ይበረታል፤
ታላቁም ለታናሹ አገልጋይ ይሆናል"
አላት::
24የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስም፣ እነሆ፤ በማሕ
ፀንዋ መንታ ወንዶች ልጆች ነበሩ:: 25በመ
ጀመሪያ የተወለደው መልኩ ቀይ፣ ሰውነ
ቱም በሙሉ ጠጕር የለበሰ ነበር፤ ስለዚህ
ስሙ ዔሳው[ለ] ተባለ:: 26ከዚያም ወንድሙ
ተወለደ፤ በእጁም የዔሳውን ተረከዝ ይዞ
ወጣ፤ ከዚህም የተነሣ ስሙ ያዕቆብ[ሐ] ተባለ::
ርብቃ ልጆቿን ስትወልድ፣ ይስሐቅ የሥ
ልሳ ዓመት ሰው ነበር::
27ልጆቹም አደጉ፤ ዔሳው ጐበዝ ዐዳኝ፣
የበረሓም ሰው ሆነ፤ ያዕቆብ ግን ጭምት፣
ከድንኳኑ የማይወጣ ሰው ነበር:: 28ይስሐቅ
ከዐደን የመጣ ሥጋ ደስ ይለው ስለ ነበር፣ ዔሳ
ውን ይወደው ነበር፤ ርብቃ ግን ያዕቆብን
ትወደው ነበር::
29አንድ ቀን ያዕቆብ ወጥ እየሠራ ሳለ ዔሳው
እጅግ ተርቦ ከዱር መጣ:: 30ዔሳውም ያዕ
ቆብን፣ "ቶሎ በል፤ በጣም ርቦኛልና ከዚህ
ቀይ ወጥ አብላኝ" አለው:: ስለዚህም ስሙ
ኤዶም ተባለ::
31ያዕቆብም፣ "በመጀመሪያ ብኵርናህን ሽጥ
ልኝ" አለው::
32ዔሳውም፣ "እነሆ፣ ልሞት ደርሻለሁ፤ ታዲያ
ብኵርናው ምን ያደርግልኛል!" አለ::
33ያዕቆብም ዔሳውን፣ "እንግዲያማ፣ አስ
ቀድመህ ማልልኝ" አለው፤ ስለዚህም ማለ
ለት፤ ብኵርናውንም ለያዕቆብ ሸጠለት::
34ያዕቆብም ለዔሳው እንጀራና የምስር ወጥ
ሰጠው፤ እርሱም ከበላና ከጠጣ በኋላ ተነ
ሥቶ ሄደ::

25፥12 ዘፍ2፥4፡16፥1፡17፥20፡21፥18፤
25፥13 ዘፍ28፥9፤36፥3፤መዝ120፥5፤ማሕ1፥5፤ኢሳ21፥16፤42፥11፤60፥7፤ኤር2፥10፤49፥28፤ሕዝ27፥21
25፥14 ኢሱ15፥52፤ኢሳ21፥11፤አብ1፥1
25፥15 1ዜና5፥19፤ኢዮ6፥19፤ኢሳ21፥14፤ኤር25፥23
25፥16 ዘፍ13፥16፤17፥20፤መዝ83፥6
25፥17 ቍ8
25፥18 ዘፍ17፥20፤21፥18፤16፥7:12
25፥19 ዘፍ2፥4
25፥20 ቍ26፤ዘፍ24፥29:67፤26፥34፤28፥2:5:6፤30፥20፤31፥18:20:4፤35፥9:26:28፤46፥15፤48፥7፤ዘዳ26፥5
25፥21 ዘፍ11፥30፤30፥17:22፤1ሳሙ1፥17:23፤1ዜና5፥20፤2ዜና33፥13፤ዕዝ8፥23፤መዝ127፥3
25፥22 ዘፀ18፥15፤28፥30፤33፥7፤ዘሌ24፥12፤ዘኍ9፥6-8፤27፥5:21፤ዘዳ17፥9፤መሳ18፥5፤1ሳሙ9፥9፤10፥22፤14፥36፤22፥10፤1ነገ22፥8፤2ነገ3፥11፤22፥13፤ኢሳ30፥2፤ኤር21፥2፤37፥7:17፤ሕዝ14፥7፤20፥1:3
25፥23 ዘፍ9፥25፤17፥4፤48፥14:19፤ሮሜ9፥11-12
25፥24 ዘፍ38፥27፤ሉቃ1፥57፤2፥6
25፥25 ዘፍ27፥1:11:15፤1ሳሙ16፥12
25፥26 ቍ7:20፤ዘፍ27፥36፤32፥27፤38፥29፤ዘዳ23፥7፤ኢሱ24፥4፤ሆሴ12፥3፤አብ1፥10:12
25፥27 ቍ29፤ዘፍ10፥9፤27፥3:5
25፥28 ዘፍ27፥3:4:6:9:14:19፤3፥73 25፥29 ቍ27፤2ነገ4፥38-40 25፥30 ቍ34፤ዘፍ32፥3፤36፥1:8-9:19፤ዘኍ20፥14፤ዘዳ23፥7፤መዝ137፥7፤ኤር25፥21፤40፥11፤49፥7 25፥31 ዘዳ21፥16-17፤1ዜና5፥1-2 25፥33 ዘፍ21፥23፤27፥36፤47፥31፤ዕብ12፥16

[ሀ]18 ወይም *በስተ ምሥራቅ ኖሩ*
[ለ]25 *ዔሳው* ማለት *ጠጕራም* ማለት ነው፤ በተጨማሪ *ኤዶም* ተብሎ ተጠርቶአል፤ ትርጕሙም *ቀይ* ማለት ነው
[ሐ]26 *ያዕቆብ* ማለት *ተረከዝ ይይዛል* ማለት ነው፤ በምሳሌያዊ አገላለጽ *ያታልላል* ማለት ነው

25፥12 *ትውልድ፤* የ2፥4 ማብ ይመ::

25፥13 *የእስማኤል ልጆች ስም፤* በርካታ የዐረብ ስሞች የዐረቦችን ወግና ባህል መሠረት ያደረጉ በመሆናቸው እስማኤል አባታቸው እንደ ሆነ ያወሳሉ::

25፥16 *የዐሥራ ሁለት ነገድ አለቆች፤* በ17፥20 ላይ አስቀድሞ እንደ ተነገረው ከአብርሃም ልጅ ከእስማኤል የተወለዱ ነገዶች ናቸው:: የአብርሃም ወንድም ናኮርም እንደዚሁ የዐሥራ ሁለት ነገድ አባት ነው (የ22፥23-24 ማብ ይመ)::

25፥18 *በጠላትነት፤* የ16፥12 ማብ ይመ::

25፥19 *ትውልድ፤* የ2፥4 ማብ ይመ::

25፥22 *ይጋፉ ጀመር፤* የያዕቆብና የዔሳው ትግል የተጀመረው በማሕፀን ውስጥ ነው (ቍ 26 ይመ):: *ሄደች፤* ምናልባት በአቅራቢያዋ ወዳለው የአምልኮ ሥፍራ ሳይሆን አይቀርም::

25፥23 *ታላቁም ለታናሹ አገልጋይ ይሆናል፤* በጥንት ዘመን በነበረው፣ "በኵርናን የማውረስ" ሕግ (የቍ 5 ማብ ይመ) ታናናሾች ለታላላቆች እንደ አገልጋይ በመሆን ይገዙ ነበር:: እግዚአብሔር ታናሹን ልጅ መምረጡ ግን እግዚአብሔር በራሱ መለኮታዊ አሠራር በሰው ጕዳይ ውስጥ ጣልቃ እየገባ (የ11፥30 ማብ ይመ) የራሱን ሕዝብ እንደሚመርጥ የሚገልጽ ነው:: ይህ ክፍል እግዚአብሔር የወደደውን ለማድረግ መለኮታዊ ሥልጣን እንዳለው ለመግለጽ ምሳሌ ሆኖ (መዝ 115፥3) በሮሜ 9፥10-12 ላይ ተጠቅሶአል፤ ይኸውም እግዚአብሔር ፍጹም በሆነው ፈቃዱ ያደረገው ለመግለጽ እንጂ፣ ለማዳላት ያደረገው አለመሆኑን የሚገልጽ ነው (ሮሜ 9፥14 ይመ)::

*25፥24-26፤* በ38፥27-30 ላይም ሁለት መንታ ወንዶች ልጆች ልዩ በሆነ መልክ ተወልደዋል::

25፥25 *ቀይ፤* በኅብር ቅኔ ለኤዶም የተሰጠ ስም ነው (ቍ 30 ይመ)::

25፥26 *የዔሳውን ተረከዝ ይዞ ወጣ፤* የያዕቆብ ዘሮች በሆኑት በእስራኤላውያንና የዔሳው ዘሮች በሆኑት ኤዶማውያን መካከል የተፈጠረው ጠብ እንደ አጋጣሚ መታየት ሲገባው እንደ መሠረታዊ ነገር ተቈጠረ (ዘኍ 20፥14፤ አብ 9-10 ይመ):: *ያዕቆብ፤* የስሙ ቀጥተኛ ትርጕም፣ "ተረከዝ ይይዛል" ማለት ሲሆን፣ ተምሳሌታዊ ትርጕሙ ደግሞ፣ "ያታልላል" ማለት ነው::

25፥31 *ብኵርናህን ሽጥልኝ፤* በጥንት ጊዜ ብኵርና በመጀመሪያ ለተወለደው ልጅ የሚሰጠውን የውርስ መብትንም ይመለከታል (ዕብ 12፥16 ይመ፤ እንዲሁም የቍ 5 ማብ ይመ):: ያዕቆብ የሌሎችን መልካም ዕድል ለራሱ ለማድረግ ሌት ተቀን የማያርፍ መሰሪ ነበር፤ የተባረከው ግን በራሱ ጥበብ ሳይሆን በእግዚአብሔር ውሳኔና ጥበቃ ነበር::

25፥33 *አስቀድመህ ማልልኝ፤* ውልን ወይም ስምምነትን ሕጋዊ ለማድረግ የቃል መሐላ ብቻውን በቂ ነበር::

25፥34 *የምስር ወጥ፤* አተር የሚመስል፣ ልጣጩ ሲቀቀል የሚቀላና በያመቱ የሚመረት የጥራጥሬ እህል ዐይነት ነው::

ዔሳው ብኵርናውን እንዲህ አድርጎ አቃ
ለላት::

## ይስሐቅና አቢሜሌክ

26፥1-11 ማመ - ዘፍ 12፥10-20፤ 20፥1-18

26 ቀድሞ በአብርሃም ዘመን ከደረሰው
ራብ ሌላ፣ በአገሩ ላይ ራብ ሆነ::
ይስሐቅም የፍልስጥኤም ንጉሥ አቢሜሌክ
ወደሚኖርበት ወደ ጌራራ ሄደ:: 2በዚያም
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ለይስሐቅ ተገልጦ እን
ዲህ አለው፤ "እኔ በምነግርህ ምድር ተቀ
መጥ እንጂ፣ ወደ ግብፅ አትውረድ፤ 3ለጥ
ቂት ጊዜ እዚሁ አገር ተቀመጥ፤ እኔም
ካንተ ጋር እሆናለሁ፤ እባርክሃለሁም፤ ይህን
ምድር በሙሉ ለአንተና ለዘርህ በመስጠት
ለአባትህ ለአብርሃም በመሐላ የገባሁለትን
ቃል አጸናለሁ:: 4ዘርህን እንደ ሰማይ ከዋ
ክብት አበዛለሁ፤ ይህን ምድር በሙሉ ለዘ
ርህ እሰጣለሁ፤ የምድር ሕዝቦችም ሁሉ በዘ
ርህ አማካይነት ይባረካሉ፤ 5ይኸውም አብ
ርሃም ቃሌን ሰምቶ፣ ድንጋጌዬን፣ ትእዛ
ዜን፣ ሥርዐቴንና ሕጌን በመጠበቁ ነው::"
6ስለዚህ ይስሐቅ በጌራራ ተቀመጠ::
7የዚያም አገር ሰዎች ስለ ሚስቱ በጠየ
ቁት ጊዜ፣ "እኅቴ ናት" አለ፤ ምክንያቱም፣
"ሚስቴ ናት ብል ርብቃ ቈንጆ ስለ ሆነች፣
ያገሬው ሰዎች በእርሷ ምክንያት ይገድሉ
ኛል" በማለት ፈርቶ ነበር::
8ይስሐቅ ብዙ ጊዜ በዚያ ከኖረ በኋላ፣
የፍልስጥኤም ንጉሥ አቢሜሌክ አንድ ቀን
ወደ ውጭ ሲመለከት፣ ይስሐቅ ሚስቱን
ርብቃን ሲዳራት አየ:: 9አቢሜሌክም ይስሐ
ቅን ጠርቶ፣ "እርሷ ሚስትህ ሆና ሳለች፣
እንዴት እኅቴ ናት ትላለህ?" አለው::
ይስሐቅም፣ "በእርሷ ሰበብ፣ ሕይወቴን
እንዳላጣ ብዬ ነው" አለው:: 10አቢሜሌክም
መልሶ፣ "እንዲህ ያለ ነገር ያደረግህብን ለም
ንድን ነው? ከሰዎቻችን አንዱ ሚስትህን
ቢደፍራት ኖሮ በእኛ ላይ በደል አስከትለ
ህብን ነበር እኮ!" አለው::
11አቢሜሌክም፣ "ይህን ሰው ወይም ሚስ
ቱን የነካ በሞት ይቀጣል" የሚል ትእዛዝ
ለሕዝቡ ሁሉ አወጣ::
12ይስሐቅም በዚያች ምድር ዘር ዘራ፣ *እግ
ዚአብሔርም* (ያህዌ) ባረከለትና በዚያኑ ዓመት
መቶ ዕጥፍ አመረተ:: 13ሰውየውም እጅግ
ባለ ጠጋ እስኪሆን ድረስ ሀብት በሀብት
ላይ እየተጨመረለት ሄደ:: 14ብዙ የበግና
የፍየል መንጋ፣ ብዙ ከብት፣ ብዙ አገልጋ
ዮችም ስለ ነበሩት፣ ፍልስጥኤማውያን ተመ
ቀኙት:: 15ከዚህ የተነሣ ፍልስጥኤማውያን፣
አባቱ አብርሃም በሕይወት በነበረበት ጊዜ፣
የአብርሃም አገልጋዮች የቈፈሩአቸውን የውሃ
ጕድጓዶች በሙሉ ዐፈር ሞልተው ደፈኑ
ዋቸው::
16አቢሜሌክም ይስሐቅን፣ "ከእኛ ይልቅ
ኀያል ሆነሃልና አገራችንን ልቀቅልን" አለው::
17ይስሐቅም ያን ቦታ ትቶ ሄደ፤ በጌራራ
ሸለቆም ተቀመጠ:: 18ይስሐቅም በአባቱ በአ
ብርሃም ጊዜ ተቈፍረው የነበሩትን፣ አባቱ
ከሞተ በኋላ ፍልስጥኤማውያን የደፈኑአቸ
ውን የውሃ ጕድጓዶች እንደ ገና እንዲከ
ፈቱ አደረገ፤ አባቱ ቀድሞ ባወጣላቸው
ስምም መልሶ ጠራቸው::
19የይስሐቅ አገልጋዮች በሸለቆው ውስጥ
ሲቈፍሩ፣ ከጕድጓዱ የሚፈልቅ ውሃ አገኙ::
20የጌራራ እረኞች ግን፣ "ውሃው የእኛ
ነው" በማለት ከይስሐቅ እረኞች ጋር ጠብ
አነሡ፤ ከዚህ የተነሣ ይስሐቅ ያን የውሃ ጕድ
ጓድ ኤሴቅ[ሐ] ብሎ ጠራው፤ በጕድጓዱ ምክ
ንያት ተጣልተውታልና:: 21አሁንም እንደ

[ሐ]20 ኤሴቅ ማለት ክርክር ማለት ነው

25፥34 ቍ30
26፥1 ዘፍ10፥14፤ 12፥10፤20፥1፤ዘዳ32፥24፤መሳ10፥6
26፥2 ዘፍ12፥1:7፤ 46፥3
26፥3 ቍ12፤ዘፍ 12፥2:7፤17፥19፤20፥1፤21፥20፤27፥45፤31፥3:5፤32፥9፤35፥3፤48፥21፤ዘፀ3፥12፤33፥14-16፤ዘኍ23፥21፤ዘዳ31፥23፤ኢሱ1፥5፤ኢሳ43፥2፤ኤር1፥8:19፤ሐጌ1፥13፤ሐሥ7፥5
26፥4 ቍ24፤ ዘፍ12፥2:3:7፤48፥4፤ዘኍ10፥36፤ሐሥ 3፥25፤ገላ3፥8
26፥5 ዘፍ18፥19፤ ዘሌ18፥4:5:26፤19፥19:37፤20፥8:22፤25፥18፤26፥3፤ዘኍ15፥40፤ዘዳ4፥40፤6፥2፤11፥1፤1ነገ2፥3፤መዝ119፥80:112፤ሕዝ18፥21
26፥6 ዘፍ20፥1
26፥7 ዘፍ12፥13
26፥8 ዘፍ10፥14
26፥9 ዘፍ12፥19
26፥10 ዘፍ12፥18
26፥11 ዘፍ20፥3፤ 1ሳሙ24፥6፤26፥9፤ መዝ105፥15
26፥12 ቍ3፤ማቴ 13፥8
26፥13 ዘፍ13፥2፤ ዘዳ8፥18
26፥14 ዘፍ12፥16፤ 24፥36፤32፥23፤ 37፥11
26፥15 ዘፍ21፥25:30
26፥16 ቍ27፤ዘፀ 1፥9፤መሳ11፥7፤መዝ 105፥24-25
26፥17 ዘፍ20፥1
26፥18 ዘፍ21፥30
26፥20 ዘፍ13፥7፤ 21፥25

ለም ባልሆነ ዐፈር ላይ እንኳ በደንብ በቅሉ ያድጋል፤ ከጥንት ጀምሮም በመካከለኛው ምሥራቅ ምግብ በመሆን አገልግሉአል (2ሳሙ 17፥28፤ 23፥11፤ ዕብ 4፥9 ይመ):: *ዔሳው ብኵርናውን እንዲህ አድርጎ አቃለላት፤* በእያንዳንዱ ብኵርና ውስጥ ይስሐቅ ከአብርሃም የወረሰው ቃል ኪዳን ስላለ፣ ዔሳው ይህን በማድረጉ ምን ያህል ነውረኛ ሰው እንደ ሆነ ተገንዝቦአል (ዕብ 12፥16)::

*26፥1-33፤* በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉት አንዳንድ ታሪኮች፣ (ለምሳሌ ቍ 1-11) ዔሳውና ያዕቆብ ከመወለዳቸው በፊት የተፈጸሙ ድርጊቶች ናቸው:: ቍ 1-11 በዚህ ቦታ የገባው፣ ያዕቆብ ከአባቱ ጋር ታግሎ ለማግኘት የሞከረው ብኵርናና በረከት (25፥22:31-33፤ 27፥5-29 ይመ)፣ ይስሐቅ ከአብርሃም የተቀበለውንም ቃል ኪዳን የሚጨምር መሆኑን በግልጽ ለማሳየት ነው::

26፥1 *ቀድሞ በአብርሃም ዘመን ከደረሰው ራብ፤* 12፥10 ይመ:: *አቢሜሌክ፤* ቀደም ሲል በዚሁ ስም ይጠራ የነበረውን ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ሳይሆን አይቀርም (20፥2 ይመ):: *የፍልስጥኤም፤* የ10፥4 ማብ ይመ:: *ጌራራ፤* 20፥1 ማብ ይመ::

26፥2 *ተገልጦ፤* የ12፥7 ማብ ይመ::

26፥3 *እኔም ካንተ ጋር እሆናለሁ፤* እግዚአብሔር የሕዝቡ ጠባቂና ታዳጊ እንደሚሆን የተነገረው የተስፋ ቃል በተደጋጋሚ ተጠቅሶአል (ቍ 24፤ 28፥15፤ 31፥3፤ ኢሱ 1-5፤ ኢሳ 41፥10፤ ኤር 1፥8:19፤ ማቴ 28፥20፤ ሐሥ 18፥10፤ እንዲሁም ዘፍ 17፥7 እና ማብ ይመ):: *ለአባትህ ለአብርሃም በመሐላ የገባሁለትን ቃል፤* 22፥16-18 ይመ::

26፥4 *ዘርህን እንደ ሰማይ ከዋክብት፤* 13፥16፤15፥5 እና ማብ ይመ:: በዘርህም በኩል የምድር ሕዝቦች ሁሉ ይባረካሉ፤ የ12፥2-3 ማብ ይመ::

26፥5 *አብርሃም ቃሌን ሰምቶ፤* የ17፥9 ማብ ይመ:: *ትእዛዜን፣ ሥርዐቴንና ሕጌን፤* የእግዚአብሔር ሕዝብ መጠበቅ ያለበትን (ዘሌ 26፥14-15:46፤ ዘዳ 11፥1 ይመ) የተለያዩ መለኮታዊ ሕጎች የሚገልጹ ቃላት ናቸው:: የዘፍጥረት መጽሐፍ ጸሓፊ በሲና ተራራ ላይ ከተደረገው ቃል ኪዳን በኋላ፣ ከቃል ኪዳኑ ጋር በቀጥታ የሚዛመዱ ቃላትን ለሕዝበ እስራኤል ተናግሮአል:: ይሁን እንጂ አባታቸው አብርሃም በዘመኑ ለእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ታዘዘ ሁሉ፣ ሕዝቡም በቃል ኪዳኑ የተሰጣቸውን ተስፋ ለመቀበል የአባታቸውን አርአያ መከተል እንዳለባቸው በአጽንዖት ተናግሮአል::

26፥7 *ቈንጆ ስለ ሆነች፤* 12፥11:14 ይመ::

26፥8 *ሲዳራት፤* በዚህ ቦታ የገባው የዕብራይስጡ ቃል በ17፥17፤ 18፥12-13:15፤ 21:6 ላይ "ሣቀ" ከሚለው ግሥ ጋር የሚዛመድ ነው:: በይስሐቅ ስም ላይ የተሠራ የኅብር ቅኔ ነው::

26፥16 *ከእኛ ይልቅ ኀያል ሆነሃልና፤* በቃል ኪዳኑ ላይ የተጠቀሱት ተስፋዎች መፈጸማቸውን የሚያመለክት ነው:: ገና በእስራኤል አባቶች ዘመን የእግዚአብሔር ሕዝብ በዚያ ምድር ላይ መስፈር፣ በአገሩ ነዋሪዎች ዘንድ ሥጋት ፈጥሮ ነበር:: የዓለም ሕዝቦች ክፉ መንገዳቸውን በሚከተሉበት ምድር፣ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በዚያ መገኘት ጠላትነትን አነሣሣ:: ከብዙ መቶ ዓመት በኋላ፣ ከግብፅ ፈርዖኖች አንዱ ተመሳሳይ ተቃውሞ አቅርቦ ነበር (ዘፀ 1፥9)::

26፥20 *ውሃው የእኛ ነው፤* ይህን በመሰለ ምድረ በዳ፣ በውሃ ጕድጓዶችና በግጦሽ መሬት ባለቤትነት ላይ መጣላት የተለመደ ነበር (6፥11፤ 21፥25፤ 36፥7 ይመ)::

ገና ሌላ የውሃ ጉድጓድ ቈፈሩ፤ አሁንም
ሌላ ግጭት ተፈጠረ፤ ስለዚህ የውሃ ጉድ
ጓዱን ስጥና[ፕ] ብሎ ጠራው:: [22]ይስሐቅም ያን
ቦታ ትቶ ሌላ ስፍራ ላይ የውሃ ጉድጓድ
አስቈፈረ፤ በዚህ ጊዜ ግን አንድም ሰው ጠብ
አላነሣበትም፤ ስለዚህ ያን የውሃ ጉድጓድ፣
"አሁን *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሰፊ ቦታ ሰጥቶ
ናል፤ እኛም በምድር ላይ እንበዛለን" ሲል
ርኆቦት[ሀ] ብሎ ጠራው::
[23]ከዚያም ይስሐቅ ወደ ቤርሳቤህ ወጣ::
[24]በዚያም ሌሊት *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ተገለጠለ
ትና፣ "እኔ የአባትህ የአብርሃም *አምላክ* (ኤሎሂም)
ነኝ፤ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ እባርክሃ
ለሁ፤ ስለ አገልጋዬም ስለ አብርሃም ስል
ዘርህን አበዛለሁ" አለው::
[25]ይስሐቅም በዚያ ስፍራ መሠዊያ ሠርቶ፣
*የእግዚአብሔርን* (ያህዌ) ስም ጠራ፤ ድንኳንም
ተከለ፤ አገልጋዮቹም በዚያ የውሃ ጉድጓድ
ቈፈሩ::
[26]አቢሜሌክም ከአማካሪው ከአዘኮትና ከሰ
ራዊቱ አዛዥ ከፊኮል ጋር ከጌራራ ተነሥቶ
ይስሐቅ ወዳለበት ስፍራ መጣ:: [27]ይስሐቅም፣
"ጠልታችሁኝ ካባረራችሁኝ በኋላ፣ አሁን
ደግሞ ለምን መጣችሁ?" ብሎ ጠየቃቸው::
[28]እነርሱም እንዲህ አሉ፤ "*እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ከአንተ ጋር መሆኑን በግልጽ ተረድ
ተናል፤ ስለዚህም፣ 'በመሐላ የጸና ውል በመ
ካከላችን መኖር አለበት' አልን፤ ይህም በእ
ኛና በአንተ መካከል የሚጸና ውል ነው፤
አሁንም ከአንተ ጋር ስምምነት እናድርግ፤
[29]አንተን እንዳልጐዳንህ፣ ነገር ግን በጎነትን
እንዳሳየንህና በሰላም እንደ ሸኘንህ ሁሉ፣
አንተም ክፉ እንዳታደርግብን በመካከላችን
ውል ይደረግ፤ አንተን እንደሆን መቼም
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ባርኮሃል::"
[30]ይስሐቅም ድግስ ደገሰ፣ አበላቸው፤
አጠጣቸው:: [31]በማግስቱም በማለዳ ተነሥ
ተው፣ በመካከላቸው መሐላ ፈጸሙ:: ይስሐቅም
አሰናበታቸው፤ እነርሱም በሰላም ሄዱ::
[32]በዚያኑ ዕለት፣ የይስሐቅ አገልጋዮች
መጥተው ስለ ቈፈሩት የውሃ ጉድጓድ ነገሩት፤
"ውሃ አኮ አገኘን!" አሉት:: [33]እርሱም የው
ሃውን ጉድጓድ ሳቤህ[^] አለው፤ ከዚያም የተ
ነሣ የከተማዪቱ ስም እስከ ዛሬ ድረስ ቤር
ሳቤህ ተብሎ ይጠራል::
[34]ዔሳው አርባ ዓመት በሆነው ጊዜ፣ የኬ
ጢያዊውን የብኤሪን ልጅ ዮዲትን እንዲ
ሁም የኬጢያዊውን የኤሎንን ልጅ ቤሴሞ
ትን አገባ፤ [35]በእነዚህም ሴቶች ምክንያት
የይስሐቅና የርብቃ ልብ ያዝን ነበር::

**ይስሐቅ ያዕቆብን ባረከው**

**27** ይስሐቅ አርጅቶ፣ ዐይኖቹ ደክመው
ማየት በተሳናቸው ጊዜ፣ ታላቁን
ልጁን ዔሳውን ጠርቶ፣ "ልጄ ሆይ" አለው::
እርሱም፣ "እነሆ፤ አለሁ" አለ::
[2]ይስሐቅም እንዲህ አለ፤ "ይኸው እኔ አር
ጅቻለሁ፤ የምሞትበትንም ቀን ዐላውቅም
[3]ስለዚህ የአደን መሣሪያህን:- የፍላጻ ኰሮጆ
ህንና ቀስትህን ይዘህ ወደ ዱር ሂድ፤ አድ
ነህም አምጣልኝ:: [4]ከመሞቴ በፊት እንድ
መርቅህ የምወደውን ዐይነት ጣዕም ያለው
ምግብ አዘጋጅተህ አብላኝ::"
[5]ይስሐቅ ለልጁ የተናገረውን ርብቃ ትሰማ
ስለ ነበር፣ ዔሳው የታዘዘውን ለማምጣት
ለዐደን እንደ ወጣ፣ [6]ርብቃ ለልጇ ለያዕ
ቆብ እንዲህ አለችው፤ "አባትህ ዔሳውን፣
[7]'ከመሞቴ በፊት *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት
እንድመርቅህ፣ ጥሩ ጣዕም ያለው ምግብ እን
ድበላ አዘጋጅልኝ::' ሲለው ሰምቻለሁ፤ [8]ልጄ
ሆይ፤ እንግዲህ የምነግርህን በጥሞና ስማኝ፤

26፥21 ዘፍ13፥7
26፥22 ዘፍ17፥6፤ 36፥37፤ መዝ18፥19፤ ኢሳ33፥20፤54፥2፤ አሞ9፥11
26፥23 ዘፍ22፥19
26፥24 ቍ4፤ዘፍ 15፥1፤17፥7፤21፥20፤ 22፥17፤24፥12፤28፥ 14፤30፥27፤39፥5፤ ዘጸ13፥17፤ኢሱ8፥1
26፥25 ዘፍ4፥26፤ 8፥20፤21፥30፤ሐሥ 2፥21
26፥26 ዘፍ21፥22
26፥27 ቍ16
26፥28 ዘፍ21፥22: 27፤ኢሱ9፥6
26፥29 ዘፍ24፥31፤ 31፥29:52
26፥30 ዘፍ31፥54፤ ዘፀ18፥12፤24፥11፤ 1ሳሙ20፥27
26፥31 ዘፍ21፥23:27
26፥32 ዘፍ21፥30
26፥33 ዘፍ21፥14
26፥34 ዘፍ10፥15፤ 25፥20፤28፥9፤36፥2፤ ኢሱ3፥10፤1ሳሙ26፥ 6፤1ነገ10፥20
26፥35 ዘፍ27፥46፤ 28፥8፤ኢዮ7፥16

27፥1 ዘፍ25፥25፤ 48፥10፤ዘጸ34፥7፤ 1ሳሙ3፥2
27፥2 ዘፍ47፥29፤ 1ነገ2፥1
27፥3 ዘፍ25፥27
27፥4 ቍ7:10:25: 31፤ዘፍ24፥60፤25፥ 28፤49፥28፤ዘጸ33፥ 1፤ዕብ11፥20
27፥5 ዘፍ25፥27
27፥6 ዘፍ25፥28
27፥7 ቍ4
27፥8 ቍ13:43

[ፕ]21 *ስጥና ማለት ተቃውሞ* ማለት ነው
[ሀ]22 *ርኆቦት ማለት ክፍል (የቤት) ማለት ነው*
[^]33 *ሳቤህ ማለት መሐላ ወይም ሰባት ማለት ሊሆን ይችላል*

26፥25 ***መሠዊያ ሠርቶ፤*** የ12፥7 ማብ ይመ:: ***የእግዚአብሔርን ስም ጠራ፤*** 4፥26 እና ማብ ይመ::

26፥26 ***ፊኮል፤*** የ21፥22 ማብ ይመ::

26፥30 ***ድግስ ደገሰ፤*** ቃል ኪዳን የተጋቡ ሁለት ወገኖች፣ ቃል ኪዳናቸውን የሚያስሩት አብረው ምግብ በመመገብ ነው፤ ይህም በመካከላቸው ያለውን ወዳጅነት ይገልጻል (31፥54፤ ዘፀ 24፥11 ይመ)::

26፥33 ***የከተማዪቱ ስም ... ቤርሳቤህ ተብሎ ይጠራል፤*** የ21፥31 ማብ ይመ::

26፥34 ***ዔሳው አርባ ዓመት በሆነው ጊዜ ... አገባ፤*** አባቱ ይስሐቅ ያገባው በዚህ ዕድሜው ነበር፤ እርሱም በዚሁ ዕድሜ አገባ (25፥20 ይመ):: በኋለኞቹ ዘመናት፣ አርባ ዓመት በአማካይ የአንድ ትውልድ ዕድሜ ነበር (ዘኍ 32፥13 ይመ):: ***ዮዲትን... ቤሴሞትን፤*** ዔሳው ከእነዚህ ሁለት ሚስቶቹ በተጨማሪ "የእስማኤል ልጅና የነባዮት እኅት" የሆነችውን ማዕሌትን አግብቶአል (28፥9):: በም 36 ላይ የተጠቀሰው የዔሳው የትውልድ ሐረግ ከእነዚህ ሚስቶች ሌላ በተጨማሪ ሦስት ሚስቶችን ይጠቅሳል፤ እነዚህ ሚስቶች የሚታወቁት ግን "የኬጢያዊው የዔሎን ልጅ ዓዳን"፣ የኤዋያዊው የፅብዖን ልጅ ዓና "እና" የነባዮት እኅት የእስማኤል ልጅ ቤሴሞት ተብለው ነው (36፥2-3):: ይህ የስም ዝርዝር በቅጂ ጊዜ ሳይምታታ አልቀረም፤ ወይም በዚህ ቦታ የተጠቀሱት ስሞች አማራጭ ወይም የቍልምጫ ስሞች ሊሆኑ ይችላሉ:: ምናልባትም ዔሳው ከሦስት ሚስቶች በላይ አግብቶ ይሆናል::

26፥35 ***የይስሐቅና የርብቃ ልብ ያዝን ነበር፤*** ይስሐቅና ርብቃ፣ ያዕቆብ የኬጢያውያንን ወይም የከነዓናውያንን ሴቶች እንዳያገባና እነርሱ የፈጸሙትን ስሕተት እርሱም እንዳይደግም ለማድረግ ቍርጥ ውሳኔ አድርገው ነበር (27፥46-28፥2 ይመ)::

27፥1 ***ዐይኖቹ ደክመውና ማየት በተሳናቸው ጊዜ፤*** በጥንት ዘመን ዕድሚያቸው በገፉ ሰዎች ላይ የዐይን መታወር ወይም የመታወር ምልክት ማየት የተለመደ ነበር (48፥10፤ 1ሳሙ 4፥15 ይመ):: ***"ልጄ ሆይ" አለው፤*** የ22፥1 ማብ ይመ::

27፥2 ***ይኸው እኔ አርጅቻለሁ፤*** በዚህ ወቅት የይስሐቅ ዕድሜ 137 ዓመት ነበር፤ ከዚያ በኋላ ለ43 ተጨማሪ ዓመታት ኖሮአል (ከ35፥28 ጋር ያነጻጽሩ)::

27፥4 ***የምወደውን ዐይነት ጣዕም ያለው ምግብ፤*** ርብቃና ያዕቆብ ይስሐቅ የሚወደውን ዐይነት ምግብ በማዘጋጀት የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት ሞከሩ:: ***ከመሞቴ በፊት እንድመርቅህ፤*** በጥንት ቅርብ ምሥራቃውያን ሕግ መሠረት፣ የኑዛዜ ቃልን ጨምሮ (49፥28-33 ይመ) አንድ ሰው የሚናገራቸው የምርቃት ወይም የቡራኬ ቃላት ሁሉ ሕጋዊነት አላቸው:: ***እንድመርቅህ፤*** የቍ 36 ማብ ይመ::

27፥5 ***ትሰማ ስለ ነበር፤*** ተደብቃ በምስጢር ማለት ነው::

27፥5 ***ርብቃ፤*** በዚህ በያዕቆብ ታሪክ ውስጥ ጸሓፊው ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸውን ቃላት ይኸውም "ብኵርና" እና "በረከት" በመጠቀም ሐሳቡን ይገልጻል፤ ርብቃ ደግሞ የያዕቆብን ምኞት እውን ለማድረግ የተቻላትን ሁሉ ታደርግ ነበር:: ***ለልጇ ለያዕቆብ... አለችው፤*** በ25፥28 ላይ የተጠቀሰው አድልዎ ያለበት የወላጅ ፍቅር መርዛም ፍሬውን ሊያፈራ ደርሶአል::

27፥8 ***ልጄ ሆይ... የምልህንም አድርግ፤*** ርብቃም እንደ ያዕ

የምልህንም አድርግ። 9ተሦና ወደ መንጋው
ሄደህ ሁለት ፍርጥም ያሉ የፍየል ጠቦቶች
አምጣልኝ፤ እኔም አባትህ፣ የሚወደውን ዐይ
ነት ምግብ አዘጋጅለታለሁ፤ 10እርሱም ከመ
ሞቱ በፊት እንዲመርቅህ፣ ይዘህለት ግባና
ይብላ።"
11ያዕቆብም እናቱን ርብቃን እንዲህ አላት፤
"ወንድሜ ዔሳው ሰውነቱ ጠጕራም ነው፤
የእኔ ገላ ግን ለስላሳ ነው። 12ታዲያ፣ አባቴ
ቢዳስሰኝ እንዳታለልሁት ያውቃል፤ ይህ ከሆነ
ደግሞ፣ በምርቃት ፈንታ ርግማን አተር
ፋለሁ ማለት ነው።"
13እናቱም፣ "ልጄ ሆይ፤ የአንተ ርግማን
በእኔ ላይ ይድረስ፤ ግድ የለህም፤ እንደ ነገ
ርሁህ ሄደህ ጠቦቶቹን አምጣልኝ" አለችው።
14እርሱም ሄዶ ጠቦቶቹን ለእናቱ አመጣ
ላት፤ እርሷም ልክ አባቱ እንደሚወደው ዐይ
ነት አጣፍጣ ጥሩ ምግብ አዘጋጀችለት።
15ከዚያም ርብቃ በቤት ያስቀመጠችውን የታ
ላቁን ልጇን የዔሳውን ምርጥ ልብስ አን
ሥታ ለታናሹ ልጇ ለያዕቆብ አለበሰችው።
16እንዲሁም የዐንገቱን ለስላሳ ክፍል የጠቦቶ
ቹን ቈዳ አለበሰችው። 17ከዚያም ያሰናዳች
ውን ጣፋጭ መብልና እንጀራ ለያዕቆብ
ሰጠችው።
18ያዕቆብም ወደ አባቱ ሄዶ፣ "አባቴ ሆይ፤
አለ፤ ይስሐቅም፣ "እነሆ፤ አለሁ ልጄ፤ ለመ
ሆኑ አንተ ማን ነህ?" አለው።
19ያዕቆብም አባቱን፣ "እኔ የበኵር ልጅህ
ዔሳው ነኝ፤ ያዘዝኸኝን አድርጌአለሁ፤ እስቲ
ቀና በልና እንድትመርቀኝ አድኜ ካመጣ
ሁት ብላ" አለ።
20ይስሐቅ ልጁን፣ "ልጄ ሆይ፤ ከመቼው
ቀናህና መጣህ?" ሲል ጠየቀው። ያዕቆብም፣
"እግዚአብሔር አምላክህ (ያህዌ ኤሎሂም) አሳካልኝ"
ብሎ መለሰለት።
21ይስሐቅም ያዕቆብን፣ "ልጄ ሆይ፤ አንተ
በእርግጥ ልጄ ዔሳው መሆንህን እንዳውቅ፣
እስቲ ቀረብ በልና ልዳብስህ" አለው።
22ያዕቆብም ወደ አባቱ ወደ ይስሐቅ
ተጠጋ፤ አባቱም በእጁ እየዳሰሰው፣ "ይህ
ድምፅ የያዕቆብ ድምፅ ነው፤ እጆቹ ግን
የዔሳው እጆች ናቸው" አለ። 23እጆቹ እንደ
ወንድሙ እንደ ዔሳው እጆች ጠጕራም ስለ
ሆኑ፣ ይስሐቅ ያዕቆብን ለይቶ ማወቅ አል
ቻለም፤ ስለዚህ ባረከው። 24ይስሐቅም፣ "በእ
ርግጥ አንተ ልጄ ዔሳው ነህ?" ሲል ጠየቀው።

27፥9 ዘፍ25፥28፤ 1ሳሙ16፥20
27፥10 ቍ4
27፥11 ዘፍ25፥25
27፥12 ቍ22፤ዘፍ 9፥25
27፥13 ቍ8፤ማቴ 27፥25
27፥14 ዘፍ25፥28
27፥15 ቍ27፤ዘፍ 25፥25፤ማሕ4፥11
27፥16 ቍ22-23
27፥18 ቍ32
27፥19 ቍ4:32፤ ዘፍ25፥28
27፥20 ዘፍ24፥12
27፥21 ቍ12
27፥22 ቍ12፤ዘፍ 45፥4
27፥23 ቍ16
27፥25 ቍ4
27፥27 ቍ15፤ዘፍ 31፥28:55፤33፥4፤ 48፥10፤ዘፀ4፥27፤ 18፥7፤ሩት1፥9፤ 1ሳሙ20፥41፤2ሳሙ 14፥33፤19፥39፤መዝ 65፥9-13፤ዕብ11፥20
27፥28 ቍ37:39፤ ዘፍ49፥25፤ዘሌ26፥20 ፤ዘኍ18፥12፤ዘዳ7፥ 13፤33፥13:28፤2ሳሙ 1፥21፤2ነገ18፥32፤ ኢዮ18፥16፤29፥19፤ መዝ4፥7፤65፥9፤72፥ 16፤ምሳ3፥20፤ኢሳ 26፥19፤36፥17፤ኤር 31፥12፤40፥10፤ሆሴ 14፥5፤ሐጌ1፥10፤ ዘካ8፥12፤
27፥29 ቍ33፤ዘፍ 9፥25፤12፥3፤25፥23፤ 37፥7፤2ሳሙ8፥14፤ መዝ68፥31፤72፥11፤ ኢሳ19፥21:23፤27፥ 13፤45፥14:23፤49፥7 :23፤60፥12:14፤66፥ 23፤ኤር12፥17፤ዳን 2፥44፤ዘካ14፥17-18
27፥31 ቍ4
27፥32 ቍ18:19
27፥33 ቍ29:35
27፥34 ዘፀ12፥32 ፤ዕብ12፥17
27፥35 ቍ19:45፤ ኤር9፥4፤12፥6

ያዕቆብም፣ "አዎን፤ ነኝ" ብሎ መለሰ።
25ከዚያም፣ "በል እንግዲህ ልጄ፤ እንድ
መርቅህ፣ አድነህ ካመጣኸው አቅርብልኝና
ልብላ" አለው።
ያዕቆብም ምግቡን ለአባቱ አቀረበለት፤
የወይን ጠጅም አመጣለት፤ እርሱም በላ፤ ጠጣም።
26ከዚያም አባቱ ይስሐቅ፣ ያዕቆብን፣ "ልጄ
ሆይ፤ እስቲ ቀረብ በልና ሳመኝ" አለው።
27ያዕቆብም ቀርቦ ሳመው፤ ይስሐቅ የያዕ
ቆብን ልብስ ካሸተተ በኋላ እንዲህ ብሎ
መረቀው፤

"እነሆ፤ የልጄ ጠረን፣
እግዚአብሔር (ያህዌ) እንደ ባረከው፣
እንደ መስክ መዐዛ ነው።
28እግዚአብሔር (ኤሎሂም) የሰማይን ጠል፣
የምድርንም በረከት፣
የተትረፈረፈ እህልና የወይን ጠጅ
ይስጥህ።
29መንግሥታት ይገዙልህ፤
ሕዝቦችም ተደፍተው እጅ ይንሡህ፤
የወንድሞችህ ጌታ ሁን፤
የእናትህም ልጆች ተደፍተው እጅ
ይንሡህ፤
የሚረግሙህ የተረገሙ ይሁኑ፤
የሚባርኩህ የተባረኩ ይሁኑ።"

30ይስሐቅ ያዕቆብን መርቆ እንዳበቃ፣
ያዕቆብ ገና ከአባቱ ዘንድ ሳይወጣ ወዲያ
ውኑ፣ ወንድሙ ዔሳው ከዐደን ተመለሰ።
31እርሱም ደግሞ ጣፋጭ ምግብ በማዘጋጀት
ለአባቱ አቀረበ፣ "አባቴ ሆይ፤ እንድትመ
ርቀኝ፣ እስቲ ቀና በልና ካደንሁት ብላ"
አለው።
32አባቱ ይስሐቅም፣ "አንተ ደግሞ ማን
ነህ?" ሲል ጠየቀው። እርሱም፣ "እኔማ የበ
ኵር ልጅህ ዔሳው ነኝ" አለው።
33በዚህ ጊዜ ይስሐቅ ክፉኛ እየተንቀጠ
ቀጠ፣ "ታዲያ ቀደም ሲል አድኖ ያመጣ
ልኝ ማን ነበር? አንተ ከመምጣትህ በፊት
በልቼ መረቅሁት፤ እርሱም በእርግጥ የተባ
ረከ ይሆናል" አለው።
34ዔሳው የአባቱን ቃል ሲሰማ፣ ድምፁን
ከፍ በማድረግ ምርር ብሎ አለቀሰ፤ አባቱ
ንም፣ "አባቴ ሆይ፤ እኔንም ደግሞ እባክህ
መርቀኝ" አለው።
35ይስሐቅም፣ "ወንድምህ መጥቶ አታሎኝ
ምርቃትህን ወስዶብሃል" አለው።

ቆብ አታላይነቷ በአደባባይ ታየ። ያዕቆብ ማለት አታላይ ማለት ነው።

27፥13 *የአንተ ርግማን በእኔ ላይ ይድረስ፤* በማቴ 27፥25 ላይ ከተጠቀሰው መሐላ ጋር ያነጻጽሩ።

27፥20 *አምላክህ፤* በሌላ ስፍራ ያዕቆብ ከተናገረው ጋር ተመሳሳይ ነው (31፥5:42፤ 32፥9)። ያዕቆብ ከካራን በሰላም እስከ ተመለሰበት ጊዜ ድረስ፤ እግዚአብሔር የእርሱ አምላክ እንደ ሆነ ተናግሮ አያውቅም (ከ28፥20-22፤ 33፥18-20 ጋር ያነጻጽሩ)።

27፥27 *ሳመው፤* የእስራኤል ሕዝብ አባት የሆነው ያዕቆብ፣ በቃል ኪዳኑ ላይ የተሰጠውን በረከት ለማግኘት ሲል አባቱን በመሳም ከዳ።

27፥29 *የወንድሞችህ ጌታ ሁን፤* ይስሐቅ ሳያስተውል ያዕቆብን ባረከው፤ በዚህም እግዚአብሔር ለርብቃ የገባላትን ቃል ፈጸመ (25፥23)።

27፥33 *እርሱም በእርግጥ የተባረከ ይሆናል፤* በጥንቱ ዓለም ከአንደበት የሚወጡ የበረከትና የመርገም ቃላት የተባለው ነገር እንዲደርስ የማድረግ ምትሀታዊ ኀይል አላቸው ተብሎ ይታመን ነበር። ይስሐቅ ግን ወራሽና የእግዚአብሔርም የኪዳኑ በረከት መጋቢ እንደ መሆኑ ሕጋዊ በሆነ ምርቃት፣ (የቍ 4 ማብ ይመ) በረከቱን ለያዕቆብ ማስተላለፍ እንዳለበት ያውቅ ነበር።

27፥34 *ድምፁን ከፍ በማድረግ ምርር ብሎ አለቀሰ፤* የዔሳው በእንባው "መልስ ሊያገኘው አልቻለም" (ዕብ 12፥17)።

36ዔሳውም፣ “ይህ ሰው ያዕቆብ መባሉ
ትክክል አይደለምን? እኔን ሲያታልለኝ ይህ
ሁለተኛ ጊዜው ነው፤ መጀመሪያ ብኵርና
ዬን ወሰደብኝ፤ አሁን ደግሞ ምርቃቴን
ቀማኝ” አለ። ቀጥሎም፣ “ታዲያ ለእኔ ያስ
ቀረኸው ምንም ምርቃት የለም?” ብሎ ጠየቀ።
37ይስሐቅም ለዔሳው፣ “በአንተ ላይ የበ
ላይነት እንዲኖረው፣ ወንድሞቹ ሁሉ አገል
ጋዮቹ እንዲሆኑ፣ እህሉ፣ የወይን ጠጁም
የተትረፈረፈ እንዲሆንለት መርቄዋለሁ።
ታዲያ ልጄ፣ ለአንተ ምን ላደርግልህ እች
ላለሁ?” ሲል መለሰለት።
38ዔሳውም አባቱን፣ “አባቴ ሆይ፤ ምርቃ
ትህ ይህችው ብቻ ናትን? እባክህ አባቴ፣
እኔንም መርቀኝ” አለው፤ ድምፁንም ከፍ
አድርጎ አለቀሰ።
39አባቱ ይስሐቅም እንዲህ ሲል መለሰለት፤

“መኖሪያህ ከምድር በረከት፣
ከላይም ከሰማይ ጠል የራቀ ይሆናል፤
40በሰይፍ ትኖራለህ፤
የወንድምህም አገልጋይ ትሆናለህ።
አምርረህ በተነሣህ ጊዜ ግን፣
ቀንበሩን ከጫንቃህ ላይ፣
ወዲያ ትጥላለህ።”

### ያዕቆብ ወደ ላባ ሸሸ

41አባቱ ያቆብን ስለ መረቀው፣ ዔሳው
በያዕቆብ ላይ ቂም ያዘ፤ በልቡም፣ “ግድ
የለም፤ የአባቴ መሞቻው ተቃርቦአል፤ ከል
ቅሶው በኋላ ወንድሜን ያዕቆብን እገድላለሁ”
ብሎ አሰበ።
42ርብቃ፣ ታላቁ ልጇ ዔሳው ያሰበው በተ
ነገራት ጊዜ ታናሹን ልጇን ያዕቆብን አስጠ
ርታ እንዲህ አለችው፤ “ወንድምህ ዔሳው
ሊገድልህ ጊዜ እየጠበቀ ነው፤ 43አሁንም፣
ልጄ ሆይ፤ እኔ የምልህን አድርግ፤ በካራን
ምድር ወደሚኖረው ወደ ላባ ቶሎ ሸሽ።
44የወንድምህ ቍጣ እስከሚበርድ እዚያው
ቈይ፤ 45ነገር ግን ቍጣው በርዶለት ያደረ
ግህበትን ከረሳ በኋላ፣ እንድትመለስ እልክ
ብህና ትመጣለህ። ሁለታችሁንም በአንድ
ቀን ለምን ልጣ?”
46ከዚያም ርብቃ ይስሐቅን፣ “ዔሳው ባገባ

27፥36 ዘፍ25፥26፡ 33፥29፥25፥31፥20፡ 26፥34፥13፥1ሳሙ 28፥12፥ዕብ12፥16-17
27፥37 ቍ28፥ዘጸ 16፥13፥ዕዝ6፥9፥ኢሳ 16፥10፥ኤር40፥12
27፥38 ዘፍ29፥11፥ ዘኁ14፥1፥መሳ2፥4፥ 21፥2፥ሩት1፥9፥1ሳሙ 11፥4፥30፥4፥ዕብ 12፥17
27፥39 ቍ28፥ዘፍ 36፥6፥ዕብ11፥20
27፥40 ዘፍ9፥25፥ 2ሳሙ8፥14፥2ነገ 8፥20-22
27፥41 ቍ42፥ዘፍ 31፥17፥32፥11፥37፥ 4፥49፥23፥50፥4፡10፡ 15፥ዘኁ20፥29፥ 1ሳሙ17፥28፥ሆሴ 10፥14፥አብ1፥10
27፥42 ቍ41፥ዘፍ 32፥3፡11፥33፥4
27፥43 ቍ8፥ዘፍ 11፥31፥24፥29
27፥44 ዘፍ31፥38፡ 41
27፥45 ቍ35፥ዘፍ 26፥3
27፥46 ዘፍ10፥15- 19፥26፥35፥ኢዮ7፥7
28፥1 ዘፍ24፥3፡60
28፥2 ዘፍ25፥20፥ 21፥21፥24፥29
28፥3 ዘፍ12፥2፥ 17፥1፡6፥48፥16፥ዘኁ 6፥24፥ሩት2፥4፥መዝ 129፥8፥134፥3፥ኤር 31፥23
28፥4 ዘፍ12፥2፡3፥ 15፥7፥17፥8
28፥5 ዘፍ11፥31፥ 24፥29፥25፥20፥ሆሴ 12፥12
28፥6 ቍ1
28፥8 ዘፍ10፥15- 19፥26፥35
28፥9 ዘፍ16፥15፥ 25፥13፥26፥34
28፥10 ዘፍ11፥31፥ 21፥14
28፥11 ቍ18፥ዘፍ 12፥8

ቸው በኬጢያውያን ሴቶች ምክንያት መኖር
አስጠልቶኛል፤ ያዕቆብም ከዚሁ አገር ከኬጢ
ያውያን ሴቶች ሚስት የሚያገባ ከሆነ፣
ሞቴን እመርጣለሁ” አለችው።
28 ይስሐቅ ያዕቆብን አስጠርቶ ከመረ
ቀው* በኋላ፣ እንዲህ ሲል አዘዘው፤
“ምንም ቢሆን ከነዓናዊት ሴት አታግባ።
2አሁኑኑ ተነሥተህ በሰሜን ምዕራብ መስ
ጴጦምያ ወደሚኖረው፣ ወደ እናትህ አባት
ወደ ባቱኤል ቤት ሂድ፤ እዚያም ከአጎትህ
ከላባ ሴቶች ልጆች መካከል አንዲቷን
አግባ። 3ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ**
ይባርክህ፤ ብዙ ሕዝብ እስክትሆን ድረስ
ልጆች አፍራ፤ ዘርህን ያብዛው። 4እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) ለአብርሃም ሰጥቶ የነበረውን አንተም
በስደት የምትኖርበትን ይህችን ምድር ርስት
አድርጎ ያወርስህ ዘንድ፣ ለአብርሃም የሰጠ
ውን በረከት ለአንተና ለዘርህ ይስጥ። 5ይስሐ
ቅም ያዕቆብን በሰሜን ምዕራብ መስጴጦ
ምያ ወደሚኖረው፣ የያዕቆብና የዔሳው እናት
የርብቃ ወንድም ወደ ሆነው ወደ ሶርያዊው
የባቱኤል ልጅ ወደ ላባ ላከው።
6ዔሳው፣ ይስሐቅ ያዕቆብን መርቆ ሚስት
እንዲያገባ ወደ ሰሜን ምዕራብ መስጴጦ
ምያ እንደ ላከውና በባረከውም ጊዜ ከነዓ
ናዊት ሴት እንዳያገባ ትእዛዝ እንደ ሰጠው
ሰማ። ያዕቆብ የአባት የእናቱን ፈቃድ
ለመፈጸም፣ ወደ መስጴጦምያ መሄዱንም
ተረዳ። 8በዚህም የከነዓናውያን ሴቶች በአ
ባቱ በይስሐቅ ዘንድ የቱን ያህል የተጠሉ
መሆናቸውን ተገነዘበ፤ 9ስለዚህም ወደ እስ
ማኤል ሄደ፣ የአብርሃም ልጅ እስማኤል
የወለዳትን፣ የነባዮትን እኅት ማዕሌትን
በሚስቶቹ ላይ ተጨማሪ አድርጎ አገባ።

### ያዕቆብ በቤቴል ያየው ሕልም

10ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ተነሥቶ ወደ ካራን
ሄደ። 11ወደ አንድ ስፍራ እንደ ደረሰም
ፀሓይዋ ጠልቃ ስለ ነበር፣ ዐዳሩን በዚያ
አደረገ፤ በአቅራቢያው ከነበሩትም ድንጋ
ዮች አንዱን ተንተርሶ ተኛ። 12በሕልሙም፣

*1 *ወይም ለላምታ ከሰጠው*
**3 *በዕብራይስጥ ኤልሻዳይ ማለት ነው*

27፥36 *ይህ ሰው ያዕቆብ መባሉ ትክክል አይደለምን?* 25፥26 ይመ። *መጀመሪያ ብኵርናዬን ወሰደብኝ፤ አሁን ደግሞ ምርቃቴን ቀማኝ፤* በዕብራይስጥ “ብኮርና” ማለት “በኮራ” ሲሆን፣ “ምርቃቴን/በረከቴን” ደግሞ “በራካ” ማለት ነው (የቍ 6 ማብ ይመ)። ምንም እንኳ ዔሳው ብኵርናን ከበረከት ለመነጠል/ለመለየት ቢሞክርም፣ ሁለቱም በብኵርና መብት የሚገኙ ውርሶች በመሆናቸው፣ የመጀመሪያው ሁለተኛውን ሊያስከትል ችሎ አል (ዕብ 12፥16-17 ይመ)።

27፥39 *ከሰማይ ጠል የራቀ ይሆናል፤* ከቍ 28 ጋር ያነጻጽሩ። ይስሐቅ ለዔሳው ያደረገው ሁለተኛው ምርቃቱ፣ ለያዕቆብ ያደረገው የመጀመሪያ ምርቃት ተቃራኒ ነው።

*27፥40፤* 25፥23 እና የ25፥22፡26 ማብ ይመ።

27፥43 *እኔ የምልህን አድርግ፤* ቀደም ሲል ከፉ ሐሳብ አቀብላው ነበር (ቍ 8ና13 ይመ)፤ አሁን ግን መልካም ምክር ሰጠችው።

27፥44 *እስከሚበርድ፤* በወንድሙ ላይ የነበረው ጥላቻና ቂም ለሃያ ዓመት ቈይቶአል (ቍ 31፡38፡41 ይመ)።

27፥45 *ሁለታችሁንም፤* ያዕቆብና ይስሐቅ ወይም ያዕቆብና ዔሳው ማለት ሊሆን ይችላል (ከ2ሳሙ 14፥16-17 ጋር ያነጻጽሩ)።

*27፥46፤* የ26፥35 ማብ ይመ።

28፥2 *መስጴጦምያ፤* ጳዳን አራም ተብሎ የሚጠራ ሲሆን፣ ትርጕሙም “የአራም ሜዳ” ማለት ነው፤ የዚህም ሌላ ስሙ “አራም ናሃይም” ይባላል (የ24፥10 ማብ ይመ)። *እዚያም... አንዲቷን አግባ፤* 24፥3-4 ይመ።

28፥3 *ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ፤* የ17፥1 ማብ ይመ።

28፥4 *እግዚአብሔር ለአብርሃም ሰጥቶ የነበረውን፤* ጳውሎስ ይህንን ሐረግ ከክርስቲያን አማኞች ጋር እንዴት እንዳዛመደው በገላ 3፥14 ላይ ይመ።

28፥9 *በሚስቶቹ ላይ ተጨማሪ አድርጎ* 26፥34 እና ማብ ይመ።

28፥11 *ከነበሩትም ድንጋዮች አንዱን... ተንተርሶ፤* በጥንት ዘመን የራስ ትራሶች (ለምሳሌ በግብፅ) የሚሠሩት እንደ

ጫፉ ሰማይ የሚደርስ መሰላል በምድር ላይ
ቆሞ፣ በላዩም የእግዚአብሔር (ኤሎሂም) መላእክት
ሲወጡና ሲወርዱ አየ:: 13እግዚአብሔርም
(ያህዌ) ከጫፉ ላይ[ሠ] ቆሞ እንዲህ አለ፤ "የአ
ባትህ የአብርሃም አምላክ (ኤሎሂም)፣ የይስሐቅ
አምላክ (ኤሎሂም) እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ፤
የተኛህበትን ምድር ለአንተና ለዘርህ እሰጣ
ለሁ:: 14ዘርህ እንደ ምድር አሸዋ ይበዛል፤
በምዕራብና በምሥራቅ፣ በሰሜንና በደቡብ
ትስፋፋለህ፤ የምድርም ሕዝቦች ሁሉ በአን
ተና በዘርህ አማካይነት ይባረካሉ:: 15እኔ
ከአንተ ጋር ነኝ፤ በምትሄድበት ስፍራ ሁሉ
እጠብቅሃለሁ፤ ወደዚችም ምድር እመልስ
ሃለሁ፤ የሰጠሁህን ተስፋ እስከምፈጽምልህ
ድረስ አልተውህም::"

16ያዕቆብም ከእንቅልፉ ሲነቃ፣ "በእውነት
እግዚአብሔር (ያህዌ) በዚህ ስፍራ አለ፤ እኔ
ግን ይህን አላወቅሁም ነበር" አለ:: 17እርሱም
በፍርሀት፣ "ይህ ስፍራ እንዴት የሚያስፈራ
ነው! ይህስ ሌላ ሳይሆን የእግዚአብሔር (ያህዌ)
ቤት መሆን አለበት፤ የሰማይ ደጅ ነው" አለ::
18ያዕቆብም በማግስቱ ማልዶ ተነሣ፣ ተን
ተርሶት ያደረገውን ድንጋይ አንሥቶ እንደ ሐው
ልት አቆመው፤ በዐናቱም ላይ የወይራ ዘይት
አፈሰሰበት:: 19ያንን ቦታ ቤቴል[ረ] ብሎ ሰየ
መው፤ ቀደም ሲል ግን የከተማዪቱ ስም
ሎዛ ነበር::

20ከዚያም ያዕቆብ እንዲህ ሲል ተሳለ፤
"እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከእኔ ጋር ቢሆን በምሄ
ድበትም መንገድ ቢጠብቀኝ፣ የምበላው
ምግብ፣ የምለብሰውን ልብስ ቢሰጠኝ 21ወደ
አባቴ ቤት በደኅና ቢመልሰኝ፣ እግዚአብሔር
አምላኬ (ያህዌ ኤሎሂም) ይሆናል፤ 22ይህ ሐውልት
አድርጌ ያቆምሁት ድንጋይ፣ የእግዚአብሔር
(ኤሎሂም) ቤት ይሆናል፤ ከምትሰጠኝም ሀብት
ሁሉ፣ ከዐሥር እጅ አንዱን ለአንተ እሰጣ
ለሁ::"

28፥12 ዘፍ20፥3፤ 37፥19፤ዮሐ1፥51
28፥13 ዘፍ12፥7፤ 24፥12፤35፥7፡9፤46፥ 4፤48፥3፡16፡21፤49፥ 25፤50፥17
28፥14 ዘፍ12፥2፡ 3፤13፥14፤26፥4፡24፤ ሐሥ3፥25፤ገላ3፥8
28፥15 ቍ20፡21፡ 22፤ዘፍ15፥16፤21፥ 20፤30፥25፤31፥30፤ 35፥10፤ዘሌ26፥42፤ ዘዳ 31፥6፡8፤ኢሱ 1፥5፤ነህ4፥14፤መዝ 9፥10፤105፥10፤121፥ 5፡7-8
28፥16 1ነገ3፥15፤ ኤር31፥26
28፥17 ቍ22፤ዘፍ 32፥2፤ዘፀ3፥5፤19፥21፤ ኢሱ5፥15፤1ዜና22፥1 ፤2ዜና3፥1፤መዝ 68፥24፡35፤
28፥18 ቍ11፡22፤ ዘፍ31፥13፡45፡51፤ 35፥14፤ዘፀ24፥4፤ዘሌ 8፥11፤ኢሱ4፥9፤24፥ 26፡27፤ኢሳ19፥19
28፥19 ዘፍ12፥8፤ 35፥6፤ 48፥3፤መሳ 1፥23፡26፤ኢሱ16፥2፤ 18፥13
28፥20 ቍ15፤ዘፍ 31፥13፤ዘሌ7፥16፤22፥ 18፤23፥38፤27፥2፡9፤ ዘኍ6፥2፤15፥3፤ዘዳ 12፥6፤መሳ11፥30፤ 1ሳሙ1፥21፤2ሳሙ 15፥8፤1ጢሞ6፥8
28፥21 ቍ15፤መሳ 11፥31፤ዘፀ15፥2፤ዘዳ 26፥17፤ኢሱ24፥18፤ መዝ48፥14፤118፥28
28፥22 ቍ17፡18፤ ዘፍ14፥20፤ዘኍ18፥ 21፤1ሳሙ7፥12፤ሉቃ 18፥12
29፥1 ዘፍ25፥6
29፥2 ቍ3፡8፡10፤ ዘፍ24፥11
29፥9 ዘፀ2፥16

### ያዕቆብ መስጴጦምያ ደረሰ

29 ያዕቆብም ጕዞውን ቀጠለ፤ የምሥራ
ቅም ሰዎች ወደሚኖሩበት ምድር
ደረሰ:: 2እዚያም በአንድ ሜዳ ላይ ሦስት
የበግ መንጋዎች ተኝተው በነበሩበት አጠ
ገብ የውሃ ጕድጓድ አየ:: የበግ መንጋዎቹ
የሚጠጡት ከዚሁ ጕድጓድ ሲሆን፣ የጕድ
ጓዱም አፍ ትልቅ የድንጋይ መክደኛ ነበ
ረው:: 3መንጎቹ ሁሉ በጕድጓዱ አጠገብ
በሚሰበሰቡበት ጊዜ፣ እረኞች ድንጋዩን ያን
ከባልሉና በጎቹን ውሃ ያጠጣሉ፤ ከዚያም
ድንጋዩን በቦታው መልሰው የጕድጓዱን
አፍ ይገጥሙታል::

4ያዕቆብም እረኞቹን፣ "ወንድሞቼ፤ ከየት
ነው የመጣችሁት?" ብሎ ጠየቃቸው::

እነርሱም፣ "ከካራን ነን" አሉት::

5እርሱም፣ "የናኮርን የልጅ ልጅ ላባን
ታውቁታላችሁ?" አላቸው::

እነርሱም፣ "አዎን እናውቀዋለን" አሉት::

6ያዕቆብም፣ "ለመሆኑ ደኅና ነው?" አላቸው::

እነርሱም፣ "አዎን ደኅና ነው፤ ልጁም
ራሔል እነሆ፤ በጎች እየነዳች በመምጣት
ላይ ነች" አሉት::

7ያዕቆብም፣ "እንደምታዩት ጊዜው ገና ነው፤
መንጎቹ የሚገቡበት ሰዓት አይደለም፤ ታዲያ፣
ለምን በጎቹን አጠጥታችሁ ወደ ግጦሽ አት
መልሷቸውም?" አላቸው::

8እነርሱም፣ "መንጎቹ ሁሉ ተሰብስበው
ድንጋዩ ከጕድጓዱ አፍ ካልተንከባለለ በስ
ተቀር አንችልም፤ ከዚያም በጎቹን እናጠጣ
ቸዋለን" አሉ::

29፥3 ቍ2፡8 29፥4 ዘፍ11፥31፤42፥7፤መሳ19፥17 29፥5 ዘፍ 11፥29 29፥6 ዘፍ30፥22-24፤35፥16፤46፥19፡22፤ዘፀ2፥16 29፥8 ቍ2፤ዘፍ24፥13

ሠ13 ወይም *በዚህ በአጠገቡ*

ረ19 *ቤቴል ማለት የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው*

ብረትና እንደ ዕንጨት ከመሳሰሉት ጠንካራ ነገሮች ስለ ነበር ምቹ አልነበሩም:: ሰዎች ይተኙ የነበረውም በመሬት ላይ ነበር::

28፥12 *መሰላል፤* መወጣጫ ያለው አሁን የምናውቀው ዐይነት መሰላል ሳይሆን በጥንት መስጴጦምያ የሚገኙ ዚጉራት ያላቸውን ዐይነት ደረጃ ነው (የ11፥4 ማብ ይመ):: *የእግዚአብሔር መላእክት ሲወጡና ሲወርዱ፤* እግዚአብሔር የያዕቆብ አምላክ መሆኑን የገለጸበት ምልክት ነው:: ኢየሱስ፣ ከደቀ መዛሙርቱ ለአንዱ "ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአብሔር መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ" (ዮሐ 1፥51) አለው:: ኢየሱስ ራሱ በሰማይና በምድር መካከል ያለ ድልድይ ነው (ዮሐ14፥6 ይመ)፤ እንዲሁም "በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛ " (1ጢሞ 2፥5) እርሱ ብቻ ነው::

28፥13 *እግዚአብሔር ከጫፉ ላይ ቆሞ፤* በመስጴጦምያ የሚገኙ ዚጉራት ለአምልኮ የሚወጡ ሰዎች፣ ወደ አማልክታቸው የሚጸልዩበት ትንሽ ክፍል ከጫፉ ላይ አላቸው::

28፥14 *እንደ ምድር አሸዋ፤* የ13፥16 ማብ ይመ:: *የምድርም ሕዝቦች ሁሉ በአንተና በዘርህ አማካይነት ይባረካሉ፤* በ12፥3 ላይ የተነገረው በረከት በዚህም ቦታ ተደግሞአል::

28፥15 *እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፤* የ26፥3 ማብ ይመ:: *አልተውህም፤* በአረማውያን ሃይማኖታዊ ልምምድ ውስጥ አማልክት የአንድ ቀበሌ ወይም ክልል አማልክት በመሆናቸው፣ የሚጠብቁትም ሆነ የሚንከባከቡት በራሳቸው ቀበሌ ወይም ክልል ውስጥ ያሉ አምላኪዎችን ብቻ ነው:: እውነተኛው አምላክ እግዚአብሔር ግን ለያዕቆብ በሚሄድበት ስፍራ ሁሉ ምን ጊዜም ከእርሱ ጋር እንደሚሆን አረጋገጠለት::

28፥17 *የእግዚአብሔር ቤት... የሰማይ ደጅ ነው፤* የያዕቆብ መሰላል ከመስጴጦምያ ዚጉራት ጋር የሚዛመድ መሆኑን የሚያመለክቱ ሐረጎች ናቸው (የ11፥9 ማብ ይመ)::

28፥18 *ሐውልት፤* በጥንት ዘመን ለአምልኮ ወይም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን ኅብረት ለማስታወስ መታሰቢያን ወይም ሐውልትን ማቆም የተለመደ ነው:: *በዐናቱም ላይ የወይራ ዘይት አፈሰሰበት፤* የተቀደሰ እንዲሆን (ዘፀ 30፥25-29 ይመ)::

28፥21 *በደኅና ቢመልሰኝ፤* በ33፥18 ላይ በከፊል ተፈጽሞአል:: *እግዚአብሔር አምላኬ ይሆናል፤* ያዕቆብ ለመጀመሪያ ጊዜ የአብርሃምና የይስሐቅ አምላክ የእርሱም አምላክ መሆኑን በሙሉ ልቡ ተቀበለ (ቍ 13፥27፡20 ይመ):: ይህንንም ሙሉ በሙሉ ያስታወቀው ከካራን በሰላም ከተመለሰ በኋላ ነው (33፥20 እና ማብ ይመ)

28፥22 *ያቆምሁት ድንጋይ፤* የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል፤ ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር በቤቴል መገናኘቱን ዘወትር እንዲያስታውስለት ለማስታወስ ነው:: *ከምትሰጠኝም ሀብት ሁሉ፤* ከዐሥር አንድ ለአንተ እሰጣለሁ፤ እግዚአብሔር የእርሱ አምላክና ንጉሥ መሆኑን ያስታወቀበት መንገድ ነው (የ14፥20 ማብ ይመ)::

29፥1 *የምሥራቅም ሰዎች ወደሚኖሩበት ምድር፤* በካራን አቅራቢያ ያለ ምድር ነው::

29፥5 *የናኮርን የልጅ ልጅ ላባን፤* 24፥15፡29 ይመ:: እዚህ ላይ "የሰው ልጅ" ለሚለው የገባው የዕብራይስጡ ቃል በቀጥታ "ወንድ ልጅ" ማለት ሲሆን፣ ይህም ማንኛውንም ልጅ ያመለክታል::

9ያዕቆብ ከእረኞቹ ጋር በመነጋገር ላይ ሳለ፣
ራሔል፣ እረኛ ነበረችና የአባቷን በጎች
እየነዳች መጣች። 10ያዕቆብ የእናቱን ወን
ድም የላባን ልጅ ራሔልን፣ እንዲሁም የእ
ኅቱን የላባን በጎች ሲያይ፣ ወደ ጕድጓዱ
ሄዶ ድንጋዩን ከጕድጓዱ አፍ አንከባለለ፤
የአጎቱንም በጎች አጠጣ። 11ከዚያም ያዕቆብ
ራሔልን ሳማት፤ ድምፁንም ከፍ አድርጎ
አለቀሰ። 12ያዕቆብም የአባቷ ዘመድና የር
ብቃ ልጅ መሆኑን ለራሔል ነገራት፤ እር
ሷም ሮጣ ሄዳ ይህንኑ ለአባቷ ነገረችው።
13ላባም የእኅቱ ልጅ ያዕቆብ መምጣቱን
እንደ ሰማ፣ ሊቀበለው ፈጥኖ ወጣ። ዐቅፎ
ከሳመውም በኋላ፣ ወደ ቤቱ ይዞት ሄደ።
ያዕቆብም ሁኔታውን ሁሉ ለላባ ነገረው።
14ላባም ያዕቆብን፣ "አንተማ የዐጥንቴ ፍላጭ
የሥጋዬ ቍራጭ ነህ" አለው።

### ያዕቆብ ልያንና ራሔልን አገባ

ያዕቆብ አንድ ወር ሙሉ አብሮት ከተቀ
መጠ በኋላ፣ 15ላባ ያዕቆብን፣ "ዘመዴ በመ
ሆንህ ብቻ በነጻ ልታገለግለን አይገባምና
ደመወዝህ ምንድን ነው?" አለው።
16ላባ ሁለት ሴቶች ልጆች ነበሩት፤ የታ
ላቂቱ ስም ልያ የታናሺቱ ራሔል ነበር።
17ልያ ዐይነ ልም[ሀ] ስትሆን ራሔል ግን ቁመ
ናዋ ያማረ መልኳም የተዋበ ነበር። 18ያዕቆ
ብም ራሔልን ስለ ወደዳት፣ "ታናሺቱ ልጅ
ህን ራሔልን የምትድርልኝ ከሆነ ሰባት ዓመት
አገለግላለሁ" አለው።
19ላባም መልሶ፣ "ለሌላ ሰው ከምድራት
ላንተ ብድራት ይሻላል፤ እዚሁ አብረኸኝ
ተቀመጥ" አለው። 20ያዕቆብም ራሔልን ለማ
ግኘት ሲል ሰባት ዓመት አገለገለ፤ አጥብቆ
ይወዳትም ስለ ነበረ፣ ሰባት ዓመት እንደ
ጥቂት ቀን ሆኖ ታየው።
21ከዚያም ያዕቆብ ላባን፣ "እነሆ፤ የተባባ
ልነው ጊዜ አብቅቶአል፤ ስለዚህ ሚስቴን
አስረክበኝና የባልና የሚስት ወጋችንን እና
ድርስ" አለው።
22ስለዚህ ላባ የአካባቢውን ሰዎች በሙሉ ጠርቶ
ሰርግ አበላ። 23ሲመሽ ግን ላባ ልጁን ልያን
አምጥቶ ለያዕቆብ ሰጠው፤ ያዕቆብም አብ
ሮአት ተኛ። 24ላባም ዘለፋ የተባለች አገ
ልጋዩን ለልጁ ለልያ ደንገጡር እንድትሆን
ሰጣት።
25ሲነጋም እነሆ፤ ልያ ሆና ተገኘች፤ ስለዚ
ህም ያዕቆብ ላባን፣ "ምነው፣ እንዲህ ጕድ
ሠራኸኝ? ያገለገልኹህ ለራሔል ብዬ አልነ
በረምን? ታዲያ ለምን ታታልለኛለህ?" አለው።
26ላባም እንዲህ አለው፤ "በአገራችን ታላቋ
እያለች ታናሿን መዳር የተለመደ አይደ
ለም፤ 27ይህን የጫጕላ ሳምንት ፈጽምና፣
ሌላ ሰባት ዓመት የምታገለግለን ከሆነ፣
ታናሺቱን ደግሞ እንሰጥሃለን።
28ያዕቆብም በነገሩ ተስማማ፤ ከልያ ጋር
ተሞሽሮ ሰባት ቀን ከቈየ በኋላ፤ ላባ ልጁን
ራሔልን ለያዕቆብ ዳረለት፤ 29ባላ የተባለች
አገልጋዩንም ደንገጡር እንድትሆናት ለራሔል
ሰጣት። 30ያዕቆብ ከራሔልም ጋር ተኛ፤
ራሔልን ከልያ አብልጦ ወደዳት፤ ከዚያም
የተነሣ ሌላ ሰባት ዓመት ላባን አገለገለው።
31እግዚአብሔር (ያህዌ) ልያ እንዳልተወደ
ደች ባየ ጊዜ ማሕፀኗን ከፈተላት፤ ራሔል
ግን መካን ነበረች። 32ልያ ፀነሰች፤ ወንድ
ልጅም ወለደች፤ "እግዚአብሔር (ያህዌ) መከ
ራዬን ስለ ተመለከተልኝ፣ ከእንግዲህ ባሌ
ይወደኛል" ስትል ስሙን ሮቤል[ለ] አለችው።
33እንደ ገናም ፀንሳ ወለደች፤ እርሷም "እግ
ዚአብሔር (ያህዌ) እንዳልተወደድኩ ሰምቶ
ይህን ልጅ በድጋሚ ሰጠኝ' አለች። ከዚያም
የተነሣ ስምዖን[+] ብላ ጠራችው።
34አሁንም እንደ ገና ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች፤
እርሷም፣ ሦስት ወንዶች ልጆች ስለ ወለድሁለት

29፥10 ቍ2:3:16፤ ዘፍ24፥11፤ዘፀ2፥17
29፥11 ቍ13፤ዘፍ 33፥4፤42፥24፤43፥30፤45፥2:14-15፤46፥29፤50፥1:17፤ሩት1፥9
29፥12 ቍ15፤ዘፍ 24፥28-29
29፥13 ዘፍ24፥29፤ 33፥4፤45፥14-15፤ 48፥10፤ዘፀ4፥27፤18፥7፤ሉቃ15፥20
29፥14 ዘፍ2፥23፤ 37፥27፤መሳ9፥2፤2ሳሙ5፥1፤19፥12-13፤20፥1፤ነህ5፥5፤ኢሳ58፥7
29፥15 ቍ12፤ዘፍ 30፥28:32፤31፥7:41
29፥16 ቍ9-10:17:23:28:30፤ዘፍ 30፥9፤35፥23፤47፥30፤49፥31፤ሩት4፥11
29፥17 ቍ16፤ዘፍ 12፥11
29፥18 ቍ20:27:30፤ዘፍ24፥67፤30፥26፤ሆሴ12፥12
29፥20 ቍ18፤ዘፍ 31፥15፤ማሕ8፥7፤ ሆሴ12፥12
29፥21 መሳ15፥1
29፥22 መሳ14፥10፤ ኢሳ25፥6፤ዮሐ2፥1-2
29፥23 ቍ16
29፥24 ዘፍ16፥1፤ 30፥9
29፥25 ዘፍ12፥18፤ 27፥36
29፥26 መሳ15፥2፤ 1ሳሙ14፥49፤18፥17:20፤2ሳሙ6፥23
29፥27 ቍ18፤ዘፍ 31፥41፤መሳ14፥12
29፥28 ቍ16፤ዘፍ 4፥19
29፥29 ዘፍ16፥1፤ 30፥3፤35፥22፤49፥4፤ ዘዳ22፥30፤1ዜና5፥1
29፥30 ቍ16:20
29፥31 ቍ33፤ዘፍ 11፥30፤16፥2፤ዘዳ 21፥15-17፤ሩት 4፥13፤1ሳሙ1፥19፤ መዝ127፥3
29፥34 ዘፍ30፥20፤34፥25፤46፥11፤49፥

29፥32 ዘፍ16፥11፤30፥23፤ዘፍ37፥21፤46፥8፤48፥5:14፤49፥3፤ዘፀ6፥14፤ዘኍ1፥5:20፤26፥5፤ዘዳ33፥6፤ኢሱ4፥12፤ሩት4፥13፤1ሳሙ1፥20፤1ዜና5፥1:3 29፥33 ቍ31፤ዘፍ34፥25፤46፥10፤48፥5፤49፥5፤ዘፀ6፥15፤ዘኍ1፥6:22፤34፥20፤1ዜና4፥24፤ሕዝ48፥24

[ሀ]17 ወይም *አደጋ የማይችል ዐይን*
[ለ]32 *ሮቤል* የሚለው ቃል *ሥቃዬን ተመልክቶ* የሚል ትርጕም ካለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ ድምፅ አለው፤ የስሙ ትርጕም ግን *ማየት፣ ልጅ* ማለት ነው።
[+]33 *ስምዖን* ማለት *የሚሰማ* ማለት ሊሆን ይችላል።

29፥9 *እረኛ፤* በመካከለኛው ምሥራቅ በጎችንና ፍየሎችን መጠበቅ የወንዶችም የሴቶችም ኀላፊነት ነው።

29፥10 ድንጋዩን ... አንከባለለ፤ አንድ ሰው እንዲህ ያለውን ድንጋይ ያንከባልላል ብሎ መገመት በጣም ያስቸግራል፤ ምክንያቱም ድንጋዩ በጣም ትልቅ ነው (ቍ 2 ይመ)።

29፥11 *ድምፁንም ከፍ አድርጎ አለቀሰ፤* ለቅሶው የደስታ ነው።

29፥14 *የዐጥንቴ ፍላጭ የሥጋዬ ቍራጭ፤* በዚህ ቦታ የገባው የዕብራይስጡ ሐረግ በቁሙ፣ "ዐጥንትና ሥጋ" ማለት ሲሆን፣ ይህም የሥጋ ዝምድናን ያመለክታል (2፥23 ይመ)።

29፥16 *ልያ... ራሔል፤* የስማቸው ትርጕም በቅደም ተከተል "ላም" እና "ሴት በግ" ማለት ሲሆን፣ እንዲህ ዐይነቱ የስም አወጣጥ በከብት አርቢዎች ዘንድ የተለመደ ነበር።

29፥22 *ሰርግ አበላ፤* በዚያን ዘመን የሰርግ ግብዣ ሰባት ቀን ሙሉ ይበላ ነበር (ቍ 27-28፤ መሳ 14፥10:12 ይመ)።

29፥23 *ሲመሽ ግን... ያዕቆብም አብሮአት ተኛ፤* ጨለማው ምናልባትም በፊቱ ላይ የተደረገው መሸፈኛ የልያን ማንነት እንዳያውቅ አድርጎታል (24፥65 ይመ)።

*29፥24* ቍ 29 ይመ፤ በጥንቱ ባቢሎናውያን የጋብቻ ውል ላይ የጋብቻን ልማዶች በሚገባ መጻፍ የተለመደ ነበር።

29፥25 *ታታልለኛለህ?፤* የስሙ ትርጕምና ባሕርይ አታላይ (27፥36 ይመ) የሆነው ያዕቆብ እርሱ ራሱ ተታለለ። በብኵርና የሚገኘውን በረከት ለማግኘት የተቻለውን ሁሉ ሲያደርግ የነበረው ያዕቆብ፣ አሁን እርሱም ያለ ፍላጐቱ በኵር የሆነች ሴት ተሰጠው (ቍ 16፥26)።

29፥28 *ላባ ልጁን ራሔልን ለያዕቆብ ዳረለት፤* ይህም የሆነው ያዕቆብ ሌላ ሰባት ዓመት ከማገልገሉ በፊት ነበር (ቍ 30 ይመ)።

29፥30 *ያዕቆብ ... ራሔልን ከልያ አብልጦ ወደዳት፤* ያዕቆብ ራሔልን እንዲህ ሊወዳት የቻለው ከመጀመሪያው ይወዳት ስለ ነበረ ብቻ ሳይሆን፣ ላባ ልያን እንዲያገባ ስላታለለውም ጭምር እንደ ሆነ ምንም ጥርጥር የለውም።

*29፥31-35፤* ምንም እንኳ ልያ ያልተወደደች ብትሆንም ሌዊን (የአሮናዊው ክህነት አገልግሎት ቅደመ አያት የሆነው) እና እንዲሁም ይሁዳን ጨምሮ (የዳዊትና የእርሱም ንጉሣዊ የዘር ሐረግ፣ በመጨረሻም የኢየሱስ ትውልድ ቅድመ አያት የሆኑት) የያዕቆብ የመጀመሪያዎቹ አራት ወንድ ልጆች እናት ለመሆን በቅታለች።

29፥32 *እግዚአብሔር መከራዬን ስለተመለከተልኝ... ስሙን ሮቤል አለችው፤* እስማኤልም ስሙን ያገኘው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ነው (16፥11 ይመ)።

ከእንግዲህ ባሌ ያቀርበኛል” አለች፤ ስለዚህ
ሌዊ[θ] ብላ ጠራችው::
35እንደ ገና ፀንሳ አሁንም ወንድ ልጅ
ወለደች፤ እርሷም፣ “እንግዲህ እግዚአብሔ
ርን (ያህዌ) አመሰግናለሁ” አለች፤ ስሙንም
ይሁዳ[+] ብላ ጠራችው:: ከዚያም በኋላ መው
ለድ አቆመች::

30ራሔል ለያዕቆብ አንድም ልጅ እን
ዳልወለደችለት ባየች ጊዜ በእኅቷ
ቀናች:: ስለዚህ ያዕቆብን፣ “ልጅ ስጠኝ፤ አለ
በለዚያ እሞታለሁ” አለችው::
2ያዕቆብም ራሔልን ተቈጥቶ “እኔ እንዳ
ትወልጂ ያደረገሽን እግዚአብሔርን (ኤሎሂም) መስ
ልኹሽን?” አላት::
3እርሷም፣ “እነሆ፤ አገልጋዬ ባላ አለችልህ፤
ልጆች እንድትወልድልኝና እኔም ደግሞ
በእርሷ አማካይነት ልጆች እንዳገኝ ከእርሷ
ጋር ተኛ” አለችው::
4ስለዚህም አገልጋይዋን ባላን ሚስት እን
ድትሆነው ሰጠችው፤ ያዕቆብም አብሮአት
ተኛ፤ 5እርሷም ፀነሰች፤ ወንድ ልጅም ወለ
ደችለት:: 6ራሔልም፣ “እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፈር
ዶልኛል፣ ልመናዬንም ሰምቶ ወንድ ልጅ
ሰጥቶኛል” አለች:: ስለዚህ ስሙን ዳን ብላ
አወጣችለት::
7የራሔል አገልጋይ ባላ እንደ ገና ፀነ
ሰች፤ ለያዕቆብም ሁለተኛ ወንድ ልጅ ወለ
ደች:: 8ራሔልም፣ “እኅቴን ብርቱ ትግል
ገጥሜ አሸነፍሁ” አለች፤ ስሙንም ንፍታ
ሌም ብላ አወጣችለት::
9ልያም ልጅ መውለድ ማቆሟን እንደ
ተረዳች፣ አገልጋይዋን ዘለፋን ሚስት እን
ድትሆነው ለያዕቆብ ሰጠችው:: 10የልያ አገ
ልጋይ ዘለፋም ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለ
ደችለት፤ 11ልያም፣ “ምን ዐይነት መታደል[*]
ነው” አለች፤ ስሙንም ጋድ[ገ] ብላ አወጣች
ለት::
12የልያም አገልጋይ ዘለፋ፤ ለያዕቆብ ሁለ
ተኛ ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ 13ልያም፣
“ምንኛ ደስተኛ ሆንሁ! ከእንግዲህ ሴቶች
ደስተኛዋ ይሉኛል” አለች፤ ስሙንም አሴር[ʼ]
ብላ አወጣችለት:: 14ስንዴ በሚታጨድበት
ወቅት፣ ሮቤል ወደ ሜዳ ወጣ እንኮይም
አግኝቶ ለእናቱ ለልያ አመጣላት:: ራሔ
ልም ልያን፣ “እባክሽን ልጅሽ ካመጣልሽ
እንኮይ ስጪኝ” አለቻት::
15ልያም፣ “ባሌን የቀማሽኝ አነሰና የል
ጄን እንኮይ ደግሞ ልትወስጂ አማረሽ?”
አለቻት::
ራሔልም፣ “ስለ ልጅሽ እንኮይ ዛሬ ከአ
ንቺ ጋር ይደር” አለቻት::
16በዚያች ምሽት ያዕቆብ ከዕርሻ ሲመ
ለስ፣ ልያ ወጥታ ተቀበለችውና፣ “በልጄ እን
ኮይ ስለ ተከራየሁህ የዛሬው አዳርህ ከእኔ
ጋር ነው” አለችው፤ ያዕቆብም በዚያች ሌሊት
ከእርሷ ጋር አደረ::
17እግዚአብሔር (ኤሎሂም) የልያን ጸሎት ሰማ፤ ፀነ
ሰች፤ ለያዕቆብም አምስተኛውን ወንድ ልጅ
ወለደች:: 18ልያም፣ “አገልጋዬን ለባሌ በመ
ስጠቴ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከሶኛል” አለች፤
ስሙንም ይሳኮር[ፕ] ብላ አወጣችለት::
19ልያ አሁንም ደግማ ፀነሰች፤ ለያዕቆብም
ስድስተኛውን ወንድ ልጅ ወለደች:: 20እር
ሷም፣ “እግዚአብሔር (ኤሎሂም) በከበረ ስጦታ ዐድ
ሎኛል፣ ስድስት ወንዶች ልጆች ስለ ወለ
ድሁለት፣ ከእንግዲህ ባሌ አክብሮ ይይዘኛል’::
አለች፤ ስሙንም ዛብሎን[^] አለችው::
21ከዚያም በኋላ ሴት ልጅ ወለደች፤ ስም
ዋንም ዲና አለቻት::
22እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ራሔልን ዐሰባት፤
ልመናዋንም ሰምቶ ማሕፀንዋን ከፈተላት::
23ከዚያም ፀንሳ፣ ወንድ ልጅ ወለደችና

5-7፤ዘፀ1፥6፡16፡19፤ ዘኍ1፥47፤3፥17-20፤ 26፥57፤ዘዳ33፥8፤1ሳሙ1፥2-4፤1ዜና6፥1:16፤ 23፥6-24
29፥35 ዘፍ30፥9፤ 35፥23፤37፥26፤38፥1፤43፥8፤44፥14:18፤ 46፥12፤49፥8፤1ዜና 2፥3፤4፥1፤ኢሳ48፥1፤ ማቴ1፥2-3
30፥1 ዘፍ11፥30፤ 16፥4፤ዘሌ18፥18፤ኢሳ 49፥21፤54፥1
30፥2 ዘፍ16፥2፤ 50፥19፤ዘዳ32፥35፤ 2ነገ5፥7
30፥3 ቍ7፤ዘፍ 16፥2፤24፥61፤29፥29
30፥4 ቍ9:18፤ዘፍ 16፥3-4
30፥6 ቍ23፤ዘፍ 21፥2፤46፥23፤49፥ 16-17፤ዘኍ26፥42-43፤ኢሱ19፥40-48፤ መሳ1፥34፤13፥2፤18፥ 2፤ሩት4፥13፤1ሳሙ 1፥20፤መዝ35፥24፤ 43፥1፤ኤር4፥15፤8፥ 16፤ሕዝ48፥1
30፥7 ቍ3
30፥8 ዘፍ32፥28፤ 35፥25፤46፥24፤49፥ 21፤ዘኍ1፥42፤26፥48፤ዘዳ33፥23፤መሳ4፥6፤ 5፥18፤1ዜና7፥13፤ ሆሴ12፥3-4
30፥9 ቍ4፤ዘፍ29፥ 16:24:35
30፥10 ዘፍ46፥18
30፥11 ዘፍ35፥26፤ 46፥16፤49፥19፤ዘፀ1፥ 4፤ዘኍ1፥24፤26፥28፤ ኢሱ4፥12፤1ዜና5፥11፤12፥8፤ኤር49፥1
30፥13 ሩት4፥14፤ ዘፍ35፥26፤46፥17፤ 49፥20፤ዘኍ1፥40፤ 26፥47፤ዘዳ33፥24፤ ኢሱ19፥24-31፤1ዜና 7፥30-31፤መዝ127፥ 3-5፤ሉቃ1፥48
30፥14 ቍ15:16፤ ዘፀ34፥22፤መሳ15፥1፤ሩት2፥23፤1ሳሙ6፥ 13፤12፥17፤ማሕ7፥13
30፥15 ዘፍ38፥16፤ ዘኍ16፥9:13፤
30፥23 ቍ6፤ዘፍ 29፥32፤ኢሳ4፥1፤25፥ ኢሳ7፥13፤ሕዝ16፥33፤34፥18፤ሆሴ9፥1 30፥16 ቍ14 30፥17 ዘፍ25፥21 30፥18 ቍ4፤ዘፍ46፥13፤49፥14፤ዘኍ1፥8:28:29፤ 26፥25፤ዘዳ27፥12፤33፥18፤ኢሱ17፥10፤19፥17፤21፥6:28፤መሳ5፥15፤ 10፥1፤1ዜና7፥1 30፥20 ዘፍ29፥34፤35፥23፤46፥14፤49፥13፤ዘኍ 1፥30፤26፥27፤34፥25፤ዘዳ33፥18፤መሳ5፥18፤1ጴጥ3፥7 30፥21 ዘፍ34፥1፤46፥15 30፥22 ዘፍ8፥1፤11፥30፤25፥21

[θ]34 *ሌዊ የሚለው ቃል የተያያዘ የሚል ትርጕም ካለው የዕብ ራይስጥ ቃል የመጣ ሲሆን ከዚሁ ቃል ጋር አንድ ዐይነት ድምፅ አለው::*
[+]35 *ይሁዳ የሚለው ቃል ውዳሴ የሚል ትርጕም ካለው የዕብራ ስጥ ቃል ጋር አንድ ዐይነት ድምፅ አለው::*
[*]11 *ወይም ጭፍራ እየመጣ ነው*
[ገ]11 *ጋድ ማለት መልካም ዕድል ወይም ሰራዊት ማለት ነው*
[ʼ]13 *አሴር ማለት ደስተኛ ማለት ነው*
[ፕ]18 *ይሳኮር የሚለው ቃል ሽልማት የሚል ትርጕም ካለው የዕ ብራይስጥ ቃል ጋር አንድ ዐይነት ድምፅ አለው*
[^]20 *ዛብሉን ማለት ማክበር ማለት ነው*

30፥1 *በእኅቷ ቀናች፤* ያዕቆብ በታላቅ ወንድሙ በዔሳው ላይ እንደ ቀና ሁሉ እርሷም በእኅቷ ቀናችባት:: *ልጅ ስጠኝ፤ አለበለዚያ እሞታለሁ፤* አሳዛኝ ትንቢታዊ ቃላት ናቸው (35፥16-19 ይመ)::

30፥2 *እግዚአብሔርን መሰልኹሽን?* ዝንተ ዓለሙን በራሱ ድካምና ጥረት በረከትን ለማግኘት ይዋትት ነበር:: በዚህ ክፍል ግን ልጅ ከእግዚአብሔር ብቻ የሚገኝ በረከት እንደ ሆነ ማወቅ ነበረበት (የከብቶች በረከትን በሚመለከት 31፥7-13 ይመ):: በኋላም ዮሴፍ ይህንኑ ቃል ጠቅሶ ተናግሮአል (50፥19 ይመ)::

30፥3 *ከእርሷ ጋር ተኛ፤* ቍ 9 እንዲሁም 16፥2 እና ማብ ይመ:: *እንድትወልድልኝና፤* በቍሙ “በጉልበቴ/በጭኔ” ማለት ሲሆን፣ ይህም የሌላውን ሰው ልጅ እንደ ራስ ልጅ አድርጉ ማሳደግን የሚያሳይ ምሳሌያዊ አገላለጽና (48፥10-16 ይመ) “እንደ ራሱ ልጆች” የሚል ፍቺ ያለው ነው (50፥23 ይመ)::

30፥4 *ሚስት እንድትሆነው፤* እንደ ቁባት (35፥22 ይመ)::

*30፥5-12፤* የያዕቆብ አምስተኛ፣ ስድስተኛና ስምንተኛ ልጆች፣ ቁባቶቹ ከነበሩት ገረዶቹ የተወለዱ ናቸው::

30፥14 *ልጅሽ ካመጣልሽ እንኮይ ስጪኝ፤* እንኮይ ከወገብ በታች ያለውን የሰው አካል የሚመስሉ ሥሮች ያሉት ሲሆን፣ ፍሬውን የበሉ ሴቶች ልጅ እንዲፀንሱ ያደርጋል የሚል እምነት ነበር (ማሕ 7፥13 ይመ)::

30፥16 *ስለ ተከራየሁህ፤* ለዚህ ቃል የገባው የዕብራይስጡ ቃል ለይሳኮር የተሰጠ የቀልምጫ ስም ነው፤ ይሳኮር ማለት ሽል ማት ማለት ነው::

*30፥17-20፤* ዘጠነኛና ዐሥረኛው የያዕቆብ ልጆች የተወለ ዱት ከልያ ሲሆን፣ በዚህ መሠረት ልያ ከ12ቱ የያዕቆብ ልጆች 6ቱን ወልዳለች ማለት ነው (የ29፥31-35 ማብ ይመ)::

30፥20 *ስጦታ ዐድሎኛል፤* ለዚህ ሐረግ የገቡት የዕብራ ይስጥ ቃላት ለዛብሉን የተሰጡ የቀልምጫ ስሞች ናቸው:: ዛብ ሉን ማለት ክብር ማለት ነው::

30፥21 *ዲና፤* ም 34 ይመ::

30፥22 *እግዚአብሔርም ራሔልን ዐሰባት፤* የ8፥1 ማብ ይመ::

'እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ዕፍረቴን አስወገደልኝ' አለች፤
24ስሙንም፣ "እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሌላ ወንድ
ልጅ ጨምሮ ይስጠኝ ስትል፣ ዮሴፍ"[ከ] አለ
ችው።

### የያዕቆብ መንጎች መብዛት

25ራሔል ዮሴፍን ከወለደች በኋላ ያዕቆብ
ላባን እንዲህ አለው፤ "ወደ ገዛ ቤቴ፣ ወደ
አገሬ እንድመለስ አሰናብተኝ፤ 26የድካሜ
ዋጋ የሆኑትን ሚስቶቼንና ልጆቼን ስጠኝና
ይዤአቸው ልሂድ፤ መቼም የቱን ያህል
እንዳገለገልኹህ ታውቃለህ" አለው።
27ላባም እንዲህ አለው፤ "በጎ ፈቃድህ ቢሆን፣
እባክህ እዚሁ ከእኔ ጋር ተቀመጥ፤ ምክን
ያቱም እግዚአብሔርም (ያህዌ) በአንተ ምክ
ንያት እንደ ባረከኝ በንግርት ተረድቻለሁ፤[ኸ]
28ይልቅስ ይገባኛል የምትለውን ደሞዝ ንገ
ረኝና እከፍልሃለሁ።"
29ያዕቆብም እንዲህ አለው፤ "መቼም እን
ዴት እንዳገለገልሁህ፣ ከብቶችህ በእኔ ጥበቃ
ምን ያህል እንደ ተመቻቸው አንተ ታው
ቃለህ። 30እኔ ከመምጣቴ በፊት ጥቂት የነ
በረው ሀብትህ ዛሬ ተትረፍርፎአል፣ በተሰ
ማራሁበት ሁሉ እግዚአብሔር (ያህዌ) በረከቱን
አብዝቶልሃል። ታዲያ፣ ስለ ራሴ ቤት የማ
ስበው መቼ ነው?"
31ላባም፣ "ታዲያ ምን ልስጥህ?" ሲል ጠየ
ቀው።
ያዕቆብም መልሶ እንዲህ አለው፤ "ምንም
አትስጠኝ፤ ነገር ግን የምጠይቅህን አንዲት
ነገር ብቻ ብታደርግልኝ ከብቶችህን ማገ
ዴን እቀጥላለሁ፤ 32በመንጎቹ መካከል ዛሬ
ልዘዋወርና ከበጎቹ መካከል ዝንጉርጉር የሆ
ኑትን፣ ነቍጣ ያለባቸውንና ጥቋቁሮቹን እን
ዲሁም ከፍየሎቹ ነቍጣ ያለባቸውንና ዝን
ጉርጉሮቹን ልምረጥ፤ እነዚህ ደሞዜ ይሁኑ።
33ወደፊት ደሞዜን ለመቈጣጠር በምትመ
ጣበት ጊዜ ታማኝነቴ ይታወቃል፤ በመንጋ
ዎቼ መካከል ዥንጕርጕር ወይም ነቍጣ
የሌለበት ፍየል፣ ወይም ጥቁር ያልሆነ ቢገኝ
ያ እንደ ተሰረቀ ይቈጠር"።
34ላባም፣ "እሺ፣ ይሁን፤ ባልኸው ተስማ
ምቼአለሁ" አለው። 35ነገር ግን በዚያኑ ዕለት
ኩተባት ፍየሎች ሽመልመሌ የሆኑትን ወይም
ነቍጣ ያለባቸውን ሁሉ፣ እንዲሁም ከእን
ስት ፍየሎች ነቍጣ ያለባቸውን ዝንጕር
ጕር የሆኑትን ሁሉ፣ ማንኛውንም ነጭ ያለ
በትን ሁሉ መረጠ፤ ደግሞም ጥቋቁር የሆ
ኑትንም በጎች ሁሉ ለየና ወንዶች ልጆቹን
አስጠበቃቸው። 36ከዚያም በእርሱና በያዕ
ቆብ መካከል የሦስት ቀን መንገድ ርቀት
እንዲኖር አደረገ፤ ያዕቆብም የቀሩትን የላ
ባን መንጎች ማገዱን ቀጠለ።
37ነገር ግን ያዕቆብ እርጥብ የልብን፣ የለ
ውዝንና የኤርሞን በትሮች ወሰደ፤ ቅርፊታ
ቸውንም በቀጭን ልጦ እያነሣ የበትሮቹ
ግንድ ነጩ እንዲታይ፣ ሽመልመሌ መልክ
እንዲኖራቸው አደረገ። 38የላጣቸውንም በት
ሮች መንጎቹ ውሃ ለመጠጣት ሲመጡ ከፊት
ለፊት እንዲያዩአቸው በማጠጫ ገንዳዎቹ
ሁሉ አስቀመጠ። መንጎቹም ስሜታቸው ሲነ
ሣሣና ውሃ ለመጠጣት ሲመጡ፣ 39በትሮቹን
ፊት ለፊት እያዩ ይሳረሩ ነበር፤ ሽመል
መሌ፣ ዝንጕርጕርና ነቍጣ የባለባቸውንም
ግልገሎች ወለዱ። 40ያዕቆብ ግልገሎቹን
ለብቻ ለያቸው፤ የቀሩትንም የላባ መንጎች
ሽመልመሌና ጥቋቁር በሆኑት ትይዩ አቆ
ማቸው፤ በዚህም መሠረት የራሱ መንጋ
ከላባ መንጋ ጋር እንዳይቀላቀል ለብቻ ለየ።
41ያዕቆብም ብርቱ እንስቶች አውራ ፈልገው
በሚቅበጠበጡበት ጊዜ፣ በትሮቹ አቅራቢያ
እንዲጠቁ በትሮቹን በውሃ ገንዳዎቹ ውስጥ
ፊት ለፊታቸው ያስቀምጥ ነበር፤ 42ደካማ
በሆኑት እንስቶች ፊት ግን፣ በትሮቹን
አያስቀምጥም ነበር፤ ስለዚህ ደካማ ደካ
ማዎቹ ለላባ ሲሆኑ፣ ብርቱ ብርቱዎቹ ለያዕ
ቆብ ሆኑ። 43በዚህም ሁኔታ ይህ ሰው
እጅግ ባለ ጠጋ ሆነ፤ የብዙ መንጎች፣ የሴ
ትና የወንድ አገልጋዮች፣ እንዲሁም የግመ
ሎችና የአህዮች ባለቤት ሆነ።

### ያዕቆብ ከላባ ቤት ኰበለለ

31 1የላባ ወንዶች ልጆች፣ "ያዕቆብ የአ
ባታችንን ሀብት እንዳለ ወስዶታል፤
ይህ ሁሉ እርሱ ያካበተውም ሀብት ከአባታችን

[ከ]24 *ዮሴፍ ማለት እርሱ ይጨምር ማለት ነው*
[ኸ]27 *ወይም እየበለጸግሁና እግዚአብሔርም በአንተ ምክንያት እየባረከኝ ነው*

8፥45፥17፥54፥4፤ሉቃ 1፥25
30፥24 ዘፍ29፥6፤ 32፥22፤33፥2፡7፤35፥17፡24፤37፥2፤39፥1፤ 49፥22-26፤ዘዳ33፥13 ፤1ሳሙ4፥20
30፥25 ዘፍ24፥54፤ 28፥15
30፥26 ዘፍ29፥18
30፥27 ቍ30፤ዘፍ 26፥24፤31፥38፤33፥10፤44፥5፡15፤50፥4፤ ዘሌ19፥26፤ዘኍ22፥7፤23፥23፤24፥1፤ዘዳ 28፥11፤ኢሳ13፥22፤ 2ሳሙ6፥11፤2ነገ 17፥17፤አስ2፥15፤ ኤር27፥9
30፥28 ዘፍ29፥15
30፥29 ዘፍ31፥6፡ 38-40
30፥30 ቍ27፤ 1ጢሞ5፥8
30፥32 ቍ33፡35፡ 39፡40፤ዘፍ29፥15፤ 31፥8፡12
30፥33 ቍ32፤ዘፍ 31፥39
30፥35 ቍ32፤ዘፍ 31፥1
30፥36 ዘፍ31፥22፤ ዘፀ3፥18፤5፥3፤8፥27
30፥37 ቍ38፡41፤ ኤር1፥11፤ሕዝ31፥8
30፥38 ቍ37፡41፤ ዘፀ2፥16፤ኤር2፥24
30፥39 ቍ32፡41
30፥40 ቍ32
30፥41 ቍ37፡38
30፥42 ዘፍ31፥1፡9፡ 16፡43
30፥43 ዘፍ12፥16
31፥1 ዘፍ30፥35፡ 42
31፥2 ቍ5
31፥3 ቍ13፤ዘፍ

30፥23 *ዕፍረቴን፤* መካንነት የሚያሳፍርና በእግዚአብሔርም ዘንድ የመጠላት ምልክት ተደርጐ ይቆጠር ነበር (16፥2፤ 30፥2 ይመ)።

30፥24 *ጨምሮ ይስጠኝ፤* ራሔል ምኞቷ እውን እንዲሆን የተሰጣት ነገር የሞቷ ምክንያት ሆነ። (35፥16-19 ይመ)።

*30፥27 በንግርት ተረድቻለሁ፤* የተሰወረን ነገር መርምሮ ለማወቅ (44፥5 ይመ) የታረዱ እንስሳትን ጕበትና ሞራ በማንበብና (ሕዝ 21፥21 ይመ)፣ በጥንቈላ በመታገዝ የሚደረግ ሙከራ ነው (ሐሥ 16፥16 ይመ)። እስራኤል ግን እንዲህ በመሰለው ድርጊት ውስጥ ምንም ተሳትፎ እንዳይኖራት በጥብቅ ተከልክላለች (ዘሌ 19፥26፥ ዘዳ 18፥10፡14)፤ የዚህ ምክንያቱ እንዲህ ያለው ድርጊት የሚያንጸባርቀው፣ ይህ ዓለም በክፉ ኀይላት ቍጥጥር ሥር ነው የሚለውን የአረማውያን አስተሳሰብ ሲሆን፣ ይህም ባንጻሩ ዓለም በእግዚአብሔር ሉዓላዊ አገዛዝ ሥር እንዳይደለች የሚያሳይ በመሆኑ ነው። *እግዚአብሔርም በአንተ ምክንያት እንደ ባረከኝ፤* ከ21፥22፤ 26፥28-29 ጋር ያነጻጽሩ። የአብርሃም ልጆች የበረከት ምንጮች ናቸው (12፥2 ይመ)።

30፥35 *ለየና፤* ይህንን ያደረገው ለያዕቆብ ሳይነግር በምስጢር ነው።

30፥37 *የልብን... ነጩ፤* በዚህ ቦታ የገባው የዕብራይስጥ ቃል ላባ ለሚለው ስም ሲሆን፣ ሁለት ትርጕም ያለው አስቂኝ ስም ነው ያዕቆብ በቀይ ወጥ (25፥30) የዔሳውን (ሌላ ስሙ ኤዶም ሲሆን፣ ትርጕሙም "ቀይ" ማለት ነው) በረከት እንደወሰደበት ሁሉ፣ የላባንም (ትርጕሙ "ነጭ" ማለት ነው) በረከት በነጭ የዛፍ ቅርንጫፎች ሊወስድበት የተቻለውን ጥረት አድርጐአል። በእርግጥ ያዕቆብ በላባ ላይ የተጠቀመው የላባን የማታለል ዘዴ ነው።

*30፥39፤* ዕቅዱ ተፈጸመ፤ የተፈጸመው ግን በያዕቆብ ዘዴ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት ነው (ይህንንም ያዕቆብ እንደ ተቀበለው በ31፥9 ላይ ይመ)።

30፥43 *እጅግ ባለጠጋ ሆነ፤* ከስድስት ዓመት በላይ ወስዶበታል (31፥41 ይመ)። ያዕቆብ ካራን በነበረ ጊዜ ቤተ ሰብም ሀብትም አግኝቶአል።

የተገኘ ነው” እያሉ ሲያወሩ ያዕቆብ ሰማ::
2የላባ አመለካከት ከቀድሞው የተለወጠበት
መሆኑንም ያዕቆብ ተረዳ::
3እግዚአብሔርም (ያህዌ) ያዕቆብን፣ “ወደ አባ
ቶችህና ዘመዶችህ አገር ተመለስ፤ እኔም
ካንተ ጋር እሆናለሁ” አለው::
4ስለዚህም ያዕቆብ መንጎቹ ወደ ተሰማሩ
በት መስክ እንዲመጡ፣ ራሔልንና ልያን
አስጠራቸው፤ 5እንዲህም አላቸው፤ አባታ
ችሁ ስለ እኔ ያለው አመለካከት እንደ ቀድ
ሞው አለመሆኑን ተረድቻለሁ፤ ቢሆንም የአ
ባቴ ስምባክ (ኤሎሂም) አልተለየኝም፤ 6መቼም
ባለኝ ዐቅም አባታችሁን ማገልገሌ ከእናንተ
የተሰወረ አይደለም:: 7አባታችሁ ደሞዜን ዐሥር
ጊዜ እየለዋወጠ አታልሎኛል፣ ሆኖም አን
ዲጎዳኝ ስግዚስብሔር (ኤሎሂም) አልፈቀደለትም::
8እርሱ፣ ‘ደሞዝህ ዝንጕርጕሮቹ ይሆናሉ’
ሲለኝ፣ መንጎቹ ሁሉ ዝንጕርጕር ወለዱ፤
ደግሞም ‘ደሞዝህ ሽመልመሌዎቹ ይሆናሉ’
ሲለኝ፣ መንጎቹ ሁሉ ሽመልመሌ መልክ
ያላቸውን ወለዱ፤ 9ስለዚህ ስግዚስብሔር (ኤሎሂም)
የአባታችሁን ከብቶች ወስዶ ለእኔ ሰጠኝ::
10“እንስሳቱ በሚጠቁበት ወራት፣ የሚ
ያጠቋቸው አውራ ፍየሎች መልካቸው፣ ሽመ
ልመሌ፣ ዝንጕርጕርና ነቍጣ ያለባቸው
መሆናቸውን ዐይኔን አንሥቼ በሕልሜ አየሁ::
11የስግዚስብሔርም (ኤሎሂም) መልአክ፣ ‘ያዕቆብ’
አለኝ፤ እኔም፣ ‘እነሆ አለሁኝ’ አልሁት::
12እርሱም ‘መንጎቹን የሚያጠቋቸው አውራ
ፍየሎች ሁሉ ሽመልመሌ መልክ ያላቸው፣
ዝንጕርጕርና ነቍጣ ያለባቸው መሆናቸ
ውን ቀና ብለህ ተመልከት፤ ላባ በአንተ ላይ
የሚፈጽመውን ድርጊት ሁሉ አይቻለሁና፤
13የድንጋይ ሐውልት በማቆም ዘይት ቀብ
ተህ የተሳልህባት የቤቴል አምላክ (ኤል) እኔ
ነኝ፤ አሁንም ይህን አገር ፈጥነህ ልቀቅ
ወደ ተወለድህበትም ምድር ተመለስህ ሂድ’
አለኝ::”
14ራሔልና ልያም እንዲህ ብለው መለሱ
ለት፤ “ከአባታችን ሀብት የምናገኘው ምን
ውርስ አለ? 15እኛን የሚያየን እንደ ባዕድ
አይደለምን? ደግሞም እኮ እኛን ሸጦናል፣

21፥22፤26፥3፤32፥9፤
ዘዳ30፥3፤ኢሳ10፥21፤
35፥10፤ኤር30፥3፤
42፥12
31፥5 ቍ2:29:42:
53፤ዘፍ21፥22፤26፥3፤
43፥23፤ዳን2፥23
31፥6 ዘፍ30፥29
31፥7 ቍ 41:52፤
ዘፍ24፥50፤29፥15፤
ዘሌ6፥2፤ዘኍ14፥22፤
ኢዮ19፥3፤አሞ8፥5
31፥8 ዘፍ30፥32
31፥9 ዘፍ30፥42፤
ኢዮ39፥2፤ሕዝ31፥6
31፥10 ዘፍ20፥3
31፥11 ዘፍ16፥7፤
20፥3፤22፥1፤ዘፀ3፥4
31፥12 ዘፍ30፥32፤
ዘፀ3፥7
31፥13 ቍ3፤ዘፍ
28፥10-22
31፥14 2ሳሙ20፥
1፤1ነገ12፥16
31፥15 ዘፍ29፥20፤
ዘዳ15፥3፤23፥20፤ሩት
2፥10፤2ሳሙ15፥19፤
1ነገ8፥41፤አብ1፥11
31፥16 ዘፍ30፥42
31፥17 ዘፍ24፥63-
64፤27፥41
31፥18 ዘፍ10፥9፤
12፥5፤25፥20፤35፥27
31፥19 ቍ30:32:
34-35፤ዘፍ35፥2፤38፥
12፤13፤ኢሱ24፥14፤
መሳ17፥5፤18፥14:17:
24:30፤1ሳሙ7፥3፤
19፥13፤25፥2:4:7፤
2ሳሙ13፥23፤2ነገ23፥
24፤ሆሴ3፥4
31፥20 ቍ27፤ዘፍ
25፥20፤27፥36
31፥21 ቍ22:23:
25፤ዘፍ2፥14፤37፥25፤
ዘፀ2፥15፤14፥5፤ዘኍ
26፥30፤32፥1፤ዘዳ3፥
10፤ኢሱ12፥2፤1ነገ
18፥46፤19፥3፤ኤር
22፥6፤26፥21
31፥22 ቍ21፤ዘፍ
30፥36
31፥23 ቍ21:37፤
ዘፀ14፥9
31፥24 ዘፍ20፥3፤
31፥29 ቍ5:7፤ዘፍ
24፥50፤26፥29

የተሸጥንበትንም ዋጋ ራሱ በልቶታል:: 16ስግ
ዚስብሔር (ኤሎሂም) ከአባታችን ወስዶ ለአንተ
የሰጠው ሀብት ሁሉ የእኛና የልጆቻችን ነው፤
ስለዚህ ስግዚስብሔር (ኤሎሂም) የነገረህን ሁሉ አድ
ርግ::”
17ከዚያም ያዕቆብ ልጆቹንና ሚስቶቹን
ግመሎች ላይ አስቀመጠ፤ 18በመስጴጦምያ
ካፈራው ሀብት ሁሉ ጋር ከብቶቹን በሙሉ
ወደ ፊት አስቀደመ፤ ወደ አባቱም ወደ
ይስሐቅ አገር፣ ወደ ከነዓን ምድር ጒዞውን
ቀጠለ::
19ላባ በጎቹን ሊሸልት ሄዶ ሳለ፣ ራሔል
የአባቷን ቤት የጣዖታት ምስል ሰረቀች::
20ያዕቆብም ቢሆን፣ መኰብለሉን ለሶርያ
ዊው ለላባ ሳይገልጥለት በመቅረቱ አታል
ሎታል:: 21ያዕቆብ የእርሱ የሆነውን ሁሉ
ይዞ፣ የኤፍራጥስን ወንዝ ተሻግሮ ወደ ኰረ
ብታማው አገር፣ ወደ ገለዓድ አመራ::

### ላባ ያዕቆብን ተከታተለው

22የያዕቆብ መኰብለል ለላባ በሦስተኛው
ቀን ተነገረው:: 23ላባ ዘመዶቹን ይዞ ተነሣ፤
ያዕቆብንም ሰባት ቀን ተከታትሎ ገለዓድ
በተባለ ኰረብታማ አገር ደረሰበት:: 24ከዚ
ያም ስግዚስብሔር (ኤሎሂም) ለሶርያዊው ለላባ
በሕልም ተገለጠ፣ “ያዕቆብን፣ ክፉም ሆነ
ደግ፣ እንዳትናገረው ተጠንቀቅ” አለው::
25ያዕቆብ ገለዓድ በተባለው ኰረብታማ
አገር ድንኳኑን ተክሎ ሳለ፣ ላባ ደረሰበት፤
ላባና ዘመዶቹም በዚያው ሰፈሩ:: 26ከዚያም
ላባ ያዕቆብን እንዲህ አለው፤ “ምን ማድ
ረግህ ነው? አታልለኸኛል፤ ልጆቼን የጦር
ምርኮኛ ይመስል አካልበህ ወሰድሃቸው::
27ለመሆኑ ለምን ተደብቀህ ሄድህ? ለምንስ
አታለልኸኝ? ብትነግረኝ ኖሮ፣ በደስታና
በዘፈን በከበሮና በበገና አልሸኝህም ነበር?
28የልጆቼን ልጆችና ልጆቼንም ስሜ ብሰና
በት ምን ነበረበት? የሠራኸው የጅል ሥራ
ነው:: 29ልጉዳችሁ እችል ነበር፤ ዳሩ ግን ባለፈው

24፥50፤25፥20 31፥25 ቍ21 31፥26 ዘፍ12፥18፤27፥36፤34፥29
፤1ሳሙ30፥2-3 31፥27 ቍ20፤ዘፍ4፥21፤ዘፀ15፥20፤መሳ11፥34፤
1ሳሙ10፥5፤2ሳሙ6፥5፤መዝ68፥25፤ኢሳ24፥8፤ኤር31፥4 31፥28
ዘፍ27፥27፤ሩት1፥14፤ሐሥ20፥37

31፥3 *ወደ አባቶችህ... አገር ተመለስ፤* ያዕቆብ ከሚስቶቹ (ቍ 14-16 ይመ)፣ ከላባ (ቍ 2 ይመ)፣ ከላባ ወንዶች ልጆችና (ቍ 1 ይመ) አሁን ደግሞ ከራሱ ከእግዚአብሔር ያገኘው ምልክት ወደ ከነዓን መመለሻው ጊዜ እንደ ደረሰ ያመለክታል:: *እኔም ካንተ ጋር እሆናለሁ፤* የ26፥3 ማብ ይመ::

31፥4 *ራሔልንና ልያን፤* ከብዙ ጊዜ በኋላ (ቍ 14 ይመ) የልያ ታናሽ የሆነችው ራሔል ከታላቋ ከልያ ቅድሚያ ተሰጣት፤ ራሔል ግን ወዲያው እንደ ባለቤቷ እንደ ያዕቆብ አታላይ ሆነች (ቍ 31፥35 ይመ)::

31፥7 *ዐሥር ጊዜ፤* ቍ 41 ይመ:: እዚህ ላይ “ዐሥር” የሚለው ቃል ምናልባት ፍጹምነትን ሳያመለክት አይቀርም:: ላባ ብዙ ጊዜ ያታለለው ስለ ነበር ያዕቆብ ይከሰው ነበር::

*31፥9* የ30፥39 ማብ ይመ::

31፥11 *የእግዚአብሔርም መልአክ፤* የ16፥7 ማብ ይመ:: *‘እነሆኝ፤ አልሁት’፤* የ22፥1 ማብ ይመ::

31፥13 *የድንጋይ ሐውልት በማቆም ዘይት ቀብተህ የተሳልህባት የቤቴል፤* የ28፥18 ማብ ይመ::

31፥18 *በመስጴጦምያ፤* የ24፥10 ማብ ይመ::

31፥19 *የአባቷን ቤት የጣዖታት ምስል፤* ይጠብቁኛል ወይም በረከት ይሰጡኛል ብላ ራሔል የሰረቀቻቸው ትናንሽ በእጅ ተይዘው የሚጓጓዙ ጣዖቶች ሊሆኑ ይችላሉ:: ወይም ከፊቷ ለሚጠብቃት ረጅም ጒዞ እንደ ረዳት የሚሆናት ተጨባጭ አምላክ ልታመልክ ፈልጋም ሊሆን ይችላል፤ ከብዙ ዓመት በኋላ ይህንን ልምምድ ዮሴፍ ወልደ ኮሪዮን የተባለው የመጀመሪያው ምእተ ዓመት የአይሁድ ታሪክ ጸሓፊ በጽሑፉ ገልጾታል:: ያም ሆነ ይህ፣ ራሔል ከአረማዊ (ልማዷ) ወይም ከጣዖት አምላኪነቷ አልተላቀቀችም ነበር (35፥2፤ ኢያ 24፥2 ይመ)::

31፥21 *አመራ፤* ከዚህ በፊት ከዔሳው እንደ ሸሸ ሁሉ፣ አሁንም ሸሸ (27፥42-43):: የያዕቆብ አታላይነት ያተረፈለት ነገር ቢኖር፣ ሁልጊዜ ጠላትነትን ብቻ ነው:: *ገለዓድ፤* ከገሊላ ባሕር በስተ ደቡብ ምሥራቅ የሚገኝ ለም ምድር ነው::

31፥26 *አታልለኸኛል፤* በስሙ ትርጒም ላይ የሚንጸባረቀው የያዕቆብ አታላይነት፣ በታሪኩ ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል::

31፥27 *በበገና፤* ከዘመናዊ በገና ያነሰ፣ (አብዛኛውን ጊዜ ከ6 እስከ 12 ክሮች ያሉት) የሙዚቃ መሣሪያ ነው::


ሌሊት የአባታችሁ አምላክ (ኤሎሂም) ‘ያዕቆብን፣
ክፉም ሆነ ደግ እንዳትናገረው ተጠንቀቅ’
አለኝ። 30አንተ ወደ አባትህ ቤት ለመመለስ
ስለ ናፈቅህ ሄደሃል፤ ነገር ግን የቤቴን
የጣዖት ምስል የሰረቅኸው ለምንድ ነው?”
31ያዕቆብም ለላባ እንዲህ ሲል መለስ
ለት፤ “ሴቶች ልጆችህን በኀይል ነጥቀህ ታስ
ቀርብኛለህ ብዬ ስለ ፈራሁ ነው። 32ነገር
ግን ከእኛ መካከል የአንተን የጣዖታት ምስል
ደብቆ የተገኘ ሰው ካለ ይሙት። ያንተ የሆነ
አንዳች ነገር ከኔ ዘንድ ቢገኝ፣ አንተው ራስህ
ዘመዶቻችን ባሉበት ፈልግና ውሰድ።” ይህን
ሲል፣ ራሔል የጣዖታቱን ምስል መስረቋን
ያዕቆብ አያውቅም ነበር።
33ላባም ወደ ያዕቆብ፣ ድንኳንና ወደ ልያ
ድንኳን እንዲሁም ወደ ሁለቱ ደንገጡሮቿ
ድንኳኖች ገባ፤ ነገር ግን ምንም አላገኘም።
ከልያ ድንኳን ከወጣ በኋላ ወደ ራሔል
ድንኳን ገባ። 34ራሔል የጣዖታቱን ምስል
ከግመሏ ኮርቻ ሥር ሸሽጋ፣ በላዩ ተቀም
ጣበት ነበር፤ ላባም ድንኳኑን አንድ በአንድ
በርብሮ ምንም ሊያገኝ አልቻለም።
35ራሔልም አባቷን፣ “በፊትህ ተነሥቼ
መቆም ስላልቻልሁ፣ ጌታዬ አትቈጣ፤ የወር
አበባዬ መጥቶ ነው።” አለችው፤ ስለዚህ በረ
በረ፤ የጣዖታቱን ምስል ግን ማግኘት አልቻ
ለም።
36በዚህ ጊዜ ያዕቆብ ተቈጣ፤ ላባንም እን
ዲህ ሲል ወቀሰው፤ “እስቲ ወንጀሌ ምን
ድን ነው? ይህን ያህል የምታሳድደኝ ኀጢ
አቴ ምን ቢሆን ነው? ዕቃዬን አንድ በአ
ንድ በርብረሃል፤ ታዲያ፣ የአንተ ሆኖ ያገ
ኘኸው ዕቃ የትኛው ነው? ካለ፣ እስቲ በአ
ንተም በእኔም ዘመዶች ፊት አቅርብና እነ
ርሱ ያፋርዱን።
38ሃያ ዓመት አብሬህ ኖሬአለሁ፤ በዚህ
ጊዜ ውስጥ ከመንጋህ አንድ ጠቦት እንኳ
አልበላሁም። 39አውሬ የሰበረውንም ቢሆን
እተካ ነበር እንጂ፣ ትራፊውን ለምልክት
ነት አምጥቼ አላውቅም፤ በቀንም ሆነ በሌ
ሊት የተሰረቁትን ሁሉ ስታስከፍለኝ ኖረ
ሃል። 40ቀን በሐሩር ሌሊት በቍር ተቃጠልሁ፤


31፥30 ቍ19፤ዘፍ 28፥15፤44፥8፤ኢዮ 29፥2
31፥31 ዘፍ20፥11
31፥32 ቍ19፤ ዘፍ44፥9
31፥33 ቍ37፤ ዘፍ16፥1፤24፥67
31፥34 ቍ19:37፤ ዘፍ24፥63-64፤44፥12
31፥35 ቍ19፤ዘፀ 20፥12፤ዘሌ15፥19-23፤19፥3:32፤ዘዳ21፥18፤27፥16፤ኤር 35፥18
31፥36 1ሳሙ19፥5፤20፥32፤23፥23፤ 24፥11
31፥37 ቍ33:23፤ ዘዳ1፥16፤16፥18
31፥38 ዘፍ27፥44፤ 30፥27
31፥39 ዘፍ30፥33፤ ዘፀ22፥13
31፥40 መዝ132፥ 4፤2ቆሮ11፥27
31፥41 ቍ7፤ዘፍ 27፥44፤29፥15:30፤

31፥32 *የአንተን የጣዖታት ምስል ደብቆ የተገኘ ሰው ካለ ይሙት፤* ከ44፥7-12 ጋር ያነጻጽሩ። ያዕቆብ በየዋህነት መሥዋዕቱን ቢያቀርብም፣ የሚወዳትን ራሔልን ግን ለትንሽ አጥቶአት ነበር፤ የገዛ ሚስቱ እንኳ ሳትቀር አታለለችው።

31፥34 *ከግመሏ ኮርቻ ሥር ሸሽጋ፣ በላዩ ተቀምጣበት፤* የቤት ጣዖቶች ትናንሽና ኀይልም የሌላቸው መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።

31፥35 *የወር አበባዬ መጥቶ ነው፤* ሴት በወር አበባዋ ወቅት የተቀመጠችበት ማንኛውም ነገር ሁሉ እንደ ርኩስ ይቈጠር ነበር (ዘሌ 15፥20)። ራሔልም አታላይ ሆና ተገኘች።






ኤፍራጥስ- ያዕቆብ ከዔሳው ሲሸሽ የደረሰበት ስፍራ ነው፤ ይህም በመጨረሻ የእናቱ ወንድም ላባ ዘንድ ካራን አጠገብ እንዲቀመጥ ምክንያት ሆኗል።

ረጅሙ የመኖሪያነት ኑሮው ከላባ ጋር በተፈጠረው ግጭት ካበቃ በኋላ ወደ ከነዓን ሄደ። የጉዞው መስመር በያቦቅ ወንዝ በኩል ወደ ጵንኤል ከመድረሱ በፊት ወደ ደማስቆ ነበር።

ላባ ከያዕቆብ ጋር ይዟቸው የነበሩትን ቤተሰቦች ሳይዝ በፊት ያዕቆብና በእርሱ ሥር የሚተዳደሩት ሰዎች ተራራማው የገለዓድ አገር ደርሰው ነበር። በምጽጳ በአንድ ኮረብታ ላይ የተገባው የኪዳን ስፍራ በኋላ በአራምና በእስራኤል የድንበር ጣቢያ በመሆን ያገለግል ነበር።

ያዕቆብ በሱኮት ዘግይቶ ወደ ከነዓን ከዚያም ለጌታ መሥዋዕያ ወደሠራበት ወደ ሴኬም ሄደ።

እንቅልፍም በዐይኔ አልዞር አለ፤ 41ሃያ ዓመት
በቤትህ የኖርሁት በዚህ ሁኔታ ነበር፤ ዐሥራ
አራት ዓመት ለሁለቱ ልጆችህ ብዬ አገለ
ገልሁ፤ ስድስት ዓመት ስለ መንጋዎችህ
ስል አገለገልሁ፤ ይህም ሆኖ ደመወዜን ዐሥር
ጊዜ ለዋውጠኸብኛል:: 42የአባቴ ኤሎሂም (ኤሎ
ሂም)፣ የአብርሃም ኤሎሂም (ኤሎሂም)፣ የይስሐቅም
ፍርሀት ከእኔ ጋር ባይሆን ኖሮ ባዶ እጄን
ሰድደኸኝ ነበር፤ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ግን
መከራዬን አይቶ፣ ልፋቴን ተመልክቶ ትና
ንት ሌሊት ገሥጾሀ::"
43ላባም ለያዕቆብ እንዲህ ሲል መለሰ
ለት፤ "ሴቶቹም፣ ልጆቹም የእኔው ልጆች
ናቸው፣ መንጎቹም ቢሆኑ የራሴ ናቸው::
ታዲያ፣ በእነዚህ ሴቶች ልጆቼና በወለዷ
ቸው ልጆቻቸው ላይ ዛሬ ምን ማድረግ እች
ላለሁ? 44በል አሁን ቃል ኪዳን እንጋባ፤ ኪዳ
ኑም በአንተና በእኔ መካከል ምስክር ይሁን::"
45ያዕቆብም ድንጋይ ወስዶ ሐውልት አድ
ርጎ አቆመው፤ 46ከዚያም ዘመዶቹን፣ "ድን
ጋይ ሰብስቡ" አላቸው:: እነርሱም ድንጋይ
እያመጡ ከመሩ፤ በክምሩም አጠገብ ምግብ
በሉ:: 47ላባም ክምር ድንጋዩን ይጋርሠህ
ዱታ[m] ብሎ ጠራው፤ ያዕቆብ ደግሞ ገለዓድ[o]
አለው::
48ላባም "ይህ ክምር ድንጋይ በእኔና በአ
ንተ መካከል ዛሬ ምስክር ነው" አለው::
ጋልዒድ ተብሎ የተጠራውም በዚሁ ምክን
ያት ነው፤ 49ደግሞም ምጽጳ[n] ተባለ፤ ምክን
ያቱም ላባ እንዲህ ብሎአልና፤ 50"ልጆቼን ብት
በድላቸው ወይም ሌሎች ሚስቶች በላያ
ቸው ላይ ብታገባ፣ ማንም ከእኛ ጋር ባይ
ኖርም እንኳ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) በአንተና
በእኔ መካከል ምስክር መሆኑን አትርሳ::"
51ደግሞም ላባ ያዕቆብን እንዲህ አለው፤
"ክምር ድንጋዩ እነሆ፤ በአንተና በእኔ መካ
ከል ያቆምሁትም ሐውልት እነሆ፤ 52ይህን
ክምር ድንጋይ አልፌ አንተን ለማጥቃት
ላልመጣ፣ አንተም ይህን ክምር ድንጋይና
ይህን ሐውልት አልፈህ እኔን ለማጥቃት ላት
መጣ፣ ይህ ክምር ድንጋይ ምስክር ነው፤
ይህም ሐውልት ምስክር ነው:: 53የአብር
ሃም ኤሎሂም፣ የናኮር ኤሎሂም፣ የአባታቸውም
ኤሎሂም (ኤሎሂም) በመካከላችን ይፍረድብን"::
ስለዚህ ያዕቆብ በአባቱ በይስሐቅ ፍርሀት
ማለ:: 54ያዕቆብ በኰረብታማው አገር ላይ
መሥዋዕት አቀረበ፤ ዘመዶቹንም ምግብ እን
ዲበሉ ጋበዛቸው፤ እነርሱም ከበሉ በኋላ እዚ
ያው አደሩ::
55በማግስቱም ማለዳ ላባ የልጅ ልጆቹን
እንዲሁም ሴቶች ልጆቹን ስሞ መረቃቸው፤
ከዚያም፣ ወደ አገሩ ተመለሰ::

## ያዕቆብ፣ ወንድሙን ዔሳውን ሊገናኝ ተዘጋጀ

32 ያዕቆብም ደግሞ ጒዞውን ቀጠለ፤
የእግዚአብሔርም (ኤሎሂም) መላእክት ተገናኙት፤
2ባያቸውም ጊዜ፣ "ይህ የእግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ሰፈር ነው" አለ፤ የዚያንም ቦታ ስም መሃና
ይም[w] አለው::
3ያዕቆብም በኤዶም አገር ሴይር በተባለው
ምድር ወደሚኖረው ወንድሙ ወደ ዔሳው
መልእክተኞችን አስቀድሞ ላከ፤ 4እንዲህም
ብሎ አዘዛቸው፤ "ጌታዬን ዔሳውን እንዲህ
ትሉታላችሁ፤ 'አገልጋይህ ያዕቆብ እንዲህ
ብሎአል በሉት፤ "ከላባ ዘንድ ተቀምጬ
እስከ አሁን ድረስ እዚያው ኖርሁ፤ 5ከብቶች፣
አህ ዮች፣ የበግና የፍየል መንጎች እንደዚ
ሁም የወንድና የሴት አገልጋዮች አሉኝ፤
አሁንም ይህን መልእክት ለጌታዬ መላኬ
በጎ ፊቃ ድህን እንዳገኝ በማሰብ ነው::"
6የተላኩትም ሰዎች ወደ ያዕቆብ ተመል
ሰው፣ "ወደ ወንድምህ ወደ ዔሳው ሄደን

30፥32
31፥42 ቊ5:53፤ ዘፍ3፥17፤21፥22፤24፥12:50፤46፥1፤ዘፀ3፥15፤መዝ124፥1-2
31፥43 ዘፍ30፥32:42
31፥44 ዘፍ21፥27:30
31፥45 ዘፍ28፥18
31፥46 ቊ48:51:52
31፥47 ዘፍ21፥30
31፥48 ቊ46፤ዘፍ21፥30፤ኢር29፥23፤42፥5
31፥49 ኢሱ11፥31፤መሳ10፥17፤11፥29
31፥50 ዘፍ16፥6፤21፥30፤ዘዳ4፥26፤31፥19፤ኢሱ24፥27፤መሳ11፥10፤1ሳሙ12፥5፤20፥14:23:42፤ኢዮ16፥19፤ኢር7፥11፤29፥23፤42፥5፤ሚክ1፥2
31፥51 ቊ46፤ዘፍ28፥18
31፥52 ቊ 7:46፤ ዘፍ21፥30፤26፥29
31፥53 ቊ42፤ዘፍ11፥27፤16፥5፤21፥23:27፤24፥12
31፥54 ዘፍ26፥30፤46፥1፤ዘፀ24፥5፤ዘሌ3፥1
31፥55 ቊ28፤ዘፍ18፥33፤24፥60፤ዘፀ39፥43፤ሩት1፥9
32፥1 ዘፍ16፥11፤2ነገ6፥16-17፤1ዜና21፥15፤መዝ34፥7፤35፥5፤91፥11፤ዳን6፥22
19፥32፤1ነገ2፥8፤4፥14፤1ዜና6፥80
32፥2 ዘፍ28፥17፤ኢሱ13፥26:30፤21፥38፤2ሳሙ2፥8:29፤17፥24
32፥3 ዘፍ14፥6፤25፥30፤27፥41-42፤36፥16፤ዘኍ21፥21፤24፥18፤መሳ11፥17
32፥4 ዘፍ18፥3፤24፥9፤31፥41
32፥7 ቊ10:11፤ዘፍ33፥1፤35፥3፤መዝ

32፥5 ዘፍ12፥16፤24፥9፤33፥8:10:15፤34፥11፤47፥25:29፤50፥4፤ሩት2፥13 32፥6 ዘፍ33፥1

[m]47 *ይጋርሠሀዱታ* የሚለው ቃል በአረማይስጥ *የኪዳን ክምር ድንጋይ* ማለት ነው
[o]47 *ገለዓድ* የሚለው ቃል በዕብራይስጥ *የኪዳን ክምር ድንጋይ* ማለት ነው
[n]49 *ምጽጳ* የሚለው ቃል *መጠበቂያ ማማ* ማለት ነው
[w]2 *መሃናይም* ማለት *ሁለት ጭፍራ* ማለት ነው

31፥42 ***ፍርሀት፤*** ይህ ቃል "እግዚአብሔር" በሚለው ምትክ የገባ ነው፤ ወይም ደግሞ ለዚህ ቃል የገባው የዕብራይስጡ ቃል "ቤተ ሰብ" የሚል ትርጒም ሊኖረው ይችላል፤ ይህም፣ እግዚአብሔር ከእስራኤል አባቶች ጋር ምን ያህል የቀረበና የጠበቀ ኅብረት እንዳለው የሚያሳይ ነው::

31፥46 ***ምግብ በሉ፤*** የ26፥30 ማብ ይመ::

*31፥48* በተመሳሳይ ሁኔታ ስም የተሰጠውን መሠዊያ ኢያ 22፥10-12:34 ላይ ይመ::

31፥51 ***ክምር... በአንተና በእኔ መካከል... ሐውልት፤*** የላባንና የያዕቆብን የግዛት ክልል ለመለየት የቆመ ምልክት ነው፣ ያዕቆብ ገለዓድ ብሎ ስም የሰጠው የድንጋይ ክምር ገለዓድ ለሚለው ቃል ሁለት ትርጒም ያለው ስም ነው (ቍ 47 ይመ)::

31፥54 ***መሥዋዕት... ጋበዛቸው፤*** እነዚህ ሁለቱ ቃል ኪዳን በሚደረግበት ጊዜ (ቍ 44 ይመ) በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው፤ ***ዘመዶቹንም፤*** በጋራ አብሮ መመገብ፣ እርስ በርስ መቀባበልን ያሳያል (የ26፥30 ማብ ይመ)::

31፥55 ***መረቃቸው፤*** ወይም "ተሰናብቶአቸው" ማለት ነው (31፥28 ይመ)::

32፥1 ***የእግዚአብሔርም መላእክት ተገናኙት፤*** ያዕቆብ የጠላቱን የላባንን አገር ለቆ፣ ወደ ጠላቱ ወደ ዔሳው አገር ሊገባ ጥቂት ቀርቶታል:: በጒዞ ላይ ሳለ ከዚህ በፊት ሸሽቶ ወደ ላባን ሲሄድ በቤቴል ካያቸው ከእግዚአብሔር መላእክት ጋር ተገናኘ (28፥12):: በዚህ ዐይነት እግዚአብሔር በገባለት ቃል ኪዳን መሠረት ከያዕቆብ ጋር ነበረ (28፥15፤ 31፥3፤ እንዲሁም የ26፥3 ማብ ይመ)::

32፥2 ***መሃናይም፤*** በገለዓድ (የ31፥21 ማብ ይመ) ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ፣ ከያቦቅ ደግሞ በስተ ሰሜን በኩል (የቍ 22 ማብ ይመ) የሚገኝ ቦታ ነው:: ከዚህ ቀደም የሁለት ሰፈር ወገኖች በጥላቻ ተገናኝተው በሰላም ተለያይተው ነበር:: አሁን ደግሞ ሌሎች ሁለት ወገኖች እንደ ገና ሊገናኙና በሰላም ሊለያዩ ነው:: ያዕቆብ ግን መላእክትን በዙሪያው በሰላም ሲሰፍሩ ከተመለከተ በኋላ፣ የእግዚአብሔርን በዙሪያው መስፈር እንደ መለኮታዊ ማረጋገጫ የሚያየው መሆኑን ለማመልከት፣ ያንን ወሳኝ ቦታ፣ "ሁለት ሰፈሮች" ብሎ ጠራው:: ያዕቆብ ወደ ከነዓን ሲሄድ የእግዚአብሔር መልአክ ሊያጅበው ቢመጣም (33፥12:15 ይመ) ያዕቆብ ከዔሳው ጋር እገናኝ ይሆን ብሎ ፈርቶ ነበር፤ ስለዚህም ቤተ ሰዎቹን (ቍ 7:10 ይመ) በሁለት ሰፈር ከፍሎ፣ ፊቱን ወደ ከነዓን አቀና፤ በዚህ ሁሉ ሂደት ራሱን ለመጠበቅ በራሱ ዘዴና ኀይል መመካቱን አልተወም ነበር::

32፥3 ***በኤዶም... ሴይር፤*** ያዕቆብ ሊሄድካሰበበት አገር በስተ ደቡብ በጣም ርቆ የሚገኝ ቦታ ነው፤ ያዕቆብ ወደዚህ ቦታ መምጣቱን ዔሳው ካወቀ፣ መንገድ ጠብቆ ይበቀለኛል የሚል ሥጋት ነበረው::

32፥4 ***አገልጋይህ፤*** መልካም ጠባይንና ትሕትናን የሚያሳይ ቃል ነው::

ነበር፤ እርሱም ሊቀበልህ በመምጣት ላይ ነው፤
አራት መቶ ሰዎችም አብረውት አሉ" አሉት::
7ያዕቆብም በታላቅ ፍርሀትና ጭንቀት ተውጦ፣
አብረውት የነበሩትን ሰዎች ሁለት ቦታ[*] ከፈ
ላቸው፤ በጎቹን ፍየሎቹን ከብቶቹንና ግመ
ሎቹንም ሁለት ቦታ ከፈላቸው፣ 8"ዔሳው
መጥቶ በአንደኛው ላይ አደጋ ቢጥል፣ ሌላው
ክፍል[*] ሊያመልጥ ይችላል" ብሎ አስቦ ነበር::
9ያዕቆብ እንዲህ ሲል ጸለየ፤ "የአባቴ የአ
ብርሃም አምላክ፣ የአባቴ የይስሐቅ አምላክ
(ኤሎሂም) ሆይ፤ 'ወደ አገርህና ወደ ዘመዶችህ
ተመለስ፤ እኔም በጎ ነገር አደርግልሃለሁ'
ያልኸኝ እግዚአብሔር (ያህዌ) ሆይ፤ 10እኔ ባሪያህ
እስካሁን ላደረግህልኝ ቸርነትና ታማኝነት
ብቁ አይደለሁም፤ ዮርዳኖስን ስሻገር በእጄ
ላይ ከነበረው በትር በስተቀር ምንም አል
ነበረኝም፤ አሁን ግን ይኸው ሁለት ሰራዊት
ሆኛለሁ:: 11ከወንድሜ ከዔሳው እጅ እንድ
ታድነኝ እለምንሃለሁ፤ መጥቶ እኔንም ሆነ
እነዚህን እናቶች ከነልጆቻቸው ያጠፋናል
ብዬ ፈርቻለሁና፤ 12ነገር ግን፣ አንተ ራስህ፣
'አበለጽግሃለሁ፤ ዘርህንም ሊቈጠር እንደማ
ይቻል እንደ ባሕር አሸዋ አበዛዋለሁ' ብለኸ
ኛል::"
13በዚያችም ሌሊት ያዕቆብ እዚያው አደረ፤
ካለው ሀብት ለወንድሙ ለዔሳው እጅ መንሻ
እነዚህን መረጠ:- 14ሁለት መቶ እንስት ፍየ
ሎችና ሃያ አውራ ፍየሎች፣ ሁለት መቶ
እንስት በጎችና ሃያ አውራ በጎች፣ 15ሠላሳ
የሚያጠቡ ግመሎች ከነግልገሎቻቸው፣ አርባ
ላሞችና ዐሥር ኮርማዎች፣ ሃያ እንስት አህ
ዮችና ዐሥር ተባት አህዮች:: 16እነዚህንም
በየመንጋው ለይቶ፣ የሚነዱአቸውን ጠባ
ቂዎች መደበላቸው፤ ጠባቂዎቹንም፣ "እና
ንተ ቀድማችሁኝ ሂዱ፣ መንጋዎቹንም አራ
ርቃችሁ ንዱአቸው" አላቸው::
17ቀድሞ የሚሄደውንም እንዲህ ሲል አዘ
ዘው፤ ዔሳው አግኝቶህ፣ 'የማን ነህ? ወዴ
ትስ ትሄዳለህ? የምትነዳውስ ይህ ሁሉ ከብት
የማን ነው?' ብሎ ቢጠይቅህ፣ 18'የአገልጋ
ይህ የያዕቆብ ናቸው፤ ለጌታዬ ለዔሳው እጅ
መንሻ የሰደዳቸው ናቸው፤ እርሱም ከበስተ
ኋላችን እየመጣ ነው' ብለህ ንገረው፣"
19እንዲሁም ሁለተኛውን፣ ሦስተኛውንና
መንጎችን የሚነዱትን ሌሎቹንም ሁሉ እን
ዲህ ሲል አዘዛቸው፤ "ዔሳውን ስታገኙት
ይህንኑ ትነግሩታላችሁ፤ 20በተለይም አገል
ጋይህ ያዕቆብ ከኋላችን እየመጣ ነው' ማለ
ትን አትዘንጉ::" ይህንም ያዘዘው፣ "ዔሳው
ከእኔ ጋር ከመገናኘቱ በፊት እጅ መንሻዬ
አስቀድሞ ቢደርሰው ምናልባት ልቡ ይራራና
በሰላም ይቀበለኛል" ብሎ ስላሰበ ነበር::
21ስለዚህ የያዕቆብ እጅ መንሻ ከእርሱ አስ
ቀድሞ ተላከ፤ እርሱ ራሱ ግን እዚያው በሰ
ፈሩበት ቦታ አደረ::

## ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር የገጠመው ትግል

22በዚያች ሌሊት ያዕቆብ ተነሣ፤ ሁለቱን
ሚስቶቹን እንዲሁም ሁለቱን ሴት አገልጋ
ዮቹንና ዐሥራ አንድ ልጆቹን ይዞ በያቦቅ
መልካ ተሻገረ:: 23ወንዙን አሻግሮ ከሸኛ
ቸው በኋላ፣ ጓዙን ሁሉ ሰደደ:: 24ያዕቆብ
ግን ብቻውን እዚያው ቀረ፤ አንድ ሰውም
እስኪነጋ ድረስ ሲታገለው አደረ:: 25ያም
ሰው ያዕቆብን ታግሎ ማሸነፍ እንዳቃተው
በተረዳ ጊዜ፣ የጭኑን ሹልዳ ነካው፤ በግብ
ግቡም የያዕቆብ ጭን ከመጋጠሚያው ላይ
ተናጋ:: 26በዚያን ጊዜ ሰውየው፣ "እንግዲህ
መንጋቱ ስለሆነ ልቀቀኝና ልሂድ" አለው::
ያዕቆብም፣ "ካልባረክኸኝ አልለቅህም"
አለው::
27ሰውየውም፣ "ስምህ ማን ነው?"አለው::
እርሱም፣ "ያዕቆብ ነው" አለ::
28ሰውየውም፣ "ከእግዚአብሔርም (ኤሎሂም)፣ ከሰ
ዎችም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና ከእንግዲህ
ስምህ እስራኤል[*] እንጂ፣ ያዕቆብ አይባልም"
አለው::

4፥1፤77፥2፤107፥6
32፥9 ዘፍ24፥12፤
26፥3፤28፥13፤
31፥12
32፥10 ቍ7፤ዘፍ
24፥27፤38፥18፤
47፥31፤ዘኍ17፥2
32፥11 ቍ7፤ዘፍ
27፥41፤43፥18፤መዝ
59፥2
32፥12 ዘፍ12፥2፤
13፥14፤22፥17፤1ነገ
4፥20:29፤ሆሴ1፥10፤
ሮሜ9፥27
32፥13 ቍ13-15:
18:20:21፤ዘፍ33፥10
፤43፥11:15:25:26፤
1ሳሙ16፥20፤ምሳ
18፥16፤21፥14
32፥14 ዘኍ7፥88
32፥15 ዘፍ13፥2፤
42፥26፤45፥23
32፥16 ዘፍ33፥8
32፥18 ቍ13፤ዘፍ
18፥3
32፥20 ቍ13፤ዘፍ
18፥3፤33፥10፤ዘፀ28፥
38፤ዘሌ1፥4፤1ሳሙ
9፥7፤25፥19፤2ነገ8፥8፤
ኤር40፥5፤ሚል1፥8
32፥21 ቍ31
32፥22 ዘፍ30፥24፤
ዘኍ21፥24፤ዘዳ2፥37፤
3፥16፤ኢያ12፥2
32፥23 ዘፍ26፥14
32፥24 ዘፍ18፥2፤
ዳን10፥8
32፥25 ቍ32
32፥26 ሆሴ12፥4
32፥27 ዘፍ25፥26
32፥28 ዘፍ17፥5፤
30፥8፤ኢሳ1፥26፤56፥
5፤60፥14፤62፥2:4:
12፤65፥15
32፥29 ዘፍ25፥11፤
35፥9፤48፥3፤ዘፀ3፥13

'7 ወይም ጉራ፤ በቍ 10 ላይ ያለውም እንዲሁ
'8 ወይም ጉራ
ᵡ28 እስራኤል ማለት ከእግዚአብሔር ታገለ ማለት ነው::

32፥6 *አራት መቶ፤* አንድ ተዋጊ ሰራዊት ሊይዝ የሚችለውን አኃዝ የሚያመለክት በቂ ቍጥር ነው (1ሳሙ 22፥2፤ 25፥13፤ 30፥10 ይመ)::

32፥9 *ያዕቆብ ... ጸለየ፤* ከቤቴል ከወጣ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ጸለየ::

32፥11 *እናቶች ከነልጆቻቸው፤* ያዕቆብ፣ የዔሳው ቍጣ ለቤተ ሰቦቹ ሁሉ ይተርፋል ብሎ ፈርቶ ነበር::

32፥12 *ዘርህንም ... እንደ ባሕር አሸዋ፤* በ28፥14 ላይ እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን የሚያስታውስ ነው (22፥17 እና ማብ ይመ)::

32፥13 *እጅ መንሻ፤* ምናልባት ተመሳሳይ ድምፅ ባላቸው ቃላት የተደረገ ገለጻ ሳይሆን አይቀርም፤ ያዕቆብም ከእነዚህ "ሁለት ሰፈሮች" (በዕብራይስጥ "ማሃናይም" ቍ 2፤ እንዲሁም ቍ 7-8:10 ይመ) "የእጅ መንሻ" ወይም "ስጦታ"" መርጦ ለወንድሙ አዘጋጀ::

32፥22 *በያቦቅ፤* በአሁኑ ጊዜ ዋዲ ዜርቃ ተብሎ የሚጠራ ወንዝ ሲሆን፣ ከሙት ባሕር በስተ ሰሜን 32 ኪሎ ሜትር ርቆ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ይገባል::

32፥24 *ብቻውን... ቀረ፤* በቤቴል ብቻውን እንደ ቀረ ሁሉ ማለት ነው (28፥10-22):: *አንድ ሰውም፤* በመልአክ መልክ ወይም አምሳል ተገልጦ (ሆሴ 12፥3-4 እና የዘፍ 16፥7 ማብ ይመ)፤ የታገለው ራሱ እግዚአብሔር ነው (ሁኔታውንም ያዕቆብ የኋላ ኋላ አስተውሎታል፤ ቍ 3 ይመ) *ሲታገለው፤* እግዚአብሔር ከያዕቆብ ጋር ስለመታገሉ (በዕብራይስጥ "ያቤቅ")፣ የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ ተመሳሳይነት ባላቸው ቃላት መጠቀም የሚወድ ይመስላል:: ያዕቆብ ዘመኑን ሁሉ በትግል ያሳለፈ ሰው ነው፤ በመጀመሪያ ከዔሳው ጋር፣ ቀጥሎም ከላባን ጋር ታገለ:: አሁን ደግሞ ወደ ከነዓን ለመግባት በተቃረበበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር "መታገል" ነበረበት:: ምክንያቱም የያዕቆብ ዕድል ፈንታ ያለው በእግዚአብሔር እጅ ነው::

32፥25 *ማሸነፍ እንዳቃተው... የጭኑን ሹልዳ ነካው፤* እግዚአብሔር በእንዲህ ዐይነት ሁኔታ ተገልጦ፣ ያዕቆብ ከእርሱ ጋር በብርቱ እንዲታገል ዕድል ቢሰጠውም፣ በማንኛውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ ሊሰባብረው እንደሚችል አሳይቶታል::

32፥26 *አልለቅህም፤* ያዕቆብ ከብርቱ ጽናቱ የተነሣ ወዲያውኑ ተባረከ (ቍ 29):: *ካልባረክኸኝ፤* ያዕቆብ በረከት የሚገኘው ከእግዚአብሔር ብቻ እንደ ሆነ በመጨረሻ ተገነዘበ::

32፥28 *ከእንግዲህ ስምህ... ያዕቆብ አይባልም፤* አሁን እንግዲህ ያዕቆብ፣ የበረከት ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር እንደ ሆነ በመገንዘቡና ወደ ተስፋዪቱም ምድር ለመግባት የተቃረበ በመሆኑ፣ እግዚአብሔር የያዕቆብን ስም በመለወጥ እንደ አገልጋዩ እንደሚያየው አስታወቀ (17፥5 እና ማብ ይመ:: *እስራኤል፤*

29ያዕቆብም፣ “እባክህ ስምህን ንገረኝ”
ብሎ ጠየቀው።
ሰውዬውም፣ “ስሜን ለማወቅ ለምን ፈለ
ግህ?” አለው፤ በዚያም ስፍራ ባረከው።
30ስለዚህ ያዕቆብ፣ “እግዚአብሔርን (ኤሎሂም) ፊት
ለፊት አይቼ እንኳ ሕይወቴ ተርፋለች” ሲል፣
የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል[1] አለው።
31ጵኒኤልንም[m] እንዳለፈ ፀሓይ ወጣችበት፤
እርሱም በጭኑ ምክንያት ያነክስ ነበር።
32ከዚህም የተነሣ የእስራኤል ልጆች እስከ
ዛሬ ድረስ ሹልዳን ከጭኑ ጋር የሚያገናኘ
ውን ሥጋ አይበሉም፤ ምክንያቱም በጭኑ
መጋጠሚያ ላይ ያለው የያዕቆብ ሹልዳ
ተነክቶ ነበር።

## የያዕቆብና የዔሳው መገናኘት

33 ያዕቆብ አሻግሮ ተመለከተ፤ እነሆ
ዔሳው አራት መቶ ሰዎች አስከትሎ
እየመጣ ነበር። ስለዚህ ልጆቹን ለልያ፣ ለራሔ
ልና ለሁለቱ አገልጋዮች አከፋፈላቸው። 2ከዚ
ያም ሁለቱን አገልጋዮች ከነልጆቻቸው አስ
ቀደመ፤ ልያንና ልጆቿንም አስከተለ፤ ራሔ
ልንና ዮሴፍን ግን ከሁሉ ኋላ እንዲሆኑ
አደረገ። 3እርሱ ራሱም ቀድሞአቸው ሄደ፤
ወንድሙም ዘንድ እስኪደርስ ድረስ ሰባት
ጊዜ ወደ መሬት ለጥ ብሎ እጅ ነሣ።
4ዔሳው ግን ሊገናኘው ወደ እርሱ ሮጦ
ሄዶ ዐቀፈው፤ በዐንገቱም ላይ ተጠምጥሞ
ሳመው፤ ሁለቱም ተላቀሱ። 5ከዚያም ዔሳው
ቀና ብሎ ሲመለከት ሴቶቹንና ልጆቹን
አየ፤ እርሱም፣ “እነዚህ አብረውህ ያሉት
እነማን ናቸው?” ብሎ ጠየቀው።
ያዕቆብም መልሶ፣ “እነዚህማ እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) በቸርነቱ ለእኔ ለአገልጋይህ የሰጠኝ
ልጆች ናቸው” አለው።
6በዚህ ጊዜ ሁለቱ ሴት አገልጋዮችና

16፥3፤መሳ13፥17:18
32፥30 ዘፍ16፥13፤
1ቆሮ13፥12
32፥31 መሳ8፥9
32፥32 ቍ25
33፥1 ዘፍ32፥6:7
33፥2 ቍ6፤ዘፍ
30፥24
33፥3 ቍ6:7፤ዘፍ
17፥3፤37፥7-10፤42፥
6፤43፥26፤44፥14፤
48፥12፤1ሳሙ20፥
41፤2ነገ5፥10:14
33፥4 ዘፍ27፥41-
42፤29፥11፤ሉቃ
15፥20
33፥5 ዘፍ18፥3፤48፥
9፤መዝ127፥3፤ኢሳ
8፥18
33፥6 ቍ2:3
33፥7 ቍ2:3፤ዘፍ
30፥24
33፥8 ዘፍ24፥9፤
32፥5:14-16
33፥9 ቍ11፤ዘፍ
13፥6
33፥10 ዘፍ16፥13፤
30፥27፤32፥5:13:20
33፥11 ቍ9፤ዘፍ
19፥3፤30፥26:43፤
1ሳሙ25፥27
33፥13 ቍ8፤ኢሳ
40፥11፤ኤር31፥8
33፥14 ዘፍ14፥6፤
ዘፀ12፥38
33፥15 ዘፍ32፥5
33፥16 ዘፍ14፥6
33፥17 ኢሱ13፥

ልጆቻቸው ቀርበው እጅ ነሡ፤ 7ከዚያም
ልያና ልጆቿ መጥተው እጅ ነሡ፤ በመጨ
ረሻም ዮሴፍና ራሔል መጡ፤ እነርሱም ቀር
በው እጅ ነሡ።
8ዔሳውም፣ “ወደ እኔ ተነድቶ የመጣው
ይህ ሁሉ መንጋ ምንድን ነው?” አለው።
እርሱም፣ “ጌታዬ ሆይ፤ በአንተ ዘንድ
ሞገስ ባገኝ ብዬ ነው” አለው።
9ዔሳው ግን፣ “ወንድሜ ሆይ፤ እኔ በቂ
አለኝ፤ የራስህን ለራስህ አድርገው” አለው።
10ያዕቆብም፣ “የለም፣ እንዲህ አይደለም፤
በአንተ ዘንድ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ፣ እጅ
መንሻዬን ተቀበል፤ በመልካም ሁኔታ ተቀ
ብለኸኝ ፊትህን ማየት መቻሌ ራሱ፣ የእግ
ዚአብሔርን (ኤሎሂም) ፊት የማየት ያህል እቈ
ጥረዋለሁ። 11እግዚአብሔር (ኤሎሂም) በቸርነቱ
አሟልቶ ስለ ሰጠኝ የሚያስፈልገኝ ሁሉ አለ
ኝና ያቀረብኹልህን እጅ መንሻ እባክህ
ተቀበለኝ” አለው። ያዕቆብ አጥብቆ ስለ ለመ
ነው፣ ዔሳው እጅ መንሻውን ተቀበለ።
12ዔሳውም “በል ተነሥና ጕዟችንን እን
ቀጥል፤ እኔም እሄዳለሁ” አለው።
13ያዕቆብ ግን እንዲህ አለው፤ “ጌታዬ፣
እንደምታየው ልጆቹ ይህን ያህል የጠኑ
አይደሉም፣ ለሚያጠቡት በጎችና ጥገቶች
እንክብካቤ ማድረግ አለብኝ፤ እንስሳቱ ለአ
ንዲት ቀን እንኳ በጥድፊያ ቢነዱ በሙሉ
ያልቃሉ። 14ስለዚህ ጌታዬ፣ አንተ ቀድመኸኝ
ሂድ፤ እኔም በምነዳቸው እንስሳትና በልጆቹ
ጕዞ ዐቅም ልክ እያዘገምሁ ሴይር ላይ
እንገናኛለን።”
15ዔሳው፣ “እንግዲያስ ከሰዎቼ ጥቂቶቹን
ልተውልህ” አለው።

[1] 30 *ጵኒኤል ማለት የእግዚአብሔር ፊት ማለት ነው።*
[m] 31 በዕብራይስጥ *ጵኑኤል ማለት ሲሆን የጵኒኤል አማራጭ* ትርጕም ነው።

የቃሉ ትርጕም፣ “ከእግዚአብሔር ጋር የታገለ” ማለት ነው። የእስራኤል ሕዝብ ስማቸውንም ሆነ የማንነታቸውን መግለጫና መታወቂያ የወሰዱት ከአባታቸው ከያዕቆብ (እስራኤል) ነው። እንደ ያዕቆብ ሁሉ የእስራኤል ሕዝቦችም ከእግዚአብሔር ጋር (እስራኤል) በሚለው ስም ሲታወስ ይኖራል፤ እንዲሁም ከሰዎች ጋር ታግለው (ያዕቆብ በሚለው ስም ሲታወስ ይኖራል) አሸን ፈዋል። በኋላም እግዚአብሔር የያዕቆብን አዲሱን ስም ተቀብሎ አጽድቆለታል፤ (35፥10 ይመ)።

32፥29 *ስሜን ለማወቅ ለምን ፈለግህ?* እንዲህ ዐይነቱን የእግዚአብሔርን ጥያቄ መመለስ ከቶ አይቻልም (መሳ 13፥17-18 ይመ)።

32፥30 *እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አይቼ እንኳ ሕይወቴ ተርፋለች፤* የ16፥13 ማብ እንዲሁም መሳ 6፥22-23፤13፥22 ይመ። የእግዚአብሔርን “ጀርባ” (ዘፀ 33፥23 ይመ) ወይም “እግር” (ዘፀ 24፥10 ይመ)፣ ወይም “አምሳል” ዘኍ 12፥8 ይመ) እንደ ምል ክት ማየት ይቻል ይሆናል።

32፥32 *ሹልዳን ከጭኑ ጋር የሚያገናኘውን ሥጋ አይበሉም፤* ምናልባት የታፋ ጡንቻ ሳይሆን አይቀርም። ይህ ሐረግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በየትም ቦታ ተጠቅሶ አይገኝም፤ ሆኖም ከጊዜ በኋላ በተጻፉ የዕብራውያን መጻሕፍት ውስጥ የታፋን (የወርች ሹልዳን) ሥጋ መብላት የሚከለክል/የሚያወግዝ ሕግ ተጠቅሶ ይገኛል። ይህን ከእግዚአብሔር ጋር የተደረገውን ትግል ለዘላለም በሚያስታውስ ሁኔታ ያዕቆብ በሰውነቱ (በአካሉ)፣ እስራ ኤል ደግሞ የሚበላና የማይበላ ምግብን በሚለየው ሥርዐቷ ጠብ ቀውት ይኖራሉ።

33፥2 *ራሔልንና ዮሴፍን ግን ከሁሉ ኋላ፤* ያዕቆብ ከሁሉ አብልጦ የሚወዳትን ሚስቱንና ልጁን ከሚመጣው አደጋ ለማራቅ መፈለጉን ያመለክታል።

33፥3 *ወደ መሬት ለጥ ብሎ እጅ ነሣ፤* ፍጹም መስጠትን የሚያመለክት ሲሆን፣ እንዲህ ያለው ታዛዥነት/ፍጹም መስጠት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ14ኛው ምዕተ ዓመት፣ በግብፅ ቴል ኤል አማርና በተባለ ስፍራ በተገኙ ጥንታዊ መዛግብት ላይ ተጠ ቅሶአል።

*33፥4፤* የያዕቆብ ፍርሀት ሁሉ መሠረት የሌለው ነበር። ምክንያቱም ዔሳው በያዕቆብ ላይ አንዳች ቂም ወይም ቅሬታ እንዳይዝ እግዚአብሔር ዔሳውን ይባርክና ሥራውንም ይሠራ ነበር (ቍ 9)።

33፥9 *ወንድሜ ሆይ፤* ዔሳው ከቸርነትና ከፍቅር የተነሣ ለያዕቆብ የሰጠው በጎ ምላሽ፣ ያዕቆብ በጥርጣሬና በፍርሀት “ጌታዬ ሆይ” (ቍ 8) በማለት ከተናገረው ነገር ጋር የሚነጻጸር ነው።

33፥11 *እጅ መንሻ፤* “እጅ መንሻ” ለሚለው ሐረግ የገባው የዕብራይስጥ ቃል፣ በ27፥35 ላይ “ምርቃት” ተብሎ ከተጠቀሰው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። ያዕቆብ ሲታገልለት የኖረው በረከት ከእግዚአብሔር የተገኘ እንደ ሆነ አሁን መገንዘቡን የዘፍጥረት ጸሓፊ በምፀት ያስተውላል። ያዕቆብ ከዔሳው ጋር ለመታረቅ መፈለጉን ለመጨረሻ ጊዜ ለመግለጽ የሞከረው፣ ከወንድሙ የነጠቀውን “በረከት” እግዚአብሔር ከሰጠው በረከት ላይ ወስዶ በመመለስ ነበር።

33፥14 *እያዘገምሁ ሴይር ላይ እንገናኛለን፤* አሁንም አታላይነቱን ያልተወው ያዕቆብ ዔሳውን ተከትሎ ወደ ሴይር ለመ ሄድ ሐሳብ አልነበረውም።

ያዕቆብ ግን፣ "ለምን ብለህ? በአንተ ዘንድ
ሞገስ ማግኘቴ ብቻ ይበቃኛል" አለው::
16ስለዚህ ዔሳው በዚሁ ዕለት ወደ ሴይር
ለመመለስ ተነሣ:: 17ያዕቆብ ግን ወደ ሱኮት[ሠ]
ሄደ፤ እዚያም ለራሱ መጠለያ፣ ለከብቶቹም
በረት ሠራ፤ ከዚህም የተነሣ የቦታው ስም
ሱኮት ተባለ::
18ያዕቆብ ከሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ
ከተመለሰ በኋላ፣ በከነዓን ወዳለችው ወደ
ሴኬም በደኅና ደረሰ፤[ረ] በከተማዪቱም ፊት
ለፊት ሰፈረ:: 19ድንኳኑን የተከለበትንም
ቦታ ከኤሞር ልጆች በመቶ ጥሬ ብር ገዛ፤
ኤሞርም የሴኬም አባት ነበር:: 20በዚያም
መሠዊያ አቁሞ፣ ኤል ኤሎሄ እስራኤል[ሰ] ብሎ
ጠራው::

## የያዕቆብ ልጅ ተደፈረች

34 ልያ ለያዕቆብ የወለደችለት ሴት
ልጅ ዲና፣ አንድ ቀን የዚያን አገር
ሴቶች ለማየት ወጣች:: 2ሴኬም የተባለው
የአገሩ ገዢ የኤዊያዊ የኤሞር ልጅ ባያት
ጊዜ ይዞ በማስገደድ ደፈራት:: 3ልቡ በያዕ
ቆብ ልጅ በዲና ተማረከ፤ ልጂቷንም በጣም
ወደዳት፤ በጣፈጠም አንደበት አናገራት::
4ሴኬምም አባቱን ኤሞርን፣ "ይህችን ልጅ
አጋባኝ" አለው::
5ያዕቆብ፣ ልጁን ዲናን ሴኬም እንዳስነወ
ራት ሰማ፤ በዚህ ጊዜ ወንዶች ልጆቹ ከብ
ቶቹን በመስክ ያግዱ ነበር፤ ያዕቆብም ልጆቹ
እስኪመለሱ ድረስ ታግሦ ቈየ::
6ከዚያም የሴኬም አባት ኤሞር፣ ያዕቆ
ብን ሊያነጋግረው ወጣ:: 7የያዕቆብ ወንዶች
ልጆችም የተፈጸመውን ድርጊት እንደ ሰሙ
ወዲያውኑ ከመስክ መጡ፤ ሴኬም መደረግ
የማይገባውን አስነዋሪ ነገር በእስራኤል ላይ
በመፈጸም፣ የያቆብን ልጅ ስለ ደፈረ ዐዘኑ፤
ክፉኛም ተቈጡ::
8ኤሞር ግን እንዲህ አላቸው፤ "ልጄ ሴኬም
ልቡ በልጃችሁ ፍቅር ተነድፎአል፤ እባካችሁ
እንዲያገባት ፍቀዱለት:: 9በጋብቻ እንተሳ
ሰር፣ ሴት ልጆቻችሁን ስጡን፣ የእኛንም ሴቶች
አግቡ:: 10አብራችሁንም መኖር ትችላላችሁ፤
አገራችን አገራችሁ ናት፤ ኑሩባት፤ ነግዱባት፤[ሸ]
ሀብት ንብረትም አፍሩባት::"
11ሴኬም ደግሞ የዲናን አባትና ወንድ
ሞቿን እንዲህ አላቸው፤ "በእናንተ ዘንድ
ሞገስ ላግኝ እንጂ የተጠየቅሁትን ሁሉ እሰ
ጣለሁ፤ 12ጥሎሽ ብትሉኝ ጥሎሽ፣ ስጦታ
ብትሉም የፈለጋችሁትን ያህል እሰጣለሁ፣
ብቻ ልጂቱን እንዳገባ ፍቀዱልኝ::"
13የያዕቆብ ወንዶች ልጆችም፣ በእኅታቸው
በዲና ላይ ስለ ተፈጸመው ነውር፣ የሆዳቸ
ውን በሆዳቸው ይዘው፣ ለሴኬምና ለአባቱ
ለኤሞር መልስ ሰጡ፤ 14እንዲህም አሉአቸው፤
"እኅታችንን ላልተገረዘ ሰው ብንሰጥ ውርደት
ስለሚሆንብን፣ እንዲህ ያለውን ነገር አናደ
ርገውም:: 15ሆኖም የምንስማማበት አንድ
መንገድ ብቻ አለ፤ ይህም ወንዶቻችሁን ሁሉ
ገርዛችሁ እኛን የመሰላችሁ እንደ ሆን ነው::
16ከዚያ በኋላ ሴቶች ልጆቻችንን እንድርላ
ችኋለን፤ አብረን እንኖራለን፤ አንድ ሕዝ
ብም እንሆናለን:: 17በመገረዙ የማትስማሙ
ከሆነ ግን ልጃችንን[ቀ] ይዘን እንሄዳለን::"
18ያቀረቡትም ሐሳብ ለኤሞርና ለልጁ
ለሴኬም መልካም መስሎ ታያቸው:: 19ከአ
ባቱ ቤተ ሰብ ሁሉ እጅግ የተከበረው ይህ
ወጣት የያዕቆብን ልጅ እጅግ ወዶአት ስለ
ነበር፣ ያሉትን ለማድረግ ጊዜ አልወሰደበ
ትም:: 20ስለዚህ ኤሞርና ልጁ ሴኬም ይህ
ንኑ ለወገኖቻቸው ለመንገር ወደ ከተማቸው
በር ሄዱ፤ 21እንዲህም አሏቸው፤ "እነዚህ ሰዎች

27፤መሳ8፥5:6:8:
14-16፤1ነገ7፥46፤
2ዜና4፥17፤መዝ
60፥6፤108፥7
33፥18 ዘፍ25፥20፤
12፥6
33፥19 ዘፍ12፥8፤
34፥2:10:16:21፤47፥
27፤ኢሱ24፥32፤መሳ
9፥28፤ዮሐ4፥5፤ሐሥ
7፥16
33፥20 ዘፍ4፥26፤
8፥20
34፥1 ዘፍ30፥21
34፥2 ዘፍ10፥17፤
33፥19፤ ዘዳ21፥14፤
2ሳሙ13፥14
34፥3 ቍ19:26፤
ዘፍ24፥67፤50፥21፤
ኢሳ14፥1፤40፥2
34፥4 ዘፍ21፥21
34፥5 ቍ2:13:27፤
ዘፍ35፥22፤49፥4፤ዘዳ
27፥20፤33፥6፤1ዜና
5፥1
34፥6 መሳ14፥2-5
34፥7 ዘፍ20፥9፤39፥
19፤49፥6-7፤ዘዳ22፥
21፤መሳ19፥23፤20፥
6፤2ሳሙ12፥5፤13፥12
:21፤እስ7፥7፤ምሳ6፥
34፤ኤር29፥23፤
1ቆሮ5፥2
34፥8 ዘፍ21፥21፤
ዘዳ21፥11
34፥9 ቍ16:21፤
ዘዳ7፥3፤ኢሱ23፥12
34፥10 ቍ23፤ዘፍ
13፥9፤33፥19፤42፥34
፤46፥34፤47፥6:27
34፥11 ዘፍ32፥5
34፥12 ዘፀ22፥16፤
ዘዳ22፥29፤1ሳሙ
18፥25
34፥13 ቍ5፤ዘፍ
27፥36
34፥14 ዘፍ17፥14፤
መሳ14፥3፤1ሳሙ31፥
4፤ኢሳ52፥1
34፥15 ቍ22፤
34፥21 ቍ9፤ዘፍ
33፥19

ዘፀ12፥48፤1ሳሙ11፥2 34፥16 ቍ9፤ዘፍ 33፥19 34፥19 ቍ3፤
ዘፍ49፥3፤1ዜና11፥21 34፥20 ዘፍ18፥1

[ሠ]17 *ሱኮት ማለት መጠለያዎች ማለት ነው::*
[ረ]18 *ወይም ሳሌም ደረሰ*
[ሰ]20 *ኤል ኤሎሄ እስራኤል ማለት የእስራኤል አምላክ እግዚ አብሔር ወይም የእስራኤል አምላክ ኀያል ነው ማለት ነው::*
[ሸ]10 *ወይም በነጻነት መንቀሳቀስ፥ ቍ 21 ላይ ያለውም*
[ቀ]17 በዕብራይስጥ *ሴት ልጅን ያመለክታል*

33፥18 *ከሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ፤* የ24፥10 ማብ ይመ:: *በደኅና ደረሰ፤* ያዕቆብ ከ20 ዓመት በፊት ለጸለየው ጸሎት መልስ አገኘ (28፥21 ይመ):: *ሴኬም፤* በመካከለኛው ከነዓን የምትገኝ ታዋቂ ከተማ ስትሆን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የተ ቈረቈረችውና መኖሪያም የሆነችው በእስራኤል አባቶች ዘመን ነው:: ያዕቆብ የአያቱን የአብርሃምን ፈለግ ተከተለ (12፥6 ይመ):: ያዕቆብ በዚህች ቦታ የውሃ ጕድጓድ የቈፈረ ሲሆን፣ (ዮሐ 4፥5-6 ይመ) ይህ ጕድጓዱም እስከ ዛሬ ድረስ በዚሁ ቦታ ይገኛል::

33፥19 *ጥሬ ብር፤* ለዚህ ሐረግ የገባው የዕብራይስጡ ቃል በእስራኤል አባቶች ታሪክ ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል (ኢያ 24፥32፤ ኢዮ 42፥11 ይመ)::

33፥20 *በዚያ መሠዊያ አቆሞ፤* የ12፥7 ማብ ይመ:: *ኤል ኤሎሄ እስራኤል ብሎ ጠራው፤* ትርጕሙ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ወይም የእስራኤል አምላክ ኀያል ነው ማለት ነው:: ያዕቆብ የአባቶቹ አምላክ የእርሱም አምላክ መሆኑን በግ ልጽ መሰከረ (28፥21 ይመ):: እርሱ ግን ሴኬምን ለቆ ወደ ቤቴል መመለስ ስላልፈለገ (35፥1 ይመ)፣ ባካባቢው ችግር ፈጠረ (ም 34 ይመ)::

*34፥1-31፤* ም 33 የሚያበቃው በእግዚአብሔር ስም ሲሆን፣ ም 35 ደግሞ የሚጀምረው በእግዚአብሔር ስም ነው፤ በዚህ አሳ ዛኝ ምዕራፍ ውስጥ ግን የእግዚአብሔር ስም ፈጽሞ አልተጠ ቀሰም (የ7፥16 ማብ ይመ)::

34፥2 *ሴኬም፤* 33፥19 ይመ:: ስሙን ያገኘው ከከተማዋ ስም ሳይሆን አይቀርም::

34፥4 *"ይህችን ልጅ አጋባኝ" አለው፤* የ21፥21 ማብ ይመ::

*34፥7 በእስራኤል፤* የእስራኤል ነገድ ማለት ነው:: *መደ ረግ የማይገባውን፤* ትዕማር በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ወድቃ ለአምኖን ያቀረበችውን አቤቱታ ከዚሁ ጋር ያነጻጽሩ (2ሳሙ 13፥12)::

34፥9 *በጋብቻ እንተሳሰር፤* ከነዓናውያን የእስራኤልን ሕዝብ በጋብቻና በጥቅማ ጥቅም ተብትቦ በመያዝ (ቍ 16 ይመ)፣ ያዕ ቆብ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን በረከት ማለትም ልጆቹንና ሀብቱን "ቍ 12-13" ለመውረስ ፈለጉ:: እስራኤል፣ ከሌሎች ሕዝ ቦችና መንግሥታት በተደጋጋሚ የገጠማት አደጋ ይህ ነበር:: ይህንና ይህን በመሳሰሉ ነገሮች ተብትቦ መያዝ፣ አለበለዚያ ጠላት መሆን፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚደርስ የተለመደ ፈተና ነበር::

*34፥12 ጥሎሹን... እሰጣለሁ፤* የዚህን ዐይነት ጋብቻ ልማ ድና ምሳሌ በ24፥53 ላይ ይመ::

34፥13 *የያዕቆብ ወንዶች ልጆችም... የሆዳቸውን በሆዳ ቸው ይዘው፤* እንደ አባታቸው ሁሉ እነርሱም ተንኰለኞች ነበሩ (27፥24 እንዲሁም የ25፥26 ማብ ይመ)::

*34፥15፤* ለክፉ ተግባርና ተልእኮ ቅዱስ የሆነውን ሥርዐት ሲጠቀሙ ይታያል (ቍ 24-25 ይመ)::

34፥20 *ከተማቸው በር፤* የ19፥1፤ 23፥10 ማብ ይመ::

ወዳጆቻችን ናቸው፤ በአገራችን እንዲኖሩ፣
ተዘዋውረውም እንዲነግዱ እንፍቀድላቸው፤
ምድሪቱ እንደሆን ለእኛም ለእነርሱም ትበ
ቃለች:: ሴቶች ልጆቻቸውን እናገባለን፤ እነ
ርሱም የእኛን ሴቶች ያገባሉ:: 22ሆኖም ሰዎቹ
ከእኛ ጋር እንደ አንድ ሕዝብ ሆነው አብረ
ውን ለመኖር ፈቃደኞች የሚሆኑት፣ የእኛ
ወንዶች እንደ እነርሱ የተገረዙ እንደ ሆነ
ብቻ ነው:: 23ታዲያ እንዲህ ብናደርግ ከብ
ታቸው ንብረታቸው፣ እንስሶቻቸው ሁሉ የእ
ኛው ይሆኑ የለምን? ስለዚህ ባሉት እንስማማ፤
እነርሱም አብረውን ይኑሩ::”

24ከከተማዪቱ በር ውጪ የተሰበሰቡት
ሁሉ በኤሞርና በልጁ በሴኬም ሐሳብ ተስ
ማሙ፤ በከተማዪቱም ያሉት ወንዶች ሁሉ
ተገረዙ::

25በሦስተኛውም ቀን የሁሉም ቍስል ገና
ትኵስ ሳለ ከያዕቆብ ልጆች ሁለቱ፣ የዲና
ወንድሞች ስምዖንና ሌዊ፣ ሰይፋቸውን
መዘው ሳይታሰብ ወደ ከተማዪቱ ገብተው
ወንዶቹን በሙሉ ገደሏቸው:: 26ኤሞርንና
ሴኬምንም በሰይፍ ገድለው፣ እኅታቸውን
ዲናን ከሴኬም ቤት አውጥተው ይዘዋት
ተመለሱ:: 27የያዕቆብ ልጆች ሁሉ በሬሳ
ላይ እየተረማመዱ እኅታቸው የተደፈረች
በትን ከተማ[T] ዘረፉ:: 28የበግና የፍየል መን
ጋቸውን፣ ከብቶቻቸውንና አህዮቻቸውን
እንዲሁም በከተማዪቱና በአካባቢው የሚገ
ኘውን ንብረታቸውን ሁሉ ወሰዱባቸው፤
29ሀብታቸውን ሁሉ ዘርፈው ሴቶቻቸውንና ሕፃ
ኖቻቸውን ሁሉ ማርከው በየቤቱ ያገኙትን
ሁሉ ይዘው ሄዱ::

30ያዕቆብም ስምዖንና ሌዊን እንዲህ አላ
ቸው፤ “በዚህ አገር በሚኖሩት በከነዓናው
ያንና በፌርዛውያን ዘንድ እንደ ጥምብ አስ
ቈጠራችሁኝ፣ ጭንቀትም እንዲደርስብኝ
አድርጋችኋል:: እኛ በቍጥር አነስተኞች
ነን፤ ተባብረው ቢነሡብኝና ቢያጠቁኝ
እኔና ቤተ ሰቤ መጥፋታችን አይደለምን?”

31እነርሱ ግን፣ “ታዲያ፤ እኅታችንን እንደ
ዝሙት አዳሪ ይድፈራት?” አሉት::

34፥22 ቍ15
34፥23 ቍ10:28፤
ዘፍ12፥16
34፥24 ዘፍ18፥1
34፥25 ዘፍ29፥33:
34፤49፥5:7፤ኢሱ5፥8፤
መሳ18፥7:10:27፤ሕ
ዝ38፥11፤ሚል2፥16
34፥26 ቍ3:7፤
ዘፍ48፥22
34፥27 ቍ5፤2ነገ
21፥14
34፥28 ቍ23፤ዘፍ
43፥18
34፥29 ዘፍ31፥26፤
ዘኍ14፥3፤31፥9:53፤
ዘዳ2፥35፤ኢሱ7፥21፤
2ነገ8፥12፤ኢሳ13፥16
፤ሰቆ5፥11፤አሞ1፥13፤
ዘካ14፥2
34፥30 ዘፍ13፥7፤
35፥26፤43፥6፤46፥27
፤ዘፀ1፥5፤5፥21:23፤6፥
9፤ዘኍ11፥11፤ዘዳ10፥
22፤26፥5፤1ሳሙ13፥4
፤27፥12፤2ሳሙ10፥6፤
1ዜና16፥19፤19፥6፤
መዝ105፥12
34፥31 ቍ2
35፥1 ቍ3:7፤ዘፍ
4፥26፤8፥20፤12፥7፤8፤
27፥43፤12፥7
35፥2 ዘፍ18፥19፤
31፥19፤ዘፀ19፥10:14፤
ዘኍ8፥7:21፤19፥19፤
ኢሱ24፥14:15
35፥3 ቍ1፤ዘፍ32፥
7፤26፥3፤መሳ2፥15
35፥4 ቍ8፤
ዘፍ12፥6፤24፥22፤ዘፀ
32፥3፤35፥22፤መሳ
8፥24፤ምሳ25፥12
35፥5 ዘፀ15፥16፤
23፥27፤ዘዳ2፥25፤ኢሱ
2፥9፤1ሳሙ7፥10:13፥
7፤14፥15፤2ዜና14፥
14፤17፥10፤20፥29፤
መዝ9፥20፤105፥14፤
ኢሳ19፥17፤ዘካ14፥13
35፥6 ዘፍ10፥19፤
28፥19
35፥7 ቍ1፤ዘፍ8፥
20፤28፥13:19
35፥8 ቍ4፤ዘፍ12፥
8፤24፥59፤1ሳሙ10፥3
35፥9 ዘፍ25፥20፤
28፥13፤32፥29
35፥10 ዘፍ17፥5
35፥11 ዘፍ12፥2፤
17፥1:6

### ያዕቆብ ወደ ቤቴል ተመለሰ

35 እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ያዕቆብን፣ “ተነሥና
ወደ ቤቴል ውጣ፤ እዚያም ተቀመጥ፤
ከወንድምህ ከዔሳው ሸሽተህ በሄድህ ጊዜ
ለተገለጠልህ አምላክ (ኤል) በዚያ መሠዊያ
ሥራ” አለው::

2ስለዚህም ያዕቆብ ለቤቱ ሰዎችና አብ
ረውት ለነበሩት ሁሉ እንዲህ አላቸው፤
“በእናንተ ዘንድ ያሉትን ባዕዳን አማልክት
አስወግዱ፤ ሰውነታችሁን አንጹ፤ ልብሳችሁ
ንም ለውጡ:: 3ተነሥተን ወደ ቤቴል እን
ውጣ፤ እዚያም በመከራዬ ጊዜ ለሰማኝ፣ በሄ
ድሁበትም ስፍራ ሁሉ ላልተለየኝ አምላክ
(ኤል) መሠዊያ እሠራለሁ::” 4ስለዚህ በእነርሱ
ዘንድ የነበሩትን ባዕዳን አማልክት ሰብስበው፣
የጆሮ ጉትቻቸውን አውልቀው ለያዕቆብ
ሰጡት:: ያዕቆብም ወስዶ ሴኬም አጠገብ
ካለው ወርካ ዛፍ ሥር ቀበራቸው:: 5ያንንም
ቦታ ለቀው ሄዱ፤ እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) በዙ
ሪያቸው በነበሩት ከተሞች ሁሉ ላይ ፍርሀ
ትና ድንጋጤ ስለ ለቀቀባቸው ያሳደዳቸው
አልነበረም::

6ያዕቆብና አብረውት የነበሩት ሰዎች ሁሉ፣
በከነዓን ወደምትገኘው፣ ቤቴል ወደ ተባለ
ችው ወደ ሎዛ ደረሱ:: 7ያዕቆብም በዚያ
ስፍራ መሠዊያ ሠርቶ፣ ስሙን ኤል-ቤቴል[ሀ]
አለው፤ ምክንያቱም ከወንድሙ ሸሽቶ በሄደ
ጊዜ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) የተገለጠለት በዚህ
ቦታ ነበር::

8በዚህ ጊዜ የርብቃ ሞግዚት ዲቦራ ሞተች፤
ከቤቴል ዝቅ ብሎ በሚገኘው የዋርካ ዛፍ
ሥር ተቀበረች:: ከዚህ የተነሣም ያ ቦታ
አሎንባኩት[ለ] ተባለ::

9ያዕቆብ ከሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ
ከተመለሰ በኋላ፣ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ለያዕቆብ
ዳግመኛ ተገለጠለት፤ ባረከውም:: 10እግዚአ
ብሔርም (ኤሎሂም)፣ “እስካሁን ስምህ ያዕቆብ[ሐ]
ነበረ፤ ከእንግዲህ ያዕቆብ ተብለህ አትጠራም፤
ነገር ግን ስምህ እስራኤል[መ] ይባላል”አለው::

[T]27 ወይም እኅታቸው ተደፍራለችና የያዕቆብ ልጆች...
[ሀ]7 ኤል ቤቴል ማለት የቤቴል አምላክ ማለት ነው::
[ለ]8 አሎንባኩት ማለት የለቅሶ ዋርካ ማለት ነው::
[ሐ]10 ያዕቆብ ማለት ተረከዝ ይይዛል ማለት ነው፤ በምሳሌያዊ አገላለጽ ያታልላል ማለት ነው::
[መ]10 እስራኤል ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ታገለ ማለት ነው::

*34፥23፤* የሴኬምን ሰዎች ስለታምኑት ለጥፋት ዳረጋቸው::

*34፥24፤* ከነዓናውያን ያሰቡትን ዐላማ ለማሳካትና፣ ለእስራ ኤል ሕዝብ ለተሰጠው ኪዳን ለመገዛት ፈቃደኞች ነበሩ::

*34፥25 ስምዖንና ሌዊ፤* የሴኬምን ሰዎች ስላረዱ የእነር ሱም ልጆች በየቦታው ተበተኑ (የ49፥7 ማብ ይመ):: *የዲና ወን ድሞች፤* ሦስቱም የልያ ልጆች ናቸው (29፥33-34፤ 30፥21 ይመ):: ወንዶችን ሁሉ አንድ ሳይቀር ገደሏቸው፤ ሴኬም የፈ ጸመው ወንጀል ምን ያህል ከባድ መሆኑን፣ ይህ ጭካኔ የተሞላ በት ብቀላ ያስረዳል (ቍ 27-29 ይመ)::

34፥30 *ፌርዛውያን፤* የ13፥7 ማብ ይመ::

35፥1 *በሸሽህ ጊዜ ለተገለጠልህ አምላክ፤* ቍ 7፤ 28፥13 ይመ::

35፥2 *በእናንተ ዘንድ ያሉትን ባዕዳን አማልክት፤* የ31፥19 ማብ፣ እንዲሁም ኢያ 24፥23 ይመ::

35፥3 *ላልተለየኝ አምላክ፤* የ31፥19 ማብ ይመ:: እንዲ ሁም የ26፥3 ማብ ይመ::

35፥4 *የጆሮ ጉትቻቸውን፤* ከከታብ ወይም ከአሸንክታብ ጋር የሚደረግ ሲሆን፣ ባዕዳን አማልክትን በሚያመልኩ ሕዝቦች ዘንድ እንዲህ ያሉ ነገሮችን በጆሮና በዐንገት ላይ ማድረግ በጣም የተለመደ ነው (ከሆሴ 2፥13 ጋር ያነጻጽሩ):: *ሴኬም አጠገብ ካለው ወርካ፤* የታወቀ ዛፍ ሲሆን ምናልባትም በ12፥6 ላይ ከተጠ ቀሰ ትልቅ ዛፍ ጋር አንድ ሳይሆን አይቀርም (ኢያ 24፥26 ይመ)::

35፥7 *መሠዊያ ሠርቶ፤* የ12፥7 ማብ ይመ::

35፥8 *የርብቃ ሞግዚት ዲቦራ ሞተች፤* ለብዙ ዘመን በታ ማኝነት ካገለገለቻት በኋላ፣ ዲቦራ ሞተች (24፥59 ይመ):: *የዋርካ ዛፍ፤* ይህ የታወቀ ዛፍ ሳይሆን አይቀርም (የቍ 4 ማብ ይመ)፤ እንዲሁም በ1ሳሙ 10፥3 ላይ “ትልቅ ዛፍ” ተብሎ ከተጠ ቀሰው ጋር አንድ ሳይሆን አይቀርም:: *ሥር፤* ከዛፉ በታች ወይም ከዛፉ በስተ ደቡብ ማለት ነው::

35፥9 *መስጴጦምያ፤* የ24፥10 ማብ ይመ::

35፥10 *ያዕቆብ... እስራኤል፤* ቀደም ሲል የተሰጠው አዲስ ስም (32፥28 ይመ) በዚህ ቦታ ጸና:: በዚህ ጉዳይ ላይ ተመሳሳይ

ስለዚህም እስራኤል ብሎ ጠራው::
11ደግሞም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ያዕቆብን እን
ዲህ አለው፤ "እኔ ሁሉን ማድረግ የሚችል[ሠ]
አምላክ ነኝ፤ ብዛ ተባዛ፤ ሕዝብና የሕዝቦች
ማኅበር ከአንተ ይወጣሉ፤ ነገሥታትም ከአ
ብራክህ ይከፈላሉ:: 12ለአብርሃምና ለይስሐቅ
የሰጠኋትን ምድር ለአንተ እሰጥሃለሁ፤ ከአ
ንተም በኋላ ይህችኑ ምድር ለዘርህ እሰጣ
ለሁ::" 13እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ከእርሱ ጋር
ከተነጋገረበት ስፍራ ወደ ላይ ወጣ::
14ያዕቆብ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከእርሱ ጋር
በተነጋገረበት ስፍራ የድንጋይ ሐውልት አቆመ፤
በሐውልቱ ላይ የመጠጥ ቍርባን አፈሰሰ፤
ዘይትም አፈሰሰበት:: 15ያዕቆብም፣ እግዚአ
ብሔር (ኤሎሂም) ከእርሱ ጋር የተነጋገረበትን
ስፍራ ቤቴል[ረ] ብሎ ጠራው::

## የራሔልና የይስሐቅ መሞት

35፥23-26 ተጓ ማብ - 1ዜና 2፥1-2

16ከዚያም ከቤቴል ተነሥተው ሄዱ፤ ኤፍ
ራታ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው ራሔልን
ምጥ ያዛት፤ ምጡም ጠናባት:: 17ምጡ እስ
ጨንቆአት ሳለ፣ አዋላጇ፣ "አይዞሽ አትፍሪ፤
ሌላ ወንድ ልጅ ልትገላገይ ነው" አለቻት::
18እርሷ ግን ሕይወቷ ልታልፍ በማጣጣር
ላይ ሳለች፣ ልጇን ቤንኦኒ[ሰ] አለችው፤ አባቱ
ግን ብንያም[ሸ] አለው::
19ራሔልም ሞተች፤ ወደ ኤፍራታ በሚወ
ስደው መንገድ በቤተልሔም ተቀበረች::
20ያዕቆብም በራሔል መቃብር ላይ ሐው
ልት አቆመ፤ እስከዛሬም የራሔል መቃብር
ምልክት ይኸው ሐውልት ነው::
21እስራኤልም ጕዞውን በመቀጠል ከጋ
ዴር ወንዝ ባሻገር ድንኳኑን ተከለ:: 22እስራ
ኤልም በዚያ ምድር ሳለ፣ ሮቤል ከአባቱ
ቁባት ከባላ ጋር ተኛ፤ እስራኤልም ድርጊ
ቱን ሰማ::

ያዕቆብ ዐሥራ ሁለት ልጆች ነበሩት፤ እነ
ርሱም:-
23የልያ ልጆች:-
የያዕቆብ የበኵር ልጅ ሮቤል፣
ስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣ ይሳኮር፣
ዛብሎን፤
24የራሔል ልጆች:-
ዮሴፍ፣ ብንያም፤
25የራሔል አገልጋይ የባላ ልጆች:-
ዳን፣ ንፍታሌም፤
26የልያ አገልጋይ የዘለፋ ልጆች:-
ጋድ፣ አሴር ናቸው::
እነዚህ ያዕቆብ በሰሜን ምዕራብ መስጴ
ጦምያ ሳለ የተወለዱለት ወንዶች ልጆች
ነበሩ::
27ያዕቆብ አባቱ ወዳለበት ወደ መምሬ
መጣ፤ አብርሃምና ይስሐቅ የኖሩባት፣ ቂር
ያትአርባቅ ወይም ኬብሮን የተባለችው ቦታ
ናት:: 28ይስሐቅ መቶ ሰማንያ ዓመት ኖረ፤
29አርጅቶ፣ ዕድሜ ጠግቦ ሞተ፤ ወደ ወገ
ኖቹ ተሰበሰበ፤ ልጆቹም ዔሳውና ያዕቆብ
ቀበሩት::

## የዔሳው ዝርያዎች

36፥10-14 ተጓ ማብ - 1ዜና 1፥35-37
36፥20-28 ተጓ ማብ - 1ዜና 1፥38-42

36 ኤዶም የተባለው የዔሳው ትውልድ
ይህ ነው:-

35፥12 ዘፍ12፥7፤ 15፥7፤28፥13
35፥13 ዘፍ17፥22
35፥14 ዘፍ28፥18፡ 22፤ዘፀ29፥40፤ዘሌ23፥13፤ዘኍ6፥15:17፤15፥5፤28፥7:14፤2ሳሙ23፥16፤2ዜና29፥35
35፥15 ዘፍ12፥8
35፥16 ቍ19፤ዘፍ29፥6፤48፥7፤ሩት1፥2፤4፥11፤1ሳሙ17፥12፤ሚክ5፥2
35፥17 ዘፍ30፥24፤ 38፥28፤ዘፀ1፥15
35፥18 ቍ24፤ዘፍ42፥4፤43፥16:29፤45፥12:14፤49፥27፤ዘኍ1፥36፤ዘዳ33፥12፤ 1ሳሙ4፥21፤14፥3
35፥19 ቍ16፤ዘፍ48፥7፤ኢሱ19፥15፤መሳ12፥8፤17፥7፤19፥1:18፤ሩት1፥1:19፤ 1ሳሙ17፥12፤ሚክ5፥2
35፥20 ኢሱ4፥9፤ 7፥26፤8፥28፤10፥27፤ 1ሳሙ6፥18፤10፥2
35፥21 ኢሱ15፥21
35፥22 ዘፍ22፥24፤ 29፥29፤34፥5፤ዘሌ18፥8
35፥23 ዘፍ29፥16፤ 43፥33፤46፥8፤29፥35፤30፥20
35፥24 ቍ18፤ ዘፍ30፥24
35፥25 ዘፍ30፥8፤ 37፥2
35፥26 ዘፍ25፥20፤ 30፥11:13፤34፥30፤ 37፥2፤ዘፀ1፥1-4
35፥27 ዘፍ13፥18፤ 17፥8፤23፥2፤31፥18፤ ኢሱ15፥54፤
36፥2 ቍ14:18፡ መሳ1፥10፤ነህ11፥25 35፥28 ዘፍ25፥7:20 35፥29 ዘፍ15፥15፤ 23፥20፤25፥8:9 36፥1 ዘፍ2፥4፤ 25፥30

ሠ11 በዕብራይስጥ *ኤልሻዳይ* ማለት ነው::
ረ15 *ቤቴል* ማለት *የእግዚአብሔር ቤት* ማለት ነው::
ሰ18 *ቤንኦኒ* ማለት *የመከራዬ ልጅ* ማለት ነው::
ሸ18 *ብንያም* ማለት *የቀኜ ልጅ* ማለት ነው::

ምሳሌዎችን ለማየት 2፥31ን ከ26፥33 ጋር፤ 28፥19ን ከ35፥15 ጋር ያነጻጽሩ::

*35፥11-12፤* ይህ ድርጊት የይስሐቅ-ያዕቆብን ዑደት ከመጨረሻው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲያደርሰው ይታያል (በዘፍጥረት መግቢያ ሥነ ጽሑፋዊ ገጽታ የሚለውን ይመ):: በመጨረሻ ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት መነጋገር/መገናኘት ወደ ጀመረበት ወደ ቤቴል ተመለሰ፤ እግዚአብሔርም ለአብርሃም ገብቶለት የነበረውን ቃል ኪዳን አደሰለት (17፥1-8፤ 28፥3 ይመ):: ይህም ኪዳን ለመጀመሪያው ሰው ተሰጥቶ የነበረውንና (1፥28) ከጥፋት ውሃ በኋላ የታደሰውን የእግዚአብሔርን ቡራኬ (9፥1:7) የሚያስታውስ ነው:: እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው በረከት በያዕቆብና በዘሩ በኩል ይፈጸማል፤ 47፥27፤ ዘፀ 1፥7 ይመ::

*35፥13፤* የ17፥22 ማብ ይመ::

*35፥14፤* 28፥18 እና ማብ ይመ:: ***የመጠጥ ቍርባን፤*** ለአምላክ እንደ መሥዋዕት የሚቀርብ ፈሳሽ ነው::

*35፥15፤* 28፥19 እንዲሁም የቍ 10 ማብ ይመ::

35፥16 ***ኤፍራታ፤*** በይሁዳ የምትገኘው (ሩት 1፥2፤ ሚክ 5፥2 ይመ) ቤተልሔም፣ ቀድሞ በዚህ ስም ትጠራ ነበር (ቍ 19 ይመ)::

35፥17 ***ሌላ ወንድ ልጅ፤*** ዮሴፍ በተወለደ ጊዜ ራሔል ያቀረበችውን ጥያቄ የሚያስታውስ ነው (30፥24 ይመ)::

*35፥18* ***ብንያም፤*** የስሙ ትርጕም "የቀኝ እጅ ልጅ" ማለት ሲሆን፣ "የደቡብ ልጅ" የሚል ትርጕምም አለው፤ ይህም በሰሜን የተወለዱትን ሌሎች ልጆች ለመለየት የተደረገ ነው:: የጥንት ዕብራውያን አቅጣጫን የሚለዩት ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ በማዞር ነበር፤ በዚህ ጊዜ ደቡብ በስተ ቀኝ ይውላል::

35፥19 ***ራሔል ሞተች፤*** ራሔል የሞተችው በወሊድ ምክንያት ነው (የ30፥1 ማብ ይመ)::

35፥20 ***የራሔል መቃብር፤*** 1ሳሙ 10፥2 ይመ:: ምንም እንኳ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ባይቻልም፣ የራሔል መቃብር በዘልማድ በቤተልሔም አቅራቢያ እንደሚገኝ ይነገራል::

35፥21 ***ጋዴር፤*** የስሙ ትርጕም "የከብቶች ግንብ" ማለት ሲሆን፣ ሌቦች ገብተው በጎችን ወይም ሌሎች የቤት እንስሳትን እንዳይሰርቁ ለመከላከል ከግንብ የተሠራ የከብቶች በረት ወይም ጕረኖ ነው (2ዜና 26፥10 ይመ):: ይኸው የዕብራይስጥ ሐረግ በሚክ 4፥8 ላይ ተምሳሌታዊ ፍቺ ይዞ የገባ ሲሆን፣ በዚያ ጽሑፍ ላይ "መንጋ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የይሁዳን ሕዝብ ነው (ሚክ 4፥6-7 ይመ)::

*35፥22፤* የሮቤል ድርጊት አጸያፊ ከመሆኑም በላይ፣ የብኵርናው መብት የሚገባው ለእኔ ስለሆነ የአባቴን ቁባቶች እወርሳለሁ ብሎ የፈጸመው ተግባር ያለ ጊዜው የተፈጸመ መጥፎ ሥራ ነበር፤ በዚህም ምክንያት ለብኵርና የሚያበቃውን ሕጋዊ መብት አጣ:: (49፥3-4፤ 1ዜና 5፥1 እንዲሁም የ37፥21 ማብ ይመ)::

35፥26 ***መስጴጦምያ ሳለ የተወለዱለት ወንዶች ልጆች፤*** ብንያም በከነዓን ከተወለደ በኋላ ስለ ሁኔታው የተሰጠ የማጠቃለያ ቃል እንደ ሆነ ግልጽ ነው (ቍ 16-18 ይመ)::

35፥27 ***መምሬ... ቂርያትአርባቅ ወይም ኬብሮን፤*** የ13፥18፤ የ23፥2 ማብ ይመ::

*35፥29፤* የ25፥8 ማብ ይመ:: ***ቀበሩት፤*** በማክጴላ ዋሻ ውስጥ በሚገኘው በአባቶቹ መቃብር ቀበሩት (49፥30-31)::

36፥1 ***ትውልድ፤*** የ2፥4 ማብ ይመ:: ምንም እንኳ ይህ ሐረግ በቍ 9 ላይ ቢደገምም፣ ሐረጉ ግን ሌላ አዲስ/ዐቢይ ክፍል መጀመሩን አያመለክትም፤ ምክንያቱም በቍ 9-43 ላይ ያለው ሐሳብ በቍ 1-8 ላይ ያለውን ሐሳብ ይበልጥ የሚያብራራ ነው:: ***ኤዶም የተባለው የዔሳው፤*** የ25፥30 ማብ ይመ:: ከሙት ባሕር

2ዔሳው ከከነዓን ሴቶች አገባ፤ እነርሱም:-
የኬጢያዊው የዔሎን ልጅ ዓዳን፣ የኤዊያ
ዊው የፅብዖን ልጅ ዓና የወለዳት አህሊባማ፣
3እንዲሁም የነባዮት እኅት የሆነችው የእስ
ማኤል ልጅ ቤሴሞት ነበሩ::
4ዓዳ ለዔሳው ኤልፋዝን ወለደችለት፤ ቤሴ
ሞት ደግሞ ራጉኤልን ወለደችለት:: 5እን
ደዚሁም አህሊባማ የዑስን፣ የዕላምንና ቆሬን
ወለደችለት፤ እነዚህ ዔሳው በከነዓን አገር
የወለዳቸው ልጆች ናቸው::
6ዔሳው ሚስቶቹን፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆ
ቹን፣ ቤተ ሰቦቹን በሙሉ እንደዚሁም የቀ
ንድ ከብቶቹንና ሌሎቹንም እንስሳት ሁሉ
በከነዓን ምድር ያፈራው ሀብት እንዳለ ይዞ
ከወንድሙ ከያዕቆብ ራቅ ወዳለ ቦታ ሄደ::
7ብዙ ሀብት ስለነበራቸው አብረው መኖር
አልቻሉም፤ የነበሩበትም ስፍራ ከከብቶቻ
ቸው ብዛት የተነሣ ሊበቃቸው አልቻለም::
8ስለዚህ ኤዶም የተባለው ዔሳው መኖሪያ
ውን በተራራማው አገር በሴይር አደረገ::
9በሴይር ተራራማ አገር የሚኖሩ የኤዶ
ማውያን አባት፣ የዔሳው ዝርያዎች እነዚህ
ናቸው፤
10የዔሳው ልጆች ስም:-
የዔሳው ሚስት የዓዳ ልጅ ኤልፋዝና
የዔሳው ሚስት የቤሴሞት ልጅ ራጉኤል፤
11የኤልፋዝ ልጆች:-
ቴማን፣ ኦማር፣ ስፎ፣ ጎቶምና ቄኔዝ፤
12የዔሳው ልጅ ኤልፋዝ ትምናዕ የም
ትባል ቁባት ነበረችው፤ እርሷም አማ
ሌቅን ወለደችለት፤ የዔሳው ሚስት
የዓዳ የልጅ ልጆች እነዚህ ናቸው::
13የራጉኤል ልጆች:-
ናሖት፣ ዛራ፣ ሣማና ሚዛህ፤ እነዚህ
ደግሞ የዔሳው ሚስት የቤሴሞት የልጅ
ልጆች ናቸው::
14የፅብዖን የልጅ ልጅ፣ የዓና ልጅ የዔ
ሳው ሚስት አህሊባማ ለዔሳው የወለ
ደቻቸው ልጆች:-
የዑስ፣ የዕላማና ቆሬ፤
15ከዔሳው ዝርያዎች እነዚህ የነገድ አለ
ቆች ነበሩ፤
የዔሳው የበኵር ልጅ የኤልፋዝ ልጆች:-
አለቃ ቴማን፣ አለቃ ኦማር፣ አለቃ
ስፎ፣ አለቃ ቄኔዝ፣ 16አለቃ ቆሬ፣+
አለቃ ጎቶምና አለቃ አማሌቅ፤ እነ
ዚህ በኤዶም ምድር ከኤልፋዝ የተ
ገኙ የነገድ አለቆች፣ የዓዳ የልጅ
ልጆች ነበሩ::
17የዔሳው ልጅ ራጉኤል ልጆች:-
አለቃ ናሖት፣ አለቃ ዛራ፣ አለቃ
ሣማና አለቃ ሚዛህ፤ እነዚህ በኤዶም
ምድር ከራጉኤል የተገኙ የነገድ አለ
ቆች፣ የዔሳው ሚስት የቤሴሞት
የልጅ ልጅ ነበሩ::
18የዔሳው ሚስት የአህሊባም ልጆች:-
አለቃ የዑስ፣ አለቃ የዕላማና፣ አለቃ
ቆሬ፤ እነዚህ ከዓና ልጅ፣ ከዔሳው
ሚስት ከአህሊባማ የተገኙ የነገድ አለ
ቆች ነበሩ:: 19እነዚህም ኤዶም የተባ
ለው የዔሳው ልጆችና የነገድ አለቆ
ቻቸው ነበሩ::
20በዚያች ምድር ይኖሩ የነበሩ የሖሪው
የሴይር ልጆች እነዚህ ነበሩ:-
ሎጣን፣ ሦባል፣ ፅብዖን፣ ዓና፣ 21ዲሶን፣
ኤጽርና ዲሳን፤ እነዚህ በኤዶም የነ
በረው የሴይር ልጆች፣ የሖሪውያን
የነገድ አለቆች ነበሩ::
22የሎጣን ልጆች:-
ሖሪና ሔማም፤° የሎጣንም እኅት ቲምናዕ
ትባል ነበር::
23የሦባል ልጆች:-
ዓልዋን፣ ማኔሐት፣ ዔባል፣ ስፎና አው
ናም፤
24የፅብዖን ልጆች:-
አያና ዓና፤ ይህ ዓና የአባቱን የፅብ
ዖንን አህዮች ሲጠብቅ፣ የፍል ውሃ
ምንጮችን+ በምድረ በዳ ያገኘ ሰው
ነው::
25የዓና ልጆች:-
ዲሶንና የዓና ሴት ልጅ አህሊባማ፤
26የዲሶን* ልጆች:-
ሔምዳን፣ ኤስባን፣ ይትራንና ክራን፤
27የኤጽር ልጆች:-
ቢልሐን፣ ዛዕዋንና ዓቃን፤

24:25፤ዘፍ10፥17፤
26፥34፤28፥8-9፤
1ዜና1፥40
36፥3 ቊ4:10:13:
17፤ዘፍ25፥13
36፥4 ቊ3፤1ዜና
1፥35
36፥5 ቊ14:18፤
1ዜና1፥35
36፥6 ዘፍ12፥5፤
27፥39
36፥7 ዘፍ13፥6
36፥8 ዘፍ14፥6፤25፥
30፤ዘዳ2፥4
36፥9 ቊ1:43፤
ዘፍ2፥4
36፥10 ቊ3
36፥11 ቊ15-16፤
1ዜና1፥45፤ኢዮ2፥11
፤4፥1፤ኤር49፥7:20፤
ሕዝ25፥13፤አሞ1፥
12፤አብ1፥9፤ዕን3፥3
36፥12 ቊ16፤ዘፍ
22፥24፤ዘፀ17፥8:16፤
ዘኁ24፥20፤ዘዳ25፥17
:19፤1ሳሙ15፥2፤
27፥8
36፥13 ቊ3
36፥14 ቊ2:5
36፥15 ቊ11:19:
40፤ዘፀ15፥15፤ኢዮ
2፥11፤ኤር49፥7፤ሕዝ
25፥13፤አሞ1፥12፤
ዕን3፥3
36፥16 ቊ11:12፤
ዘፍ32፥3፤ዘፀ15፥15፤
ዘኁ20፥14፤33፥37
36፥17 ቊ3፤1ዜና
1፥37
36፥18 ቊ2:5
36፥19 ቊ15፤ዘፍ
25፥30፤1ዜና1፥35
36፥20 ቊ29፤ዘፍ
14፥6
36፥21 ቊ30
36፥24 ቊ2፤ኢሱ
15፥19፤ኢዮ1፥14
36፥25 ቊ2
36፥29 ቊ20
36፥30 ቊ21

+16 ከማሶሬቲኩ ጽሑፍ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን በአሪተ ሳምራ ውያን ግን ( በተጨማሪ ዘፍ 36፥11 እና 1ዜና 1፥36 ይመ) ውስጥ "ቆሬ" የሚለው ቃል የለም
°22 ሔማም የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ሖማም ለሚለው ቃል አማራጭ ትርጒም ነው (1ዜና 1፥39 ይመ)::
+24 ከቩልጌት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ሱርስቱ ግን የተገኘ ውሃ ይለዋል፤ በዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጒም አይታወቅም::
*26 በዕብራይስጥ ዲሳን፣ የዲሶን አማራጭ ትርጒም ነው::

በስተ ደቡብና በስተ ምሥራቅ በሚገኘው የኤዶማውያን ምድር፣ ቀላ ያለ ዐለት ያለበትና በተለይም የአሸዋ ድንጋይ በብዛት የሚ ታይበት ምድር ነው::

*36፥2-3፤* የ26፥34 ማብ ይመ::

*36፥7፤* 13፥6 እንዲሁም 26፥20 እና ማብ ይመ::

36፥8 *በሴይር፤* የኤዶም ሌላ ስም ነው:: ቃሉ "ጠጕር" የሚል ትርጒም ካለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር የሚዛመድ ሲሆን "ዔሳው" ማለትም ሊሆን ይችላል:: የዔሳው ዘሮች በሴይር ይኖሩ የነበሩትን የመጀመሪያዎቹን ሖራውያንን (ቊ 20 ይመ) ማሳደድ ነበረባቸው (14፥6 እና ማብ ይመ):: የሴይር የዘር ሐረግ ስም በቊ 20-28 ተዘርዝሯል::

*36፥10-14፤* ይኸው የዔሳው የዘር ሐረግ የስም ዝርዝር (1ዜና 1፥35-37 ይመ)፣ እንደ ነገድ አለቆች ዝርዝር ሆኖ በቊ 15-19 ላይ በድጋሚ ቀርቦአል::

36፥11 *ኤልፋዝ... ቴማን፤* ከኢዮብ ወዳጆች አንዱ ቴማናዊው ኤልፋዝ ተብሎአል (ኢዮ 2፥11)፤ ኢዮብ ደግሞ የዖፅ አገር ሰው ነበር (ኢዮ 1፥1):: በዚህ ዐይነት ኢዮብ የኤዶም ነዋሪ የነበረ ሊሆን ይችላል (ቊ 28:34 ይመ)::

36፥12 *አማሌቅ፤* የ14፥7 ማብ ይመ::

*36፥20-28፤* የቊ 8 ማብ ይመ:: ይኸው የሴይር ዝርያዎች የስም ዝርዝር (1ዜና 1፥38-42 ይመ)፣ እንደ ነገድ አለቆች ዝርዝር ሆኖ በቊ 29-30 ላይ በአጭሩ ተደግሞአል::

36፥24 *ዓና የአባቱን፤* ይህ በቊ 2:14:18 ላይ ከተጠቀሰው ዓና የሚለይ ነው፤ በቊ 25 ላይ ግን ሁለቱም ሰዎች ተጠቅሰዋል::

28የዲሳን ልጆች:-
ዑፅና አራን::
29የሖሪውያን የነገድ አለቆች እነዚህ ነበሩ:-
ሎጣን፣ ሦባል፣ ፅብዖን፣ ዓና፣ 30ዲሶን፣
ኤጽርና ዲሳን፤ እነዚህ በሴይር ምድር
እንደየነገዳቸው የሖሪውያን የነገድ አለ
ቆች ነበሩ::

## የኤዶም ነገሥታት

36፥31-43 ተጓ ማብ - 1ዜና 1፥43-54

31ንጉሥ በእስራኤል ከመንገሡ በፊት፣[ን]
በኤዶም የነገሡ ነገሥታት እነዚህ ነበሩ:-
32የቢዖር ልጅ ባላቅ በኤዶም ነበር፤ የከተ
ማውም ስም ዲንሃባ ይባል ነበር::
33ባላቅ ሲሞት፣ የባሶራው የዛራ ልጅ ኢዮ
ባብ በምትኩ ነገሠ::
34ኢዮባብ ሲሞት፣ የቴማኒው ሑሳም በም
ትኩ ነገሠ::
35ሑሳም ሲሞት፣ የምድያምን ሰዎች በሞዓብ
ምድር ድል ያደረጋቸው የባዳድ ልጅ ሃዳድ
በምትኩ ነገሠ፤ የከተማውም ስም ዓዊት
ይባል ነበር::
36ሃዳድ ሲሞት፣ የመሥሬቃው ሠምላ በም
ትኩ ነገሠ::
37ሠምላ ሲሞት፣ በወንዙ[ነ] አጠገብ ያለው
የርሆቦቱ ሳኡል በምትኩ ነገሠ::
38ሳኡል ሲሞት፣ የዓክቦር ልጅ በኣልሐናን
በምትኩ ነገሠ::
39የዓክቦር ልጅ በኣልሐናን ሲሞት፣ ሃዳር
በምትኩ ነገሠ፤ የከተማውም ስም ፋው ይባል
ነበር፤ የሚስቱም ስም መሄጣብኤል ሲሆን፣
እርሷም የሜዛሃብ ልጅ መጥሬድ የወለደ
ቻት ነበረች::
40ከዔሳው የተገኙት የነገድ አለቆች ስም፣
እንደየነገዳቸውና እንደየአገራቸው ይህ ነው:-
ቲምናዕ፣ ዓልዋ፣ የቴት፣ 41አህሊባማ፣
ኤላ፣ ፊኖን፣ 42ቄኔዝ፣ ቴማን፣ ሚብ

36፥31 ዘፍ17፥6
36፥33 ኢሳ34፥6፤
63፥1፤ኤር49፥13:22
36፥34 ኤር49፥
7፤ሕዝ25፥13፤አብ
1፥9
36፥35 ዘፍ19፥37፤
25፥2፤ዘኍ21፥11፤
22፥1፤ዘዳ1፥5፤መሳ
3፥30፤ሩት1፥1:6
36፥37 ዘፍ26፥22
36፥40 ቍ15
36፥43 ቍ9
37፥1 ዘፍ10፥19፤
17፥8
37፥2 ዘፍ2፥4፤30፥
24፤35፥25:26፤41፥
46፤46፥32፤1ሳሙ
2፥24፤16፥11፤17፥
15፤2ሳሙ5፥4፤መዝ
78፥71፤አሞ7፥15
37፥3 ቍ23:31:
32፤ዘፍ17፥5፤25፥28፤
43፥27:34፤44፥20፤
45፥22፤1ሳሙ1፥4-5፤
2ሳሙ13፥18-19፤
አስ2፥9
37፥4 ቍ24፤ዘፍ
27፥41፤ሐሥ7፥9
37፥5 ቍ8:10፤
ዘፍ20፥3፤28፥12
37፥7 ቍ9:10፤
ዘፍ27፥29፤42፥6:9፤
43፥26:28፤44፥14፤
50፥18፤ሩት2፥7:15፤
2ሳሙ1፥2፤9፥6
37፥8 ቍ5፤ዘፍ41፥
44፤42፥10፤44፥16:
18፤48፥22፤49፥26፤
ዘዳ33፥16
37፥9 ቍ7፤ዘፍ
28፥12፤ዘዳ4፥19፤
17፥3፤ራእ12፥1

ሳር፣ 43መግዲኤልና ዒራም፤ እነዚህ፣
በያዙት ምድር እንደየይዞታቸው ከኤ
ዶም የተገኙ የነገድ አለቆች ነበሩ::
ይህም ዔሳው፣ የኤዶማውያን አባት ነው::

## የዮሴፍ ሕልሞች

37 ያዕቆብ አባቱ በኖረበት በከነዓን ምድር
ተቀመጠ:: 2የያዕቆብ ትውልድ ታሪክ
ይህ ነው::
ዮሴፍ የዐሥራ ሰባት ዓመት ወጣት በነ
በረ ጊዜ፣ ከአባቱ ሚስቶች ከባላና ከዘለፋ
ከተወለዱት ወንድሞቹ ጋር የአባቱን በጎ
ችና ፍየሎች ይጠብቅ ነበር:: እርሱም ስለ
ወንድሞቹ ድርጊት ለአባቱ መጥፎ ወሬ
ይዞለት መጣ::
3እስራኤል ዮሴፍን በስተርጅናው ስለ ወለ
ደው፣ ከልጆቹ ሁሉ አብልጦ ይወደው ነበር፤
በኅብረ ቀለማት ያጌጠ[ን] እጀ ጠባብም አደ
ረገለት:: 4ወንድሞቹም፣ አባታቸው ከእነ
ርሱ አብልጦ የሚወደው መሆኑን ሲያዩ፣
ዮሴፍን ጠሉት፤ በቅን አንደበትም ሊያናግሩት
አልቻሉም::
5ዮሴፍም ሕልም አለመ፤ ሕልሙንም ለወ
ንድሞቹ ሲነግራቸው የባሰ ጠሉት:: 6እር
ሱም እንዲህ አላቸው፤ "ያየሁትን ሕልም
ልንገራችሁ አድምጡኝ 7እኛ ሁላችን በዕ
ርሻ ውስጥ ነዶ እናስር ነበር፤ የእኔ ነዶ በድ
ንገት ተነሥታ ቀጥ ብላ ቆመች፤ የእናን
ተም ነዶዎች ዙሪያዋን ከበው ለእኔ ነዶ
ሰገዱላት::"
8ወንድሞቹም፣ "ለካስ በላያችን ለመንገሥ
ታስባለህና! ለመሆኑ አንተ እኛን ልትገዛ!"
አሉት፤ ስለ ሕልሙና ስለ ተናገረው ቃል
ከፊት ይልቅ ጠሉት::

[ን]31 ወይም *እስራኤላዊ መንግሥት በእነርሱ ላይ ከመንገሡ በፊት*
[ነ]37 የኤፍራጥስ ወንዝ ሊሆን ይችላል
[ን]3 በዕብራይስጥ *በኅብረ ቀለማት ያጌጠ* የሚለው ሐረግ ትር
ጒም አይታወቅም፤ በቍ 23 እና 32 ላይ ያለውም እንዲሁ

36፥31 *ንጉሥ በእስራኤል ከመንገሡ በፊት፤* ከጊዜ በኋላ የሚመጣውን የእስራኤልን ንጉሣዊ አገዛዝ የሚያገናዝብና ከሙሴ ዘመን በኋላ ካለው ሁኔታ ጋር እንዲስማማ የሚያደርግ የአርታኢ ማስተካከያ ነው (የ14፥14 ማብ ይመ)::

36፥43 *እነዚህ... ከኤዶም፤* (ቍ 1 የምዕራፉ ርእስ እንደ ሆነ ሁሉ) ይህም ሐረግ የምዕራፉን አጠቃላይ ሐሳብ የሚያስር ነው::

37፥1 *በከነዓን፤* ያዕቆብ የተስፋይቱን ምድር መኖሪያው አደረገ፤ በኋላም በዚያው ተቀበረ (49፥29-30፤ 50፥13):: ልጁ ዮሴፍም እግዚአብሔር ምድሪቱን ለእስራኤል እንደ ሰጠ (50፥24-25) ስላስተዋለ በከነዓን እንዲቀብሩት አጥብቆ ለመነ:: ስለ ያዕቆብና ዮሴፍ ዑደት፣ (በመጽሐፉ መግቢያ ላይ "ሥነ ጽሑፋዊ ገጽታ" የሚለውን ይመ) የሚጀምረውና የሚጨርሰው የተስፋይቱን ምድር በመጥቀስ ነው::

37፥2 *ታሪክ፤* የ2፥4 ማብ ይመ:: ይህ ቃል የዘፍጥረትን መጽሐፍ የያዘውን ዐሥረኛውንና የመጨረሻውን ዋና ክፍል ያስተዋውቃል:: *ዮሴፍ፤* የመጽሐፉ ጸሓፊ ዮሴፍንና የእስራኤል አባቶች ታሪክ ያማከለበትን ዑደት በማስተዋወቅ ይጀምራል:: ከማንም ይልቅ ዮሴፍ በኖረበት ዘመንና ትውልድ እስራኤልን ወክሎ የኖረ ሰው ነው:: የእስራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር ታግሎ ያሸነፈና (የ32፥28 ማብ ይመ) ለምድር ሕዝቦች ሁሉ የበረከት ምንጭ የሆነ ሕዝብ ነው (12፥2-3 ይመ):: ከዚህ ሁሉ በላይ ግን በከነዓን ምድር ይኖር የነበረው የቃል ኪዳን ቤተ ሰብ በግብፅ ምድር ታዋቂ ሊሆን የቻለው፣ በዮሴፍ ሕይወት ምክንያት ነው፤ ይኸውም ከግብፅ ምድር ለመውጣት መሠረትን የጣለ በመሆኑ ነው:: እግዚአብሔር በእስራኤል አባቶች ሕይወት ውስጥ ያደርግ የነበረው ቀጥተኛ ተሳትፎ ለእስራኤል ሕዝብ ያለውን ዐላማ አስቀድሞ የሚያመለክት ነው:: እግዚአብሔር በሕዝቡ ታሪክ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማድረግ የጀመረው፣ በቅድመ ባቤል ከነበረው ሕዝብ መካከል አብራምን በመምረጥና በመጥራት ሲሆን የተጠናቀቀው ደግሞ በግብፅ የሕዝቡን ማለትም የእስራኤልን ሕይወት (ህልውና) (በዮሴፍ አማካይነት) ከጥፋት በመጠበቅ ነው (41፥57፤ 50፥20 ይመ):: እንግዲህ እግዚአብሔር እስራኤልን ከሕዝቦች መካከል ከታገደ (ዘፀአት) በኋላ፣ ለሕዝቦች መዳን ምክንያት ይሆኑ ዘንድ መልሶ ይልካቸዋል (ከማቴ 28፥18-20፤ ከሐሥ 1፥8 ጋር ያነጻጽሩ):: *መጥፎ ወሬ ይዞለት መጣ፤* የአባቱ ቍባቶች ልጆቻቸው የፈጸሙበትን በደል ብቻ ሳይሆን፣ (ከዚህ በታች ያለው ክፍል/ዐውደ ምንባብ እንደሚያመለክተው) ወንድሞቹ ሁሉ የፈጸሙበትን በደል ጭምር እንደ ሆነ ምንም ጥርጥር የለውም::

37፥3 *በኅብረ ቀለማት ያጌጠ እጀ ጠባብም፤* ያዕቆብ ለዮሴፍ ያለውን ልዩ ፍቅር ያመለክታል፤ "እንዲህ ያለውን ልብስ የንጉሥ ደናግል ልጆች ይለብሱ ነበር" (2ሳሙ 13፥18)::

37፥5 *ሕልም፤* የ20፥3 ማብ ይመ::

37፥7 *ሰገዱላት፤* የዮሴፍ ሕልም ከጥቂት ዓመታት በኋላ እውን እንደሚሆን ያመለክታል ይሆናል፤ (42፥6፤ 43፥26፤ 44፥14 ይመ)::

37፥8 *ለመሆኑ፣ አንተ እኛን ልትገዛ፤* ዮሴፍ ከጥቂት ጊዜ በኋላ "በወንድሞቹ መካከል መሪ" (ዘዳ 33፥16) በመሆን "የብኵርናውን መብት" (1ዜና 5፥2) ቢያንስ በሁለት ዕጥፍ ይቀበላል (የ25፥5 ማብ ይመ)፤ ምክንያቱም አባቱ ሁለት ወንዶች ልጆቹን እንደ ራሱ ልጆች አድርጐ ወስዶአቸዋል (48፥5)::

9እንደ ገናም ሌላ ሕልም አለመ፤ ለወን
ድሞቹም፣ "እነሆ፤ ሌላ ሕልም አለምሁ፤ ፀሐ
ይና ጨረቃ፣ ዐሥራ አንድ ከዋክብትም ሲሰ
ግዱልኝ አየሁ" ብሎ ነገራቸው::
10ሕልሙን ለአባቱና ለወንድሞቹ በነገራ
ቸው ጊዜ፣ አባቱ "ይህ ያየኸው ሕልም ምን
ድን ነው? እኔና እናትህ ወንድሞችህም በፊትህ
ወደ ምድር ተጐንብሰን በእርግጥ ልንሰግድ
ልህ ነው?" ሲል ገሠጸው:: 11ወንድሞቹ
ቀኑበት፤ አባቱ ግን ነገሩን በልቡ ያዘው::

## ወንድሞቹ ዮሴፍን ሸጡት

12ከዚህም በኋላ የዮሴፍ ወንድሞች የአባ
ታቸውን በጎችና ፍየሎች ለማሰማራት ወደ
ሴኬም አካባቢ ሄዱ፤ 13እስራኤልም ዮሴፍን
"እንደምታውቀው ወንድሞችህ መንጎቹን
በሴኬም አካባቢ አሰማርተዋል፤ በል ተነሥ፣
ወደ እነርሱ ልላክህ::" አለው::
ዮሴፍም "ይሁን እሺ" አለው::
14ያዕቆብም፣ "ሄደህ ወንድሞችህም፣ መንጎ
ቹም ደኅና መሆናቸውን አይተህ ወሬያቸ
ውን አምጣልኝ" አለው፤ ከኬብሮንም ሸለቆ
ወደ ሴኬም ላከው::
ዮሴፍም ሴኬም በደረሰ ጊዜ፣ 15ሜዳ ላይ
ወዲያ ወዲህ ሲባዝን አንድ ሰው አግኝቶት
"ምን እየፈለግህ ነው?" ሲል ጠየቀው::
16ዮሴፍም፣ "ወንድሞቼን እየፈለግኋቸው
ነው፤ መንጎቻቸውን የት እንዳሰማሩ ልትነ
ግረኝ ትችላለህ?" አለው::
17ሰውየውም፣ "ከዚህ ሄደዋል፤ ደግሞም፣
'ወደ ዶታይን እንሂድ' ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ"
አለው::
ከዚያም ዮሴፍ ወንድሞቹን ፍለጋ ሄደ፣
ዶታይን አቅራቢያም አገኛቸው:: 18ወንድሞ
ቹም ዮሴፍ ወደ እነርሱ ሲመጣ በሩቅ

37፥10 ቊ5:7፤ ዘፍ9፥25፤33፥3፤ሩት 2፥16፤መዝ9፥5፤68፥30፤106፥9፤119፥21፤ ኢሳ17፥13፤54፥9፤ ዘካ3፥2
37፥11 ዘፍ26፥14፤ሐሥ7፥9፤ሉቃ 2፥19:51
37፥12 ዘፍ12፥6
37፥13 ዘፍ17፥5፤ 33፥19
37፥14 ዘፍ13፥18፤ 1ሳሙ17፥18
37፥17 2ነገ6፥13
37፥18 1ሳሙ19፥1 ፤2ዜና24፥21፤መዝ 31፥13:20፤37፥12: 32፤ማቴ12፥14፤ማር 14፥1፤ሐሥ23፥12
37፥19 ዘፍ28፥12
37፥20 ቊ22:31-33፤ዘፍ4፥10፤50፥20፤ ዘለ 26፥6:22፤ዘዳ 32፥24፤2ነገ17፥25፤ ኤር38፥6-9፤ሕዝ 34፥25
37፥21 ዘፍ29፥32፤ 42፥22
37፥22 ቊ20:29-30
37፥23 ቊ3
37፥24 ቊ4፤ዘፍ 49፥23፤ኤር38፥6፤ 41፥7፤ሕዝ22፥27
37፥25 ቊ28፤ዘፍ 16፥11፤31፥21፤39፥1፤43፥11፤ዘፀ30፥23፤ መዝ45፥8፤105፥17፤ ምሳ7፥17፤ማሕ1፥13፤ 4፥1፤ኤር8፥22፤22፥6 ፤46፥11፤ማቴ2፥11
37፥26 ዘፍ4፥10፤ 29፥35
37፥27 ዘፍ29፥14፤ 42፥21
37፥28 ቊ36፤
37፥29 ቊ34፤ዘፍ 44፥13፤ዘኍ14፥6፤ ኢሱ7፥6፤2ሳሙ1፥11፤

አዩት፤ ወደ ነበሩበትም ስፍራ ከመድረሱ
በፊት ሊገድሉት ተማከሩ::
19እነርሱም እንዲህ ተባባሉ፤ "ያ ሕልም ዐላሚ
መጣ፤ 20ኑ እንግደለውና ከጕድጓዶቹ በአንዱ
ውስጥ እንጣለው፤ ከዚያም፣ 'ክፉ አውሬ ነጥቆ
በላው' እንላለን፤ እስቲ ሕልሞቹ ሲፈጸሙ
እናያለን::"
21ሮቤል ግን ይህን ምክር ሲሰማ ከእጃ
ቸው ሊያድነው ፈለገ እንዲህም አለ፤ "ሕይ
ወቱ በእጃችን አትለፍ፤ 22የሰው ደም አታ
ፍስሱ፤ እዚህ ምድረ በዳ፣ ጕድጓድ ውስጥ
ጣሉት እንጂ፣ እጃችሁን አታንሡበት::"
ሮቤል ይህን ያለው ሕይወቱን ከእጃቸው አት
ርፎ ወደ አባቱ ሊመልሰው አስቦ ነበር::
23ዮሴፍ ወደ ወንድሞቹ እንደ ደረሰ፣
የለበሳትን በኅብረ ቀለማት ያጌጠች እጀ ጠባ
ቡን ገፈፉት፤ 24ይዘውም ወደ ጕድጓድ
ጣሉት፤ ጕድጓዱም ውሃ የሌለበት ደረቅ
ነበር::
25ምግባቸውን ለመብላት ተቀመጡ፤ አሻ
ግረው ሲመለከቱም ከገለዓድ የሚመጡ እስ
ማኤላውያን ነጋዴዎች የግመል ጓዝ አዩ::
ነጋዴዎቹ ሽቶ፣ በለሳን ከርቤ በግመሎቻ
ቸው ጭነው ወደ ግብፅ የሚወርዱ ነበሩ::
26ይሁዳም ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው፤
"ወንድማችንን መግደልና አሟሟቱን መደ
በቅ ምን ይጠቅመናል? 27ከዚህ ይልቅ ለእ
ስማኤላውያን ነጋዴዎች እንሽጠው፤ እጃች
ንን ግን በእርሱ ላይ አናንሣ:: ምንም ቢሆ
ንኮ ወንድማችን፣ ሥጋችን ነው" ወንድሞ
ቹም በሐሳቡ ተስማሙ::
28የምድያም ነጋዴዎችም እነርሱ ዘንድ
እንደ ደረሱ፣ ወንድሞቹ ዮሴፍን ከጕድጓድ
አውጥተው ለእስማኤላውያን በሃያ ጥሬ ብር

ዘፍ16፥11፤25፥2፤39፥1፤45፥4-5፤ዘፀ21፥16፤ዘሌ27፥5፤መዝ105፥17፤ ኤር12፥6፤38፥13፤ማቴ26፥15፤ሐሥ7፥9

37፥10 *እናትህ፤* ራሔል ቀደም ብላ ሞታ ስለ ነበር (35፥19 ይመ)፣ እዚህ ላይ ያዕቆብ ልያን ማለቱ ሳይሆን አይቀርም:: *ወደ ምድር ተጐንብሰን፤* ቀደም ሲል ይስሐቅ ለያዕቆብ የሰጠው ተስፋ (27፥29 ይመ) ነበር::

37፥11 *ነገሩን በልቡ ያዘው፤* ዮሴፍ ያየው ሕልም አንድ በአንድ ሲፈጸም ያዕቆብ ነገሩን እንዳስታወሰ የሚጠቁም ፍንጭ ነው:: ኢየሱስ ልጅ በነበረ ጊዜ እናቱ ማርያም በልጇ ሕይወት የሚሆነውን ነገር ሁሉ ልብ ብላ ትከታተል የነበረውን (ሉቃ 2፥19:51) ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ::

37፥12 *ሴኬም፤* የ33፥18 ማብ ይመ::

37፥17 *ዶታይን፤* ከሴኬም በስተ ሰሜን 20 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ትገኛለች፤ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ዶታይን ብዙ ዘመን ያስቈጠረች ከተማ ነበረች::

37፥19 *ሕልም ዐላሚ፤* ይህን ሐረግ ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጥ ቃል፣ "የሕልም አለቃ" የሚል ትርጕም ያለው ሲሆን፣ በዚህ ቦታ ግን የአግቦ ወይም የአሽሙር ንግግር ሆኖ እንደ ገባ ግልጽ ነው::

37፥21 *ሮቤል... ሊያድነው ፈለገ፤* የያዕቆብ የበኵር ልጅ በመሆኑ ዮሴፍ አንድ ነገር ቢሆን ተጠያቂ እንደሚሆን ያውቃል:: ይህን ሁኔታና ቀን ሌላ ጊዜ ለወንድሞቹ ሲያስታውሳቸው ይታያል (42፥22):: ሮቤል ሁኔታዎቹን ለመለወጥ ያደረገው ሙከራ የተሳካ ይመስል ነበር (30፥14-17):: ነገር ግን ከአባቱ ቍባት ከባላ ጋር ከተኛ በኋላ፣ (35፥22 እና ማብ ይመ)፣ ጥረቱ ሁልጊዜ ከንቱ ይሆንበት ነበር (42፥37-38 ይመ):: ይህም የብኵርናውን ክብር ማጣቱን ያመለክታል (49፥3-4 ይመ):: ከዚህ በኋላ የመሪነት ሥልጣኑ ለይሁዳ ተላለፈ (ቍ 26-27)፤ 43፥3-5:8-10፤ 44፥14-34፤ 46፥28፤ 49፥8-12 ይመ)::

*37፥23-24፤* በተመሳሳይ ሁኔታ ዮሴፍ ግብፅ በነበረ ጊዜ (ምንም እንኳ ከማንኛውም ክፉ ተግባር ንጹሕ ቢሆንም) ከሥልጣኑ እንዲነሣና ወህኒ ቤትም እንዲወረወር የአገሬው ነዋሪዎች ያልቈፈሩት ጕድጓድ የለም (ም 39):: ልብሱ ተቀዶ ለጲጥፋራ እንዲታይ ቢደረግም፣ እርሱ ግን አዳነው (41፥14)::

37፥25 *እስማኤላውያን፤* እንደዚሁም ምድያማውያን፣ (ቍ 28፤ መሳ 8፥22፡ 24:26 ይመ) ሜዶናውያን ተብለዋል:: እነዚህ የተለያዩ ጐሣዎች የእርስ በርስ ዝምድና ያላቸው ሲሆን፣ እስማኤል የአብርሃም ልጅ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ምድያምና ሜዶንም የአብርሃም ልጆች ናቸው (25፥2):: *ከገለዓድ፤* የ31፥21 ማብ ይመ:: *በለሳን፤* ከአንድ ወይም ከብዙ ትናንሽ የዛፍ ዐይነቶች ተጨምቆ የሚዘጋጅና የመፈወስ ባሕርይ ያለው (ኤር 51፥8 ይመ) ዘይት ወይም ሙጫ ነው:: የገለዓድ በለሳን ፍቱን መድኀኒት ነው (ኤር 8፥22፤ 46፥11 ይመ):: *ከርቤ፤* ምናልባት ከዝባድ ጋር አንድ ዐይነት ሆኖ መልካም መዐዛ ያለው ሙጫ ሳይሆን አይቀርም (መዝ 45፥8፤ ምሳ 7፥17፤ ማሕ 3፥6፤ 5፥13 ይመ፤ ይህ ሙጫ ከጽጌረዳ አበባ ቅጠል ጭማቂ የሚዘጋጅ ሲሆን፣ ዘይቱ ደግሞ ለውበት፣ ለቀንጅና ሥራ ያገለግላል፤ (አስ 2፥12 ይመ):: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሥቃይን ወይም ሕመምን ለመቀነስ ከወይን ጠጅ ጋር እየተቀላቀለ ይጠጣ ነበር (ማር 15፥23 ይመ):: ከርቤ ለንጉሥ የሚሰጥ ስጦታ በመሆኑ ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ ስጦታ ሆኖ ቀርቧል (ማቴ 2፥11) ከሞተም በኋላ ደግሞ፣ የኢየሱስን ሥጋ ከርቤና ሽቱ ቀላቅለው ቀብተውታል (ዮሐ 19፥39-40)::

37፥28 *በሃያ ጥሬ ብር፤* ከጊዜ በኋላ ይህ የዋጋ ተመን፣ በዮሴፍ ዕድሜ ለሚገኝ ራሱን ለጌታ የሰጠ ወንድ ዋጋ ሆኖአል

ሽጡላቸው፤ እነርሱም ዮሴፍን ወደ ግብፅ ወሰዱት።

29ሮቤል ወደ ጕድጓዱ ተመልሶ ሲያይ፣ ዮሴፍን በማጣቱ ልብሱን በሐዘን ቀደደ። 30ወደ ወንድሞቹም ተመልሶ፣ "ብላቴናው ጕድጓድ ውስጥ የለም፤ የት አባቴ ልሂድ?" አለ።

31ከዚያም የዮሴፍን እጀ ጠባብ ወሰዱ፤ አንድ ፍየልም ዐርደው እጀ ጠባቡን በደሙ ነከሩት። 32በኅብረ ቀለማት ያጌጠችውን እጀ ጠባብ ወደ አባታቸው ወስደው፣ "ይህን ወድቆ አገኘነው፤ የልጅህ እጀ ጠባብ መሆን አለመሆኑን እስቲ እየው" አሉት።

33እርሱም ልብሱን ዐውቆት፣ "ይህማ የልጄ እጀ ጠባብ ነው!፤ ክፉ አውሬ በልቶታል፣ በእርግጥም ዮሴፍ ተቦጫጭቋል" አለ።

34ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ልብሱን ቀደደ፤ ማቅም ለብሶ ስለ ልጁ ብዙ ቀን አለቀሰ፤ 35ወንዶችና ሴቶች ልጆቹም ሁሉ ሊያጽናኑት መጡ፤ እርሱ ግን ሊጽናና ባለመቻሉ "በሐዘን እንደ ተኵራመትሁ ልጄ ወዳለበት መቃብር[ሀ] እወርዳለሁ" አለ። ስለ ልጁም አለቀሰ።

36በዚህ ጊዜ፣ የምድያም[ለ] ነጋዴዎች ዮሴፍን፣ ወደ ግብፅ ወስደው፣ ከፈርዖን ሹማምንት አንዱ ለነበረው ለዘበኞች አለቃ፣ ለጲጥፋራ ሸጡት።

## ይሁዳና ትዕማር

38 በዚያም ወራት ይሁዳ ከወንድሞቹ ተለይቶ፣ ኤራስ ወደ ተባለ ዓዶሎማዊ ሰው ወረደ፤ እርሱም ዘንድ ለመኖር ቤቱ ገባ። 2እዚያም ሳለ፣ ይሁዳ የከነዓናዊውን የሴዋን ሴት ልጅ አየ፤ እርሷንም አግብቶ አብሯት ተኛ፤ 3እርሷም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙም ዔር ተባለ። 4እንደ ገናም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙን አውናን አለችው። 5አሁንም ደግማ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ሴሎም ብላ አወጣችለት፤ እርሱንም የወለደችው ክዚብ በተባለ ቦታ ነበር።

6ይሁዳ የበኵር ልጁን ዔርን፣ ትዕማር የምትባል ሚስት አጋባው። 7የይሁዳ የበኵር ልጅ ዔር ግን በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፊት ክፉ ነበር፤ *እግዚአብሔርም* (ያህዌ) ቀሠፈው።

8በዚህ ጊዜ ይሁዳ አውናንን፣ "ዋርሳዋ እንደ መሆንህ ከወንድምህ ሚስት ጋር ሩካቤ ሥጋ በመፈጸም የወንድምህን ስም የሚያስጠራ ለት ዘር ተካለት" አለው። 9አውናን ግን የሚወለደው ልጅ የእርሱን ስም የሚያስጠራ እንደማይሆን ስላወቀ፣ ከወንድሙ ሚስት ጋር ሩካቤ-ሥጋ በፈጸመ ቍጥር የወንድሙንም ስም የሚያስጠራ ልጅ እንዳይወልድ ዘሩን በምድር ላይ ያፈስ ነበር። 10ይህም *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ክፉ አድራጎት ሆኖ ስለ ተገኘ፣ እርሱንም *እግዚአብሔር* (ያህዌ) በሞት ቀሠፈው።

11ከዚያም ይሁዳ ምራቱን ትዕማርን፣ "ልጄ ሴሎም ለአካለ መጠን እስኪደርስ ድረስ ወደ አባትሽ ቤት ሄደሽ መበለት ሆነሽ ብትኖሪ

2ነገ2፥12፤5፥7፤11፥14፤22፥11፤ኢዮ1፥20፤2፥12፤ኢሳ36፥22፤37፥1፤ኤር36፥24፤41፥5፤ኢል2፥13 37፥30 ቍ22 37፥31 ቍ3፤ራእ19፥13 37፥32 ቍ3 37፥33 ቍ20፤ዘፍ42፥13:38፤44፥20:28 37፥34 ቍ29፤ዘፍ50፥3:10:11፤ዘኍ20፥29፤ዘዳ34፥8፤2ሳሙ3፥31፤1ነገ20፥31፤21፥27፤2ነገ6፥30፤19፥1-2፤ኢዮ16፥15፤መዝ69፥11፤ኢሳ3፥24፤15፥3፤22፥12፤32፥11፤37፥1፤ኤር48፥37፤49፥3፤ኢል1፥13 37፥35 ዘፍ29፥31፤42፥38፤44፥22:29፤ሳሙ12፥17:23፤ኢዮ2፥11፤15፥11፤16፥5፤42፥11፤መዝ77፥2፤ኤር31፥15 37፥36 ቍ28፤ዘፍ25፥2፤39፥1፤40፥3፤41፥10:12፤1ሳሙ22፥14 38፥1 ቍ12:20፤ዘፍ29፥35፤2ዜና11፥7፤ኢሱ12፥15፤15፥35፤1ሳሙ22፥1፤2ሳሙ23፥13 38፥2 ቍ12፤1ዜና2፥3 38፥3 ቍ6፤ዘፍ46፥12፤ዘኍ26፥19 38፥4 ቍ8:9፤ዘፍ46፥12፤ዘኍ26፥19 38፥5 ዘኍ26፥20፤ 38፥12 ቍ1:2:14፤ዘፍ31፥19፤ኢሱ15፥10:57፤19፥43፤መሳ 1ዜና2፥3፤4፥21 38፥6 ቍ11:13 38፥7 ቍ10፤ዘፍ6፥5፤46፥12፤ዘሌ10፥1-2፤1ዜና2፥3 38፥8 ዘዳ25፥5-6፤ሩት 4፥5፤ማቴ22፥24-28 38፥10 ቍ7፤ዘዳ25፥7-10 38፥11 ቍ6:14:26፤ዘፍ11፥31፤ሩት1፥8፤1፥13

[ሀ]35 በዕብራይስጡ ሲኦል ይለዋል

[ለ]36 ከእሬተ ሳምራውያን፣ ከሰብዓ ሊቃናት፣ ከቩልጌትና ከሱርስት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን የማሶሬቲክ ጽሑፍ ግን *ሜዳናውያን* ይለዋል።

(ዘሌ 27፥5 ይመ)።

*37፥31-33፤* በዚህም ሥፍራ፣ የታረደ ፍየል የአታላይነት ምሳሌ ሆኖ ቀርቦአል (27፥5-13 ይመ)።

37፥34 *ልብሱን ቀደደ፤* ቍ 29 ይመ። *ማቅ ለብሶ፤* በመ ደበኛው ልብስ ፈንታ ሻካራ ልብስና ማቅ መልበስ የሐዘን ምል ክት ነው።

37፥35 *ሴቶች ልጆቹ፤ ምራቶችንም* ሳያጠቃልል አይቀ ርም (የያዕቆብ ምራት በ38፥2 ላይ ተጠቅሳለች)። *መቃብር፤* እንደ አንዳንድ ሊቃውንት አባባል ሼኦል የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ሙታን የሚገኙበትን ቦታ ወይም የታችኛውን ዓለም የሚገ ልጽ አጠቃላይ መጠሪያ ሲሆን፣ በሞት የተለየች ነፍስ ወይም መንፈስ የምትኖረውም በዚሁ ቦታ ነው የሚል አስተያየት አለ (ሼኦል የሚለው ቃል የሰጠውን ትርጕም ለማየት ኢዮ 3፥13-19 ይመ)።

37፥36 *ሽጡት፤* "ባሪያ እንደሚሸጥ" ማለት ነው (መዝ 105፥17)። በፀረብ በረሓ የነበሩ ሕዝቦች ለብዙ ዘመን በባሪያ ንግድ ላይ ተሰማርተው ነበር (ከአሞ 1፥6:9 ጋር ያነጻጽሩ)። *ለዘበኞች፤* ይህን ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጥ ቃል "ፍርድ አስ ፈጻሚ" (የቤተ መንግሥት እስረኞች አለቃ፤ 40፥4 ይመ) ወይም "ሥጋ በላች" (የቤተ መንግሥት የምግብ አለቃ ከ1ሳሙ 9፥23-24 ጋር ያነጻጽሩ) የሚል ትርጕም አለው።

*38፥1-30፤* አሳዛኝ በሆነ ድርጊት የተሞላው ይህ ምዕራፍ፣ ለእግዚአብሔር የተለዩት የእስራኤል ሕዝቦች በከነዓናውያን መካ ከል ቢቈዩ ኖሮ፣ ሊገጥማቸው ይችል የነበረውን ፈተና ይገልጻል (15፥16 እንዲሁም ማብ ይመ)። እስራኤላውያን በግብፅ በነበሩ ጊዜ፣ ግብፃውያን ይንቋቸው ስለ ነበር (43፥32፤ 46፥34)፣ ከግብፃ ውያን ተለይተው ይኖሩ ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝብ በዚያ ሳለ ማንነቱን ሳያጣ አንድ ሕዝብ ለመሆን ችሎ ነበር።

38፥1 *ከወንድሞቹ ተለይቶ፤* ዮሴፍ ከወንድሞቹ የተለየው ተገዶ ሲሆን፣ ይሁዳ ግን በከነዓናውያን መካከል የራሱን ዕድል ለመወሰን በገዛ ፈቃዱ ተለየ። *ዓዶሎማዊ፤* ዓዶሎም፣ ከኢየሩሳ ሌም በስተ ደቡብ ምዕራብ የምትገኝ ከተማ ናት (2ዜና 11፥5:7 ይመ)።

38፥3-4 *ዔር... አውናን፤* እነዚህ ስሞች የጐሣ ወይም የብሔር መለያ ሆነው በመስጴጦምያውያን መዛግብት ላይ ተጠቅሰዋል።

38፥5 *ክዚብ፤* ምናልባት አክዚብ ከሚለው ጋር አንድ ሳይ ሆን አይቀርም (ኢሱ 15፥44)፤ አክዚብ ከዓዱላም 5 ኪሎ ሜትር ርቆ ይገኛል። "የኮዜባ ሰዎች" (የክዚብ ሰዎች) የይሁዳ ልጅ የሼላ ዘሮች ናቸው (1ዜና 4፥21-22)። የስሙ ትርጕም "አታላይ" ማለት ሲሆን (ሚክ 1፥14 ይመ)፣ ይህም በያዕቆብና በልጆቹ ታሪክ ውስጥ ዋና ሐሳብ ነው።

38፥6 *ይሁዳ...ዔርን... ሚስት አጋባው፤* የ21፥21 ማብ ይመ።

*38፥8፤* የወንድምን ሚስት ስለ ማግባት የሚናገር አጭር ማብራሪያ ነው። ዝርዝር ጉዳዩ በዘዳ 25፥5-6 ላይ የተነገረ ሲሆን፣ ይህም በእስራኤል ዘንድ እንደ አንድ ሕግ ተደንግጉአል (ከማቴ 22፥24 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ልማድ በሩት 4፥5 ላይ የተገለጸ ሲሆን፣ ምንም እንኳ በዚህ ታሪክ ውስጥ ጉዳዩ ከቅርብ ዘመዶች ጋር ተያ ይዞ ቢቀርብም ቦዔዝም ሆነ የቅርብ ዘመዷ የባሏ ወንድሞች አይደሉም (ሩት 3፥12)።

38፥9 *የሚወለደው ልጅ የእርሱን ስም የሚያስጠራ እንደ ማይሆን ስላወቀ፤* በተመሳሳይ ሁኔታ የሩት የቅርብ ዘመድም ሩትን ካገባሁ ርስት አጣለሁ ብሎ ፈርቶ ነበር (ሩት 4፥5-6)። *ዘሩን በምድር ላይ ያፈስ ነበር፤* ይህም ከወሊድ መቈጣጠሪያ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ በውጪው ዓለም "አውናኒዝም" ይባላል (አውናን ከተባለው ስም የተወሰደ ነው)።

38፥10 *ይህም... አድራጎት፤* ከወንድሙ ሚስት ልጅ ለመ ውለድ ፈቃደኛ አለመሆኑን ያመለክታል።

ይሻላል" አላት፤ ይህን ያለውም፣ ሴሎም
እንደ ወንድሞቹ ተቀሥፎ ይሞትብኛል ብሎ
ስለ ሠጋ ነበር። ትዕማርም እንዳላት
ሄደች፤ በአባቷም ቤት ተቀመጠች።
12ከብዙ ጊዜ በኋላ የሹዓ ልጅ፣ የይሁዳ
ሚስት ሞተች። ይሁዳ ከሐዘኑ ከተጽናና
በኋላ ከዓዶላማዊው ከሒራ ጋር የበጎቹን
ጠጕር የሚሸልቱ ሰዎች ወዳሉበት ወደ ተምና
ሄደ።
13ሰዎቹም ለትዕማር፣ "ዐማትሽ የበጎቹን
ጠጕር ወደሚሸልቱ ሰዎች ዘንድ ወደ ተምና
እየሄደ ነው" አሏት። ይህን እንደ ሰማች
14የመበለትነት ልብሷን አውልቃ፣ ማንነቷ
እንዳይታወቅ ፊቷን በሻሽ ተከናንባ ወደ
ተምና በሚወስደው መንገድ ዳር ባለች ኤናይም
በተባለች ከተማ መግቢያ ላይ ተቀመጠች፤
ይህን ያደረገችው፣ ሴሎም ለአካለ መጠን
ቢደርስም፣ እርሷን እንዲያገባ አባቱ አለ
መፈለጉን ስላወቀች ነው።
15ፊቷ በሻሽ ተሸፋፍኖ ሲያያት፣ ይሁዳ
ዝሙት ዐዳሪ መሰለችው። 16ምራቱ መሆኗን
ባለማወቁ፣ እርሷ ወዳለችበት ወደ መንገዱ
ዳር ጠጋ ብሎ፣ "እባክሽ አብሬሽ ልተኛ"
አላት። እርሷም፣ "አብሬህ ብተኛ ምን ትሰጠ
ኛለህ?" ብላ ጠየቀችው።
17"ከመንጋዬ መካከል አንድ የፍየል ጠቦት
እልክልሻለሁ" አላት። እርሷም መልሳ፣ "ጠቦ
ቱን እስክትልክልኝ ድረስ ምን መያዣ ትሰጠ
ኛለህ?" ብላ ጠየቀችው።
18"ታዲያ ምን መያዣ ልስጥሽ?" አላት።
እርሷም፣ "የማኅተም ቀለበትህን ከነማሰሪ
ያው፣ እንደዚሁም ይህን በትርህን ስጠኝ"
አለችው። የጠየቀችውን ሁሉ ሰጣትና አብ
ሯት ተኛ፤ እርሷም ፀነሰች። 19ከዚያም ወደ
መኖሪያዋ ተመልሳ፣ ሻሽዋን አውልቃ እንደ
ወትሮዋ የመበለት ልብሷን ለበሰች።
20ይሁዳ በመያዣ ስም የሰጣትን ዕቃዎች
ለማስመለስ የፍየሉን ጠቦት በዓዶሎማዊ
ወዳጁ እጅ ላከላት፣ መልእክተኛው ግን
ሴትየዋን ሊያገኛት አልቻለም። 21"በኤና
ይም ከተማ መግቢያ ከመንገዱ ዳር የነበ
ረች ያቺ ዝሙት ዐዳሪ የት ደረሰች?" ሲል

14፥1፡2፤2ዜና28፥18
38፥13 ቍ6፤ዘፍ 31፥19
38፥14 ቍ11፡12፡19፤ዘፍ24፥65፤ኤር3፥2
38፥15 መሳ11፥1፤16፥1
38፥16 ዘፍ30፥15፤39፥7፡12፤42፥23፤ዘሌ 18፥15፤20፥12፤ሩት 1፥6፤2ሳሙ13፥11
38፥17 ቍ20፤መሳ15፥1
38፥18 ቍ25፤ዘፍ 19፥32፤32፥10፤ዘፀ4፥2፤1ነገ21፥8፤አስ3፥12፤8፥8፤ማሕ8፥6፤ኢሳ 49፥16፤ኤር22፥24፤ሐጌ2፥23፤2ቆሮ 1፥22፤ኤፌ1፥13
38፥19 ቍ14
38፥20 ቍ1፡17
38፥21 ዘፍ19፥5፤ዘሌ19፥29፤ዘዳ22፥21፤ 23፥17፤2ነገ 23፥7፤ሆሴ4፥14
38፥23 ቍ18፤ዘፀ 32፥25፤ኢዮ12፥4፤ኤር20፥7፤ሰቆ3፥14
38፥24 ዘሌ20፥10፡14፤21፥9፤ዘዳ22፥21፡22፤ኢሱ7፥25፤መሳ 15፥6፤1ሳሙ31፥12፤ኢዮ31፥11፡28፤ሕዝ 16፥38
38፥25 ቍ18
38፥26 ቍ11፤1ሳሙ24፥17
38፥27 ዘፍ25፥24
38፥28 ቍ30፤ዘፍ 35፥17
38፥29 ዘፍ25፥26፤46፥12፤ዘኍ26፥20፡21፤ሩት4፥12፡18፤2ሳሙ5፥20፤6፥8፤1ዜና2፥4፤9፥4፤ኢሳ 28፥21፤ማቴ1፥3
38፥30 ቍ28፤ዘፍ 46፥12፤1ዜና2፥4፤ነህ 11፥24
39፥1 ዘፍ30፥24፤37፥25፡36
39፥2 ዘፍ21፥20፡22፤ኢሱ1፥5፤6፥27፤መሳ1፥19፤1ሳሙ-

ጠየቃቸው። ሰዎቹም፣ "በዚህ አካባቢ ኧረ
ምንም ዝሙት ዐዳሪ ታይታ አትታወቅም"
አሉት።
22መልእክተኛውም ወደ ይሁዳ ተመልሶ፣
"ሴቲቱን ላገኛት አልቻልኩም፤ ነዋሪዎ
ቹም 'በዚህ አካባቢ እንደዚህች ያለች ዝሙት
ዐዳሪ የለችም' አሉኝ" ብሎ ነገረው።
23ይሁዳም፣ "እንግዲህ መያዣውን እንደ
ያዘች ትቅር፤ አለዚያ መሣቂያ እንሆናለን።
ለነገሩማ ይህን ፍየል ላክሁ፤ አንተም ፈል
ገህ አላገኘሃትም" አለ።
24ከሦስት ወር ያህል በኋላ፣ "ምራትህ
ትዕማር ዘማዊ ሆናለች፤ ከዚህም የተነሣ
አርግዛለች" ተብሎ ለይሁዳ ተነገረው።
ይሁዳም፣ "አውጧትና በእሳት ተቃጥላ
ትሙት" አለ።
25እርሷም ተይዛ በምትወሰድበት ጊዜ ለዐ
ማትዋ፣ "እኔ ያረገዝሁት የእነዚህ ዕቃዎች
ባለቤት ከሆነ ሰው ነው" ስትል ላከችበት፤
ደግሞም፣ "የማኅተሙ ቀለበት ከነማንገ
ልጠያውና በትሩ የማን እንደ ሆነ እስቲ
ተመልከት" አለችው።
26ይሁዳም ዕቃዎቹን ዐውቆ፣ "ልጄ ሴሎም
እንዲያገባት ባለማድረጌ፣ እርሷ ከእኔ ይልቅ
ትክክል ናት" አለ። ከዚያም በኋላ ከእርሷ
ጋር አልተኛም።
27የመውለጃዋ ጊዜ እንደ ደረሰም ፅንሷ
መንታ መሆኑ ታወቀ። 28በምትወልድበትም
ጊዜ አንደኛው እጁን አወጣ፤ አዋላጂቱም፣
"ይህኛው መጀመሪያ ወጣ" ስትል በእጁ ላይ
ቀይ ክር አሰረችለት፤ 29ነገር ግን፣ እጁን
መልሶ ሲያስገባ ወንድሙ ተወለደ። አዋላ
ጂቱም "አንተ እንዴት ጥሰህ ወጣህ!"
አለች፤ ከዚያም ስሙ ፋሬስ[n] ተባለ። 30ከዚያ
በኋላ እጁ ላይ ቀይ ክር የታሰረለት ወን
ድሙ ተወለደ፣ ስሙም ዛራ[o] ተባለ።

## ዮሴፍና የጲጥፋራ ሚስት

39 በዚህ ጊዜ ዮሴፍ ወደ ግብፅ ተወ
ስዶ ነበር፤ ከፈርዖን ሹማምንት አንዱ
የሆነውም የዘበኞች አለቃ፣ ግብፃዊው ጲጥፋራ

[n]29 ፋሬስ ማለት ጥሶ መውጣት ማለት ነው
[o]30 ዛራ የሚለው ደማቅ ቀይ ወይም ብሩህ እንደ ማለት ነው

38፥11 *ሴሎም እንደ ወንድሞቹ ተቀሥፎ ይሞትብኛል ብሎ ስለ ሠጋ፤* ስለዚህም ይሁዳ ልጁ ሴሎም ትዕማርን እንዲያገባ ምንም ሐሳብ አልነበረውም (ቍ 14 ይመ)።

38፥12 *ተምና፤* ትክክለኛው ቦታ ባይታወቅም፣ በተራራማው አገር በይሁዳ እንደሚገኝ ይታመናል (ኢሱ 15፥48፡57 ይመ)።

38፥14 *መንገድ ዳር... ተቀመጠች፤* በተለምዶ ዝሙት ዐዳሪዎች (ቍ 15 ይመ) የሚቀመጡት በመንገድ ዳር ነበር (ኤር 3፥2)። *ኤናይም፤* "ሁለት ምንጮች" ማለት ሲሆን፣ ምናልባት በምዕራብ ይሁዳ ኮረብታማ አካባቢ ከሚገኘው፣ አይናም ተብሎ ከሚጠራው ቦታ ጋር አንድ ሳይሆን አይቀርም (ኢሱ 15፥33-34 ይመ)።

38፥18 *የማኅተም ቀለበትህን ከነማሰሪያው፤* ምናልባት አነስተኛ የሲሊንደር ማኅተም ሲሆን በሸክላ መዛግብት ላይ ለመፈረም ወይም ምልክት ለማድረግ፣ በሸክላዎቹ ላይ የሚንከባለለውን ዐይነት የመሰለ ሳይሆን አይቀርም። ይህን የመሰለ የማኅተም ቀለበት ያላቸው ሰዎች በቀለበቱ ውስጥ ክር አስገብተው በዐንገታቸው ላይ ያስሩታል።

38፥21 *ዝሙት ዐዳሪ፤* ይህን ሐረግ ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጥ ቃል፣ የቤተ ጣዖት ዝሙት ዐዳሪ የሚል ነው። የይሁዳ ወዳጅ በአብዛኛው ተቀባይነት ያለውን ይህን መጠሪያ የተጠቀመችበት ሆን ብላ ሳይሆን አይቀርም፤ ምክንያቱም በከነዓናውያን ዘንድ ከተራ ዝሙት ዐዳሪነት ይልቅ በማኅበረ ሰቡ ውስጥ ከፍተኛ እሴት ያለው ሃይማኖታዊው ዝሙት ዐዳሪነት ነው።

38፥24 *በእሳት ተቃጥላ ትሙት፤* ኋላ ኋላ ዝሙት ዐዳሪዎችን በእሳት ማቃጠል ሕጋዊ ቅጣት ሆኖ ነበር (ዘሌ 21፥9 ይመ)።

*38፥27-30፤* በእንዲህ ዐይነት አስደናቂ ሁኔታ መንታ ሆነው ስለ ተወለዱ ሕፃናት፣ በ25፥24-26 ላይ ይመ።

38፥29 *ፋሬስ፤* በይሁዳ መሪ ነገድ ለሆነው ራስ፣ ለዳዊት (ሩት 4፥18-22 ይመ) እና በመጨረሻም ለክርስቶስ (ማቴ 1፥1-6 ይመ) ቅድመ አያት ሆነ።

*39፥1፤* 37፥36 ይመ። *ወደ ግብፅ ተወስዶ፤* ዮሴፍ በግብፅ እንዲሁም ወጣት ሳለ በከነዓን ያሳለፈው ሕይወት (የ 37፥23፥24 ማብ ይመ)፣ የእስራኤል ሕዝብ በግብፅ ካሳለፈው ሕይወት ጋር

ወደዚያ ከወሰዱት ከእስማኤላውያን ነጋዴ
ዎች እጅ ገዛው::
2*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ከዮሴፍ ጋር ነበረ፤
ኑሮው ተቃናለት፤ እርሱም በግብፃዊው አሳ
ዳሪው ቤት ኖረ:: 3አሳዳሪውም *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ከእርሱ ጋር እንዳለና ሥራውንም ሁሉ
እንዳከናወለት ባየ ጊዜ፣ 4ዮሴፍ በእርሱ
ዘንድ ሞገስ አገኘ፤ የቅርብ አገልጋዩም ሆነ::
ጲጥፋራ በቤቱ ላይ ሾመው፤ ያለውንም ሀብት
ሁሉ በኀላፊነት ሰጠው:: 5ዮሴፍ በጲጥፋራ
ቤትና ባለው ሀብት ሁሉ ላይ ከተሾመበት
ጊዜ ጀምሮ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) የግብፃዊ
ውን ቤት ባረከ፣ *የእግዚአብሔርም* (ያህዌ)
በረከት በግቢም በውጭም ባለው የጲጥፋራ
ሀብት ንብረት ሁሉ ላይ ሆነ:: 6ስለዚህ ጲጥ
ፋራ ባለው ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጠው፤ የቀ
ረበለትንም ከመመገብ በስተቀር፣ ማናቸ
ውንም ጉዳይ በዮሴፍ ላይ ጥሎ ነበር::
ዮሴፍ ጥሩ ቁመና ያለውና መልከ መል
ካም ነበር፤ 7እያደርም የጌታው ሚስት ዐይኗን
ጣለችበት፤ አፍ አውጥታም፣ "አብረኸኝ
ተኛ" አለችው::
8እርሱ ግን ፈቃደኛ አልሆነም፤ እንዲህም
አላት፤ "ጌታዬ ያለውን ሁሉ በኀላፊነት ስለ
ሰጠኝ፣ በቤቱ ውስጥ ስላለው ሁሉ ምንም
የሚያውቀው ነገር የለም:: 9በዚህ ቤት ላይ
ከእኔ የበለጠ ኀላፊነት ያለው ማንም የለም፤
እርሱ ያልሰጠኝ ነገር ቢኖር፣ አንቺን ብቻ
ነው፤ ያውም ሚስቱ ስለሆንሽ ነው፤ ታዲያ፣
እኔ ይህን ክፉ ድርጊት ፈጽሜ እንዴት
በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፊት ኀጢአት እሠራ
ለሁ?" 10ምንም እንኳ ዮሴፍን በየቀኑ ብት
ጐተጕተውም፣ አልሰማትም፤ ከእርሷ ጋር
መተኛቱ ይቅርና አብሯትም መሆን አልፈ
ቀደም::
11አንድ ቀን ዮሴፍ የዕለት ተግባሩን ለማ

18፥14፤ሐሥ7፥9
39፥3 ቍ23፤ዘፍ
21፥22፤1ሳሙ18፥14፤
2ነገ18፥7፤2ዜና
20፥20፤መዝ1፥3፤
128፥2፤ኢሳ33፥6
39፥4 ቍ8:22፤ዘፍ
6፥8፤18፥3፤40፥4፤42፥
37፤47፥6፤1ነገ11፥28፤
ምሳ22፥29
39፥5 ዘፍ26፥24፤
ዘዳ28፥3፤2ሳሙ6፥
11፤መዝ128፥4
39፥6 ዘፍ12፥11፤
24፥2፤ዘፀ2፥2፤1ሳሙ
9፥2፤16፥12፤17፥42፤
አስ2፥7፤ዳን1፥4
39፥7 ዘፍ38፥16፤
ምሳ7፥15-18
39፥8 ቍ4፤ምሳ
6፥23-24
39፥9 ዘፍ41፥33:
40፤13፥13፤ዘኍ22፥34
39፥10 አስ3፥4
39፥11 ቍ14፤ዘፀ
18፥20፤ዘዳ1፥18
39፥12 ቍ15፤ዘፍ
38፥16፤2ሳሙ13፥
11፤ምሳ5፥8፤7፥13፤
2ጢሞ2፥22
39፥14 ቍ11፤ዘፍ
14፥13፤21፥9፤ዘዳ
22፥24:27
39፥15 ቍ12
39፥17 ዘፍ14፥13፤
21፥10፤ዘፀ20፥16፤
23፥1:7፤ዘዳ5፥20፤
መዝ101፥5
39፥19 ዘፍ34፥7፤
አስ1፥12
39፥20 ዘፍ40፥3፤
41፥10፤መዝ105፥18
39፥21 ዘፍ19፥19፤
21፥20፤ዘፀ3፥21፤
11፥3፤12፥36፤አስ
2፥9፤መዝ106፥46፤
ምሳ16፥7፤ዳን1፥9
39፥22 ቍ4
39፥23 ቍ3፤ዘፍ

ከናወን ወደ ቤት ገባ፤ ከቤቱ አገልጋዮችም
አንድም ሰው በቤት ውስጥ አልነበረም::
12እርሷም ልብሱን ጨምድዳ ይዛ "ከል አብረኸኝ
ተኛ" አለችው:: እርሱ ግን ልብሱን እጇ ላይ
ጥሎ ሸሽቶ ከቤት ወጣ::
13እርሷም ልብሱን እጇ ላይ ጥሎ ሸሽቶ
መውጣቱን ባየች ጊዜ፣ 14የቤት አገልጋዮቿን
ጠራች፤ እንዲህም አለቻቸው፤ "እያችሁ፤
ለካስ ይህ ዕብራዊ የመጣው መሣለቂያ ሊያ
ደርገን ኖሮአል! እዚህ ድረስ ሰተት ብሎ
ገብቶ ካልተኛሁሽ አለኝ፤ እኔም ጮኽቴን
ለቀቅሁት፤ 15ለእርዳታ መጮኼን ሲሰማም፣
ልብሱን ከአጠገቤ ጥሎ ሸሽቶ ከቤት ወጣ::"
16ጌታውም ወደ ቤት እስኪመለስ ድረስ፣
ልብሱን አጠገቧ አቆየችው:: 17ታሪኩንም
እንዲህ ስትል ነገረችው፤ "አንተ ያመጣኸው
ዕብራዊ ባሪያ መሣቂያ ሊያደርገን ወዳለሁ
በት ሰተት ብሎ ገባ፤ 18ታዲያ እኔ ድረሱ
ልኝ ብዬ ስጮኽ ልብሱን አጠገቤ ጥሎ
ሸሽቶ ወጣ::"
19ጌታውም "ባሪያህ እንዲህ አደረገኝ" ብላ
ሚስቱ የነገረችውን ታሪክ ሲሰማ፣ ተቈጣ::
20ጌታውም ዮሴፍን ወስዶ፣ የንጉሥ እስረ
ኞች ወደ ተጋዙበት እስር ቤት አስገባው::
ይሁን እንጂ ዮሴፍ እዚያ እስር ቤት
ባለበት ጊዜ ሁሉ፣ *እግዚአብሔር* (ያህዌ) ከእ
ርሱ ጋር ነበረ፤ ቸርነቱንም አበዛለት፣ በወ
ህኒ አዛዡም ዘንድ ሞገስን ሰጠው:: 22ስለዚህ
የወህኒው አዛዥ ዮሴፍን የእስረኞች ሁሉ
አለቃ አደረገው፤ በእስር ቤቱ ላለውም ነገር
ሁሉ ኀላፊ ሆነ:: 23እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከዮ
ሴፍ ጋር ሆኖ ሥራውን ሁሉ ያሳካለት፣
ስለ ነበር የወህኒ ቤት አዛዡ በዮሴፍ ኀላፊ
ነት ሥር ስላለው ስለማንኛውም ጉዳይ ሐሳብ
አይገባውም ነበር::

---

ተመሳሳይ ነው:: አስቀድሞ እግዚአብሔር ባርኮት ስለ ነበር ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤት ክብርን አገኘ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ወህኒ ወረደ፤ ለዚህም የበቃው መልከ ቀናና ንጹሕ ሰው በመሆኑ ብቻ ነበር፤ በመጨረሻ ግን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ነበር በግብፃውያን መካከል ከፍ ከፍ አለ፤ የግብፃውያንንም ሕይወት ሊያ ድን ቻለ:: በተመሳሳይ ሁኔታ ሕዝበ እስራኤልም በዮሴፍ ምክንያት በምድረ ግብፅ ክብር አገኘ፤ በኋላ ግን ለአስከፊ ባርነት ተዳረገ፤ ለዚህም የበቃው የእግዚአብሔር ልዩ በረከት በእርሱ ላይ ስለ ነበር ብቻ ነው:: በመጨረሻ ግን እግዚአብሔር በግብፃውያን ፊት ከፍ ከፍ አደረጋቸው (በሙሴ አገልግሎት ምክንያት)፤ ግብፃውያንም እነዚህ ሕዝቦችና አምላካቸው በእር ግጥ ሕይወታቸውን በእጃቸው ውስጥ እንደ ጨበጡ ተገነዘቡ:: የዘ ፍጥረት መጽሐፍ ጸሓፊ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ምድር መውጣት ያውቅ ስለ ነበር፣ የእግዚአብሔርና የእስራኤል አባቶች ታሪክ ይህንን ሁሉ አስቀድሞ እንዴት እንደሚያሳይ በሚገባ አስ ታውቆአል (15፥13-16፤ 48፥21-22፤ 50፥24-25 ይመ):: ***እስ ማኤላውያን፤*** የ37፥25 ማብ ይመ::

*39፥2-6* ቍ 20-23 ይመ:: ዮሴፍ የነበረበት ሁኔታ በድንቅ ቢለወጥም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያደርግ የነበረው ግንኙነት ግን ያው እንደ ድሮው ነበር::

*39፥2* ***እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ፤*** የ26፥3 ማብ ይመ፤ ይህ እውነታ በዚህ ክፍል ብዙ ጊዜ ተጠቅሶአል (ቍ 3፥21:23)፤ እስጢፋኖስም በአጽንዖት ተናግሮታል (ሐሥ 7፥9)::

39፥5 ***ዮሴፍ... ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር የግብፃዊውን ቤት ባረከ፤*** የአብርሃም ዘር ለትውልድ ሁሉ በረ ከት እየሆነ ነው (12፥2-3፤ 30፥27 ይመ)::

39፥6 ***ባለው ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጠው፤*** ዮሴፍ ከጊዜ በኋላ በእስር ቤት ላይ ሙሉ ኀላፊነትና (ቍ 22-23) ቀጥሎም በግብፅ ሁሉ ላይ ኀላፊነት እንደ ተሰጠው ሁሉ (41፥41)፣ የጲጥፋራንም ቤት እንዲያስተዳድር ሙሉ ኀላፊነት ተሰጠው:: ይህ እስራኤላዊ የሚኖርባትን "ዓለም" ሀብት ንብረት ሁልጊዜ በእጁ ውስጥ ማስገባት ችሎ ነበር፤ ይሁን እንጂ የሚኖርባትን ዓለም ሀብት ንብረት ሁልጊዜ ያገኝ የነበረው አባቱ ያዕቆብ ከዚህ በፊት ዘመኑን ሁሉ ሲያደርግ እንደ ነበረው፣ በራሱ ድካምና ጥረት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር እንደ ባረከውና እንዳስቻለው መጠን ነው:: ዮሴፍ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ የፈጸመው ድርጊትና የአሳለ ፈው አኗኗር፣ እስራኤልን በእውነት የሚወክል ነው::

39፥7 ***ዐይኗን ጣለችበት፤*** በምኞት ተሞልታ ተመለከተ ችው:: ይህ ዐረፍተ ነገር በአካዲያን መዛግብት በክፍል 25 ሐሙ ራቢ ባዘጋጀው ሕግ ውስጥ በተመሳሳይ መንገድ ተገልጸ ይገኛል::

39፥9 ***እንዴት በእግዚአብሔር ፊት ኀጢአት እሠራለሁ፤*** አንድ ሰው ኀጢአት ሲሠራ ከሁሉ በፊት በመጀመሪያ የሚበድ ለው እግዚአብሔርን ነው (መዝ 51፥4 ይመ)::

39፥10 ***ምንም እንኳ... በየቀኑ ብትጐተጕተውም... አልፈቀደም፤*** ሳምሶን በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ሁለት ጊዜ የገጠመውን ፈተና መቋቋም አቃተው (መሳ 14፥17፤ 16፥16-17 ይመ)::

39፥14 ***ዕብራዊ፤*** ቍ 17 እንደሁም የ14፥13 ማብ ይመ፣ 39፥20-23 የቍ 2-6 ማብ ይመ::

39፥20 ***የንጉሥ እስረኞች ወደ ተጋዙበት እስር ቤት፤*** ጲጥፋራ በነገሩ ቢበሳጭም (ቍ 19 ይመ፣ ዮሴፍን "የዘበኞቹ አለቃ ወደሚያስተዳድረው እስር ቤት" (40፥3) አስገባው፤ ይህም በወቅቱ ከነበሩት አስከፊ እስር ቤቶች የተሻለ ነበር::

## የመጠጥ አሳላፊውና የእንጀራ ቤቱ

40 ከዚህም በኋላ የግብፅ ንጉሥ የመጠጥ
አሳላፊና እንጀራ ቤቱ ጌታቸውን
የግብፅን ንጉሥ በደሉት። 2ፈርዖንም በመጠጥ
አሳላፊዎቹ አለቃና በእንጀራ ቤቱ አዛዥ፣
በሁለቱም ሹማምንቱ ላይ ክፉኛ ተቈጣ፤
3በዘበኞቹ አለቃ ቤት ወዳለው ዮሴፍ ወደ
ተጋዘበትም እስር ቤት አስገባቸው።
4የዘበኞቹም አለቃ እስረኞቹን ለዮሴፍ
አስረከባቸው፤ ዮሴፍም በሚያስፈልጋቸው
ይረዳቸው ነበር።
እስር ቤት ገብተው ጥቂት እንደቈዩም፣
5ታስረው የነበሩት የግብፅ የንጉሥ የመጠጥ
አሳላፊዎች አለቃና የእንጀራ ቤቱ አዛዥ፣
በአንድ ሌሊት የየራሳቸውን ሕልም አዩ፤
የሁለቱም ሕልም ለየራሱ የተለየ ፍቺ ነበ
ረው።
6በማግስቱ ጧት ዮሴፍ ወደ እነርሱ ሲ
ገባ ተክዘው አገኛቸው። 7ስለዚህም፣ “ምነው
ዛሬስ ፊታችሁ ላይ ሐዘን ይነበባል?” በማ
ለት አብረውት በጌታው ግቢ የታሰሩትን
የፈርዖን ሹማምት ጠየቃቸው።
8እነርሱም “ሁለታችንም ሕልም አየን፤ ነገር
ግን የሚተረጕምልን ሰው አጣን” ሲሉ መለ
ሱለት።
ዮሴፍም፣ “ሁልጊዜስ ቢሆን የሕልም ትርጓሜ
ከእግዚአብሔር (ኤሎሂም) የሚገኝ አይደለምን?
እስቲ ያያችሁትን ሕልም ንገሩኝ” አላቸው።
9ስለዚህ የመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃ እን
ዲህ ሲል ሕልሙን ለዮሴፍ ነገረው፤ ከፊት
ለፊቴ አንዲት የወይን ተክል አየሁ፤ 10ተክ
ሏም ሦስት ሐረጎች ነበሯት፤ ወዲያው
አቈጥቊጣ አበበች፤ ዘለላዎቿም ተንዠርግ
ግገው በሰሉ። 11የፈርዖንንም ጽዋ ይዤ ነበረ፤
የወይኑን ፍሬ ለቅሜ በጽዋው ውስጥ ጨምቄ
ጽዋውን በእጁ ሰጠሁት።”
12ዮሴፍም እንዲህ አለው፤ “እንግዲህ የሕ
ልሙ ትርጓሜ ይህ ነው፤ ሦስቱ ሐረግ
ሦስት ቀን ነው፤ 13በሦስት ቀን ውስጥ ፈር
ዖን ከእስር ቤት ያወጣሃል፣ ወደ ቀድሞ
ሹመትህም ይመልስሃል፤ በፊት የመጠጥ
አሳላፊ በነበርህበት ጊዜ ታደርግ እንደነበ
ረው ሁሉ የፈርዖንን ጽዋ በእጁ ትሰጠዋ
ለህ። 14እንግዲህ፣ በጎ ነገር በገጠመህ ጊዜ፣
እኔን አስበህ ቸርነት አድርግልኝ፤ ስለ እኔም
ለፈርዖን ንገርልኝ፤ ከዚህም እስር ቤት አስ
ወጣኝ፤ 15ከዕብራውያን ምድር ወደዚህ የመ
ጣሁት በአፈና ነው፤ አሁንም ቢሆን እዚህ
እስር ቤት የተጣልሁት አንዳች ጥፋት ኖሮ
ብኝ አይደለም።”
16የእንጀራ ቤት አዛዡም፣ ለመጠጥ አሳ
ላፊዎቹ አለቃ ሕልም፣ የተሰጠው ፍቺ ደስ
የሚያሰኝ መሆኑን ሲሰማ፣ የራሱን ሕልም
ለዮሴፍ እንዲህ ሲል ነገረው፤ “እኔም ደግሞ
ሕልም አይቻለሁ፤ ሦስት መሶቦች[o] በራሴ ላይ
ተሸክሜ ነበር፤ 17በላይኛው መሶብ ውስጥ
ለፈርዖን የተዘጋጀ የተለያየ ምግብ ነበረበት፤
ወፎችም ራሴ ላይ ካለው መሶብ ይበሉ
ነበር።”
18ዮሴፍም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ “የሕ
ልሙ ፍቺ ይህ ነው፤ ሦስቱ መሶብ ሦስት
ቀን ነው፤ 19በሦስት ቀን ውስጥ ፈርዖን ከእ
ስር ቤት ያወጣሃል፤ በዕንጨትም ላይ ይሰ
ቅልሃል፤[n] ወፎችም ሥጋህን ይበሉታል።”
20በሦስተኛውም ቀን የፈርዖን የልደት
በዓል ነበረ፤ ለሹማምቱም ሁሉ ግብር
አበላ። በዚያኑ ዕለትም የመጠጥ አሳላፊዎ
ችን አለቃና የእንጀራ ቤት አዛዡን ሹማ
ምቱ ካሉበት ከእስር ቤት አወጣቸው።
21የመጠጥ አሳላፊዎቹን አለቃ ወደ ቀድሞ
ሹመቱ መለሰው፤ እርሱም እንደ ቀድሞው
ጽዋውን ለፈርዖን በእጁ ይሰጠው ጀመር፤
22የእንጀራ ቤት አዛዡን ግን ልክ ዮሴፍ
እንደተረጐመላቸው ሰቀለው።[v]
23የሆነው ሆኖ፣ የመጠጥ አሳላፊዎቹ አለቃ
ዮሴፍን አላስታወሰውም፤ ረሳው።

## የፈርዖን ሕልም

41 ድፍን ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ
ፈርዖን ሕልም ዐለመ፤ በሕልሙም፣
በዐባይ ወንዝ ዳር ቆሞ ነበር፤ 2እነሆ መል
ካቸው ያማረ፣ ሥጋቸው የወፈረ ሰባት ላሞች
ከወንዙ ወጥተው በወንዙ ዳር የበቀለውን ሣር

21፥20፤ዘኍ14፥43
40፥1 ቍ9:13:16:20:21፤ነህ1፥11
40፥2 ዘፍ41፥10፤አስ2፥21፤ምሳ16፥14:15፤19፥12
40፥3 ዘፍ37፥36፤39፥20
40፥4 ቍ7፤ዘፍ37፥36፤39፥4፤42፥17
40፥5 ዘፍ20፥3፤41፥11
40፥7 ቍ4፤ነህ2፥2
40፥8 ዘፍ41፥8:15:16:25:28:32፤ዘዳ29፥29፤ዳን2፥22:28:47
40፥9 ቍ1
40፥10 ኢሳ27፥6፤35፥1-2፤ሆሴ14፥7
40፥12 ቍ16:18፤ዘፍ41፥12:15:25፤ዳን2፥36፤4፥19
40፥13 ቍ1:19:20፤ኢሱ1፥11፤3፥2፤ዕዝ8፥32፤ነህ2፥11
40፥14 ቍ23፤ዘፍ19፥19፤41፥9፤1ሳሙ20፥14:42፤25፥31፤2ሳሙ9፥1፤1ነገ2፥7፤መክ9፥15፤ሉቃ23፥42
40፥15 ዘፍ14፥13፤39፥20፤ኢዮ13፥27
40፥16 ቍ1:12፤አሞ8፥1-2
40፥18 ቍ12
40፥19 ቍ13:22፤ዘዳ21፥22-23፤28፥26፤1ሳሙ17፥44፤2ሳሙ21፥10፤1ነገ14፥11፤16፥4፤21፥24፤አስ2፥23፤7፥10፤ሕዝ39፥4
40፥20 ቍ1:13፤አስ2፥18፤ማቴ14፥6-10፤ማር6፥21
40፥21 ቍ1:13፤2ነገ25፥27፤ኤር52፥31፤ማር6፥21
40፥22 ቍ19፤ዘፍ41፥13፤መዝ105፥19
40፥23 ቍ14፤መክ1፥11
41፥1 ቍ17፤ዘፍ2፥14፤20፥3፤ዘፀ1፥22፤2፥5፤7፥15
41፥2 ቍ18:26፤ዘፀ2፥3፤ኢዮ40፥21፤ኢሳ19፥6፤ኤር5፥28

[o]16 ወይም ሦስት የሸንበቆ ቅርጫቶች
[n]19 ወይም በእንጨትም ላይ ይወጋሃል
[v]22 ወይም ወጋው

40፥2 *በመጠጥ አሳላፊዎቹ፤* ዮሴፍን ከፈርዖን ጋር ለማስተዋወቅ ከእግዚአብሔር የተሾመ መልእክተኛ ነበር (41፥9-14 ይመ)።

40፥5 *የሁለቱም ሕልም ለየራሱ የተለየ ፍቺ ነበረው፤* በሁሉም የጥንት ቅርብ ምሥራቅ ሕዝቦች ዘንድ ሕልሞች የተወሰነ ትርጕም ያላቸው ሲሆን፣ ሕልሞችን በትክክል መተርጐም ዐላሚው ወደፊት የሚሆነውን ነገር እንዲተነብይ ይረዳዋል (የ20፥3 ማብ ይመ)። ዮሴፍ በግብፅ ላይ ከፍ ከፍ እንዲል እግዚአብሔር መንገድ ያዘጋጀለት ነበር።

40፥8 *የሕልም ትርጓሜ ከእግዚአብሔር የሚገኝ አይደለምን?* ሕልምን በትክክል የሚተረጕም እግዚአብሔር ብቻ ነው (41፥16:25:28፤ ዳን 2፥28 ይመ)። *ንገሩኝ፤* ዮሴፍ፣ እግዚአብሔር በሕልማቸው ውስጥ ያለውን መገለጥ የሚያስታውቅበት የእግዚአብሔር መልእክተኛ አድርጐ ራሱን አቀረበ፤ በተመሳሳይ ሁኔታ እስራኤል፣ እግዚአብሔር ለሕዝቦች የሚያደርገውን መገለጥ የሚያስታውቅባት ልዩ ሕዝብ ናት (18፥17 እና ማብ፤ 41፥16:28:32 ይመ)።

40፥13 *ወደ ቀድሞ ሹመትህም ይመልስሃል፤* መዝ 3፥3፤ 27፥6 ይመ።

40፥14 *በጎ ነገር በገጠመህ ጊዜ እኔን አስበህ፤* ያጋጣሚ ጉዳይ ሆነና የወይን ጠጅ አሳላፊው ሁለት ዓመት ሙሉ (41፥1:9-13 ይመ) ዮሴፍን ረሳው (ቍ 23)።

40፥15 *እስር ቤት፤* የዮሴፍን ተስፋ መቍረጥ ለማመልከት የገባ ተጋኖ አነጋገር ነው (የ39፥20 ማብ ይመ)፤ በ37፥24 ላይ ይኸው የዕብራይስጥ ቃል “ጕድጓድ” ተብሎ የተተረጐመ በመሆኑ የዘፍጥረት መጽሐፍ ጸሓፊ ዮሴፍ ከዚህ ቀደም በወንድሞቹ እጅ የተፈጸመበትን በደል በዚህ ክፍል ካለው ታሪክ ጋር እያይዞታል።

40፥19 *በዕንጨት ላይ ይሰቅልሃል፤* በቍ 13 ላይ ከገባው ፈሊጣዊ አነጋገር ጋር ተመሳሳይነት ያለው አባባል ነው።

40፥20 *የፈርዖን የልደት በዓል፤* ከአያሌ ዓመታት በኋላ በሄሮድስ የልደት በዓል ላይ የአንድ ሌላ ሰው ራስ ተቈረጠ (ማቴ 14፥6-10 ይመ)።

41፥2 *ሰባት ላሞች ከወንዙ ወጥተው፤* አብዛኛውን ጊዜ

ይበሉ ጀመር። 3ቀጥሎም መልካቸው የከፋ ዐጥ
ንታቸው የወጣ፣ ሌሎች ሰባት ላሞች ከወ
ንዙ ወጥተው አስቀድመው ከወጡት ላሞች
አጠገብ ቆሙ። 4እነዚህ መልካቸው የከፋና ዐጥ
ንታቸው የወጣ ላሞች፣ እነዚያን ያማሩና የወ
ፈሩ ላሞች ሲውጡአቸው አየ፤ ከዚያም ፈር
ዖን ከእንቅልፉ ነቃ።
5ፈርዖንም እንደ ገና እንቅልፍ ወስዶት
ሳለ፣ ሌላ ሕልም አየ። በሕልሙም በአንድ
የእህል አገዳ ላይ፣ ፍሬያቸው የተንዠረገ
ገና ያማረ ሰባት የእሸት ዛላዎች ሲወጡ አየ።
6ከዚያም የቀጨጨና በምሥራቅ ነፋስ ተመ
ትተው የደረቁ ሰባት የእሸት ዛላዎች ወጡ።
7የቀጨጨት የእሸት ዛላዎች፣ ፍሬያቸው
የተንዠረገገውን ሰባቱን ያማሩ ዛላዎች ዋጡ
አቸው። በዚህ ጊዜ ፈርዖን ከእንቅልፉ ነቃ፤
ነገሩ ሕልም ነበር።
8በነጋታውም ፈርዖን መንፈሱ ታወከበት፤
ስለዚህ በግብፅ አገር ያሉትን አስማተኞችና
ጥበበኞች በሙሉ አስጠርቶ ሕልሞቹን ነገ
ራቸው፣ ይሁን እንጂ ሕልሞቹን ሊተረጕ
ምለት የቻለ አንድም ሰው አልተገኘም።
9በዚያን ጊዜ የመጠጥ አሳላፊዎች አለቃ
ፈርዖንን እንዲህ አለው፤ "የሠራሁት በደል
ዛሬ ታወሰኝ። 10በአንድ ወቅት ፈርዖን እኔ
ንና የእንጀራ ቤት አዛዡን ተቈጥቶ በዘበ
ኞቹ አለቃ ግቢ አስሮን ነበር። 11ሁለታች
ንም በአንዲት ሌሊት የተለያየ ሕልም አየን፤
የእያንዳንዳችንም ሕልም የየራሱ ትርጕም
ነበረው። 12በዚያን ጊዜ የዘበኞች አለቃ
አገልጋይ የሆነ አንድ ዕብራዊ ወጣት ከእኛ
ጋር እስር ቤት ነበር። ሕልማችንን በነገር
ነው ጊዜ፣ ፍቺውን ነገረን፤ ለእያንዳንዳች
ንም እንደ ሕልማችን ተረጐመልን፤ 13ነገሩም
ልክ እርሱ እንደተረጐመልን ሆነ፤ እኔ ወደ
ቀድሞ ሹመቴ ተመለስሁ፤ የእንጀራ ቤት
አዛዡም ተሰቀለ[f]።
14ፈርዖን ዮሴፍን እንዲያመጡት ትእዛዝ
ሰጠ፤ ከእስር ቤትም በጥድፊያ ይዘውት መጡ፤
ጢሙንም ከተላጨና ልብሱን ከለወጠ በኋላ
ፈርዖን ፊት ቀረበ።
15ፈርዖንም ዮሴፍን፣ "ሕልም አይቼ ነበር፤
ሕልሜን ሊተረጕምልኝ የቻለ አንድም ሰው
አልተገኘም፤ አንተ ግን ሕልም ሲነገርህ የመ
ተርጐም ችሎታ እንዳለህ ሰማሁ" አለው።
16ዮሴፍም ፈርዖንን፣ "እኔ የመተርጐም
ችሎታ የለኝም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ለፈርዖን የሚሻውን ትርጕም ይሰጠዋል" አለው።
17ከዚህ በኋላ ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህ አለው፤
"በሕልሜ በዐባይ ወንዝ ዳር ቆሜ ነበር።
18ሥጋቸው የወፈረና መልካቸው ያማረ ሰባት
ላሞች ከወንዙ ወጥተው በወንዙ ዳር የበ
ቀለውን ሣር ሲበሉ አየሁ። 19ከእነርሱም
በኋላ፣ ዐቅመ ደካማ፣ መልካቸው እጅግ
የከፋና ዐጥንታቸው የወጣ ሌሎች ሰባት
ላሞች ወጡ፤ እነዚያን የመሰሉ የሚያስከፉ
መልክ ያላቸው ላሞች በግብፅ ምድር ከቶ
አይቼ አላውቅም። 20ዐጥንታቸው የወጣና
አስከፊ መልክ ያላቸው ላሞች መጀመሪያ
የወጡትን፣ ሥጋቸው የወፈረውን ሰባቱን ላሞች
ዋጧቸው። 21ከዋጧቸውም በኋላ፣ ያው የበ
ፊቱ መልካቸው ስላልተለወጠ እንደዋጧቸው
ማንም ሊያውቅ አይችልም ነበር፤ ከዚያም
ከእንቅልፌ ነቃሁ።
22እንደዚሁም፣ በሕልሜ በአንድ የእህል
አገዳ ላይ ፍሬያቸው የፋፋና ያማሩ ሰባት
እሸት ዛላዎች ወጥተው አየሁ። 24የቀጨ
ጨት የእሸት ዛላዎችም ሰባቱን ያማሩ የእ
ሸት ዛላዎች ዋጧቸው፤ ይህንኑም ለአስማ
ተኞች ነገርሁ፤ ነገር ግን ማንም ሊፈታው
አልቻለም።"
25ዮሴፍም ለፈርዖን እንዲህ አለው፤ "ሁለ
ቱም የፈርዖን ሕልሞች ተመሳሳይና አንድ
ዐይነት ናቸው፤ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ወደ ፊት
የሚያደርገውን ለፈርዖን ገልጦለታል። 26ሰባቱ
የሚያማምሩ ላሞች፣ ሰባት ዓመታት ናቸው፣
ሰባቱም የሚያማምሩ የእሸት ዛላዎች ሰባት ዓመ
ታት ናቸው፤ ሕልሙም አንድና ተመሳሳይ
ነው። 27ከእነርሱም በኋላ ዐጥንታቸው የወጣ
አስከፊ መልክ ያላቸው ሰባት ላሞች፣ ሰባት ዓመ
ታት ናቸው፤ እንደዚሁም ፍሬ አልባ የሆ
ኑትና በምሥራቅ ነፋስ ተመትተው የደረቁት
ሰባት የእሸት ዛላዎች ሰባት የራብ ዓመታት
ናቸው።
"አስቀድሜ ለፈርዖን እንደተናገርኩት፣
እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ወደ ፊት የሚያደርገውን
ነገር ለፈርዖን ገልጦለታል። 29በመላው የግብፅ

[f]13 ወይም ተወጋ

41፥4 ቍ7
41፥5 ኢሱ13፥3፤ 2ነገ4፥42፤ኢዩ13፥5፤ኢሳ23፥3፤ኤር 2፥18
41፥6 ዘፀ10፥13፤ 14፥21፤ኢዮ6፥26፤ 11፥2፤15፥2፤መዝ 11፥6፤48፥7፤ኢሳ11፥ 15፤27፥8፤ኤር4፥11፤ 18፥17፤ሕዝ19፥12፤ 27፥26፤ሆሴ12፥1፤ 13፥15፤ዮና4፥8
41፥7 ቍ4
41፥8 ቍ24፤ዘፍ 40፥8፤ዘፀ7፥11:22፤ ኢዮ7፥14፤ዳን1፥20፤ 2፥1:2:3:4፥:5:19: 27፤4፥7:18፤5፥7
41፥9 ዘፍ40፥14
41፥10 ዘፍ37፥36፤ 39፥20፤40፥2
41፥11 ዘፍ40፥5
41፥12 ዘፍ14፥13፤ 37፥36፤39፥17፤40፥4: 12
41፥13 ዘፍ40፥22
41፥14 ዘፍ35፥2፤ 45፥22፤ሩት3፥3፤ 2ሳሙ12፥20፤መዝ 105፥20፤ኢሳ18፥2:7
41፥15 ዘፍ40፥8: 12፤ዳን4፥18፤5፥16
41፥16 ዘፍ40፥8
41፥17 ቍ1
41፥18 ቍ2
41፥24 ቍ8
41፥25 ዘፍ40፥8: 12፤ኢሳ46፥11፤ ዳን2፥45
41፥26 ቍ2
41፥27 ዘፍ12፥10
41፥28 ዘፍ40፥8
41፥29 ቍ47
41፥30 ቍ54:56፤ ዘፍ12፥10፤45፥6:11፤ 47፥13፤መዝ105፥16

ላሞች ከፀሐይና ከተባዮች ለመሸሽ ሲሉ በዐባይ ወንዝ ውስጥ እስከ ዐንገታቸው ድረስ ይዘፈቁ ነበር።

41፥6 *በምሥራቅ ነፋስ ተመትተው የደረቁ፤* በፀሐይ ወራት ማብቂያና በበልጉ ወራት ዋዜማ ላይ ከምድረ በዳ የሚነፍሰው (ሆሴ 13፥15 ይመ) የፓሌስቲና መንጠሌ ነፋስ (ግብፃውያን ከምሲን ይሉታል) አብዛኛውን ጊዜ ዕፀዋትን ያደርቃል (ኢሳ 40፥7፤ ሕዝ 17፥10 ይመ)።

41፥8 *መንፈሱ ታወከበት፤* 40፥6-7 ይመ። *አስማተኞችና* የጥንቈላን ሥራ የሚሠሩ ካህናት ሊሆኑ ይችላሉ። *ሕልሞቹን ነገ ራቸው፤ ይሁን እንጂ... ሊተረጕምለት የቻለ አንድም ሰው አልተገኘም፤* ዳን 2፥10-11 ይመ።

41፥13 *ልክ እርሱ እንደተረጐመልን ሆነ፤* ምክንያቱም የሚናገረው ቃል ከእግዚአብሔር ተሰጥቶታልና ነው (መዝ 105፥19 ይመ)።

41፥14 *ፈርዖን ዮሴፍን እንዲያመጡት ትእዛዝ ሰጠ፤* ከእስር ቤት እንዲለቀቅ አደረገ (መዝ 105፥20 ይመ)። *ጢሙን ከተላጨና፤* በግብፃውያን ዘንድ ጢሙር ሙልጭ አድርጎ መላጨት የተለመደ ሲሆን፣ በመካከለኛው ምሥራቅ ነዋሪዎች ዘንድ ደግሞ ጢምን ማሳደግ የተለመደ ነበር (2ሳሙ 10፥5፤ ኤር 41፥5 ይመ)።

41፥16 *እኔ የመተርጐም ችሎታ የለኝም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ለፈርዖን የሚሻውን ትርጕም ይሰጠዋል፤* 40፥8፤ ዳን 2፥27-28:30፤ 2ቆሮ 3፥5 ይመ።

41፥27 *ሰባት የራብ ዓመታት፤* ሐሥ 7፥11 ይመ። የዐባይ ወንዝ ዓመቱን ሙሉ ካፍ እስከ ገደፉሞልቶ ስለሚፈስ፣ በግብፅ ምድር ለረጅም ዘመን የሚቈይ ራብ ብዙ ጊዜ አይከሠትም፤ በሌሎች ቦታዎች ግን እንዲህ ያለውን ራብ ማየት የተለመደ ነው (2ነገ 8፥1 ይመ)። እንደ አዲስ ኪዳን አባባል በኤልያስ ዘመን የተከሠተው ታላቅ ራብ ለሦስት ዓመት ተኩል ቈይቶ ነበር (ያዕ 5፥17)፤ ራቡ ለሰባት ዓመት መቈየት ሲገባው በሦስት ዓመት ተኩል ሊቀንስ የቻለው በኤልያስ ጸሎት ነው። (1ነገ 18፥42፤ ያዕ 5፥18 ይመ)።

ምድር እጅግ የተትረፈረፈ ጥጋብ የሚሆን
ባቸው ሰባት ዓመታት ይመጣሉ:: 30ከዚህ
በኋላ ግን በተከታታይ ሰባት የራብ ዓመታት
ይሆናሉ:: የራቡ ዘመን አገሪቱን እጅግ ስለ
ሚጐዳት፣ በግብፅ የነበረው ያለፈው የጥ
ጋብ ዘመን ሁሉ ጨርሶ አይታወስም:: 31ከጥ
ጋቡ ዓመታት በኋላ የሚመጣው የራብ ዘመን
እጅግ ጽኑ ከመሆኑ የተነሣ፣ ቀደም ሲል
የነበረው የጥጋብ ዘመን ፈጽሞ ይረሳል::
32ሕልሙ ለፈርዖን በሁለት መልክ በድጋሚ
መታየቱ፣ ነገሩ ከእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ዘንድ የተ
ቈረጠ ስለ ሆነ ነው፤ ይህንንም እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) በቅርብ ጊዜ ይፈጽመዋል::

33እንግዲህ ፈርዖን ብልኅና አስተዋይ ሰው
ፈልጎ፣ በመላው የግብፅ ምድር ላይ አሁኑኑ
ይሹም:: 34እንደዚሁም በሰባቱ የጥጋብ ዓመ
ታት ከሚገኘው ምርት፣ አንድ አምስተኛው
እንዲሰበሰብ የሚያደርጉ ኀላፊዎችን ይሹም::
35እነርሱም በሚመጡት የጥጋብ ዓመታት
ከሚገኘው ምርት ሁሉ ይሰብስቡ፤ በፈርዖ
ንም ሥልጣን ሥር ያከማቹ፤ ለምግብ እን
ዲሆኑም በየከተማው ይጠበቁ:: 36የሚከማ
ቸው እህል፣ ወደ ፊት በግብፅ አገር ላይ
ለሚመጣው የሰባት ዓመት ራብ መጠባበቂያ
ይሁን፤ በዚህም ሁኔታ አገሪቱ በራብ አትጠፋም::"

37ዕቅዱንም ፈርዖንና ሹማምንቱ ሁሉ መል
ካም ሆኖ አገኙት:: 38ፈርዖንም፣ "የእግዚአ
ብሔር (ኤሎሂም) መንፈስ* ያለበት እንደዚህ ያለ
ሰው ማንን ልናገኝ እንችላለን?" ብሎ ጠየ
ቃቸው::

39ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ "እግዚአ
ብሔር (ኤሎሂም) ይህን ሁሉ ስለ ገለጠልህ፣ እን
ዳንተ ያለ አስተዋይና ብልኅ ሰው የለም::
40አንተ በቤተ መንግሥቴ የበላይ ትሆናለህ፤
ሕዝቤም ሁሉ ለሥልጣንህ ይገዛል፤ እኔ ከአ
ንተ የምበልጠው በዙፋኔ ብቻ ይሆናል::"

41፥32 ዘፍ40፥8፤ ዳን2፥5
41፥33 ቍ39፤ዘፍ 39፥9
41፥34 ቍ48፤ዘፍ 24:2፤47፥14:1ሳሙ 8፥15
41፥35 ቍ48
41፥36 ቍ56፤ዘፍ 42፥6፤47፥14
41፥37 ዘፍ45፥16፤ አስ2፥4፤ኢሳ19፥11
41፥38 ዘኍ27፥18፤ ዘዳ34፥9፤ዳን2፥11፤ 4፥8-9:18፤5፥11:14
41፥39 ቍ33፤ዳን 2፥11፤5፥11
41፥40 ዘፍ39፥9፤ 1ነገ4፥6፤2ነገ15፥5፤ አስ10፥3፤መዝ105፥ 21-22፤ኢሳ22፥15፤ 36፥3፤ሐሥ7፥10
41፥41 ቍ43:55፤ ዘፍ42፥6፤45፥8:13: 26፤አስ8፥2፤ኤር 40፥7፤ዳን6፥3
41፥42 ዘፍ24፥22፤ ዘፀ25፥4፤1ሳሙ17፥ 38፤18፥4፤1ነገ19፥19 ፤አስ3፥10፤6፥8:11፤ 8፥2:8:15፤መዝ73፥6 ፤ማሕ4፥9፤ኢሳ3፥18 ፤ሕዝ16፥11፤ዳን5፥7 :16:29፤ዘካ3፥4
41፥43 ቍ41፤ዘፍ 46፥29፤50፥9፤አስ6፥9 ፤10፥3፤ኢሳ2፥7፤22፥18
41፥44 ዘፍ37፥8፤ አስ10፥2፤መዝ105፥22
41፥45 ቍ50፤ዘፍ 46፥20:27፤ዘፀ2፥16፤ አስ2፥7፤ሕዝ30፥17
41፥46 ዘፍ37፥2፤ 1ሳሙ8፥11፤16፥21፤ ምሳ22፥29፤ዳን1፥19
41፥47 ቍ29
41፥48 ቍ34
41፥49 ዘፍ12፥2
41፥50 ቍ45
41፥51 ዘፍ46፥20፤ 48፥1:14:18:20፤49፥

## ዮሴፍ በግብፅ ተሾመ

41ከዚያም፣ ፈርዖን ዮሴፍን "በመላዪቱ የግ
ብፅ ምድር ላይ ኀላፊ አድርጌሃለሁ" አለው::
42ፈርዖንም ባለማኅተሙን ቀለበት ከጣቱ
አውልቆ በዮሴፍ ጣት ላይ አደረገው፤ እንዲ
ሁም ከጥሩ የተልባ እግር የተሠራ ልብስ አለ
በሰው፤ በዐንገቱም የወርቅ ሐብል አጠለቀ
ለት:: 43በማዕረግ ከእርሱ ሁለተኛ ሰው አድ
ርጎ፣ በሠረገላ ላይ አስቀመጠው*፤ ሰዎችም በፊቱ፣
"እጅ ንሡ" እያሉ ይጮኹ ነበር፤ በዚህ ሁኔ
ታም በግብፅ ምድር ሁሉ ላይ ሾመው::

44ከዚህ በኋላ ፈርዖን ዮሴፍን፣ "እኔ ፈር
ዖን ነኝ፤ ሆኖም በመላዪቱ ግብፅ ያላንተ
ትእዛዝ እጁንም ሆነ እግሩን ልውስ የሚያ
ደርግ አይኖርም" አለው:: 45ፈርዖንም ዮሴ
ፍን ጸፍናት ፐዕናህ ብሎ ስም አወጣለት::
እንዲሁም የሄልዮቱ* ከተማ ካህን የጶጥፌራ
ልጅ አስናትን አጋባው:: ዮሴፍም በመላዪቱ
የግብፅ ምድር ተዘዋወረ::

46ዮሴፍ የግብፅ ንጉሥ ፈርዖንን ማገልገል
ሲጀምር፣ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበር::
ዮሴፍም ከፈርዖን ፊት ወጥቶ የግብፅን
ምድር በሙሉ ዞረ::

47በሰባቱም የጥጋብ ዓመታት ምድሪቱ የተ
ትረፈረፈ ሰብል ሰጠች:: 48በእነዚያ ሰባት
የጥጋብ ዓመታት፣ ዮሴፍ በግብፅ አገር የተ
ገኘውን ምርት ሰብስቦ በየከተሞቹ አከማቸ፤
በእያንዳንዱ ከተማ ከየአቅራቢያው የተመረ
ተውን እህል እንዲከማች አደረገ:: 49ዮሴፍ
ብዛቱ እንደ ባሕር አሸዋ የሚሆን የእህል
ሰብል አከማቸ፤ ሰብሉ እጅግ ከመብዛቱ
የተነሣ ልኩን መስፈርና መመዝገብ አልቻ
ለም ነበር::

50ሰባቱ የራብ ዓመታት ከመምጣቱ በፊት፣
የሄልዮቱ ካህን የጶጥፌራ ልጅ አስናት ለዮሴፍ

*38 ወይም የአማልክት መንፈስ
*43 ወይም በማዕረግ ሁለተኛ በሆነው የእርሱ ሠረገላ ላይ፤ ወይም በሁለተኛ ሠረገላው ላይ *43 ወይም ስገዱ
*45 በቍ50 ላይ ያለውንም ጨምሮ ሆልዮፖሊስን ያመለክታል

*41፥32፤* መለኮታዊ መገለጦች ብዙውን ጊዜ የሚደጋገሙት ለአጽንዖት ነው (37፥5-9፤ አሞ 7፥1-6:7-9፤ 8፥1-3 ይመ)::

41፥38 *የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት፤* ይህ ሐረግ "የአ ማልክት መንፈስ ያደረበት" ተብሎም ሊተረጐም ይችላል፤ ቃሉን የተናገረው አረማዊ ንጉሥ በመሆኑ፣ ቃሉ የሚያመለክተው መን ፈስ ቅዱስን ነው ብሎ መገመት እጅግ ያስቸግራል::

41፥40 *አንተ... የበላይ ትሆናለህ፤* ፈርዖን የዮሴፍን ምክር ተቀብሎ (ቍ 33 ይመ)፣ ዮሴፍን "በግብፅ ሁሉ ላይ አዛዥ" እን ዲሆን ወሰነ (ሐሥ 7፥10፤ መዝ 105፥21 ይመ):: *ሕዝቤም ሁሉ ለሥልጣንህ ይገዛል፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ሕዝቤ ሁሉ ለጥ ብሎ እጅ ይነሣሃል" ማለት ነው፤ በሌላ አነጋገር ሕዝቤ ሁሉ ለአንተ ያለውን አክብሮትና ታዛዥነት ለመግለጽ እጅህን ወይም እግርህን ይስማል ማለት ነው (መዝ 2፥12 እና ማብ ይመ)::

*41፥42* አንድ ንጉሥ ሥልጣኑን ለሌላ ሰው ማስተላለፉን ወይም ማካፈሉን በተለያዩ ምልክቶች ይገልጽ ነበር፤ ይኸውም ቀለበት (አስ 3፥10)፣ መጐናጸፊያና (አስ 6፥11) የወርቅ ሐብል የመሳሰሉትን (ዳን 5፥7:16:29) በመስጠት ነው::

41፥43 *በማዕረግ ከእርሱ ሁለተኛ ሰው፤* ከራሱ ከንጉሡ ቀጥሎ የሚሰጥ ከፍተኛ ማዕረግ ነው:: *"እጅ ንሡ"፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ለጥ ብላችሁ እጅ ንሡ" ማለት ነው፤ ይህን ሐረግ ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጥ ቃል ከሲም ቋንቋ የተወሰደ ሲሆን ምናልባት "በግንባራችሁ ተደፍታችሁ እጅ ንሡ" የሚል ትርጕም ያለው የግብፃውያን ትእዛዝ ሰጪ አንቀጽ ሳይሆን አይቀርም::

41፥45 *ዮሴፍን ጸፍናት ፐዕናህ ብሎ ስም አወጣለት፤* በን ጉሣዊ አገዛዙ ውስጥ ከፍተኛ ባለሥልጣን አድርጎ ሾመው (የ1፥5 ማብ ይመ):: ፈርዖን ይህን አስደናቂ የጌታ ባሪያ ለራሱ ንጉሣዊ አገዛዝ ዐላማ ሊጠቀምበት ፈለገ፤ ይህም ከእርሱ በኋላ የተነሣው ሌላው ፈርዖን በእግዚአብሔር የተባረከችውን እስራኤልን፣ ግብፅን ለማበልጸግ ሊጠቀምባት እንደፈለገው ዐይነት ነው (ዘጸ 1):: ዮሴፍ የሚያገለግለው መንግሥቱና የማዳን ኀይሉ እጅግ ታላቅ የሆነ ውን አምላክ እንደ ሆነ ፈርዖን አላስተዋለም:: *አስናት፤* ግብፃዊ ስም ሲሆን ምናልባት የቃሉ ትርጕም "የኔይት (እንስት አምላክ) ነሽ" ማለት ሳይሆን አይቀርም:: *ጶጥፌራ፤* ጶጥፌራ (37፥36፤ 39፥1) በሚል ስም ከሚታወቀው ጋር አንድ አይደለም፤ ይህም ግብ ፃዊ ስም ሲሆን "ከ'ራ' (የፀሐይ አምላክ ነው) የተሰጠ" ማለት ነው:: *የሄልዮቱ ከተማ፤* ከአሁኗ ካይሮ በስተ ሰሜን 16 ኪሎ ሜትር ርቃ የምትገኝ ስትሆን፣ ግሪኮች ሄልዮት (የፀሐይ ከተማ) በማለት ሰይመዋታል፤ ይህች ከተማ "ራ" ተብሎ ለሚጠራው አምላክ የአምልኮ ማእከል ስትሆን፣ በከተማዋም ውስጥ ቤተ መቅደስ ይገኛል፤ ስለዚህ ጶጥፌራ በሚል ስም መጠራቱ ትክክል ነው::

41፥46 *ሠላሳ ዓመት፤* ዮሴፍ በዐሥራ ሦስት ዓመት (37፥2 ይመ) ጊዜ ውስጥ በግብፅ ምድር ሁሉ ላይ ከንጉሡ ቀጥሎ ከፍተኛ ሥልጣን የነበረው ሰው (ቍ 43) ሆነ::

41፥49 *እንደ ባሕር አሸዋ፤* እግዚአብሔር፣ አብርሃምንና ያዕቆብን ታላቅ ዘር እንደሚያደርጋቸው ቃል በገባ ጊዜ በዚህ

ሁለት ወንዶች ልጆች ወለደችለት። 51ዮሴፍም፣ "እግዚአብሔር (ኤሎሂም) መከራዬን ሁሉ፣ የአባቴንም ቤት እንድረሳ አድርጎኛል" በማለት የመጀመሪያ ልጁን ስም ምናሴ[ሠ] አለው። 52እንደዚሁም፣ "መከራ በተቀበልኩበት ምድር እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፍሬያማ አደረገኝ" ሲል ሁለተኛ ልጁን ኤፍሬም[ሸ] አለው።

53በግብፅ ምድር የነበረው ሰባቱ የጥጋብ ዘመን ዐለፈና 54ዮሴፍ አስቀድሞ እንደ ተናገረው የሰባቱ ዓመት የራብ ዘመን ጀመረ። ሌሎች አገሮች ሁሉ ሲራቡ፣ በመላው የግብፅ ምድር ግን ምግብ ነበር። 55ራቡ በመላው የግብፅ ምድር መስፋፋት ሲጀምር፣ ሕዝቡ ምግብ ይሰጠን በማለት ወደ ፈርዖን ጮኸ። ፈርዖንም ግብፃውያኑን፣ "ወደ ዮሴፍ ሂዱና የሚላችሁን አድርጉ" አላቸው።

56ራቡ በአገሩ ላይ እየተስፋፋ ስለ ሄደ፣ ዮሴፍ ጐተራዎቹን ከፍቶ እህሉ ለግብፃውያን እንዲሸጥ አደረገ፤ ምክንያቱም ራቡ በመላዪቱ ግብፅ ጸንቶ ነበር። 57ራቡ በመላው ዓለም ጸንቶ ስለ ነበር፣ የየአገሩ ሰዎች ሁሉ ከዮሴፍ ዘንድ እህል ለመሸመት ወደ ግብፅ ምድር መጡ።

## የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ግብፅ ሄዱ

42 ያዕቆብ በግብፅ እህል መኖሩን ሲሰማ፣ ልጆቹን እንዲህ አላቸው፤ "ለምን እርስ በርስ ትተያያላችሁ? 2በግብፅ እህል መኖሩን ሰምቻለሁ፤ ስለዚህ ከመሞት መስንበት ይሻላልና ወደዚያው ወርዳችሁ እህል ሸምቱልን" አላቸው።

3ከዚያም ዐሥሩ የዮሴፍ ወንድሞች እህል ለመሸመት ወደ ግብፅ ወረዱ። 4ነገር ግን ያዕቆብ የዮሴፍን ወንድም ብንያምን፣ ክፉ ነገር ይደርስበታል በሚል ፍርሀት ከወንድሞቹ ጋር አላከውም። 5ራቡ በከነዓንም በመበርታቱ፣ እህል ለመሸመት ወደ ግብፅ ከሄዱት ሰዎች መካከል የእስራኤል ልጆችም ነበሩ።

3፥50፥23፤ዘኍ1፥34፤ ዘዳ33፥17፤ኢሱ4፥12፤ 17፥1፤1ዜና7፥14
41፥52 ዘፍ17፥6፤ 46፥20፤48፥1:5፤50፥ 23፤ዘኍ1፥32፤26፥28 ፤ዘዳ33፥17፤ኢሱ14፥ 4፤መሳ5፥14፤1ዜና7፥ 20፤2ዜና30፥1፤መዝ 60፥7፤ኤር7፥15፤ አብ1፥19
41፥54 ዘፍ12፥10 ፤ሐሥ7፥11
41፥55 ቍ41፤ዘዳ 32፥24፤2ዜና20፥9፤ ኢሳ51፥19፤ኤር5፥ 12፤27፥8፤42፥16፤ 44፥27፤ዮሐ2፥5
41፥56 ቍ30:36፤ ዘፍ12፥10
41፥57 ዘፍ12፥10፤ 42፥5፤47፥15
42፥1 ሐሥ7፥12
42፥2 ቍ19:33፤ ዘፍ43፥2:4:8፤44፥25፤ 47፥19፤መዝ33፥18-19
42፥3 ቍ10፤ዘፍ 43፥20
42፥4 ቍ38፤ዘፍ 35፥18
42፥5 ቍ13:29፤ ዘፍ12፥10፤31፥18፤ 41፥57፤45፥17፤ዘዳ 32፥24፤ሐሥ7፥11
42፥6 ዘፍ33፥3፤ 41፥36:41፤ ነህ 5፥14
42፥7 ቍ30፤ዘፍ 29፥4
42፥8 ዘፍ37፥2
42፥9 ቍ12:14: 16:30፤ ዘፍ 37፥7፤ ዘዳ1፥22፤ኢሱ2፥1፤ 6፥22፤
42፥10 ቍ3፤ዘፍ 37፥8
42፥11 ቍ13:15: 16:19:20:31:34፤ዘፍ 44፥7:9:16:19:21:3 1፤46፥34፤47፥3
42፥12 ቍ9
42፥16 ቍ11:9: 15:19
42፥17 ዘፍ40፥4

6በዚህ ጊዜ ዮሴፍ የምድሪቱ ገዥ ነበር፤ ለአገሩ ሰዎች ሁሉ እህል የሚሸጥላቸው እርሱ ነበር። የዮሴፍ ወንድሞችም እንደ ደረሱ፣ ከፊቱ ቀርበው ወደ ምድር ለጥ ብለው እጅ ነሡት። 7ዮሴፍም ወንድሞቹን ገና ሲያያቸው ወዲያውኑ ዐወቃቸው፤ ነገር ግን እንደማያውቃቸው ሆኖ፣ "ከየት የመጣችሁ ናችሁ?" ብሎ በቍጣ ቃል ተናገራቸው። እነርሱም፣ "እህል፤ ለመሸመት ከከነዓን ምድር የመጣን ነን" ብለው መለሱለት።

8ዮሴፍ ወንድሞቹን ቢያውቃቸውም እንኳ እነርሱ ግን አላወቁትም። 9በዚህ ጊዜ ስለ ወንድሞቹ ያየው ሕልም ትዝ አለውና፣ "ሰላዮች ናችሁ፤ የመጣችሁት አገራችን በየትኛው በኩል ለጥቃት የተጋለጠች መሆኗን ለመሰለል ነው" አላቸው።

10እነርሱም እንዲህ አሉት፤ "ጌታችን ሆይ፤ እንዲህስ አይደለም፤ አገልጋዮችህ የመጣነው እህል ለመሸመት ነው፤ 11ሁላችንም የአንድ አባት ልጆች ነን፤ አገልጋዮችህ የታመንን ሰዎች እንጂ ሰላዮች አይደለንም።"

12እርሱም መልሶ፣ "አይደለም፤ በየት በኩል ለጥቃት የተጋለጠች መሆኗን ለመሰለል ነው" አላቸው።

13እነርሱ ግን መልሰው፣ "እኛ አገልጋዮችህ በከነዓን አገር ከሚኖር ከአንድ ሰው የተወለድን ዐሥራ ሁለት ወንድማማቾች ነን። ትንሹ ወንድማችን አባታችን ዘንድ ሲሆን፣ አንዱ ግን የለም" አሉት።

14ዮሴፍም እንዲህ አላቸው፤ "ነገርኋችሁ እኮ፤ ሰላዮች ናችሁ! 15ታናሽ ወንድማችሁ እዚህ እስካልመጣ ድረስ ከዚህ ንቅንቅ እንደማትሉ በፈርዖን ስም እምላለሁ፤ ማንነታችሁ

42፥13 ቍ5:11:24:32:36፤ዘፍ29:33፤37፥33፤43፥7፤44፥8፤46፥31 ፤47፥1፤ኤር31፥15 42፥14 ቍ9 42፥15 ቍ11፤ዘፍ43፥3:5:7፤ 44፥21:23፤1ሳሙ17፥55

ሠ51 *ምናሴ* የሚለው ቃል *መርሳት* የሚል ትርጒም ካለው የዕብራይስጥ ቃል የወጣ ሲሆን ከዚሁ ቃል ጋር አንድ ዐይነት ድምፅ አለው
ሸ52 *ኤፍሬም* የሚለው ቃል በዕብራይስጥ *ዕጥፍ ፍሬያማ* የሚል ትርጒም ካለው ቃል ጋር አንድ ዐይነት ድምፅ አለው።

ምሳሌያዊ አነጋገር ተጠቅሞአል (22፥17፤32፥12 ይመ)።

41፥52 ***ኤፍሬም፤*** የስሙ ትርጒም እግዚአብሔር ለዮሴፍ ሁለት ወንዶች ልጆች እንደ ሰጠው የሚያመለክት ሲሆን (ቍ 50 ይመ)፣ ኤፍሬም የሚለው ቃል በዕብራይስጡ "ዕጥፍ ፍሬ" የሚል ፍቺ አለው።

41፥57 ***በመላው ዓለም፤*** ጸሓፊው የሚያውቀውን ዓለም ማለትም (መካከለኛውን ምሥራቅ) የሚያመለክት አነጋገር ሊሆን ይችላል። በዮሴፍ ዘመን ስለ ደረሰው ራብ የተሰጠው ገለጻ ጸሓፊው በኖኅ ዘመን ደርሶ ስለ ነበረው የጥፋት ውሃ የሰጠውን ገለጻ የሚያስታውስ ነው። ኖኅ ከጥፋት ውሃ በኋላ ለነበረው ትውልድ አባት (ከአዳም ቀጥሎ) እንዲሆን፣ እግዚአብሔር ኖኅንና ቤተ ሰቡን ብቻ ከጥፋት ውሃ አዳነ። እግዚአብሔር ከድኅረ ውሃ ጥፋት በኋላ እና ከድኅረ ባቢሎን ሕዝቦች መካከል አብርሃምን በመጥራት ለሁለተኛ ጊዜ አንድን ሰው ብቻ መርጦ የሕዝቡ አባት አደረገው። እግዚአብሔር በዚህ ሰውና በዘሩም በኩል "የምድር ነገዶች ሁሉ ይባረካሉ" (12፥3) በማለት ተስፋ ሰጥቶ ነበር። በዚህ አዲስ ክሥተት ውስጥ የተስፋው ቃል የተመሠረተው ከእነዚህ ዘሮች በአንዱ ላይ እንደ ሆነ፣ ጸሓፊው ያለውን እምነት በእርግጠኛነት ይገልጻል።

*42፥2-3* በዚህ ቦታ የተነገረውን ታሪክ እስጢፋኖስ ጠቅሶታል (ሐሥ 7፥12)።

42፥4 ***ያዕቆብ የዮሴፍን ወንድም ብንያምን... አላከውም፤*** እናታቸው ራሔል ሞታ ስለ ነበር (35፥19) ዮሴፍም ሞቶአል ብሎ ያዕቆብ ዐሰበ (37፥33)። ያዕቆብ ከሚወዳት ሚስቱ የተወለደውን፣ አንድ የቀረውን ልጁን ብንያምን ማጣት አልፈለገም።

42፥5 ***ራቡ በከነዓንም በመበርታቱ፤*** በአብርሃም ዘመን እንደ ነበረ ሁሉ ማለት ነው (12፥10 እና ማብ ይመ)።

42፥6 ***ለጥ ብለው እጅ ነሡት፤*** የዮሴፍ ሕልም መፈጸሙን የሚያመለክት ነው፤ (37፥7:9 ይመ)።

42፥8 ***ዮሴፍ ወንድሞቹን ቢያውቃቸውም፤*** ምንም እንኳ ለመጨረሻ ጊዜ ካያቸው ቢያንስ 20 ዓመት ያለፈ ቢሆንም (37፥2፤ 41፥46: 53-54 ይመ)፣ ከመጐልመሳቸው በቀር መልካቸው ብዙም አልተለወጠበትም። ***እነርሱ ግን አላወቁትም፤*** ዮሴፍ ለባርነት ሲሸጥ ገና ለጋላጋ ወጣት የነበረ ሲሆን፣ አሁን ግን ባልተጠበቀ ሁኔታ ከሥልጣን መንበር ላይ ሲወጣ ጐልማሳ ሆኖ አል፤ የግብፃውያንን ልብስ ለብሶአል፤ ወንድሞቹንም የሚያናግራቸው በአስተርጓሚ ነበር (ቍ 23 ይመ)፤ ከዚህም በተጨማሪ ጠጕሩን የተላጨው፣ በግብፃውያን ባሕልና ልማድ መሠረት ነው (የ41፥14 ማብ ይመ)።

42፥10 ***ጌታችን ሆይ... አገልጋዮችህ፤*** የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍ ያየውን ሕልምና እነርሱም ሲፈሩት የነበረውን ነገር ሳያስተውሉት እንደ ገና ፈጸሙት (37፥8 ይመ)።

42፥15 ***በፈርዖን ስም እምላለሁ፤*** በወቅቱ በሥልጣን መንበር ላይ ባለው ገዢ ስም (በዚህ ቦታ እንደ ተነገረው) ወይም

የሚረጋገጠውም በዚህ ነው። [16]በሉ፣ ከእና
ንተ አንዱን ላኩና ወንድማችሁን ይዞ ይመ
ለስ፤ የቀራችሁት ግን የተናገራችሁት ቃል
እስኪረጋገጥ ድረስ፣ እስር ቤት ትቈያላችሁ።
እንደተናገራችሁት ካልሆነ ግን፣ በፈርዖን
ስም እምላለሁ፤ ሁላችሁም ሰላዮች ናችሁ”
አላቸው። [17]ሁሉንም ሦስት ቀን በእስር አቈ
ያቸው።

[18]በሦስተኛውም ቀን ዮሴፍ እንዲህ አላ
ቸው፤ “እኔ እግዚአብሔርን (ኤሎሂም) ስለምፈራ
እንዲህ በማድረግ ሕይወታችሁን አትርፉ።
[19]ታማኝ ሰዎች ከሆናችሁ፣ ከመካከላችሁ
አንዱ እዚህ እስር ቤት ሲቈይ፣ የቀራችሁት
ግን ለተራቡት ቤተ ሰቦቻችሁ እህል ትወስ
ዱላቸዋላችሁ፤ [20]ታናሽ ወንድማችሁን ግን
ይዛችሁ መምጣት አለባችሁ፤ በዚህም የተ
ናገራችሁት ቃል እውነተኛነት ይረጋገጣል፤
እናንተም ከመሞት ትተርፋላችሁ።” እነር
ሱም ይህንኑ ለመፈጸም ተስማሙ።

[21]እርስ በርሳቸውም፣ “ይኸው በወንድማ
ችን ላይ ባደረስነው በደል ምክንያት ቅጣ
ታችንን እየተቀበልን ነው። እርሱ እንደዚያ
ተጨንቆ ስለ ሕይወቱ ሲማጠነን፣ እኛ አል
ሰማነውም ነበር፤ ይህ መከራ የደረሰብንም
በዚሁ ምክንያት ነው” ተባባሉ።

[22]ሮቤልም መልሶ፣ “በዚህ ልጅ ላይ፣ ‘ክፉ
ነገር አታድርጉ’ ብዬ አልነበረምን? እናንተ
ግን አልሰማችሁኝም፤ ስለዚህም ደሙ ከእጃ
ችን ይፈለጋል” አላቸው። [23]ዮሴፍ የሚያነጋግራ
ቸው በአስተርጓሚ ስለ ሆነ የሚነጋገሩትን
እንደሚሰማቸው አላወቁም ነበር።

[24]ከፊታቸውም ዘወር ብሎ አለቀሰ፤ ከዚ
ያም ወደ እነርሱ ተመልሶ እንደ ገና አነጋ
ገራቸው፤ ስምዖንንም ከእነርሱ ለይቶ ዐይ
ናቸው እያየ አሰረው።

[25]በስልቻዎቻቸው እህል እንዲሞሉላቸው፣
ብሩንም በያንዳንዱ ሰው ስልቻ ውስጥ መል
ሰው እንዲያስቀምጡና ለጕዞአቸው ስንቅ እን
ዲያሲዟቸው ዮሴፍ ትእዛዝ ሰጠ። ይህም
ከተደረገላቸው በኋላ፣ [26]እህላቸውን በአህዮ
ቻቸው ጭነው ጕዞአቸውን ቀጠሉ።

[27]በመንገድም ለዐዳር ሰፍረው ሳሉ፣ ከእ
ነርሱ አንዱ ከያዘው እህል ላይ ለአህያው
ለመስጠት ስልቻውን ሲፈታ፣ በስልቻው አፍ
ላይ ብሩን አገኘ። [28]እርሱም ወንድሞቹን፣
“ኧረ ብሬ ተመልሶልኛል፤ ይኸው ስልቻዬ
ውስጥ አገኘሁት” አላቸው።

ሁሉም ልባቸው በድንጋጤ ተሞልቶ እየ
ተንቀጠቀጡ በመተያየት፣ “እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ምን ሊያመጣብን ይሆን?” አሉ።

[29]በከነዓን ምድር ወዳለው ወደ አባታቸው
ወደ ያዕቆብ ከደረሱ በኋላ፣ ያጋጠማቸውን
ሁሉ እንዲህ ብለው ነገሩት፤ [30]“የአገሩ ጌታ የሆ
ነው ሰው ምድሪቱን እንደምንሰልል ቈጥ
ሮን በቍጣ ተናገረን። [31]እኛ ግን እንዲህ
አልነው፤ ‘እኛ የታመንን ሰዎች እንጂ ሰላ
ዮች አይደለንም። [32]እኛ የአንድ አባት ልጆች
የሆንን፣ ዐሥራ ሁለት ወንድማማቾች ነን፤
አንዱ የለም፤ ታናሽ ወንድማችን ግን ከአ
ባታችን ጋር በከነዓን ይገኛል።’

[33]“ከዚህ በኋላ የአገሩ ጌታ የሆነው ሰው
እንዲህ አለን፤ ‘ታማኝ ሰዎች መሆናችሁን
የማውቀው በዚህ ነው፤ ከእናንተ መካከል
አንዱን ወንድማችሁን እዚህ እኔ ዘንድ ትታ
ችሁ የተቀራችሁት ለተራቡት ቤተ ሰቦቻ
ችሁ እህል ይዛችሁላቸው ሂዱ። [34]ነገር ግን
ታናሽ ወንድማችሁን ወደ እኔ አምጡት።
በዚያንም ጊዜ ታማኝ ሰዎች እንጂ ሰላዮች
አለመሆናችሁን ዐውቃለሁ፤ ወንድማችሁንም
መልሼ እሰጣችኋለሁ፤ እናንተም በምድሪቱ
እንደ ልብ ለመዘዋወር ትችላላችሁ።’ ”

[35]እህሉንም ሲዘረግፉ በየስልቾቻቸው ውስጥ
ብራቸው እንደ ተቋጠረ ተገኘ፤ የእያንዳን
ዳቸውን የተቋጠረ ብር ሲያዩም፣ እነርሱም
ሆኑ አባታቸው ደነገጡ። [36]አባታቸው ያዕ
ቆብም፣ “ያለ ልጅ እኮ አስቀራችሁኝ፤ ዮሴፍ
የለም፤ ስምዖንም የለም፤ አሁን ደግሞ ብን
ያምን ልትወስዱ ትፈልጋላችሁ፤ ኧረ ምን
ጕድ ነው የመጣብኝ!” አላቸው።

[37]በዚህን ጊዜ ሮቤል አባቱን፣ “መልሼ
ባላመጣው፣ ሁለቱን ወንዶች ልጆቼን ግደ
ላቸው፤ ኀላፊነቱን ለእኔ ተውልኝ፤ እኔው
መልሼ አመጣዋለሁ” አለው።

[38]ያዕቆብም፣ “ልጄ አብሮአችሁ ወደዚያ
አይወርድም፤ ወንድሙ እንደሆን ሞቶአል፤
የቀረው እርሱ ብቻ ነው። ይዛችሁት ስት
ሄዱ በመንገድ ላይ አደጋ ቢደርስበት፣ ሽበ
ቴን በመሪር ሐዘን ወደ መቃብር[a] ታወር
ዱታላችሁ” አላቸው።

### የዮሴፍ ወንድሞች ዳግመኛ ወደ ግብፅ መሄዳቸው

43 ራቡ አሁንም በምድሪቱ ላይ እንደ
ጸና ነበር፤ [2]ከግብፅ ያመጡትንም
እህል በልተው ከጨረሱ በኋላ፣ አባታቸው
“እስቲ እንደ ገና ወርዳችሁ፣ ጥቂት እህል
ሸምቱልን” አላቸው።

[3]ይሁዳ ግን እንዲህ አለው፤ “ያ ሰው ‘ወን
ድማችሁን ይዛችሁ ካልመጣችሁ ዳግመኛ

[a]38 ዕብራይስጡ ሲኦል ይለዋል

42፥18 ዘፍ20፥11፤ 22፥12፤ዘሌ19፥14፤ 25፥43፤2ሳሙ23፥3
42፥19 ቍ2፡11፡16
42፥20 ቍ15
42፥21 ዘፍ37፥26-28፤45፥5
42፥22 ዘፍ9፥5፤ 37፥21-22፤45፥24
42፥23ዘፍ11፥7፤ 38፥16
42፥24 ቍ13፤ዘፍ 29፥11፤43፥14፡23
42፥25 ቍ 27፡35፤ ዘፍ 43፥2፡12፡18፡21፤ 44፥1፡8፤ 45፥21፡23፤ ኢር40፥5
42፥26 ዘፍ32፥15፤ 44፥13፤45፥17፤1ሳሙ25፥18፤ኢሳ30፥6
42፥27 ቍ25፤መሳ 19፥19፤ኢዮ39፥9፤ ኢሳ1፥3
42፥28 ዘፍ43፥23፤ ኢሱ2፥11፤5፥1፤7፥5፤ ማር5፥33
42፥29 ቍ5፤ዘፍ 44፥24
42፥30 ቍ7፡9
42፥31 ቍ11
42፥32 ቍ13
42፥33 ቍ2
42፥34 ቍ11፡24፤ ዘፍ34፥10
42፥35 ቍ25፤ዘፍ 43፥18
42፥36 ቍ13፡24
42፥37 ዘፍ39፥4፤ 43፥9፤44፥32
42፥38 ቍ4፤ዘፍ 37፥33፡35፤44፥29፡ 34፤48፥7
43፥1 ዘፍ12፥10
43፥2 ዘፍ42፥2፡25
43፥3 ቍ8፤ዘፍ44፥ 14፡18፤42፥15፤ 46፥28
43፥4 ዘፍ42፥2
43፥5 ዘፍ42፥15፤ 44፥26፤2ሳሙ3፥13

በተናጋሪው አማልክት ስም (መዝ 16፥4፤ አሞ 8፥14) ወይም በራሱ በእግዚአብሔር ስም የሚነገር ከሁሉ የበለጠ ታላቅ መሐላ ነው (መሳ 8፥19፤ 1ሳሙ 14፥39፡45፤ 19፥6)።

42፥21 *ቅጣታችንን እየተቀበልን ነው፤* የዮሴፍ ወንድሞች የዘሩትን በማጨድ ላይ መሆናቸውን እየተገነዘቡ መጡ (ገላ 6፥7 ይመ)።

*42፥22፤* 37፥21-22 እና የ37፥21 ማብ ይመ።

42፥24 *ስምዖንንም ከእነርሱ ለይቶ፤* የያዕቆብ ሁለተኛ ልጅ (29፥32-33 ይመ) በበኵሩ በሮቤል ፈንታ ታሰረ፤ ይህ የሆነው ምናልባትም ሮቤል ከዓመታት በፊት የዮሴፍን ሕይወት ስላዳነ ሊሆን ይችላል (37፥21-22)።

42፥37 *ሁለቱን ወንዶች ልጆቼን፤* ሮቤል ለወንድሙ ለብንያም ደኅንነት ሲል ለመክፈል ያሰበውን መሥዋዕትነት ያመለክታል (የ37፥21 ማብ ይመ)።

43፥3 *ይሁዳ ግን እንዲህ አለው፤* ከዚህ በኋላ ይሁዳ የወን

ፊቴን አታዩም’ ብሎ በጥብቅ አስጠንቅቆ
ናል፤ 4ወንድማችን ከእኛ ጋር እንዲወርድ
ከፈቀድህ ወደዚያ ሄደን እህል እንሸምት
ልሃለን፤ 5እርሱን የማትልከው ከሆነ ግን እኛም
ወደዚያ አንወርድም፤ ያም ሰው፣ ‘ወንድማች
ሁን ይዛችሁ ካልመጣችሁ ዳግመኛ ፊቴን
አታዩም’ ብሎናል።”
6እስራኤልም፣ “ሌላ ወንድም አለን ብላ
ችሁ ለዚያ ሰው በመንገር ለምን ይህን
ችግር እንዲደርስብኝ አደረጋችሁ?” ሲል
ጠየቃቸው።
7እነርሱም፣ “ሰውየው ስለ ራሳችንና ስለ
ቤተ ሰባችን አጥብቆ ጠየቀን፤ እንደ ገናም
አባታችሁ አሁንም በሕይወት አለ? ሌላስ
ወንድም አላችሁ’ ሲል ጠየቀን። እኛም
ለጥያቄው መልስ ሰጠነው። ታድያ፣ ‘ወን
ድማችሁን ይዛችሁ ወደዚህ እንድትመጡ’
እንደሚል እንዴት ማወቅ እንችል ነበር?”
ብለው መለሱለት።
8ይሁዳም አባቱን እስራኤልን እንዲህ አለው
“ልጁን ከእኔ ጋር ስደደው፤ እኛም በቶሎ
እንሂድ፤ ይህ ከሆነ፣ አንተም፣ እኛም፣ ልጆ
ቻችንም አንሞትም፤ እንተርፋለን። 9ስለ ልጁ
ደኅንነት እኔ ራሴ ኀላፊ ነኝ፤ ስለ እርሱም
በግል ተጠያቂ እሆናለሁ፤ እርሱንም በደኅና
መልሼ ባላመጣውና እዚህ በፊትህ ባላቆ
መው ለዘላለም በደለኛ እኔ ልሁን። 10ይህን
ያህል ባንዘገይ ኖሮ፣ እስካሁን ሁለት ጊዜ
ደርሰን መመለስ በቻልን ነበር።”
11ከዚህ በኋላ አባታቸው እስራኤል እንዲህ
አላቸው፤ “ነገሩ እንዲህ ከሆነስ ይህን አድ
ርጉ፤ ምድሪቱ ከምታፈራው ምርጥ ነገሮች
ጥቂት በለሳን፣ ጥቂት ማር፣ ሽቱ፣ ከርቤ
ተምርና ለውዝ በየስልቻችሁ ይዛችሁ ለዚያ
ሰው እጅ መንሻ ውሰዱለት። 12በየስልቻቻ
ችሁ አፍ ላይ የተገኘውን ብር መመለስ
ስላለባችሁ፣ ዕጥፍ ገንዘብ ያዙ፤ ያ በየስል
ቾቻችሁ ውስጥ የተገኘው ብር ምናልባት
በስሕተት የመጣ ሊሆን ይችላል። 13ወንድ
ማችሁንም ይዛችሁ ወደ ሰውዬው በቶሎ
ሂዱ። 14ሌላውን ወንድማችሁንና ብንያምን
ይዛችሁ ለመመለስ እንድትችሉ ሁሉን የሚ
ችል[θ] አምላክ በምሕረቱ የዚያን ሰው ልብ
ያራራላችሁ። እንግዲህ ልጆቼንም ባጣ ምን
አደርጋለሁ፤ ያመጣውን እቀበላለሁ።”

15ሰዎቹም እጅ መንሻውን፣ የብሩን ዕጥፍ
እንዲሁም ብንያምን ይዘው ተነሡ፤ ወደ
ግብፅም በፍጥነት ወረዱ፤ ዮሴፍም ፊት
ቀረቡ። 16ዮሴፍ ብንያምን ከወንድሞቹ ጋር
ባየው ጊዜ የቤቱን አዛዥ፣ “እነዚህን ሰዎች
ወደ ቤት ይዘሃቸው ሂድ፤ ዛሬ ቀትር ላይ
አብረውኝ ስለሚበሉ ፍሪዳ ተጥሎ ምሳ ይዘ
ጋጅ” አለው።
17አዛዡም ዮሴፍ የነገረውን አደረገ፤ ሰዎ
ቹንም ወደ ዮሴፍ ቤት ወሰዳቸው። 18ሰዎ
ቹም ወደ ዮሴፍ ቤት በመወሰዳቸው ፈሩ፤
እነርሱም፣ “ወደዚህ የመጣነው፣ ቀደም ሲል
እዚህ መጥተን ስንመለስ በየስልቾቻችን
ውስጥ ተመልሶ በተጨመረው ብር ሰበብ
ነው። ሰውዬው ጥቃት ሊፈጽምብን፣ አስገ
ድዶ ባሮቹ ሊያደርገንና አህዮቻችንን ሊቀ
ማን ይፈልጋል” ብለው ሠጉ።
19ወደ ዮሴፍ ቤት አዛዥ ቀርበው፣ በቤቱ
መግቢያ ላይ አነጋገሩት፤ 20እንዲህም አሉት፤
ለመጀመሪያ ጊዜ እህል ለመሸመት ወደዚህ
መጥተን ነበር፤ 21ነገር ግን ለዐዳር በሰፈር
ንበት ቦታ የየስልቾቻችንን አፍ ስንከፍት፣
እያንዳንዳችን በስልቾቻችን አፍ ላይ፣ ብራ
ችንን ሙሉውን አገኘነው። ገንዘቡንም ይኸው
መልሰን ይዘን መጥተናል። 22አሁንም እህል
መሸመቻ የሚሆነን ተጨማሪ ብር ይዘን
መጥተናል፤ ያኔ ገንዘቡን በየስልቾቻችን
ውስጥ ማን መልሶ እንዳስቀመጠው ግን አና
ውቅም” አሉት።
23የቤቱ አዛዥም፣ “አይዞአችሁ አትፍሩ፤
በየስልቾቻችሁ ውስጥ ያገኛችሁትን ገን
ዘብ የሰጣችሁ የእናንተም የአባቶቻችሁም
አምላክ (ኤሎሂም) ነው፤ እኔ እንደሆንኩ ብሩን
ተቀብያለሁ” አላቸው። ከዚያም ስምዖንን
አውጥቶ አገናኛቸው።
የቤቱ አዛዥ ሰዎቹን ወደ ዮሴፍ ቤት
አስገብቶ እግራቸውን የሚታጠቡበት ውሃ
አቀረበላቸው፤ ለአህዮቻቸውም የሚበሉት
ገፈራ ሰጣቸው። 25ምሳ በዚያ እንደሚበሉ
ተነግሯቸው ስለ ነበር፣ ዮሴፍ በቀትር
ከመግባቱ በፊት እጅ መንሻዎቻቸውን ለማ
በርከት ተዘጋጁ።
26ዮሴፍም ወደ ቤቱ ሲገባ ያመጧቸውን
እጅ መንሻዎች አበረከቱለት፤ ወደ መሬት
ዝቅ ብለውም እጅ ነሡት። 27ዮሴፍም ስለ

θ14 ዕብራይስጡ ኤልሻዳይ ይላል።

43፥6 ቊ8:11፤ ዘፍ17፥5፤34፥30
43፥7 ቊ27፤ዘፍ 42፥13:15፤ 44፥19፤ 45፥3
43፥8 ቊ3:6፤ዘፍ 29፥35፤42፥21፤መዝ 33፥18-19
43፥9 ዘፍ42፥37፤ 44፥10:17፤1ሳሙ 23፥20፤ፊሞ1፥18-19
43፥10 ዘፍ45፥9
43፥11 ቊ6፤ዘፍ 24፥10፤32፥13፤37፥25፤ዘፀ30፥23፤1ነገ 10፥2፤ሕዝ27፥17:22
43፥12 ቊ15፤ዘፍ 42፥25፤ዘፀ22፥4:7፤ ምሳ6፥31
43፥13 ቊ3
43፥14 ዘፍ17፥1፤ 42፥24፤ዘዳ13፥7፤መዝ 25፥6፤2ሳሙ18፥33፤ አስ4፥16
43፥15 ቊ12፤ዘፍ 45፥9-13፤47፥2:7፤ ማቴ2፥11
43፥16 ቊ17:24: 26:31፤ዘፍ35፥18፤ 44፥1:4:12፤2ሳሙ 19፥17፤ኢሳ22፥15፤ ሉቃ 15፥23
43፥17 ቊ16
43፥18 ዘፍ32፥11፤ 34፥28፤42፥25:35፤ 44፥14፤44፥9:14:16: 33፤50፥18፤34፥28
43፥19 ቊ16
43፥20 ዘፍ42፥3
43፥21 ቊ15፤ዘፍ 42፥25
43፥23 ዘፍ24፥12፤ 31፥5፤42፥24:28፤ዘፀ 3፥6
43፥24 ቊ16፤ዘፍ 18፥4
43፥25 ቊ16፤ዘፍ 32፥13
43፥26 ቊ16፤ዘፍ 32፥13፤33፥3፤ማቴ 2፥11
43፥27 ቊ7፤ዘፍ 37፥3
43፥28 ዘፍ44፥24: 27:30፤18፥2፤37፥7፤ ዘፀ18፥7
43፥29 ዘፍ35፥18፤ 42፥13፤ዘኁ6፥25፤ መዝ67፥1፤119፥58፤ ኢሳ30፥18-19፤33፥2
43፥30 ዘፍ29፥11፤ ዮሐ11፥33:38

ድሞቹ አፈ ቀላጤ ሆነ (ቊ 8-10፤ 44-34፣ 46፥28 ይመ)።
የይሁዳ ነገድ ከዐሥራ ሁለቱ ነገዶች የላቀ ቦታ ያገኘ ሲሆን፣
የኢየሱስ የዘር ሐረግ ለመሆንም በቅቶአል (ማቴ 1:2:17፤ ሉቃ
3፥23:33 ይመ)።

*43፥9፤* ይሁዳ ከሮቤል በተሻለ ሁኔታ ራሱን ለብንያም
ደኅንነት ሲል፣ መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ (42፥37 እና ማብ
ይመ)።

43፥11 *በለሳን... ከርቤ፤* 37፥25 እና ማብ ይመ። *ማር፤*
ንቦች የሚያዘጋጁት ወይም ከተፈላ የወይን ወይም የተምር ጭማቂ
የሚዘጋጅ ጣፋጭ መጠጥ ነው። *ለውዝ፤* በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ
የተጠቀሰው በዚህ ቦታ ብቻ ነው፤ በትንሹ እስያ፣ በሶርያና በመ
ካከለኛው ምሥራቅ የሚበቅል የአንድ አጭር ዛፍ ፍሬ ነው፤ ዛፉ
በግብፅ አይበቅልም። *እጅ መንሻ ውሰዱለት፤* በዚያን ዘመን ከፍ
ባለ የሥልጣን መንበር ላይ ያለን ሰው ማለትም ፖለቲካዊ (1ሳሙ
16፥2 ይመ)፣ ወታደራዊ (1ሳሙ 17፥18 ይመ) ወይም ሃይማኖ
ታዊ (2ነገ 5፥15 ይመ) ሥልጣን የጨበጠን ሰው እጅ ለመንሳት
ሲገባ የሚደረግ ባሕላዊ ልማድ ነው።

43፥14 *ሁሉን የሚችል አምላክ፤* የ17፥1 ማብ ይመ። *እን
ግዲህ ልጆቼንም ባጣ ምን አደርጋለሁ፤* አስቴር የተናገረችውን
ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (ኢሳ 4፥16)።

*43፥21፤* ወንድማማቾቹ ለዮሴፍ ቤት አዛዥ የተናገሩት
ቃል የሆነውን ነገር ባጭሩ የሚገልጽ ነው (42፥27:35 ይመ)።

43፥23 *ገንዘብ የሰጣችሁ የእናንተም... አምላክ ነው፤*
የዮሴፍ የቤቱ አዛዥ ከሚያውቀው በላይ ዘልቆ ተናገረ።

*43፥24፤* የ18፥2 ማብ ይመ።

43፥26 *ዝቅ ብለውም እጅ ነሡት፤* ይህም የሚገልጸው
ከዮሴፍ ሕልም ፍጻሜዎች አንዱን ነው (37፥7:9፤ 42፥6፤ 43፥28
ይመ)።

ደኅንነታቸው ጠየቃቸው፤ ከዚያም "ሽማግሌ
አባት እንዳላችሁ ነግራችሁኝ ነበር፤ ደኅና ነው?
አሁንም በሕይወት አለ?" አላቸው።
28እነርሱም መልሰው፣ "አገልጋይህ አባታ
ችን አሁንም በሕይወት አለ፤ ደኅና ነው'።
በማለት ወደ መሬት ዝቅ ብለው በአክብ
ሮት እጅ ነሡት።
29ዮሴፍ በዐይኑ ሲቃኝ የእናቱን ልጅ ብንያ
ምን አየና፣ "ያ የነገራችሁኝ ታናሽ ወንድማችሁ
ይህ ነው?" ብሎ ጠየቃቸው። ብንያምንም፣
"ልጄ፤ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ይባርክህ" አለው።
30ዮሴፍ ወንድሙን በማየቱ ስሜቱ በጥልቅ
ስለ ተነካ፣ ፈጥኖ ከፊታቸው ገለል አለ፤ ሰወር
ያለ ቦታም ፈልጎ፣ ዕልፍኙ ውስጥ አለቀሰ።
31ፊቱን ከታጠበ በኋላ፣ ተመልሶ፣ ስሜ
ቱን በመቈጣጠር፣ "ማእድ ይቅረብ" አለ።
32ለዮሴፍ ለብቻው ቀረበለት፤ ለወንድሞ
ቹም ለብቻቸው ቀረበላቸው፤ እንዲሁም
ከእርሱ ጋር ለሚበሉት ግብፃውያን ደግሞ
ሌላ ገበታ ቀረበላቸው፤ ምክንያቱም ግብፃ
ውያን ከዕብራውያን ጋር አብሮ መመገብን
እንደ ጸያፍ ይቈጥሩት ነበር። 33ወንድማማ
ቾቹ ከበኵሩ እስከ ታናሹ እንደየዕድሜ
አቸው በዮሴፍ ፊት በተርታ ተቀምጠው
ነበር፤ በመገረምም እርስ በርሳቸው ተያዩ።
34ከዮሴፍ ገበታ ላይ እየተነሣ ለእያንዳንዳ
ቸው ምግብ ሲቀርብ፣ የብንያም ድርሻ
ከሌሎቹ አምስት ዕጥፍ ነበር። እነርሱም
እንዲህ ባለ ሁኔታ አብረውት ተደሰቱ፤
እስኪረኩም ጠጡ።

## የብር ዋንጫ በስልቻ

44 ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ለቤቱ አዛዥ
እንዲህ ሲል መመሪያ ሰጠው፤ "የሰ
ዎቹ ስልቻ የሚይዘውን ብር በየስልቻቸው
አፍ ክተተው። 2ከዚያም የብር ዋንጫዬን
በታናሹ ወንድማቸው ስልቻ አፍ ከእህሉ
ዋጋ ጋር ጨምረው።" አዛዡም ዮሴፍ እን
ዳለው አደረገ።
3ጎሕ ሲቀድ ሰዎቹ ከነአህዮቻቸው ተሸኙ።
4ከከተማው ምንም ያህል ርቀው ሳይሄዱ፣
ዮሴፍ የቤቱን አዛዥ እንዲህ አለው፤ "እን

43፥31 ቊ16፤ዘፍ 45፥1፤ኢሳ30፥18፤ 42፥14፤63፥15፤ 64፥12
43፥32 ዘፍ14፥13፤ 46፥34፤ዘፀ8፥26፤ገላ 2፥12
43፥33 ዘፍ35፥23፤ 42፥13፤44፥12
43፥34 ዘፍ37፥3፤ 2ነገ25፥30፤ሉቃ 15፥23
44፥1 ዘፍ42፥25፤ 43፥16
44፥2 ቊ5:8:10: 12:16
44፥3 መሳ19፥9
44፥4 ዘፍ43፥16፤ መዝ 35፥12፤ 38፥20፤ 109፥5፤ ምሳ 17፥13፤ ኤር18፥20
44፥5 ቊ2፤ዘፍ30፥ 27፤ዘዳ18፥10-14
44፥7 ዘፍ18፥25፤ 42፥11
44፥8 ቊ2፤ዘፍ31፥ 30፤42፥13:25፤ 43፥15፤
44፥9 ቊ10፤ዘፍ 42፥11፤31፥32፤ 43፥18
44፥10 ቊ2:9:17: 33፤ዘፍ43፥9
44፥12 ቊ2፤ዘፍ 31፥34፤43፥16:33
44፥13 ዘፍ37፥29፤ 42፥26
44፥14 ቊ16፤ዘፍ 29፥35፤33፥3፤ 43፥3:18
44፥15 ዘፍ12፥18፤ 30፥27
44፥16 ቊ2:14: 22:24፤ዘፍ37፥8፤42፥ 11፤43፥18፤መዝ 26፥6፤73፥13
44፥17 ቊ10፤ዘፍ 18፥25፤43፥9
44፥18 ቊ16፤ዘፍ

ዚያን ሰዎች ቶሎ ድረስባቸውና፣ "ለበጎ
ነገር ስለምን ክፉ መለሳችሁ? 5ይህ ጌታዬ
የሚጠጣበት፣ የተሰወረ ነገርም የሚያውቅ
በት ጽዋ አይደለምን? የፈጸማችሁት ድር
ጊት ክፉ ነው" በላቸው።
6የቤቱ አዛዥም እንደ ደረሰባቸው፣ ልክ
እንደተባለው ተናገራቸው። 7እነርሱ ግን
እንዲህ አሉት፤ "ጌታችን እንዲህ ያለ ነገር
ለምን ይናገራል? እኛ አገልጋዮችህ እንዲህ
ያለውን ነገር አናደርገውም። 8ከዚህ ቀደ
ምም በየስልቾቻችን አፍ የተገኘውን ብር
ከከነዓን እንኳ መልሰን አምጥተናል፤ ታዲያ
አሁን ብር ወይም ወርቅ ከጌታህ ቤት እን
ዴት እንሰርቃለን? 9የጠፋው ዕቃ ከአገልጋ
ዮችህ የተገኘበት ይሙት፤ የቀረነው የጌታ
ችን ባሮች እንሁን።"
10እርሱም "መልካም ነው፤ እንዳላችሁት
ይሁን፤ ጽዋው የተገኘበት ሰው ባሪያዬ ይሆ
ናል፤ የቀራችሁት ግን ከበደሉ ነጻ ትሆናላ
ችሁ" አላቸው።
11እያንዳንዱ ሰው ጭነቱን ወዲያውኑ አራ
ግፎ ስልቻውን ፈታ። 12ከዚያም አዛዡ ፍተ
ሻውን ከታላቁ ጀምሮ እስከ ታናሹ ድረስ
ቀጠለ። በመጨረሻም፣ ጽዋው በብንያም
ስልቻ ውስጥ ተገኘ። 13በዚህ ጊዜ ልብሳቸ
ውን በሐዘን ቀደዱ፤ ሁሉም ስልቾቻቸውን
በየአህዮቻቸው ጭነው ወደ ከተማዪቱ ተመ
ለሱ።
14ይሁዳና ወንድሞቹ ወደ ዮሴፍ ቤት ሲገቡ፣
እርሱ ገና ከቤቱ አልወጣም ነበር። እነር
ሱም ከፊቱ መሬት ላይ ተደፉ። 15ዮሴፍም፣
"ለምን እንዲህ ያለ ነገር አደረጋችሁ? እንደ
እኔ ያለ ሰው ስውር ነገርን የሚያውቅበት
ልዩ ጥበብ እንዳለው አታውቁምን?" ሲል
ጠየቃቸው።
16ይሁዳም፣ "ከእንግዲህ ለጌታችን ምን
ማለት እንችላለን? ምንስ እንመልሳለን?
እንዲህ ካለው በደል ንጹሕ መሆናችንን
ማስረዳትስ እንዴት ይቻለናል? እግዚአብሔር
(ኤሎሂም) የእኛን የአገልጋዮችህን በደል ገልጦ
አል፤ ከእንግዲህ ጽዋው የተገኘበት ብቻ
ሳይሆን ሁላችንም ባሮችህ ነን" አለ።

43፥29 *የእናቱን ልጅ ብንያምን፤* ዮሴፍ ከብንያም ጋር ያለውን ልዩ ግንኙነት በግልጽ ያሳያል። *እግዚአብሔር ይባርክህ፤* ከጊዜ በኋላ የተነገሩት የምርቃትና የቡራኬ ቃላት ይህንን ቃል የሚያስታውሱ ናቸው (ዘኍ 6፥25፤ መዝ 67፥1 ይመ)።

43፥30 *ዮሴፍ... አለቀሰ፤* ስሜቱ በተነካ ጊዜ ሁሉ ያለቅስ ነበር (42፥24፤ 45፥2:14-15፤ 46፥29 ይመ)።

43፥32 *ግብፃውያን ከዕብራውያን ጋር አብሮ መመገብን እንደ ጸያፍ ይቈጥሩት ነበር፤* ድርጊቱ በግብፃውያን ዘንድ እንደ ውግዘት የሚቈጠረው ምናልባት ሃይማኖታዊ ምክንያት ስላለው ሊሆን ይችላል (ዘፀ 8፥26 ይመ)፤ ግብፃውያን ከማኅበራዊ ምክን ያት የተነሣ ከእስረኞች ጋር ኅብረትና አንድነት አያደርጉም (46፥34 ይመ)።

43፥34 *የብንያም ድርሻ ከሌሎቹ አምስት ዕጥፍ ነበር፤* ከዮሴፍ ጋር ያላቸውን ልዩ ትስስር (ግንኙነት) ያመለክታል (የቍ 29 ማብ 45፥22 ይመ)።

44፥4 ከከተማው፤ ምንም እንኳ ሜምፊስና (ከአሁኗ ካይሮ በስተ ደቡብ 21 ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኝ ቦታ ነው) ዞአን (ዴልታ ተብሎ በሚታወቀው ክልል በስተ ምሥራቅ የሚገኝ ቦታ ነው) ናቸው የሚል አስተያየት ቢኖርም፣ ቦታው ግን በትክክል አይታ ወቅም።

44፥5 *የተሰወረ ነገርም የሚያውቅበት፤* ቍ15 እና የ30፥27 ማብ ይመ።

44፥9 *የጠፋው ዕቃ ከአገልጋዮችህ የተገኘበት ይሙት፤* ከዓመታት በፊት ያዕቆብ ግራና ቀኙን ሳያይ ለላባን ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥቶት ነበር (31፥32 እና ማብ ይመ)።

*44፥10፤* የዮሴፍ ቤት አዛዥ ወንድማማቾቹ ይደርስብናል ያሉትን ነገር አቀለለላቸው።

44፥12 *ከታላቅየው ጀምሮ እስከ ታናሹ፤* በልብ አንጠልጣይነቱ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሐሳብ በ31፥33 ላይ ይገኛል።

44፥13 *ልብሳቸውን... ቀደዱ፤* የጭንቀትና የሐዘን ምል ክት ነው (37፥29 ይመ)።

44፥14 *ከፊቱ መሬት ላይ ተደፉ፤* በ37፥7:9 ላይ የተጠቀ ሰው የዮሴፍ ሕልም በዚህም ስፍራ ሲፈጸም ይታያል (42፥6፤ 43፥26:28 ይመ)።

44፥16 *እግዚአብሔር የእኛን የአገልጋዮችህን በደል ገል ጦአል፤* የዮሴፍ የቤቱ አዛዥ እንዳደረገው ሁሉ (የ43፥23 ማብ

17ዮሴፍም፣ "ይህንንስ ፈጽሞ አላደርገውም፤
ባሪያዬ የሚሆነው ጽዋው የተገኘበት ሰው
ብቻ ነው፤ የቀራችሁት በሰላም ወደ አባታ
ችሁ ተመለሱ" አላቸው።
18ይሁዳም ወደ ዮሴፍ ቀረብ ብሎ፣ "ጌታዬ
ሆይ፤ እኔ አገልጋይህ አንዲት ቃል ብቻ
ልናገር፤ አንተም የፈርዖን ያህል የተከበርህ
ስለሆንህ፣ እባክህን እኔን አገልጋይህን አት
ቈጣኝ። 19ጌታዬ 'አባት ወይም ወንድም
አላችሁ?' ብሎ አገልጋዮቹን ጠይቈ ነበር።
20እኛም፣ 'አዎን፣ ሽማግሌ አባት አለን፤
አባታችንም በስተርጅና የወለደው ትንሽ ልጅ
አለው፤ ወንድምየው ሞቶአል፤ ከአንድ እናት
ከተወለዱት ልጆች መካከል የተረፈው
እርሱ ብቻ ነው፤ አባቱም በጣም ይወደዋል'
ብለንህ ነበር።
21"ከዚያም አንተ አገልጋዮችህን፣ 'እንዳ
የው ወደ እኔ አምጡት' አልኸን። 22እኛም
ለጌታዬ 'ልጁ ከአባቱ ሊለይ አይችልም፤
ከተለየው ደግሞ አባትየው ይሞታል' አል
ንህ። 23አንተ ግን እኛን አገልጋዮችህን፣
'ታናሽ ወንድማችሁ አብሮአችሁ ወደዚህ
ካልመጣ ዳግመኛ ፊቴን አታዩም' አልኸን።
24እኛም ወደ አገልጋይህ ወደ አባቴ በተ
መለስን ጊዜ አንተ ጌታዬ ያልኸንን ነገር ነው።
25"ከዚያም አባታችን 'እስቲ ተመልሳችሁ
ጥቂት እህል ሸምቱልን' ሲለን፤ 26'መሄድ
አንችልም፤ መሄድ የምንችለው ታናሽ ወን
ድማችን አብሮን ሲሄድ ብቻ ነው። ታናሽ
ወንድማችንን ይዘን ካልሄድን በስተቀር፣
የሰውየውን ፊት ማየት አንችልም' አልነው።
27"አገልጋይህ አባቴም እንዲህ አለን፤
'ሚስቴ ሁለት ወንዶች ልጆች እንደ ወለደ
ችልኝ ታውቃላችሁ፤ 28አንዱ በወጣበት
በመቅረቱ፣ "በእርግጥ የአውሬ እራት ሆኖ
አል" አልሁ፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ይኸው
የውሃ ሽታ ሆኖ ቀርቶአል። 29አሁን ደግሞ
ይህን ልጅ ወስዳችሁ አንዳች ጕዳት ቢደ
ርስበት ሽበቴን በመሪር ሐዘን ወደ መቃ
ብር[ሀ] ታወርዱታላችሁ።'
30"እንግዲህ አሁን ልጁን ሳንይዝ ወደ
አገልጋይህ ወደ አባቴ ብመለስ፣ ሕይወቱ
ከልጁ ሕይወት ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ስለ
ሆነ፣ 31የልጁን ከእኛ ጋር አለመኖር ሲያይ

18፥30፤29፥35
44፥19 ዘፍ42፥11፤
43፥7
44፥20 ዘፍ37፥3፡
33፤42፥13
44፥21 ዘፍ42፥11፡
15
44፥22 ቍ16፤ዘፍ
37፥35
44፥23 ዘፍ42፥15፤
43፥5
44፥24 ቍ16፤ዘፍ
42፥29፤43፥28
44፥25 ዘፍ42፥2
44፥26 ዘፍ43፥5
44፥27 ዘፍ43፥28፤
46፥19
44፥28 ዘፍ37፥33፤
45፥26፡28፤ 46፥30፤
48፥11
44፥29 ዘፍ37፥35፤
42፥38
44፥30 ዘፍ43፥28፤
1ሳሙ18፥1፤2ሳሙ
1፥26
44፥31 ቍ22፤ዘፍ
37፥35፤42፥11
44፥32 ዘፍ42፥37
44፥33 ቍ10፤ዘፍ
43፥18፤ዮሐ15፥13
44፥34 ዘፍ42፥38፤
አስ8፥6
45፥1 ዘፍ43፥31፤
2ሳሙ13፥9
45፥2 ቍ16፤ዘፍ
29፥11፤ሐሥ7፥13
45፥3 ቍ15፤ዘፍ
43፥7፤44፥20፤ኢዮ
21፥6፤23፥15፤ማቴ
17፥6፤ማር6፥49-50
45፥4 ዘፍ27፥21-
22፤37፥28
45፥5 ቍ7-8፤ዘፍ
42፥21፡22፤50፥20፤
ኢዮ10፥12፤መዝ
105፥17
45፥6 ዘፍ41፥30
45፥7 ቍ5፤ዘፍ49፥
18፤ዘፀ15፥2፤1ሳሙ
14፥45፤25፥9፤2ነገ
13፥5፤19፥4፡30፡31፤
ዕዝ9፥8፡13፤አስ4፥14፤
ኢሳ1፥9፤10፥20፡21፤
11፥11፡16፤25፥9፤46፥
3፤ኤር6፥9፤42፥2፡
50፥20፤ሚክ4፥7፤
5፥7፤7፥7፤ሶፎ2፥7
45፥8 ቍ5፤ዘፍ41፥
41፤መሳ17፥10፤2ነገ
6፥21፤13፥14

አባቴ ይሞታል። ከዚህም የተነሣ እኛ አገ
ልጋዮችህ የአባታችንን ሽበት በመሪር ሐዘን
ወደ መቃብር እናወርደዋለን። 32እኔ አገል
ጋይ፣ 'ልጅህን መልሼ ሳላመጣ ብቀር፣ ለዘ
ላለም በደለኛ አድርገህ ቍጠረኝ' በማለት፣
ስለ ልጁ ደኅንነት በአባቴ ፊት ራሴን ዋስ
አድርጌአለሁ።
33"ስለዚህ አሁን፣ አገልጋይህ በልጁ ፈንታ
የአንተ የጌታዬ ባሪያ ሆኜ እዚሁ ልቅር፤
ልጁ ግን ከወንድሞቹ ጋር ይመለስ። 34ልጁን
ሳልይዝ እንዴት ተመልሼ ወደ አባቴ እሄ
ዳለሁ? ፈጽሞ አላደርገውም፤ እባክህ በአ
ባቴ ላይ የሚደርሰውን መከራ እንዳይ አታ
ድርገኝ።"

### ዮሴፍ ለወንድሞቹ ራሱን ገለጠ

45 በዚያን ጊዜ ዮሴፍ አጠገቡ በነበሩ
ሰዎች ፊት ስሜቱን ሊገታ ባለመ
ቻሉ፣ "እዚህ ያሉትን ሰዎች በሙሉ አስ
ወጡልኝ" ብሎ ጮኽ ተናገረ፤ ስለዚህም
ዮሴፍ ራሱን ለወንድሞቹ በገለጠበት ጊዜ፣
ከእርሱ ጋር ሌላ ማንም ሰው አልነበረም።
ዮሴፍም ድምፁን ከፍ አድርጎ በማልቀሱ፣
ግብፃውያን ሰሙት፤ ወሬውም ወደ ፈርዖን
ቤተ ሰዎች ደረሰ።
3ዮሴፍም ወንድሞቹን፣ "እኔ ዮሴፍ ነኝ፤
ለመሆኑ አባቴ እስካሁን በሕይወት አለ?"
ሲል ጠየቃቸው። ወንድሞቹ ግን በፊቱ ተደ
ናግጠው ስለ ነበር መልስ ሊሰጡት አልቻ
ሉም።
4ዮሴፍም ወንድሞቹን፣ "እስቲ ወደ እኔ
ቀረብ በሉ" አላቸው፤ ወደ እርሱም በቀረቡ
ጊዜ እንዲህ አለ፤ "ወደ ግብፅ የሸጣችሁኝ
ወንድማችሁ እኔ ዮሴፍ ነኝ፤ 5አሁንም በመ
ሸጣችሁ አትቈጩ፤ በራሳችሁም ዐትዘኑ፤
ምክንያቱም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሕይወት ለማ
ዳን ሲል ከእናንተ አስቀድሞ እኔን ወደዚህ
ልኮኛል። 6በምድር ላይ ራብ ከገባ ይኸው
ሁለት ዓመት ሆነ፤ ከዚህ በኋላም የማይታ
ረሱበትና ሰብል የማይሰበሰብበት አምስት ዓመ
ታት ገና አሉ። 7ነገር ግን እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ሕይወታችሁን በታላቅ ማዳን ለመታደግና[ለ]
ዘራችሁ ከምድር ላይ እንዳይጠፉ በማሰብ

[ሀ]29 ቍ31 ላይ ያለውንም ጨምሮ ዕብራይስጡ ሲኦል ይለዋል
[ለ]7 ወይም *በሕይወት እንደ ተረፉ ታላቅ ሰራዊት ለመታደግ*

ይመ)፣ ይሁዳም ከሚያውቀው በላይ ተናገረ፤ ምናልባት ይሁዳ የተናገረው ነገር ሁለት ትርጒም ሳይኖረው አይቀርም (42፥21 ይመ)።

44፥18 *ይሁዳም... ብሎ፤* የ43፥3 ማብ ይመ። *ጌታዬ ሆይ፤ እኔ አገልጋይህ፤* የ42፥10 ማብ ይመ።

44፥30 *ሕይወቱ ከልጁ ሕይወት ጋር በጥብቅ የተሳሰረ፤* ይህን ሐረግ ለመግለጽ የገቡት የዕብራይስጥ ቃላት፣ ከዓመታት በኋላ፣ "የዮናታን ነፍስ በዳዊት ነፍስ ታሰረች" (1ሳሙ 18፥1) የሚለውን ለመግለጽ ገብቶአል።

44፥33 *በልጁ ፈንታ፤* ይሁዳ በብንያም ምትክ ራሱን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኑ፣ ዮሴፍን ለመሸጥ የተጫወተውን ሚና የሚያካክስ ነው (37፥26-27 *ይመ*)።

44፥34 *መከራ እንዳይ አታድርገኝ፤* ይሁዳ ከዚህ በፊት የተፈጸመውን አሳዛኝ ሁኔታ አስታወሰ (37፥34-35 *ይመ*)።

45፥2 *በማልቀሱ፤* ቍ 14-15 ይመ። እንዲሁም 43፥30 እና ማብ ይመ።

45፥3 *ወንድሞቹ... ተደናግጠው፤* መንፈስ ያዩ ስለ መሰላቸው ወይም ዮሴፍ አንድ ነገር ያደርገናል ብለው ስለ ፈሩ ነው።

45፥4 *ወንድማችሁ እኔ ዮሴፍ ነኝ፤* ቍ 31፤ ሐሥ 7፥13 ይመ። በዚህ ጊዜ ዮሴፍ ከእነርሱ ጋር ያለውን ዝምድና ገልጦ ተናገረ። *የሸጣችሁኝ፤* የ37፥28 ማብ ይመ።

45፥5 *እግዚአብሔር... ልኮኛል፤* ቍ 7-9፤ ሐሥ 7፥9 ይመ። እግዚአብሔር የዮሴፍ ወንድሞች ባለማስተዋልና በጭካኔ በፈጸሙት ተግባር የራሱ ዐላማ ነበረው (ሐሥ 2፥23፤ 4፥28 ይመ)።

*45፥6፤* በዚህ ጊዜ የዮሴፍ ዕድሜ 39 ዓመት ሆኖ ነበር (41፥46፡53 *ይመ*)።

45፥7 *ዘራችሁ፤* ምንም እንኳ ከእነርሱ አንድም ሰው ባይጠፋም፣ ሊደርስባቸው ከነበረውም አስከፊ ሁኔታ አምልጠዋል፤ ስለዚህ ዮሴፍ አንድ ቀን ታላቅ ሕዝብ እንደሚሆኑ በመተ

ከእናንተ አስቀድሞ ወደዚህ ላከኝ።
8“ስለዚህ አሁን ወደዚህ የላከኝ ስግዚስብሔር
(ኤሎሂም) እንጂ እናንተ አይደላችሁም፤ እር
ሱም ለፈርዖን እንደ አባት፣ በቤት ንብረቱ
ላይ ጌታ፣ እንዲሁም በግብፅ ምድር ላይ
ገዥ አደረገኝ። 9አሁንም በፍጥነት ወደ አባቴ
ተመልሳችሁ እንዲህ በሉት፤ ‘ልጅህ የሴፍ እንዲህ
ይላል፤ ‘ስግዚስብሔር (ኤሎሂም) የመላው ግብፅ
ጌታ አድርጎኛል፤ ስለዚህ ሳትዘገይ ወደ እኔ
ና። 10ልጆችህን፣ የልጅ ልጆችህን፣ በጎችህን፣
ፍየሎችህን፣ ከብቶችህንና ያለህን ሁሉ ይዘህ
በአቅራቢያዬ በጌሤም ትኖራለህ። 11ገና
ወደ ፊት የሚመጣ የአምስት ዓመት ራብ
ስላለ፣ በዚያ የሚያስፈልጋችሁን እኔ እሰ
ጣችኋለሁ፤ ያለበለዚያ ግን አንተና ቤተ ሰዎ
ችህ ያንተም የሆነው ሁሉ፣ ችግር ላይ ትወ
ድቃላችሁ።’

12“ፊታችሁ ሆኜ የማናግራችሁ እኔ ዮሴፍ
ራሴ መሆኔን እናንተም ሆናችሁ ወንድሜ
ብንያም በዐይናችሁ የምታዩት ነው። 13በግ
ብፅ ስላለኝ ክብርና ስላያችሁትም ሁሉ ለአ
ባቴ ንገሩት፤ አባቴንም በፍጥነት ይዛችሁት
ኑ።

14ከዚያም በወንድሙ በብንያም ዐንገት ላይ
ተጠምጥሞ አለቀሰ፤ ብንያምም እያለቀሰ ዮሴ
ፍን ዐቀፈው። 15የቀሩትንም ወንድሞቹን አንድ
በአንድ እየሳመ አለቀሰ። ከዚያም ወንድሞቹ
ከእርሱ ጋር መጫወት ጀመሩ።

16የዮሴፍ ወንድሞች መምጣት በፈርዖን
ቤተ መንግሥት በተሰማ ጊዜ፣ ፈርዖንና ሹማ
ምንቱ ሁሉ ደስ አላቸው። 17ፈርዖንም ዮሴ
ፍን እንዲህ አለው፤ “ለወንድሞችህ እንዲህ
ብለህ ንገራቸው፤ ‘እንዲህ አድርጉ፤ አህዮቻ
ችሁን ጭናችሁ ወደ ከነዓን ምድር ተመለሱ።
18ከዚያም አባታችሁንና ቤተ ሰባችሁን ይዛ
ችሁ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም እጅግ ለም ከሆ
ነው የግብፅ ምድር እሰጣችኋለሁ፤ በምድሪቱ
በረከት ደስ ብሎአችሁ ትኖራላችሁ።’ 19“ደግ
ሞም እንዲህ ብለህ እዘዛቸው፤ ‘ይህን አድ
ርጉ፤ ከግብፅ ምድር ልጆቻችሁንና ሚስቶ
ቻችሁን የምታጓጉዙበት ሠረገላዎች ወስዳ
ችሁ፣ አባታችሁን ይዛችሁት ኑ። 20ስለ ንብ
ረታችሁ ምንም አታስቡ፣ ከግብፅ ምድር
እጅግ ለም የሆነው የእናንተ ይሆናልና።’ ”

21የእስራኤልም ልጆች ይህንኑ አደረጉ።
ዮሴፍም ፈርዖን ባዘዘው መሠረት ሠረገላ
ዎች አቀረበላቸው፤ የመንገድም ስንቅ አስ
ያዛቸው። 22ለእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት
የክት ልብስ ሰጣቸው፤ ለብንያም ግን ሦስት
መቶ ጥሬ ብርና አምስት የክት ልብስ ሰጠው።
23ለአባቱም በግብፅ ምድር ከሚገኘው የተ
መረጠ ነገር በዐሥር አህዮች፣ እንደዚሁም
ለመንገዱ ስንቅ የሚሆነው እህል፣ ዳቦና ሌላ
ምግብ በዐሥር እንስት አህዮች አስጭኖ
ሰደደለት። 24ከዚህ በኋላ ወንድሞቹን አሰ
ናበታቸው፤ ከእርሱም ሲሰናበቱ፣ መንገድ
ላይ እንዳትጣሉ” አላቸው።

25እነርሱም ከግብፅ ወጥተው በከነዓን ምድር
ወደሚኖረው ወደ አባታቸው ወደ ያዕቆብ
መጡ። 26አባታቸውንም፣ “እነሆ ዮሴፍ በሕ
ይወት አለ፤ እንዲያውም በግብፅ ምድር ሁሉ
ገዥ ሆኖአል” ብለው ነገሩት። ያዕቆብም
በድንጋጤ ክው አለ፤ ሊያምናቸውም አልቻ
ለም። 27ነገር ግን ዮሴፍ የነገራቸውን ሁሉ
ሲያጫውቱትና እርሱንም ወደ ግብፅ ለማጓጓዝ
ዮሴፍ የላከለትን ሠረገላዎች ሲያይ የአባታ
ቸው የያዕቆብ መንፈስ ታደሰ። 28ከዚያም እስ
ራኤል፤ “ልጄ ዮሴፍ በሕይወት አለ፤ ከመሞቴ
በፊት ሄጄ ልየው” አለ።

### ያዕቆብ ወደ ግብፅ ሄደ

46 እስራኤልም ጓዙን ሁሉ ጠቅልሎ
ተነሣ፤ ቤርሳቤህም ሲደርስ፣ ለአባቱ
ለይስሐቅ ስምላክ (ኤሎሂም) መሥዋዕት ሠዋ።
2ስግዚስብሔርም (ኤሎሂም) ሌሊት በራእይ ለእ
ስራኤል ተገልጦ “ያዕቆብ፣ ያዕቆብ” ብሎ
ጠራው። እርሱም፣ “እነሆ፣ አለሁ” አለ።
3እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፤ “እኔ የአ
ባትህ አምላክ ስግዚስብሔር (ኤሎሂም) ነኝ፤ ወደ ግብፅ
ለመውረድ አትፍራ፤ በዚያ ታላቅ ሕዝብ
አደርግሃለሁና፤ 4አብሬህ ወደ ግብፅ እወር

45፥9 ዘፍ43፥10፡15፤ሐሥ7፥14
45፥10 ዘፍ46፥6-7፡28፡34፤47፥1፡11፡27፤50፥8፤ዘፀ8፥22፤9፥26፤10፥24
45፥11 ዘፍ41፥30፤47፥12፤50፥21፤መዝ102፥17
45፥12 ዘፍ35፥18፤ማር6፥50
45፥13 ዘፍ41፥41፤43፥15፤ሐሥ7፥14
45፥14 ዘፍ29፥13፤35፥18
45፥15 ቊ3፤ዘፍ29፥11፡13፤46፥4፤ሉቃ15፥20
45፥16 ቊ2፤ዘፍ50፥7፤41፥37፤ሐሥ7፥13
45፥17 ዘፍ42፥5፡26
45፥18 ቊ20፤ዘፍ20፥15፤46፥34፤47፥6፡11፡27፤ዕዝ9፥12፤መዝ37፥19፤ኢሳ1፥19፤ኤር40፥4
45፥19 ቊ21፡27፤ዘፍ46፥5፤ዘኍ7፥3-8
45፥20 ቊ18፤ዘፍ46፥6፡32
45፥21 ቊ19፤ዘፍ42፥25
45፥22 ዘፍ24፥53፤37፥3፤41፥14፤መሳ14፥12፡13፤2ነገ5፥22
45፥23 ዘፍ24፥10፤42፥25፡26
45፥24 ዘፍ42፥21-22
45፥25 ዘፍ13፥1፤42፥29
45፥26 ዘፍ41፥41፤44፥28፤1ነገ10፥7
45፥27 ቊ19
45፥28 ዘፍ44፥28፤ሉቃ16፥31
46፥1 ቊ5፤ዘፍ21፥14፤31፥42፡54
46፥2 ዘፍ15፥1፤17፥5፤22፥1
46፥3 ዘፍ12፥2፤15፥1፤26፥2፤28፥13፤ዘፀ1፥7
46፥4 ቊ29፤ዘፍ15፥16፤28፥13፤45፥

ማመን ትሩፋን (ቅሬታዎች) ናችሁ በማለት ይጠራቸዋል።

45፥8 *አባት፤* ከነገሥታት በታች ላሉ ባለ ሥልጣናትና (የ41፥43 ማብ ይመ) ለሌሎቹ ከፍተኛ ገገሮች የሚሰጥ የክብር ማዕረግ ነው፤ (በአዋልድ መጻሕፍት ውስጥ መቃቢያን ቀዳማዊ 11፥32 ይመ)። በዚህ ቍጥር ላይ የተጠቀሱት ሦስቱም የዮሴፍ ማዕረጐች የግብፅ ናቸው።

45፥9 *በፍጥነት... ተመልሳችሁ... ሳትዘገይ፤* ዮሴፍ አባቱን በሕይወት ለማየት ቸኵሎአል (ቍ 13 ይመ)።

45፥10 *ጌሤም፤* የዐባይ ደለል (ናይል ዴልታ) ከሚባለው በስተ ምሥራቅ የሚገኝ እጅግ ለም አካባቢ ሲሆን (ቍ 18 ይመ)፣ ይህ አካባቢ ዛሬም እንዲሁ ለም ነው።

45፥12 *የማናገራችሁ እኔ፤* ከዚህ በፊት በአስተርጓሚ እን ደሚያነጋግራቸው ዐይነት አይደለም (42፥23 ይመ)።

45፥14 *አለቀሰ፤* 43፥30 እና ማብ ይመ።

45፥15 *ወንድሞቹ ከእርሱ ጋር መጫወት ጀመሩ፤* ከ20 ዓመት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በመካከላቸው በጠላትነት መተያየት ወይም መፈራራት ሳይኖር፣ ከልብ በሆነ ወንድማማ ችነት ተነጋገሩ (37፥2 እና የ45፥6 ማብ ይመ)።

45፥18 *በምድሪቱ በረከት ደስ ብሎአችሁ ትኖራላችሁ፤* ይስሐቅ ለያዕቆብ የሰጠውን በረከት የሚያስታውስ ነው (27፥28 ይመ)።

45፥22 *ሦስት መቶ ጥሬ ብር፤* የ20፥16 ማብ ይመ። *ለብ ንያም... አምስት የክት ልብስ ሰጠው፤* የ43፥34 ማብ ይመ።

45፥24 *እንዳትጣሉ፤* ዮሴፍ፣ ወንድሞቹ ከሄዱበት ሲመለሱ እንዳይዘገዩና (የቍ 9 ማብ ይመ)፣ ያለፈውን ነገር አንሥተው እንዳይጨቃጨቁ ፈለገ።

46፥1 *ተነሣ፤* ምናልባት በኬብሮን የሚገኘውን የቤተ ሰቡን ርስት ለቆ ሳይሆን አይቀርም (35፥27 ይመ)። *ቤርሳቤህም ሲደ ርስ... መሥዋዕት ሠዋ፤* አብርሃምና ይስሐቅም በዚህ ስፍራ እግዚአብሔርን አምልከዋል፤ ለእርሱም መሥዋዕት አቅርበዋል (21፥33፤ 26፥23-25 ይመ)።

46፥2 *እግዚአብሔር ሌሊት በራእይ ለእስራኤል ተገለጠ፤* 26፥24 ይመ “*ያዕቆብ፣ ያዕቆብ*”፤ የ22፥11 ማብ ይመ። “*እነሆ አለሁ*”፤ የ22፥1 ማብ ይመ።

*46፥3-4፤* እስራኤልና ቤተ ሰቡ ከነዓንን ለቀው ሊወጡ ሲሰናዱ እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ላይ የሰጠውን ተስፋ እንደ ገና አጸናላቸው።

46፥3 *እኔ... የአባትህ አምላክ... ነኝ... አትፍራ፤* በ26፥24 ላይ እግዚአብሔር ለይስሐቅ የተናገረውና በዚህ ቦታ ቃል በቃል የተደገመ የተስፋ ቃል ነው። *ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁና፤* እግዚአብሔር ለአብርሃም ገብቶለት ከነበረው

ዳለሁ፤ ከዚያም መልሼ አወጣሃለሁ፤ የዮሴፍ
የራሱ እጆችም ዐይኖችህን ይገጥሟቸዋል::”
5ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ተነሣ፤
የእስራኤል ወንዶች ልጆችም አባታቸውን
ያዕቆብን፣ ልጆቻቸውንና ሚስቶቻቸውን ፈር
ዖን ለያዕቆብ በላካቸው ሠረገሎች ላይ አወ
ጧቸው:: 6ከብቶቻቸውንና በከነዓን ምድር
ያፈሩትን ሀብት ንብረታቸውን ይዘው፣ ያዕ
ቆብና ዘሮቹ በሙሉ ወደ ግብፅ ወረዱ::
7ወደ ግብፅም የወረደው፣ ወንዶች ልጆቹ
ንና ወንዶች የልጅ ልጆቹን፣ ሴቶች ልጆቹንና
ሴቶች የልጅ ልጆቹን ማለት ዘሮቹን ሁሉ
ይዞ ነው::
8ወደ ግብፅ የወረዱት የእስራኤል ልጆች፣
ያዕቆብ ዘሮቹ እነዚህ ናቸው:-

የያዕቆብ የበኵር ልጅ ሮቤል::
9የሮቤል ልጆች:-
ሄኖኅ፣ ፈሉሶ፣ አስሮን እና ከርሚ ናቸው::
10የስምዖን ልጆች:-
ይሙኤል፣ ያሚን፣ አሃድ፣ ያኪን፣
ጾሐርና ከከነዓናዊቷ ሴት የተወለደው
ሳኡል ናቸው::
11የሌዊ ልጆች:-
ጌድሶን፣ ቀዓትና ሜራሪ ናቸው::
12የይሁዳ ልጆች:-
ዔር፣ አውናን፣ ሴሎም፣ ፋሬስ እና
ዛራ ናቸው:: ነገር ግን ዔርና አውናን
በከነዓን ምድር ሞቱ::
13የይሳኮር ልጆች:-
ቶላ፣ ፋዋ፣[ሀ] ዮብና ሺምሮን ናቸው፤
14የዛብሉን ልጆች:-
ሴሬድ፣ ኤሎንና ያሕልኤል ናቸው፤
15እነዚህ ወንዶች ልጆች ያዕቆብ በሰሜን
ምዕራብ መስጴጦምያ ሳለ፣ ልያ የወለደች
ለት ናቸው:: ሴቷን ዲናን ጨምሮ፣ የወን
ዶችና የሴቶች ልጆቹ ቍጥር ሠላሳ ሦስት
ነው::
16የጋድ ልጆች:-
ጽፎን፣[ለ] ሐጊ፣ ሹኒ፣ ኤስቦን፣
ዔሪ፣ አሮዲና አርኤሊ ናቸው፤
17የአሴር ልጆች:-
ዪምና፣ የሱዋ፣ የሱዊና በሪዓ ናቸው፤
እኅታቸውም ሤራሕ ናት፤
የበሪዓ ልጆች:-
ሐቤርና መልኪኤል ናቸው፤
18እነዚህ ዐሥራ ስድስት ልጆች ሁሉ፣ ላባ
ለልጁ ለልያ ከሰጣት ከዘለፋ ላይ ያዕቆብ
የወለዳቸው ናቸው::

19የያዕቆብ ሚስት የራሔል ልጆች:-
ዮሴፍና ብንያም ናቸው፤ 20በግብፅም
የሄልዮቱ[ሐ] ከተማ ካህን የጶጥፌራ ልጅ አስ
ናት፣ ምናሴንና ኤፍሬምን ለዮሴፍ ወለደ
ችለት::
21የብንያም ልጆች:-
ቤላ፣ ቤኬር፣ አስቤል፣ ጌራ፣ ናዕማን፣
አኪ፣ ሮስ፣ ማንፌን
ሑፊምና አርድ ናቸው::
22እነዚህ ዐሥራ አራቱ፣ ራሔል ለያዕቆብ
የወለደችለት ልጆችና የልጅ ልጆች ናቸው::

23የዳን ልጅ:-
ሑሺም ነው፤
24የንፍታሌም ልጆች:-
ያሕጽኤል፣ ጉኒ፣ ዬጽርና ሺሌም ናቸው፤
25እነዚህ ሰባቱ ልጆች ሁሉ ላባ ለልጁ
ለራሔል ከሰጣት ከባላ ላይ ያዕቆብ የወለዳ
ቸው ናቸው::
26ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብፅ የሄዱት የገዛ
ዘሮቹ ብዛት ሥልሳ ስድስት ሲሆን ይህ ቍጥር
ግን የልጆቹን ሚስቶች አይጨምርም::
27ዮሴፍ በግብፅ የወለዳቸውን ሁለት ልጆች[መ]
ጨምሮ፣ ወደ ግብፅ የወረደው የያዕቆብ ቤተ
ሰብ ቍጥር ሰባ ነበር::
28ያዕቆብም ወደ ጌሤም ለመሄድ መመሪ
ያን ይቀበል ዘንድ፣ ይሁዳን አስቀድሞ
ወደ ዮሴፍ ላከው:: እነርሱም ጌሤም ሲደ
ርሱ፣ 29ዮሴፍ ሠረገላውን አዘጋጅቶ፤ አባቱን
እስራኤልን ለመቀበል ወደ ጌሤም አመራ::

14-15፤50፥1
46፥5 ቍ1፤ዘፍ 21፥14፤45፥19
46፥6 ዘፍ12፥5፤ 45፥20፤ዘኍ20፥15፤ ዘዳ26፥5፤ኢሱ24፥4፤ 1ሳሙ12፥8፤መዝ 105፥23፤ኢሳ52፥4 ፤ሐሥ7፥15
46፥7 ቍ6፤ ዘፍ13፥10፤45፥10
46፥8 ዘፍ29፥32፤ 35፥26፤ዘፀ1፥1፤ዘኍ 26፥4
46፥9 ዘፀ6፥14፤ዘኍ 1፥20፤26፥5:6:7፤ 1ዜና5፥3
46፥10 ዘፍ29፥33፤ ዘፀ6፥15፤ዘኍ26፥12: 13:14
46፥11 ዘፍ29፥34፤ ዘፀ6፥16:19፤ዘኍ3፥ 17:20:21:27:33፤ 4፥29:38፤26፥57፤ 1ዜና6፥19፤23፥12
46፥12 ዘፍ29፥35፤ 38፥3:4:7:29:30፤ ዘኍ26፥19:21፤ 1ዜና2፥5፤ማቴ1፥3
46፥13 ዘፍ30፥18፤ ዘኍ26፥23:24፤መሳ 10፥1፤1ዜና7፥1
46፥14 ዘፍ30፥20
46፥15 ዘፍ25፥20፤ 29፥31-35፤30፥21
46፥16 ዘፍ30፥11፤ ዘኍ1፥25፤26፥15
46፥17 ዘፍ30፥13
46፥18 ዘፍ16፥1፤ 30፥10
46፥19 ዘፍ29፥6፤ 44፥27
46፥20 ዘፍ41፥45: 51:52፤ዘኍ26፥28- 37
46፥21 ዘኍ26፥38- 41፤1ዜና7፥6-12፤ 8፥1:3
46፥22 ዘፍ29፥6
46፥23 ዘፍ30፥6፤ ዘኍ26፥42
46፥24 ዘፍ30፥8
46፥25 ዘፍ24፥61፤ 30፥8
46፥26 ቍ5-7፤
46፥29 ቍ1:4:30፤ ዘፍ29፥11፤32፥28፤ 41፥43፤47፥29:31፤ ዘፀ1፥5፤ዘዳ10፥22
46፥27 ዘፍ34፥30፤41፥45፤ሐሥ7፥14
46፥28 ዘፍ43፥3፤45፥10

[ሀ]13 ከአራተ ሳምራውያንና ከሱርስቱ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን (1ዜና 7፥1 ይመ) የማሶሬቲክ ጽሑፍ ግን ፋቫ ይለዋል::
[ለ]16 ከአራተ ሳምራውያንና ከሰብዓ ሊቃናት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን (ዘኍ 26፥15 ይመ) የማሶሬቲክ ጽሑፍ ግን ጸፊን ይለዋል
[ሐ]20 ሆሊዮፖሊስን ያመለክታል
[መ]27 ከዕብራይስጡ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ሰብዓ ሊቃናት ግን ዘጠኝ ልጆች ይለዋል [መ]27 ከዕብራይስጡ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን (ዘፀ 1፥5 እና ማብ ይመ)ሰብዐ ሊቃናት ግን (ሐሥ 7፥14 ይመ) ሰባ አምስት ይለዋል

ቃል ኪዳን ውስጥ አንዱን እንደ ገና አጸና (12፥2 ይመ):: *ከዚያም፤* ዘፀ 1፥7 ይመ::

46፥4 *አብሬህም ወደ ግብፅ እወርዳለሁ፤* ያዕቆብ በሰሜን በኩል ወደ ካራን በሄደ ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደ ነበረ ሁሉ፣ በደቡብ በኩል ወደ ግብፅ በወረደም ጊዜ ከእርሱ ጋር ነበር:: ቀደም ሲል እንዳደረገውም መልሶ ወደ ነበረበት ያመጣዋል (28፥15፤ 15፥16፤ 48፥21 ይመ)::

46፥8 *ወደ ግብፅ የወረዱት የእስራኤል ልጆች... እነዚህ ናቸው፤* በዘፀ 1፥1 ላይ ቃል በቃል የተደገመ ሲሆን (ማብ ይመ)፣ ከግብፅ የወጡት እስራኤላውያን ታሪካቸው ምን እንደ ሆነ የሚያሳይ ነው (በዚሁ ምዕራፍ በቍ 4 ላይ አስቀድሞ ተነግሮአል)::

46፥15 *መስጴጦምያ፤* የ25፥20 ማብ ይመ:: *ሠላሳ ሦስት፤* ከቍ 8-15 ባለው ክፍል ላይ ሠላሳ አራት ስሞች ተጠቅሰዋል:: ቍጥሩን ወደ ሠላሳ ሦስት ዝቅ ለማድረግ፣ ምናልባት በቍ 10 ላይ አሃድ ተብሎ የተጠቀሰው መሠረዝ አለበት፤ ምክንያቱም ይህ ስም በዘኍ 26፥12-13 እና በ1ዜና 4፥24 ላይ በተዘረዘሩት ተጓዳኝ የስም ዝርዝሮች ላይ አልተጠቀሰም:: በዕብራይስጥ አሃድ የሚለው ስም በዚሁ በቍጥር 10 ላይ “ጾሐር” ተብሎ ከተጠቀሰው ስም ጋር በቅርጽ ተመሳሳይ ነው (ዘፀ 6፥15 ይመ)::

46፥20 የ41፥45 ማብ ይመ::

46፥26 *ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብፅ የሄዱት... ብዛት ሥልሳ ስድስት ሲሆን፤* የ33 (ቍ 15 እና ማብ ይመ)፣ የ16 (ቍ 18)፣ የ14 (ቍ 22) እና የ7 (ቍ 25 ይመ) አጠቃላይ ድምር 70 (ቍ 27) ይሆናል፤ ቍጥሩ ወደ 66 ዝቅ እንዲል ግን “በከነዓን ምድር የሞቱት” ዔርና አውናን (ቍ 12) እንዲሁም በግብፅ የተወለዱት (ቍ 27) ምናሴና ኤፍሬም (ቍ 20) መቀነስ አለባቸው::

46፥27 *ሰባ፤* ዘዳ 10፥22 ይመ:: ዔርናና አውናን አስቀድመው ባይሞቱ ኖሮ (38፥7-10 ይመ)፣ በግብፅ የነበሩት የያዕቆብ ዘሮች ቍጥር ሰባ ይሆን ነበር:: ሰባ ቍጥር ደግሞ ፍጹም ቍጥር ነው (በመጽሐፉ መግቢያ ላይ “ሥነ-ጽሑፋዊ ገጽታ” የሚለውን ይመ፤ እንዲሁም የ 5፥5 የ10፥2 ማብ ይመ):: በሐሥ 7፥14 ላይ ሰባ አምስት ቍጥርን በተመለከተ ያንኑ ማብ ይመ::

46፥28 *ያዕቆብም... ይሁዳን አስቀድሞ... ላከው፤* የ43፥3 ማብ ይመ::

የሴፍ አባቱ ዘንድ እንደ ደረሰ፣ ዐንገቱ ላይ[ሬ]
ተጠምጥሞ ለረጅም ጊዜ አለቀሰ።
[30]እስራኤልም ዮሴፍን፣ "በሕይወት መኖ
ርህን ስላየሁ፣ ከእንግዲህ ብሞትም አይቈ
ጨኝ" አለው።
[31]ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ወንድሞቹንና የአባ
ቱን ቤተ ሰዎች እንዲህ አላቸው፤ "ወደ
ፈርዖን ወጥቼ እናገረዋለሁ፤ እንዲህም እለ
ዋለሁ፣ 'በከነዓን ምድር የሚኖሩት ወንድ
ሞቼና የአባቴ ቤተ ሰዎች ወደ እኔ መጥተ
ዋል። [32]ሰዎቹ ከብት የሚጠብቁ ስለሆኑ
እረኞች ናቸው፤ ሲመጡም በጎቻቸውን፣ ፍየ
ሎቻቸውንና ከብቶቻቸውን እንዲሁም ያላ
ቸውን ሁሉ ይዘው መጥተዋል።' [33]ፈርዖን
አስጠርቶአችሁ፣ 'ሥራችሁ ምንድን ነው?'
ብሎ ቢጠይቃችሁ፣ [34]እናንተ 'እኛ ባሮችህ
ሥራችን ከልጅነታችን ጀምሮ ልክ እንደ
አባቶቻችን ከብት ማርባት ነው' ብላችሁ
መልሱለት። ከዚያም ግብፃውያን ከብት አርቢ
ዎችን እንደ ጸያፍ ስለሚቈጥሩ፣ በጌሤም
ምድር እንድትኖሩ ይፈቅድላችኋል።"

47 ዮሴፍም ወደ ፈርዖን ሄዶ፣ "አባ
ቴና ወንድሞቼ በጎቻቸውን፣ ፍየሎ
ቻቸውን እንዲሁም ያላቸውን ሁሉ ይዘው
ከከነዓን አገር መጥተው በጌሤም ሰፍረዋል"
አለው። [2]ከወንድሞቹም መካከል አምስቱን
መርጦ፣ ፈርዖን ፊት አቀረባቸው።
[3]ፈርዖን የዮሴፍን ወንድሞች፣ "ሥራችሁ
ምንድነው?" ሲል ጠየቃቸው።
እነርሱም ፈርዖንን፣ "እኛ አገልጋዮችህ
ልክ እንደ አባቶቻችን ከብት አርቢዎች ነን"
አሉት፤ [4]ደግሞም፣ "በከነዓን ምድር ራብ እጅግ
የጸና በመሆኑ በጎችና ፍየሎች የሚሰማሩበት
በማጣታቸው፣ ለጊዜው እዚህ ለመኖር መጥተ
ናል፤ አሁንም ባሮችህ በጌሤም ምድር እንድ
ንኖር እንድትፈቅድልን እንለምንሃለን" አሉት።
[5]ፈርዖንም ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ "አባ
ትህና ወንድሞችህ ወደ አንተ መጥተዋል፤
[6]የግብፅ ምድር እንደ ሆነ በእጅህ ነው፤
አባትህንና ወንድሞችህን ምርጥ በሆነው ምድር
አስፍራቸው፤ በጌሤም ይኑሩ። ከመካከላቸው
ልዩ ችሎታ ያላቸው መኖራቸውን የምታ
ውቅ ከሆነ፣ የከብቶቼ ኀላፊዎች አድርጋቸው።"
[7]ከዚህ በኋላ ዮሴፍ አባቱን ያዕቆብን ቤተ
መንግሥት አግብቶ በፈርዖን ፊት አቀረበው፤
ያዕቆብ ፈርዖንን ከመረቀው[ሶ] በኋላ [8]ፈርዖን፣
"ለመሆኑ ዕድሜህ ምን ያህል ነው?" ሲል
ያዕቆብን ጠየቀው።
[9]ያዕቆብም ለፈርዖን፣ "በምድር ላይ በእን
ግድነት ያሳለፍኩት ዘመን 130 ዓመት ነው፤
ይህም አባቶቼ በእንግድነት ከኖሩበት ዘመን
ጋር ሲነጻጸር አጭር ነው፤ ችግር የበዛበትም
ነበር" ሲል መለሰለት። [10]ከዚያም ያዕቆብ
ፈርዖንን መርቆ፣ ተሰናብቶት ወጣ።
[11]ዮሴፍም አባቱንና ወንድሞቹን በግብፅ
እንዲኖሩ አደረገ፤ ፈርዖን በሰጠውም ትእ
ዛዝ መሠረት ምርጥ ከሆነው ምድር ራም
ሴን በርስትነት ሰጣቸው። [12]ዮሴፍም ለአ
ባቱ፣ ለወንድሞቹና ለመላው የአባቱ ቤተ
ሰዎች በልጆቻቸው ቍጥር ልክ ቀለብ እን
ዲሰፈርላቸው አደረገ።

## የራብ ዘመንና የዮሴፍ አመራር

[13]በመላው ምድር እህል ባለመኖሩ ራቡ
እየጸና ሄደ፤ ከዚህ የተነሣም ግብፅና ከነዓን
በራብ እጅግ ተጐዱ፤ [14]ዮሴፍ የግብፅና የከ
ነዓን ሰዎች እህል በመሸመት የከፈሉትን
ገንዘብ ሁሉ ሰብስቦ ወደ ፈርዖን ቤተ መን
ግሥት አስገባ። [15]የግብፅና የከነዓን ሕዝቦ
ችም ገንዘባቸው ባለቀ ጊዜ፣ ግብፃውያን ሁሉ
ወደ ዮሴፍ ቀርበው፣ "የምንበላው እህል ስጠን፤
ገንዘባችን አልቆብናል፤ ዐይንህ እያየ እን
ዴት በራብ እንለቅ?" አሉት።
[16]ዮሴፍም፣ "ከብቶቻችሁን አምጡ፤ ገንዘ
ባችሁ ካለቀ በከብቶቻችሁ ለውጥ እህል እሰ
ጣችኋለሁ አለ። [17]ስለዚህ ከብቶቻቸውን ወደ
ዮሴፍ አመጡ፤ እርሱም በፈረሶቻቸው፣ በበ
ጎቻቸው፣ በፍየሎቻቸው፣ በከብቶቻቸውና
በአህዮቻቸው ለውጥ እህል ሰጣቸው። በከብ
ቶቻቸው ልዋጭ ባገኙት ምግብ የዚያን ዓመት
ራብ እንዲወጡት አደረገ።
[18]ያም ዓመት ካለፈ በኋላ ሕዝቡ በሚቀ
ጥለው ዓመት ወደ ዮሴፍ መጥተው እንዲህ
አሉት፣ "እንግዲህ ከጌታችን የምንሰውረው
ምንም ነገር የለም፤ ገንዘባችን አልቆአል፤
ከብቶቻችንንም አስረክበንሃል፤ እንግዲህ ለጌ
ታችን የምንሰጠው፣ ከመሬታችንና ከእኛ
ከራሳችን በስተቀር፣ አንዳች ነገር የለም።
[19]ታዲያ፣ እያየኸን እንዴት እንለቅ? መሬ
ታችንስ ለምን ጠፍ ሆኖ ይቅር? እኛንና
መሬታችንን ውሰድና በለውጡ እህል ስጠን፤
እኛ የፈርዖን ገባሮች እንሁን፤ መሬታችንም

ሉቃ15፥20
46፥30 ቍ29፤ዘፍ 44፥28
46፥31 ዘፍ42፥13፤ 45፥10
46፥32 ዘፍ37፥2፤ 45፥20፤ 47፥3
46፥33 ዘፍ47፥3
46፥34 ዘፍ34፥10፤ 42፥11፤43፥32፤ 45፥10፤47፥3
47፥1 ዘፍ42፥13፤ 46፥31
47፥2 ዘፍ43፥15
47፥3 ዘፍ42፥11፤ 46፥32:33
47፥4 ዘፍ46፥34፤ ዘፀ12፥10፤ሩት1፥1፤ 1ነገ18፥5፤ኤር14፥5-6፤ኢል1፥18
47፥6 ዘፍ13፥9፤ 34፥10፤39፥4፤45፥ 18፤ዘፀ18፥21:25፤ ዘዳ1፥13:15፤2ዜና 19፥5፤መዝ15፥2
47፥7 ቍ10፤ዘፍ 43፥15፤2ሳሙ14፥ 22፤19፥39፤1ነገ 8፥66
47፥9 ዘፍ3፥17፤ 25፥7፤መዝ39፥4:12፤ 89፥47፤ኢዮ8፥9
47፥10 ቍ7
47፥11 ዘፍ45፥10፤ 18፤ዘፀ1፥11፤12፥37፤ ዘኍ33፥3:5
47፥12 ዘፍ45፥11
47፥13 ዘፍ12፥10፤ 41፥30
47፥14 ዘፍ41፥34: 36፤ዘፀ7፥23፤8፥24፤ ኤር43፥9
47፥15 ቍ16:18: 19፤ዘፍ41፥57፤ዘፀ 16፥3
47፥16 ቍ15:18: 19
47፥17 ዘፍ12፥16፤ ዘፀ14፥9
47፥18 ቍ15:16
47፥19 ቍ15:16: 21:25፤ዘፍ42፥2
47፥20 ዘፍ12፥10
47፥21 ቍ19
47፥22 ቍ26፤ዘዳ

[ሬ]29 *ዕብራይስጡ በላዩ ላይ ይለዋል*
[ሶ]7 *ወይም ሰላምታ ካቀረበ*

46፥29 *አለቀሰ፤* 43፥30 እና ማብ ይመ።
46፥34 *ግብፃውያን ከብት አርቢዎችን እንደ ጸያፍ ስለሚ ቈጥሩ፤* የ43፥32 ማብ ይመ።
*47፥4 ራብ እስከሚያልፍ ብቻ እንጂ እስከ ወዲያኛው በጌሤም ምድር ለመኖር እንደማይፈልጉ በግልጽ አስታወቁት።*
47፥9 *በምድር ላይ በእንግድነት ያሳለፍኩት ዘመን፤* ያዕቆብ ለአብርሃምና ለዘሩ የምትሰጠውን ምድር በተስፋ ሲጠባበቅ ሳለ፣ የእስራኤል አባቶችና የእርሱም ሕይወት በመንከራተት የታወቀ መሆኑን ያወሳል (ዘዳ 26፥5 ይመ) *አባቶቼ... ከኖሩበት ዘመን ጋር ሲነጻጸር አጭር ነው፤* አብርሃም አንድ መቶ ሰባ አምስት ዓመት (25፥7)፣ ይስሐቅ ደግሞ አንድ መቶ ሰማንያ ዓመት (35፥28) ኖረል።
47፥11 *ምርጥ... ምድር፤* የ45፥10 ማብ ይመ። *ራምሴ፤* የራምሴ ከተማ በዘፀ 1፥11፤ 12፥37፤ ዘኍ 33፥3:5 ላይ ተጠቅሶ አል። ራምሴ የሚለው ስም ከዓመታት በኋላ በግብፅ ነግሦ የነበረውን ዳግማዊ ራምሴ የሚያመለክት ስለ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። የራምሴ ምድር ጌሤም (ቍ 27 ይመ) ተብላ ከመታወቋም ሌላ በመዝ 78፥12:43 ላይ "የጣኔዎስ በረሐ" ይባል ነበር (የ44፥4 ማብ ይመ)።
47፥13 *ራቡ እየጸና፤* ሕዝቡ እህል የሚሸምትበትን ገንዘብ በመጨረሱ (ቍ 14-15 ይመ) በመጀመሪያ ከብቶቻቸውን (ቍ 16-17)፣ ቀጥሎም መሬታቸውን (ቍ 20)፣ በመጨረሻም ራሳቸውን ለመሸጥ ተገደዱ (ቍ 21)።
*47፥21፤* የሚዘሩት ዘር እስኪሰጣቸው ድረስ ግብፃውያን

የእርሱ ርስት ይሁን፤ እኛም እንዳንሞት
መሬታችንም ጠፍ ሆኖ እንዳይቀር የምንዘራው
ዘር ስጠን።”
[20]ስለዚህ ዮሴፍ የግብፅን ምድር ሁሉ ለፈ
ርዖን ገዛለት፤ ራቡም እጅግ ስለጸናባቸው
ግብፃውያን ሁሉ እንዳቸውም ሳይቀሩ መሬ
ታቸውን ሸጡ፤ ምድሪቱም የፈርዖን ርስት
ሆነች። [21]ዮሴፍም የግብፅን ሕዝብ ከዳር
እስከ ዳር[a] የፈርዖን ገባር አደረገው። [22]ሆኖም
ዮሴፍ የካህናቱን መሬት አልገዛም፤ ምክንያቱም
ካህናቱ ከፈርዖን ቋሚ ድርጎ ስለሚያገኙና
ፈርዖን ከሚሰጣቸው ድርጎ በቂ ምግብ ስለ
ነበራቸው ነው፤ ከዚህም የተነሣ መሬታቸ
ውን አልሸጡም።
[23]ዮሴፍ ሕዝቡን እንዲህ አላቸው፤ “እነሆ፣
ዛሬ እናንተንም መሬታችሁንም ለፈርዖን
ገዝቻችኋለሁና ይህን ዘር ወስዳችሁ በመሬት
ላይ ዝሩ። [24]መከሩ በሚሰበሰብበት ጊዜ ግን
ከአምስት እጅ አንዱን ለፈርዖን ታስገባላ
ችሁ፤ ከአምስት እጅ አራቱን ደግሞ ለመ
ሬታችሁ ዘር፣ እንዲሁም ለራሳችሁ፣ ለቤተ
ሰቦቻችሁና ለልጆቻችሁ ምግብ ታደርጉታ
ላችሁ።”
[25]እነርሱም፣ “እንግዲህ ሕይወታችንን አትር
ፈህልናል፤ በጌታችን ፊት ሞገስ ካገኘን፣ ለፈ
ርዖን ገባሮች እንሆናለን” አሉት።
[26]ስለዚህ ዮሴፍ የምርቱ አንድ አምስተኛ
ለፈርዖን እንዲገባ የሚያዝ የመሬት ሕግ
አወጣ፤ ይህም ሕግ እስከ ዛሬ ይሠራበታል።
በዚያን ጊዜ በፈርዖን እጅ ያልገባው መሬት
የካህናቱ ብቻ ነው።
[27]በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን በግብፅ አገር
በጌሤም ይኖሩ ነበር፤ በዚያም ሀብት ንብ
ረት አፈሩ፤ ቍጥራቸውም እጅግ እየበዛ
ይሄድ ጀመር።
[28]ያዕቆብ በግብፅ ዐሥራ ሰባት ዓመት ኖረ፤ ዕድ
ሜውም አንድ መቶ አርባ ሰባት ዓመት
ነበር። [29]እስራኤልም የሚሞትበት ጊዜ መቃ

14፥28-29
47፥23 ነህ5፥3፤ኢሳ 55፥10፤61፥11
47፥24 ዘፍ41፥34
47፥25 ቍ19፤ዘፍ 32፥5
47፥26 ቍ22፤ዘፍ 41፥34
47፥27 ዘፍ1፥22፤ 12፥2፤17፥6፤33፥19፤ 45፥10፡18
47፥28 ዘፍ25፥7፤ መዝ105፥23
47፥29 ዘፍ19፥19፤ 24፥2:27፤27፥2፤32፥ 5፤46፥29፤መሳ1፥ 24፤2ሳሙ2፥6
47፥30 ዘፍ15፥15፤ 23፥20፤25፥9፤29፥ 16፤50፥25፤ዘፀ13፥ 19፤ኢሱ24፥32፤ሐሥ 7፥15-16
47፥31 ዘፍ21፥23፤ 32፥10፤24፥3፤46፥ 29፤ኢሱ2፥20፤መሳ 15፥12፤1ሳሙ24፥ 21፤30፥15፤1ነገ1፥ 47፤ዕብ11፥21
48፥1 ዘፍ41፥ 52፤ዕብ11፥21
48፥2 ቍ8:9:11: 14:20
48፥3 ዘፍ17፥1፤ 28፥13፡19፤32፥29
48፥4 ዘፍ12፥2:7፤ 15፥7፤17፥6፤28፥13
48፥5 ዘፍ29፥32: 33፤41፥50-52፤1ዜና 5፥1
48፥7 ዘፍ25፥20፤ 35፥19፤42፥38፤ሩት 1፥2፤1ሳሙ16፥4
48፥8 ቍ2:10
48፥9 ዘፍ24፥60፤ 33፥5

ረቡን እንደ ተረዳ ልጁን ዮሴፍን አስጠርቶ
እንዲህ አለው፤ “በአንተ ዘንድ ሞገስ ካገኘሁ
እጅህን በጭኔ ላይ አኑረህ፣ በጎነትንና ታማ
ኝነትን ልታደርግልኝ ቃል ግባልኝ፤ በምሞ
ትበት ጊዜ በግብፅ አትቅበረኝ፤ [30]እኔም
ከአባቶቼ ጋር ሳንቀላፋ፣ ከግብፅ አውጥተህ
እነርሱ በተቀበሩበት ቦታ ቅበረኝ።”
ዮሴፍም፣ “እሺ፣ እንዳልከኝ አደርጋለሁ”
አለ።
[31]ያዕቆብም፣ “በል ማልልኝ“ አለው። ዮሴ
ፍም ማለለት፤ እስራኤልም በዐልጋው ራስጌ
ላይ ሆኖ ጉንበስ አለ።[+]

## ምናሴና ኤፍሬም

**48** ከጥቂት ጊዜ በኋላም፣ “አባትህ ታሞ
አል” ተብሎ ለዮሴፍ ስለ ተነገረው
ሁለቱን ልጆቹን ምናሴንና ኤፍሬምን ይዞ
ሄደ። [2]ለያዕቆብ፣ “ልጅህ ዮሴፍ ወደ አንተ
መጥቶአል” ተብሎ በተነገረው ጊዜ፣ እስራ
ኤል ተበረታትቶ ዐልጋው ላይ ተቀመጠ።
[3]ያዕቆብም ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ “ሁሉን
የሚችል አምላክ[b] በከነዓን ምድር ሎዛ በም
ትባል ቦታ ተገለጠልኝ፤ ባረከኝም፤ [4]እንዲህም
አለኝ፤ ‘ፍሬያማ አደርግሃለሁ፣ ይህችንም
ምድር ከአንተ በኋላ ለሚነሡ ዘሮችህ የዘ
ላለም ርስት አድርጌ እሰጣቸዋለሁ።’
[5]“ወደዚህ ከመምጣቴ በፊት በግብፅ የወ
ለድሃቸው ሁለቱ ልጆችህ ከእንግዲህ የእኔ
ልጆች ሆነው ይቈጠራሉ፤ ሮቤልና ስምዖን
ልጆቼ እንደ ሆኑ ሁሉ፣ ኤፍሬምና ምና
ሴም ልጆቼ ይሆናሉ። [6]ከእነርሱ በኋላ የሚ
ወለዱልህ ልጆች ግን፣ የአንተ ይሁኑ፤ በር
ስት ድልድላቸው ግን በወንድሞቻቸው ስም
ይቈጠራሉ። [7]ከሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ

[a]21 ከአራተ ሳምራውያንና ከሰብዐ ሊቃናት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን (ቩልጌትንም ይመ) የማሶሬቲኩ ጽሑፍ ግን ሕዝቡን ወደ ከተሞች አጋዘ ይለዋል።
[+]31 ወይም እስራኤልም በዐልጋው ራስጌ በኩል ሰገደ
[b]3 ዕብራይስጡ ኤልሻዳይ ይላል

ለጊዜው ወደ ተለያዩ ከተሞች እንደሚበታተኑ ተደረገ (ቍ 23 ይመ)።

47፥26 *የምርቱ አንድ አምስተኛ ለፈርዖን እንዲገባ፤* “በሰ ባቱ የጥጋብ ዓመታት” (41፥34) ከምርቱ አንድ አምስተኛ ለፈር ዖን ይሰጥ ነበር፤ አሁን ግን እህሉ የሚመረትበት መሬትም ጭምር ለፈርዖን እንዲገባ ተደረገ።

47፥27 *እስራኤላውያን... ሀብት ንብረት አፈሩ፤* እየተዋ ለዱም በቍጥር እጅግ ጨመሩ፤ 35፥11-12፤ 46፥3 እና ማብ ይመ።

47፥29 *እጅህን በጭኔ ላይ አኑረህ፤* 24፥2 እና ማብ ይመ፤ በሁለቱም ክፍሎች ላይ በቤተ ሰብ በኩል ያለው ዝምድና አጽንዖት ተሰጥቶታል።

47፥30 *ከአባቶቼ ጋር ሳንቀላፋ፤* የ25፥8 ማብ ይመ። *እነርሱ በተቀበሩበት ቦታ ቅበረኝ፤* በማክፄላ ዋሻ ማለት ነው (50፥12-13 ይመ)።

47፥31 *በዐልጋው ራስጌ ላይ፤* በዕብ 11፥21 ላይ ተጠቅ ሶአል።

48፥3 *ሁሉን የሚችል አምላክ፤* የ17፥1 ማብ ይመ። *ሎዛ፤* ቀድሞ የቤቴል ስም ነበር (28፥19 ይመ)።

48፥5 *ሁለቱ ልጆችህ... የእኔ ልጆች ሆነው ይቈጠራሉ፤* ያዕቆብ እንደ ራሱ ልጆች አድርጎ አሳደጋቸው። *ኤፍሬምና ምናሴም፤* ምናሴ የዮሴፍ የመጀመሪያ ልጅ በመሆኑ (41፥51 ይመ) የስማቸውን ትክክለኛ ቅደም ተከተል በቍ 1 ላይ ይመ። ያዕቆብ የኤፍሬምን ስም ከምናሴ በፊት የጠቀሰው፣ የመጀመሪያ ውን በረከት ሊሰጠውና “ኤፍሬምን ከምናሴ ሊያስቀድመው” ስለ ፈለገ ነው (ቍ 20)። *ሮቤልና ስምዖን ልጆቼ እንደ ሆኑ ሁሉ... ልጆቼ ይሆናሉ፤* የዮሴፍ የመጀመሪያ ሁለት ልጆች ከያዕቆብ የመጀመሪያ ሁለት ልጆች ጋር እኩል መብት የነበራቸው ሲሆን (35፥23)፣ የኋላ ኋላ የያዕቆብን የመጀመሪያ ሁለት ልጆች ተክተ ዋቸዋል። ሮቤል ከዚህ በፊት በፈጸመው ኀጢአት ምክንያት (35፥22 እና ማብ ይመ) የብኵርናውን መብት አጣ፤ የሮቤል የብኵርና መብት ያዕቆብ ከልጆቹ ሁሉ አብልጦ ለሚወደው ልጁ ለዮሴፍና (49፥3-4፤ 1ዜና 5፥2 ይመ) ለዮሴፍ ልጆች ተሰጥ ቶአል (1ዜና 5፥1 ይመ)።

48፥6 *ከእነርሱ በኋላ የሚወለዱልህ ልጆች ግን፣ የአንተ ይሁኑ፤* ያዕቆብ የራሱ ልጆች አድርጎ ያሳደጋቸውን የኤፍሬም ንና የምናሴን ቦታ ወሰዱ። በርስት ድልድላቸው ግን የወንድሞ ቻቸውን ድርሻ ይወርሳሉ፤ በርስት ክፍፍል ጊዜ የኤፍሬምና የምናሴ ስም ሳይጠፋ ሕያው ሆኖ መቀጠል ይችላል (ለተመሳ ሳይ ሐሳብ 38፥8 እና ማብ፤ ዘዳ 25፥5-6 ይመ)። ሆኖም የዮሴፍ ድርሻ ለኤፍሬምና ለምናሴ የተከፋፈለ ሲሆን፣ ሌዊ ግን (የያዕ ቆብ ሦስተኛ ልጅ፤ 35፥23 ይመ) “የርስት ድርሻ አልተመደበለ ትም” (ኢሱ 14፥4)። እንግዲህ ለየነገዶቹ የተመደበው ርስት፣ ከነገዶቹ ብዛት ጋር እኩል ነበር ማለት ነው።

48፥7 *መስጴጦምያ፤* የ24፥10 ማብ ይመ።

መልስ ኤፍራታ ለመድረስ ጥቂት ሲቀረኝ፣
እናትህ ራሔል በከነዓን ምድር ሞታብኝ
ዐዘንሁ:: እኔም ወደ ኤፍራታ ማለት ወደ
ቤተልሔም በሚወስደው መንገድ ዳር ቀበር
ኋት::”
[8]እስራኤልም የዮሴፍን ልጆች ባየ ጊዜ፣
“እነዚህ እነማን ናቸው?” ሲል ጠየቀ፤
[9]ዮሴፍም፣ “እነዚህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) የሰጠኝ
ልጆች ናቸው” ብሎ ለአባቱ መለሰለት፤
እስራኤልም፣ “አቅርባቸውና ልመርቃቸው”
አለ::
[10]በዚህ ጊዜ እስራኤል ዐይኖቹ በእርጅና
ምክንያት በመድከማቸው አጥርቶ ማየት
ይሳነው ነበር፤ ስለዚህ ዮሴፍ ልጆቹን አባቱ
ዘንድ አቀረባቸው፤ አባቱም ስሞ ዐቀፋቸው::
[11]እስራኤልም ዮሴፍን፣ “ዐይንህን እንደ
ገና ዐያለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር፤ እግዚአ
ብሔር (ኤሎሂም) ግን ልጆችህን ጭምር ለማየት
አበቃኝ” አለው::
[12]ዮሴፍም ልጆቹን ከእስራኤል ጒልበት
ፈቀቅ በማድረግ አጐንብሶ በግንባሩ መሬት
ላይ ተደፋ:: [13]ከዚያም ዮሴፍ ሁለቱን ልጆ
ቹን ይዞ ኤፍሬምን ከራሱ በስተ ቀኝ፣ ከእ
ስራኤል በስተ ግራ፣ ምናሴን ደግሞ ከራሱ
በስተ ግራ፣ ከእስራኤል በስተ ቀኝ በኩል አቀ
ረባቸው:: [14]እስራኤል ግን ቀኝ እጁን በታ
ናሹ በኤፍሬም ራስ ላይ አኖረ፤ ግራ እጁንም
በቀኝ እጁ ላይ አስተላልፎ በበኵሩ በምናሴ
ራስ ላይ አኖረ::
[15]ከዚህ በኋላ ዮሴፍን ባረከ፤ እንዲህም
አለው፤

“አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ
የተመላለሱት እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣
ለእኔም እስከ ዛሬ ድረስ
በዘመኔ ሁሉ እረኛ የሆነኝ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣
[16]ከጒዳትም ሁሉ የታደገኝ መልአክ፣
እርሱ እነዚህን ልጆች ይባርክ፤

48፥10 ዘፍ27፥1፡ 27፤29፥13
48፥11 ቍ2፤ዘፍ 44፥28፤50፥23፤ኢዮ 42፥16፤መዝ103፥17፤ 128፥6
48፥12 ዘፍ19፥1፤ 33፥3፤37፥10፤ 50፥23፤ኢዮ3፥12
48፥13 መዝ16፥8፤ 73፥23፤110፥1፤ማቴ 25፥33
48፥14 ቍ2:17: 18፤ዘፍ25፥23፤29፥ 32፤41፥51
48፥15 ዘፍ5፥22፤ 24፥60፤49፥24፤ 2ሳሙ5፥2፤መዝ23፥ 1፤80፥1፤ኢሳ40፥11፤ ኤር23፥4
48፥16 ዘፍ12፥2፤ 13፥4፤16፥7፤24፥50፤ 28፥3:13፤2ሳሙ4፥9፤ 1ዜና5፥1፤መዝ71፥4፤ ኤር15፥21፤ሕዝ47፥ 13፤ዳን3፥17፤ዕብ 11፥21
48፥17 ቍ13:14
48፥18 ቍ14
48፥19 ዘፍ12፥2፤ 17፥20፤25፥23
48፥20 ቍ2፤ዘፍ 24፥60፤41፥51፤ዘሌ 9፥22፤ዘኍ2፥18:20፤ 6፥23፤10፥23፤ዘዳ10፥ 8፤21፥5፤ሩት4፥11፤ ኤር31፥9፤ዕብ11፥21
48፥21 ዘፍ15፥16፤ 26፥3፤28፥13፤ዘዳ30፥ 3፤መዝ126፥1፤ኤር 29፥14፤ሕዝ34፥13
48፥22 ዘፍ34፥26፤ 37፥8፤ኢሱ24፥32፤ ዮሐ4፥5
49፥1 ዘኍ24፥14፤ ዘዳ31፥29፤ኤር23፥ 20፤ዳን28፥45
49፥2 ቍ16:28፤ ኢሱ24፥1፤መዝ 34፥11

እነርሱም በስሜ፣
በአባቶቼ በአብርሃምና በይስሐቅ ስም ይጠሩ፤
በምድር ላይ እጅግ ይብዙ::
[17]ዮሴፍ፣ አባቱ ቀኝ እጁን በኤፍሬም ራስ
ላይ ማድረጉን ሲያይ ተከፋ፤ ከኤፍሬም
ራስ ላይ አንሥቶ በምናሴ ራስ ላይ ለማ
ኖር የአባቱን እጅ ያዘ፤ [18]ዮሴፍም፣ “አባቴ
ሆይ፤ እንዲህ አይደለም በኵሩ ይህኛው ስለ
ሆነ፣ ቀኝ እጅህን እርሱ ራስ ላይ አድርግ”
አለው::
[19]አባቱ ግን፣ “ዐውቃለሁ፤ ልጄ ዐውቃ
ለሁ፤ እርሱም እኮ ሕዝብ ይሆናል፤ ታላቅም
ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ታናሽ ወንድሙ ከእ
ርሱ ይበልጣል፤ ዘሮቹም ታላቅ ሕዝቦች ይሆ
ናሉ” ብሎ እምቢ አለው:: [20]በዚያን ዕለት ባረ
ካቸው፤ እንዲህም አላቸው፤

“በአንተ ስም እስራኤል እንዲህ ብሎ
ይመርቃል፤
‘እግዚአብሔር (ኤሎሂም) እንደ ኤፍሬምና
እንደ ምናሴ ያድርጋችሁ::’”

በዚህ ሁኔታም ኤፍሬምን ከምናሴ አስቀ
ደመው::
[21]ከዚህ በኋላ እስራኤል ዮሴፍን እንዲህ
አለው፤ እኔ የምሞትበት ጊዜ ተቃርቦአል፤
ነገር ግን እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከእናንተ ጋር
ይሆናል፤ ወደ አባቶቻችሁም ምድር መልሶ
ያገባችኋል:: [22]እነሆ በሰይፌና በቀስቴ ከአ
ሞራውያን እጅ የወሰድኳትን ዐምባ ከወን
ድሞችህ ድርሻ አብልጬ ለአንተ ሰጥቼሃለሁ::”[+]

## ያዕቆብ ልጆቹን ባረከ
49፥1-28 ማብ - ዘዳ 33፥1-29

**49** ከዚህ በኋላ ያዕቆብ ልጆቹን ሁሉ
አስጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ “በኋለ
ኛው ዘመን ምን እንደሚደርስባችሁ እነግራችሁ

[+]22 *ወይም ከወንድሞችህ ድርሻ አብልጬ ለአንተ አንድ ክፍል እሰጥሃለሁ*

*ራሔል... ሞታብኝ፤* 35፥16-19 ይመ:: የዮሴፍ አባት የራሱ ልጆች አድርጎ ሊያሳድጋቸው የወሰዳቸው ኤፍሬምና ምናሴ፣ የዮሴፍ እናት ራሔል ባትሞት ኖሮ ሌሎች ልጆች ትወልድ ነበር፤ ምንም እንኳ ልጆችን ሳትወልድ ብትሞትም የልጅ ልጆቿ ተተኩ:: *ኤፍ ራታ፤* የ35፥16 ማብ ይመ::

48፥8 *እስራኤልም... “እነዚህ እነማን ናቸው?” ሲል ጠየ ቀው፤* ከዚህ በፊት አይቶአቸው ስለማያውቅ ወይም ከማርጀቱ የተነሣ በትክክል ሊያያቸው ስላልቻለ ሊሆን ይችላል::

48፥10 *ዐይኖቹ በእርጅና ምክንያት በመድከማቸው አጥ ርቶ ማየት ይሳነው ነበር፤* የ27፥1 ማብ ይመ:: *ስሞ ዐቀፋቸው፤* የሳ ማቸው በጒልበቱ ላይ አድርጎ በመሆኑ (ቍ 12 ይመ)፣ ምናል ባት ይህ ሁኔታ የራሱ ልጆች አድርጎ ሊያሳድጋቸው የወሰዳቸው መሆኑን ያሳያል:: (የ30፥3 ማብ ይመ)::

*48፥13-20፤* የሐሥ 6፥6 ማብ ይመ::

48፥13 *ምናሴን... ከእስራኤል በስተ ቀኝ፤* ያዕቆብ ቀኝ እጁን የዮሴፍ የመጀመሪያ ልጅ በሆነው በምናሴ ራስ ላይ አድ ርጎ እንዲባርከው ዮሴፍ ፈልጎ ነበር::

48፥15 *ባረከ፤* አባቱ ይስሐቅ እርሱን እንደ ባረከው ሁሉ ማለት ነው (22፥27-29):: *ዮሴፍን፤* በዚህ ቦታ ኤፍሬምንና ምና ሴን ለማመልከት የገባ ቃል ነው:: *አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ የተመላለሱት፤* የ5፥22፤ የ17፥1 ማብ ይመ:: *እረኛ፤* ይህ ቃል በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰው በዚህ ቦታና ያዕቆብ ዮሴፍን በባረከበት ክፍል (49፥24) ብቻ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ጽኑ ኅብረት እንዳለው የሚያሳይ ቃል ነው (መዝ 23፥1 ይመ)::

48፥16 *መልአክ፤* የ16፥7 ማብ ይመ:: መልአኩ፣ (እግዚአ ብሔር ራሱ) ቀደም ሲል ያዕቆብን ባርኮት ነበር (32፥29፤ እንዲ ሁም የ32፥24 ማብ ይመ)::

48፥19 *ታናሽ ወንድሙ... ይበልጣል፤* የ25፥23 ማብ ይመ:: የእስራኤል መንግሥት ከሁለት ተከፍሎ በነበረበት ወቅት (930-722 ዓ.ቅ.ክ.) የኤፍሬም ዝርያዎች በሰሜኑ ግዛት ከነበሩት ሁሉ እጅግ ብርቱዎች ነበሩ:: “ኤፍሬም” የሚለው ስም አብዛኛ ውን ጊዜ ሰሜናዊውን መንግሥት ለማመልከት ያገለግል ነበር (ኢሳ 7፥2:5:8-9፤ ሆሴ 9፥13፤ 12፥1:8 ይመ)::

48፥20 *ኤፍሬምን ከምናሴ አስቀደመው፤* ብኵርናንና በረ ከትን ለማግኘት ሲል፣ ከዔሳው ጋር በጽኑ የታገለው፣ ታናሿን (ራሔልን) ከታላቋ (ከልያ) አብልጦ የወደደው ያዕቆብ፣ አሁን ደግሞ ከዮሴፍ ልጆች መካከል ከታላቁ ይልቅ ታናሹን አስቀደመ::

48፥21 *ዮሴፍን፤* የቍ 15 ማብ ይመ:: *እኔ የምሞትበት ጊዜ ተቃርቦአል፤* ከብዙ ዓመታት በኋላ ዮሴፍ ይህንኑ ቃል ለወ ንድሞቹ ተናግሮአል (50፥24)::

48፥22 *ዐምባ፤* ይህን ቃል ለመግለጽ የገባው የዕብራ-ይስጡ ሐረግ ሴኬም ከሚለው የቦታ ስም ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን፣ ዮሴፍ የተቀበረው የዘሮቹ ርስት በሆነችው በዚችው በሴኬም ምድር ነው (ኢሱ 24፥32 ይመ፤ እንዲሁም 33፥19፤ ዮሐ 4፥5 ይመ):: *ከአሞራውያን እጅ የወሰድኳትን፤* ምናልባት በ34፥25-29 ላይ ያለውን ታሪክ የሚያስታውስ ሳይሆን አይቀርም::

49፥1 *በኋለኛው ዘመን ምን እንደሚደርስባችሁ፤* ይህ ሐረግ

ዘንድ ተሰብሰቡ።

2“እናንተ የያዕቆብ ልጆች ሆይ፤ ተሰብሰቡና
ስሙ፤
አባታችሁ እስራኤልንም አድምጡ፤

3“ሮቤል፣ አንተ የበኵር ልጄ ነህ፤
ኀይሌና የጕብዝናዬም መጀመሪያ፤
በክብር ትልቃለህ በኀይልም
ትበልጣለህ።
4እንደ ውሃ የዋለልህ ነህና እልቅና
አይኖርህም፤
የአባትህን መኝታ ደፍረሃል፤
ምንጣፌንም አርክሰሃል።

5ስምዖንና ሌዊ ወንድማማቾች፣
ሰይፎቻቸው[ሀ] የዐመፅ መሣሪያዎች ናቸው።
6ወደ ሸንጎአቸው አልግባ፤
ጉባኤያቸው ውስጥ አልገኝ፤
በቍጣ ተነሣሥተው ሰዎችን ገድለዋል፤
የበሬዎችንም ቋንጃ እንዳሻቸው
ቈራርጠዋል።
7እጅግ አስፈሪ የሆነ ቍጣቸው፣
ጭከና የተሞላ ንዴታቸው የተረገመ
ይሁን፤
በያዕቆብ እበትናቸዋለሁ፤
በመላው እስራኤልም አሠራጫቸዋለሁ።

8“ይሁዳ፣[ለ] ወንድሞችህ ይወድሱሃል፤
እጅህም የጠላቶችህን ዐንገት ዐንቆ ይይዛል፤
የአባትህ ልጆች በፊትህ ተደፍተው
ይሰግዱልሃል።
9“አንተ የአንበሳ ደቦል ይሁዳ፤
ከዐደንህ የምትመለስ ልጄ፣
እንደ አንበሳ ያደፍጣል፤ በምድርም ላይ
ይተኛል፤
እንደ እንስት አንበሳም ያደባል፤
ታዲያ ማን ሊቀሰቅሰው ይደፍራል?
10በትረ መንግሥት ከይሁዳ እጅ አይወጣም፤
የገዥነት ምርኵዝም ከእግሮቹ መካከል።
ገዥነት የሚገባው እስኪመጣ ድረስ፣[ሐ]
ሕዝቦች ሁሉ ይታዘዙታል።
11አህያውን በወይን ግንድ፣
ውርንጫውንም በምርጡ የወይን ሐረግ
ቅርንጫፍ ላይ ያስራል፤
ልብሱን በወይን ጠጅ፣
መጐናጸፊያውንም በወይን ጭማቂ ያጥባል።
12ዐይኖቹ ከወይን ጠጅ የቀሉ፣
ጥርሶቹም ከወተት ይልቅ የነጡ ይሆናሉ።

13“ዛብሎን፣ በባሕር ዳር ይኖራል፤
የመርከቦች መጠጊያም ይሆናል፤
ወሰኑም እስከ ሲዶና ይደርሳል።

14“ይሳኮር፣ ዐጥንተ ብርቱ አህያ፣
በጭነት[መ] መካከል የሚተኛ፣
15ማረፊያ ቦታው መልካም፣
ምድሪቱም አስደሳች መሆኗን ሲያይ፣
ትከሻውን ለሸክም ያመቻቻል፤
ተገድዶም ያገለግላል።

49፥3 ዘፍ29፥32፤ 34፥19፤41፥51፤ዘዳ 21፥17፤መዝ78፥51፤ 105፥36
49፥4 ዘፍ29፥29፤ 34፥5፤ኢሳ57፥20፤ ኤር49፥23
49፥5 ዘፍ29፥33፡ 34፤34፥25፤ምሳ4፥17
49፥6 ዘፍ34፥26፤ ኢሱ11፥6፡9፤2ሳሙ 8፥4፤1ዜና18፥4፤ መዝ1፥1፤ምሳ1፥15፤ ኤፌ5፥11
49፥7 ዘፍ34፥7፡25፤ ኢሱ19፥1፡9፤21፥1-42
49፥8 ዘፍ9፥25፤ 29፥35፤ዘዳ28፥48፤ 1ዜና5፥2
49፥9 ቍ27፤ዘኍ 23፥24፤24፥9፤ኢዮ 38፥39፤መዝ7፥2፤10፥ 9፤17፥12፤22፥13፤ 104፥21፤ሕዝ19፥2፡5፤ ሚክ5፥8፤ራእ5፥5፤
49፥10 ዘኍ24፥17፡ 19፤መሳ1፥1-2፤20፥ 18፤1ዜና5፥2፤28፥4፤ መዝ2፥9፤60፥7፤72፥ 8-11፤98፥3፤108፥8፤ 110፥2፤ኢሳ2፥4፤26፥ 18፤42፥1፡4፤45፥22፤ 48፥20፤49፥6፤51፥5፤ ሕዝ21፥27
49፥11 ዘዳ8፥8፤32፥ 14፤መሳ5፥10፤10፥4፤ 2ነገ18፥32፤ኢሳ63፥2 ፤ዘካ9፥9
49፥12 ማሕ5፥12
49፥13 ዘፍ10፥19፤
49፥16 ቍ2፤ዘፍ 30፥6
49፥17 ቍ19፤መሳ 30፥20 49፥14 ዘፍ30፥18፤መሳ5፥16፤መዝ68፥13 49፥15 ኢሱ 19፥17-23፤1ነገ4፥6፤5፥13፤9፥21፤ሕዝ29፥18፤ኢሳ14፥2፤31፥8

[ሀ]5 በዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጕም አይታወቅም
[ለ]8 ይሁዳ የሚለው ቃል ውዳሴ የሚል ትርጕም ካለው የዕብራይስጥ ቃል የመጣ ሲሆን፣ ከዚሁ ቃል ጋር አንድ ዐይነት ድምፅ አለው
[ሐ]10 ወይም ሴሎ እስኪመጣ ድረስ ወይም ክብር የሚገባው እስኪመጣ ድረስ
[መ]14 ወይም በሰፈር ግዳ የሚነድ እሳት

እስራኤል በመጨዎች ዘመናት ምን እንደሚያጋጥማት የሚያመለክት ሲሆን፣ ሐረጉ ሁለት ገጽታ እንዳለው እንደ አንድ ሳንቲም ሊታይ የሚችል ነው። በአንድ በኩል እስራኤላውያን የከነዓንን ምድር እንደሚወርሱ ሲያሳይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ መሲሑ የሚመጣበትን ቀን ያሳያል። ሐረጉ አንዳንድ ጊዜ እስራኤል በታላቁ መከራ ቀን የሚደርስባትን (ዘዳ 4፥30) ወይም የአሕዛብን መንግሥታት ታሪክ (ዳን 2፥28) ወይም ደግሞ በጥቅሉ የቤተ ክርስቲያንን ዘመንና (ዕብ 1፥2) ፍጻሜውን (2ጢሞ 3፥1፤ ያዕ 5፥3) ሊያመለክት ይችላል። ያዕቆብ በዘፍ 49 ላይ የተናገረው ቃል የትንቢት ቃል (ቍ 1) እና የበረከት ቃል (ቍ 28) ነው።

*49፥2-27፤* አብዛኛውን ጊዜ “የያዕቆብ በረከት” ተብሎ የሚታወቀው ሲሆን፣ በዘፍጥረት መጽሐፍ ረጅሙ ግጥም ነው። በረከቶቹ የተሰጡት ለዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ብቻ ሳይሆን፣ ከእነርሱም አብራክ ለሚከፈሉት ዘሮች ጭምር ነው (ቍ 28 ይመ)። በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ስላሉት የበረከት ግጥሞች 9፥26-27፤ 14፥19-20፤ 27፥27-29፤ 27፥39-40፤ 48፥15-16፤ 48፥20 ይመ።

49፥4 *እንደ ውሃ የዋለልህ፤* የሮቤል ዘሮች በወላዋይነት የታወቁ ናቸው (መሳ 5፥15-16 ይመ)። *እልቅና አይኖርህም፤ የአባትህን መኝታ ደፍረሃል፤* 35፥22 እና ማብ፤ እንዲሁም የ37፥21፤ የ48፥5 ማብ ይመ።

49፥5 *ስምዖንና ሌዊ ወንድማማቾች፤* ቍጣቸው ብስጭታቸውና ጭካኔአቸው ተመሳሳይ ነው (ቍ 6-7 ይመ)።

49፥7 *እበትናቸዋለሁ፤* ይህ ትንቢት የስምዖን ዘሮች ለይሁዳ በተሰጠው ግዛት ውስጥ በገቡ ጊዜና (ኢያ 19፥1፡9 ይመ) የሌዊ ዘሮች ደግሞ በመላ አገሪቱ ተበትነው በ48 ከተሞች በመኖራቸውና በአካባቢው ያሉትን የግጦሽ መሬቶች ሁሉ በያዙባቸው ጊዜያት ተፈጽሞአል። 48፥6 ማብ እንዲሁም ዘኍ 35፥2፡7፤ ኢያ 14፥4፤ 21፥41 ይመ)።

*49፥8፤* ከ27፥29፡40፤ 37፥7፡9 ጋር ያነጻጽሩ። *ይሁዳ ወንድሞችህ... በፊትህ ተደፍተው ይሰግዱልሃል፤* የ43፥3 ማብ ይመ። ይሁዳ የደቡቡ መንግሥት/ነገድ፣ ዮሴፍ ደግሞ የሰሜኑ መንግሥት/ነገድ መራሕያን በመሆናቸው፣ የያዕቆብን ረጅም በረከት የተቀበሉ እነርሱ ናቸው (ቍ 8፥12፡22-26)። ይሁዳ ለልያም ሆነ ለያዕቆብ አራተኛ ልጅ (29፥35) ሲሆን፣ ሮቤል፣ ስምዖንና ሌዊ በፈጸሙት ጥፋት መራሔ ነገድነት ለይሁዳ (ለልያ ልጅ) እንዲሁም ዕጥፍ ድርብ መራሔ ነገድነት ለዮሴፍ (ለራሔል ልጅ) ተሰጠ። 1ዜና 5፥2 ይመ።

49፥9 *የአንበሳ ደቦል፤* የሉዓላዊነት፣ የኀያልነትና የደፋርነት ምሳሌ ነው። ከጊዜ በኋላ ይሁዳ (ወይም እስራኤል) አብዛኛውን ጊዜ በአንበሳ ተመስሎአል (ሕዝ 19፥1-7፤ ሚክ 5፥8፤ በተለይም ዘኍ 24፥9 ይመ)። ከይሁዳ ነገድ የተገኘው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ (የ43፥3 ማብ ይመ) “ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ” (ራእ 5፥5) ተብሎ ተጠርቶአል።

*49፥10፤* ምንም እንኳ የዚህን ቍጥር ቃል ለመተርጐም አስቸጋሪ ቢሆንም፣ ከጥንት ጀምሮ ይህ ቍጥር የሚናገረው ስለ መሲሑ ነው የሚል አስተያየት አለ። በዚህ ቍጥር ላይ የተነገረው ቃል በመጀመሪያ በዳዊት፣ በመጨረሻ ደግሞ በክርስቶስ ተፈጽሞአል። *በትረ መንግሥት፤* ዘኍ 24፥17 እና ማብ ይመ። *ገዥነት የሆነው እስኪመጣ ድረስ፤* ይህ ሐረግ የይሁዳ መንግሥት የመጨረሻው ንጉሥ የሆነው ሴዴቅያስ “የራስ ዘውድህን አንሣ” ተብሎ በተነገረበት ክፍል ውስጥ ቃል በቃል ተጠቅሶአል (ሕዝ 21፥27)፤ ሴዴቅያስ ዘውድህን ከራስህ ላይ አንሣ የተባለው በኢየሩሳሌም ላይ መንገሥና መግዛት የሚገባው ትክክለኛው ንጉሥና ገዥ አንድ ቀን ስለሚመጣ ነው።

*49፥11፤* የይሁዳ ዘሮች እፎይታ የሚያገኙትና የሚበለጽጉበት ቀን እንደሚመጣ ያመለክታል።

*49፥13፤* የዛብሎን ዘሮች ምንም እንኳ ለአሴርና ለምናሴ በተሰጡ ርስቶች የታጠሩ (ወይም የባሕር በር የሌላቸው) ቢሆኑም፣ ለሜድትራኒያን ባሕር ቅርብ በመሆናቸው (ከባሕሩ 16 ኪሎ ሜትር ብቻ ይርቃሉ)፣ “የባሕሩን ባለ ጠግነት ይጠግባሉ” (ዘዳ 33፥19)።

16“ዳንᵃ ከእስራኤል ነገዶች እንደ አንዱ
ሆኖ፣
በራሱ ሕዝብ ላይ ይፈርዳል።
17ዳን የመንገድ ዳር እባብ፣
የመተላለፊያም መንገድ እፉኝት ነው፤
ጋላቢው የኋሊት እንዲወድቅ፣
የፈረሱን ሰኮና ይነክሳል።
18“እግዚአብሔር ሆይ (ያህዌ)፤ ማዳንህን
እጠባበቃለሁ።
19“ጋድንᵇ ወራሪዎች አደጋ ይጥሉበታል፤
እርሱ ግን ዱካቸውን ተከታትሎ
ብድሩን ይመልሳል።
20“አሴር ማእደ ሰፊ ይሆናል፤
ለነገሥታትም የሚስማማ ምግብ
ያቀርባል።
21“ንፍታሌም ነጻ እንደ ተለቀቀች፣
የሚያማምሩም ግልገሎችᶜ
እንደምትወልድ ሚዳቋ ነው።
22“ዮሴፍ፤ ፍሬያማ የወይን ተክል፣
በምንጭ ዳር የተተከለ ወይን ነው።
ሐረጎቹ ቅጥርን ያለብሳሉ።ᵈ
23ቀስተኞች በጭካኔ አጠቁት፤
በጥላቻም ነደፉት።

18፥27፤ኢር18፥17፤ አሞ9፥3
49፥18 ዘፍ45፥7፤ መዝ40፥1-3፤119፥ 166፡174
49፥19 ቀኑ17፤ዘፍ 30፥11
48፥20 ዘፍ30፥13፤ ኢሳ25፥6፤ኢዮ29፥6
49፥21 ዘፍ30፥8፤ ኢዮ39፥1
49፥22 ዘፍ17፥6፤ 30፥24፤መዝ80፥10፤1 28፥3፤ሕዝ19፥10
49፥23 ዘፍ27፥41፤ 37፥24፤1ዜና10፥3
49፥24 ዘፍ48፥15፤ ዘዳ32፥4፡15፡18፡31፤ ኢዮ29፥20፡34፤132፥

ᵃ16 *ዳን ማለት ፍትሕ ይሰጣል ማለት ነው*
ᵇ19 *ጋድ ማለት ማጥቃት እንዲሁም ወራሪ ሰራዊት ማለት ነው*
ᶜ21 *ወይም ነጻ፤ ውብ ቃሉችን የሚናገር*
ᵈ22 *ወይም ዮሴፍ የዱር የፈረስ ግልገል፣ በምንጭ ዳር ያለ የፈረስ ግልገል፣ በባለ ዕርከን ኮረብታ ላይ የዱር አህያ ነው*

49፥17 *ዳን... እባብ... እፉኝት ነው፤* የዳናውያን ተንኰል በመሳ 18፥27 ላይ ተገልጾአል። *የፈረሱን ሰኮና ይነክሳል፤* ከዳን ነገድ የሆነው ሶምሶን ምንም መሣሪያ ሳይዝ በባዶ እጁ ፍልስጥኤማውያንን ያስጨንቃቸው ነበር (መሳ 14-16)።

*49፥18፤* ያዕቆብ የልጆቹን ስም አንድ በአንድ እየጠራ መባረኩን አቋርጦ እግዚአብሔር እንዲረዳው ጸለየ።


49፥19 *ጋድ በወራሪዎች አደጋ ይደርስበታል፤* ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ይኖሩ የነበሩትን የጋድ ዘሮች (ኢሱ 13፥24-27 ይመ) በስተ ደቡብ ይኖሩ የነበሩትን ሞዓባውያንን በየጊዜው እየወረሩ አደጋ ይጥሉባቸው እንደ ነበር አንድ ሜሻዕ ስቴል (2ነገ 3፥4 ይመ) የተባለ የሞዓባውያን የድንጋይ ጽሑፍ ይገልጻል (ይህ ጽሑፍ ከክርስቶስ ልደት በፊት በዘጠነኛው ምዕተ ዓመት እንደ ተጻፈ ይገመታል)።

49፥20 *አሴር ማእደ ሰፊ ይሆናል፤* በሜድትራኒያን ባሕር አካባቢ የሚገኙት ለም የዕርሻ መሬቶች (ኢሱ 19፥24-30 ይመ) የአሴር ዘሮች ምን ያህል ባለ ጠጎች እንደ ነበሩ ያረጋግጣሉ።

49፥21 *ንፍታሌም ነጻ እንደ ተለቀቀች... ሚዳቋ ነው፤* የንፍታሌም ዘሮች ከገሊላ ባሕር በስተ ሰሜን በኰረብታማው አገር ለብቻቸው ተለይተው እንዲኖሩ በመደረጉ የተሰማቸውን ደስታ ሳያመለክት አይቀርም (ኢሱ 19፥32-38 ይመ)።

49፥22 *ፍሬያማ፤* የኤፍሬም ስም ሁለት ፍሬ እንዲኖረው የሚያደርግ ቅኔያዊ አገባብ ሲሆን፣ ኤፍሬም ከዮሴፍ የመጀመሪያ ልጅ ከምናሴ እንደሚበልጥ ያዕቆብ ትንቢት ተናግሮለታል (48፥19-20)። *ሐረጎች ቅጥርን ያለብሳሉ፤* የኤፍሬም ዘሮች ግዛታቸን (ርስታቸውን) እንደሚያሰፉ የሚያሳይ ቃል ነው (ኢሱ 17፥14-18 ይመ)።

## የእስራኤል ነገዶች




*በጵንኤል ያዕቆብ ከመለኮታዊ መልእክተኛ ጋር ሲታገል ስሙ ትእምርታዊ በሆነ መልኩ ወደ እስራኤል ተቀየረ። የ12ቱ ነገዶች አባት እንደ መሆኑ መጠን፣ ይህ ሕዝብ በእርሱ ስም መጠራት ጀመረ፤ በግጥምም “ያዕቆብ” እየተባለ ይጠራል።

** ከነዓንን ከወረሱ በኋላ ለሌዊ ወገን ርስት አልተሰጠውም ነበር (ዘፍ 49፥7)። በምትኩ ሌዋውያን ለሕዝቡ የክህነት አገልግሎትን በመስጠት ለእግዚአብሔር የተለዩ እንዲሆኑ ሙሴ አደረገ (ዘኍ 3፥1-4: 49)፤ ኢያሱም በመላው እስራኤል የተለያዩ 48 ከተሞችን ለሌዋውያን ሰጠ (ኢሱ 21፥1-45)።

*** ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች ኤፍሬምንና ምናሴን ልጆቹ አድርጎ ስለ ወሰዳቸው ዮሴፍ በእስራኤል የሁለት ነገዶች አባት ሆኖአል።

24ነገር ግን በያዕቆብ ኀያል አምላክ ክንድ፣[ዐ]
እረኛው በሆነው በእስራኤል ዐለት፣
ቀስቱ ጸና፤
ጠንካራ ክንዱም ቀለጠፈ::
25አንተን በሚረዳህ በአባትህ አምላክ፣
በሚባርክህ፣ ሁሉን ማድረግ በሚችል
አምላክ፣[ሀ]
ከላይ ከሰማይ በሚገኝ ረድኤት፣
ከምድር ጥልቅ በሚገኝ በረከት፣
ከማሕፀንና ከጡት በሚገኝ ምርቃት
ይባርክሃል::
26ከጥንት ተራሮች በረከት፣
ከዘላለም ኰረብቶች ምርቃት ይልቅ፣
የአባትህ በረከት ይበልጣል፤[ለ]
ይኸ ሁሉ በዮሴፍ ራስ ላይ ይውረድ፤
በወንድሞቹ መካከል አለቃ በሆነውም
ግንባር ላይ ይረፍ::[ሐ]

27ብንያም፣ ነጣቂ ተኵላ ነው፤
ያደነውን ማለዳ ይበላል፤
የማረከውን ማታ ይከፋፈላል::

28እነዚህ ሁሉ ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ናቸው:: ይህም እያንዳንዳቸውን ተገቢ በሆነው በረከት አባታቸው ሲባርካቸው የተናገረው ቃል ነው::

### የያዕቆብ መሞት

29ከዚህ በኋላ ያዕቆብ እንዲህ ሲል አዘዛ
ቸው፤ "እነሆ፤ ወደ ወገኖቼ የምሰበሰብበት
ጊዜ ደርሶአል፤ በኬጢያዊው በኤፍሮን ዕርሻ
ውስጥ ባለችው ዋሻ ከአባቶቼ ዘንድ ቅበሩኝ፤
30ይህ በከነዓን ምድር፣ በመምሬ አጠገብ፣
በማክፈላ ዕርሻ ውስጥ ያለው ዋሻ፣ የመ
ቃብር ቦታ እንዲሆን አብርሃም ከኬጢያ
ዊው ኤፍሮን ላይ ከነዕርሻ ቦታው የገዛው
ነው:: 31በዚያ አብርሃምና ሚስቱ ሣራ ተቀ
ብረዋል፤ በዚያ ይስሐቅና ሚስቱ ርብቃ ተቀ
ብረዋል፤ እኔም ልያን የቀበርኋት እዚያው
ነው፤ 32ዕርሻውና ዋሻው የተገዙት ከኬጢ
ያውያን[መ] ላይ ነው::"
33ያዕቆብ እነዚህን ቃላት ለልጆቹ ተናግሮ እን
ደበቃ፣ እግሮቹን በዐልጋው ላይ ሰብስቦ፣ የመ
ጨረሻ ትንፋሹን ተነፈሰ፤ ወደ ወገኖቹም
ተሰበሰበ::

50 ዮሴፍ በአባቱ ፊት ተደፍቶ አለቀሰ፣
ሳመውም:: 2ከዚያም የአባቱ የእስራ
ኤል ሬሳ እንዳይፈርስ ባለ መድኀኒት የሆኑ
አገልጋዮቹ በመድኀኒት እንዲቀቡት አዘዘ:: ባለ
መድኀኒቶቹም እንዳይፈርስ ሬሳውን፣ በመ
ድኀኒት ቀቡት:: 3ሬሳው እንዳይፈርስ መድ
ኀኒት መቀባቱ በአገሩ ልማድ መሠረት
አርባ ቀን ወሰደባቸው፤ ግብፃውያንም ሰባ
ቀን አለቀሱለት::
4የሐዘኑ ጊዜ እንዳበቃ ዮሴፍ የፈርዖንን
ቤተ ሰዎች እንዲህ አላቸው፤ "በፊታችሁ
ሞገስ አግኝቼ ከሆነ፣ ለፈርዖን እንዲህ ብላ
ችሁ ንገሩልኝ፣ 5'የምሞትበት ጊዜ ስለ ተቃ
ረበ፣ በከነዓን ምድር ራሴ ቈፍሬ ባዘጋጀ
ሁት መቃብር እንድትቀብረኝ' ሲል አባቴ
አስምሎኛል፤ ስለዚህ ወደዚያ ሄጄ አባቴን
ልቅበር ከዚያም እመለሳለሁ::"
6ፈርዖንም፣ "ባስማለህ መሠረት ሄደህ አባ
ትህን ቅበር" አለው::
7ከዚያም ዮሴፍ አባቱን ለመቅበር ወጣ፤
የፈርዖን ሹማምንት በሙሉ፣ የቤተ መንግ
ሥቱ ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖች እንዲሁም የግ
ብፅ ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖች ሁሉ ተከተሉት::
8እንደዚሁም የዮሴፍ ቤተ ሰዎች፣ ወንድሞ
ቹና ሌሎችም የአባቱ ቤተ ሰዎች በሙሉ
አብረውት ሄዱ:: በጌሤም የቀሩት ሕፃናት
ልጆቻቸው፣ የበግ፣ የፍየልና የከብት መንጋ
ዎቻቸው ብቻ ነበሩ:: 9እንዲሁም ሠረገሎችና
ፈረሰኞች[ሠ] አብረውት ወጡ፤ አጀቡም እጅግ
ብዙ ነበረ::
10እነርሱም በዮርዳኖስ ማዶ ካለው አጣድ
ከተባለው ዐውድማ ሲደርሱ፣ ድምፃቸውን
ከፍ በማድረግ ምርር ብለው አለቀሱ፤ ዮሴፍም

2:5፤1ሳሙ2፥2፤2ሳሙ22፥32፤መዝ18፥2:31:34፤19፥14፤78፥35፤89፥26፤132፥2:5፤144፥1፤ኢሳ1፥24፤10፥34፤17፥10፤26፥4፤30፥29፤44፥8፤49፥26፤60፥16፤63፥12፤ዕን1፥12
49፥25 ዘፍ17፥1፤27፥28፤28፥13፤ዘፀ18፥4፤ዘዳ7፥13፤28፥4፤መዝ27፥9፤107፥38፤ምሳ10፥22፤ኢሳ66፥11
49፥26 ዘፍ37፥8፤1ዜና5፥1፤ሕዝ47፥13፤ዕን3፥6
49፥27 ቍ9፤ዘፍ35፥18፤ዘኍ31፥11፤ዘዳ2፥35፤መሳ8፥24፤20፥12-13፤ኢሱ7፥21፤8፥2፤22፥8፤ዕን1፥8፤ሶፎ3፥3
49፥28 ቍ2፤ዘፍ27፥4
49፥29 ዘፍ15፥15፤25፥8:9፤50፥16:25፤2ሳሙ2፥32፤19፥37
49፥30 ዘፍ13፥18፤23፥4:9:20
49፥31 ዘፍ23፥19:20፤24፥67፤25፥9፤29፥16
49፥32 ዘፍ10፥15
49፥33 ዘፍ25፥8፤ሐሥ7፥15
50፥1 ዘፍ29፥11፤46፥4
50፥2 ቍ26፤2ዜና16፥14፤ ማቴ26፥12፤ማር16፥1፤ዮሐ19፥39-40
50፥3 ዘፍ37፥34፤ዘዳ1፥3
50፥4 ቍ7፤ዘፍ27፥41፤30፥27፤32፥5
50፥5 ቍ24፤ዘፍ24፥37፤47፥31፤2ሳሙ18፥18፤2ዜና16፥14፤ኢሳ22፥16፤ማቴ8፥21፤27፥60
50፥7 ቍ4፤ዘፍ45፥16
50፥10 ዘፍ27፥41፤37፥34፤ዘሌ10፥6፤ዘኍ15፥20፤ሩት
50፥8 ቍ14፤ዘፍ45፥10 50፥9 ዘፍ41፥43

ዐ23-24 ወይም *ቀስተኞች ያጠቃሉ... ያስፈንጥሩሉ... ይናራሉ... ይቈያሉ*
ሀ25 ዕብራይስጡ *ሻዳይ* ይለዋል
ለ26 *...ከአያት ቅድማያቶቼ... ታላቅ ነው*
ሐ26 ወይም *ከ... የተለየ*
መ32 ወይም *ከኬጢ ልጆች*
ሠ9 ወይም *ሠረገለኞች*

49፥24 *ቀስቱ ጸና፤* ጦረኞቹ ኤፍሬማውያን (መሳ 8፥1፤ 12፥1 ይመ)፣ በጦር ሜዳ ዘወትር ድል አድራጊዎች ነበሩ (ኢሱ 17፥18 ይመ):: *በያዕቆብ ኀያል አምላክ፤* እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚታደግና የሚቤዥ አምላክ መሆኑን በአጽንዖት ይገልጻል (ኢሳ 49፥26 ይመ):: *እረኛው፤* የ48፥15 ማብ ይመ:: *በእስራኤል ዐለት፤* እግዚአብሔር የእስራኤል ጽኑ ተከላካይ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን (ዘዳ 32፥4:15:18:30-31)፣ በዳዊት መዝሙራትና በኢሳይያስ የትንቢት መጻሕፍት ውስጥ የተለመደ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው::

49፥25 *ሁሉን ማድረግ በሚችል አምላክ፤* የ17፥1 ማብ ይመ:: *ከላይ ከሰማይ በሚገኝ ረድኤት፤* ከሰማይ በሚወርደው ዝናብና ከምድር በሚፈልቀው የምንጭና የወንዝ ውሃ የምትርሰውን ለም መሬት ያመለክታል:: *ከማሕፀንና ከጡት፤* የሰውንና የእንስሳትን ፍሬያማነት የሚያመለክት አነጋገር ነው:: ከጊዜ በኋላ የኤፍሬም ዘሮች ያገኙትን በረከት በሆሴ 12፥8 ላይ ይመ::

49፥26 *በወንድሞቹ መካከል አለቃ፤* የቍ 8 ማብ ይመ:: ኤፍሬም አለቅነትን፣ በተለይም በስተ ሰሜን ባሉት ነገዶች ላይ ልዕልናን ይቀዳጃል (ኢሱ 16፥9፤ ኢሳ 7፥1-2፤ ሆሴ 13፥1 ይመ)::

49፥27 *ብንያም ነጣቂ ተኵላ ነው፤* ኤሁድ (መሳ 3፥12-30)፣ ሳኦልና ዮናታን (1ሳሙ 11-15) የበዘበዙትን ይመ:: ከብንያም ዘሮች መካከል አንደኛው ወገን ሲበዛ ጨካኝ መሆኑን በመሳ 19-21 ላይ ይመ::

49፥28 *ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች፤* የቍ 2-27 ማብ ይመ::

49፥29 *ከአባቶቼ ዘንድ ቅበሩኝ፤* የ25፥8 ማብ ይመ:: ያዕቆብ የአባቶቹ ምድር ከአምላኩ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው መኖሪያ መሆኑን ምንጊዜም አይዘነጋውም (የ23፥19 ማብ ይመ)::

49፥33 *ወደ ወገኖቹም ተሰበሰበ፤* የ25፥8 ማብ ይመ::

50፥1 *አለቀሰ፤* የ43፥30 ማብ ይመ::

50፥2 *ባለመድኀኒት... እንዳይፈርስ... በመድኃኒት ቀቡት፤* ዮሴፍ በሙያቸው የታወቁ ባለ መድኀኒቶችን ለዚሁ ዐላማ ቀጥሮ ማሠራት ይችል ነበር፤ ሆኖም ራሱን ከአረማውያን ሃይማኖታዊ እምነትና ልምድ ጋር ማነካካት ስላልፈለገ፣ ማድረግ የሚችለውን ነገር አላደረገም::

50፥3 *አርባ ቀን... ሰባ ቀን፤* ምናልባት ሁለቱ ጊዜያት እርስ በርሳቸው ተደራርበው ይሆናል::

50፥5 *አባቴ አስምሎኛል፤* 47፥29-31 ይመ:: *ቈፍሬ፤* ወይም በሆሴ 3፥2 ላይ የገባው የዕብራይስጥ ቃል እንደሚያመለክተው "ገዝቼ" ማለቱ ነው (ዘዳ 2፥6 ይመ):: *ሄጄ፤* ከጌሤም ከፍ ብሎ ወደሚገኘው ወደ ኬብሮን ሄደ::

50፥10 *ዐውድማ፤* በዚያን ዘመን እህል የሚወቃው ዐለት ተጠርቦ ወይም መሬት ተደልድሎ በተዘጋጀ ዐውድማ (ውድማ) ላይ ነበር:: እህል መውቂያ ዐውድማ አብዛኛውን ጊዜ የሚዘጋ

በዚያ ለአባቱ ሰባት ቀን ልቅሶ ተቀመጠ::
[11]በዚያ የሚኖሩ ከነዓናውያን በአጣድ ዐው
ድማ የተደረገውን ልቅሶ ባዩ ጊዜ፣ “ይህ ለግ
ብፃውያን መራራ ልቅሶአቸው ነው” አሉ:: በዮ
ርዳኖስ አጠገብ ያለው የዚያ ቦታ ስም አቤል[1]
ምጽራይም ተብሎ መጠራቱም ከዚሁ የተ
ነሣ ነበር::
[12]የያዕቆብ ልጆችም አባታቸው እንዳዘዛ
ቸው አደረጉ፤ [13]አስከሬኑን ወደ ከነዓን ምድር
ወስደው አብርሃም ከኬጢያዊው ከኤፍሮን
ላይ ከነዕርሻው በገዛው፣ በመምሬ አጠገብ፣
በማክፌላ ዕርሻ በሚገኘው ዋሻ ውስጥ ቀበሩት::
[14]ዮሴፍ አባቱን ከቀበረ በኋላ፣ ከወንድሞ
ቹና ለአባቱ ቀብር አብረውት ሄደው ከነ
በሩት ሁሉ ጋር ወደ ግብፅ ተመለሰ::

### ዮሴፍ ወንድሞቹን እንደማይበቀላቸው አረጋገጠ

[15]የዮሴፍ ወንድሞች ከአባታቸው ሞት በኋላ፣
“ከፈጸምንበት በደል የተነሣ ዮሴፍ ቂም ይዞ
ቢበቀለን ምን እናደርጋለን?” ተባባሉ:: [16]ስለ
ዚህ እንዲህ የሚል መልእክት ወደ ዮሴፍ
ላኩ፤ “አባትህ ከመሞቱ በፊት እንዲህ
የሚል ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር፤ [17]‘ለዮሴፍ፣
“ወንድሞችህ በአንተ ላይ የፈጸሙትን ኀጢ
አትና ክፉ በደል ይቅር በላቸው” ብላችሁ
ንገሩት::’ አሁንም፣ የእኛን የአባትህን አምላክ
(ኤሎሂም) አገልጋዮች ኀጢአት ይቅር በለን::”
መልእክታቸው ሲደርሰው ዮሴፍ አለቀሰ::
[18]ከዚያም ወንድሞቹ መጡና በፊቱ ተደ
ፍተው፣ “እኛ የአንተ ባሮች ነን” አሉት::
[19]ዮሴፍ ግን እንዲህ አላቸው፤ “አትፍሩ፤
እኔን በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ቦታ ማን አስቀ
መጠኝ? [20]እናንተ እኔን ለመጕዳት አስባ
ችሁ አድርጋችሁት ነበር፤ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
ግን ዛሬ እንደሚታየው ብዙ የብዙዎችን ሕይ
ወት ለማዳን ለበጎ ነገር አዋለው:: [21]አሁ
ንም ቢሆን አትፍሩ፤ ለእናንተና ለልጆቻ
ችሁ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አደርግላች
ኋለሁ” በማለት አረጋገጠ፣ በደግ ቃል አና
ገራቸው::

### የዮሴፍ መሞት

[22]ዮሴፍ ከአባቱ ቤተ ሰቦች ጋር በግብፅ
ተቀመጠ፤ አንድ መቶ ዐሥር ዓመትም ኖረ፤
[23]የኤፍሬምንም የልጅ ልጆች እስከ ሦስት
ትውልድ ድረስ አየ:: የምናሴ ልጅ ማኪር
የወለዳቸውም ልጆች በዮሴፍ ጭን ላይ
ተወለዱ::
[24]ከዚህ በኋላ ዮሴፍ ወንድሞቹን፣ “እነሆ፤
የመሞቻዬ ጊዜ ተቃርቦአል፤ እግዚአብሔርም
(ኤሎሂም) በረድኤቱ ይጐበኛችሁና ከዚህ አገር
ያወጣችኋል፤ ለአባቶቻችን ለአብርሃም፣ ለይ
ስሐቅና ለያዕቆብ በመሐላ ተስፋ ወደ ሰጣ
ቸው ምድር ያገባችኋል” አላቸው:: [25]ዮሴ
ፍም የእስራኤልን ልጆች፣ “እግዚአብሔር (ኤሎሂም)
በረድኤቱ ያስባችኋል፤ በዚያን ጊዜ ዐፅሜን
ከዚህ አገር ይዛችሁ እንድትወጡ” ሲል አስ
ማላቸው::
[26]ዮሴፍም በመቶ ዐሥር ዓመቱ ሞተ፤ ሬሳው
እንዳይፈርስ በአገሩ ደንብ በመድኀኒት ከደ
ረቀ በኋላ ሣጥን ውስጥ አስገብተው በግብፅ
ምድር አስቀመጡት::

3፥2፤1ሳሙ31፥13፤2ሳሙ1፥17፤3፥33፤24፥18፤2ዜና35፥25፤1ነገ22፥10፤ኢዮ2፥13፤ሕዝ3፥15፤32፥16፤ሐሥ8፥2፤
50፥11 ዘፍ10፥18፤37፥34
50፥12 ዘፍ49፥29
50፥13 ዘፍ13፥18፤23፥9:20፤25፥9
50፥14 ቍ8
50፥15 ቍ17፤ዘፍ9፥5፤27፥41፤37፥28፤ሶፎ3፥11፤1ጴጥ3፥9
50፥16 ዘፍ49፥29
50፥17 ቍ15፤ዘፍ28፥13፤29፥11፤ማቴ6፥14
50፥18 ዘፍ37፥7፤43፥18
50፥19 ዘፍ30፥2፤ዘዐ32፥34፤ሮሜ12፥19፤ዕብ10፥30
50፥20 ዘፍ37፥20፤45፥5፤አስ4፥14፤ኢሳ4፥14፤10፥7፤ሚክ4፥11-12፤ሮሜ8፥28
50፥21 ዘፍ34፥3፤45፥11፤ኤፌ4፥32
50፥22 ዘፍ25፥7፤ኢያ24፥29
50፥23 ዘፍ41፥51:52፤48፥11:12፤ዘኍ26፥29፤27፥1፤32፥39:40፤36፥1፤ዘዳ3፥15፤ኢያ13፥31፤17፥1፤መሳ5፥14፤ኢዮ42፥16
50፥24 ቍ5፤ዘፍ15፥14፤13፥17፤17፥19፤12፥7፤15፥16፤ሩት1፥6፤መዝ35፥21
106፥4፤ኢሳ38፥14 50፥25 ዘፍ24፥37፤47፥29-30፤49፥29፤ዕብ11፥22 50፥26 ቍ2፤ዘፍ25፥7፤ዘጸ1፥6

[1]11 *አቤል ምጽራይም ማለት የግብፃውያን ሐዘን ማለት ነው*

ጀው ከፍ ባለና ነፋስ በሚኖርበት አካባቢ፣ በተለይም በከተማ ጳርቻና በቅጥር በሮች አቅራቢያ ነበር (1ነገ 22፥10 ይመ):: የሩት 1፥22 ማብ ይመ::

50፥15 *ቂም ይዞ ቢበቀለን፤* ይስሐቅ ከሞተ በኋላ ዔሳው ያዕቆብን ለመግደል በአንድ ወቅት አሚሮ ነበር (27፥41 ይመ)::

50፥17 *ዮሴፍ አለቀሰ፤* የ43፥30 ማብ ይመ:: ዮሴፍ ያለ ቀሰው ወንድሞቹ አባታቸው ያልተናገረውን ነገር እንደ ተናገረ አድርገው በሐሰት በግቅረባቸው አዝኖ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ ከዚህ በፊት የፈጸሙብትን በደል ገና ድሮ ከልቡ ይቅር እንዳላቸው ስላላረጋገጠላቸው ሊሆን ይችላል::

50፥18 *ተደፍተው፤* ዮሴፍ ከዚህ በፊት ያያቸው ሕልሞች ሁሉ የመጨረሻ ፍጻሜያቸውን በዚህ ቦታ አገኙ (የ37፥7 ማብ እንዲሁም 37፥9 ይመ):: *“እኛ የአንተ ባሮች ነን”፤* ከዚህ በፊት የእርሱ ባሮች ለመሆን ፈቃደኝነታቸውን ያሳዩ ቢሆንም፣ ሁኔ ታው ግን ከዚህ የተለየ ነበር (44፥9:33 ይመ)::

50፥19 *እኔን በእግዚአብሔር ቦታ ማን አስቀመጠኝ?* የ30፥2 ማብ ይመ::

50፥20 *እግዚአብሔር... ለበጎ ነገር አዋለው፤* በጥላቻ ተነ ሣሥተው ወንድማቸውን ለማጥፋት የፈጸሙትን በደል እግዚአ ብሔር ሕይወትን ለማዳን ይኸውም የእስራኤላውያንን፣ የግብፃ ውያንንና በራቡ ምክንያት እህል ለመሸመት ወደ ግብፅ የወረዱ ትን ሕዝቦች ሁሉ ሕይወት ለማዳን ተጠቀመበት:: ከዚህም በተ ጨማሪ እግዚአብሔር ለሕዝቦች ሁሉ ያለው ዐላማ ሕይወት መሆኑንና ይህም ዐላማው በአብርሃም ዘሮች በኩል እውን እንደ ሚሆን በዚሁ ጊዜ አሳይቶአል::

50፥23 *እስከ ሦስት ትውልድ ድረስ አየ፤* ከኢዮብ ታሪክ ጋር ያነጻጽሩ (ኢዮ 42፥16):: *ማኪር፤* የምናሴ የመጀመሪያ ልጅ ሲሆን፣ የነያላኑ የገለዓዳውያን ቅድመ አያት ነው (ኢያ 17፥1):: ከጊዜ በኋላ የማኪር ስም ከምናሴ ስም ጋር እየተቀያየረ ያገለግል ነበር (መሳ 5፥14 ይመ):: *በዮሴፍ ጭን ላይ ተወለዱ፤* ዮሴፍ ምናልባት የማኪርን ልጆች ወስዶ እንደ ራሱ ልጆች አድርጎ ሳያ ሳድጋቸው አልቀረም (የ30፥3 ማብ ይመ)::

50፥24 *ወንድሞቹን፤* በዚህ ቦታ ይህ ቃል ከሥጋ ወንድ ሞቹ በተጨማሪ ሌሎችንም የሚያመለክት አጠቃቀም ሳይኖረው አይቀርም:: *የመሞቻዬ ጊዜ ተቃርቦአል፤* የ48፥21 ማብ ይመ:: *እግዚአብሔርም... ከዚህ አገር ያወጣችኋል፤* ዮሴፍ፣ እግዚአ ብሔር “ከግብፅ አወጣችኋለሁ” በማለት የገባውን ቃል ከቶ አል ረሳም (ከ15፥16፤ 46፥4፤ 48፥21 ጋር ያነጻጽሩ)::

*50፥25፤ ያዕቆብ ያቀረበውን ተመሳሳይ ጥያቄ* በ47፥29-31 ላይ ይመ:: *ዐፅሜን ከዚህ አገር ይዛችሁ እንድትወጡ፤* ከብዙ ዓመታት በኋላ ሙሴ የቅድመ አያቱን ቃል ለመፈጸም የዮሴ ፍን ዐፅም ይዞ ከግብፅ ወጣ (ዘፀ 13፥19 ይመ):: የዮሴፍ ዐፅም “ያዕቆብ... ከሐሞር ልጆች በገዛው ዕርሻ በሴኬም” ተቀበረ (ኢያ 24፥32፤ ዘፍ 33፥19 ይመ)::

50፥26 *ዮሴፍም በመቶ ዐሥር ዓመቱ ሞተ፤* ቍ 22 ይመ:: የጥንት ግብፃውያን መዛግብት እንደሚያመለክቱት፣ 110 ዓመት አንድ ሰው ሊኖረው የሚገባ የዕድሜ ዘመን ሲሆን፣ ይህ ለጥንት ግብፃውያን የሚያሳየው ዮሴፍ የተባረከ ሰው መሆ ኑን ነው::